የመጠሪያ ስሞች

ዘዝገብ

የመጠሪያ ፣ የክርስትና እና የማዕርግ ስሞችን
ያካተተ በታሪክ ላይ የተመሠረተ ።

ዋና ጠቀሜታው ወላጆች ለሕፃናት ልጆቻቸው
ስም ለመሰየም ምርጫ እንዲያገኙ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

መልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት

ጥቅምት ፳፱ ቀን ፪ሺ፱ ዓ. ም.
October 2008
ከ 600ሺ በላይ ስሞችን የያዘ።
የመጀመሪያ አትም

ለ _____

ከ _____

ቀን _____


የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

© 2008 By Melak Berhan BERHANU BISRAT
All Rights Reserved

የመጀመሪያ እትም

ኤች. ዋይ ኢንተርናሽናል የኅትመት ሥራ ድርጅት
H.Y. International Printers Enterprise Pvt.Ltd.Co
P.O Box 50676
Addis Ababa

ስለጽሑፉ አስተያየት ቢኖርዎ
በዚህ አድራሻ መገናኘት ይቻላል።
P.O.Box 24842 Code 1000
Addis Ababa



ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በመላው አውሮፓ ሊቀ ጳጳስ
የርእሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም
የበላይ ጠባቂ ለነበሩት
እና
በስማቸው ለተሰየመው
"አቡነ ዮሐንስ የልጆች ትምህርት ቤት"
መታሰቢያ ይኹንልኝ።



ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በመላው አውሮፓ ሊቀ ጳጳስ
የርእሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም
የበላይ ጠባቂ ለነበሩት
እና
በስማቸው ለተሰየመው
"አቡነ ዮሐንስ የልጆች ትምህርት ቤት"
መታሰቢያ ይኹንልኝ።

ምስጋና

መልካም ሴት ለባሏ ዘውድ ናት (ምሳ. 12:4)
እንደተባለው በሥራዬ ረዳት ሽና ላበረታታችኝ ባለቤቴ መቅደሰወርቅ ዓለሙ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

የዚህን ጽሑፍ ረቂቅ በማንበብ ሐሳባቸውን ላካፈሉኝ ኢንጂነር ከበደ ጎበና፣ ዶክተር ማንደፍሮ በላይነህ፣ ልጅ ወሌ ነጋ እና የመጽሐፉን ሽፋን ንድፍ ላዘጋጁልኝ ለአርክቴክት አበባው መስፍን ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

ይህ መጽሐፍ ለኅትመት በቅቶ አንባብያን እጅ እንዲደርስ የተባበሩኝ አቶ ታምራት ከበደ እንዲሁም የተራዱኝን እማሆይ ትርሚት አንለን በእግዚአብሔር ስም ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

የድካም ዋጋ ውጡቱ እንዲታይ በማተሚያ ድርጅታቸው ለኅትመት እንዲበቃ ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረጉልኝን፣ ኤች ዋይ ኢንተረናሽናል የኅትመት ሥራ ድርጅት ኃላፊ አቶ ሀብቴ ፈርሻ እና ምክትል ሥራ አስኪያጅ ወ/ሮ ይሳለሙሽ ተክሌ በተጨማሪም የመሥሪያ ቤቱን ሠራተኞ ስለትብብራቸው በእግዚአብሔር ስም ከልብ አመሰግናለሁ።

ማውጫ

መቅድም ..... ገጽ

ምዕራፍ ፩

መጠሪያ ስሞች (ስመ ተጸውዖ) 10
(ሀ) ወላጆች የሚሰይሙት ስም 10
(ለ) ስምን መልአክ ያወጣዋል። 13
(፩) ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቀ መለኮት 13
(፪) አቴጌ መሶበወርቅ 14
(፫) ቅዱስ ላሊበላ 15
(፬) ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ 16
(ሐ) የባሕርይ ስም (ስመ ባሕርይ) 16
(መ) የመጠሪያ ስም በቅኔ ምርምር 17
(ሠ) የፍቅርና የቍልምጫ ስሞች 20
(ረ) ለቤተሰብ የሚሰጥ ያክብሮት ስም 22
(ሰ) በጥንታዊው ትምህርት ቤት የሚሰየም ስም 23
(ሸ) የተዋሐዱ የመጠሪያ ስሞች 24
(፩) የወንድ የመጠሪያ ስም 26
(፪) የሴት የመጠሪያ ስም 122

ምዕራፍ ፪

የክርስትና ስሞች (ስመ ጥምቀት) 196

(ሀ) የሚያከራክሩ የክርስትና ስሞች 197

(ለ) የክርስትና አባትና እናት 199

(ሐ) የወንዶች የክርስትና ስሞች 201

(መ) የሴቶች የክርስትና ስሞች 220

ምዕራፍ ፫

የማዕረግ ስሞች (ስመ ተቀብዖ) 232

(ሀ) ጳጳሳት ቅብዐ ክህነት ሲቀቡ የሚሰየሙት ስሞች..... 232

(ለ) የሥልጣነ ክህነትና ያስተዳደር የማዕርግ ስሞች 234

(፩) በደብር አለቆች የማዕርግ ስም 234

(፪) በደብር አገልግሎት የማዕርግ ስሞች 234

(፫) የአብነት ትቤት መምህራን የማዕርግ ስሞች... 235

(፬) የሊቅነት፣ የመዘምርነት የማዕርግ ስሞች 235

(፭) የመነኰሳት፣ የገዳማውያን የማዕርግ ስሞች .. 236

(ሐ) ነገሥታት ቅብዐ መንግሥት ሲቀቡ የሚሰየሙ ስሞች... 236

(፩) አባ የሚለው የማዕርግና የመጠሪያ ስም..... 239

(፪) ንገሥታት ማዕረግ ሲሰጡ የሚሰየም ስም..... 241

(፫) ማንኛውም ሰው የሚጠራበት የክብር ስም 242

(መ) ፊደል 243

መቅድም

ይህንን የመጠሪያና የክርስትና ስም የሚል ጽሑፍ ለማዘጋጀት ያነሳሳኝ ብዙዎች ወላጆች ለሚወልዱት ልጅ ፅንስ ከተፀነሰ ጀምሮ ስም ለመስየም ሲጨነቁ፤ ስም ፍለጋ ጥያቄ በመጠየቅ እንዲሁም ድኅረ ገጽ (ኢንተርኔት) ውስጥ ገብተው ሲባክኑ በማየቴ ነው።

ለንደን የምትኖረው ወይዘሮ ማርታ ሙሉጌታ ባንድ ወቅት ደብዳቤ በመጻፍ እንዲህ ስትል አሳሰባኝ ነበር።

ለተከበሩ መልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት

ለንደን

በቅድሚያ በእግዚአብሔር ስም ሰላምታዬን እያቀረብኩ አንድ ጉዳዬን በተመለከተ ላስቸግሮት።

በአሜሪካ አገር በሜሪላንድ ግዛት የምትኖር እኅቴ በቅርቡ ትወልዳለች። ስለምትወልዳትም ሴት ልጅ የመጠሪያና የክርስትና ስም የሚኾን ፈልጊ ብላ አስጨንቃ ይዛኛለች። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመምረጥ ደጋግሚ ባገላብጥም ላገኝ አልቻልኩኝም። አምላክን የሚያመሰግን ቃል ካለ ብዬም ብፈልግ አልተሳካልኝም፤ እባክዎን የሚያውቁት ለሴት ልጅ የሚኾን ስም ካለ ቢነግሩኝ የተለመዱትና ባኹኑ ጊዜ ብዙዎች እየተጠሩበት ያሉትን አይኾንም ብላለች። እናታችን "ስምን መልአክ ያወጣዋል" የሚባለው በዘልማድ አይደለምና ስም በታወጡ ጥሩ ሥነምግባር ያለውን ቅዱስ ፈልጋችሁ አውጡ ምክንያቱም የሚወለደው ልጅ ቅዱሱን የመምሰል ልቦና እንዲኖረው ትለን ነበር።

ስለዚህ በግዕዝ ቋንቋ የጸሎቴ ፣ የልመናዬ ምላሽ ወይንም አምላክ ስለቸርነቱ፤ ስለ ስጦታው፣ ስለ መሐሪነቱ፣ የሚያመሰግን ቃል ለስም የሚኾን ካለ አለቪያ ኢትዮጵያዊትነትን የሚያንጸባርቅ ወይም ሌላ በታሪክ የታወቁት ቅድስት ካለች አባክዎትን ላስቸግርዎ።

የርስዎ አክባሪ ማርታ ሙሉጌታ።

ይህ የወይዘሮ ማርታ ሙሉጌታ ደብዳቤ ለዚህ ጽሑፍ አንዱ መነሻ ኾኖኝ በዲስ ለሚወለዱ ሕፃናት ስም ፍለጋ ጀመርኩ ። ብዙ ወላጆች ለልጆቻቸው ምርጥ የኾነ የመጠሪያ ስም ለማውጣት ፤ እንዲሁም ምርጥ የኾነ የክርስትና ስም ለማውጣት እና እንዲወጣላቸው በማሰብ ሲጨነቁ አይቻለሁ፤ ስም ለመ ምረጥ ደግሞ አንድ ነገርን የሚያንጸባርቅና ምክንያቱንም ፣ ጊዜውንም የሚገ ልጽ መኾን እንዳለበት የታወቀ ነው።

በዓለም ላይ ያለ ጎብረተሰብ ዅሉ በጎባው፣ በቋንቋው፣ በባህሉ ስም ይሰይማል ። በኢትዮጵያ ጎብረተሰብ ቋንቋ ብዙ የተለያየ የነገድ ስም አለ ፤ ዅሉም ልጅ ሲወልድ ትርጕም የሚሰጠውንና የሚሰይምበት ለምን እንደዅነ የሚያመለክት ምክንያት አለው ። አንዳንዱ የሚመርጠው ከሙያው፣ ከኑሮው ጋር የተያያዘ ሊዅን ይችላል። የወታደር ልጅ ከጀግንነት ጋር የተያያዘ፤ የገበሬ ልጅ ከግብርና ጋር የተያያዘ፤ የካህን ልጅ ከክህነት ጋር የተያያዘ (ቤተ ክህነት)፤ ከተሜው ከከተሜው ጋር የተያያዘ የመጠሪያ ስም መሰየም የተለመደ ነው ። አንዳንዴ አባትና እናት የልጃቸውን ጠረን ተከትለው ሽታዬ፣ ሽቶ፣ መዐዛዬ ፣ የሚለውንም ምርጫ መርጠው ይሰይማሉ። አንዳንዴም ደግሞ ከፈጣሪ ጋራ ያላ ቸውን ፍቅር ለመግለጽ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን የቅዱሳን ስሞችና በስመ ክርስትና (ጥምቀት) ስሞች መጥራት ይመርጣሉ።

የኢትዮጵያውያን የመጠሪያ ስሞች ከዕብራይስጥ፤ ከግእዝ፣ ከግሪክ ፣ ከዐማርኛ ፣ ከኦሮምኛ ፣ ከትግሪኛ ፣ ከጉራግኛ ፣ ከዶርዝኛ ፣ ከዐረብኛ... ከሌ ሎችም ነገዶች የተዋሐደ ፣ የተወራረሰ ነው ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ከአባት ጋር ሲገጥሙ ቅኔ ለበሰ የሴትና የወንድ ስሞች በምሳሌነት ተጠቅሰው ይገኛሉ ። የኢትዮጵያውያን ስሞች በአብዛኛው በተውላጠ ስም ላይ የተመሠረቱ ናቸው ።

ለምሳሌ፦ <u>ብርሃን</u>፣ <u>አምባ</u> እና <u>ገበያ</u> በሚለው ዘር <u>ተውላጠ ስም</u> ሲተካ ይህንን ይመስላል።

<u>ተውላጠ ስም</u>			
እኔ ፤	ብርሃኔ	አምባዬ	ገበያዬ
አቡ ፤	ብርሃኑ	አምባው	ገበያው
አሲ ፤	ብርሃኗ	አምባዋ	ገበያዋ
አንተ	ብርሃንህ /ብርሃን/	አምባህ /አምባ/	ገበያህ /ገበያ/
አንቺ	ብርሃንሽ /ብርሃን/	አምባሽ /አምባ/	ገበያሽ /ገበያ/
አነርሱ፤	ብርሃናቸው	አምባቸው	ገበያቸው

ለሴትም ለወንድም የወል መጠሪያ የዅኑ ስሞችም አሉ ።
<u>ለምሳሌ</u>፦ አንተ እና አንቺ በሚለው ተውላጠ ስም ብርሃን፣ አምባ እና ገበያ ለወንድም ለሴትም ጸታ ይዅናል ማለት ነው ። በተጨማሪ መሠረት፣ መዓዛ፣ ቀለመወርቅ፣ ኒሻን፣ ተቋም... ሌላም ብዙ የወል መጠሪያ ስሞች አሉ።

የመጠሪያ ስም የሚዅኑ ስመ ክርስትና፣ ስመ ሀገር፣ ስመ ግብር፣ ስመ ባሕርይ ፣ ስመ ተቀብዖ ፣ ስመ ደብር ፣ ስመ አዕዋፍ ሌሎችም በመጠሪያነት ተለውጠው ሰዎች ይጠሩበታ።

ለምሳሌ አንበሳው፣ አውራሪስ፣ ስመ ባሕርይን ፤ የኃያልነት ባሕርይን ያመለክታል። ሊባኖስ ፣ ደብሪ ፤ ስመ ደብር ሲዅን ታላቅነትን ያመለክታል። ዮርዳኖስ ፣ ወባይ ስመ አፍላግ ሲዅን ታላቅነትን ኀያልነትን ያመለክታል። እስ ራኤል ፣ ኢትዮጵያ ስመ ሀገር ፤ አሞራው፣ ርግብ ስመ አዕዋፍ ናቸው ።

ቅጽል ተጨምሮበትም የሚሰየሙ ስሞች አሉ ። ጥሩ-ወርቅ ፣ አምደ ወርቅ ፣ አሰፋ-ወሰን፣ ዓለም-ሰገድ... ሌሎችም ።

ሌላው በኢትዮጵውያን አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ሥርዐት ጥምቀተ ሲፈጸም ከእግዚአብሔር ልጅነት ማግኘቱን የሚገልጽ መጠ ሪያ ስም ወይም የክርስትና ስም ይሰጣል። ይህም ስያሜ ጥምቀት ሲጠመቁ በዋ ለው ቅዱስ ስም ላይ ተጨማሪ ቅጽል በማስገባት ነው (ሉቃ.10፥20፤ ዘፀ. 32፥32)።

ለምሳሌ አበበ በክርስትና ስሙ ጎይስ ሚካኤል ሊባል ይችላል። በምዕ ራባውያን ዘንድ ግን የክርስትና ስም በቀጥታ የዓለም ስም እና ከቤተሰብ የወ ረደ የመጠሪያ ስም ይዅናል ፤ ያለ ቅጽል በነጠላው ማይክል (ሚካኤል) ፤ ጆርጅ (ጊዮርጊስ)፣ ጆን (ዮሐንስ) ብሎ መጥራት የተለመደ ባህል ነው።

በርግጥ በኢትዮጵያውያን ዘንድ አልፎ አልፎ የክርስትና ስም ያለቅጽል የተሰየመም አለ ። በነጠላው ያለ ቅጽል የሚጠሩ ጸዳሳት፣ ማዕርግ ጵጵስና ሲሰ ጣቸው ብቻ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ያሉ የቅዱሳን መጠ ሪያ ስም፤ የክርስትና መጠሪያ ስም፤ የቤተ ክህነት የመጠሪያ ስም፣ የቤተ መን ግሥት የመጠሪያ ስም ፤ የኢትዮጵያውያን የነገድ ስም ተዘጋጅተዋል። ባጠቃላ ለሚወለዱ ሕፃናት ስም ለመሰየም ይረዳል በማለት ፤

- ወላጆች ለልጃቸው ስም ለመሰየም ምርጫ እንዲኖራቸው፤
- በሆስፒታል ለሚወልዱ በቶሎ ስም ለመሰየም ለሚቸገሩ ፤
- ከአገር ወጥተው በውጭ አገር ኑሯቸውን አድርገው ከሌላው ጎብ ረተሰብ ጋር ተቀላቅለው ኢትዮጵያዊ ባህል ለተዘነጋቸው ፤
- ለሚወልዱት ልጅ ስም ለማውጣት ለሚቸገሩ፤

እንዲረዳና ጥቅም እንደሚሰጥ በማሰብ ተዘጋጅቷል ። ዅኖም ግን በዚህ መጽ ሐፍ ውስጥ ያልተካተቱ የኢትዮጵያውያን ስሞችን ለዅለተኛው አትም በጥናት እናቀርባለን የሚል ምኞት አለን።

አዘጋጁ

ምዕራፍ ፭

የመጠሪያ ስሞች (ስመ ተጸውዖ)

(ሀ) ወላጆች የሚሰይሙት ስም

የሰው ልጅ በመጀመሪያ አግዚአብሔር ሲፈጥረው የወል ስም ሰጥቶት ነበር። ይህም የወል ስም "ሰው" የሚል ነው። ሌላ ደግሞ በጾታው የወል ስም ወንድ እና ሴት አለ። ከዚያም የፈጠረውን ወንዱን አዳም ብሎ ጠራ። ሴቷን ደግሞ ሔዋን ብሎ እንደጠራ በቅዱስ መጽሐፍ ተገልጿል ። አዳምና ሔዋንም ከነሱ አብራክ የተፈጠሩትን ልጆች ቃየል ፣ አቤል ፣ ከዚያም ሔዋን በአቤል ፈንታ እግዚአብሔር ሌላ ዘር ተክቶልኛል ስትል የአቤልን ተከታይ ሴት በማለት የመጠሪያ ስም በመስጠት መሰየም ጀመሩ (ዘፍ. 4፥25)።

ወላጆች ልጃቸውን የሚጠሩበትን ስም መሰየም ከአዳና ከሔዋን ጊዜ ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው።

ማንኛውም ሰው በአገሩ ባህል፣ በቋንቋው ፤ በሃይማኖቱ ረገድ ለልጁ መጠሪያ ስም ይሰይማል። እንዲሁም ደግሞ ዅሉም በሙያው የወታደር ልጅ የጀግንነትን የሚያንጸባርቅ ፤ የካህን ልጅ አምነትን የሚያንጸባርቅ፣ የገበሬ ልጅ ግብርናን የሚያንጸባርቅ ሌሎችም በዚሁ መልክ ለልጆቻቸው ይሰይማሉ።

አንዳንድ ጊዜ ወቅቱን፣ የኑሮውን ገጠመኝ ተከትሎ ወይም የወደፊት የልጁን ዕጣ ፋንታ ነጋሪ ኾኖ የሚሰየም ስም አለ። በረኃብና በጥጋብ ዘመን፤ በመከራና በደስታ ዘመን፤ በጦርነትና በሰላም ዘመን ወላጅ ስም ይሰይማል።

ለምሳሌ አጋሪደች ወይም ጋረደው በማለት ወቅቱን አስታኮ ሰያሜ ይሰጣል፤ ከመክራ ሰወረ(ች) ሊኾን ይችላል ። አናቱን ከሞት ያዳነ ሕጻን ከኾነ ደግሞ አዳነ ፤ ሴት ከኾነች አዳነች በማለት መጥራት የተለመደ ነው ። አንዳንዴም የተወለደው ልጅ ታሞ ሊሞት ነው አይተርፍም ከተባለ በኋላ ከሞት ተርፏል ለማለት ተረፈ ይሉታል። ሀብት የተገኘ እንደኾነ፤ ሀብታሙ፣ አዶኛ፣ ንዋይ፤ ክብረት አየተባለ ይጠራል።

የፍቅር አሰከ መቃብር መጽሐፍ ደራሲ ዐዲስ ዓለማየሁ የመጽሐፉን ከፍተኛውን ገጸ ባሕርይ የሚጫወተውን በዛብህ የተባለውን ሲገልጹ ከተወለደ

ጀምሮ አምስት ዓመት አስኪሞላው ድረስ ጤና ስላልነበረው ፤ በሽታው ስለ በዛበት ይህ ስም መጠሪያው እንዲኾን የተመረጠለት ነው ይላሉ ።

ጠብ በቤት፣ በዘመድ አዝማድ እና በጎረቤት ገብቶ ሲኖር ልጅ በመወለዱ ሰላም ከመጣ ሰላም (ሰላሙ) በማለት ይሰየማል ወይም ደግሞ አማን ብሎ መጥራት የተለመደ ነው ። ይህንም ሲባል ደግሞ ሰላም ተብለው የሚጠሩ ዅሉ ወላጆቻቸው የተጣሉ ነበሩ ተብሎ ትርጓሜ ሰጥቶ እንዲታሰብ ማለት አይደለም ።

ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ ከወቅቱ ጋር የሚስማማ ብዙ ስም ተሰይሟል ። ለምሳሌ ሳይታሰብ ጠላት ልጁ ሲወለድ በእኩል የደረሱባቸው ቤተሰቦች ልጃቸውን ዝቅ-አለ ብለው ሰይመውታል። በጦር ሜዳ ውጊያ ጀግናዋ ዐርበኛ ከበደች ስዩም የወለደችውን ልጇን ታሪኩ አበራ ብላዋለች። በጣሊያን ወረራ ዘመን ይሰየሙ የነበሩ ስሞች አዳንዶቹ ከጀግንነት ጋር ፤ ከበቀል ጋር የተያያዙ ነበሩ ። ለምሳሌ ይለይለት ፤ ግፋው ፤ ጠቅጥቃቸው ፤ ታጠቅ ፤ ታፈረ ድንበሩ ፤ ደምሳቸው ፤ ሽጉጤ ... የመሳሰሉ ነበሩ ።

የዐፄ ኀይለ ሥላሴ መንግሥት ተቀይሮ የደርግ መንግሥት ዐታውን በያዘበት ዘመን የተወለዱ ልጆች አብዮት ፤ አንድነት ፤ ወዛደር እየተባሉ ተሰይመዋል። በተቃራኒው ደግሞ አቶ ይንገሡ የተባሉትም የጎጃም ሰው ልጃቸውን አስከጊዜው ብለው ሰይመውታል።

<u>በእስራኤላውያን</u> ዘንድ ስም ሲሰየም ጠባይን፣ ግብርን (ሥራን) ወይም የቤተሰብ ዅኔታን የሚገልጥ ኾኖ ይሰየም ነበር።

ያዕቆብም ሲወለድ ዞሮ የወንድሙን ተረከዝ ይዞ ሲወጣ አዋላጂቷ የቀደመውን የያዕቆብ አውራ ጣት አሰረች በዚህ ጊዜ አሰናካይ ተብሎ ተሰየመ። በዚህ አይነት የተሰየሙ ብዙ ስሞች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ።
(ዘፍ. 25፥26 ፤ ዘፍ. 38፥27)

በአንድ ቀን ውስጥ የተለወጠው ስም የብንያም ነው ፤ እናቱ ራሔል ምጥ ይዟት በተጨነቀች ጊዜ አዋላጂቱ አትፍሪ ወንድ ልጅ ነው አለቻት ፤ እርሷም ጭንቁ በዝቶባት ነበርና ቤንኦኒ አለችው። ይህም ማለት የሐዘኔ ወይ የጭንቀቴ ልጅ ማለት ነው። ወዲያው አንደተገላገለች ዐረፈች፤ አባቱ ያዕቆብ ግን ብንያም (ዕብ) አለው። ትርጕሙም የቀኝ እጅ (የማን) ወይም የደቡብ ልጅ ዕድለኛ ማለት ነው (ዘፍ. 35፥18 ፤ 24) ። የያዕቆብና የራሔል ልጅ ታሪክ ደስ የሚያሰኝ እንዲሁም ከቤተሰቡ የመጨረሻ በአባቱና በወንድሞቹ ተወዳጅ ስለ ነበረ ይመስላል ብዙ ኢትዮጵያውያን ብኒያም በማለት ለልጃቸው ስም ይሰይማሉ ።

ይሥሐቅ የሚለው ስም ኾኔታዎችን ተከትሎ የተሰየመ ስም ነው ። ይህ ስም የወጣው ሣራ በተጎበኘችበት ጊዜ ስለሣቀች ነው ።
(ዘፍ.17፥17 ፤ 18፥12 ፤ 21፥3)

ሙሴም የፈርኦን ሴት ልጅ ልዕልቲቷ ከባሕር ስላገኘችው "ከባሕር የተገኘ" ስትል ሙሴ ብላ ሰየመችው (ዘጸ. 2፥10)።

ሳሙኤልም በእናቱ ጸሎትና ስእለት የተወለደ ስለነበር ፤ ጸሎቷ ስለተ ሰማ "እግዚአብሔር ሰማኝ ስትል" ሳሙኤል አለችው ።(1ኛሳሙ. 1፥20) (በዕብ ራይስጥ ኤል ማለት እግዚአብሔር ማለት ነው)

ታቦተ ጽዮን በፍልስጥኤማውያን ስትማረክ የእግዚአብሔር ክብር ከእ ስራኤል ተገፈፈ ወይም ክብር ራቀ ስትል የፊንሐስ ሚስት የወለደችውን ልጅ ኢካቦድ (ክብር ራቀ) ብላ ሰየመችው (1ኛ ሳሙ. 4፥21)። የያዘው ትርጉም ደስ ስለማያሰኝ በዚህ ስም ሰዎች ሲጠሩበት ተሰምቶ አይታወቅም ።

በቅዱስ መጽሐፍ በበጎነታቸው እና በጥሩ ትርጉም የሚታወቁ ስሞች ተለውጠው ነውርና መጥፎ ምግባራት የነበራቸው ሰዎች ብዙዎች ነበሩ ። በመ ጥፎ ተግባራት የታወቁት ሰዎች ፤ በእስከፊ ሥራቸው የተነሣ ትውልድም ሳይ ጠራባቸው ይኖራል።

<u>ስምሳሌ፡-</u> **ቃየል** መሥዋዕቱን በንጽሕና ስላላቀረበ በእግዚአብሔር ዘንድ አልተወደደም፤ ይህም አልበቃ ብሎት ወንድሙን **አቤልን** ስለገደለ የተረ ገመ ኾነ። ስለዚህ ቃየል ብሎ የሚሰይምና የሚጠራ የለም ። እንዲሁም ሴት ስር ብሎ የሚሰይም የለም። ከሴቶችም **ሚልኮል** ፣ ደሊላ ብሎ የሚጠራ የለም
(ዘፍ. 4፥8 ፤ 2ኛ ሳሙ.6፥16-23 ፤ መሳ. 16፥4–22)።

ከዳዊት ልጆች በኩር የኾነው አምኖን አኅቱ ትዕግርን አስገድዶ ስላ ስነወራት የናት ልጅ ወንድሟ አቤሴሎም በዚህ አሳፋሪ ድርጊቱ በንዴትና በበ ቀል አስገድሎት ሸሸ። ይህም ቤተሰቡን አበጣበጠ። በዚህ ክፉ ሥራው የተነሳ በአምኖን ስም አምኖን ብሎ የሚሰይም የለም (2ኛሳሙ. 13፥1 ፤ 3፥2–5)።

እዚህ ላይ ሊታሰብበት የሚገባ ልጆች መጥፎ ምግባር ይዘው እንዳ ያድጉ ወላጆች ኀላፊነት አለባቸው ። በተለይም እናት ልጇን ለማስተማር የቅ ርብ ሰው ነች። ይህም ጢሞቴዎስ በናቱ በኤውንቄ በአያቱ በሎይድ የተሰጠው ትምህርት፤ የወረሰው መልካም ሥነምግባር ለኋላ ጊዜ ለኦሮውና ለመንፈሳዊ ሥራው ጠቅሞታል፤ ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ መስክሮለታል ። ለልጆች ጥሩ ስም ብቻ ለመሰየም መፈለግ ሳይኾን አስተዳደጋቸውንም መከታተልና መንከባ ከብ ያስፈልጋል (2ኛ ጢሞ 1፥5፤ የሐ. ሥራ 16፥1)።

በሕይወት አጋጣሚ የደረሰውን፤ ጠባይን ወይም ድርጊትን፣ ማኅበራዊ ኦሮን፣ ቦታን የሚያንጸባርቁ ስሞች ይሰየማሉ ። ኹሉም ደስ የሚሰውንና ትር ጕም የሚሰጠውን ስም ይሰይማል። ሌሎችም ሃይማኖቶች ለነሱ እንደሚስማማ ቸው በራሳቸው መንገድ ይሰይማሉ።

(ለ) "ስምን መልአክ ያወጣዋል"

ስምን መልአክ የሚያወጣው መኾኑን እግዚአብሔር ብቻ የሚያውቀው ለሰው ልጆች የተሰጠ ፍጹም ምስጢር ነው። ወንድ ወንድ ኾኖ እንዲፈጠር ፤ ሴት ሴት ልጅ ኾና እንድትፈጠር የኾነበት ምስጢር የእግዚአብሔር ምስጢር ነው። እንዲሁም ስም የመለኮታዊ ባሕርይ ምስጢር ነው።

ለመውለድም ኾነ ለመወለድ ምስጢር እንደኾነ ኹሉ ፤ ከአባት አብ ራክ ከእናት ማሕፀን ሳይደርስ ስለግብሩ ትንቢት መናገር መለኮታዊ የኾነ ከሰው ኅሊና በላይ ነው ። ይህ ስጦታ ግን የእግዚአብሔር እንደራሴዎች ለኾ ኑት ቅዱሳን መላእክት ይቻላቸዋል ። ይኽን ምስጢር ማንም በምርምር ሊረ ዳው የማይቻል ነው ። ኾኖም ግን ቅዱሳት መጽሐፍት በሚያበረዱን መንገድ ስምን መልአክ እንዲሚያወጣው እናያለን (ሉቃ. 1፥11 ፤ ማቴ. 1፥21)።

(ፀ) ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቀ መለኮት

በቅዱስ ወንጌል ካህኑ **ዘካርያስ** በሰሞን ተራው በቤተ መቅደስ ኾኖ ዕጣን ሲያጥን ሕዝቡም ሲጸልዩ የጌታ መልአክ ተገለጸለት ።

መልአኩም ጸሎትህ ተሰምቷልና አትፍራ ሚስትህ **ኤልሳቤጥ** ወንድ ልጅ ትወልዳለች ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ደስታና ተድላ ይኾንልሃል ። በመ ወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል። በጌታ ፊት ታላቅ ይኾናል ፤ የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም ፤ ገና በናቱ ማሕፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላ በታል አለው።... (ሉቃ. 1፥11) ዘካርያስም ለመልአኩ የሰጠው መልስ – እኔ ሽማ ግሌ ነኝ ምስቴም በዕድሜዋ አርጅታለች ይህን በምን ዐውቃለሁ ? **መልአኩም** መልሶ እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ እንድናገርህም ይህ ችን የምሥራች እንድሰብክልህ ተልኬ ነበር እነሆም በጊዜው የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንክ ይህ ነገር እስከሚኾን ድረስ ድዳ ትኾናለህ መናገር አትች ልም አለው።

የኤልሳቤጥ የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ ወንድ ልጅም ወለደች ጎረቤቶቿም ዘመዶቿም ጌታ ምሕረቱን እንዳገነነላት ሰምተው ከርሷ ጋር ደስ አላቸው ። በስምንተኛው ቀን ሕፃኑን ሊገርዙት መጡ በአባቱም ስም ዘካርያስ ሊሉት

ወደዱ፤ እናቱ ግን መልሳ አይኾንም ዮሐንስ ይባል አለች። እነሱም ከወገንሽ ማንም በዚህ ስም የተጠራ የለም አሏት ፤ አባቱንም ማን ሊባል እንደሚወድ ጠቀሱት፤ ብራናም ለምኖ ስሙ ዮሐንስ ነው ብሎ ጻፈ ። ኹሉም አደነቁ። (ሉቃ.1፥57 - 64)።

(፪) አቴጌ መሶበወርቅ

ዐፄ ድልነአድ (902 -913 ዓ. ም.) በቤተመንግሥታቸው መራ ተክለሃይማኖት የሚባል የላስታ እና የአገው ሰው አጋፋሪ ነበራቸው ። **ዐፄ ድልነአድ** ሴት ልጅ ከወለዱ ለመንግሥታቸው መጥፋት ምክንያት እንደምትኾን ትንቢት ይነገር ስለነበር ሴት ልጅ በመውለዳቸው በመንግሥታቸው ሥጋት እደረባቸው። ትንቢቱ እንዳይፈጸምባቸው ስለፈሩ ሳትታወቅ ቶሎ ሊያጠፏት አሰቡ። ለዚህም ሰው እንዳይሰማባቸው ሕፃኗን **በመሶበወርቅ** አድርገው ለታማኙ አጋፋሪያቸው መራ ተክለሃይማኖት መሶበወርቁን ሳይከፍት ወደ ወንዝ አንዲጥል ሰጡት

መራ ተክለሃይማኖት ወንዝ ሳይደርስ ድምፅ ስለሰማ መሶቡን ከፍቶ ቢያይ ሕፃን ልጅ አገኘ ። መሶቡን ብቻ ወደ ወንዝ ጥሎ ሕፃኗን በድብቅ እን ዲያሳድጉለት ራቅ ወዳሉት ዘመዶቹ በአደራነት አሰቀመጣት። ከብዙ ዓመታት በኋላ ላቅመ ሔዋን በደረሰች ጊዜ የቅርብ ወዳጅ ታማኝ በመኾኑ ልጃቸውን ይድሩለት ዘንድ ንጉሡን ዐፄ **ድልነአድን** ለመነ ። ንጉሡም ከዘመን ብዛት የተ ነሳ ሴት ልጅ መውለዳቸውን ረስተውት ነበር። ወደ ወንዝ እንዲጥል ከታዘዘው መሶብ ውስጥ ልጅቱን እንዳገኘና እንዳሳደጋት ነገራቸው። ንጉሡም ብዙ ሰዓት ከሰዙ በኋላ ከጃቸው እንዳልወጣች ስላወቁ መልካም ነው ፈቅጃለሁ ሰርጓን ደግሰን ለለምንድራት አምጣልን አሉት፤ እሱም ለማምጣት ተሰናብቶ ወደዘመ ዶቹ ኼደ። ለዘመዶቹም ታሪኩን ነገራቸው ። ዘመዶቹም በዚህች ሕፃን የዚህ ዓይነት ጭካኔ ቀደም ብለው የፈጸሙባት ያለ ምክንያት አይደለም፤ አንተም ታማኝነትኽን ለላፈረስክ ቅጣት ያገኝሃል ፤ ልጅቱንም አንተንም ያጠፏችኋል አሉት።

መራ ተክለሃይማኖት የዘመዶቹን ምክር ከሰማ በኋላ ወደንጉሡ ቤት መመለስ ፈራ ። ንጉሡም ኼዶ በመቅረቱ በመልቀቃቸው ተጸጸቱ ። ወታደሮቻ ቸውን ፈልገው ይዘው አንዲያቀርቡት ላኩ ። ወታደሮቻቸው ከመራ ተክለሃይ ማኖት ወገኖች ጋር ታላቅ ጦርነት አደረጉ ። የንጉሥ ወታደሮች በሽንፈት ሸሽ ተው ወደ ንጉሡ ኼዱ ። ራሳቸው ንጉሡ ወደ ጦርነቱ ገቡበት ጥቂት እንደተ ዋጉ ወታደሮቻቸው ስለደከሙባቸው ወደ አንድ ተራራ አመሩ ። መራ ተክለሃ ይማኖት ሕዝቡን አረጋጋ። ንጉሡም ረዳት ስላላገኙ ወደ ሸዋ ሸሹ ። መራ ተክ

ለሃይማኖት የንጉሡን ርቆ መኼድ ባወቀ ጊዜ ልጅቱን አስመጥቶ ታላቅ ሰርግ አድርጎ አገባት። በኋላ ሥልጣነ መንግሥቱን ይዞ ተቀመጠ ።

ወደወንዝ ልትጣል በመሶበወርቅ የተወሰደችው **ልዕልት መሶበወርቅ** ተብላ መጠራት ጀመረች። ነጉሡ ሸሽተው ስለኼዱ መራ ተክለሃይማኖት ድልን ስለተቀዳጀ በግእዝ "ዘአጉየየ መራ ለድልነአድ" ተባለ ። ትርጕሙም መራ ድ ልነአድን አሸሸው ማለት ነው። ዘአጉየየ የሚለው ስያሜ ስመ መንግሥቱ አደ ረገው። ዛጉዬ የሚለው ዘአጉየየ ከሚለው የመጣ እንደ ኾነ ይነገራል ። መራ ተክለሃይማኖት እና ንጉሡ ድልነአድ የተዋጉበት ቦታ አስከዛሬ መራ በመባል ይታወቃል ። ይህ ከኾነ ንግሥና ከቀዳማዊ ምኒልክ ከሰሎሞናዊ ዘር በቴጌ መሶ በወርቅ አማካኝነት ተላልፏል ማለት ነው።

(፫) ቅዱስ ላሊበላ

መራ ተክለሃይማኖትና **ልዕልት** መሶበወርቅ ከወለዷቸው ልጆች አንዱ ንጉሥዩም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ኾነ ።

ቅዱስ ላሊበላ ከንጉሠ ነገሥቱ ከንጉሥዩምና ከእናቱ ኬረዎርና ከተባ ለችው ከአገው ሴት ታኅሣሥ 29 ቀን 1120 ዓ. ም. ተወለደ ።

ኬረዎርና ከላስታ አገው መጥታ በንጉሡ ቤት በአገልጋይነት የተቀመ ጠች ነበረች። ኬረዎርና ማለት ቤተክርስቲያን ማለት ነው። ንጉሠ ዣንሥዩም ውበቷ ስለማረከው ደረሰባት ልጅም ፀነሰች። በሌሊት በራእይ በዚህች ሌሊት በማሕፀንሽ የተቀረጸው ሕፃን ፈጣሪውን ለማገልገል የተመረጠ ነው የሚል ድምፅ ቅዱስ ሚካኤል አበሠራት። ጥቂት ቀኖችም እንዳለፉ ፅንሱ እየገፋ ኼደ። አቴጌ ዕፅፍት የተባለችው የነጉሡ የሕግ ባለቤት መኻን ሰለነበረች አል ወደደቻትም ፤ ኬረዎርናን ከባድ ሥራ ታሠራት ጀመር። የመውለጃዋ ጊዜ ሲደ ርስ እንጨት ለመልቀም እኼደችበት ጫካ ውስጥ ወለደችው። ኬረዎርና አቴጌ ዕፅፍት በተንኰል እንደተነሣችባት ስለምታውቅ ሕፃኑን ይዛ ወደ ቤተ መንግ ሥት ለመመለስ የሚያሠጋ እንደኾነ አሰበች። ሮሃ ከተባለው ቦታ ላይ በአንድ ዋሻ ውስጥ አስተኟቸው። እንድትወለድ የፈቀደ ፈጣሪህ ነው፤ ወደ ቤት ወስጄ ዐይኔ እያየ ከማስገድልህ ሳላይህ ከዚህ ብትሞት ይሻላል ብላ ከዋሻው ውስጥ ትታው ኼደች ።

ወደ ቤተ መንግሥቱም በደረሰች ጊዜ ኬረዎርና ተዳክማ ስለነበር ወደ ቀች። ይኽንን የሰማ የንጉሥ አገልጋይ አየሮጠ ኼዶ የኾነውን ኹሉ ለንጉሡ ነገረው። ንጉሡ ወዲያው ለድኳሚ ማስታገሻ የሚረዳትን ነገር አንዲያደርጉላት አዘዘና ስለልጁ ኹኔታ ጠየቃት ። እርሷም የተፈጸመውን ኹሉ ገለጸችለት። ንጉሡም አዛዡንና አገልጋዮቹን ጠርቶ ትታው ወደመጣችበት በቶሎ ይዘዋት

እንዲኼዱና በሕይወቱ ቢገኝ መልካም በሕይወቱም ባይገኝ ሬሳውን በፍጥነት እንድታመጡልኝ ብሎ ላካቸው ።

እነርሱም እንደታዘዙት ኹሉ አየተፋጠኑ ኼደው ሕፃኑ ወደ አለበት ደረሱ። በዚያን ጊዜ ንቦች ከላዩ ላይ ሰፍረው አገኙት ። የንቦቹ በሕፃኑ ላይ መስፈር ያስደነቃቸው ላሊብላ አሉት። በአገው ቋንቋ ላል ማለት ማር ማለት ስለኾነ ማር ይበላል ማለት ነው።

ፈላጊዎች ንብ ሰፍሮበት በመገኘቱ ሊመግቡት ይኾናል በማለት ላሊበላ ቢሉትም ፤ እሱ ግን አድጎ በንጉሥነት በመረነት በመቀጠሉ ሕዝብና ንብን በማ መሳሰል የተነገረለት ምስጢራዊ ትንቢት ተፈጻሚነትን አገኘለት ። ስሙም ላሊ በላ ተብሎ በመረነት ኖረ ።

(፪) ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ

የላሊበላ የወንድሙ የሐርቤይ (ገብረ ማርያም) እና የመርኬዛ ልጅ ፤ ነአኩቶ ለአብ ይባላል። የሰም አወጣጡ እናቱ ምጥ ተይዛ እያለ በቅዳሴ ጊዜ ዲያቆኑ ሥጋ ወደሙ አቀብለው ሲመለሱ ነአኩቶ እያለ ሲያዜም በመወለዱ ነአኩቶ ከሚለው ላይ አብ የሚል ቅጥያ ተጨምሮበት ነአኩቶ ለአብ ተብሎ እንዲጠራ ኾነ ፤ ትርጕሙ አብን አናመሰግነዋለን ማለት ነው።

(ሐ) የባሕርይ ስም (ስመ ባሕርይ)

ባሕርይን ፣ ጠባይን የሚያመለክተው ስም ከራሱ ከባለቤቱ በስተቀር ሊወረስ ወይም ሌላ ሊጠራበት የማይቻል ነው። <u>ለምሳሌ</u>፦ እግዚአብሔር፣ ኤልሻዳይ፣ አዶናይ፣ መለኮት ... የፈጣሪ የባሕርይ ስሙ ነው ። እንዲሁም ደግሞ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ የፈጣሪ የአንድነት የሦስትነት ስም ስለኾነ የባሕርይ ስም ይባላል። እንደ አገባቡ ቅጽል ተጨምሮበት ግን መሰየም ይቻላል።

ነቢዩ ኢሳይያስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም በሥጋ ተገልጾ እንደሚመጣ ሲተነብይ ፤ ድንግል ትፀንሳለች ስሙንም ዐማኑኤል ተለዋ ለች ይህም ማለት "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" ማለት ነው ብሎ ትንቢት በተናገ ረው መሠረት በስሙ ትርጓሜ ጌታ ሲወለድ ስሙም ዐማኑኤል ተባለ ። ይህም ለሱ ብቻ የሚነገር ሌላ ሊጋራው የማይገባ የባሕርይ ስሙ ነው (ኢሳ. 7፥14 ፤ 8 ፥8 ፤ ማቴ. 1፥32)። ዘወማኑኤል (ዘማኔል) ብሎ ቅጽል ጨምሮ መሰየም የተሻለ ነው።

እመቤታችንን ቅድስት ድንግል ማርያም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ሲያበሥራት ስሙንም ኢየሱስ ይባላል ይህም መድኃኒት (መድኃኒዓለም) ማለት

ነው፤ መንግሥቱም ዘላለማዊ ነው አለት። ይህ መንግሥቱ ዘላለማዊ የተባለው ክርስቶስ ነው። በግሪክ ቋንቋ ክርስቶስ፤ በዕብራይስጥ ቋንቋ መሢሕ ፤ በግእዝ ቋንቋ ቅቡዕ ወይም ንጉሠ ነገሥት ማለት ነው። መንግሥቱም ዘላለማዊ ነው። እነዚህ ስሞች የጌታ የባሕርይ ስሞቹ ናቸው (ዮሐ.1፥1 ፤ ሉቃ.1 ፤ ማቴ.1፥18 ፤ ማር.1፥1 ፤ ማቴ.16፥16)።

(መ) የመጠሪያ ስም በቅኔ ምርምር

አንዳንድ ጊዜም የመጠሪያ ስም ከአባት ስም ጋር እንዲመሳሰል ቅኔ ተላብሶ ይሰየማል ፤

<u>ለምሳሌ</u>፦ በጎንደር፣ በመርሐቤቴ ወይም በሞረት እንዲሁም በተለያየ አካባቢ የልጅ ስም ከአባት ስም ጋር ገጥሞ የተፈለገውን ሐሳብ እንዲያስተላ ልፍ ተደርጎ በምርምር ቅኔ ይሰየማል። ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ወቅትን እና ጊዜን ተከትሎ የሚሰየምም ስም አለ ።

<u>ለምሳሌ</u>፦ በጣሊያን ጊዜ ታዋቂው ዐርበኛ የነበሩት በላይ ዘለቀ የአባታ ቸው ስም ዘለቀ የሳቸው በላይ ተብሎ ተጠርቷል ። ለዘፈን አቀንቃኞችና ለፋከ ራም የሚስማማ ቅኔያዊ ስም በመኾኑ ኹሉም ሲያንጐራጉረው ይሰማል ።

ዐባይ ውሃ ሞልቶ ባያሻግርህ
<u>በላይ</u> አትመጣም ወይ ባፋፉ ዞረህ

የፍቅር አስከ መቃብር ልብወለድ መጽሐፍ ደራሲ ዐዲስ ዓለማየሁ የሳቸው ስም ራሱ ከአባታቸው ስም ጋር እንዲገጥም ተደርጎ የተሰየመ ነው። በመጽሐፋቸው ድርሰት የተገለጡ ስሞች ከባት ጋር እንዲስማሙ ተደርገው ተሰይመዋል።

<u>የወንድ ጸታ</u>	<u>የሴት ጸታ</u>
■ መሠረት ተሠራ ፤	መሠረት
■ መንግሥቱ ዘላለም ፤	መንግሥቱ
■ በዛብህ ውበቱ ፤	በዛብሽ
■ ቦጋለ መብራቱ ፤	ቦጋለች
■ ታፈረ ድንበሩ ፤	ታፈረች
■ አበራ ፀሓይ ፤	አበራሽ
■ እንተነህ መኰሪያዬ ፤	እንቺነሽ
■ አየለ ጎይሉ ፤	አየለች
■ ውድነህ በጣሙ ፤	ወድነሽ

■ ዋጋዬ አንተነህ ፤	ዋጋዬ
■ የሠራህ ግሩም ፤	የሠሸ
■ ይኹን በፍቃዱ ፤	ትኹን
■ ግሩም ተሠራ ፤	ግሩምነሽ

የሚሉ ስሞች በፍቅር አስከ መቃብር መጽሐፍ ውስጥ ይገኛሉ ።

ሰዎች እየተጠሩበት ከአባት ጋር ገጥመው የሚሰሙ ስሞች አሉ።
ለምሳሌ፦

■ ስማኸኝ በለው	ስማችኝ
■ ሹመት ሲሻኝ	ሹመቴ
■ አድጎ አይቼው	አድጋልኝ
■ አገሬ ይልማ	አገሬ
■ እውነቱ ገነነ	እውነት
■ ዘላለም እንየው	ዘላለም
■ ይገደብ ዓባይ	ትገደብ
■ ግርማቸው አማረ	ግርማዋ
■ ጸጋ ቸኮለ	ጸጋ
■ በጸጋ አንዳርጋቸው	በጸጋሽ
■ ፍቅር ዐዲስ	ፍቅር
■ ፍቅር አሸናፊ	ፍቅሬ

ሌሎችም ካባት አልፈው አያት ተቀናጅተው ቅኔያዊ ምስጢር ፤ ዐረፍተ ነገር የሚሠሩ ስሞች አሉ።

ለምሳሌ፦ ቢወጣ አያለቅበት ብሩ።
ተመስገን ዘላለም ደሳለኝ።
ቃል-ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት።

ከቅዱስ መጽሐፍ ጋር ካሉት ስሞች የተገናኙ እንደዚሁ የተሰየሙ ስሞች አሉ።
ለምሳሌ፦ የሥላሴ ዕለት የተጋቡ ባልና ሚስቶች ባማርኛ የምርምር ቅኔ ሲቀኙ ላቸው ።

ሥላሴ በቤትሽ ገብተው ሲባርኩሽ
ለይኩን ብርሃን የሚባል ልጅ ይስጥሽ ።

በትንቢቱ መሠረት ልጁ ባመቱ ሲወለድ የተነገረው ተፈጽሟልና ለይኩን ተባለ ማለት ነው። ትርጕሙም እግዚአብሔር ዓለምን ፈጥሮ ሲያበቃ ብርሃን ይኹን አለ ማለት ነው። በዚህ አይነት የሚሰየሙ ስሞች ብዙ ናቸው (ዘፍ. 1፥16)።

■ ታመነ አብርሃም (ዘፍ. 18፥)
■ ጎይመተ አብርሃም ፤ (ለሴትም ይኾናል)

■ ነቢዩ ኤርምያስ ፤ ነቢዩ ዳንኤል ፤ ነቢዩ ኢዩኤል .....
■ መጽሐፈ ሲራክ ፤ (ለሴትም ይኾናል)
■ ግርማ ሞገስ ፤
■ በእምነት ደረጀ (ለሴትም ይኾናል)
■ ለባሲተ ሞገስ (ለሴት)

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አምላክን ለስችሮታው በማድነቅ ፤ በማፍቀር የሚሰየም ስም አለ ለምሳሌ፦

■ ላመስግነው	ላመስግን
■ አላምረው	አላምር
■ ሰማ-እግዜር	ሰማኝ-እግዜር
■ ሲምር-ጌታ	ሲምርሽ-ጌታ
■ ሰጠኝ-ጌታ (ጌታ-ሰጠኝ)	ሰጠኝ-ጌታ
■ ባንተ-አምላክ	ባንቺ-አምላክ
■ ባሳዝነው	ባሳዝን

አንዳንድ ጊዜ ከዘመድ ወይም ከጐረቤት ጋር በሚደረገው አለመግባባት፤ የደረሰባቸውን በደል፣ ሐዘንና ጥቃትን ለመግለጽ መልእክቱን በሚወለደው ልጅ አማካኝነት አንዲተላለፍ ይደረጋል ።

■ አሰመላሽ	አሰመልሺው
■ አንዳርጋቸው	አንድአርጊያቸው
■ አንዳልካቸው	አንዳልሻቸው
■ ዝምበላቸው	ዝምበያቸው
■ ይግረማቸው	ትግረማቸው
■ ደምመላሽ	ደመልሺ
■ ድፋባቸው	ድፊባቸው
■ ጸጥአርጋቸው	ጸጥአርጊያቸው
■ ሽጉጤ	መሣሪያን ያመለክታል:: ወደብቡቴ ሽጉጥ ያለ ማለት ነው::
■ ሸንቁጥ	ግረፍ: ጥበስ ማለት ነው (ሸንቁጤ)

ይህን የመሳሰሉ አሉ ፤ ነበሩ።
አንዳንድ ጊዜ ስም ባሕርይን ፣ ግብርን እና ጠባይን ይዞ ሲኼድ ይታያል። "ስም ይመርሐ ኀበ ግብሩ" ስላም ተብላ የምትጠራ ልጅ ሰላማዊ የኾነ ባሕርይ ይታይባታል ማለት ነው ። በርግጥ ይህንን የመሰለው ስም ድምፅን ጎላ አድርገው ቢጣሩት ለሰው ልጆች ደስታን የሚሰጥ መልእክት አለው ። በሕርዩ ሸጋ ነው ሲሉ እንግዳወርቅ ይሉታል።

(ሠ) የፍቅር እና የቍልምጫ ስሞች

ቍልምጫ ፍቅርን ፣ ማሞገስን ወይም ወዳጅነትን ፣ የሚገልጽ ነው ።

የይሥሐቅና የርብቃ ልጅ ስሙ ያዕቆብ ነበር። እግዚአብሔር ግን አስ ራኤል ብሎ በቍልምጫ ስም እንደጠራው በትንቢተ ኢሳይያስ ተገልጿል። እስ ራኤል ማለት ትርጓሜው "ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ ያሸንፋል" ማለት ነው። (ኢሳ. 45፥4 ፤ ዘፍ. 32፥22–32)።

ፍቅርን ወይም ወዳጅነትን ለመግለጽ አንዳንዴ ታላቅ ወንድም ታናሽ ኣኅቱን በቁልምጫ መጥራቱ የተለመደ ነው። በተለይም ሕፃናትን በቍልምጫ መጥራት የተለመደ ነው። እንዲሁም አንድ ሰው ወዳጁን ሌሎች በማይጠሩት ስም ከፍቅሩ የተነሣ ቢጠራ ያ ስም የቍልምጫ ስም ነው ለሚለት ይቻላል።

አብዛኛውን ጊዜ የቍልምጫ ስም የመጨረሻው ፊደል ዬ የሚለውን ያስከትላል ። ብርሃንዬ፣ ማኅሌትዬ... ወይም ደግሞ በኹለት ፊደል የሚጠቀ ለል ቁልምጫ ለምሳሌ መኰንን የሚለውን መጠሪያ መኩዬ፤ ጌታቸው የሚለ ውን ጌትዬ (ጌትሽ) ይባላል። አንዳንድ በኹለት ፊደል ሲጠቀለል ለቍልምጫ የማይመችም ስም ደግሞ አለ። <u>ለምሳሌ</u> ፦ አረጋ፣ አረጋይ፣ አርአያ፣ አሮን የሚለውን በኹለት ፊደል ዬ ተጨምሮበት ለማቆላምጥ ቢሉት አይመችም ። ረ ፊደል ባለጌነት ይባላል (ሩ ፣ ሪ ፣ ራ)።

በፍቅር የተነሣ ፍቅረኛሞች ፤ ባልና ሚስት እንዲሁም የሚቀራረቡ ቤተሰቦችና ወዳጆች በዚህ መልኩ እየተቈለማመጡ ፣ ቢሞጋገሱ ፍቅርን ፤ የማኅበራዊ ኦርጋ፤ መቀራረብን ይፈጥራልና የሚደገፍ ነው።

አንዳንድ ሰዎች በውጭ አገርም ኾነ በአገር ውስጥ የራስ ባህል ያልኾ ነውን ስማቸውን ወደ ፈረንጅ ስሞች ቀይረው የሚቆለማመጡ አሉ፤ ጄሪ (ኢየ ሩሳሌም) ቲጂ (ትዕግሥት) ጆኒ (ዮሐንስን)፤ ጆርጅ (ገብረ ጊዮርጊስን) ፤ ማርዮ (ኀይለ ማርያም) ፤ ማይክ (ኀይለ ሚካኤል) ፤ በማለት በዚህ አይነቱ አጠራር ሲጠራሩ ይሰማል። አውሮፓ ቀመስ በመኾኑ «የሰው ወርቅ አያደምቅ» ያሰኛል

የራሳችን አለን፦ ኢየሩስ (ኢየሩሳሌም)፤ ኤልቢ (ኤልሳቤጥ) ቤቲ (ቤተ ልሔም) ጂጂ (እጅጋየሁ) ፤ ሩፊ (ወልደ ሩፋኤል) ጉሌ (ጉልላቴ) ማዱ (ማኅ ደረ) ሌላም ማለት የተለመደ ነው ። ይህ ዅሉ ከፍቅር የመጣ ስለሚመስል ተቃውሞ የለበትም።

ድንገት የሚከሠት ሕፃን ከተወለደ በኋላ እስከሚሰየም ስም ሲፈልጉ ጊዜ በመወሰዱ ሳይታሰብ እንደቀልድ የሚሰየሙ የቍልምጫ ስሞች አሉ።

<u>ለምሳሌ፦</u> በቤተሰብ በመጥራት ተለምዶ ማሙዬ፣ ማሙሽዬ (ማሙሽት) ማሚቱዬ (ማሚቱ)፣ ሚሚ፣ ይባላል። አብዛኛው በኋላ ዕድሜ ላይ ይቀይሩታል

ሮዚና፣ ቤቢ ፣ ቢሲ ፣ ቢጢ፣ ቢጣ፣ ቡጪ፣ ሲዲ፤ ቦቢሻ፣ ሙኒሻ፣ ኢሚ ፤ እንዲህ አይነቱ የቍልምጫ ስም አንዳንዴ በዕድሜ ሲጐለምሱ ይቀ ራል። አንዳንዶችም መልካምነቱን ተቀብለው በዚያው እየተጠሩበት ይቀጥላሉ። ላንዳንዶችም ተጨማሪ የቤት ስም ይኾናል ፤ ባለቤቱ ከወደደው ጕዳት የለ ውም ። ዋናው ነገር ግን ግራ ከሚያጋባ ስም ጥሬ ወጥ ከመግባት መጠንቀቅ ይገባል ለማለት ነው።

አንዳንድ ጊዜም የቤት እንስሳትን ስም ይዞ የሚጠሩበት የቍልምጫ ስሞች አሉ። ለምሳሌ፦ ዉሮ፣ ዉሪ፣ ውርዬ ፤ ቲቲ. ቲቲዬ፣ ቡጢ፣ ኩኩ (ኩኩ መለኮቴ) ። አንዳንድ ጊዜ መጠሪያ ስም ኾኖ የሚቀር አለ። ለምሳሌ፦ ኦኦ - ኦኦሻ ፤ ፋፋ - ፋፋሻ ፤ ቡጡ - ቡጡሻ ፤ ደቦጭ ፣ ቻቻ ፣ ኮኪ ሌሎችም ስሞች አሉ።

ኣኹንም፤ ያለውን እውነት ለመግለጽ ነው እንጂ ባለቤቱ ከተሰማማ፣ ኅብረተሰቡም ከለመደው ለመጠራት ኾነ ላለመጥራት የሚከለክል ምንም ነገር የለም። መጠራት ወይም አለመጠራት የራስ ምርጫ ነው ። ነገር ግን እነዚህ የቍልምጫ ስሞች ለምሳሌነት ያኽል የተጠቀሱት ወላጆች ስምን ለልጆቻቸው ሲያወጡ ከመጀመሪያው መንፈሳቸውን ደስ የሚያሰኝበትን መሰየም እንዲችሉ ነው ። ልጆች ግን ለሚሰየምላቸው ስም ለወላጆች ሽልማት ወይም ምስጋና ሲሰጡ ታይቶ አይታወቅም ፤ ካልተደሰቱበት ግን ራሳቸውን አሳምነው እስከሚለ ውጡ ድረስ ጊዜ ይወስድባቸዋል ።

ልጅ ከተወለደ በኋላ በለም ለያሜ ብዙ ጊዜ አለመስማማትና ይኹን አይኹን የሚል ወላጆችም (ባልና ሚስት) የየራሳቸው ስም ማውጣት የተለመደ ነው ። አንዳንዴም እቤተሰብ ውስጥ የቅርታ ለሜት መኖሩና እንግዳ የኾነ ስም ቶሎ አለመለመዱ እና ተቀባይነት አለማግኘቱ የተለመደ ነው ። ወላጆች ግን የሌሎችን ትችት ሳይፈሩ ለነሱ መንፈስ ደስ ያላቸውን ቢያወጡ ቀስ አያለ ይለመዳል፣ ተቀባይነትም አያገኝ ይኼዳል ማለት ነው።

(ረ) ለቤተሰብ የሚሰጥ ያክብሮት ስም

በማንኛውም ነገድ በዕድሜ የሚቀድመውን ማክበር የተለመደ ባህልና ሥርዐት ነው ። ይህም ሲባል ተከባሪው አክባሪውን በበታችነት እንዲያየው ወይም እን ዲንቀው በመከበሩ ራሱን ከማንም በላይ ከፍ አድርጎ እንዲያይ አይደለም።

አባትና እናትኽን አክብር በተባለው ትእዛዝ መሠረት (ዘጸ.. 20) አባት አባባ፣ አባዬ ፤ አባብዬ እናት እማማ፣ እማዬ ፣ እማምዬ (እምዬ) ይባላል። በፈረንጅ አገር ያደጉት ልጆች ወደ ፈረንጅኛው እያደሉ፤ በአባባ ፋንታ ዳዲ፤ በእማማ ፋንታ ማሚ (ማም) በማለት ይጠራሉ ። አክብሮቱ ቢደገፍም ይህ አይ ነቱ የኢትዮጵያውያን ባህል አይደለም።

በዚህ ዘመን በተለይም በከተሞች አካባቢ የሚወለዱ ልጆች አባትና እናታቸውን አባባ (አባዬ) እማማ (እማዬ) ከማለት ይልቅ በስማቸው በነጠላው አንጠልጥለው ሲጠሯቸው ይሰማል። አንዳንዶቹ ወላጆች ሕፃናቱ እንዲያርሙ ከማድረግ ይልቅ በስም መጠራትን የሥልጣኔ ምልክት አድርገው ይቈጥሩታል። ወላጆችም አባባና (አባዬ) እማማ (እማዬ) ከመባል ፋንታ በስማቸው እየዘረ ጠጡ በመጠራታቸው ዘመናዊ የኾኑ የሚመስላቸው ካሉ ተሳስተዋል ። ምርጫ ቸው ነው በስማቸው መጥራት አለባቸው የሚባል አባባልም አለ ፤ ዲሞክራሲ አዚህ ላይ አይሠራም ።

ዘጠኝ ወር በሆዷ ተሸክማ ጡቷን አጥብታ ያሳደገች እናት እናትነቷን የሚገልጸውን የእናትነት ሥልጣኗን ፣ ማዕረጓን ፣ ክብሯን ማጣት የለባትም ። አማዬ ወይም አማማ በማለት ኹሉም በባህሉ (እናንዬ ፣ አባዬ፣ እምወድሽ) በማለት እናት ትጠራለች ። አባትም እንደዚሁ አባባ ፣ አባብዬ ፣ አብዬ በመ ባል ያባትነት ሥልጣኑን እና ማዕረጉን ፣ ያባትነት ክብሩን ማጣት የለበትም ። ወላጆችም ልጆቻቸውን አያከበሩ በፍቅር አንዲንከባከቧቸው፤ በሥርዓት አንዲ ያሳድጓቸው ይገባል ። ልጆችም ወላጆችን የሚገባውን ክብራቸውን ሊሰጧቸው ይገባል።

በዕድሜ ታላቅንም እትዬ እገሊት፣ ጋሼ እገሌ ማለት አየተዘነጋ ነው። ወላጆች ይህን በማረም የማስተማር፤ ሥርዓት የማስያዝ ኀላፊነት አለባቸው።

በቤተሰብ ውስጥ የበኵር ልጅ ታላቅና ታናሽ መከባበር እንዲገባቸው በቅዱስ መጽሐፍ የታዘዘ ነው ። የመጀመሪያ የኾነውን በኵር (አንጋፋ) የሚባለ ውን፤ ታናናሾች የኾኑት ባክብሮት ወንዱንም ሴቷንም ይጠራሉ። እንዲሁም ባባ ትነት ቦታ በናትነት ቦታ ያዩዋቸዋል። በአርኣያነት፤ በመመኪያነት፣ ባለኝታነት ያክብሯቸዋል፤ እነሱ የሚሉት ተሰሚነት አለው።

- ወንድምዬ
- ወንድም አበባ
- ወንድም እሸት
- ወንድም ዓለም
- ወንድም ጋሼ (ሻ)
- ወንድም ጌታ
- ወንድም ጥላ
- ጋሼ (ጋሽዬ)
- አበባ (አበብዬ)
- እታበባ (እታባ)
- እቴቴ (እቴትዬ)
- እትዬ
- አታለም
- እምወድሽ
- አባዬ
- ሽንኮሬ

ይህን ቤተሰብ ነኝ ያለ ኹሉ ይጠራዋል ። ከኹሉም ዕድሜ በኵር (አንጋፋ) የኾነ በደረጃ ኹሉም ይጠራበታል። አንት ደግሞ ጋሼ የጋሼን ታላቅ አብዬ። አክስትን እትዬ ፣ አባዬ ተብሎ ይጠራል ። ቤተ ዘመድ ኹሉ በታላቅነት ያ ሉትን በንዲህ ባለ ኹኔታ ይከባበራሉ ።

(ሰ) በጥንታዊ ትምህርት ቤት የሚሰየም ስም

የጥንታዊ ትምህርት ቤት የሚባለው ወጣቶች ከወላጆቻቸው እና ከተወለዱበት አካባቢ ተለይተው ወይም ኮብልለው ወደ ሩቅ አገር በመኼድ ወላጆቻቸው ፈልገው አንዳያገኟቸው በሉላም ምክንያት ስማቸውን ይቀይራሉ ። የሚማሩት ትምህርት መንፈሳዊ የኾነ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ነው ፤ በዚህ ምክንያት የተቀየረው ስማቸው መጠሪያ ኾኗቸው ይኖራል ማለት ነው።

የወንድ ጸታ	ትርጉም
ሐዋዝ	አማረ - ማፋጭ (መኃ. 3፡24)
ሠረቀ-በርሃን	ብርሃን ወጣ (መዝ. 96(97)፡11)
ሠረገላ-በርሃን	የብርሃን ሠረገላ
ሰቡሕ	ምስጉን (ነግሥ)
ነቅዐ-ጥበብ (ነቃጥበብ)	የጥበብ መፍለቂያ
ናሁ-ሠናይ	እነሆ መልካም (መዝ.132፡1)
እም-አእላፍ	ከመቶ ሺዎች
ክነፈ-ርግብ	የርግብ ክንፍ (ይዌድ)
ወሃቤ-ጸጋ	ጸጋን የሚሰጥ (ኪዳን ጸሎ)
ወልደ-ነጐድጓድ	የነጐድጓድ ልጅ (ማር. 3፡17)
ዕንቈ-ባሕርይ	ጸባዩ እንቁ የኾነ

- ዲበ-ኩሉ — ከኹሉ ላይ (መዝ. 96(97)፤9)
- ጎሐጽባሕ — የማለዳ ጎሕ (ቅዳ. ማር)
- ጥቀ-ጌር — ቸርነትህ እጅግ በዛ (መዝ.72፤1)
- ጥዑመ-ልሳን — አንደበቱ የሚጥም (ያሬድ)
- ፈለገ-ሕይወት — የውሃ ምንጭ
- ፈለገ-ብሉም — የሰላም ምንጭ
- ፍሬ-ወናይ — ጥሩ ፍሬ

<u>የሴት ጸታ</u>

- ለኪ ይደሉ — ላንቺ ይገባል (አንቀጸ ብርሃን)

በጣሊያን ወረራ ጊዜ የቅኔ ትምህርት አስተማሪ የነበሩ አንዲት ምሁር ሴት ይጠሩበት ነበር።

- ሐረገ-ወይን — የወይን ሐረግ (መሐ.. 1፤6)
- ሥኑ-ሕይወት — የሕይወት ውበት
- ሰብለ-ወንጌል — የወንጌል አሸት
- ነገደ-እስራኤል — የእስራኤል ነገድ (ዘፍ. 49፤7)
- አስካለ-ወይን — የወይን ዘለላ (መሐ.. 4፤29)
- አንቀጸ-ብርሃን — የብርሃን መውጫ (ወዳ. ማ)
- አፀደ-ወይን — የወይን ተክል (መሐ.. 1፤6)
- ዕንቈ-ብርሃን — የሚያበራ ዕንቁ (ዘጸ. 28፤18)
- ከብከብ — ሠርግ (ዮሐ. 2፤1)

(ሸ) የተዋሐዱ የመጠሪያ ስሞች

ኢትዮጵያውያን በባህልም ፣ በዘርም በመዋሐድ ፣ በመጎራበትም ፣ ተደባልቀው አምቾና ጋብቻ ኾነው ከጥንት ጀምሮ እስከ ቤተመንግሥት ድረስ ተሳስረው ኖረዋል። በየዘመኑ የተነሡትም ነገሥታት ከኹሉም ዘር በመደባለቅ ተዋልደዋል፣ ወልደዋል፣ ተዋርሰዋል ፤ በዚህም የተነሣ የመጠሪያ ስሙም አብዛኛው የጋራ ስሞች ኾነዋል። ለምሳሌ እኹሉም ዘንድ ከሚታወቁት ሀገራውያን ስሞች፤ ከበደ (ከበደች)፣ በቀለ (በቀለች) ጉግሳ፣ ጌታቸው፣ ተስፋዬ፣ ሸዋዬ... ሌሎችም የሚጠሩባቸው የተዋረሱ አሉ።

የወንዶች እና የሴቶችን ስሞች ግእዝ (ግእ)፣ ዐማርኛ (ዐማ)፣ ኦሮምኛ (ኦሮ)፣ ትግርኛ (ትግ)፣ ጉራጌኛ (ጉራ)፣ ዶርዜኛ (ዶር)፣ ዕብራይስጥ (ዕብ) ፣ ግሪክ (ግሪ) ፣ ዐረብ (ዐብ)... ከየትኛው ክፍል ተሰባስበው በተቀራረቢ ትርጉም ቀርበዋል።

በዚህ ዝግጅት ኹሉንም የኢትዮጵያውያንን የመጠሪያ ስሞች በማሟላት ያካትታል ማለት አይቻልም ፤ ነገር ግን ለማስታወሻነት ጠቃሚነት ይኖረዋል በማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን በመጨመር፤ በዘመነ ነገሥታት፣ በዘመነ መሳፍንት ፣ በዘመነ አንድነት እና በዘመነ ኮሚኒስት በነበሩት የታሪክ ጊዜያት የተሰየሙትን እንዲሁም ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ፣ የታሪክ ሰዎች ፣ ለዘመናት ሲጠሩባቸው የኖሩትና እኹንም ብዙዎች እየተጠሩበት ያለውን ሲጠሩበት የተሰማውን በዋቢነት በመጥቀስ ማብራሪያ ጭምር በመስጠት በማሰባሰብ በዚህ ጽሑፍ ሰፍረዋል።

ብዙዎቹ የታሪክ ሰዎች ሞክሸ ስሞች ስላላቸው የእንዱን በቻ በመውሰድ ተጽፈዋል።

መጠሪያ ስሞች ከአባት ስም ጋር ሲገጥሙ በምሰጢር መንታ ትርጉም ወይም የምርምር ቅኔ እንዲሰጥ በማድረግ ቀርቧል። ይህንም ደራሲው አንባቢ ሳይሰለች እንዲመራመርበት ለማድረግ ከመኾኑ በስተቀር ማንንም የግለሰብ ስም አይወክልም። የሚወክለው የኢትዮጵያውያንን ስም ነው። ትርጉምና ትንታኔው ለመንደርደሪያ ያህል ቢጠቀስም ፤ የትርጉም አሰጣጥ እንዲሁም ምርጫ ግን የባለቤቱ ወይም የወላጅ ነው ።

የስም አወጣጥ እና አተረጓጐም እንደ ጊዜ ፣ እንደ ሰው ኹሉ የተለያየ አመለካከት ሊሰጠው ይችላል። ስለዚህ ፤ ደራሲው በመሰለው መንገድ ተርጉሞ ያላለቀ ቀጣይ መኾኑን የሚያመለክት <u>ነጠላ ጥቅስ</u> (...።) አድርጓል።

(፩) የወንድ የመጠሪያ ስሞች

- ሀ -

1. **ሀሎ** (ግእ)
ሀለወ ከሚለው ግስ የተገኘ ሲኾን ፤ ትር ጕመ ፡ አለ፣ ያለ፣ ኖረ ፣አኗኗር ፣ ባሕ ርይን የሚመለከት ነው።
ሀልውና – ሀላዌ

2. **ሀርቤ** (ግእ) (ዐርቤ)
ገፋረ ማርያም በመባል በክርስትና ስማቸ ውም ይታወቃሉ። ካራቱ የዛጌ ታላላቅ መንግሥታት ከይምርሓነ፣ ከላሊበላ እና ከነአኩቶ ለአብ አንዱ ናቸው። በዘመናቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷ ሊቀ ጳጳስ (ፖትርያርክ) እንዲኖ ራት ጥረት አድርገው ነበር።

3. **ሀበነ** (ግእ)
ስጠኝ ማለት ነው።
ያባት ስም አእምሮ ቢል ይገጥማል።

4. **ሀብቴ** (ግእ)
ወሀበ ሰጠ ከሚለው ግስ ይወጣል።
በብዙ መንገድ ይተረጎማል ፤ ጤንነት ሀብት ነው ። ልጅ ማግኘት ሀብት ነው። ገንዘብ ማግኘት ሀብት ነው።
ሀብትዬ - ሀብቱ - ሀበታሙ
ሀብታገኘሁ - ሀብትደግ - ሀብቶም
ሀብትይመር = ጌታ ኹን፣ አደግ ፣ ግዛ፣ ንዳ፣ ተሾም፣ ተሸለም ማለት ነው።
ሀብተ ማርያም ክርስትና ስምን ተመልከት።
ኽብት የሚለውን ተመልከት።

5. **ሀገር** (ግእ) አገር (ዐማ)
ያባት ስም ይልማ ቢል ይገጥማል።
አገሬ በሚለው ይመ.

6. **ሁንዴ** (ኦሮ)
ሥር መሠረት ማለት ነው።
ሁንዴሳ
ኹሉ (ሁሉታዬ)
ገጽ 89 ቁ. 836 ተመልከት

7. **ሃይማኖት** (ግእ)
ሀይመነ፣ አመነ ታመነ ከሚለው ግስ የወ ጣ ነው ። በክርስትና እምነት ማመን አነዱ ሃይማኖት ነው ።
በራስም ታምኖ መገኘት ፤ በቃል ኪዳን መገኘት ሃይማኖት ነው።

8. **ሄኖክ** (ዕብ.)
ታደሰ፣ ጥበብን የተማረ ማለት ነው።
በዘመነ አበው የቃየን ልጅ ነው ። ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ተወሰደ ያየውንና የተገለጸለትን በመጽሐፉ ጸፈ። መጽሐፉ በኢትዮጵያ ብቻ ተርፎ ተገኘ (ዘፍ.4፥17 ፤ 5፥18)።

9. **ሆሳዕና** (ዕብ)
አባክህ አኹን አድን ፤ ደኅንነትን ስጥ ማለት ነው። ወይም መድኃኒት ማለት ይኾናል (ማቴ. 21፥9)።

10. **ሆሴዕ** (ዕብ.)
ዕርዳ፤ አድን ወይም እግዚአብሔር ያድ ናል ማለት ነው ። በዚህ ስም በቅዱስ መጽሐፍ ኹለት ሰዎች ተጠርተውበታል (ሆሴ. 1፥1)።

11. **ሆዴ - ሆድዬ**
የእኔ ሆድ ...።
ከፍቅር የተነሣ ወላጅ እናት የምትሰይ መው ስም ።

- ለ -

12. **ለማ**
ለመለመ ፤ ዘር አዝመራው በዛ ማለት ነው (ዘፍ. 1፥29)።
ያባት ስም አታክልቴ ቢል ይገጥማል።
ለማልኝ - ለማወርቅ - ለማወሰን
ለማየሁ - ለምለሙ - ለምነህ

13. **ለሙ - ለሚ** (ኦሮ)
ኹለት ጥንድ ማለት ነው።
ለሚላ - ለሚቾ - ለሚያ - ለመታ

14. **ለቤዛ** (**ለቤዛዓለም**)
ለምትክ፣ ለካሳ...። ዋስ ኾንክ (ምሳ.13፥8 ፤ ዘሌ. 25፥24 ፤ ማር. 10፥45)።
ያባት ስም ዓለሙ ቢል ይገጥማል።

15. **ለታ** (ኦሮ)
ለምለም ፤ ልምላሜ ወይም በቀለ ጸደቀ ማለት ነው።

16. **ለታሪክ**
ወደፊት የሚነገር ፤ ይነገራል ...።
ያባት ስም ዕርቅይኹን ቢል ይገጥማል።

17. **ለዕለት**
ተገኝቷል። ማምሻም ዕድሜ ነው...።
ያባት ስም ሲሳይ ቢል ይገጥማል።

18. **ለወጠኝ**
ቀየረኝ፣ ሌላ ሰው አደረገኝ ...።
ያባት ስም ፍቅሩ ቢል ይገጥማል።
ለወጣቸው - ለወጠው

19. **ለዓለም** (ግእ) **ላለም** (ዐማ)
አንትሙ ለዓለም ብርሃኑ። ትርጕም፤ እና ንተ ያለም ብርሃን ናችሁ (ማቴ.5፥14)።
ያባት ስም ብርሃኑ፣ ጥላኹን ፣ ጌታኹን ቢል ይገጥማል።

20. **ለዝና**
ለሰም ፤ ከብር ለማግኘት።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።
ለዝናው - ለዝናዬ - ለዝናቸው

21. **ለይኩን** (ግእ)
ለይኩን ብርሃኑ ለእግዚአብሔር እምላክነ ሳዕሌነ ። የእምላካችን የእግዚአብሔር ብርሃን በላያችን ይኹን (መዝ. 89(90)፥17 ፤ዘፍ. 1፥3)።

22. **ለገሠ**
ባለ መቆጠብ ሰጠ፤ ቸርነትን አደረገ።
ያባት ስም ብሩ ቢል ይገጥማል።
ለገኘ - ለጋሥ - ለገሠልኝ
ለግሥ - ለገሢ

23. **ለጋው - ለጋዓለም**
ለምለም ያልጎመራ (ያልበሰለ)።
ያባት ስም አበበ ቢል ይገጥማል።

24. **ለጥይበሉ**
ይስገዱ ...።
በዚህ ስም የሚታወቁ ደጃዝማች ለጥይ በሉ ገብሬ በማጨው ጦርነት ባለቤታቸው ከጎናቸው ሳይለዩ አብረው ሳገራቸው

ወ

ከብር ሲዋጉ ባለቤታቸው በጠላት እውሮ ፕላን ቦንብ ተመተው የሞቱባቸው ናቸው
ለማርጋቸው - ለጥይበል

25. **ሉልወርቅ**
ከባሕር የሚገኝ የከበረ ዕንቁ (ዘፍ. 2፥12)።
ሉል ንጉሥ ሲነግሥ በእጁ የሚጨብጠው።
ይህም አገርን በእጁ አስተዳድራለኹ ማለትን ያመለክታል።
ያባት ስም አገኘሁ ቢል ይገጥማል ።
ሉልዬ - ሉሉ - ሉሌ - ሉልአየሁ
ሉልሰገድ = ሉል የሰገደለት አስቀድሞ የንጉሥ ስም ብቻ ነበር ፤ በኋላ ዘመን ግን ተለውጦ ለኹሉም ኾነ።

26. **ሉቃስ (ሮማ)**
ጌታ ከመረጣቸው ከሰባ ኹለቱ አርድዕት አንዱ ነው ። በወንጌል አጻጻፉ የተማረ፤ ሐኪምና ሠዐሊ እንደነበረ ይነገርለታል (ሉቃስ 1፥1) ።

27. **ሉባንጃው**
ሉባንጃ ነጭ ጥሩ መዓዛ ያለው ልዩ ዕጣን ነው።

28. **ሉፋ (ጉራ)**
በድካምህ ዋጋኽን አግኝ ማለት ነው።

29. **ሊቀመልአኩ**
የመላእክት አለቃ ማለት ነው ። የሚወዱት ሊቀመልአክ በሚከበርበት ዕለት የተወለደ ልጅ ሊኾን ይችላል።
ያባት ስም ታደገኝ ቢል ይገጥማል።

30. **ሊቁ - ሊቃውንት**
አዋቂው ፤ ምሁሩ፤ የተማረ በዕድሜ የበሰለ (ዶክተር) ።
ያባት ስም ታዬ ቢል ይገጥማል።

31. **ሊበን (ኦሮ)**
በኦሮሞ የዘር ሐረግ ከከረዩ ልጆች አንዱ ነገድ ሊበን ይባል ነበር።

32. **ሊባኖስ (ግሪ)**
ከገሊላ በስተሰሜን ተራራማ አገር፤ በዝ ግባ ዛፍ የታወቀ ፤ አመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደችበት ቦታ ሊባኖስ ነው (መዝ. 91፥12 ፤ ኢሳ.2፥12)።
በዚህ ስም ከሶርያ ከመጡት ዘጠኙ ቅዱሳን አባቶች በፊት ኢትዮጵያ የደረሱት ሊባኖስ ይባሉ ነበር። በስማቸው ደብረ አሰቦት ገዳም የነበረ በዐፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን ደብረ ሊባኖስ ተብሎ ተሰየመ።

33. **ላመስግነው - ላመስግን**
በተሰጠኝ ስጦታና በጎ ነገር ...።
ያባት ስም ሙሉቀን ቢል ይገጥማል።

34. **ላሰብለት**
ልጨነቅለት፤ እንዳይጎዳ ...።
ያባት ስም ፍቅሬ ቢል ይገጥማል።

35. **ላቀው**
በሊጠው ፤ የተሻለ ኾነ ማለት ነው።
ያባት ስም በላቸው ቢል ይገጥማል።
ላቃቸው - ላቅያለው

36. **ላንተይደሩ**
ይዝሙልህ ፤ ይታዘዙልህ።
ያባት ስም በጎሰው ቢል ይገጥማል።

37. **ላእከ (ግእ) ላእከ ማርያም**
ለእከ ከሚለው ግስ የወጣ ነው ።
ላከ ሰደደ፣ ተላከ ማለት ነው።

38. **ላውጋው**
ልናገረው ፤ ልመሰክር ማለት ነው።
ያባት ስም ለዓለም ቢል ይገጥማል።
ላውጋለት - ላውጋላቸው

39. **ላጲሶ (ሀድያ)**
በዚህ ስም የሚታወቁት ዶክተር ላጲሶ ጌ. ዴልቦ የታሪክ ምሁርና ተመራማሪ ዘጠኝ መጻሕፍቶች አሳትመዋል።

40. **ሌንጮ (ኦሮ)**
አንበሳ ፣ ጎበዝ ማለት ነው ።

41. **ሌዊ (ዕብ)**
ይጠጋል ማለት ነው።
ልያ ለያዕቆብ የወለደችለት ሦስተኛ ልጅ ቢኾን ሙሴና አሮን ከሌዊ ነገድ ነበሩ።
ስለዚህም ሌዋውያን የኾኑ ኹሉ ለክህነት አገልግሎት ተለዩ (ዘፍ. 46፥11 ፤ ዘጸ. 32፥25 ፤ ዘዳ. 33፥8)።

42. **ልመንህ**
እውነተኛነትኽን ልየው ...።
ያባት ስም አባቴነህ ቢል ይገጥማል።
ልመነው - ልመናቸው

43. **ልሳኑ (ግእ)**
የድምጽን ውበት ይገልጻል። ጥሁመ ልሳን ቢል የበለጠ ነው።
ወልሳኑ ይነብብ ጽድቀ። ትርጕም፤ አንደበቱ ፍርድን ይናገራል (መዝ. 36(37)፥30)።
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።
ልሳነወርቅ - ልሳንነ

44. **ልበሙሉ**
የማይደነግጥ፣ ደፋር ፣ ጀግና፤ ጉብዝናን ያመለክታል።

ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።
ልበብርሃን - ልባሙ ቢል እውነትን፣ ሕጽን ፣ ዕውቀትን ፣ ማስተዋልን ያመለክታል (ዳን. 4፥16 ፤ 7፥4 ፤ ማር. 3፥5 ፤ ማር. 2፥6)። እንዲኹ ደረትን።

45. **ልብስፀሓይ**
ክብርን ያመለክታል (ማቴ. 17፥2)።
ያባት ስም ሞገስ ቢል ይገጥማል።
ልብስማርያም - ለባሲ - ልብሴ
ልብሰታል - ልብስህ

46. **ልንገረው - ልንገርህ**
ያለፈ ታሪክ፣ ምሰጢር ለማለት ...።
ያባት ስም በእምነት ቢል ይገጥማል።

47. **ልክየለህ**
ለአቋምኽ አቻ ፤ ለሀብትኽ ወሰን የለውም ለማለት ይነገራል ...።
ያባት ስም ይታገሡ ቢል ይገጥማል።
ልክየለበት - ልኬ - ልኩ
ልኬነህ - ልክነው - ልክነህ

48. **ልዑል (ግእ)**
ልዑል እምልዑሳን ። ትርጕም ፤ ከከፍተኞች ይልቅ ከፍ ያለ ማለት ነው።
ይህ ስም ከነገሥታት ዘር ለኾኑት የሚሰጥ ቅጽል ነው። በአኹኑ ጊዜ ማንም ሰው በመጠሪያ ስም ሊጠራበት ይችላል።
ላዕላይ - ልዕልና (ግእ)
ታላቅነት ማለት ነው (ኢሳ. 2፥11)።

49. **ልየው - ልይህ**
አስቲ ልመልክተው?
የተጻጻ ፤ የተናፈቀ ዐዲስ ነገር ...።
ያባት ስም ፋንታዬን ቢል ይገጥማል።

50. **ልዩወርቅ**
ማንም የማይተካከለው።
ያባት ስም ተሾመ ቢል ይገጥማል።
ልዩሰው - ልዩነህ - ልዩነት
ልዩዜና - ልዩዝና - ልዩፋንታ

51. **ልደቴ**
የኔ ልደት ፤ የትውልድ ቀኔ ፤ ልጅ በማግኘት እንደገና መታደሰን ያመለክታል።
ያባት ስም ታደሰ ቢል ይገጥማል።
ልደቱ - ልደት - ልደታ

52. **ልዳ - ዘልዳ**
ከኢየሩሳሌም በስተ ምዕራብ የምትገኝ ከተማ ነች ። በዚህች ቦታ ጴጥሮስ ኢንያን የሚባለውን ሰው ፈውሷል (የሐ. ሥራ 9፤32-35) ። በአዩን ጊዜ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ሲጠሩበት የሰማል።
የቅዱስ ጊዮርጊስ ዕለት የተወለደ ወይም ወዳጅ የኾነ በዚህ ስም ይሰይማል።
[ፀሓይ ዘልዳ]።

53. **ልጃምሮ (ልጅአምሮ)**
ልጅ ለማግኘት በጉጉት ላይ ያሉ ወላጆች የሚሰይሙት ስም ነው።
ያባት ስም ሰጠኝ ቢል ይገጥማል።
ልጅዓለም - ልጅሽጋው

54. **ሎሚነህ - ሎሚዬ**
ደስ የሚል ሽታ የምትሸተኝ ነህ ...።
መዓዛው ጥፍጥ ፤ የሚመጠጥ ኮምጠጥ የሚል ተወዳጅ ፍሬ ነው።
ያባት ስም ሽታዬ ቢል ይገጥማል።

55. **ሎሬንዞ**
በዚህ ስም ይጠሩ የነበሩ ብላቴን ጌታ ሎሬንዞ ትእዛዝ ናቸው። (የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) (1892- 1939 ዓ.ም.) ኤርትራ ውስጥ አካለ ጉዛይ ተወለዱ በማጨው በጣሊያን ጦርነት ላይ ተሳትፈዋል ። በሰደት ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ወደ ለንደን ተጉዘዋል። የራስ እምሩ ጎይለ ሥላሴን የመጀመሪያ ልጅ ወይዘሮ የምሥራች እምሩ ባለቤታቸው ነበሩ።

- ሐ -

56. **ሐሊፎም** (ትግ)
አለፈ ፣ አለፉ ማለት ነው ። **ሕሱፍ**

57. **ሐምታ** (ዶር)
ጎበዝ ተራማጅ ማለት ነው።

58. **ሐረገወይን (ግእ) ዐረገወይን**
ዐጸደ ወይን ፥ የወይን ቦታ ፤ አስካለ ወይን ፥ የወይን ዘለላ እንደሚለው ጉሱ ሐረገ ወይንም ፥ የወይን ሐረግ ይባላል (መኃ. መኃ. 7፤10-14)።
ያባት ስም ፍሬው ቢል ይገጥማል።
ሐረጉ - ሐረጌነህ - ሐረግ

59. **ሐረጎት** (ትግ) ዐረጎት
በዚህ ስም ይታወቁ የነበሩት ደጃዝማች ሐረጎት ዓባይ ናቸው (1901-1967 ዓ.ም.)።

60. **ሐሳቤ** (ግእ)
የኔ ሐሳብ ፣ ምኞቴ ነበረ ...።
ያባት ስም ሞላ ቢል ይገጥማል።
ሐሳቡ - ሐሳቤወርቅ - ሐሳብነህ

61. **ሐብለወርቅ - ሐብሌነህ**
በአንገት ላይ የሚደረግ ጌጤ ...።
ያባት ስም ከፈለኝ ቢል ይገጥማል።

62. **ሐኪምነህ** (ግእ) **ሐኪም**
እዳንክኝ ፣ ፈወስክኝ ...።
ሐኪመ ካሰው ግስ የወጣ፤ ዐከመ ብልህ ኾነ ማለት ነው። ከበሽታ የሚገላግል ።
ያባት ስም ደጉ ቢል ይገጥማል።

በዐፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት በአንግሊዞች ከልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስ ጋር ተማርከው የተወሰዱ ወርቅነህ እሸቴ ። በኋላ በአስኮትላንድና በህንድ ህክምናን ተምረው የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ዶክተር በቅጽል ሐኪም ወርቅነህ እሸቴ በመባል በታሪክ ይታወቃሉ።
ሐኪሙ - ሐኪማቸው

63. **ሐውልተ** (ግእ)
ሐውልተ ስምዕ ዘኢያሱ ። ትርጉም የኢያሱ የምስክሩ ሐውልት (ኢያ. 8፤29)።
ያባት ስም ኢያሱ ቢል ይገጥማል።
ሐውልቴ - ሐውልት - ሐውልቱ

64. **ሐዋርያ - ሐዋርያው**
የተላከ፣ መልእክተኛ ማለት ነው። ያባት ስም ከሐዋርያት አንዱ ከኾነ ይገጥማል።
ጴጥሮስ ፣ ቶማስ ፣ ማቴዎስ ።

65. **ሐዋዝ** (ግእ)
መልካም፣ ያማረ የጣፈጠ ደስ የሚያሰኝ ማለት ነው። (መሐ. ሰሎ. 3፤24(2) ፤ ምሳ .3፤24) መዝሙረ ሐዋዝ ዘምስለ መበንቆ።

66. **ሐይሶ** (ዶር)
አንተ ፣ አንተነህ ማለት ነው።

67. **ሐደራ** (ትግ) ዐደራ ማለት ነው።

68. **ሐዲስ** (ግእ)
ሐዲስ (ግእ) ዳራሲ ዐዲስ ዓለማየሁ ተጠርተውበታል ። ሰባት መጽሐፎችን ጽፈዋል ። ዐዲስን ይመልከቱ ።

69. **ሐጎስ** (ትግ)
ደስታ ማለት ነው ...።
በዚህ ስም የሚታወቁት ግራዝማች ሐጎስ በርሄ ናቸው ። ለአገር ነጻነትና ድንበር በማይጨው ጦርነት በዐርበኛ ከጣሊያን ጋር የተፋለሙ (1896 - 1948 ዓ.ም)።

70. **ሕልሜ**
አናፍቀው የነበረ ፣ ጉጉቴ ...።
ይናፈቅ፣ በጉጉት ይጠበቅ የነበረ አውነት ኾኖ ልጅ በመገኘቱ፤ ሕልም ተፈ (ዘፍ. 40፤13 ፤ 18፤19 ፤ 41፤45)።
ያባት ስም ታመነ ቢል ይገጥማል።
ሕልሜነህ - ሕልምነህ - ሕልማቸው

71. **ሕዝባየሁ - ሕዝባለም**
ብዛት ያለው ሰው ...።
ያባት ስም ተዋሕዶ ቢል ይገጥማል ፡

72. **ሕዝቅኤል** (ዕብ)
እግዚአብሔር ጽንዕትን ብርታትን ይሰጣል ማለት ነው ። ሕዝቅኤል ወደ ባቢሎን ከተማረኩት አንዱ ነበር ፤ ከታላላቆች ነቢያት አንዱ ነው (ሕዝ. 1፤3)።

73. **ሕዝቅያስ** (ዕብ.)
እግዚአብሔር ጎይሌ ነው ማለት ነው። የእስራኤል ንጉሥ ነበር። ከአሶር ንጉሥ ከሰናክሬም ጦር እግዚአብሔር መልአኩ ቅዱስ ሚካኤልን ልኮ አዳነው (2ኛ ነገ.18፤9 ፤ ኢሳ.38፤1)።

ወ

74. **ሕይወቴ - ሕይወት** (ግእ)
ሕይወ ከሚለው ግስ ይወጣል ።
ጤናዬ፣ አተረፍከኝ፤ ደስ የምትል ...።
መኖር፣ መዳን፣ መፈወስ፣ ጤንነት፣ ደኅን
ነት ማለት ነው። ዘላለማዊ ሕይወት ፤
መንፈሳዊ ሕይወት፤ ሥጋዊ ሕይወት፤
(ዘፍ. 2፥7 ፤ 6፥17 ፤ ሮሜ. 8፥6)።
ያባት ስም ፍሥሐ ቢል ይገጥማል።
ሕይወተ - ሕይወትነህ

75. **ሕጉ - ሕግነህ**
ገታህኝ፣ መስመር አሲያዝክኝ ...። ይኽ
ንን አድርጉ ያንን አታድርጉ የሚል
(ዘጸ. 20)።
ያባት ስም ተገኔ ቢል ይገጥማል።
ሕገእግዚአብሔር - ሕገሥላሴ

- መ -

76. **መለስካቸው**
አዳንካቸው ፣ ወደቀድሞው ቦታ ...።
ያባት ስም ሳላስብ ቢል ይገጥማል።
መልስ - መለሰው - መልሴ
መልሳቸው - መለሰው - ወደኋላ ቀስ
ሰው፤ አዞረው ፣ ወሰደው ወይም ወይ ብሎ
መልስ ሰጠው፤ ቃል ሰጠው (ማቴ. 17፥4 ፤
ኤር. 7፥13 ፤ መዝ. 138፥3)።

77. **መላን — መሉ - መለኪያነህ**
በዛን ፣ ደርዘን፣ ሙሉ ቍጥ፤ ይበቃል።
ያባት ስም ጸጋ ቢል ይገጥማል።

78. **መልአኩ** (ግእ) **መላኩ** (ዐማ)
የእግዚአብሔር መልአክ ስማዳን ፣ ስመ
ራዳት ፣ ለአዳኝነት የሚላክ ነው።
ይህን ተገን አድርጎ የሚሰየም ስም።
ያባት ስም ገነነ ቢል ይገጥማል።
መልአኬ - መልአከ

79. **መልካምሰው**
መልከ መልካም ደግ፣ ጥሩ፣ በጎ ሰው።
ባሕርይን፣ በጎነትን ይገልጻል ።
ያባት ስም ቀናው ቢል ይገጥማል።
መልካሙ - መልካም- መልኩ የሚያምር
ቆንጉ (ዳን. 2፥31)። **መልኬ - መልኬነህ**
መልካግርያም - መልኩ - ገጽታን፣
መሳይ መኾኑን ይገልጿል።

80. **መልከ ጼዴቅ** (ዕብ.)
መለከ ካለው ገዛ፣ አሸነፈ ማለት ነው።
የጽድቅ ንጉሥ፤ የሰላም ንጉሥ ማለት
ነው ። የእግዚአብሔር ካህን ነበር። አብ
ርሃምን ባረከው ። አብርሃምም ከሀብቱ
ዓሥራትን ሰጠው (ዕብ. 7፥1፤ ዘፍ.14፥18
፤ መዝ.109፥4) ።

81. **መልእክቱ (መልክቱ)**
የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ሊቀ
ሥልጣናት በኋላ ጊዜ የኢትዮጵያ ፓትር
ያርክ የነበሩ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍ
ሎስ በቀድሞ ስማቸው **መልእክቱ ወልደ**
ማርያም በመባል ይታወቁ ነበር።

82. **መሐሪ** (ግእ)
መሐረ ፤ ይቅር አለ፣ ተወ ማለት ነው።
መሐሪ ርሑቀ መዓት ወብዙሐ ሣህል ።
ትርጉም ፤ ይቅር ባይ ከቀጣ የራቅህ
ይቅርታህ የበዛ (ጸሎ. ምና. 2ዜና. መዋ.
33፥5)። **መሐረ - መሐረነ - መሐሩ**

83. **መሠረት**
ከሥር፣ ከመጀመሪያ ...።
መሠረታቲሃ ውስተ አድባር ቅዱሳን ።
ትርጉም፤ መሠረቶቹ በተቀደሱ ተራሮች
ናቸው። (መዝ. 86፥1)።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።
መሠረቱ - መሠረትነህ

84. **መሥራት**
በፊትህ ወዝ አንጀራ ትበላለህ (ዘፍ.3፥19)።
ያባት ስም ዘላለም ቢል ይገጥማል።

85. **መረጡህ - መረጠህ**
ብቁ ኾኖ በመገኘት ።
ያባት በላቸው ቢኾን ይገጥማል።

86. **መራሒ** (ግእ) **መርሐ**
መርሐ ፤ መመሪያ ሰጠ መራ ካለው
የወጣ ነው። መራሒ ሲል መሪ አስተማሪ
ማለት ነው።

87. **መረራ** (ኦሮ)
አማረኝ ፣ አማረ ማለት ነው።

88. **መርሥኤ ሐዘን** (ግእ)
ሐዘን ማስረሻ ...።
በዚህ ስም የሚታወቁት ብላታ መርሥኤ
ሐዘን ወልደ ቂርቆስ ናቸው።
(1891 - 1971 ዓ.ም.) በ1910 ዓ. ም. በግእ
ዝ የተጻፉትን መጽሐፍ ከሊሎች ምሁራን
ጋር በመኾን ወደ ዐማርኛ የተረጐመዋል።
ሃያ አንድ መጽሐፍ ጽፈው አሳትመዋል።

89. **መርሻ**
ያለፈውን ፣ የተፈጸመውን ፣ ሐዘንም
ደስታንም የምታስረሳ ...።
ያባት ስም ቢኾነኝ ቢል ይገጥማል።
መርሻው - መርሻዬ - መርሻዬነህ
መርሻነህ - መርሻዓለም

90. **መርከቤ**
ከአንዱ ወደ አንዱ መሸጋገሪያ ፤
ያባት ስም ተበጀ ቢል ይገጥማል።
መርከቡ - መርከብ

91. **መርዓዊ** (መራዊ) (ግእ)
መርዐ፤ ጐመገ ካለው የወጣ ነው።
ሙሽራ ማለት ነው። ወጐንደዮ **መርዓዊ**
ደቀሳ ኩሎን ወኖማ ። ትርጉም ፤ ሙሽ
ራውም በዘገየ ጊዜ ኹሉም አንቀላፉ ተኙ
(ማቴ. 25፥5)።

92. **መርድ - (መርዕድ)** (ግእ)
የሚያንቀጠቅጥ ጽምፁ የሚያስፈራ።
(ደባትሪሁ ዘነድ ወሠረገላሁ **መርዕድ**)
ማዕረጉ ከንጉሥ በታች ከራሶች በላይ
አልጋ ወራሽ የሚጠራበት (ዕዝሁ 1፥19)።
በዚህ ስም የሚታወቁ ጀነራል **መርድ** መን
ገሻ ናቸው (1908 - 1959 ዓ.ም.)።

93. **መርዳባ** (ኦሮ)
በዚህ ስም የሚታወቁት ፊታውራሪ መር
ደላ ጆቴ ናቸው ። በዐፄ ምኒልክ ዘመን
ወለጋን ያስተዳድሩ ከነበሩት ደጃዝማች
ጆቴ ቱሉ ልጅ ናቸው። የመርዳባ ታላቅ
አጎት ወይዘሮ አስካለ ማርያም ጆቴ
የልጅ ኢያሱ ባለቤት ነበሩ።

94. **መርጊያ - መርጊያው**
ረግአ ካለው ግስ የወጣ ፤ ረጋ፣ ቆመ፣
ማቆሚያ፣ ማረፊያ ማለት ነው።

95. **መርጋ** (ኦሮ)
በቀለ ፣ ጸደቀ ፤ የበቀለ ለምለም ሳር
ማለት ነው። መግራን ተመልከት።

ወ

96. **መሰለ**
መልክን፣ ባሕርይን፣ ጸባይን መስሎ ታየ ማለት ነው ።
ያባት ስም ውበቱ ቢል ይገጥማል።
መሰልክ - መሰልካቸው - መሰለኝ

97. **መሰንበት**
ሰንብቶ የተገኘ ...።
ጊዜን፣ ዘመንን፣ መቆየትን ያመለክታል።
ያባት ስም ደጉ ቢል ይገጥማል።

98. **መስክረም**
ወርን፣ ክረምት ማለፉን ያመለክታል ።
ያባት ስም ንጋቱ ቢል ይገጥማል።

99. **መስፍን**
ከንጉሥ ዘር ያይደለ፤ ነገር ግን አገርን ከጠላት ወረራ የሚያድን ጀግና ፤ ሺህ ሰው የሚመራ አለቃ ነው (ዘፍ. 36፥20፤ መሳ. 2፥11፤ 3)።
በዚህ ስም ብዙ ኢትዮጵያውያን ተጠርተዋል። ከነዚህም ውስጥ አንዱ ወርቀኛው ራስ መስፍን ስለሺ ናቸው።
መሳፍንት — ብዛትን ያመለክታል።

100. **መሳይ**
በኹሉም ነገር መስሎ የታየ ማለት ነው።
ያባት ስም ካሣኝ ቢል ይገጥማል።
መሳየ /ዬ/ - መሳይህ - መሳየወርቅ

101. **መስቀሌ - መስቀሉ**
ጌጤ ወይም መክራዬ ፤
የመስቀል ዕለት የተወለደ ሊኾን ይችላል
ያባት ስም በዙበህ ቢል ይገጥማል።
መስቀላ (ዶር)

102. **መሸሻ - መሸሻዬ**
መጠጊያ ፣ መሰወሪያ ...።
በዚህ ስም ብዙ ኢትዮጵያውያን ተጠርተዋል ። ከነዚህም ውስጥ
የዐፄ ቴዎድሮስ የመጀመሪያ ልጅ ራስ መሸሻ ቴዎድሮስ ይባሉ ነበር።

103. **መቅድም**
አስቀድሞ የሚነገር ነገር ...።
ቀደመ ካለው ግስ የወጣ ነው። ጀመረ በፊት ኾነ፤ መጀመሪያ ማለት ነው ።
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።

104. **መቂያ**
ሌላ አስኪገኝ፣ መጠበቂያ ...።
ያባት ስም አስነ ቢል ይገጥማል።

105. **መባእ (መባ)**
ስጦታ ማለት ነው ። ለክርስትና ስም ቅጽል ይኾናል ። ተወከፍ መባእነ ፤ ትርጉም መባችንን ተቀበል (ቅዳ.)።
ያባት ስም ሰጠኝ ቢል ይገጥማል።

106. **መብራቴ - መብራቱ**
የኔ ብርሃን፤ ጨለማን የገለጽከልኝ ...።
ያባት ስም ታዬ ቢል ይገጥማል።
መብራት - መብራሀቶም
መብራሀቱ(ትግ)

107. **መታሰቢያ - መታሰቢያዬ**
ምልክት የሚኾን ዘመትር አየታየ የሚኖር ሐውልት፤ ልጅ፤ ማለት ነው (ዘጸ. 28፥12 ፤ ማቴ. 26፥13)።
ያባት ስም ባይነሳኝ ቢል ይገጥማል።

108. **መታደል**
በመገኘቱ፣ በሰጠታው፣ በቸርነቱ የተገኘ።
ያባት ስም በፍርዱ ቢል ይገጥማል።

109. **መታፈሪያ**
በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በዚህ ስም የሚታወቁት ደጃዝማች መታፈሪያ መልከጼዴቅ ናቸው።
በዐፄ ምኒልክ ዘመን 1899 ዓ. ም. በመጀመሪያ ከተሾሙት የንጉሡ 12 ምኒስትሮች አንዱ ነበሩ።

110. **መና**
አበዊከሙሰ መና በልዑ በገዳም፤
ትርጉም፤ አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ (ዮሐ. 6፥49) ። መልኩ የድንብላል ጣዕሙ ማር ማር የሚል ሰማያዊ ምግብ ዳቦ ነው (ዘጸ. 16፥15 - 31)።
ያባት ስም ወረደ ቢል ይገጥማል።

111. **መንበረ - መንበሩ**
የክብር ቦታን ያመለክታል።
መንበር ታቦት የሚያርፍበት ሥጋ ወደሙ የሚፈተትበት፣ የክብር ጠረጴዛ፤ የክብር ዙፋን (ወንበር) ማለት ነው።
ቡሩክ አንተ በዲበ **መንበረ** መንግሥትከ።
በጌትነትህ ዙፋን ላይ አንተ የተመሰገንኽ ነኽ፤ የሠለስቱ ደቂቅ ጸሎት (ዳን.3፥55)።
ያባት ስም ክብሩ ቢል ይገጥማል።
መንበረወርቅ

112. **መንክር** (ግእ)
ድንቅ ማለት ነው።
መንክርሰ እግዚአብሔር በእርያሙ።
እግዚአብሔር በከፍታው ድንቅ ነው።
መንክር ስብሐቲከ ዘትገብር መድምመ።
ትርጉም፤ በምስጋና የተፈራኽ ድንቅን የምታደርግ (መዝ. 92(93)፥4 ፤ ጸሎ. ሙሴ 1፥11) ።
ያባት ስም ግርማ ቢል ይገጥማል።

113. **መንገሻ**
የንጉሥ መንገሻ ስፍራ፣ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ንግሥ መፈጸሚያ ቦታ ፤ ታቦት የሚወጣበት ንግሥ የሚደረግበት ፣ በከበሮ በጽናጽል የሚዘመርበት ፣ ዕለታ ደስታ ያለበት ፤ በዚህ ቀን የተወለደ ሊኾን ይችላል ...።
በዚህ ስም ይጠሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ብዙዎች ነበሩ ። የዐፄ ዮሐንስ ልጅ ልዑል ራስ መንገሻ ዮሐንስ አንዱ ነበሩ።

114. **መንግሥቱ**
የርሱ ግዛት ለማለት ...።
የእግዚአብሔር መንግሥት መንግሥተ ሰማያት ነው። የሰው ልጆች መንግሥትም በምድራዊው አንዲ መሠርቱ የተፈቀደ ነው። **መንግሥተ አብ - መንግሥቱ መንግሥቴ**

115. **መከለያ — መከለያ**
ከለለ ጋረደ ፣ ጋሻ ኾነ ማለት ነው።
ያባት ስም ሰጠኝ ቢል ይገጥማል።

116. **መከተ**
ከተሰነዘረው፤ ከተላከው ኹሉ ከለለ ።
ጋሻ ኾነኝ ማለት ነው።
ያባት ስም በጋሻው ቢል ይገጥማል።
መከታ - መከታዬ - መከታቸው

117. **መካለ** (ዶር)
አሰደናቂ ፣ ድንቅ ማለት ነው።

118. **መካሻ**
በጠፋው ወይም በተሰወረው የተተካ።
የዕርቅ ጊዜ በጠፋው መታረቂያ።
ያባት ስም ቢኾነኝ ቢል ይገጥማል።
መካሻው - መካሻዬ

119. **መክብብ** (ግእ)
ከበበ ሾመ ካለው የወጣ ነው ። ሰባኪ፣ አስተማሪ፣ ሹም፣ ሰብሳቢ አለቃ ማለት ነው (ኩፋሌ 27)።
መክበበ ድንግል ክርስትና ስም ተመልከቱ።

120. **መኩሪያ - መኩሪያው**
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ ደጃዝማች መኩሪያ ባንተይርጉ ናቸው። በፈረስ ስማቸው አባ ጋተው ይባላሉ። በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ወደ ማይጨው ዘምተው ከጣሊያን ጋር በዐርበኝነት ተፋልመዋል።

121. **መኰንን** (ግእ) **መኳንንት**
ፈራጅ፣ ገዢ፣ ዳኛ፣ ቀጭ፣ ማለት ነው። **መኰንነ ጽድቅ** ፤ መኰንነ ምድር (መዝ. 9፥4 ፤ ሚሬ.7፥6 ፤ ኤር. 22፥30 ፤ ጥበ ሰሎ. 7፥12)።
በዚህ ስም ይታወቁ የነበሩ ብዙዎች ናቸው። ከነዚህም የዐፄ ኀይለ ሥላሴ አባት ራስ መኰንን ወልደ ሚካኤል ናቸው። ራስ መኰንን በሐረርጌ ብቻ 20 ቤተ ክርስቲያን አሠርተዋል ። አንዱም የቁልቢ ገብርኤል ነው።

122. **መውደድ**
አነሆ የውዴ ቃል! በተራሮች ላይ ሲዘል፣ በኮረብቶች ላይ ሲወረወር ይመጣል (መኃ. መኃ. 2፥8)።
ያባት ስም ተሻለ ቢል ይገጥማል።

123. **መዓዛ**
ሽታ ማለት ነው (ዘፍ.8፥21፤ ኤፌ.5፥2)።
ያባት ስም ሠናይ ቢል ይገጥማል።
መዓዛው - መዓዙ - መዓዛነህ መዓዛገነት -
መዓዛ ሕይወት ክርስትና ስምን ተመልከቱ።

124. **መዝሙር**
በዚህ ስም የሚታወቁት በሰላሴ አውራጃ ሌመን ሥላሴ 1892 ዓ.ም. የተወለዱት የቤተ ክርስቲያን የቅዱሳን ሥዕላት የሚሥሉ አለቃ መዝሙር ዳዊት ናቸው ። ሥዕላቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ግድግዳ ላይ አለ ። ለምሳሌ አጌዱ በዲስ አበባ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ግድግዳ ላይ የተሣለው ነው።
መዝሙረዳዊት - መዘምር

125. **መዝራዕተ** (ግእ)-**መዝራዕቱ**
ጡንቻው ማለት ነው ። **ልዑል መዝራዕትከ** ኢያአመሩ። ትርጉም ፤ አምላህ ከፍ ከፍ ማለቷን አላወቁም (ኢሳ. 26፥11)።
መዝራዕተ አብ ክርስትና ስምን ተመልከቱ

126. **መዝገበ**
የተከማቸ ፤ የተሰበሰበ ማንኛውም ሀብት እና ንብረቴ ነኽ ፤ **መዝገቤነህ** ተብሎ ስም ሊሰየም ይቻላል።
(ማቴ.6፥19፤ ማር.12፥14፤ ምሳ.10፥2)
መዝገቡ - መዝገቤ - መዝገብነህ
መዝገበ ሥላሴ ክርስትና ስም ተመልከቱ።

127. **መድኃኒት** (መዳኒት)
ጤናን የሚሰጥ ፣ የሚፈውስ
ወገብረ መድኃኒተ በማእከለ ምድር።
ትርጉም፤ በምድርም መካከል መድኃኒትን አደረገ። (መዝ. 73(74)፥12)።
ያባት ስም ድጋፌ ቢል ይገጥማል።

128. **መገርሳ** (አሮ) በቀለ ማለት ነው።

129. **መገኖ** (ጉራ)
ተወዳጅ፣ መጠጊያ ወገን ማለት ነው።

የእንጦጦ መንበረ ስብሐት ቅድስት ሥላሴን ቤተ ክርስቲያን ያሳነፁ አባ ኅይለ ሥላሴ ያባታቸው ስም መገኖ በመባል ይታወቃል።

130. **መግራ** (አሮ) በቀለ ማለት ነው።

131. **መጠነ** (ግእ) **መጠኑ**
በልክ የተደረገ ማለት ነው።
ወሠርአ ዕድሜሁ ወዓመታቲሁ መጠነ ይነብሩ። ትርጉም ፤ የሚኖሩበትን ጊዜውን ዘመኑን ወሰነ (ዘፍ. 11፥8 ፤ ዘዳ. 32፥8 የሐ. ሥራ 17፥26)።

132. **ሙሉጌታ**
በነዚህ ስሞች የሚጠሩ ብዙ ኢትዮጵያውያን አሉ ። ከነዚህም ውስጥ ጀነራል ሙሉጌታ ቡሊ (አሮ) ታዋቂ ጀነራል ነበሩ (1900 - 1953 ዓ.ም.)።
ሙሉፈለግ - ሙሉነህ - ሙሉሰው ሙሉሀብታም - ሙሉሀብት - ሙሉ ሙሉብርሃን - ሙሉመብራት ሙሉመብት - ሙሉሚዛን - ሙሉሸዋ ሙሉቀን - ሙሉብር - ሙሉጋት ሙሉአዳም - ሙሉዋጋው - ሙሉጸጋ ሙሏለም - ሙሉዘውድ - ሙሉፀሓይ ሙሉገበያ(ው)

133. **ሙላቱ**
መልኃ ከሚለው ጋር ይመሳሰላል። ሞልቷል፤ መሻገር አይቻልም ሊኾን ይችላል።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።
ሙላቸው - መልው - ሙላት

134. **ሙሊታ** (አሮ) ታዬ ማለት ነው።

135. **ሙቤ - (ሙሳ (ዐብ)፤ ሞሼ (ዕብ)** እጓለ ማይ ፤ ከውሃ ያወጣኹት ወይም የተገኘ ልጅ ማለት ነው፤ ከዐባይ ወንዝ ተጥሎ የፈርኦኑ ሴት ልጅ አግኝታው በፈርኦን ቤት ያደገ ፤ የወገኖቹ የእስራኤላውያን መሪ ኾኖ ከግብጽ ምድር አወጣቸው (ዘጸ.2፥10)።

136. **ሚልክያስ** (ዕብ.)
መልእክተኛዬ ማለት ነው ።
ነቢየ እግዚአብሔር ነው (ሚል.1፥1)።

137. **ሚልዮን** (ሚሊየን)
ዋጋህ ብዙ ነው፤ ወይም ብዙ ወርቅ ፣ ሀብት በሚጣ አይተካከልህም ለማለት...።
(1ኛ ዜና. 22፥14 ፤ 2ኛ ዜና.14፥9) ።
ያባት ስም ታፈሰ ቢል ይገጥማል።

138. **ሚናስ**
የሀገረ ተመይ ኤጲስ ቆጶስ አባ ሚናስ ይባል ነበር ፤ የመፈወስ የተሰወረውን የማወቅ ሀብተ ጸጋ የተሰጠውሰው ነበር (ስንክሳር ጳጉሜ 11 ገጽ269 ቁ.16)።
የዐፄ ልብነ ድንግልና የቴጌ ሰብለወንጌል ልጅ የዐፄ ገላውዲዮስ ታናሽ ወንድም ሚናስ ይባሉ ነበር።

139. **ሚክያስ** (ዕብ.)
እግዚአብሔርን የሚመስል ማን ነው።
ወይም ማነው እንደ እግዚአብሔር ማለት ነው። ነቢየ እግዚአብሔር(ሚክ. 1፥1)።

140. **ሚዛ** (ዶር) አበሳ ጋበዘ ማለት ነው።

141. **ሚዛኑ**
መሰፈሪያው፣ መለኪያው ማለት ነው።

142. **ሚደቅሳ** (አሮ) **ሚደቅሶ**
አማረ ፣ ቆንጆ ማለት ነው።

143. **ማሄ** (ዶር) ነብር ማለት ነው።

144. **ማለደ – ማለዳ**
ፀሓይ ሳትወጣ ፤ አድማስ ሲታይ ወፎች ሲንጫጩ ፤ ጎሕ ሲታይ የተወለደ ልጅ ማለዳ ሊባል ይቻላል ...።
ያባት ስም ደስታ ቢል ይገጥማል።
ኹለተኛው ትርጉም ደግሞ አማለደ ፤ አስታረቀ ማለት ነው።

145. **ማለፊያ**
አንዱ ትርጉም በጎነው ቢል። ኹለተኛው መሸጋገሪያ፣ መተላለፊያን ያመለክታል።
ያባት ስም ከልካይ ቢል ይገጥማል።

146. **ማመጫ**
መሸፈቻ ቦታ፣ በረሓ፣ መከጃ ማለት ነው።

147. **ማሞ**
ወንድ ልጅ ሲወለድ የሚጠራበት ስም። ትርጓሜው ፤ ደስ የሚያሰኝ ለማለት ነው። የቁልምጫ ስም ነው ። ከጣሊያን ወዲህ ግን ማሙሽ መባል ተጀመረ ይባላል።
በዚህ ስም ብዙ ኢትዮጵያውያን ይታወቃሉ ። ከነዚህም ውስጥ አንዱ በ1961 ዓ.ም. በሜክሲኮ ኦሎምፒክ በማራቶን ሩጫ ለኢትዮጵያ ወርቅ ሜዳልያ ተሸላሚ ማሞ ወልዴ ነው ። እናታቸው ወይዘሮ ገነሜ ጎበና አባታቸው አቶ ወልዴ ደጋጋ ይባላሉ ። 62 ጊዜ ዓለማቀፍ ውድድሮችን አድርጓል።

148. **ማረልኝ**
አዳነልኝ፤ ይቅር አለልኝ ይኾናል።
ያባት ስም በፈቃዱ ቢል ይገጥማል።
ማረን - ማረው - ማርልኝ - ማራቸው

149. **ማሩ**
ያ ማር፣ የርሱ ማር ስማለት ነው።
ጣፋጭነት ያለው የንብ ሥራ ሲኾን የብዙ አስደሳች ነገር ምሳሌ ነው።
ዐገቱኒ ከመ ንህብ መዓረ። ትርጉም፤ ንብ ማርን እንዲከብ ከበቡኝ (መዝ. 117፥12)።
ያባት ስም አይጠገብ ቢል ይገጥማል።
ኹለተኛ ይቅር አሉ ማለት ነው።
ማር - መአርነት - ማሬነህ - ማርነህ

150. **ማራኪ**
ደስ የሚያሰኝ ፣ የሚማርክ፣ ኹለተኛው ትርጉም በዐርበኝነት ድል ማድረግ ፣ አሸንፎ መያዝ።

151. **ማርቆስ** (ሮማ)
ከሰባ ኹለቱ አርድዕት አንዱ ነው ፤ በግብጽ ምድር ጣዖታትን አያጠፋ ወንጌልን የሰበከ ነው ። በተጨማሪ ወንጌሉንም ጽፏል (ማር. 14፥50)።

152. **ማርይሥሐቅ**
የቅዱስ ኤፍሬም ተማሪ ነበር (መጽሐፈ መነኰሳትን ጽፏል)።

153. **ማስረሻ**
ያለፈውን እንድረሳ ፤ እንዳላስታውስ።
ያባት ስም እንዳይከፋኝ ቢል ይገጥማል።
ማሰረሸ - ማሰረሰ

154. **ማስተዋል**
ከመደረጉ በፊት አርቆ ማሰብ ፤ በጉዳዩ ትኩረት መስጠት ።
ያባት ስም ጥበቡ ቢል ይገጥማል።

155. **ማስታወሻ**
አንዳይዘነጋ ፣ አንዳይረሳ
ያባት ስም ተገኘወርቅ ቢል ይገጥማል።

156. **ማኅተመ** (ግእ)
ምልክት አደረገ ማለት ነው።
የውል የማንኛውም ነገር መተማመኛ ፤ ስም የተቀረጸበት ሊኾን ይችላል።
ፈርኦን ለዮሴፍም በእንገቱ የወርቅ ዝር ግፍ (ማኅተብ) አደረገለት (ዘፍ. 41፥42 ፤ ኤር. 32፥10–14)። ማኅተበ - (ማኅተቤ)

157. **ማዕተብ** (ግእ) - **ማተብ** (ዐማ)
በመስቀል ላይ የተደረገ ነጭ፣ ጥቁር፣ ቀይ ክር፣ ፈትል የሃይማኖት ምስክርነት መግለጫ ነው ።
ማተቤነህ - ማተቡ - ማተቤ
አማተበ (አማዕተበ) ቤል በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አለ ማለት ነው። ማኅተበን ተመልከት።

158. **ማቱሳላ** (ዕብ)
የሄኖክ ልጅ ነው። የሕይወቱ ዘመን ዕድሜው ዘጠኝ መቶ ሰድሳ ዘጠኝ ዓመት ነበረ (ዘፍ. 5፥22)።

159. **ማቴዎስ** (ዕብ)
የአግዚአብሔር ጸጋ ወይም ምርጥ ማለት ነው፤ ከዐሥራ ኹለቱ ሐዋርያት አንዱ የኾነ የቀድሞ ሥራው ቀረጥ ይቀርጥ የነበረ በኋላ ጌታ ኢየሱስን የተከተለ ነው (ማቴ. 10፥3)።

160. **ማትያስ** (ግሪ)
ከአግዚአብሔር ጸጋ የተሰጠው ማለት ነው። በይሁዳ ቦታ የተተካው ሐዋርያ (ሐዋ. ሥራ. 1፥15–26)።

161. **ማኅደረ** (ግእ) ማኅደረ ማርያም
ማደሪያ ማለት ነው። ቅጽል ይኾናል።
ያባት ስም ዳዊት ቢል ይገጥማል።

162. **ማኑሄ** (ዕብ)
ዕረፍት ፣ ዐረፈ ተረጋጋ ማለት ነው ።
የሶምሶን አባት ነው። (መሳፍ. 13፥2)

163. **ማናለብኽ**
በጋሻህ ፣ በታላቅነትህ ፣ በሥራህ።
ማን አለ፣ ማን አለብኽ፣ ማንያኽአኽአ ማለት ነው።

164. **ማናዬ**
ጥያቄን ያመለክታል። ያየ ሰው ማነው?
ያባት ስም ሙሉዐብት ቢል ይገጥማል።
ማናየው - ማናየህ - ማናለበት
ማናለ - ማናኽሎት

165. **ማንደፍሮ**
ማን ኃይል አግኝቶ፣ ማን ተጠግቶ ...።
ያባት ስም ወሰን ቢል ይገጥማል።
ማንተዳፍሮት - ማንተጋፍቶት
ማንያዘዋል - ማንአኩል- ማንይንካው

166. **ማእዜ** (ግእ)
መቼ፤ ምንጊዜ፤ በምን ሰዓት ማለት ነው።
ማእዜ አበጽሕ ወእሬኢ ገጸ ለአምላኪየ። ትርጉም፤ መቼ እደርሳለኹ ? የአምላክንስ ፊት መቼ አያለኹ?
(መዝ. 41፥2)።
ያባት ስም በጽሑ ቢል ይገጥማል።

167. **ማዕረጉ** (ማዕርጉ)
ሹመቱ፣ ክብሩ፣ ከፍ ከፍ ያደረገው ...።
ያባት ስም አንተነኽ ቢል ይገጥማል።
መዐርግ - ማዕረግ - መዐረጉ (ማረጉ)
መዐረጌ (ማረጌ)

ወ

168. **ማዕበል** (ግእ)
ችሎታን ያመለክታል ። በትኔ ትምህርት አእምሮው ብሩህ የኾነን ተማሪ ማዕበል ይሉታል። አበለ ቢል ወረደ ፣ ፈሰሰ ፣ ተናደ፣ ጎረፈ ማለት ነው።
ኩሉ **ማዕበልክ** ወሞገድከ አንተ ላዕሌየ ጎለፈ። ትረጉም ፤ ማዕበልህና ሞገድህ ኹሉ በላዬ አለፉ (ዮና. 2፥3) ።

169. **ማዘንጊያ**፤ ማሰረሻ ማለት ነው።

170. **ማዳ** (ዶር) ምሕረቱ ማለት ነው።

171. **ምላሹ** (ትግ)
እግዚአብሔርን በጸሎት ጠይቆ የተመለሰለት ፤ ወይም መልስ የተሰጠበት።

172. **ምላት**
የሞላ የተትረፈረፈ ማለት ነው።
በሰሜን ሸዋ ዜና ማርቆስ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተወለዱት የአቶ ኽብቴ ልጅ አለቃ ምላት በተወለዱበት ዕለት 7 በጎች፣ 7 ፍየሎችና 7 ላሞች ተወልደው በማደራቸው ስማቸው ምላት ተባለ።

173. **ምሕረት** (ግእ)
መሐረ ከሚለው የወጣ ነው።
ማረን ፣ ይቅር በለን፣ ማለት ነው።
ምሕረትክ ወጽድቅክ ዘልፈ ይርከባኒ።
ትረጉም ፤ ቸርነትህና እውነትህ ዘወትር ይጠብቁኝ (መዝ.39፥11) ።
ያባት ስም ባይነሣኝ ቢል ይገጥማል።
ምሕረቴ - ምሕረቱ - ምሕረተ

174. **ምሥራቅ**
ብርሃን የሚታይበት ፤ ጠዋት ፀሓይ የምትወጣበት ።
እምሥራቀ ፀሓይ አሰከነ ዐረብ።
ትረጉም ፤ **ከፀሓይ መውጫ** አሰከ መግቢያ ድረስ (መዝ. 112፥3) ።
ያባት ስም **አገሬ፣ ፀሓዩ** ይገጥማል።
ምሥራቁ - ምሥራቂ

175. **ምሩጽ** (ትግ)
ምርጥ ማለት ነው ...።
በዚህ ስም የሚታወቀው **ምሩጽ** ይፍጠር በሞስኮ ኦሎምፒክ በሩጫ ውድድር ኹለት ወርቅ ያገኘ የኢትዮጵያ ባንዲራ ከፍ ብሎ እንዲታይ ያደረገ ነው።

176. **ምሳሌ - ምስሉ - ምሳሌው**
ነገር እንዳይረሳ ፤ ግልጥ ለማድረግ ሲፈለግ የሚቀርብ ማስረጃ። ሰሎሞን ብዙ ምሳሌዎችን ተናግሯል። (1ነገሥ. 4፥32) ጌታ ኢየሱስም ብዙ ምሳሌዎችን ተናግሯል።
ያባት ስም ደረሰ፣ ሰሎሞን ቢል ይገጥማል።

177. **ምሳዬ**
ከጸም በኋላ እኩለ ቀን ላይ የተገኘህ።
ራቤን ናፍቆቴን የምታስታግሥ፣ የኔ ምሳ።
ያባት ስም አንተነህ ቢል ይገጥማል።

178. **ምስክር - ምስክርነኽ**
ቃሉን የሚሰጥ፣ አማኝ ፣ የነበረ።
ቃል ኪዳን፣ ምልክት ፣ ምስክር ሊኾን ይችላል ። ዘፍ. 31፥44 ፤ 38፥18)።
ያባት ስም አገኘሁ ቢል ይገጥማል።

179. **ምስጋና**
እግዚአብሔር በሰውም በመላእክትም ይመሰገናል ይህም ማለት እግዚአብሔርን ከሌሎቹ ፍጡራን ከፍ የሚያደርግና የሚያከብር ቃል ወይም ድርጊት ነው (ሉቃ. 2፥13 ፤ ራእ. 7፥8-12)።
ምስጋናው - ምስግና (ትግ)

180. **ምስጢር**
ረቂቅ፣ ስውር፣ ድብቅ ፣ ሽሽግ ...።
ለተመረጡት የምስጢር መክፈቻ ተሰጣቸው። (ማር. 4፥11)
ያባት ስም **ፀወቀ** ቢል ይገጥማል።

181. **ምትኩ**
ቦታን ተክቶ የሚይዝ፣ ተረካቢው ...።
ያባት ስም **በለጠ** ቢል ይገጥማል።
ምትኬ - ምትኬነህ - ምትካቸው

182. **ምቹዓለም**
የተባባ፣ የተቃና፣ የሚመች ...።
ያባት ስም **ባዬልኝ** ቢል ይገጥማል።

183. **ምኒልክ**
የንግሥት ሳባና የንጉሥ ሰሎሞን ልጅ የኢትዮጵያ ንጉሥ ቀዳማዊ ምኒልክ ፤ በ 22 ዓመቱ ወደ አባቱ ሰሎሞን ዘንድ ሲኼድ **ምንትልክ** አናትህ ቢል **ምኒይልክ** ማለት ተያይዞ የመጣ ነው ይባላል።
እናቱ ያወጣችለት ግን የንጉሥ ልጅ በትል ኢብነ መለክ (ዕብ. ግእ) አለችው።

የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ ፤ የንጉሥ ኀይለ መለኮት ልጅ ዳግማዊ ምኒልክ በዚህ የመጠሪያ ስም ይታወቃሉ።
ምንትልክ - ምንይልክ - ኢብነ ሐኪ
ምን ተመልከት።

184. **ምናሴ** (ዕብ.)
ማሰረሻ ማለት ነው።
እግዚአብሔር መከራዬን ኹሉ የለብቴንም ቤት አስረሳኝ (ዘፍ. 41፥51) ማለት ነው።
የዮሴፍ ኹለት ልጆች የበኩር ልጁ ምናሴ ይባላል። ኹለተኛው **ኤፍሬም** ነው።

185. **ምንተሰኖት**
ለማድረግ ምንም የማይቸግረው።
አምላክ ምን ይቸግረዋል አንተን ሰጠኝ።
ያባት ስም **ሰጠኝ** ቢል ይገጥማል።

186. **ምንአለ** (ምናለ) - **ምናለሸዋ**
ሲሰማ ምን ተናገረ ?
ኹለተኛው ሲጠበቅ በቤት ምንአለ?።
ያባት ስም **አገሬ** ቢል ይገጥማል።
ምናሰቡ - ምናሉ - ምንይሉ

187. **ምንዳዬ - ምንዳ ኹን - ምንዳ**
ደመወዝ፣ የላብ፣ የስራ ዋጋ ማለት ነው።
ወንድሜ ሰለ ኾንክ በክንቱ ታገለግለኛለህን ምንዳህ ምንድነው ? ንገረኝ ?
(ዘፍ. 29፥15)። **ምንልኩ**
ምንአዳዬ - ምንዋጋው - ምንያህል

188. **ምንውዬለት**
ምንአድርጌለት፤ ውለታን ይመስክራል።
ለፈጣሪ ወይም ለሰው ሊኾን ይችላል።
ምንውዬ - ምንይዋብ - ምንይችል

189. **ምኞቴ - ምኞቱ**
የጓንኹለት፣ ያሰብኩት ተፈጸመ ...።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።

190. **ምዕራፍ**
የዓይኔ ማረፊያ ...።
ማረፊያ ቦታ ፤ የርቀት መለኪያ፤ የመጽሐፍ ክፍል (ሉቃ. 24፥13)።

191. **ምክሩ - ምክሬ - ምክረ**
መከረ ካለው የወጣ ነው ።
ይኽንን አድርግ፤ ያን አታድርግ። እንዲህ በል እንዲህ አትበል ማለት ነው ። ሐሳብን መጠየቅ (ዕዝ. 7፥14)።

ወ

መልካም ምክር ከሌለ በንድ ሕዝብ ይወ
ድቃል (ምሳ. 11፥14 ፤ ኢሳ. 3፥3)።
ያባት ስም **በዛብህ** ቢል ይገጥማል።
ምክረ ሥላሴ ከርስትና ስምን ተመልከቱ።

192. **ምግባሩ** (ግእ) - **ምግባር**
ሥራው ለማለት ነው።
አ! ብእሲ አብድ ከመ ሃይማኖት ዘእንበለ
ምግባር ምውት ይእቲ። ትርጉም፤ አንተ
ሰነፍ ሰው ሃይማኖት ያለ ምግባር (ሥራ)
የሞተች ነች። (ያዕ. 2፥20)
ያባት ስም **ታዬ** ቢል ይገጥማል።

193. **ምጽላል** (ግእ)
ጸለለ ካለው ግሰ ፤ ጥላ ኾነ፣ አለበሰ፣
ዳሰ፣ መጠለያ፣ ከለላ ማለት ነው።
ወመዋዕልየኒ ከመ ጽላሎት ሐለፈ።
ትርጉም፤ ዘመኔ እነደ ጥላ አለፈ።

194. **ሞላ**
ቁጥሩ፣ ስፍራው፣ ጅረቱ፣ ለማለት።
ተረፈ ፣ ተፈጸመ፣ ደረሰ ፣ ተጨረሰ፣
ግጥም አለ፣ በዛ፣ ከጉድለት ራቀ።
ያባት ስም **ፋንታዬ** ቢል ይገጥማል።
ሞላ ማሩ - ሞላልኝ

195. **ሞሲሳ** (ኦሮ) አሸናፊ ማለት ነው ።

196. **ሞገስ** (ግእ)
መወደድ፣ ወዳጅነት ፣ ባለሟልነት የተሰ
ጠው ። ወደደ፣ አፈቀረ ።
እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበር፤ ምሕረ
ትንም አበዛለት፥ በግዞት ቤቱ አለቃ ፊት
ሞገስን ሰጠው (ዘፍ. 34፥11፤ 39፥21)።
ያባት ስም **ሰጠኝ** ቢል ይገጥማል።

- ሠ -

197. **ሠምረ** (ግእ) - **ሠመረ**
የተወደደ መልካም የኾነ፤ ያማረ የተዋበ
ማለት ነው ። ለመሥዋዕትም ይነገራል
መሥዋዕተ አቤል ዘሠምረ ። ትርጉም፤
የአቤል መሥዋዕት ተወደደ (ዘፍ. 4፥4 ፤
ዘሌ. 1፥3)።
ሠምረ ድንግል ከርስትና ስምን ተመልከቱ።

198. **ሠረቀብርሃን** (ግእ) - **ሠረቀ**
ወጣ ፤ ተወለደ፣ ብቅ አለ ፣ ፀሐይ ፣
ጨረቃው ማለት ነው። እምከመ ሠረቀ
ፀሐይ የአትዉ። ትረጉም፤ ፀሓይ ስትወጣ
ይሰበሰባሉ (መዝ. 22፥6 ፤ 103፥62)።

199. **ሠራ**
ያባት ስም ብዙ ቢል ይገጥማል።
ሠራቸው - ሠራሕይወት - ሠራዓለም
ሠራወርቅ - ሠራው - ሠራኽድንቅ
ሠራልኝ- ሠራለህ ሲል ዛቻ እንዳይኾን።

200. **ሠርጹ** (ግእ)
ቡታያ፣ ለጋ፣ ዐዲስ ወጣ፣ በቀለ ማለት
ነው (ሕዝ. 16፥7) (**ዘሠናይ ሠርጹ**)
ለክርስትና ስም ቅጽል ይኾናል ። ሠርጸ
ድንግል። ትርጉም፤ የድንግል ቡታያ።
ያባት ስም ሠናይ ቢል ይገጥማል
ሠርጸ - ሠረጸፋና - ሠራጺ

201. **ሠናይ** (ግእ) - **ሠናያት**
አማረ፣ መልካም፣ በጎ ማለት ነው።
ሠናይት ምክረ ወግበበ ምሀረኒ። ትረጉም
መልካምን ምክርና ዕውቀትን አስተምረኝ
(መዝ. 118፥65) ።

202. **ሣህሉ** (ግእ)
ቸርነቱ ፣ ይቅር አለ ማለት ነው ።
ሣህሉ ለእግዚአብሔር መልእ ምድረ ።
ትረጉም ፤ የእግዚአብሔር ቸርነት ምድ
ርን ሞላች (መዝ. 32፥5) ። በሣህሉ ወበ
ምሕረቱ። ትርጉም፤ በምሕረቱና በቸርነቱ
(ሉቃ. 2፥78)።
ሣህለወርቅ - ሣህል - ሣህለ - ሣህሌ
ሣህለ ሥላሴ ከርስትና ስምን ተመልከቱ።

203. **ሣቁ**
ሠሐቡ ሣቀ ፈካ፣ ተደሰተ ማለት ነው።
(ዘፍ. 21፥6)
ያባት ስም በዛብህ ቢል ይገጥማል።

204. **ሥልጣን - ሥልጣኑ**
የመምራት፣ የመፍረድ፣ የመግዛት፣ ማንኛ
ውንም ነገር የማድረግ መብት ያለው።
ሰው ሥልጣንን ከእግዚአብሔር ይቀበላል
(ሮሜ. 13፥1)።
ያባት ስም **ከበደ** ቢል ይገጥማል።

205. **ሥራየ - ሥራዬ**
የኔ ሥራ ፣ ድካሜ ...።
ሥራ መሥራትን ያመለክታል።
ሠረየ ከሚለው ግሰ ደግሞ መድኃኒት
አደረገ የሚል ትርጉም አለው። ሥራይ
ተደረገ ሲል መርዝን ያመለክታል አይኾንም።

206. **ሥነ-ምግባር** (ግእ) - **ሥነ**
ሠነየ ከሚለው አማረ፣ ተዋበ ይወጣል።
ደም ግባት፣ መታበይ ቁም ነገር የለውም
መልካም ሥነ ምግባር (ሥራ) ይበልጣል።
(ሲራ. 9፥8 ፤ 11፥4 ፤ መዝ. 44፥49)።
ያባት ስም **አማረ** ቢል ይገጥማል።
ሥነሕይወት - ሥነ-ምግባሩ
ሥነ ማርያም ከርስትና ስም ተመልከቱ።

207. **ሥንቄ** (ግእ)
ለመንገድ የሚኾን ምግቤ ፣ መኖዬ ፣
ጎብስቱ ፣ ቆሎዬ፣ ዳቦ ቆሎዬ፣ በሶዬ፣
ድርቆሼ፣ ገንዘቤ።
ሰሚ ሥንቅ ነው የአመቤቱ ፥ ሰሚ ሥንቅ
ነው የአመቤቱ እንዳለ ዘማሪ ...።
ያባት ስም **አንተነህ** ቢል ይገጥማል።
ሥንቁ - ሥንቅነህ - ሥንቃቸው

208. **ሥዩም** (ግእ)
የተሾመ ሹም ማለት ነው ።
ወትሠይመኒ ውስተ ርእሰ ሕዝብ ። ትር
ጉም የሕዝብ ራስ አድርገህ ትሾመኛለህ
(መዝ. 17(18)፥43)።
ሥዩም በመባል የሚጠሩ ብዙ ኢትዮጵያ
ውያን አሉ። ከነዚህም ውስጥ ልዑል ራስ
ሥዩም መንገሻ የዐፄ ዮሐንስ አራተኛ
የልጅ ልጅ ናቸው። በማይጨው ዘምተው
ከጣሊያን ጋር በወርቡኝነት በጀግንነት ተዋ
ግተዋል (1879 - 1953 ዓ.ም)።
ሥዩማን - ሠየሙኽ

209. **ሥፍራዬ**
ቦታዬ ፣ መኖሪያን ያመለክታል ...።
ያባት ስም **ብዙዓለም** ቢል ይገጥማል።

210. **ሠፈር** (ጉራ)
አደባባይ ማለት ነው።

- ረ -

211. **ረቂቅ** - **ረቀቀ**
ሊደረስበት፣ ሊታይ፣ ሊዳሰስ የማይቻል።
ያባት ስም **ምስጢሩ** ቢል ይገጥማል።

212. **ረበበ** (ግእ) - **ረበቡ**
ዘረጋ፣ በዙሪያው በመውረድ ታየ ...።
ያባት ስም ጸጋ ቢል ይገጥማል።

213. **ረታ**
አሸነፈ ፣ ድል አደረገ ።
ያባት ስም በልሁ ቢል ይገጥማል።
ረታልኝ - ረታቸው

214. **ረዳሀኝ**
ተራዳህኝ፣ ደገፍከኝ...። ሸክምን፣ ሥራን፣ አገዝከኝ፣ ተቀበልከኝ፣ አሳረፍከኝ፣ አገለገልከኝ ይኹናል ... ።
ያባት ስም ተመስገን ቢል ይገጥማል።
ረዱ - ረዳ - ረዳኢ - ረዳኤ (ትግ)

215. **ረድኤት** (ግእ)
የእግዚአብሔር ርዳታ ተጨምሮበት የሚበረክት ማለት ነው። ለምሳሌ፦ በሰራፕታ ያለችው ባልቴት በርኃብ ዘመን ተቸግራ የእግዚአብሔር ሰው ኤልያስ በቤቷ ተገኝቶ በረከትና ረድኤት ምላላት።
(መጽ. ነገሥ. 17፥12)። **ረድኤቱ**

216. **ረጋ**
በአንድ ቦታ ተወሰነ ፤ ተሰበሰበ።
ያባት ስም ሲሳይ ቢል ይገጥማል።
ረጊኤት (ትግ) - **ረጋሸው- ረገበ - ረገቡ**

217. **ራሰ ወርቅ**
በራስ ላይ የሚደረግ ከወርቅ የተሠራ ሽልማት፤ ወይም ጌጥ፣ ጌራ ወርቅ ።
በዚህ ስም የሚጠሩ መምህር **ወልደ መስቀል** ከእናታቸው ከወይዘሮ አጫውቱኝ የተወለዱት የእንጦጦ መንበረ ፀሐይ አሰተዳዳሪ **መልአከ** ፀሐይ ራስወርቅ ነበሩ።

የትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤትን ያቋቁሙ ናቸው (1879 - 1954 ዓ.ም.)።

218. **ርስቱ (ርስቴ) ርስቱ**
አገሬ፣ ቦታዬ፣ ግዛቴ ነህ ...።
ያባት ስም **ደሴ** ፣ **ሙሉዓለም** ቢል ይገጥማል።

219. **ርካቡ** (አርካቡ)
መወጣጫው፤ ተረግጦ የሚወጣበት ...።
በፈረስና በበቅሎ ኮርቻ ግራና ቀኝ የሚንጠለጠል ለመወጣጫ፣ ሚዛን ለመጠበቂያ የሚያገለግል ።

220. **ርገጤ**
የሚረግጥልኝ ፤ ርገጥ ማለት ነው።
የጫፍ አርሻ ዘር እየተዘራ ይረገጣል።

221. **ርዳቸው**
ደግፋቸው፣ አለኝታ ኹናቸው ...።
ያባት ስም **አልፍነኽ** ቢል ይገጥማል።

222. **ሮባ** (ኦሮ)
ዝናብ ዘነበ ማለት ነው። **ሮቢ - ሮቤ**

223. **ሮሪሳ** (ኦሮ) ጀግና ማለት ነው።

- ሰ -

224. **ሰሊሆም** (ግሪ)
ለመጠቀሚያ የሚኾን ውሃ የተጠራቀመበት ቦታ ። ትረጉም የተላከ ማለት ነው (የሐ. 9፥6)።

225. **ሰላም**
እማን፣ ድኅና፣ ድኅንነት፣ ጤና፣ ዕረፍት፣ ጸጥታ፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ ምስጋና፣ በእን ድነት፣ በሰምምነት፣ በመተባበር መኖር።

ይኹን ሰላም በኃይልህ ። ትርጉም፤ በኃይልህ ሰላም ይኹን (መዝ. 121(122)፥6 ፤ ዮሐ. 20፥19)።
ሰላመ - ሰላማዊ - ሰላምይኹን - ሰላሙ

226. **ሰላማ**
የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ በመኾን የተሾሙ አባ ሰላማ በአምልኮ ባዕድ ከአ ግዚአብሔር ጋር ተጣልተው የነበሩትን የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተምረው ፣ አሳም ነው፣ አጥምቀው ከአግዚአብሔር ጋር ስላስታረቁ ሰላማ ተባሉ። **ፍሬምናጦስ - ከሣቴ ብርሃን** የሚለውን ተመልከት።

227. **ሰሎሞን** (ዕብ)
ሰላማዊ፤ የሰላም ሰው፣ ጠቢብ፣ ገባር ፣ ፈራጅ ማለት ነው ። የእሰራኤል ሦስተኛው ንጉሥ ነው። የንጉሥ ዳዊት ልጅ ጥበበኛ የነበር ፣ ዳኝነት የሚችል ነበር (2ኛ ሳሙ. 12፥24)።

228. **ሰሎ** (ዶር) ሰማይ ማለት ነው።

229. **ሰሙ**
ዐዲስ ነገር፣ ተረዱ፤ ተነገራቸው ...።
ያባት ስም ምሥራች ቢል ይገጥማል።
ሰሙንጉሥ - ሰሙወርቅ

230. **ሰማቸው**
ተረዳቸው ፣ አረጋገጠ ...።
ያባት ስም ይፍሩ ቢል ይገጥማል።
ሰማኢየሱስ - ሰማኸኝ - ሰማልኝ
ሰማአዜር - ሰማኝ - ሰማፋንታው
ሰማን (ጉራ)

231. **ሰማዕቱ**
ምስክር ኾነ፤ ለሃይማኖቱ ፤ ለዓላማው የተጋደለ።
ወእነግር ስምዐከ በቅድመ ነገሥት ። ትርጉም፤ በነገሥታት ፊት ምስክርህን እናገራለኹ (መዝ. 118(119)፥46 ፤ የሐዋ. 22፥20)።
ያባት ስም **አስጢፋኖስ** ቢል ይገጥማል።
ሰማዕተ - ሰማዕታት

232. **ሰርገው** (ግእ) **ሰርግው**
ተጌጠ ተንቆጠቆጠ ማለት ነው።
ሰርጉ ዓለም ሣራሪሃ ለምድር። ትረጉም ፤ የዓለም ጌጥ ምድርን የፈጠርክት።
ሰርጥ - ሰርጉዓለም - ሰርጉወርቅ
ሰርጋዊ - ሰርጌ

233. **ሰራዊቱ - ሰራዊት**
የመላእክት ጭፍሮች ያለቃ አለቃ ያላቸው (ኢሳ. 1፥24)። መረገላቲሁ ለፈርያን **ወሠራዊቶ** ወረወ ውስተ ባሕር። ትረጉም፤ የፈርያንን ሠረገሎች **ሰራዊቱን**ም በባሕር ጣላቸው (ዘጸ. 15፥4)።

234. **ሰርዲኖስ** (ግእ)
የደም ዓይነት ቀለም ያለው ቀይ የከበረ ድንጋይ (ዘጸ. 28፥17 ፤ ራእ. 4፥3)።

235. **ሰብሰቤ**
የተለያየን አገናኝ፣ አዋሐጅ ማለት ነው።
ሰበሰባቸው - ሰብሰብ

236. **ሰበነ-ወርቅ** (ግእ)
መጠምጠሚያ መግነዝ ማለት ነው።
ቅድስት ድንግል ማርያም ለቶማስ የሰጠችው ምልክት ።
ሰበኑማርያም - ሰበነ - ሰበን

237. **ሰብለ** (ግእ)
እሸት ዘረዘረ ደረሰ ጨረሰ ማለት ነው።
ያባት ስም እሸቱ ቢል ይገጥማል።
ሰብለገነት - ሰብሉ - ሰብለ-ማርያም

238. **ሰንበት (ሰንበተ)** (ዕብ)
ማረፍ፣ ማቆም ማለት ነው (ዘጸ. 20፥8)።
ሰንበቱ - ሰንበታ - ሰንበቶ (ኦሮ)

239. **ሰንደቅ** (ግእ)
ከብር ያለው ዓላማ የባንዲራ መስቀያው።
ሰንደቁ - ሰንደቄ

240. **ሰካወርቅ**
ወርቅ አጠለቀ ...።
ያባት ስም ማዕርጉ ቢል ይገጥማል።

241. **ሰወሃሪ** (ጉራ)
በክፉ ቀን ውለታ አድራጊ ማለት ነው።

242. **ሰውነት**
ሥጋና ነፍስ መኾን (ማቴ. 5፥29)።
ያባት ስም ሙኩሪያ ቢል ይገጥማል።
ሰውዓለም - ሰውአገኘ - ሰዋገኘሁ
ሰውሐረግ - ሰውመኾን - ሰውበለው
ሰውአለ - ሰውአለኝ

243. **ሰይፉ**
በልግድ ቤቱ ይባላል።
በኹለት ወገን ስለት ያለው። የእግዚአብሔርም ቃል ምሳሌ ነው (መዝ. 149፥6 ፤ ኤፌ. 6፥17 ፤ ዕብ. 4፥12)።
በዚህ ስም የሚታወቁ ኢትዮጵያውያን አንዱ ። የንጉሥ ኀይለ መስኮት ታናሽ ወንድም የዐፄ ምኒልክ አጎት ፤ አቤቶ ሰይፉ ሣህለ ሥላሴ ተጠርተውበታል።
ሰይፍ - ሰይፈ - ሰይፈ ሥላሴ (ክር)

244. **ሰገነት**
በቤት ጣራ ላይ የሚሠራ መናፈሻ ቦታ ወይም ማደሪያ ከፍል (2ኛ.ሳሙ. 11፥2 ፤ ዳን. 4፥29 ፤ 1ኛ ነገሥ. 17፥19)።

245. **ሰገደ**
በአክብሮት ማጐንበስ ማለት ነው።
(ኢሳ. 46፥2) **ሰገዱ - ሰገዴ - ሰጊድ**

246. **ሰጠኝ**
አበረከተልኝ ፣ በጇ አደረገልኝ ...።
ገንዘብ፣ የልፋት ዋጋ፣ ሀብት ...።
ያባት ስም በፈቃዱ ቢል ይገጥማል።
ሰጠ - ሰጠነው - ሰጠኸኝ - ሰጡ

247. **ሰጥአርገው (ሰጣርጋቸው)**
ዝም አሰኛቸው ፣ አረጋጋቸው ።
ያባት ስም ግርማኹን ቢል ይገጥማል።
ሰጥአለ - ሰጥአርጌ - ሰጥአርጋቸው

248. **ሰፈረወርቅ - ሰፈረ**
በሚዛን ፣ በአንቅብ ፣ በቁና ሞላ።
ያባት ስም ምንዳዬ ቢል ይገጥማል።

249. **ሱራፌል** (ዕብ.)
ስመ ነገድ ፤ በራእይ ለኢሳይያስ የታዩ በእግዚአብሔር ዙፋን አጠገብ የሚያገለግሉ ሰማያውያን ልዑላን ሊቃነ መላእክት (ኢሳ. 6፥1–7)።

250. **ሲራክ** (ዕብ.)
ጸሐፊ (መለመር) ማለት ነው ።
የምክር ቃል የያዘ መጽሐፍ በኢያሱ ሲራክ በራሱ አንደተጻፈ ገልጧል።
የጥበብ ኹሉ መገኛው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው ይላል (መጽ. ሲራ.1)።

251. **ሲሳይ** (ግእ)
ምግብ፣ ማንኛውንም በረከት ያመለክታል
ሲሳይ ከርሻና ከእንሰሳ ይገኛል ።
ዘይውህብ ሲሳየ ለኩሉ ዘሥጋ። ትርጉም፤ ለሥጋ ኹሉ ምግብን የሚሰጥ (መዝ. 134 (135)፥25፤ ምሳ. 13፥23) ሀበነ ዮም ሲሳየነ ዘለለ ዕለትነ። ጌታ ያስተማረው ጸሎት።
ሲሳየ - ሲሳዬነህ

252. **ሲሻው - ሲሻ - ሲሹ**
ሲፈልገው ፤ ሲመኘው ...።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

253. **ሲኝጋ**
ማለዳ ሲኾን፣ ጀምበር ስትወጣ፣ ወፎች ሲንጫጩ ...።
ያባት ስም ተገኘ ቢኾን ይገጥማል።

254. **ሲደልል - ደለለኝ**
ሲያታልል፣ ሲያምታታ፣ ሲያጭበረብር...።
ያባት ስም በዕውቀቱ ቢል ይገጥማል።

255. **ሳለአምላክ**
አምላክ ካለ ዘንድ፣ መመኪያ ካለ ...።
ያባት ስም ጌታነሽ ቢል ይገጥማል።
ሳለጌታ - ሳለኹ - ሳለአግዜር

256. **ሳላስብ - ሳልለው - ሳልልህ**
ድንገት፣ በቶሎ ፣ ሳልዘጋጅ ...።
ያባት ስም አገኘኹ ቢል ይገጥማል።

257. **ሳሙኤል** (ዕብ)
በእግዚአብሔር የተሰማ ወይም እግዚአብሔር ሰማኝ ማለት ነው። ፤ እናቱ ጡት በጣለ ጊዜ እንደ ስእለቷ ለእግዚአብሔር አቀረበችው፤ በቤተ መቅደስ አደገ። ነቢዩ ሳሙኤል ንጉሠ ሳዖልንና ንጉሥ ዳዊትን ቅብዐ መንግሥት ቀብቶ ያነገሠ የእግዚአብሔር ነቢይ ነው። (1ኛ ሳሙ. 2፥3 ፤ የሐ. 3፥24 ፤ 13፥20)

258. **ሳምንህ**
ባንተ ላይ እምነቴን ስጥልብህ ።
ያባት ስም ሰጠኸኝ ቢል ይገጥማል።

259. **ሳረይ** (ጉራ) ደሳለኝ ማለት ነው።

260. **ሳሳኹልህ - ሳሱ**
ሰለትኩ ፣ ተንገበገብኩ ...።
ያባት ስም ተስፋዬ ቢል ይገጥማል።

261. **ሳበ**
ዘርን፤ ከዚያም ከዚህም ወሰደ፤ ጎተተ።
ያባት ስም ዘርይኹን ቢል ይገጥማል።
ሳበልኝ - ሳበሸዋ - ሳበይፋት

262. **ሴም** (ዕብ)
የኖኅ ታላቅ ልጅ (ዘፍ.5፥32 ፤6፥10)
የሴም ወንድሞች ያፌትና ካም ናቸው።

263. **ሰለሺ**
ሰል ብዙዎች ...።
ያባት ስም ተሾመ ቢል ይገጥማል።
ሰለናት - ሰለወንድም - ሰለወገን

264. **ሰመኝ**
ሰፈልግ ፣ ሲሻኝ ...።
ያባት ስም ሰጠኝ ቢል ይገጥማል።
ሰመኝህ - ሰንመኝህ - ሰመኘው

265. **ሰሜ - ሰሜነህ**
ዝናዬ ፣ መጠሪያዬ ።
ያባት ስም ታደሰ ቢል ይገጥማል።
ሰመጥሩ - ሰሜወርቅ- ሰማቸው (2)

ወ

266. **ስምዖን** (ዕብ)
ስማ ፣ የጸሎት ምላሽ ማለት ነው።
በቅዱስ መጽሐፍ ዘጠኝ ሰዎች ተጠርተው በታል (ዘፍ. 29፥33) ። በዐዲስ ኪዳን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአርባ ቀን ወደ ቤተ መቅደስ ሲመሰድ ትንቢቱ ሲፈጸ ም ለማየት ይጠብቅ የነበረ **ስምዖን** አረ ጋዊ ነው (ሉቃ. 2፥25)።

267. **ስብሐት** (ግእ)
ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት መሰ ላም በምድር ሰምረቱ ለሰብ ። ትርጉም፤ በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና በምድ ርም ፍቅሩ ለሰው ኾነ (ሉቃ. 2፥14)።

እምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሎከ ስብ ሐተ። ትርጉም፤ ከሕፃናትና ከሚጠቡ ል ጆች አፍ ምስጋናን አዘጋጀኽ (መዝ. 8፥2)።
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።
ስቡሕ - ስባሔ - ስብሐቱ - ስብሐቲ
ስብሐት ለአብ = በዐጌ ኢያሱ አድያም ሰገድ ጊዜ መልክአ ሥላሴን የደረሱ ሊቅ በዚህ ስም ይታወቁ ነበር ።
ስብሐተ ጸድቃን ከርስትና ስምን ተመልከት።

268. **ስናፍቅኽ**
ስፈልግህ በጉጉት ፣ በተስፋ ስጠብቅህ አገኘኹኽ ማለት ነው።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።
ስናፍቅ - ስናፍቀው

269. **ስንታየሁ** (ስንትአየሁ)
ደስታ፣ መከራ፣ ድህነት፣ ሀብት ...።
ያባት ስም ደስታ ቢል ይገጥማል።
ስንቱ - ስንታዬ - ስንቴ

270. **ስንሻው - ስሻው**
ስንፈልገው ፣ ስንጠብቀው ።
ያባት ስም ታከለ ቢል ይገጥማል።

271. **ስኂን** (ስሐን)
የሚሸት የጭስ አንጨት። ሱባንጃ፣ ጥሩ ሽታ ያለው ነጭ ዕጣን።
ስኂነ ማርያም - ከርስትና ስም ተመልከቱ

272. **ስጦታ - ስጦታው**
ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ። የተሰጠ ...።
በበአልና በደስታ ጊዜ የሚሰጥ፤
እንዲሁ መሥዋዕትና ቍርባን ስጦታዎች ናቸው። በብዙ ይተረጉማል (ዘጸ. 28፥38)።

273. **ስፈልግ - ስፈልግኽ**
የጠፋን ፣ ተሰወረን ማግኘት።
ያባት ስም ዱባለ ቢል ይገጥማል።

274. **ሶምሶን** (ዕብ.)
እናቱ መከና ትኖር ነበረና በመልአክ ብሥራት ፀነሰችው፤ ልጁም ተወልዶ አስ ራኤላውያንን ከፍልስጥኤማውያን አዳነ። ከልጅነቱ ጀምሮ ናዝራዊ ጠጕሩ ያልተ ላጨ ነበር (መሳ. 13፥1)።

275. **ሶፎንያስ** (ዕብ.)
እግዚአብሔር የጠበቀው ፤ የሰወረው ማለት ነው ። ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚግልዱኝ፥ የተበተኑት ልጆቼ፥ ቁርባኔን ያመጡልኛል ብሎ ትንቢት ተናገረ (ትን. ሰፎ. 1፥4 ፤ 3፥10)።

- ሸ -

276. **ሸለለ**
ግጥም ገጠመ ፣ ፎከረ፣ አቅራራ ማነው የሚደፍረኝ አለ ። በዘመናዊ ደግሞ አማ ረበት፣ ተገነና ...። ማለት ነው።
ያባት ስም ጀግናው ቢል ይገጥማል።

277. **ሸለመው**
ሰጦታን ፣ ሀብትን ፣ ዋጋውን ለጠው።
ያባት ስም **አዱኛ** ቢል ይገጥማል።
ሸለመ - ሸለሙት - ሸለሙ
ሸልም - ሸልመው - ሸልማት

278. **ሸንኮሩ - ሸንኮር**
ጣፋጭነትን፣ መውደድን ያመለክታል።
ያባት ስም ጸደቀ ቢል ይገጥማል።

279. **ሸዊት** (ትግ)
ሠዊት (ግእ) ሰንዲ ማለት ነው።

280. **ሸዋ**
ማእከላዊው የኢትዮጵያ ግዛት ነው።
ሸዋረግ - ሸዋለማ - ሸዋለም
ሸዋለሩ - ሸዋሉል - ሸዋመብራት
ሸዋመና - ሸዋማረ - ሸዋማናለ
ሸዋረታ - ሸዋመብራት - ሸዋምኒል
ሸዋረዳ - ሸዋብርሃን - ሸዋታጠቅ
ሸዋነህ - ሸዋነጋ - ሸዋናፈቁ
ሸዋንግዛው - ሸዋንቅጣው - ሸዋንዳኝ
ሸዋንታጠቅ - ሸዋንገረመው
ሸዋንጣሰው - ሸዋዓለም - ሸዋአመነ
ሸዋዘመድ - ሸዋዘውዴ - ሸዋይልፋ
ሸዋይርጋ - ሸዋይስማ - ሸዋደም
ሸዋደግ - ሸዋፀጋ - ሸዋፈራ
ሸዋፈራሁ - ሸዋብዛ - ሸዋፍራው

281. **ሸጋ** (ኦሮ)
ያማረ መልክም ደበ የሚል ማለት ነው።
ያባት ስም ወንድሙ ቢል ይገጥማል።
ሸጋና - ሸጉ - ሸጉየ - ሸጋወርቅ
ሸጋው - ሸጌር - ሸጌና - ሸጌናው

282. **ሸፈነወርቅ - ሸፈና** (ኦሮ)
ደበቀ ፣ አላሳይ አለ ...።
ያባት ስም ተመሰገን ቢል ይገጥማል።

283. **ሹመት**
ማዕርግ፣ ደረጃ፣ ከፍ ማለት... ።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።
ሹምበዛ - ሹሙ - ሹሜ - ሹም
ሹምሸር - ሹመቱ - ሹምየ/ዬ/

284. **ሺመልስ** (ሽመልስ)
ጀግንነትን ያመለክታል፤ የጉበዝ ጉበዝ ማለት ነው ...።
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ ፊታውራሪ ሺመልስ ሀብቴ ናቸው። ሳገር ነጻነት ከተ ዋደቁት ጀግኖች አንዱ ዐርበኛ ነበሩ።
ሺፈራው - ሺመላሽ - ሺመርጊያ
ሺመክት - ሺመካች - ሺሰማ
ሺመብራት - ሺበላይ - ሺበሺ
ሺበቃው - ሺበዛ - ሺባባው - ሺብሩ
ሺፈራሁ - ሺኩራ - ሺወርቁ

285. **ሻማ** (ዶር) ግዛው ማለት ነው።

286. **ሻረው**
ከሥልጣንህ አውርደው፤ ኃይሉን ቀነስ።
ያስፈውን ዘመን በዐዲስ ለውጠው፣ ተካ።
ያባት ስም አባትነህ ቢል ይገጥማል።

287. **ሻወል - ሻውል (ሺ አውል)**
የሺህ ሰው አዛዥ ፤ ሺ ሰው በፈቃድህ አውል ማለት ነው።

288. **ሻጋ** (ዶር) መሐሪ ማለት ነው።

289. **ሸምብር** (ጉራ) ጀግና ማለት ነው።

290. **ሸሸጉ**
የማይታየው ድብቁ፣ ብርቁ፣ ማለት ነው።
ያባት ስም ታዬ ቢል ይገጥማል።

291. **ሸታኹን**
መዐዛህ የሚጣፍጥ...። ለኹሉም ትረፍ።
የኅብረት ምሳሌ ነው (መዝ. 132፥1 ፤ መኃ. መኃ. 4፥14)።
ያባት ስም ጥሩነሽ ቢል ይገጥማል።
ሸታወርቅ - ሸታዬ - ሸታዓለም
ሸታኹን - ሸታነሽ - ሸታው

292. **ሸንኩር** (ጉራ)
አስታራቂ ማለት ነው ። (በዐረብኛ አመሰ ግናለኹ ሲል ሽኩራን ይላል።)

293. **ሸኩር** (ጉራ)
ተመስገን ማለት ነው ። (ዐረብ አመሰግና ለኹ ሲል ሽኩራን ይላል)።

- ቀ -

294. **ቀለመወርቅ**
የወርቅ ቀለም፤ ከወርቅ የተዋሐደ ቀለም (2ኛ ቆሮ. 3፥3)።
ያባት ስም ረጋ ቢል ይገጥማል።
ቀለሜ - ቀለሙ - ቀለሜነህ
ቀለም - ቀለሞ

295. **ቀለቤ - ቀለብ**
ደመወዜ የልፋቴ ዋጋ፣ ምንዳዬ ገንዘቤ። ወንድሜ በለ ኾንክ በከንቱ ታገለግለኛለህን ምንዳህ ምንድነው? (ዘፍ. 29፥15)።
ሌላ አያሰፈልገኝም ደሞዜ እንተነህ ለማለት።

296. **ቀልቤሳ** (ኦሮ)
አስተዋለ ፤ አስተዋይ ማለት ነው።

297. **ቀነኒሳ** (ኦሮ) **ቀነኒ - ቀኑ**
ድሎተኛ፣ የተቃናለት፣ የተንቀባረረ፣ የተዝናና ማለት ነው። በዚህ ስም ከሚ ታወቁት አንዱ በሩጫ ውድድር ኢትዮጵያን ለዓለም ያሳወቀ ቀነኒሳ በቀለ ነው።

298. **ቀናው**
ጉዳዩ ተፈጸመለት፣ ኾነለት፣ ኾኖለታል ፣ ዕድል ገጠመው። **ቀናኝ - ቀናቸው**
ያባት ስም ደግሰው ቢል ይገጥማል።

299. **ቀኑበት**
ተመኙ፣ አሰቀናቸው፤ በችሎታው ...።
ያባት ስም ደግሰው ቢል ይገጥማል።

300. **ቀኜነሽ**
ረዳቴነህ፣ አጋዥ፣ አለኝታ ...።
ያባት ስም ድጋፌ ቢል ይገጥማል።

301. **ቀደመ - ቀዲሙ**
ከኹሉ በፊት አልፎ ኼደ፤ ቀዳሚ
ያባት ስም ትንቢት ቢል ይገጥማል።

302. **ቀደሰ** (ግእ)
ለየ፣ ባረከ፣ አነጻ፣ አከበረ፣ አመሰገነ ቅዱስ አደረገ፣ ከረኩሰት አነጻ፣ ቈረሰ፣ አወደሰ ማለት ነው።
ያባት ስም ዘካርያስ ቢል ይገጥማል።

303. **ቀዳሚጥበብ**
ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሀ እግዚአብሔር።
ትርጒም፤ የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው (መዝ. 110፥10)።
ያባት ስም ምግባሩ ቢል ይገጥማል

304. **ቀጀላ** (ኦሮ)
ቀጥተኛ እውነተኛ ኾኖ **የዘለቀ** ማለት ነው ።

305. **ቀጸላ** (ግእ) **ቀጸላወርቅ**
የራስ ልብስ ጌጥ ፣ በዙሪያው የወርቅ መርገፍ ያለበትና የሌለበት የሐር የፈትል ግምጃ፤ ሽልማት። ዕጨጌዎች፣ ካህናት፣ የሚከናነቡት ጥምጥም (ራእ. 9፥7 ፤ 12)።
ያባት ስም መንግሥቱ ቢል ይገጥማል።
ቀጸላ ማርያም ከርስትና ስምን ተመልከት።

306. **ቁምላቸው**
ጠበቃ ኾንላቸው ፤ ኦርላቸው ።
ያባት ስም ደጀኔ ቢል ይገጥማል ።
ቁምልኝ - ቁምለት - ቁምነገር

307. **ቂርቆስ** (ሕፃኑ ቂርቆስ)
የኢየሉጣ ልጅ ቅዱስ ገብርኤል ከንፍር ያዳናቸው ከርስቲያኖች። በአገር ልማድ **ጨርቆስ - ጨርቆሴ** ይባላል።

308. **ቃለ-ማዕነቅ** (ግእ)
ቃለ ማዕነቅ ተሰምዐ በምድርነ ። ትር ጒም፤ **የቁርዬ** ድምፅ በምድራችን ተሰማ (መኃ. ዘሰሎ. 2፥13)። የቅድስት ማርያም የቅኔ መምህር በዚህ ስም ይታወቁ ነበር።
ቃለ አብ፤ ቃለ እግዚእ ከርስትና ስምን ተመልከት።

309. **ቃል-ኪዳን**
የማይቀር፣ የማይበላ፣ የማይፈርሰ ወል ማለት ነው (ሕዝ. 31፥25)።
ነገሩን ለማጽናት ኹለት ሰዎች ወይም ከዚያ በላይ በእግዚአብሔር ስም ቃል ይገባሉ ። ዮናታንም እንደ ነፍሱ ስለወ ደደው ከዳዊት ጋር ቃል ኪዳን አደረገ (ሰሙ. ቀዳ. 18፥3)።
ያባት ስም ተክበ ቢል ይገጥማል።
ቃልሸት - ቃሌነሽ - ቃለ ጽድቅ

310. **ቃኘው - ቃኛቸው - ቃኜ**
ዙሪያውን ተመልከተው ። መለስ ቀለስ በል። በአደራነት እንዲጠበቅ የሚሰጥ...።
ያባት ስም ቢረዳኝ ቢል ይገጥማል።

311. **ቅርሴ - ቅርሴነህ - ቅርሳቸው**
ቀሪ ሀብቴ ፣ ለታሪክ የሚቆይ ...።
ያባት ስም ታደሰ ቢል ይገጥማል።

312. **ቅባቅዱስ – (ቅብዐቅዱስ)**
ለቅዱስ ነገር ሲመረጡ የሚቀቡት።
ዕድል ፣ ሀብተ ጸጋ ፣ ቅባቱ
ቅባት የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው።
(ዘጸ. 30፥30 ፤ 1ዮሐ. 2፥20)
ቅብዐ-ሥላሴ

313. **ቅዱስ**
ልዩ የተቀደሰ፣ የተባረከ፣ የነጻ፣ የበቃ፣ ቡሩክ፣ ንጹሕ፣ ምስጉን ማለት ነው።
የእግዚአብሔር የኾኑ ኹሉ ቅዱሳን ይባላሉ ። ቅዱስ ማለት ለእግዚአብሔር የተለየ ማለት ነው (2ዜና. 6፥41 ፤ መዝ. 15፥3)።

314. **ቆሪኾ** (ኦሮ) መድኃኒት ማለት ነው።

ወ

315. **ቆቱ** (ኦሮ) አራሽ ገበሬ ማለት ነው።

316. **ቈይልኝ**
ሰንብትልኝ፣ ኦርልኝ፣ በሕይወት ኦር።
ያባት ስም ሞሴ ቢል ይገጥማል።
ቈየ - ቈየኸው - ቈያቸው

- በ -

317. **በሀብቱ - በሀብቱ**
ወሀበ ሰጠ ከሚለው ግስ ይወጣል።
ያባት ስም ረታ ቢል ይገጥማል።

318. **በለሴ - በለሱ**
በበለሳ አገር ይሠራ የነበረ ወፍራም ኹኖ የተፈተለ ክርዳዳ ሽማ፣ የሚሞቅ ማለት ነው። የበለሰ ትርጉም፦ ዕድል ቀናው ማለት ነው።
አደን የሚያድኑ ሰዎች ወደ በለሳ በርሃ እየወረዱ በአደን ሀብት ሲገጥማቸው ከበለሰ በረሃ አገኘኹ ቀናኝ ለማለት በለሴ ይላሉ (የወሎ በማርኛ ነው)።

319. **በለሰ - በለሶ - በለሳን**
ጥሩ ሽቱ ያለው ቁጥቋጦ (ዘፍ.37፥25)።
ቅጠሉ በፋፊ ነጭ ደም ያለው አጭር ዛፍ (ዘፍ.3፥7 ፤ ዘዳግ. 8፥8 ማር.11፥13)።

320. **በለው - በላቸው**
ኹለት ትርጉም አለው፤ አንዱ ንገረው፤ ንገራቸው ሲኾን፤ ኹለተኛው ምታው ፤ ምታቸው ነው።

321. **በለጠ - በለጤ**
የተሻለ ኾነ ፣ ቀደመ ...።
ያባት ስም ምትኩ ቢል ይገጥማል።
በለጠው - በለጠወርቅ - በለጠህ

322. **በላይ**
በአናት፣ በማዶ፣ በተራራው ...።
የጣሊያንን ወረራ በመቃወም ከአገር ለማ ስወጣት ለነጻነት በጦርነት (በዐርበኝነት) የታገሉት ኢትዮጵያዊ ጀግና **በላይ ዘለቀ** በመባል ይታወቃሉ ።

323. **በላይነህ**
በማራቶን ሩጫ በሆላንድ የዓለምን ሪኮርድ አስመዝግቦ የአገሩን የኢትዮጵያን ከብር ያሳየው **በላይነህ ዴንሳሞ** በዚህ ስም ይታወቃል።
በላይነው - በላዩ - በላይሰው

324. **በልኹ**
ወጎይሉ ፣ እምቢ በማለቱ።
ያባት ስም ተሾመ ቢል ይገጥማል።

325. **በልዩ - በልዩኹን**
በሌላ መንገድ። ከምንም በማይገጥም...።
ያባት ስም ጥበቡ ቢል ይገጥማል።

326. **በሐርወርቅ**
ሐር ከትል የሚገኝ ድር ነው።
ዋጋው ውድ የኾነ፤ ለጌጥና ለክብር ልብስ ያገለግላል (ሕዝ. 16፥10፤ ራእ. 18፥12)።
ያባት ስም ጌጡ ቢል ይገጥማል።

327. **በሕይወት**
በቁም ባለሁ፤ በመኖር ...።
ያባት ስም **ከፈለኝ** ቢል ይገጥማል።

328. **በሥልጣኑ - በሥልጣን**
በግዛቱ ፤ ማንኛውንም ነገር የማድረግ መብት ያለው (ሮሜ. 13፥1)።
ያባት ስም ረታ ቢል ይገጥማል።

329. **በረከት**
እንዲበዛ፣ ሕይወት ጥሩ እንዲኾን ...።
እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ ባረካቸው፤ ብዙ ተባዙ የባሕርንም ውሃ ሙሏት።
(ዘፍ. 1፥22 ፤ ኤፌ. 123)።
እሰመ መምህረ ሕግ ይሁብ በረከተ።
ትርጉም፤ የሕግ መምህር በረከትን ይሰጣልና። (መዝ. 83(84)፥6)።
በረከተ ሥላሴ ክርስትና ስምን ተመልከቱ።

330. **በረደድ - በረደደ**
በረታ፣ ጠነከረ፣ ጠና ማለት ነው።

331. **በረጋ**
በቆመ ፣ በተወሰነ ።
ያባት ስም ትዛዙ ቢል ይገጥማል።

332. **በሪኹን (በር ይኹን)**
መግቢያ መውጫ፤ ማለፊያ ኹን ...።
ያባት ስም **ምሥራቅ** ቢል ይገጥማል።
በሪኹኔ - በርነኽ - በሩ

333. **በሬሳ** (ኦሮ) ጸሐፊ ማለት ነው።

334. **በርሲሳ** (ኦሮ) አስተማሪ ማለት ነው።

335. **በርቶሌሜዎስ** (ሮማ)
ተክል የማጠጣት ሥራ ያለው ልጅ (ዕንቁ) ማለት ነው ። የናትናኤል ኹለተኛው ስሙ ነው ፤ ከዐሥራ ኹለቱ ሐዋርያት አንዱ ነው (ማቴ. 10፥3)።

336. **በርናባስ**
የመጽናናት፣ የደስታ ልጅ ማለት ነው ።
በዐዲስ ኪዳን ከቅዱሰ ጳውሎስ ጋር ለወንጌል ሰብከት ዐብሮ ይጓዝ ነበር
(የሐ ሥራ 4፥36)።

337. **በርሄ** (ትግ) በራ ማለት ነው።

338. **በሰልፍ - በሰልፉ - በሰልፈ**
በተራው፤ በደረጃው፣ መሰመር ጠብቆ...።
ያባት ስም ታየ ቢል ይገጥማል።

339. **በሱፈቃድ - በሱአምላክ**
ፈቀደ ከሚለው ግስ ፤ ወደደ ጎበኘ ፤ ፈቃደኛ ኾነ ማለት ነው።
ያባት ስም ያዛቸው ቢል ይገጥማል።

340. **በሰፋት**
ጠቅልሎኽ ፤ አስፋፍተህ ።
ያባት ስም ግዛው ቢል ይገጥማል።

341. **በሺወርቅ**
ቁጥሩ ክፍ ባለ ወርቅ።
ያባት ስም **ከፈለኝ** ቢል ይገጥማል።

342. **በሻህ - በሻህውረድ - ቢሻህ**
በፈለገህ ጊዜ ...።
የዐፄ ምኒልክ አባት መጠሪያ ስማቸው **በሻህ ውረድ** ሲኾን የጥምቀት ስማቸውና ሰመ መንግሥታቸው ንኁሥ ኃይለ መለኮት ነው (1840 -1848 ዓ.ም.)።

343. **በቀለ**
ተገኘ፣ ወጣ፣ እንደ ዘንባባ አማረ ...።
ታዋቂው ጀግና ደጃዝማች **በቀለ** ወያ በጣሊያን ጦርነት በዐርበኝነት የተዋደቁ ኢትዮጵያዊ ጀግና በቀለ ይባሉ ነበር ።

344. **በቃሉ**
ሰው ከቃሉ የተነሳ ይከብራል ፤ ይፈረድበታል ። እግዚአብሔር ዓለምን በቃሉ ፈጠረ (ዘፍ. 1፥3 ማቴ. 12፥36)።
ያባት ስም እሙን፣ **አዘዘ** ቢል ይገጥማል።

345. **በቃህቢል (በቃቢል)**
ጨረስክ፤ ፈጸምክ፣ አንዳይቀጥል ቢል...።
ያባት ስም ዳግማዊ ቢል ይገጥማል።

346. **በቃና**
የናትናኤል አገር ፤ ጌታችን ኢየሱስ ከር ስቶስ በሰርግ ተገኝቶ የመጀመሪያ ተአም ሩን ያደረገበት ቦታ (ዮሐ. 21፥2 ፤ 2፥1)።
ያባት ስም ዘገሊላ ቢል ይገጥማል።

347. **በቅባቱ**
ቅባት የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው።
(ዘጸ. 30፥30 ፤ 1ዮሐ. 2፥20) ።
ያባት ስም አርጋው ቢል ይገጥማል።

348. **በተስፋ**
በተስፋ ደስ ይበላችሁ፤ በመከራ ታገሡ።
(ሮሜ. 12፥12 ፤ 15፥13 ፤ ዕብ. 11)
ያባት ስም ደሳለኝ ቢል ይገጥማል።

349. **በትረ**
በእጅ የሚያዝ መቀዋሚያ ።
ብዙ ጊዜ የሥልጣን ምልክት ነው። ከያዕ ቆብ ኮከብ ይወጣል ከእስራኤልም በትር ይነሳል (ዘኍ. 24፥17 ፤ ኢሳ. 11፥1 ፤ 9፥4)። **በትረወርቅ - በትሩ**
ያባት ስም መንግሥቱ ቢል ይገጥማል።
በትረ-ሙሴ - በትረሃይማኖት
በትረ ማርያም ከርስትና ስም ተመልክቱ።

350. **በትዛዙ - (በትዕዛዙ)**
በአዋጁ፤ በመመሪያው ...።
ያባት ስም ፍጹም ቢል ይገጥማል።

351. **በትግሉ - በትግል**
ላለመውደቅ በመፍጨርጨሩ ።
ያባት ስም አሸናፊ ቢል ይገጥማል።

352. **በጎይሉ - በጎይሌ**
በጉልበቱ፣ በችሎታው ...።
ያባት ስም ተፈራ ቢል ይገጥማል ።

353. **በነበሩ - በነበር**
ይህ ኹሉ ቢኾን ቢኖሩ፣ ባዩህ መልካም ነበር ለማለት ነው።
ያባት ስም ምልክር ቢል ይገጥማል።

354. **በንቲ (ኦሮ) በንቱ - በንቱ**
የቤት እናት ፣ ጣሪያ ማለት ነው።
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ በደርግ ዘመን ኢትዮጵያን የመሩ ጀነራል ተፈሪ በንቲ ይታወቁበታል ።

355. **በአምላክ (ባምላክ) - በአምላኩ**
ትእዛዝ፣ ፈቃድ፣ ስጦታ፣ ዳኝነት።
ያባት ስም ፈቃዱ ቢል ይገጥማል።

356. **በአካል (ባካል)**
በፊትለፊት ተገኝቶ አየነው ...።
ያባት ስም ይርዳው ቢል ይገጥማል።

357. **በእምነት (በምነት)**
ሰው በአምነት ሲኖር በእግዚአብሔር ቃል ይመራል። በተስፋ ይኖራል (ሮሜ. 4፥16 ፤ ዕብ. 11)።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

358. **በእውነት - በውነቱ**
በሀቅ፣ ያለ ሐሰት ...።
ያባት ስም ፈረደ ቢል ይገጥማል።

359. **በእደ (ግእ)**
እድ ማለት እጅ ማለት ነው።
ፊኑ እዴከ እምአርያም። ትርጉም፤ እጅህን ከአርያም ላክ (መዝ. 143(144)፥7)።

ያባት ስም መልአኩ ቢል ይገጥማል
በእደብርሃን - በእደወርቅ (ስም)
በእደ ማርያም ከርስትና ስምን ተመልከቱ።

360. **በከመይቤ** (ግእ)
እሱ እንዳለ፣ እንደ ተናገረ ማለት ነው።
ያባት ስም ዳዊት ቢል ይገጥማል።

361. **በኩረ** (ግእ)
አንደኛ ልጅ፣ የመጀመሪያ ማለት ነው።
(ዘፍ. 25፥29)። አልጋ ወራሽ የመጀመሪያ ልጅም ይኾናል።
ወለነሂ በኩርየ አሬስዮ። ትርጉም፤ እኔ ደግሞ በኩሬ አደርገዋለኹ (መዝ. 88(89) ፥27)። **በኩረ ሐዋርያት - በኩረ ጽዮን**
በኩረ ድንግል ከርስትና ስምን ተመልከቱ።

362. **በካፋ** (ግእ)
ትርጕሙ ቆራጥ ከወሰነ ወደኋላ የማ ይል ፤ ብርቱ ሰው ማለት ነው።
ዐፄ በካፋ የዐፄ ኢያሱ (አድያም ሰገድ) ልጅ ናቸው ። አያታቸው ዐፄ ዮሐንስ (ጸድቁ) ቅድመ አያታቸው ዐፄ ፋሲል ናቸው። በዘመናቸው ጎንደር ሩፋኤልን፣ ደፈጫ ኪዳነ ምሕረትን ተክለዋል ። የጽ ሕፈት ሞዒያት ተጠብቀው እንዲጸፉ ጥብቅ መመሪያ አውጥተው ነበር።

363. **በዐሉ — በዐለማርያም**
የከርሰቲያን በዐላት አሉ።
ለምሳሌ፦ ጥምቀት፣ ትንሣኤ፣ ዕርገት...
መጽአ ላዕሌየ መንፈስ በዕለተ እሑድ።
እሑድ ቀን መንፈስ በእኔ ላይ መጣ ።
በጌታ ቀን በመንፈስ ነበርሁ (ራእ. 1፥10)
በእምርት ዕለት በዓልነ ። ትርጉም፤ በከ ፍተኛ በዐላችን ቀን (መዝ. 80(81)፥3)።

በመጽሐፍ ደራሲነታቸው ታዋቂ የኾኑት ኢትዮጵያዊ በዐሉ ግርማ ተጠርተውበታል ስድስት መጽሐፍት ጽፈዋል ።

364. **በዓለም (ባለም)**
ሐዋርያት ወንጌልን በዓለም እንዲሰብኩ ተላኩ (ማር. 16፥15)።
ያባት ስም ስንታየሁ ቢል ይገጥማል።

365. **በዓይኔ (ባይኔ)**
በዓይኔ አየሁ አረጋገጥኩ ...።
ያባት ስም እንግዳየሁ ቢል ይገጥማል።

366. **በዕድሉ (በድሉ)**
በተሰጠው ስጦታ ፤ በተቸረው ።
ያባት ስም ዘለቀ ቢል ይገጥማል።

367. **በዕውቀት - በዕውቀቱ**
ዕውቀት ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ ነው (1ቆሮ. 8፥1 ፤ 12፥8)።
ያባት ስም ረታ ቢል ይገጥማል።

368. **በዛብኅ**
ያባትህ ዘር፤ ባንተ በዛ ለማለት ... ነው።
በዚህ ስም ዐርበኛ ከነበሩት አንዱ ደጃዝ ማች በዛብኅ ስለሺ ተጠርተውበታል (1894 - 1953 ዓ.ም.)።
በዛጉልቱ - በዛባቸው - በዛወርቅ
በዛረድኤት - በዛወርቄ - በዙ - በዜ

369. **በዝና - በዝናው**
በገናናነት ፤ ገኖ የተሰማ ።
ያባት ስም ግዛው ቢል ይገጥማል።

370. **በየነ - በየነልህ**
ወሰነ፣ ተቸ፣ ዐወቀ፣ ፍርድ ሰጠ ...።
በዚህ ስም በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ታዋቂ የነበሩት አገረ ገዢ የዐፄ ኀይለ

ሥላሴ አማች የሮማን ወርቅ ባለቤት
ደጃዝማች በየነ መርዕድ ይባሉ ነበር።
በየነህ - በያን (ጉራ)- በያኔ - በየኑ

371. **በዳሳ** (አሮ) ሽልማት ማለት ነው።

372. **በጊዜው**
ቢወቅቱ፣ በዘመኑ፣ በሰዓቱ ...።
ለሁሉም ጊዜ አለው ፤ ለመወለድ፣ ለመ
ሞት፣ ለመትከል፣ ለመንቀል (መክ. 3፤2)።
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።

373. **በግርማ - በግርማው**
ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በግርማ መለኮት
ይመጣል (ማቴ. 25፤31)።
ያባት ስም ይታየው ቢል ይገጥማል።

374. **በጎሰው**
ጥሩ፣ ደግ ፣ መልካም ሰው ...።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ናትናኤልን ወደ
እርሱ ሲመጣ አይቶ ስለ እርሱ ተንብል
የሌለበት የእስራኤል ሰው እነሆ አለ ።
(ዮሐ. 1፤48)
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

375. **በጸሎቴ - በጸሎት**
በልመናዬ፣ በስለቴ፣ በመማጸኔ ...።
እግዚአብሔር የልጆቹን ጸሎት በደስታ
ይሰማል። ጸሎት ብዙ ኀይል አለው
(1ጴጥ. 3፤12 ፤ ያዕ. 5፤17)።
ያባት ስም ሰጠኝ ቢል ይገጥማል።

376. **በጽሐ** (ግእ)
ቀረበ፣ ደረሰ፣ መጣ፣ ተዳረሰ ።
ወአስከ አጽናፈ ዓለም በጽሐ ነቢየሙ።
ትርጉም፤ ቃላቸው አስከ ዓለም ዳርቻ
ደረሰ (መዝ. 18(19)፤3)።
ያባት ስም ሠናይ ቢል ይገጥማል።

377. **በጸጋው**
በቸርነቱ ፣ በምሕረቱ ፣ በበጎነቱ
እግዚአብሔር በጸጋው ደህንነትን ፈጽ
ሟል (ኤፌ. 2፤6 ፤ 2ጢሞ. 1፤9)።
ያባት ስም አያልቅበት ቢል ይገጥማል።

378. **በፈቃዱ - በፍቃዱ**
በአሺባይነቱ፣ በችሮታው፣ በቸርነቱ ...።
ያባት ስም በየነ ቢል ይገጥማል ።

379. **በፍርዱ**
ነገሩን በማስተዋል አውነትን ከሐሰት መለ
የት (ዘዳ. 25፤1 ፤ ምሳ. 1፤3 ፤ 2፤8)።
ያባት ስም መሠረት ቢል ይገጥማል።
በፍርዴ - በፍርዳቸው

380. **በፍቅሩ**
ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል ? መከራ
ወይስ ጭንቀት ፣ ወይስ ስደት ፣ ወይስ
ራብ ፣ ወይስ ራቁትነት፣ ወይስ ፍርሃት፣
ወይስ ሰይፍ (ሮሜ. 8፤31)።
ያባት ስም አሸናፊ ቢል ይገጥማል።

381. **በዳኔ** (አሮ)
መምነሽነሽ የምሥራች ተደሰትን ማለት
ነው።

382. **በዳዳ** (አሮ) ሀብታሙ ማለት ነው።

383. **በዲ** (አሮ)
ያደረ መሬት ማለት ነው።

384. **በልቻ** (አሮ) - **በልቱ**
አስተዳዳሪ ፣ አሳዳሪ ማለት ነው።

385. **በሩክ - በሩኬ** (ግእ)
የተባረከ ፣ የተመሰገነ ፤ ክቡር
ወይኩን በሩክ ስመ አእግዚአብሔር።
ትርጉም፤ የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ
ይኹን (መዝ. 112፤1 ሲራ 45 ፤ ሉቃ. 1፤
42 ፤ ዘጸ.29፤21)።

386. **በካ** (ዶር) በለው ማለት ነው።

387. **በዙታ** (ጉራ)
ነገር ወዋቂ ኹሉን ያጠቃለለ ማለት ነው፤

388. **ቢልልኝ – ቢለው**
ቢፈቅድልኝ፤ እግዚአብሔር ቢያድለኝ...።
ያባት ስም ከብረት ቢል ይገጥማል ።

389. **ቢምረው - ቢምሩ**
ይቅር ቢለው ፤ ቢታረቀው ...።
ያባት ስም መልአኩ፣ ዳኛቸው ቢል ይገ
ጥማል ።

390. **ቢሠውር**
ከክፉ ቀን፣ ከመቅሰፍት ዘመን ...።
ከመከራ ፤ ከችግር ።
ያባት ስም ከብሩ ቢል ይገጥማል።

391. **ቢረሳው**
ቢተወው፣ ችላ ቢለው ...።
ከመቆየት ብዛት ባያስታውሰው ።
ያባት ስም ግሩም ቢል ይገጥማል።

392. **ቢረዳኝ – ቢረዳው**
በችግሬ ፣ በመከራዬ ቢደግፈኝ ...።
ያባት ስም መልአኩ ቢል ይገጥማል።

393. **ቢረጋ**
በአንድ ቦታ ቢቀመጥ፣ ቢወሰን ...።
ያባት ስም ወሰኑ ቢል ይገጥማል።

394. **ቢራራ**
ቢያዝን ፣ ይቅር ቢል ...።
ያባት ስም ወንድሙ ቢል ይገጥማል።

395. **ቢራቱ (አሮ) ቢራ - ብራ**
ነጋ፣ ከረምት ዐለፈ ቢጋ መጣ (መፀው
ደረሰ) ዐማርኛ ዛሬ ብራ ኾነ ይባላል ።
ቀኑ ፀሐይ ኾነ ማለት ነው።

396. **ቢሰማኝ**
ልመናዬን፣ ጸሎቴን፣ ጥያቄዬን ...።
ያባት ስም ቁምነገር ቢል ይገጥማል።

397. **ቢሰንብት**
ቢኖር፤ የተወሰነ ጊዜ ቢቆይ ...።
ያባት ስም ምግባሩ ቢል ይገጥማል።

398. **ቢሰጠኝ**
ሀብት፣ ጸጋ፣ ክብር ...።
ያባት ስም ሲሳይ ቢል ይገጥማል።

399. **ቢሻው**
ቢፈልገው፣ ቢፈቅደው ማለት ነው።

400. **ቢቂላ (አሮ) በቀላ**
ጸደቀ ማለት ነው። የአበበ ቢቂላ አባት
በዚህ ስም ይታወቃሉ።

401. **ቢተው - ቢተውልኝ**
ይቅር ቢል ፣ ባይነካ ፣
ያባት ስም ፋንታ ቢል ይገጥማል።

402. **ቢነጋ**
ፀሓይ ስትወጣ ፣ ወፎች ሲንጫጩ።
ያባት ስም ታደለ ቢል ይገጥማል።
ቢነጋፀሓይ

ወ

403. **ቢክሰኝ**
ቢተካልኝ ፤ ዋጋዬን ቢሰጠኝ ።
ያባት ስም ዋጋውን ቢል ይገጥማል።

404. **ቢኾነኝ - ቢኾን**
ነገሩ ጉሉ ቢፈጸም ጥሩ ነበር።
ያባት ስም ልየው ቢል ይገጥማል።

405. **ቢያዝን**
በነገሩ ባይደሰት ፣ ቅር ቢለው።
ያባት ስም ሰጠኝ ቢል ይገጥማል።
ቢያዝንልኝ - ቢያልፈው - ቢያባልፍ

406. **ቢያድግልኝ**
ጤንነቱ ተሟልቶ፣ በተስፋ ።
ያባት ስም ስመኝ ቢል ይገጥማል።

407. **ባለሟል (በዓለ ሙዓል)**
ብልኅ ዐዋቂ ባለ ብዙ ዕውቀት ፤ ታማኝ
የቤት ባለ አደራ ፤ ባለሙያ።
ያባት ስም ተፈራ ቢል ይገጥማል።

408. **ባለወርቅ**
የወርቅ ባለቤት ...።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

409. **ባልቻ** (ጉራ. ኦሮ)
በልቼ ፤ የስሙ ትርጕሙ ተገን ደጋፊ
መለት ነው።
በዐፄ ምኒልክ፤ በንግሥት ነገሥታት ዘው
ዲቱ፣ በቀ. ኃይለ ሥላሴ ዘመን የኖሩ የዐ
ድዋ ጦርነት ላይ የተሰለፉ ደጃዝማች
ባልቻ አባ ነፍሶ ተጠርተውበታል ። አባ
ነፍሶ የፈረሰ ስማቸው ነው ። ያባታቸው
ስም ሣር ነው። ስሊየሩሳሌም ገዳም ቤት
ገዝተው ሰተዋል። በስማቸው መታሰቢያ
ባልቻ ሆስፒታል ተሰይሞላቸዋል።

410. **ባሎ** (ጉራ) መክታዬ ማለት ነው።

411. **ባሕሩ**
የተንጣለለ ፣ ከውቅያኖስ መለስ ያለ
ባሕርኒ ርዕየት ወጉየት። ትርጕም፤ ባሕር
አየች ሸሸችም (መዝ. 13(14)፥3)።
ያባት ስም ሞላ ቢል ይገጥማል።
ባሕረጥበብ - ባሕሩን - ባሕርነኽ

412. **ባሕርይ** (ግእ)
ጠባይን ፤ ልማድን ያመለክታል ። ጠባዩ
የማያለቃቅስ ከኾነ ባሕርየሠጋ ይባላል።
(ሮሜ. 1፥20 ፤ 2፥14 ፤ 2ጴጥ. 124)።

413. **ባሕታ** (ትግ) ደስታ ማለት ነው።

414. **ባራኪ** (ግእ) **ባረኩ - ባርካ**
የሚባርክ ማለት ነው ።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

415. **ባሮክ (ዕብ.)**
ቡሩክ ማለት ነው ። የኔሪያ ልጅ የነቢዩ
የኤርምያስ ታማኝ ወዳጅ እና ጸሐፊ።
(ኤር. 32፥12 ፤ 36፥1- 32)። አቤሜሌክ
እና ባሮክ የኤርምያስ ተማሪዎች ነበሩ
(ተረፈ ኤር. 8፥8)።

416. **ባሳዝነው**
ቢራራልኝ ...። አግዜር ባሳዝነው ሰጠኝ፣
ክሙኝ፣ ታረቀኝ፣ ተክፐ ቢል ይገጥማል።

417. **ባስልዮስ (ግሪ)**
ንጉሥ ማለት ነው። በ4ኛው መቶ ክፍለ
ዘመን የቤተ ክርስቲያን አባት መጠሪያ
ስም ነበር ፤ ባስልዮስ ዘቂሳርያ ።
በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ፓትርያርክ
የተጠሩበት ስም ባስልዮስ ነው።

418. **ባንተይዳኝ**
ግራዝማች ዕንቈ ሥላሴ ባንተይዳኝ ይባሉ
የነበሩ ከልጆቻቸው ጭምር በጣሊያን
ጦርነት ለኢትዮጵያ ደኅንነት ትልቅ መሥ
ዋዕት የከፈሉ አባታቸው ባንትይዳኝ
ይባሉ ነበር ።
ባንተዓለም - ባንተይኹን - ባንተጊዜ
ባንተአምላክ - ባንተአየሁ- ባንተይርጉ
ባንተይርጋ - ባንትይዋሉ - ባንትይገኝ

419. **ባንጃው (በአንጃው) - ባንጃ**
በወገን፣ አንድ ወገን ፣ በሚናው ማለት
ነው።

420. **ባካፋ**
ዝናብ በዘነበ ካፊያ ባካፋ ነው።

421. **ባዘዘው — ባዘዘ**
አድርግ ብሎ በነገረው ።
ያባት ስም ተጌጠ ቢል ይገጥማል።

422. **ባዜን (ባዚን)**
ለዐሥራ ሰባት ዓመት በኢትዮጵያ የነገሠ
ንጉሥ ነው። ይህ ንጉሥ በነገሠ በስምንተ
ኛው ዓመት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
በቤተልሔም ተወለደ (ሉቃ. 2፥10)።

423. **ባየኽ**
ዘመዶችህ ዓለሙ ባዩ ።
ያባት ስም ከተማ ቢል ይገጥማል።
ባየንኽ - ባየልኝ - ባየው - ባዬ - ባዩ
ባየዓለም - ባዩኽ - ባዩልኝ - ባይኽ

424. **ባይለየኝ**
የሚረዳኝ ከጠገቤ ባይርቅብኝ ...።
ያባት ስም መልኩ ቢል ይገጥማል።

425. **ባይሣ** (ኦሮ) – **ባይሜ**
ብዙ በረከት ማለት ነው።

426. **ባይሣሣኹ**
ልጅ ባይ ሣሣሁኝ ለማለት ነው።

427. **ባይነሣኝ**
ሰጥቶ፣ አሳይቶ ባይወሰድብኝ ...።
ያባት ስም ምሕረት ቢል ይገጥማል።

428. **ባይከዳኝ**
በዐፄ ምኒልክ ጊዜ ወደ ውጭ አገር
ኼደው ተምረው አገራቸውን ያገለግሉ
የነበሩ ኀያድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ
ያባታቸው ስም ባይከዳኝ ይባሉ ነበር።

429. **ባደገ - ባደገልኝ - ባደጉ**
ፋፍቶ ፣ ቁመት እና ዕድሜ ጨምሮ።
ያባት ስም ስመታው ቢል ይገጥማል።

430. **ባጫ** (ኦሮ)
የነጠላ ሀብታም ማለት ነው።

431. **ቤኩማ** (ኦሮ) - **ቤኩምሳ**
ሰውቀቱ ማለት ነው ።

432. **ቤዛ**
ምትክ፣ ካሳ፣ ዐለፊ ፣ ዋስ።
የተወደደን ፣ የተያዘን ነገር ለመመለስ
የሚከፈል ካሳ ፣ ለውጥ፣ ዋጋ ...።
(ምሳ. 13፥8 ፤ ዘሌዋ. 25፥24 ፤ ማር. 10፥
45)።
ያባት ስም መድኀኒት ቢል ይገጥማል።
ቤዛለም (ቤዛዓለም) - ቤዛነኽ
ቤዛኩሉ - ቤዛወርቅ

ወ

433. **ብሌን**
በዓይን መክከል ያለ ጥቍሩ በጣም ጥን ቃቄ የሚደረግለት የዓይን ክፍል ነው።
በምሳሌነት እግዚአብሔር ለሚጠብቃቸው ኹሉ ይነገራል (ዘዳ. 32፥10 ፤ መዝ. 16፥ 8 ፤ ምሳ. 7፥2 ፤ ዘካ. 2፥8)።

434. **ብልጫ – ብልጫዬ**
የተሻለ ፣ የሚመረጥ ፣ ከፍ ያለ ...።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

435. **ብሥራት** (ግእ)
በሠረ ፤ አብሠረ ካለው ግሰ የወጣ ።
የምሥራች አለ ማለት ነው (ሉቃ. 1፥31)።
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።
ብሥራቴ - ብሥራተ
ብሥራተ ገብርኤል ከርሰትና

436. **ብሩ**
ገንዘብ ፣ ሀብት (ዘፍ. 23፥16)።
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ ራስ ብሩ **ወልደ ገብርኤል** ናቸው። በማጨው ጦር ላይ ከጣሊያን ጋር የገጠሙ ዐርበኛ ናቸው (1882-1937 ዓ.ም.)።
ብርዛፌ - ብርሸት - ብሩር
ብርይከሱ - ብርጣሉ

437. **ብሩህ**
በርቶ፣ ደምቆ፣ የሚታይ ።
ደግሞም ዐዋቂ ነው ለማለት ብሩህ አእምሮ አለው ይባላል።
ያባት ስም ተሰፋዬ ቢል ይገጥማል።

438. **ብርሃኑ**
እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ ፤ በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም። (ማቴ. 5፥14)

በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ ደራሲ ብር ሃኑ ዘሪኹን ናቸው ። አሥራ አንድ መጽ ሐፍ ጽፈዋል (1924 - 1979 ዓ.ም.)።
ብርሃነአለም - ብርሃኔ - ብርሃነ
ብርሃነሕይወት - ብርሃናት - ብርሃን
ብርሃነፀሐይ
ብርሃነ ሥላሴ ከርሰትና ስም ።

439. **ብርቃገኘኹ**
መጀመሪያ የወለደውን ልጅ ...።
ዐዲስ ነገር፣ ታይቶ የማይታወቅ።
ያባት ስም ወዲስ ቢል ይገጥማል።
ብርቅይኹን - ብርቃየሁ
ብርቅዓለም - ብርቅነህ - ብርቁ

440. **ብንያም** (ዕብ)
ቢን ማለት ልጅ ማለት ሲኾን የም ደግም የቀኝ እጅ ማለት ነው።
12ኛው የያዕቆብ ልጅ ነው (ዘፍ.35)።

441. **ብዙአየኹ**
ደስታ ፣ መክራ ፣ ዓለም ... ።
ያባት ስም ቸርነት ቢል ይገጥማል።
ብዙሰው - ብዙወርቅ - ብዙ
ብዙአየን - ብዙዓይኔ
ብዙነሽ - ብዙዓለም

442. **ብጡል** (ግእ)
ቡጠለ ከሚለው ግስ የወጣ ነው።
ጠፋ፣ ፈረሰ፣ ፈታ ማለት ነው።

443. **ብፅዐት** (ግእ)
በዕዐ ከሚለው ግስ ወሰነ ተባለ ይላል።
የተባረከ ማለት ነው (የሐ. ሥራ. 20፥35 ፤ ሉቃ.1፥48 ፤ ማቴ.5፥3)።
ያባት ስም ሰጠኝ ቢል ይገጥማል።
ብፅዐቴ - ብፁዕዓለም

444. **ቦሩ** (ኦሮ) ነገ ማለት ነው።

445. **ቦርጋ** (ጉራ) የሚበረግግ ማለት ነው፤

446. **ቦንገር** (ጉራ) ተናጋሪ ማለት ነው።

447. **ቦኤዝ** (ዕብ.)
ሀብታም የነበረ ሰው፤ የሩት ባል ፤
የቅዱስ ዳዊት ቅድመ አያት ነው።
(መጽ.ሩት 4፥17 ፤ ማቴ.1፥5)

448. **ቦኬ** (ኦሮ) ትንኝ ማለት ነው።

449. **ቦጋለ**
በኃይል በራ፤ ዓይናማ መኾኑን ያሳይል
ያባት ስም መብራቱ ቢል ይገጥማል።

- ተ -

450. **ተመስገን** (ተመስጌን)
ምስጋና ለፈጣሪ፤ ለስተደረገው ችሮታ፣ ውለታ፣ ባደረገው መልካም ነገር ...።
ያባት ስም ዘላለም ቢል ይገጥማል።

451. **ተመቸ – ተመቹ**
ደላ፣ አዝናና፣ እንደ ልብ አደረገን ።
ያባት ስም ከተማ ቢል ይገጥማል።

452. **ተማር**
ዕወቅ፣ ተረዳ፣ ጠይቅ፣ አጥና ...።
ያባት ስም ያገርሰው ቢል ይገጥማል።

453. **ተረጨ**
ተፈነጠቀ፣ ተበተነ፣ ተነዛ፣ ተወረወረ ፣ ተርከፈከፈ ፣ ተዳረሰ፣ ጠበሱ
(ኢዮ. 41፥11 ፤ ዕዝ. 10፥22) ።
ያባት ስም ጠበሱ ቢል ይገጥማል።

454. **ተረፈ - ተረፈልኝ**
ደረሰ፣ በዛ ፣ ከልክ አለፈ ፣ ከመጠን በለጠ፣ ወይም ቀሪ ተገኘ ፤ ወይም ለጥ ቂት ዳነ፣ ተፈወሰ፣ ተተወ ይኸናል ...።
ያባት ስም ሀብቱ ቢል ይገጥማል።

455. **ተስፋዬ - ተስፋነህ**
አለኝታዬ፣ የወደፊት ዋጋዬ ...።
በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተለመደ ስም ነው (ሮሜ. 15፥13 ፤ ዕብ. 11)።
ያባት ስም ታደሰ ቢል ይገጥማል።
ተስፋው - ተስፋ - ተስፋ - ተስፋይ
ተስፋዓለም - ተስፋኹነኝ - ተስፋኹን
ተስፋ ማርያም ከርሰትና ስም።

456. **ተሰማ**
ድምጹ ተደመጠ፣ ወሬው ተሰማ ...።
በወሬ ምኒልክ፣ በልጅ ኢያሱ፣ በንግሥት ዘውዲቱ፣ በወሬ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መን ግሥት በሹፌርነት፣ በመካኒክ፣ በሙዚቃ፣ በሥዕል፣ በቀልድ ዐዋቂነታቸው የተደነቁ ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ነበሩ።
ተሰማችው - ተሰማኸ

457. **ተሻለ**
በለጠ፣ ተመረጠ ፣ ረባ፣ ጠቀመ፤ በማወ ዳደር የተገኘ ...።
ያባት ስም ትዕግሥቱ ቢል ይገጥማል።

458. **ተሻገር**
ማዶ፣ ወንዙ ሳይሞላ፣ መከራን አለፈው።
ያባት ስም አድማስ ቢል ይገጥማል።

459. **ተሾመ**
ደረጃ አገኘ ፣ ከፍ ከፍ አለ ፤ ሙሉ ኾነ፣ ከበረ፣ ሥልጣን አገኘ ...።
ያባት ስም በቃሉ ቢል ይገጥማል።

460. **ተቀባ**
ቅባት ተለቀለቀ፤ ግርማ ሞገስ አገኘ ...።
ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተቀበለ።
ክህነ፣ ንጉሥ፣ አርን ...።
ያባት ስም ጸጋ ቢል ይገጥማል።

461. **ተበጀ**
ተሠራ፣ ተስተካከለ ፤ ተጠገነ ።
ያባት ስም አሱባለው ቢል ይገጥማል።

462. **ተባበር**
ተረዳዳ ፤ አንድ ኹን ...።
ያባት ስም ወገኔ ቢል ይገጥማል።

463. **ተናኘ - ተናኘኸ**
ለኹሉም ተለገሠ ፤ ተሰጠ ።
ያባት ስም ወርቁ ቢል ይገጥማል።

464. **ተንከተም** (ግእ)
መወጣጫ፤ መሰላል ማለት ነው
(ዘፍ. 28፥12)።

465. **ተአምሩ** (ግእ) - **ታምሩ** (ዐማ)
ተሰምቶ የማይታወቅ፤ ጉድ ድንቅ ታይቶ፣ ለማለት ...። በዓለም ተፈጥሮ አስደናቂ ነገር ሲደረግ ፤ ይኾናል ተብሎ የማይጠበቅ ነገር ሲፈጠር ፤ ታምር ይባላል።
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።
ተአምራቴ - ተአምራት - ታምር
ተአምረ ማርያም ክርስትና ስም ።

466. **ተክሥተ**
ከሠተ ገለጠ ፤ ከፈተ ማለት ነው።
ያባት ስም ብርሃን ቢል ይገጥማል።
(ማቴ. 3፥15፤ ሉቃ.24፥1)
ተክሥተ ብርሃን ክርስትና ስም።

467. **ተከተል**
ከኋላ ተጓዝ ፤ ይምራህ፣ ኹለተኛ ...።
ያባት ስም እንዳለ ቢል ይገጥማል

468. **ተካ**
በቦታው ሌላ አስቀምጥ፣ ለውጥ።
ያባት ስም በላቸው ቢል ይገጥማል።
ተክልኝ - ተካቸው - ተክኢ - ተኬ

469. **ተካበ**
በመልክ በመልኩ ተደራረበ፣ ተደረደረ።
ኹለተኛው፥ የሚያካብት አጠራቃሚ ...።
ያባት ስም እንግዳየሁ ቢል ይገጥማል።

470. **ተክሉ - ተክላይ** (ትግ)
አፀዱ፣ ችግኙ፣ ታዳጊው ...።
ያባት ስም በቀለ ቢል ይገጥማል።
ተክለ ለክርስትና ስም ቅጽል ይኾናል።
ተክለ ወልድ ክርስትና ስም።

471. **ተክሌ**
የተከልኩት፣ ችግኜ ...።
የአሌቃ ገብረሐና ልጅ ያቋቋም ዝማሜን የመሠረተ ማሕሌታዊ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ የወይዘሮ ማዘንጊያሽ ልጅ ተክሌ በመባል ይታወቃል።

472. **ተክሊል** (ግእ)
ከAA ፤ ክብር ማለት ነው ።
ድንበር ፤ ከዚህ አትለፍ ይኾናል።
ያባት ስም ከብሩ ቢል ይገጥማል።

473. **ተኰላ**
ኩል ኳስ፣ አደመቀ፣ ቀባ ወይም ታጠበ ጠራ ፣ ተወለወለ ፣ ታደሰ ...።
ዓይንን ለማሳመር የሚቀቡት ቅባት።
የጥንት ሰዎችም፣ ዘመናዊዎችም ለማጌጥ

ኩሉ የኳላሉ (2ነገሥ. 9፥30፤ ኤር. 4፥30 ፤ ራእ. 3፥18) ።
ያባት ስም ውበቱ ቢል ይገጥማል።

474. **ተወልደ** (ግእ. ትግ)
ተወለደ ማለት ነው ...።
ያባት ስም ሲሳይ ቢል ይገጥማል።
ተወልደ ብርሃን ክርስትና ስምን ተመልከት።

475. **ተወዳጅ - ተወዳሽ**
በጠባዩ፣ በመልኩ ይሚወደድ ...።
ያባት ስም አለኸኝ ቢል ይገጥማል።

476. **ተዋሕዶ** (ግእ)
ዋሕድ ከሚለው የመጣ ነው ።
አንድ ፣ አንድነት ፣ ማለት ነው።
ያባት ስም ሃይማኖት ቢል ይገጥማል።

477. **ተዋበ** አማረ፣ ቆነገ ማለት ነው።

478. **ተዋነይ** (ግእ)
ዋነየ ከሚለው ዋኝ ፣ ዋናተኛ ኾነ ተጫወት ማለት ነው ። በዚህ ስም የሚታወቀው በዐፄ በእደ ማርያም ዘመን (1460-1470) ቅኔን ከነ መሠረቱ ወስዶ ያነጸው ሊቅ ተዋነይ በመባል ይታወቃል።

479. **ተውህቦ** (ግእ)
ተሰጠው ማለት ነው። (1ቆሮ. 12፥8)
ጥበብ፣ ዕውቀት ...።
ያባት ስም ምሕረት ቢል ይገጥማል።

480. **ተዘራ**
የዘራው ምሳሌ ፦ በመልካም መሬት የተዘራ ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውል ነው።
(ማቴ. 13፥18)። **ተዘሩ - ተዘራወርቅ**
ያባት ስም ወርቁ ይገጥማል።

481. **ተድላ**
ደስታ፣ ድሎት ማለት ነው።
(ዘፍ.3፥23 ፤ 1ቆሮ. 10፥33 ፤ ሲራ. 9፥12)
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

482. **ተገኑ**
ረዳቱ፣ ክለላው፣ መመኪያው ...።
ያባት ስም ታደለ ቢል ይገጥማል።
ተገነኸ - ተገኒ - ተገናው - ተገኔ

483. **ተገኘ**
የጠፋው፣ የተሰወረው፣ ዐዲስ ነገር።
ያባት ስም ማሰርሻ ቢል ይገጥማል።
ተገኘህ - ተገኘወርቅ - ተገኙ - ተገኝ

484. **ተጌጠ - ተጌጡ**
ተዋበ ፣ አንዲያምር ተደረገ ።
ያባት ስም መንበሩ ቢል ይገጥማል።

485. **ተግባሩ - ተግባር**
የሚሠራው ሥራ ...።
ሰው በሙሉ ኀይሉ መሥራት ይገባዋል።
(መክ.9፥10 ፤ ቆላ.3፥17 ፤ 1ተሰ. 4፥10)።
ያባት ስም ይመር ቢል ይገጥማል።

486. **ተጠምቀ - መጥምቁ**
ተለወጠ ፣ ነጻ ፣ ተባበረ
(ማር. 1፥1-8 ፤ 1ቆሮ. 1፥13)።
ያባት ስም ወልዱ ቢል ይገጥማል።

487. **ተፈሪ**
የተፈራ፣ የሚፈራ፣ የሚታፈር፣ ጎይለኛ፣ ጉበዝ ማለት ነው።
ኢትዮጵያን ለ 43 ዓመት በንጉሥነት ያስተዳደሩ ዐፄ ኀይለ ሥላሴ ወላጆቻቸው
ያወጡላቸው ስም ተፈሪ ነው ።
ተፈራ - ተፈራወርቅ

488. **ቁሉ** (ኦሮ)
ተራራ ማለት ነው ። ቁለማ

489. **ቁራ** (ኦሮ) ዘገየ ቆየ ማለት ነው።

490. **ቲመርጋ** (ጉራ)
ከእከሌ ጋር ነው ማለት ነው ።

491. **ቲቶ** (ግሪ)
ፀሓይ ማለት ነው ። **ቲቶ** ለሐዋርያው ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ልጁ ነበር ፤ (የሐ. ሥራ 15፥1፤ ገላ2፥1፤ ቲቶ1)።

492. **ቴዎፍሎስ** (ግሪ)
የእግዚአብሔር ወዳጅ ማለት ነው ። ቅዱስ ሉቃስ ወንጌሉን እና የሐዋርያት ሥራን የጻፈለት ሰው ነው ። ዅለተኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በዚህ ስም ይታወቃሉ (ሉቃ. 1፥1፤ የሐዋ. 1፥1)።

493. **ታለጌታ - ታለ - ታለኝ**
ካለ ፈጣሪ አልወድቀም ብወድቅም አነሳስሁ።
ያባት ስም **አሸናፊ** ቢል ይገጥማል

494. **ታመነ**
በጥቂት ነገር ላይ ጎለፊነት ሲሰጠው ቃሉን የሚጠብቅ ፤ የሚፈጽም ። ክርስቲያን ታማኝ ነው (2ኛቆሮ.1፥18 ፤ 2ኛጢሞ. 2፥2 ፤ ያዕ.5፥12)።
ያባት ስም **አብርሃም** ቢል ይገጥማል።
ታመነው - ታመን - ታማኝ የታመነ የማይጠረጠር የሚታመን ማለት ነው።

495. **ታረቀ**
ሰላም ኾነ፣ ተስተካከለ የጎበጠው ተቃና።
ያባት ስም በቃሉ ቢል ይገጥማል።
ታረቀን - ታረቀኝ - ታርቆ

496. **ታሪኬ**
ያለፈው ሕይወቴ ...።
ታሪክ ያለፈን የሚነግር፣ የሚያወሳ ነው።
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።
ታሪክ - ታሪኩ - ታሪካዊ

497. **ታሲሳ** (ኦሮ)
አንድ ነገር እንዲፈጸም ማድረግ ማለት ነው።

498. **ታሸበወርቅ ፡- ታሸቤ**
ወገቡ በወርቅ ቀበቶ ታሸበ ...።
ዅለተኛው ገላው በወርቅ ታሸ ...።
ያባት ስም ገላው ቢል ይገጥማል።

499. **ታቦር**
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃነ መለኮቱን የገለጸበት ተራራማ ቦታ፤
(መዝ. 88 (89)፥12 ፤ ማር 9፥2)።

500. **ታኢኒ** (ጉራ) ተወልኝ ማለት ነው።

501. **ታክለ**
ተጨመረ፣ ተቀላቀለ ፣ ተዋሐደ ...።
ያባት ስም ክብረት ቢል ይገጥማል።
ታክል - ታኪያ - ታኪላ (ትግ)
ታክሉ - ታክለልኝ

502. **ታያቸው - ታየ**
ተገለጠ፣ ካለበት ወጣ፤ ብርሃን ተገለጠ።
ሕዝብ ዘይነበር ውስተ ጽልመት ርእየ ብርሃነ ዐቢየ። ትርጉም ፤ በጨለማ የሚኖር ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ (ኢሳ. 9፥1 ፤ ማቴ. 4፥14)። **ታየሰው - ታየው**
ያባት ስም ብርሃን ቢል ይገጥማል።
ታየኸኝ - ታይ - ታይባቸው

503. **ታደሰ**
እንደ ገና ዐዲስ ኾነ ...። በዕድሜ፣ በዘመን ብዛት እንደገና ተስወጠ ...።
ያባት ስም ምትኩ ቢል ይገጥማል።
ታደሲ - ታደሳ - ታዱ - ታደሱ

504. **ታደገ** (ግእ)
ተቤዠ፣ አስተወ ፤ አስጣለ፣ አስለቀቀ፣ አዳነ፣ ተስመነ ማለት ነው።
ዅለተኛ ትርጉም ከደገልኝ አቅመ አዳም ከደረሰልኝ... ይኾናል።
ያባት ስም **መልኩ** ቢል ይገጥማል።
ታደገኝ - ታደገው - ታደጉ - ታደግ

505. **ታደለ - ታደሉ**
ተቸረ፣ በተራ ስጦታ ተገኘ ። ዅለተኛው ትርጉም ተከፋፈለ ፣ ተቀረማመደ ።
ባለዕድል ኾነ ያላሰበውን አገኘ ...።
ያባት ስም **ጸጋ** ቢል ይገጥማል።

506. **ታዴዎስ (ግሪ)**
ተአማኒ ፣ የታመነ ማለት ነው።
ከ፸ሥራ ዅለቱ ሐዋርያት አንዱ ነው (ማቴ. 10፥3 ፤ ማር.3፥18 ፤ ሉቃ. 6፥15 የሐ ሥራ 1፥13)። ሌላው ስሙ **በርተሎሜዎስ** ነው።

507. **ታጀበ - ታጀቡ**
በሕዝብ ፣ በሰው ስለከበሩ ተከበበ።
ያባት ስም **የኔሰው** ቢል ይገጥማል።

508. **ታገል - ታገለው - ታግሎ**
ጥረት አድርግ ፣ ጠንክረህ ሥራ።
ያባት ስም **ያገርሰው** ቢል ይገጥማል።

509. **ታገሠ - ታገሢ** መከራውን፣
ፈተናውን ቻለ ፤ ጸና ...። (ሮሜ. 9፥22)
ያባት ስም **በአምነት** ቢል ይገጥማል።

510. **ታፈሠ - ታፈሠወርቅ**
በእሩኅ ተወሰደ ፣ ተሰበሰበ ።
ያባት ስም **ገንዘቤ** ቢል ይገጥማል።

511. **ቴዎድሮስ** (ግሪ) (**ቴዎ - ድሮስ**)
የእግዚአብሔር ስጦታ ማለት ነው ።
ቀዳማዊ ቴዎድሮስ ከቀዳማዊ ዳዊት ቀጥሎ የነገሠ ናቸው (1411 ዓ. ም)።
ዳግማዊ ቴዎድሮስ የተባሉት ደግሞ በፈረሰ ስማቸው አባ ታጠቅ ወይም ደጃዝማች ካሳ፣ የቋራው አንበሳ። የሚባሉት ናቸው (1811- 1868 ዓ. ም)።

512. **ትሕትና**
ራስን ዝቅ ማድረግ፤ ሌላው ሰው እንዲጠቀም መፈለግ (2ዜና. 7፥14 ፤ ያዕ. 4፥6)።
ሙሴ እጅግ ትሑት ሰው ነበር ፤
(ዘኍ. 12፥3)።
ያባት ስም **በዛብህ** ቢል ይገጥማል።
ትሕትናው - ትሑት - ትሑትነሽ

513. **ትምህርተ - ትምህርት**
ከለፈ ነገር መማር። ልጆችን ማስተማር።
(ዘጸ. 12፥25)።
ያባት ስም **ፊደሉ** ቢል ይገጥማል።

514. **ትምክህት - ትምክህተ**
በሠሩት በጎ ሥራ ራስን ማክበር ፤ ማመሥገን ። በችሎታ መተማመን (ኢር. 9፥23 ፤ ኤፌ. 2፥9)።

515. **ትርፌ**
የኔ ትርፍ፤ የልፋት ዋጋዬ (ማቴ. 25፥14)።
ያባት ስም **አመዘነ** ቢል ይገጥማል።
ትርፍዓለም - ትርፉ - ትርፈሳ

488. **ቱሉ** (ኦሮ)
ተራራ ማለት ነው ። ቱለማ

489. **ቱራ** (ኦሮ) ዘገየ ቆየ ማለት ነው።

490. **ቲመርጋ** (ጉራ)
ከእከሌ ጋር ነው ማለት ነው ።

491. **ቲቶ** (ግሪ)
ዐሓይ ማለት ነው ። **ቲቶ** ስሐዋርያው ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ልጁ ነበር ፤ (የሐ. ሥራ 15፥1፤ ገላ2፥1፤ ቲቶ1)።

492. **ቴዎፍሎስ** (ግሪ)
የእግዚአብሔር ወዳጅ ማለት ነው ። ቅዱስ ሉቃስ ወንጌሉን እና የሐዋርያት ሥራን የጻፈለት ሰው ነው ። ኹለተኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በዚህ ስም ይታወ ቃሉ (ሉቃ. 1፥1፤ የሐዋ. 1፥1)።

493. **ታስጌታ - ታስ - ታስኝ**
ካለ ፈጣሪ አልወድቀም ብወድቅም እነሳለሁ።
ያባት ስም **አሸናፊ** ቢል ይገጥማል

494. **ታመነ**
በጥቂት ነገር ላይ ጎላፊነት ሲሰጠው ቃሉን የሚጠብቅ ፤ የሚፈጽም ። ክርስቲ ያን ታማኝ ነው (2ኛቆሮ.1፥18 ፤ 2ኛጢሞ. 2፥2 ፤ ያዕ.5፥12)።
ያባት ስም **አብርሃም** ቢል ይገጥማል።
ታመነው - ታመን - ታማኝ የታመነ የማይጠረጠር የሚታመን ማለት ነው።

495. **ታረቀ**
ሰላም ኾነ፣ ተስተካከለ የጎበጠው ተቃና።
ያባት ስም **በቃሉ** ቢል ይገጥማል።
ታረቀን - ታረቀኝ - ታርቆ

496. **ታሪኬ**
ያለፈው ሕይወቴ ...።
ታሪክ ያለፈን የሚነግር፣ የሚያወሳ ነው።
ያባት ስም **ተሰማ** ቢል ይገጥማል።
ታሪክ - ታሪኩ - ታሪካዊ

497. **ታሲሳ** (ኦሮ)
አንድ ነገር እንዲፈጸም ማድረግ ማለት ነው።

498. **ታሸበወርቅ - ታሸቤ**
ወገቡ በወርቅ ቀበቶ ታሸበ ...።
ኹለተኛው ገላው በወርቅ ታሸ ...።
ያባት ስም ገላው ቢል ይገጥማል።

499. **ታቦር**
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃነ መለ ኮቱን የገለጸበት ተራራማ ቦታ፤
(መዝ. 88 (89)፥12 ፤ ማር 9፥2)።

500. **ታኢኒ** (ጉራ) ተወልኝ ማለት ነው።

501. **ታከለ**
ተጨመረ፣ ተቀላቀለ ፣ ተዋሐደ ...።
ያባት ስም **ክብረት** ቢል ይገጥማል።
ታከል - ታኪያ - ታኪላ (ትግ)
ታከሉ - ታከለልኝ

502. **ታያቸው - ታየ**
ተገለጠ፣ ካለበት ወጣ፤ ብርሃን ተገለጠ።
ሕዝብ ዘይነበር ውስተ ጽልመት ርእየ ብርሃነ ዐቢየ። ትርጕም ፤ በጨለማ የሚ ኖር ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ (ኢሳ. 9፥1 ፤ ማቴ. 4፥14)። **ታየሰው - ታየው**
ያባት ስም **ብርሃን** ቢል ይገጥማል።
ታየኸኝ - ታይ - ታይባቸው

503. **ታደሰ**
አንደ ገና ዐዲስ ኾነ ...። በዕድሜ፣ በዘ መን ብዛት እንደገና ተለወጠ ...።
ያባት ስም **ምትኩ** ቢል ይገጥማል።
ታደሲ - ታደሳ - ታዱ - ታደሱ

504. **ታደገ** (ግእ)
ተቤዠ፣ አሰተወ ፣ አስማለ፣ አስለቀቀ፣ አዳነ፣ ተለመነ ማለት ነው።
ኹለተኛ ትርጕም ካደገልኝ አቅመ አዳም ከደ ረሰልኝ... ይኾናል።
ያባት ስም **መልአኩ** ቢል ይገጥማል።
ታደገኝ - ታደገው - ታደጉ - ታደግ

505. **ታደለ - ታደሉ**
ተቸረ፣ በተራ ስጦታ ተገኘ ። ኹለተኛው ትርጕም ተከፋፈለ ፣ ተቀረማመደ ።
ባለዕድል ኾነ ያላሰበውን አገኘ ...።
ያባት ስም **ጸጋ** ቢል ይገጥማል።

506. **ታዴዎስ (ግሪ)**
ተአማኒ ፣ የታመነ ማለት ነው።
ከዐሥራ ኹለቱ ሐዋርያት አንዱ ነው (ማቴ. 10፥3 ፤ ማር.3፥18 ፤ ሉቃ. 6፥15 የሐ ሥራ 1፥13)። ሌላው ስሙ **በርተሎ ሜዎስ** ነው።

507. **ታጀበ - ታጀቡ**
በሕዝብ ፣ በሰው ስለክብሩ ተከበበ።
ያባት ስም **የኔሰው** ቢል ይገጥማል።

508. **ታገል - ታገለው - ታግሎ**
ጥረት አድርግ ፣ ጠንክረህ ሥራ።
ያባት ስም **ያገርሰው** ቢል ይገጥማል።

509. **ታገሠ - ታገሢ** መከራውን፣
ፈተናውን ቻለ ፤ ጸና ...። (ሮሜ. 9፥22)
ያባት ስም **በእምነት** ቢል ይገጥማል።

510. **ታፈሠ - ታፈሠወርቅ**
በእናኝ ተወሰደ ፣ ተሰበሰበ ።
ያባት ስም **ገንዘቤ** ቢል ይገጥማል።

511. **ቴዎድሮስ** (ግሪ) (ቴዎ - ድሮስ)
የእግዚአብሔር ስጦታ ማለት ነው ።
ቀዳማዊ ቴዎድሮስ ከቀዳማዊ ዳዊት ቀጥ ሎው የነገሡ ናቸው (1411 ዓ. ም)።
ዳግማዊ ቴዎድሮስ የተባሉት ደግሞ በፈ ረሰ ስማቸው አባ ታጠቅ ወይም ደጃዝ ማች ካሳ፣ የቋራው አንበሳ። የሚባሉት ናቸው (1811- 1868 ዓ. ም)።

512. **ትሕትና**
ራስን ዝቅ ማድረግ፤ ሌላው ሰው እንዲጠ ቀም መፈለግ (2ዜና. 7፥14 ፤ ያዕ. 4፥6)።
ሙሴ እጅግ ትሑት ሰው ነበር ፤
(ዘኍ. 12፥3)።
ያባት ስም **በዛብህ** ቢል ይገጥማል።
ትሕትናው - ትሑት - ትሑትነሽ

513. **ትምህርተ - ትምህርት**
ካለፈ ነገር መማር። ልጆችን ማስተማር።
(ዘጸ. 12፥25)።
ያባት ስም **ፊደሉ** ቢል ይገጥማል።

514. **ትምክህት - ትምክህተ**
በሠሩት በጎ ሥራ ራስን ማክበር ፤ ማመ ሥገን ። በችሎታ መተማመን (ኢር. 9፥ 23 ፤ ኢፌ. 2፥9)።

515. **ትርፌ**
የኔ ትርፍ፤ የልፋት ዋጋዬ (ማቴ. 25፥14)።
ያባት ስም **አመዘነ** ቢል ይገጥማል።
ትርፍዓለም - ትርፉ - ትርፈሳ

516. **ትንሣኤ (ተንሣይ)**
ጌታ ኢየሱስ ከርስቶስ የተነሣበት ዕለት።
ዕለተ እሑድ ፤ የጌታ ቀን (ራእ. 1፥10)።
ያባት ስም ብርሃኑ ቢል ይገጥማል።

517. **ትንቢቱ - ትንቢተ**
የሚመጣውን የሚገልጽ (ማቴ. 1፥21 ፤ ዕብ. 1፥1፤ 1ጴጥ. 1፥10)።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።

518. **ትዕግሥት (ግእ) (ትግሥት)**
የመከራን፣ የስቃይን፣ ችሎታ፣ ዝምታ መቻል፣ መርጋት፣ ጸጥ ማለት፣ በመከራ መጽናት ፤ ተስፋ ማድረግ ።
እነሆ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላ ቸዋለን፤ ኢዮብ እንደ ታገሠ ሰምታችኋል (ያዕ. 5፥11)። **ትዕግሥተኝነም**
ያባት ስም ደጉ ቢል ይገጥማል ።
ትዕግሥቴ - ትዕግሥቱ

519. **ትዛዙ (ትእዛዙ) - ትዛዝ - ትዛዜ**
አድርግ ፣ አታድርግ የሚል ።
ትእዛዛት ለአዳም ፣ ለኖኅ፣ ለአብርሃም ለሙሴ ፣ እንዲሁም ለሐዋርያት ተሰጥተዋል (ዘፍ. 2፥16፤ ዘጸ.3፥15 ፤ ማቴ. 28፥19)።
ያባት ስም ፈጠነ ቢል ይገጥማል።

520. **ትዝታው - ትዝታወርቅ - ትዝታ**
ያስፈን ነገር ማስታወስ ።
ያባት ስም አያልቅበት ቢል ይገጥማል።

521. **ትጉህ (ግእ)**
ተግሀ ከሚለው ግስ ፤ ተጋ ፣ ትጉህ ኾነ የማያንቀላፋ ፣ የማይተኛ።
ንቁ፣ በጸሎት በልመና ኹሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ ፤ በዚህ ሐሳብ ስለ ቅዱሳን እየለመናችሁ በመጽናት ትጉ (ኤፌ. 6፥18 ፤ ቆሳ. 4፥2) ።

522. **ቶሌራ (ኦሮ) አማረ ማለት ነው።**

523. **ቶማስ (አሮማ.)**
በግሪክ ዲዲሞስ በርማይስጥ ቶማስ ማለት መንቶች ማለት ነው። እንዲኹም እጽፍ ድርብ ፀሓይ ማለት ይኾናል ።
ጌታ ከይሁዳ አስቆሮታዊ ሲለይ ቶማስ አለው። ከዐሥሩ ኹለቱ ሐዋርያት አንዱ ነው፤ የጌታ ኢየሱስን ጎኑን ካልዳሰስኩ አላምንም ብሎ ከተረዳ በኋላ ጌታዬ አምላኬ ብሎ አመነ (ማቴ.10፥2)።

524. **ቶክ (ዶር.) ታታሪ ማለት ነው።**

525. **ቶሎሳ (ኦሮ) ቶላ**
ያማረ ማለት ነው።
ሯጩ ቶሎሳ ቶቱ በዚ ስም ይታወቃል።

- ቸ -

526. **ቸርነት - ቸሩ - ቸርዬ**
ደግነት ፣ ለጋሥነት ።
በለጋሥነት፤ በደግነት የሚሰጥ ስጦታ፤ አግዚአብሔር አሰቀድሞ ለሰው ቸርነትን አሳይቷል (መዝ. 32፥5 ፤ ሮሜ. 2፥4)።

527. **ቸኩለ - ቸኩሉ - ቸኩል**
ፈጠነ፣ ተጣደፈ፣ ቀሰ ማለት አልቻለም።
ያባት ስም ዳኛው ቢል ይገጥማል።

528. **ቻለው - ቻለ - ቻላቸው**
ታገሠው ፣ ተሸከመው ።
ያባት ስም አንዳገር ቢል ይገጥማል።

529. **ችሮታው**
ስጦታው ፣ ለጋሥነቱ ።
ያባት ስም ያንተአምላክ ቢል ይገጥማል።

- ኀ -

530. **ኀድጋይ - ኀድጎ (ትግ.)**
ተወ ማለት ነው።

531. **ኂሩተ (ግእ) ኂሩት - ኄር**
ቸርነት ማለት ነው። ኂሩተ ሠናይቲክ ኂሩተ ቢል ለክርስትና ስም ትጽል ይኾናል።

532. **ኃይሌ (ኀይሌ) ኃይሉ (ግእ)**
ዐየለ ማለት ነው። ዐየለን የሚሰጠኝ በክርስቶስ ኹሉን እችላለሁ። (ፊል. 4፥13 ፤ ዘፍ. 31፥29 ፤ ሉቃ. 1፥17)።
በዚህ ስም የሚታወቀው የረዥም ሩጫ ውድድር የዓለምን ክብረ ወሰን የያዘው ታዋቂው ኃይሌ ገብረ ሥላሴ ነው።
ኃይሉ - ኃይልዬ - ኃይልነህ
ኃይላቸው - ኃየሎም (ትግ)
ኃይለ ሥላሴ ክርስትና ስም።

533. **ኅሊና ፤ ልባዊ ፣ ረቂቅ ሥራ።**

534. **ኅሩይ (ግእ)**
የተመረጠ ማለት ነው።
በዚህ ስም የሚታወቁት ከዐፄ ኅይለ ሥላሴ ጋር በእንግሊዝ አገር ይኖሩ የነበሩት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ናቸው ። ከኢትዮጵያ ሊቃውንት አንዱ ነበሩ ። ኅሩያን - ኅሩየ
ኅሩየ ሥላሴ ክርስትና ስም።

535. **ኅርያቆስ**
ኅሩይ ፣ ቅን ፣ ረቂቅ ማለት ነው።

የቅዳሴ ማርያም ደራሲ የብሕንሳው ኢጲስ ቆጶስ (ቅዳ. ማር)።

536. **ኅብረት**
አንድነት መተባበር መስማማት ፤ የተባበረ ፤ የተስማማ ማለት ነው።
ይህም ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ አንዱ በረከት ነው (2ኛ ቆሮ. 13፥14) ።
ያባት ስም አጀናፊ ቢል ይገጥማል።
ኅብሩ - ኅብርነህ

537. **ኅብስተመና**
የሠመረ፣ ያማረ ማለፊያ ዳቦ ።
እስራኤል 40 ዘመን በበረሀ የተመገቡት። (ዘሌ. 24፥5 ፤ ዘጉ 4፥7 ፤ ዮሐ. 6፥35)።
ያባት ስም ተረፈ ቢል ይገጥማል።
ኅብስቱ - ኅብስቴ

538. **ኅዳግ (ግእ) – ኅዳጉ**
ትርጕሙ፡ የመጽሐፍ የጽሑፉ ጠርዝ ክፍል ግርጌው ባዶ ቦታ፤ ኅዳግ ፣ ዐምድ (ራሱ)፣ ግልየት (ቀኖ) ፣ ምስማክ (ግራው) ፣ መኸል ያለው መሰመር ሐውልት ይባላል። በዚህ ገጽ መረዳት ይቻላል።

- ኘ -

539. **ኘህምያ (ዕብ.)**
ነቢይ ነው። አባቱ ሐካልያ ይባል ነበር (መጽ. ነህ. 1፥1)።

540. **ኘመራ (ጉራ. አሮ.) ኘሙ - ኘሚ**
አሰተካክሉ ማሰማራት ማለት ነው።

541. **ኘሲቡ**
ለአባቱ ዕድሉ ኾኖ የተሰጠው ማለት ነው
ነሲብ ቢል ዕድል፣ ግምት ፤ እንዲሁም ያሰባል ማለት ነው። (በነሲብ)

በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ በዐፄ ምኒ ልክ ዘመነ መንግሥት በፍርድ ዐዋቂነት ችሎታ የነበራቸው ዳኛ የነበሩት አፈ ንጉሥ ነሺዑ መስቀሉ ናቸው ።

542. **ነቅዐጥበብ - (ነቃጥበብ)** (ግእ)
የጥበብ መፍለቂያ ምንጭ ማለት ነው።
ያባት ስም ጸውሎስ ቢል ይገጥማል።
ነቃሕይወት - ነቅዐገነት - ነቅዐጽጌረዳ

543. **ነቢዩ - ነቢያት - ነቢያተ**
ትንቢት ተናጋሪ። ቃለ እግዚአብሔርን ለሕዝብ የሚናገር (1ኛሳሙ.9፥6)።

544. **ነቢየ ልዑል** (ግእ)
ዮሐንስ ማለት ነው ።
ወአንተኒ ሕፃን ነቢየ ልዑል ትሰመይ። ትርጉም ፤ አንተ ሕፃን የልዑል ነቢይ ትባላለህ (ሉቃ. 1፥76)።

545. **ነአምን** (ግእ)
አናምናለን ማለት ነው።
ያባት ስም በቃሉ ቢል ይገጥማል።

546. **ነገሠ**
ነግሠ ከሚለው ግስ የወጣ ፤ የበላይ ኾነ ማለት ነው። (1ሳሙ. 16፥6-13)።
ያባት ስም በኀይሉ ቢል ይገጥማል።
ነገሥት - ነጋሢ - ነጋሽ - ነገሡ

547. **ነገደ**
ወገን ፤ ዘመድ የኾነ ማለት ነው ።
ከአንድ ወገን የተወለደ ሕዝብ ። ያዕቆብ ዐሥራ ኹለት ልጆቹን ባረካቸው (ዘፍ.49)
ነገደዓለም - ነገደእስራኤል
ነገደወርቅ - ነገደፀሐይ
ነገደ ሚካኤል ክርስትና ስምን ተመልከት።

548. **ነገሥ** (ኦሮ) - **ነገዬ**
ሰላም ፣ ደህና ኾነ ማለት ነው።
ነጊያ (ጉራ)

549. **ነጋ**
ፀሓይ ወጣ ፣ ጎሕ ቀደደ፣ ሌሊቱ አለፈ ወሮች ተንጭጩ። ማለዳ ኾነ ...።
በዚህ ስም ከተጠሩት አንዱ ዐርበኛ ጀነራል ነጋ ኃይለ ሥላሴ ናቸው ። ለአገራቸው ለኢትዮጵያ የደከሙ ፤ በፈረስ ስማቸው አባ ይባስ ይባሉ ነበር።
ነጋዓለም - ነጋልኝ

550. **ነጋሢ** (ግእ)
በዐማርኛው ሲተረጉም ነጋሽ ነው።

551. **ነጋሥ** (ኦሮ)
ነጋ ሰላም ማለት ሲኾን ፤ ነጋሥ ማለት ደግሞ ሰላምም ማለት ነው።

552. **ነጋሽ**
የነገሠ፣ የሚነግሥ፣ የንጉሥ ልጅ ማለት ነው ... ።

553. **ነጠረወርቅ**
ወርቅ ወርቅነቱ በአሳት ይፈተናል ...።
ንጥረወርቅ - ነጥርወርቅ

554. **ነጸረ** (ግእ) - **ነጸረአብ - ነጽር**
አስተዋለ፤ በሩቅ አየ፣ ተመለከተ ማለት ነው። ወነጽር ቃለ በአለትየ፤ ትርጉም። ወደ ጸሎቴ ተመልከት።

555. **ነጸነት**
ነጻ መኾን፣ መለቀቅ ...።
ያባት ስም ታከለ ቢል ይገጥማል።
ነጻነቴ - ነጻነኽ - ነጻው

556. **ንጉድኝድ**
ጉድጉዶ ካለው አንኳኳ ማለት ነው።
የመብረቅ ግጭታ፣ የሚያስደነግጥ ታላቅ ድምጽ ። የዮሐንስና የያዕቆብ አባት ነጐድጓድ ይባል ነበር (ማር. 3፥17)።

557. **ኑርልኝ – ኑሩ**
ቁምልኝ፣ ቁይልኝ፣ ማለት ነው።
ያባት ስም በተስፋ ቢል ይገጥማል።

558. **ኒቆዲሞስ** (ግሪ)
የሕዝብ ገዢ ማለት ነው ፤ በሌሊት ሊሰግድ ወደ ጌታ ኢየሱስ የኼደ የሕግ መምህር ነበር (ዮሐ. 3፥1)።

559. **ኒሻን (ሊሻን)**
መንግሥት የሚሸለመው የክብር የጀግንነት ማዕርግ ፤ **ሊሻንወርቅ - ሊሻኔ**

560. **ናሁ ሠናይ** (ግእ)
ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም ። ሶበ ይሄልዉ አኀው ኅቡረ ። ትርጉሙ ፤ ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ እንሆ **መልካም** ነው እንሆ ያማረ ነው (መዝ. 132፥1)።

561. **ናሆም** (ዕብ.)
መጽናናት የሚያጽናና (ፈውሰ እግዚአብሔር) ማለት ነው ። ስለ ነነዌ ውድቀት ራእይ ያየ፤ ለይሁዳ የምሥራችን የነገረ ነቢይ ነው (ናሆ.1፥1)።

562. **ናርዶስ**
ከሕንድ አገር የሚመጣ የሽቱ አይነት (ዮሐ. 12፥3-5) ።
የናርዶስ ቅጠል ፤ ደስ የሚያሰኝ ሽቱ ። ናርዶስ ዘምስለ መጽርይ ቀጺመታት ወቀና ንምስ። ትርጉም፤ ናርዶስና ከቀጋ ጋራ ሽቶ ሣርና ቀረፋ ማለት ነው ። ናርዶስ ወሀበ መዐዛሁ። የኔ ናርዶስ መዐዛውን ሰጠ (ማኀ. ዘሰ 1፥12 ፤ 3፥20 ፤ 4፥13)።

563. **ናታን** (ዕብ.)
እሱ (እግዚአብሔር) ሰቶናል ማለት ነው።
በዚህ ስም በብሉይ ኪዳን ዐሥራ አንድ ሰው ተጠርተውበታል (2ኛ ሳሙ. 7)።

564. **ናታይ**
እስቲ እንይህ ፤ ውጣ ማለት ነው።
ያባት ስም ዐዲሱ ቢል ይገጥማል።

565. **ናትናኤል**
የእግዚአብሔር ስጦታ ማለት ነው፤ የጌተ ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ነው።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ናትናኤልን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ ስለ እርሱ፦ ተንኮል የሌለበት በእውነት የእስራኤል ሰው እነሆ አለ (ዮሐ. 1፥45 ፤ 21፥2)።

566. **ናዖድ** (ግእ)
ንዑድ ብዑድ ማለትም የተመሰገነ የተደነቀ በዕውቀቱ በደግነቱ የታወቀ ማለት ነው። ኢትዮጵያዊው ዐፄ ናዖድ ፥ **የዐፄ ልብነ ድንግል** አባት ናቸው። የመጀመሪያ ስማቸው ቀልዮጳ ነበር (1467 - 1500 ዓ. ም. ነግሠዋል)። የተማሩ በምርምር ቅኔ የተደነቁ ነበሩ ።

567. **ናዝራዊ** (ዕብ)
የተቀደሰ የተለየ ማለት ነው ። ለምሳሌ ሶምሶን ናዝራዊ ነበር (ዘኍ.6፥1፤ መሳ.13፥5፤ ማቴ. 2፥23)።

568. **ናደው - ናዳቸው**
አፈራረሰው ማለት ነው።
ያባት ስም ባንተይርጋ ቢል ይገጥማል።

569. **ናፖሊዮን (ግሪ)**
ዐዲስ ከተማ ማለት ነው።
ከቅርብ ዘመን ጀምሮ በዚህ ስም የሚጠሩ ኢትዮጵያውያን አሉ ። የፈረንሳዩ ንጉሠ ነገሥት በዚህ ስም ይታወቅ ነበር።

570. **ንብረቱ - ንብረት - ንብረቱ**
ገንዘቤ፣ ሀብቴ፣ ቅርሴ ...።
የገንዘብ ብዛት፣ ሥጋዊ፣ መንፈሳዊውንም ማግኘት (ዘፍ. 13፥2 I ምሳ. 21፥24 I ኢዮ. 1፥3 I ሉቃ. 12፥33 I)።
ያባት ስም ወገኘሁ ቢል ይገጥማል።

571. **ንባቡ - ንባቤ - ንባበ (ግእ)**
ተናገረ ፣ አነበበ ፣ ተረጎመ ።
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።

572. **ንቦ - ንብነህ**
ማር የምትሰጥ ተወዳጅ I ነገር ግን ተናዳፊ የኾነች። በጎይለኝነት ትመሰላለች። ንብ ማርን እንዲከቡ ከበቡኝ (መዝ. 117 (118)፥12)።

573. **ንዋይ (ግእ) - ንዋይ - ንዋይነህ**
ገንዘብ፣ ጥሪት፣ ቅርስ ፣ ንብረት ።
(ማቴ. 6፥24 I ሲራክ 21፥8) ሀብት ሲመጣ የሚወለደው ልጅ ወይም ራሱ ሀበት በመምጣቱ ንዋዬነህ ይባላል። በጌ ንዋየ ክርስቶስ የበጌ አምደጽዮን ልጅ በዚህ በክርስትና ስማቸው ይታወቃሉ። በንጉሥነት 28 ዓመት አስተዳድረዋል።

574. **ንጉሡ - ንጉሥ - ንጉሤ**
ያገር አውራ፣ የሕዝብ አረኛ፣ መሪና አሳዳሪ ማለት ነው ። ቀደምቶቹ ፦ ንጉሥ ሳያል፣ ንጉሥ ዳዊት ፣ ንጉሥ ሰሎሞን ነበሩ ። ከኮሚኒዝም ጊዜ ጀምሮ ንጉሥ በኢትዮጵያ ቀርቷል ። ፕሬዘዳንት የሚለው ቃል የመጣው በአሜሪካኑ ጆርጅ ዋሽንግተን ነው (1776 ዓ.ም.)።

575. **ንጋቱ - ንጋቴ - ንጋት**
ማለዳ፣ ፀሓይ ሲወጣ ፣ ጎሕ ሲቀድ ፣ ወፎች ሲንጭጩ ።
ያባት ስም ቦጋለ ቢል ይገጥማል።

576. **ንጹሕ**
የነጻ፣ የጸዳ፣ ፀአዳ ልብስ ...።
ልብስን፣ ሰውነትን ፣ ነፍስን ማንጻት።
ልበ ንጹሕ ፍጥር ሊተ እግዚኦ። ትርጉም አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ። (መዝ. 50 ፥10 I ሕዝ. 36፥25 I 1ዮሐ. 1፥7)።
ያባት ስም መመረት ቢል ይገጥማል።
ንጹሐን - ንጹሐው - ንጹሐወርቅ

577. **ንቦነህ - ንቦ**
ንብ ተወዳጅ ማርን የሚሰጥ ነው ።
በኃይለኝነት ትመሰላለች (መዝ. 117 (118) ፥12)።

578. **ንፍታሌም (ዕብ)**
የሚታገል፤ በመታገል የተገኘ ማለት ነው።
የራሔል አገልጋይ ባላ የወለደችለት የያዕቆብ ስድስተኛ ልጅ ነው (ዘፍ. 30፥7)።

579. **ኖኅ**
የሰው ልጅ በምድር ላይ በበደለ ጊዜ በእግዚአብሔር ዘንድ ንጹሕ ኾኖ የተመረጠ ኖኅ ብቻ ነበር I ከጥፋት ውሃም ዳነ (ዘፍ. 6፥1)።

580. **ኖላዊ (ግእ)**
የሚጠብቅ ጠባቂ፤ መሪ፣ አረኛ፣ ንጉሥ፣ ጳጳስ የበጎች ጠባቂ (ዘፍ.4፥2 I ዘጸ.32 I ዮሐ.10)

ኖላዊያሙ ለእስራኤል አጽምዕ ። ትርጉም I የእስራኤል ጠባቂ ሆይ አድምጥ (መዝ. 79(80)፥1)።

- አ -

581. **አለማኸኩ**
አለመለምኩ፣ አላመርኩ፣ አበዛሁ ...።

582. **አለባቸው**
በትያትር አስተዋዋቂነት ፣ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን መርሐ ግብር አቀነባባሪነት የተሳካለት ኢትዮጵያዊ ። አለባቸው ተካ በዚህ ስም ይታወቃል።
አለኸኝ - አለኻቸው - አለኸልኝ
አለበል - አለልኝ - አለነ
አለብኽ - አለንኽ

583. **አሊፎም** (ትግ) አለፈ ማለት ነው።

584. **አላምረው**
ነገሩን ወደ ከፋት አልውሰደው ...።
ያባት ስም ተመስገን ቢል ይገጥማል።
አላምሬ - አላምር - አላግረው

585. **አላየ**
አልተመለከተ I አልተገነዘበም ለማለት ይገለጻል። **አላዩ - አላይ - አላውጋ**
ያባት ስም ክብሩን ቢል ይገጥማል።

586. **አልማው - አልማቸው**
በከንቱ በሐሜት አላንሳው።
ያባት ስም በሀብቱ ቢል ይገጥማል።

587. **አልባሴ (ግእ) አልባሽ**
ልብሴን፣ ክብሬን አልባሼ ...።
ያባት ስም ወርቁ ቢል ይገጥማል።

588. **አልታሰብ**
ያልታሰበ፣ ድንገተኛ ...።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።

589. **አልታዬ - አልታየህ**
ማን እንደ ኾነ አልታወቀ ...።
ያባት ስም የቺጥላ ቢል ይገጥማል።

590. **አልአዛር**
እግዚአብሔር ረድቷል ማለት ነው።
በዚህ ስም በቅዱስ መጽሐፍ ሦስት የታወቁ ሰዎች ተጠርተውበታል።
የአሮን ልጅ ካህኑ አልአዛር።
ከሞተ በኋላ በአብርሃም ዕቅፍ የተቀመጠው ደሀ።
የማርታ እና የማርያ ወንድም I ጌታ ኢየሱስ ከሙታን ያስነሣው ሰው ነው።
(ዘጸ.6 I ዮሐ.11 I 12፥1 ሉቃ.16፥19)

591. **አልፋ (ግሪ) አሌፍ (ዕብ)**
የመጀመሪያ ማለት ነው።
የመጀመሪያው የግሪክ ፊደል ነው I በትዱስ መጽሐፍ አልፋ ወኦሜጋ ተብሎ ተገ ልጿል I የመጀመሪያው የዕብራይስጥ ፊደል አሌፍ ነው (ራእ. 1፥8 I 22፥13)።
በዚህ ስም ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ የኾኑት አባ አሌፍ የሚባሉት ይታወቁበታል።

592. **አሐዱ (ግእ)**
የመጀመሪያ መነሻ፤ አንድ ማለት ነው።
እንከሰኬ ኢኮኑ ክልኤተ አሳ አሐዱ ሥጋ አሙንቱ ። ትርጉም I እንኪያስ ኹለት አይደሉም አንድ ሥጋ ናቸው አንጂ (ማቴ. 19፥6)።
ያባት ስም አክሉ ቢል ይገጥማል።

593. **አመነ**
ተረዳ፣ አረጋገጠ፣ እውነት ነው አለ ...።
ያባት ስም ስናፍቀው ቢል ይገጥማል።
አመንኩ - አመነሺዋ - አመኑ

594. **አመዘነ - ሚዛን**
ወደ አንድ ወገን አደላ፣ ደፋ፣ አጋደለ።
የእውነት ሚዛን፣ መመዘኛ፣ መስፈሪያ።
(ዘሌ. 19፥36 ፤ ሕዝ. 45፥10)።
ያባት ስም እውነቱ ቢል ይገጥማል።

595. **አማለደ**
ከአዳ፣ ከጣጥ፣ ከመከራ አዳነ ...።
የጠመመውን አቅንቶ የጐደለውን ምልቶ አስማማ፣ አስታረቀ ማለት ነው።

596. **አማረ - አመርን - አማሩ**
ቆንጆ፣ ተወደደ፣ ደስ አሰኘ ፣ መልከ መልካም ውብ፣ ሽጋ ኾነ...(ዳን. 1፥15)።
ያባት ስም ስመኝ ቢል ይገጥማል።

597. **አማን** (ግእ)
አማን አማን አብለከ ! ከመ ዘነአምር ንነ ግር። ትርጕም ፤ እውነት እውነት አልህ ለሁ የምናውቀውን እንድንናገር ። (ዮሐ. 3፥11)። **አማኔ - አማንነሽ - አማኑ**

598. **አማኖ** (ዶር)
የሃይማኖት አባት ማለት ነው።

599. **አማከለ**
ከበበ፣ አመኸል የገባ ወገን ... ።
ኹለተኛ ልጅ ማለት ነው።
ያባት ስም ወዳጇ ቢል ይገጥማል።
አማከለኝ - አማከለው - አማከሉ

600. **አምሳሉ**
ምሳሌ የሌላ ነገር መግለጫ፤ አርአያ።
(ዘፍ. 1፥26 - 28)።
ያባት ስም ቢኾነኝ ቢል ይገጥማል።
አምሳሌህ - አምሳያ - አምሳያው - አምሳልህ

601. **አምባቸው - አምባህ**
ከፍታ ቦታቸው ፤ ቀበሌ፣ ማዶ ...።
ያባት ስም አንተህ ቢል ይገጥማል።
አምባው - አምባዬ - አምባ

602. **አምኃ** (ግእ) - **አምኃየስ**
ስጦታ (አጅ መንሻ) ማለት ነው። ወርቅ ዕጣን፣ ከርቤ ለጌታ አመጡለት ፤ (ማቴ. 2፥11)።
አምኃ ደስታ የራስ ደስታ ዳምጠው ልጅ ነበሩ። በጣሊያን ጦርነት ጦር ሜዳ ላይ ካባታቸው ጋር ላገር ክብር ተዋድቀዋል።
በስማቸው ትምህርት ቤት ተሰይሟል።
አምኃ ሥላሴ ከርስትና ስምን ተመልከት።

603. **አሞኘህ - አሞኘ**
አታለለህ ማለት ነው...። በፍቅሩ ገዛህ...።
ያባት ስም ባያሌው ቢል ይገጥማል።

604. **አሞጽ**
የሚሸከም ማለት ነው፤ ከነቢያት አንዱ ነው (ትን. አሞ. 1፥1)።

605. **አሥማረ**
ይቅር አሰኘ፣ ምሕረትን አሰጠ ...።
ያባት ስም መብራቱ ቢል ይገጥማል።
አሥማሩ - አሥማር

606. **አሠመረ - አሠመሩ**
አሰወደደ፣ አስፈቀደ አሺ አሰኘ።

ሠምረ - ወደደ፣ ፈቀደ ከሚለው የወጣ።
አሥመሮም (ትግ.) - **አሚምሬ**

607. **አሠጋኸኝ**
አስፈራኸኝ፣ አሳሰብከኝ ማለት ነው።

608. **አረማም** (ጉራ) አሿፊ ማለት ነው።

609. **አረጋ**
ልጅ ከወለደች በኋላ፤ ልጂ ረግቶ በባሏ ቤት ኦሮጥን መቀጠሏን፤ ልጁ በመወለዱ ረጋች ስማለት ...።
ያባት ስም በቃሉ ቢል ይገጥማል።
አረጋኸኝ - አረጋቸው - አረጋኸ - አረጉ

610. **አራርሶ** (ኦሮ)- **አራሬሳ - አራርሳ**
አስታራቂ (ዕርቅ) ማለት ነው ።

611. **አራደ** (አርወደ (ግእ)
አስፈራ፣ አንቀጠቀጠ፣ አብረከረከ ማለት ነው።

612. **አረጋዊ - አረጋይ**
በዚህ ስም የሚታወቁት፦ በደብረ ዳሞ የዘንዶ ጅራት ይዘው ተራራው ላይ የወጡ በቀድሞ ስማቸው ዘሚካኤል የሚባሉት ናቸው። በሕግንታቸው ሳሉ መንዙሰው አረጋዊ ተባሉ ። የልጅ አዋቂ እንደ ማለት ነው።

613. **አራጋው**
አጽናናው ፣ አበረታታው፣ አስተዛዝነው ማለት ነው። **አራጌ - አራጌው**

614. **አርከበ** (ትግ) ደረሰ ማለት ነው።

615. **አርአየ** (ግእ)
አሳየ ማለት ነው።
አርአየ እግዚአብሔር አድኅኖቶ።
እግዚአብሔር ማዳኑን አሳይ፣ አስታወቀ (መዝ.97(98)፥2 ፤ 92፥7)።

616. **አርአያ** (ግእ) **አራያ**
መልክ፣ ምስል ፣ አምሳል ፣ አይነት ፣ አካል አንድ ፤ ማለት ነው ።
ሰው በእግዚአብሔር አምሳልና መልክ ተፈጠረ (ዘፍ.1፥26)።
አርአያህ (አራያህ)
አርአያ ሥላሴ ከርስትና ስምን ተመልከቱ።

617. **አርገኔ** (ኦሮ) - **ኡርጌሳ**
አገኘሁ ማስት ነው ።

618. **አሮን** (ዕብ)
ብዙ ትርጕም አለው። ደብር (ተራራ) (መደብረ ደብር) የሚያበራ ብርሃን ማለት ነው። የሙሴ እና የማርያም ወን ድም፤ የመጀመሪያው የብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህን ነው (ዘጎ. 26፥59 ፤ ዘጸ. 6፥20)።

619. **አሰሙ**
ዐዲስ ነገርን፣ የምሥራችን፣ ከፍ አድርጋ ችሁ ተናገሩ፤ አዋጅ አውጁ ...።
ያባት ስም ዜና ቢል ይገጥማል።
አሰማኸኝ - አሰማው - አሰሜ
አሰማኝ - አሰማ

620. **አስግድ - አስግደው**
በዚህ ከሚታወቁት አንዱ በዐፄ ምኒልክ ዘመን ባላምባራስ አስግድ ቦረና ኼደው ከዳዊት በቀር ምንም ሳይዙ በዚያው የመ ነኑ መንፈሳዊ ሰው ነበሩ።
አስግዳቸው - አስገዶም(ትግ)- **አስግዱ**

621. **አሰፋ - አሰፌ**
ግዛቱን፣ ቦታውን ፣ ዝምድናን ...።
ያባት ስም በላቸው ቢል ይገጥማል።
አሰፋፋው - አሰፍኅ(ትግ) አሰፋው

622. **አሳመነ**
እውነቱን ዐሳወቀ ፤ አሰረዳ፣ ሐሰትን ከሕ
ደትን አራቀ ማለት ነው።
ያባት ስም በቃሉ ቢል ይገጥማል።
አሳመነው - አሳምን - አሳምናቸው

623. **አሳየኸኝ**
ችሎታኽን፣ ጀግንነትኽን፣ ዕውቀትኽን...
ያባት ስም ኅብረት ቢል ይገጥማል።
አሳየው - አሳዩ - አሳየኸ - አሳዬ

624. **አሴር** (ዕብ)
ደስተኛ ማለት ነው።
የልያ አገልጋይ ዘለፋ ከያዕቆብ የወለደ
ችው ስምንተኛው ልጅ ። ነቢይት ሐና
ከአሴር ወገን ነበረች (ዘፍ. 30፥12፤ ሉቃ.
2፥36)።

625. **አሰመላሸ**
የጠፋውን ያስመለሰ፤ ይሚያስመልስ፣ የተ
ወሰደውን ነገር አንዲመጣ አስደረገ
ማለት ነው (1ሳሙ. 30፥18)።

626. **አሰማማው - አሰማማቸው**
አስታረቀው፣ አገናኘው።
ያባት ስም ይበቃል ቢል ይገጥማል።

627. **አሰረሰ**
ያሰረሳህኝ፤ ማሰረሻ ማለት ነው።
አሰረሳህ - አሰረሳኸኝ - አሰረሳው

628. **አስተርአየ** (ግእ)
ገለጠ ፣ አሳየ፣ ተገለጸ ማለት ነው ።
(ዮሐ. 4፥18)
ያባት ስም ጽጌ ቢል ይገጥማል።
አስተርእዮ - አስተርእዩ

629. **አስተካከለኝ - አስተካከለው**
አኩል አረገኝ ።
ያባት ስም ላመስግን ቢል ይገጥማል።

630. **አስተዋይ — አስተዋለ**
አርቆ የሚመለከት፣ የሚገነዘብ ፤ ልቦናው
ብሩሕ።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

631. **አስታረቀ**
በመወለዱኹለቱን የተለያዩ ክፍሎች
አስማማ፣ አዋሐደ ...።

632. **አስታወሰኝ**
ያለፈን ትዝታ አመጣብኝ ። የረሳሁትን
ነገረኝ ።
ያባት ስም ወንድማገኝ ቢል ይገጥማል።
አስታወሰ - አስታወሳቸው

633. **አስቻለው**
ትእግሥት ሰጠው ።
ያባት ስም ስለወገን ቢል ይገጥማል።
አስቻለኝ - አስቻሌ

634. **አስናቀ**
በኹለት ይተረጎማል። አንዱ ማወዳደርን
ነው። የበለጠ ኾነ ቢል።
ያባት ስም ወንድሙ ቢል ይገጥማል።
አስናቀኽ - አስናቅ

635. **አስደነቀ**
አስገረመ፤ በችሎታው፣ በዕውቀቱ...።
ያባት ስም ሰሎታው ቢል ይገጥማል።

636. **አስፋወሰን**
ግዛትን ፣ ወሰንን አስፋ ማለት ነው።
በዚህ ስም የሚታወቁት የዐፄ ኀይለ ሥላ
ሴና ከእቴጌ መነን ከተወለዱት ከወንድ
ልጆች የመጀመሪያው ከነበሩት ልዑል
አልጋወራሽ መርዕድ አስፋ ወሰን (ዐፄ
አምኃ ሥላሴ) በዚህ ስም ይታወቁ ነበር።

637. **አስጨናቂ**
አስጠባቢ፣ አስቸጋሪ፣ ማለት ነው።
(ኢሳ. 14፥4)

638. **አሸራሕ** (ጉራ)
አስደሰተ ማለት ነው። **አሸረካ**

639. **አሸርቃ** (ጉራ) አዳነ ማለት ነው።

640. **አሸናፊ**
በችሎታው ፣ በጀግንነቱ ፣ በጥረቱ...።
ያባት ስም ነገሠ ቢል ይገጥማል።
አሸነፈ - አሸንፍ

641. **አሻግረው**
ካንድ ቦታ ወደ አንዱ ቦታ የሚያሻግር
ወይም ዋናተኛ ... ጅረቱን፣ መከራውን፣
ወደ አሳለፈው ፤ ማደ አውጣ።
ያባት ስም በጸሎት ቢል ይገጥማል።
አሻጋሪ - አሻገሩ - አሻግሬ

642. **አሸብር - አሸብሬ**
በጦርነት ጊዜ የተወለደ ... ። ፍጅ በጥ
ብጥ፣ አተረማምሰው ማለት ነው።

643. **አሸኔ**
ጠላትን አሸን (አሸናቸው) ፣ አስደግድጋ
ቸው ማለት ነው ። በዚህ ስም ከሚታወ
ቁት አንዱ ከዐፄ ምኒልክ አስከ ዐፄ
ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ድረስ የነ
በሩት ዐርበኛ ብላታ አሸኔ ኪዳነማርያም
አንዱ ናቸው ።

644. **አበራ - አበራው**
ጨለማው አስቀ ፤ አበቃ አሳየ፣ ገለጠ
ማለት ነው። ፊቁም እንደ ፀሓይ በራ ፤
ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ኾነ።
(ማቴ. 17፥2)
ያባት ስም ኮከቡ ቢል ይገጥማል።

645. **አበበ**
አበባ አብቦ ታየ ...።
በዚህ ስም ኢትዮጵያን ስዓለም ያሳወቀ
በኦሊምፒክ ማራቶን በ1953 ዓ.ም. በርም
ኹለተኛ 1957 ዓ.ም. ቶኪዮ ያሸነፈው
ሻንበል አበበ ቢቂላ ይታወቅበታል።
አበባው - አበባነህ - አበባዬ

646. **አበዙ - አበዛ - አበዛህ**
ብዙ ጨመሩ፣ ሠሩ ...።
ያባት ስም ቸርነት ቢል ይገጥማል።

647. **አቢጋዝ** (አበ - ጋእዝ)
የጦር አዝማች ፤ የንጉሥ ጦር ዋና አዛ
ዥ። አስቃ ደምሳሽ ፊታውራሪ፤ የሰልፍ
መሪ ማለት ነው።

648. **አበጀ - አበጇ**
ሠራ፣ አዘጋጀ፣ አሳመረ፣ አስዋበ፣ ማለት
ነው። አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው አን
ዲሉ። ኹለተኛው ትርጉም፤ ደግ አደረገ
ማለት ነው (ኢሳ. 61፥5)።
ያባት ስም በለው ቢል ይገጥማል።

649. **አብዲ - አብዲሳ**
በእምነት ማለት ነው።

650. **አቢቹ** (ኦሮ) የጎሳ ስም ነው።

651. **አባተ**
ባተ ካለው ግስ አባተ ይወጣል።
ባተ ከረምት፣ ከረምት ገባ፣ ዝመረ።
ዝመረ፣ አሸንፈ፣ በረታ ማለት ነው።
አብተው አሸንፈው ማለት ነው።

652. **አባቴነህ**
ያባቴ ምትክ ... ።
ያባት ስም ረታ ቢል ይገጥማል።
አባትነህ - አባትነበር - አባትኹን

653. **አባ-ጂፋር** (ኦሮ)
አባ በመጀመሪያ ልጅ ስም የአገሌ አባት ለማለት ይሰየምበታል ።
ለምሳሌ፦ የጂፋር አባት ። በዚህ ስም ይጠሩ ከነበሩት አንዱ የጅማ ገዢ እባ ጂፋር ናቸው (1870 - 1924 ዓ.ም.)።
አባ ሲጨመር የፈረስ ስምም ይኾናል
አባ ዶቢር - አባዶላ - አባቢያ
አባባሕሩ - አባቦሩ - አባቦሬ
አባቦር - አባተግም - አባተርፋ
አባነጋ - አባኦራ - አባዋሪ
አባዱራ - አባፊጣ - አባዝናብ
አባኮራን - አባኢያ - አባአለ
አባይለቅ - አባሜጫ

654. **አቤል**
የአዳምና የሔዋን ኹለተኛው ልጅ፤ የአቤል መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ ተወዳጅ ነበረ (ዘፍ. 4፥2፤ ዕብ.4፥13)።

655. **አቤሜሌክ** (ዕብ)
ንጉሥ እና የንጉሥ አባት ማለት ነው ። ነቢዩ ኤርምያስን ከሞት ያዳነ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ነው (ኤር. 38፥6–13)።

656. **አቤሴሎም** (ዕብ)
የሰላም አባት ፤ ሰላማዊ ። አባቴ ሰላም ነው ማለት ይኾናል ። የንጉሥ ዳዊት ሦስተኛ ልጅ ነው (2ኛ ሳሙ. 13)።

657. **አቤኔዜር** (ዕብ)
ረዳት፣ የረድኤት ድንጊያ፤
እስራኤላውያን ፍልስጥኤምን ባሸነፉ ጊዜ ነቢዩ ሳሙኤል ያቆመው እግዚአብሔርን የማመስገኛ ሐውልት ነው (1ኛ ሳሙ. 7፥12)

658. **አብርሃም** (ዕብ) **ኢብራሂም**(ዐረ)
የቀድሞ ሰሞ አብራም ነበር፤ ታላቅ አባት ማለት ነው።
እግዚአብሔር ግን ስሙን ቀይሮ አብር ሃም ትባላለህ አለው ። ይህም ማለት አበ ብዙኃን ፤ የብዙዎች አባት ማለት ነው (ዘፍ. 17፥1–18)።

659. **አብነት** (ግእ)
ፍቱን መድኃኒት ጤናን የሚሰጥ፣ የሚፈውስ ማለት ነው።
ምሳሌነት ምሳሌነት ማለት ነው።
ያባት ስም ይኹኝ ቢል ይገጥማል።

660. **አብዲ** (ኦሮ ዐረ) **አብዲሳ**
መመኪያ ተስፋ (ተስፋዬ) ማለት ነው።
አብዲሳ ኡጋ ዐርበኛ የነበሩ።

661. **አብድዩ** (ዕብ ዐረ)
የእግዚአብሔር አገልጋይ ማለት ነው።
ነቢይ ነው (1ኛ ሳሙ. 22)

አብዱ - አብደል (ዐረ) አገልጋይ ማለት ነው። (አብደል መሢሕ (ዐረ)) ገብረ ክርስቶስ ማለት ነው ። **አብደላ** አገልጋይ ማለት ነው።

662. **አቦ**
የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ስም በማኅ ጠር ሲጠራ **አቦ አቡየ** (አባቴ)

663. **አቦማ** (ኦሮ) - **አቦዬ**
ሥርዓት አስጠባቂ የሚቀጣ መሪ ማለት ነው።

664. **አቦዘነ**
አሳረፈ ፣ አስታጎለ፣ ሥራን አስፈታ ማለት ነው።

665. **አተረፈ - አተረፍን**
ከሞት አዳነ ፤ ትርፍ ዋጋ አስገኘ ...።
በተሰጠው ገንዘብ ነግዶ አተረፈ (ማቴ. 25 ፥15)።

666. **አቲከም** (ኦሮ)
አንተ የየት ነህ ማለት ነው።
በዐፄ ቴዎድሮስ እና በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት። በዚህ ስም የሚታወቁት ራስ ቢቶደድ መንገሻ አባት ከንቲባ አቲከም የሚባሉት ናቸው።

667. **አታክልት - አታክልቴ**
አበቦች፣ ዛፎች ልዩ ልዩ አይነት ተክሎች (ዘዳ. 11፥10 ፤ መክ. 2፥5 ፤ አሞ. 4፥9)።
ያባት ስም በቀለ ቢል ይገጥማል።

668. **አታመንታ**
አትዘናጋ፣ ይኾናል አይኾንም አትበል።
ያባት ስም አግዘው ቢል ይገጥማል።

669. **አትርሳው - አትርሳኝ**
አትዘንጋው፣ አስታውሰው...።
ያባት ስም **ልንገረው** ቢል ይገጥማል።

670. **አትሳ** (ዶር) አሳልፍ ማለት ነው።

671. **አትናቴዎስ** (ግሪ)
ዘላለማዊ ማለት ነው ።
በ325 ዓ. ም.በኒቅያ ጉባኤ ስለ ነገረ መለ ኮት አብራርቶ የተናገረ የቤተ ክርስቲያን አባት ነው ። በዚህ ስም ብዙዎች ተጠር ተውበታል፤ በተለይ ጳጳሳት ይጠሩበታል።

672. **አቻምየለህ – አቻሚ**
የሚተካከልህ ፣ የሚደርስብህ ፣ የሚመስ ልህ ፣ የሚወዳደርህ የለም ...።
ያባት ስም **በዕውቀት** ቢል ይገጥማል።

673. **አናንያ** (ግሪ) **ሲድራቅ** (ዕብ)
ከባቢሎን ነገሥታት አንዱ የነበረው ገና ናው ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ወሮ ሕዝ ቡን ዘምርኮ ወስዶ ለሣዖት ሰገዱ ካላቸው አንዱ አናንያ ወይም ሲድራቅ የሚባለው ነው (ዳን.3፥16 ፤ ሰን. ታኅሣ. ገጽ 392)።

674. **አናጋው**
አደበላልቀው ... ።
ያባት ስም **እንዳልክ** ቢልይገጥማል።

675. **አንለይ**
አንራራቅ፣ አንራቅ ... ።
ያባት ስም **ዘመድኩን** ቢል ይገጥማል።

676. **አንሙት**
አንኑር ፣ አንቆይ ... ።
ያባት ስም **አያዩ** ቢል ይገጥማል።

677. **አንግው**
ስለሱ አንናገር ፤ በአውነትም በሐሰትም አናንሳው ...።
ያባት ስም **ልንገርህ** ቢል ይገጥማል።

678. **አንሳር** (ጉራ)
ደስ የማይለው ማለት ነው።

679. **አንቀጸ** (ግእ)
መግቢያ ማለት ነው። አንቀጸ አባግዕ።
ትርጕም፤ የበጎች በር (ዮሐ. 10፥1)።
ያባት ስም **ብርሃን** ቢል ይገጥማል።

680. **አንበርብር - አንበርብሮ**
በርብር ፣ ውረር ፣ ያገኘኸውን ውሰድ ማለት ነው ...።
ያባት ስም **አያዩ** ቢል ይገጥማል።

681. **አንበሴ**
አንበሳ ትልቅና ብርቱ ግርማው የሚያስፈራ ተወዳጅ የኾነ ነው ።
የነገሥታት ምሳሌ ነው።
በቅዱስ መጽሐፍ ዳዊትና ንጉሣዊ ወገን ከይሁዳ ወገን የሚወለዱ የይሁዳ አንበሳ ደቦል (ልጅ) ተብሎ በትንቢት ተሰየመ (ዘፍ. 49፥9 ፤ ምሳ. 30፥29 ፤ ማቴ. 2፥5 ፤ ራእ. 5፥5)።
በግራቶን የሩጫ ውድድር ኢትዮጵያን ከወከሉት አንዱ አንበሴ ቶሎሳ በዚህ ሰም ይታወቃል ።
አንበሳው - አንበሰ - አንበሳ
አንበሰዬ - አንበሶ - አንበሳቸው

682. **አንተነህ**
በትጠበት የኖርከው? በብዙ ይተረጕማል።
ያባት ስም ንጉሤ ቢል ይገጥማል።
አንተንይሰሙ - አንተዓለም
አንተኹን - አንተኹነኝ

683. **አንድነት**
ኅብረትን እና ውሕደትን ያመለክታል።
በሰላም ማሠሪያ የመንፈስን አንድነት ስመጠበቅ ትጉ (ኤፌ. 4፥3)።

684. **አንድይኹን**
ይተባበር፣ ይስማማ፣ እንደ አንድ ሰው ተናጋሪ እንደ አንድ ልብ መካሪ ይኹን።
ያባት ስም **አገሬ፣ ባሳገር፣ ከተማው፣ መንግሥቴ** ቢል ይገጥማል።

685. **አንዳርጉ**
አስማሙ፣ አስታረቁ፣ አዋሕዱ
ያባት ስም **በላቸው** ቢል ይገጥማል።
አንዳርጌ - አንዳርግ - አንድነት
አንዳርጋቸው

686. **አንዱዓለም (አንዷለም)**
አንድ በሚለው ቅጽል ብዙ ሰም ሊሰየም ይቻላል ። **አንድ ሃይማኖት**
አንድሰው - አንድአምላክ
አንድዝጌር - አንዳገር

687. **አነገሥም** (ትግ) አንግሣቸው።
አንጋሥ (አሮ) አንጋሣ

688. **አንጅሉ** (ዶር)
መረቀ ማለት ነው ።

689. **አአላፍ** (ግእ) **አአላፍ ሰገድ**
መቶ ሺ ማለት ነው።
አአላፍ በየግንከ ወገቤከሰ ኢይቀርቡ ትርጕም ፤ በቀኝህ መቶ ሺ ይወድቃሉ ወዳንተ አይቀርቡም (መዝ. 90(91)፥7)።
ዐፄ ዮሐንስ ሰመ መንግሥታቸው አአላፍ ሰገድ ነበር (1660 - 1674 ዓ.ም.)።

690. **አአመረ** (ግእ) - **አአምሮ**
በወቀ፣ ዕውቀት ማሳወቅ ማለት ነው።
አአምሮ ሥላሴ ክርስትና ስሙ።

691. **አከበረኝ**
ከፍ ከፍ አደረገኝ ...።
ያባት ስም **ፍቅሬ** ቢል ይገጥማል።

692. **አካሌ - አካሉ - አካለወርቅ**
የኔ አካል ። ሰውነትን ያመለክታል።
ያባት ስም **ተዋሕዶ** ቢል ይገጥማል።
አካለ ሥሴ ክርስትና ስሙ።

693. **አከሊለ - አከሊሉ**
በዘውድና በራሥ ወርቅ መከበል ያለ፤ የክብር ሽልማት ማለት (ማር. 15፥17)።
በዚህ ሰም የተጠሩ ፕሮፌሰር አከሊሉ ለማ በቀንድ አውጣ አማካኝነት ለሚተላ ለፍ ብሊሃርዚያ ለተባለው በሽታ መድ ኃኒት ያገኙ የሳይንስ ጠበብት ናቸው።
አከሊል ሰጠኝ
አከሊለ ሰማዕት ክርስትና ሰምን ተመልከት።

694. **አወጣኝ - አወው - አወጣኸኝ**
ከመከራ፣ ከችግር፣ ከጭንቀት፣ ከጉድጓድ ፣ ከጉድ ...።
ያባት ስም **ሰንሻው** ቢል ይገጥማል።

695. **አውግቸውው**
ተናግሬውት አልፎ አውርቼው ...።
ያባት ስም **ቢሰጠኝ** ቢል ይገጥማል።
አወጉ - አውጋቸ

696. **አዋየነህ - አዋየ**
አነጋገርነህ ፣ አስተዛዘንህ፣ አማከርንህ።
ያባት ስም **ትዝታ** ቢል ይገጥማል።

697. **አውላቸው**
ቀኑን ሙሉ፣ አቆያቸው ... ።
ያባት ስም **ደጀኔ** ቢል ይገጥማል።

698. **አውራሪስ**
ተወዳጅ የኾነ ጎይለኛ ተዋጊ በሬ መሰል አንስሳ ፤ ቀንዱ አፍንጫው ላይ የበቀለ ነው ።
ያባት ስም **ተፈራ** ቢል ይገጥማል።

699. **አውሳብዮስ** (ግሪ) **አውሳቤ**
በዘመነ ሰማዕታት መንፈሰ ቅዱስ የተመላች አውሎፊያ የምትባል የሶርያ መስፍን ልጆች ከኾኑት አውሳብዮስ ከሚባሉት አንዱ ነበር (ሰከ. የካ.13 ገጽ 774)።

700. **አዘዘው - አዘዘ**
በሥራ፣ በገንዘብ ቀርጥ ቃል ሰጠ ።
ይኹን ፣ ይደረግ አለ ...።
ያባት ስም **ክህነት** ቢል ይገጥማል።

701. **አዛርያስ** (ዕብ)
አግዚአብሔር ረዳ ማለት ነው።
የካህኑ የሳዶቅ ልጅ ካህኑ አዛርያስ በሰሎሞን ቤተ መቅደስ ያገለግል ነበር።
በኋላ የንግሥት ሳባና የሰሎሞን ልጅ ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ ታቦተ ጽዮንን ወደ ኢትዮጵያ ይዞ የተጓዘ ነው (1ኛ ነገ. 4፥2 ፤ 1ኛ ዜና. 6፥9 ፤ 2ኛ ዜና. 26፥17–20)።

702. **አዛርያ** (ግሪ) **አብድናጎ** (ዕብ)
አዛርያ ማለት ረድኤት ማለት ነው።
ከባቢሎን ነገሥታት አንዱ ገናናው ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ወሮ ሕዝቡን በምርኮ ወስዶ ለማያት ሰገዱ ካላቸው አንዱ አዛርያ ወይም አብድናጎ የሚባለው ነው

ከእሳቱም ውስጥ ቅዱስ ገብርኤል ካዳና ቸው ወጣቶች አንዱ (ዳን.3፥16 ፤ ሰን. ታሳሣ. ገጽ 392)።

703. **አዛውንት**
ትልቅ ሰው ፤ አስታራቂ ፣ ሽማግሌ...።
ያባት ስም ጨመልስ ቢል ይገጥማል።

704. **አዝመራ**
መከር ወይም ያጨዳ ወቅት (ማቴ. 13፥39፤ ሉቃ. 10፥2፤ ሩት 1፥22)።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።
አዝመራዬ - አዝመራው

705. **አዝማች – አዝምቴ - አዝምት**
በፊት በፊት ይዞ የሚጓዝ ፊታውራሪ ...።
ያባት ስም ተፈራ ቢል ይገጥማል።

706. **አዝዋኘ** (ጉራ)**አማረ** ማለት ነው

707. **አየ'ኹ – አየ'ኩብርሃን**
ያባት ስም ደሳለኝ ቢል ይገጥማል።
አየ'ኩብዙ - አየ'ኩኔ - አየ'ኩዓለም
አይተነው - አየልኝ - አየነ
አየናቸው - አየነው - አይቼኽ
አይቼው - አይነቴ - አየው - አዩኽ

708. **አያልቅበት**
አይፈጸምበት፣ አይቸግረው ...።
ያባት ስም ብሩ ቢል ይገጥማል።

709. **አያና** (ኦሮ)
ዕድለኛ ፤ መልአክ ማለት ነው።
አያናው - አያንሳ - አያንቱ - አያኖ

710. **አይሳነው - አይሳን**
ኹሉን ማድረግ፣ መጀመርና መፈጸም..።

711. **አይተንፍሱ**
ጠላቶች ዝም ይበሉ፤ ጥቂትም አይናገሩ ማለት ነው።

712. **አይችሉኽም - አይችሉም**
አይወዳደሩህም፣ ታሸንፋቸዋለህ ...።
ያባት ስም በዕውቀት ቢል ይገጥማል።

713. **አይክ** (ዶር) ያዘው ማለት ነው።

714. **አይደፈር**
የሚችለው የለም ...።
ያባት ስም ድንበሩ ቢል ይገጥማል።

715. **አይጠገብ**
ታይቶ፣ ተሰምቶ፣ ተበልቶ ተጠጥቶ ...።
ያባት ስም ፍቅሩ ቢል ይገጥማል።

716. **አደላ - አደላህ**
ለራሱ፣ ለወገኑ፣ አዘነበለ ...።
ያባት ስም ወገኔ ቢል ይገጥማል።

717. **አደራጀው**
በሀብት፣ በገንዘብ፣ በእምነት እንዲያድግ እንዲቋቋመው አደረገው።
ያባት ስም ባያሌው ቢል ይገጥማል።

718. **አደፍርሰ - አደፍርሰው**
አሸብር፣ አሸብረው ፤ ደባልቀው ፣ አቀ ላቅለው ...። ማለት ነው።
ያባት ስም ቢተው ቢል ይገጥማል።

719. **አዱኛ** (ኦሮ)
አደን ከሚለው ግስ የወጣ ነው።
ሀብት ንብረት ጌትነት፣ ክብር ፣ ልዕልና ማግኘት ማለት ነው።
ያባት ስም ታከለ ቢል ይገጥማል።

720. **አዳም**
የመጀመሪያው ሰው የሚጠራበት።
የስሙ ትርጉም ቀይ፤ የቀይ ዳማ ከመረራ ጭቃ የተገኘ ከመሬት የተፈጠረ ማለት ነው። ሰዎችን ኹሉ ያመለክታል። (ዘፍ. 1፥26 ፤ 2፥19 ፤ 3፥19) ።
አዳምጤና - አዳሙ - አዳምሰገድ
(ወሌ ፋሲል) - **አደም** (ወረ)
አደመ (ግእ) **አማረ** ማለት ነው።

721. **አዳነ**
የማዳን ሥራ ከአግዚአብሔር ወይም ከሚወለደው ወይም ከሌላው ከፍል ሰለተ ፈጸመ ይህ የስም ስያሜ ይሰጣል።
አዳነኝ - አድነው - አዳና - አዳኜ
አድኑ - አድኅኖም (ትግ)- **አድናቸው**

722. **አድርሴ** (ጉራ) **አድርሰ**
አድርሳቸው ማለት ነው።

723. **አድማሰ – አድማሱ**
ሰማይና ምድር የተገናኘ የሚመስለው የም ድር ዳር ፤ የምሥራቅ ጮራ ስትፈነጥቅ የሚታየው ወጋገን ማለት ነው።
ያባት ስም ወሰኔ ቢል ይገጥማል። **አድ ማሴ - አድያም ሰገድ** (ወሌ ኢያሱ)

724. **አድኅልኝ**
ጤና ኾኖ በሰላም ካደገ ስማለት ...።

725. **አገሬ** (ግእ)
የተወለድክበት፣ ዐታዬ፣ የምወደው ...።
ያባት ስም ይልማ ቢል ይገጥማል።
አገር-ዓለም - አገርነኽ
አገር-አቀኑ - አገር

726. **አገኘኹ - አገኘ - አገኙኽ**
በዚህ ስም ይታወቁ የነበሩት ሠዓሊና ገጣሚ አገኘሁ እንግዳ ነበሩ።

727. **አገዘ - አግዘው**
ከዕርዳታ ጋር የተገናኘ ስም ነው ።
ያባት ስም ቸሩ ቢል ይገጥማል።
አገዘው - አግዜ - አግዛቸው

728. **አግባው - አግባቸው**
ከተተው፣ ወደ መኸል ጨምረው ...።
ያባት ስም በጊዜው ቢል ይገጥማል

729. **አግናጤዎስ** (ግሪ)
የሐዋርያት ተከታይ የኾነ ሊቀ ጳጳስ ፤ በሕግነቱ ጌታ እግር ላይ ተቀምጦ የነበረ ነው ተብሎ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይታ ወቃል (ማቴ. 19፥14)።

730. **አግደው – አግዳቸው - አግዱ**
ከጠላት ጠብቃቸው አሰማራው ...።
ከልክሉ፣ ጠብቁ፣ ማለት ነው።
በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በዐዲስ አበባ የከተማውን ገበያ ለመጀመሪያ ጊዜ ሥርዓትና ንግዱን ያስፋፉ፣ ለመንግሥት ቀረጥ እንዲገባ ያስደረጉ፤ ጉምሩክን የመ ሠረቱ ነጋድራስ አግደው ይባሉ ነበር።

731. **አጉናፍር**
አጉነ - አጉነፈረ ...።
ያባት ስም በለው ቢል ይገጥማል።

732. **አጓጓኸኝ**
ምራቁን አስዋጥከኝ ...።
ያባት ስም ዘገየ ቢል ይገጥማል።

733. **አጥላው**
ጥላውን፣ ጥላኽን ጋርደው፣ ድባቡን ...። ያባት ስም ድባቤ ቢል ይገጥማል።
አጥላባቸው - አጥላቤ

734. **አጥናፌ**
ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ሲል ፤ ከዳር እስከ ዳር ማለት ይኾናል።
በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በአደዋ ዘመቻ ጊዜ የታወቁ ዐርበኛ ቢቶወደድ አጥናፌ ይባሉ ነበር ።
ያባት ስም አድማሰ ቢል ይገጥማል።
አጥናፍ ዓለም - አጥናፉ (አጽናፉ)
አጥናፍ ሰገድ (ዐፄ ገላውዲዎስ)

735. **አጽብሐ** (ግእ)
ከኢትዮጵያ ነገሥታት በፍቅር የገዙ ወን ድማማቾች **አብርሃና አጽብሐ** ይባሉ ነበር ። መታሰቢያቸው ጥቅምት አራት ቀን ይከበራል (ስንሳር)። በዘመናቸው ክር ስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባበት ዘመን ነበር አብርሃ ቀድሞ ስለሞተ አጽብሐ ግዛቱን ይዞ ብቻውን ቀጠለ (340 ዓ. ም.)።

736. **አፀደ** (ዐማ)
አጨደ ማለት ነው። **አፀደ ወይን** የአትክልት ቦታ ። ዐጸደን ተመልከት።

737. **አፈራ - አፈራው**
ፍሬ ፣ ዘር ማግኘት፤ ተማረን አፈራ ...። ያባት ስም በጊዜው ቢል ይገጥማል።

738. **አፈወርቅ - አፈወርቂ** (ትግ)
በዚህ ስም የሚጠራው የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ነው። በስብከቱ ጣዕም የተነሣ ምእመናን ያወጡለት ስም ነው (ስንግን. 12 ገ. 207)።

739. **ኤርጋ** (ጉራ) - **ኤርጋሞ**
የተጠጋ ማለት ነው ።

740. **ኤርጌ (ኦሮ) - ኤርጌሳ**
ሽቶ ወይም ጥሩ የሚሸት ማለት ነው።

741. **ኢሳይያስ** (ዕብ)
እግዚአብሔር ደኅንነት ነው ማለት ነው። ከታላላቆች ነቢያት አንዱ ነው። በንጉሡ ዖዝያን፣ በኢዮአታም፣ በአካዝ፣ በሕዝቅ ያስ ዘመን ነበር።
ይህ ስም በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተለ መደ ነው (ኢሳ. 1፥1)።

742. **ኢብሳ** (ኦሮ) ብርሃኑ ማለት ነው።

743. **ኢብኑ-መለክ** (ዕብ. ግእ)
የንጉሥ ልጅ ማለት ነው።
ንግሥት ሳባ ማይበላ በሚባለው ቦታ ስት ደርስ ወንድ ልጅ ወለደች ። ልጁም የን ጉሥ ስሎሞን ልጅ ስለኾነ ። ኢብነመ ለክ አለችው ። **ኢብኑ-ሐኪምን ፣ ምኒ ልክን** ተመልከት።

744. **ኢቲሳ (ኦሮ)**
ከልካይ ማለት ነው። አቡነ ተክለሃይ ማኖት የተወለዱበት ቦታ ።

745. **ኢትዮጵያ - ኢትዮጲስ**
ኹለተኛው የኩሽ ስም ነው ። በግሪክ ኢትዮጲስ ይባላል።

746. **ኢካ** (ዶር) ዘለለ ማለት ነው።

747. **ኢዩኤል**
እግዚአብሔር አምላክ ነው ማለት ነው። ከነቢያት አንዱ ነው (ኢዩ.1፥1)።

748. **ኢያሱ** (ዕብ)
እግዚአብሔር አዳኝ መድኀኒት ነው። ከሙሴ ቀጥሎ ሕዝበ እስራኤልን ተስፋዋ አገር መርቶ ያደረሰ ነው (ዘጸ. 33፥11)።

749. **ኢያቄም** (ዕብ.)
እግዚአብሔር መሥርቷል (የእግዚአብሔ ር ገንዘብ) ማለት ነው። የቅድስት ድንግል ማርያም አባት እና ሌሎችም በዚህ ስም ተጠርተዋል (2ኛ ነገሥ. 23፥34–24፥6)።

750. **ኢዮስያስ** (ዕብ)
እግዚአብሔር ይደግፋል ማለት ነው ። የይሁዳ ንጉሥ የንጉሥ አሞጽ ልጅ ነበር። የስምንት ዓመት ልጅ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ 31 ዓመት በእስራኤል ነገሠ። ከዳ ዊት ቤት ከነበሩት መልካም ነገሥታት የመጨረሻው ነው (1ኛ ነገሥ. 13፥2)።

751. **ኢዮቤል** (ዕብ.)
በዓለ ሃምሳ ከሰባት ሱባኤ ወይም ከ 49 ዓመት በኋላ ዐምሳኛው ዓመት (ዘሌ. 25፥1)።

752. **ኢዮአታም** (ዕብ)
እግዚአብሔር ፍጹም ነው ማለት ነው። የጌዴዎን ታናሽ ልጅ (መሳ. 9፥5)። ኹለተ ኛው 12ኛ የይሁዳ ንጉሥ ነው (ኢሳ.1፥1)።

753. **ኢዮብ** (ዕብ)
ብዙ መከራ የደረሰበትና የታገሠ እግዚአ ብሔርን ያከብር ሰው ነው (ኢዮ.1፥1)።

754. **ኤልሳዕ** (ዕብ.)
እግዚአብሔር ደኅንነት ፤ መድኀን መድኅ ኒቴ ማለት ነው (1ኛ ነገሥ. 19፥16 ፤ 2ኛ ነገ. 3፥11)።

755. **ኤልኤዜር** (ዕብ.) (አላዛር)
እግዚአብሔር ረድኤት ነው ማለት ነው። የአብርሃም ቤት መጋቢ፤ አብርሃም ለልጁ ለይሥሐቅ ሚስት እንዲያመጣለት ወደ መስጴጦምያ ላከው ። በጸሎት እግዚአብ ሔርን ስምኖ ርብቃን አገኘ (ዘፍ. 15፥2፤ 24፥1)።

756. **ኤልሳዕ** (ዕብ)
እግዚአብሔር ደኅንነት ነው ማለት ነው። በኤልያስ እንደተጠራ ሥራውን ትቶ እየ ተከተለ ያገለግለው ነበር ። አ ልያስ በሰረ ገሳ በተወሰደ ጊዜ አየው። የኤልያስም መንፈስ ዐረፈበት። (1ነገሥ. 19፥16 ፤ 2ነገሥ. 3፥11 ፤ 2፥1 ፤ 4 ፤ 5 ፤ 6)

757. **ኤልያስ** (ዕብ.)
እግዚአብሔር ጎያል ጉልበቴ ነው ፤ ያድ ነናል (ዐቃቤ ሀገር) ማለት ነው። ኤልያስ በቅዱስ መጽሀፍ በብዙ ቦታዎች ተጠቅሶ አል ። (ማቴ. 11፥14 ፤ ማር. 8፥28) ኹለተኛው የሰሙ ትርጉም የወይራ ዘይት ማለት ነው (1ኛ. ነገሥ. 17፥1)።

758. **ኤልያቄም** (ዕብ)
እግዚአብሔር ያስነሣል ማለት ነው። (ኢሳ. 36፥3–22)። በዚህ ስም ብዙዎች ተጠርተዋል።

759. **ኤሬ** (ዶር) ዘዴኛ ማለት ነው።

760. **ኤርምያስ** (ዕብ)
እግዚአብሔር ርኅሩኄ አለው ከፍ ያደር ጋል ማለት ነው ፤ ከታላላቆቹ ነቢያት አንዱ ነው ። ኹለተኛው መጽሐፉ ሰቆ ቃወ ኤርምያስ ነው (ኤር. 1፥1)።

761. **ኤቲሳ** (ዶር) ብርሃኑ ማለት ነው።

762. **ኤቢሳ** (ኦሮ) - **ኤቢሶ**
የተመረቀ፣ ምርቃት ማለት ነው።
ኤባ - ኤብሳ

763. **ኤዶም** (ዕብ) - **ኤዶምያስ**
ቀይ ማለት ነው።
የኤሳው ስምና አገር (ዘፍ. 25፥30፤ ኢሳ. 63፥1፤ መዝ. 59) ለስሙ ትርጉም ካልኾነ በስተቀር ቡኩርናውን ስለሸጠ ብዙዎች ሲጠሩበት አይሰማም ።
ዓዶም (ዓደን) ገጽ 177 ቁ. 731 ተመልከት።

764. **ኤጀርሳ** (ኦሮ.)
ወይራ ፣ ጠንካራ ማለት ነው ።
በሐረር ዐፄ ጎይለ ሥላሴ የተወለዱበት ቦታ ኤጀርሳ ጎሮ በመባል ይታወቃል።

765. **ኤፍሬም** (ዕብ)
እግዚአብሔር በመከራዬ አገር አፈራኝ ማለት ነው። በግብጽ አገር **ዮሴፍ ከአስ ናት የወለደው ዅለተኛ ልጅ** በያዕቆብ በቀኝ በኩል የተባረከው ነው (ዘፍ 41፥52)። ውዳሴ ማርያምን የደረሰው ሶሪያዊው **ቅዱስ ኤፍሬም** በዚህ ስም ይታወቃል

766. **አልፍነኽ** = ብዙነህ ማለት ነው።

767. **አሙን** (ግእ) **አምነት - አምነቱ**
ታማኝ፣ የታመነ የተረዳ ማለት ነው።
ሰው በአምነት ሲኖር በእግዚአብሔር ቃል ይመራል። በተስፋ ይኖራል (ሮሜ. 4፥16 ፤ ዕብ. 11)። **አሙንነኽ** -

768. **አምሩ** (ግእ) - **አምሬ**
አእመረ ዐወቀ ከሚለው ግስ የወጣ ነው።
ምልክቱ፣ ጫፉ ፣ አሻራው ማለት ነው።
በዚህ ስም የቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ዘመድ አና ዐብሮ አደግ የነበሩት **ልዑል ራስ አምሩ** ኃይለ ሥላሴ አንዱ ናቸው።

769. **አምሻው - አምሻህ**
አምፈልገው፣ አምናፍቀው፣ አምጓጓው።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

770. **አምቢአለ**
አልፈልግም፣ አልሻም፣ አያሻኝም ...።
ያባት ስም በዕድሉ ቢል ይገጥማል።

771. **አምአአላፍ**
ከመቶ ሺዎች ማለት ነው።
ያባት ስም ኀሩይ ቢል ይገጥማል።
አአላፍ - አልፍነህ

772. **አምኩሉ** (ግእ)
ያባት ስም ይጌይስ ቢል ይገጥማል።
ከኹሉ ይሻላል ማለት ነው።

773. **አሱባለው**
አሱበተናገረው፣ አሱበፈቀደው ...።
ያባት ስም **ዋለልኝ** ቢል ይገጥማል።
አሱንዳለ - አሱነው - አሱነህ
አሱያውቃል

774. **አሳቱ - አሳቴ**
ኃይለኛው ፣ የሚፋጀው፣ የሚሞቀው ...።
ዘፋኙ አሳቱ ተሰማ በዚህ ስሙ ይታወቃል

775. **አሴይ** (ዕብ)
የኢዮቤድ ልጅ የዳዊት አባት። አያቶቹ ቦኤዝና ሞአባዊቷ ሩት ነበሩ። (1ሳሙ. 16 ፥1 ፤ 17፥12 ፤ 1ዜና. 2፥12)።

776. **አሰራኤል** (ዕብ.)
ከእግዚአብሔር ጋር ይታገላል ያሸንፋል ማለት ነው ፤ በዚህ ስም የተጠራው ያዕቆብ በኋላም ለልጆቹ 12ቱ ነገድ የተሰጠ ስም ነው (ዘፍ. 32፥22–32)።

777. **አሰከጊዜው**
ዘመንን የሚወሰን ጊዜ ።
ያባት ስም ድረስ ቢል ይገጥማል።
አሰከዚያው - አሰከላለም

778. **አሰጢፋኖስ** (ግሪ) (አሰጢፎ)
የሚያበራ አክሊል ማለት ነው ።
ሐዋርያት ከመረጧቸው ከሰባቱ ዲያቆናት አንዱ ሊቀ ዲያቆን ነበር። የሰማዕታትም መጀመሪያ ነው (የ.ሥራ 6፥5)።
(ቀዳሜ ሰማዕት)

779. **አሰክንድር** (ግሪ)
ተከላካይ ማለት ማንኛውንም ክፉ ነገርን የሚያርቅ ወይም የሚቃወም ማለት ነው።
የመቄዶንያ ንጉሥ፤ የፊልጶስ ልጅ በግሪክ አገር የተወለደ (ዳን. 8፥21) ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት የነበረ ገናና ንጉሥ (356 ዓ. ዓ.)።

780. **አሸቱ - አሸቴ - አሸትዓየሁ**
በአጅ ተቀጥፎ የሚበላ የበሰለና የጎመራ አዝል (ዘዳ. 23፥25 ፤ ማቴ. 12፥1)።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።

781. **አሸታው**
ፈቃደኝነቱ ...።
ያባት ስም ይበቃል ቢል ይገጥማል።

782. **አናውጋው**
እንጨዋወተው ፣ እንተርከው ...።
ያባት ስም ተመስገን ቢል ይገጥማል።

783. **አንየው**
እንመልከተው፣ ሥራውን እንይ ...።
ያባት ስም እውነቱን ቢል ይገጥማል።
አንታይ - አንያቸው - አኔምአየኹ

784. **አንቻለው**
አንታገሠው፣ እንሸከመው ...።
ያባት ስም **ፍቅሬ** ቢል ይገጥማል።

785. **አንደራሴ - አንደሰው**
አንደአኔ ኾኖ ማለት ነው ...።
ያባት ስም ይግዛው ቢል ይገጥማል።

786. **አንደሻው - አንደልቡ**
አንደፈለገ ፣ አንዳፈቀደው ...።
ያባት ስም በየነ ቢል ይገጥማል።
አንደብልኃቱ - አንደታየኹ - አንደኔ
አንደዋጋው - አንደዝናው - አንደገና

787. **አንዳስ - አንዳሉ -አንዳልካቸው**
አንደፈቀደ ፣ አንደተናገረ ...።
ያባት ስም ረታ ፣ አመኑ ይገጥማል።
አንዳስልኝ - አንዳስማሁ - አንዳስም
አንዳስጌታ - አንዳላማው- አንዳላፍር
አንዳልሳባ - አንዳልክ - አንዳልጓጓ
አንዳመኹኔ - አንዳወርቅ - አንዳወቀ
አንዳይከፋኝ - አንዳገር

788. **አንዳይላሉ**
ነቅተው፣ ተግተው፣ ጠንክረው ይኑሩ ማለት ነው።

ወ

789. **አንድርያስ** (ግሪ)
ኃያል ፣ በኩር ይበልጣል ማለት ነው።
የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ ወንድም ከዐሥራ ዅለቱ ሐዋርያት አንዱ (ዮሐ. 1፥44)።

790. **እንግዳ**
ዐዲስ ወይም ከሌላ ወገን የመጣ ...።
(ዕብ. 11፥13 ፤ 1ጴጥ. 2፥11)
ላገሩ ባዳ ስሰው እንግዳ እንዲል።
ያባት ስም በዛብህ ቢል ይገጥማል።
እንግዳወርቅ - እንግዱ - እንግዳየ
እንግዳሸት - እንግዳው
እንግዳአየሁ - እንግዳወሰን

791. **እውነቱ - እውነት**
ለሕተት የሌለበት ትክክለኛ።
(ቲቶ. 1፥1 ፤ ሮሜ. 1፥19 ፤ ዮሐ. 1፥14)።
ያባት ስም ገነነ ቢል ይገጥማል።

792. **እዛና (እይዛና)**
በኢትዮጵያ ነግሦ የነበረው የነገሥታቱ
የአብርሃ እና የአጽብሐ አባት ነው። የግ
እዝ ፊደልን ቅርጽ አሻሽሎ እንደ ግሪኩ
ከግራ ወደ ቀኝ እንዲጻፍ አድርጓል።

793. **እያዩ - እያቸው**
አየተመለከቱ ...።
ያባት ስም ታረቀኝ ቢል ይገጥማል

794. **እጅግአየኹ**
የበለጠ ነገር፣ የተዋበ ነገር አየሁ ...።
ያባት ስም ብዙነህ ቢል ይገጥማል
እጅግነኽ - እጅጌ - እጅጉ
እጅግሰግኹ - እጅግ

795. **እጓለ** (ግእ) - **እጓለጽዮን**
እጅ ማለት ነው። የጽዮን **እጅ**
ደቂቀ እጓለ እመሕያው እስከ ማእዜኑ
ታከብዱ ልበክሙ ። ትርጕም ፤ እናንተ
የሰው ልጆች እስከ መቼ ድረስ ልባችኹን
ታከብዳላችሁ (መዝ. 4፥2 ፤ ዮሐ.1፥52)።

796. **እሳና** (ኦሮ)
በላይህ ማለት ነው።
አሳ - አሳኔሳ - አሳኖ- አሳኒ - አሱማ

797. **አብሳ** (ኦሮ)
ቻይ ትዕግሥት ማለት ነው።

798. **አቶሮ** (ዶር) ቀብራራ ማለት ነው።

- ከ -

799. **ከሃሊ** (ግአ) **ከሃሉ**
ታጋሽ፣ ከህለ ቢል ቻለ ታገሠ። የሚችል
ቻይ፤ ጎይለኛ ብርቱ ማለት ነው
(ሩት. 2 ፤ ሉቃ. 24፥9፤ ፊልጵ. 4፥12)።

800. **ከለላ**
መኪታ ፣ ቅጥር ፣ መጋረጃ ፣ ከመከራ
ሸፈነ ፣ አዳነ ...።
ያባት ስም ፍቅሩ ቢል ይገጥማል።
ከለለው - ከለለ - ከልል - ከለላዬ

801. **ከለቻ** (ኦሮ)
በገዳ ሕግ ውስጥ የሚገኝ ሕግ ነው።

802. **ከልላ** (ዶር) ጥጋቡ ማለት ነው።

803. **ከልካይ - ከልከል - ከልከለው**
አይቻልም አይኾንም ባይ ...።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

804. **ከሠተ** (ግአ)
ግልጥ ኾኖ ታየ ፤ ገለጠ ማለት ነው ።
ወተከሥተ አዕይንቲሆሙ ወአእመርዎ።
ትርጕም፤ ዐይናቸው ተገለጠና ዐወቁት
(ሉቃ. 24፥31)።

805. **ከሣቴ ብርሃን - ከሣቴ** (ግአ)
ፍሬምናጦስ የኢትዮጵያ ጳጳስ ኾነው ከመ
ጡ በኋላ ከሣቴ ብርሃን ተባሉ ። ይህም
ማለት በጨለማ የሚኖር ሕዝብ ብርሃን
አየ እንደተባለው፤ ለኢትዮጵያውያን የወ
ንጌል ብርሃንን ስለአበሩ ነው።
(ማቴ. 4፥16 ፤ ኢሳ. 9፥2)።
ፍሬምናጦስን እና ሰላማን ተመልከት።

806. **ከበረ**
ተሾመ፣ ተሸለመ፣ ማዕርግ አገኘ።
ያባት ስም ስሜ ቢል ይገጥማል ።

807. **ከበበ - ከበበው**
ዙሪያውን ያዘ ፤ ዙሪያውን አጠረ ...።
ያባት ስም ጸጋ ቢል ይገጥማል ።

808. **ከበደ**
ከበረ ማለት ነው።
በሚዛን፣ በቍጥር እና በግርማ ሞገስ ፣
በሀብት የከበረ፤ የሚበልጥ ማለት ነው።
(ሳሙ. 14፥26፤ ሲራ. 22፥14፤ ኢዮ.6፥3)።
ከበዱ - ከበዶም(ትግ)

809. **ከተማ – ከተማው**
የደመቀ፣ የገዙዎች መኖሪያ ...።
ያባት ስም ጋረደው ቢል ይገጥማል።

810. **ከፈኒ** (ግአ. ኦሮ)
ልብሴ ማለት ነው። **ከፈና - ከፈያ**

811. **ከፈለኝ**
ካሰኝ፣ ዋጋ ሰጠኝ፣ ተካልኝ ...።
ያባት ስም በላይ ቢል ይገጥማል።
ከፍአርጋቸው - ከፍያሉ
ከፍያለው - ከፍይበሉ - ከፍያለ

812. **ኩማ** (ኦሮ) ሺ ማለት ነው።
ከመልቻ - ኩሚ - ኩምሳ - ኩመራ

813. **ኩራባቸው**
ኮፍነን ፣ ጅንን በልባቸው ...።
ያባት ስም በጊዜው ቢል ይገጥማል።
ኩሩ - ኩራቱ - ኩራልኝ
ኩርይ - ኩራ - ኩራን ተመልከት።

814. **ኩፋ** (ኦሮ) ወደቀ ማለት ነው።

815. **ኩሉ** (ግአ) ኹሉ ማለት ነው።
ኩሉብርሃን

816. **ኪሮስ** (ግሪ)
በዚህ ስም አመቤታችን ቅድስት ድንግል
ማርያም በሥዕሏ ተገልጻ ያነጋገረችው
ጻድቀኖ መነኩስ እባ ኪሮስ በመባል የሚ
ታወቁ ጻድቅ ናቸው (ስን. ሐም. 8 ገጽ. 5
35–541)።

817. **ኪሩቤል** (ዕብ.) **ኪሩብ**
መንበር ተሸካሚዎች መላእክት፤ ሰማያው
ያን ፍጥረቶች ናቸው። አዳም በኀጢአት
በወደቀ ጊዜ ወደ ዔዴን ገነት ለመመለስ
እንዳይችል መንገዱን ይጠብቁ ዘንድ እግ
ዚአብሔር ኪሩቤልን አኖረ (ዘፍ.3፥24)።

818. **ኪነጥበብ**
የልዩ ልዩ ተግባረ አድ የዜማ፣ የድርሰት፣
የዘፈንም ሙያና ሥራ ። ብዙ ሰው ይጠ
ራበታል (ዘጸ.20፥4 ፤ 35፥30)።
መጊሙር ዘማሪ **ድምፂዊ ዲያቆን ኪነጥ**
በብ ወልደ ቂርቆስ በዚ ስሙ ይታወቃል።

819. **ኪያ** (ኦሮ) የእኔ ማለት ነው።

820. **ኪዳነ** (ግእ) **ኪዳኔ**
የተዋዋልኩት ቃሌ ማለት ነው።
ተከየደ ከለው የወጣ ነው። ተዋዋለ፣ ቃል ኪዳን ተጋባ፣ ተማማለ ማለት ነው።
(ዘዳ. 29፥1 ፤ ኤር. 31፥31 ፤ 32፥33)።
ኪዳነ ወልድ (ዮሐ. 8፥51)።
ኪዳነ ማርያም ከርስትና ስም።
ኪዳኑ - ኪዳኔ - ኪዳኒ - ኪዳን
ኪዳነ ወልድ (ከር)

821. **ካሳዬ**
በጠፋው ምትክ ተተክልኝ፣ ዋጋ ሰጠኝ...።
ያባት ስም ዘገየ ቢል ይገጥማል።
ካህሱ - ካሳ - ካሱ - ካሰኝ
ካሰው - ካሳኹን - ካህሣዬ (ትግ)
ካህሣይ - ካሜ - ካሣይ

822. **ካሌብ** (ዐብ)
የማይፈራ ደፋር ድል አድራጊ ማለት ነው ፤ (ከልብ)።
በቅዱስ መጽሐፍ ከሙሴ ሞት በኋላ ከኢያሱ ጋር ኾኖ ሕዝበ እስራኤልን መርቷል። እስራኤልን እንዲሰልሉ ከተላኩት ከዐሥራ ኹለቱ ሰዎች አንዱ ነበር (ዘኍ 13፥6 ፤ 14) ።
በኢትዮጵያ ታሪክም **ዐፄ ካሌብ** ስመ ጥር ንጉሥ ነበሩ (417 - 527 ዓ.ም.)።
የንጉሥነት ሥልጣናቸውን ለልጃቸው ለገብረ መስቀል ሰጥተው፤ ዘውዳቸውን ለኢየሩሳሌም ገዳም ልከው መነኑ (ስን. ግን. 18 ገጽ 311)።

823. **ኬር** (ጉራ)
ሰላም ይኹን ማለት ነው።

824. **ኬና** (ኦሮ) ሰጦታ ማለት ነው።

825. **ክብሩ**
በሀብት መበልጸግ ከበሬታ ማግኘት ...።
ክብሩ ይሰፋ፤ እግዚአብሔር ይመስገን።
ከፍተኛነትነት ፤ ሰው በንጽሕናው ፤ በማዕርጉ ከብር ያገኘል (ሮሜ. 13፥7)።
ያባት ስም ታዬ ቢል ይገጥማል።
ክብረዓለም - ክብረአብ
ክብረማርያም - ክብረት
ክብረቅዱሳን - ክብሮም
ክብረሥላሴ - ክብር - ክብሬ

826. **ክንዴ**
የጎይል ፤ የመመኪያ ምሳሌ ነው።
እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከግብጻውያን ባርነት አወጣቸዋለኹ ። ከተገገርነታቸውም አድናቸዋለኹ ። በተዘረጋ ክንድ በታላቅ ፍርድም አታደጋቸዋለሁ (ዘጸ. 6፥6 ፤ ኢሳ. 51፥9፤ መዝ. 17፥34፤ ሕዝ. 30፥25)።
ያባት ስም ላቀው ቢል ይገጥማል።
ክንዴኹን - ክንዳለም - ክንዱ
ክንዴነው - ክንዴሀፍትይ (ትግ)
ክንድይ - ክንድያ(ጉራ)

827. **ክበበው**
ዙሪያውን ያዘው ...።
ያባት ስም በለው ቢል ይገጥማል።

828. **ክንፈ - ክንፉ**
እንደ እጅ በግራና በቀኝ ጐን የበቀለ።
ለክርስትና ስም ቅጽል ሊኾን ይችላል።
ያባት ስም **መልአኩ** ቢል ይገጥማል።
ክነፈርግብ - ክነፈብርሃን- ክነፈወርቅ
ክንፈ ገብርኤል ክርስትና ስም።

829. **ክፈተው**
መንገዱን፣ በሩን፣ መግቢያውን ...።
ያባት ስም በለው ቢል ይገጥማል።

830. **ክፍሉ**
ዐታው፣ ደረጃው ...።
ያባት ስም ዘርዐ ብሩክ ቢል ይገጥማል።
ክፈለው - ክፍሌ - ክፍላይ (ትግ)
ክፍለ ማርያም ከርስትና ስም ።

831. **ኩራን**
ወንድ ልጅ አገኘን...። ተቸነን፣ ተጓደድን፣ ተኩፋነን ።
ያባት ስም በዕድሉ ቢል ይገጥማል።
ኩራ - ኩሬ - ኩሩ

832. **ኮርሜ** (ኦሮ)
ወንድ፣ ጎበዝ ማለት ነው።

833. **ኮርጆ** (ኦሮ)
መያዣ ከረጢት ወይም ሙዳይ ሳንቲም ጌጣጌጥ ማስቀመጫ (ኮርጆ) ማለት ነው።

834. **ኮኮቡ - ኮከበ**
ኮከብ ተሸላሚ ...።
የከዋኩበት ብዛት የእግዚአብሔርን ልግስና ምልክት ነው። አብርሃም እንደ ከዋክብት ዘሩ ኤንዲበዛ ተስፋ ተሰጠው (ዘፍ. 15፥5 ፤ ኢዮ. 22፥12 ፤ መ. 146፥4)።
ያባት ስም አበራ ቢል ይገጥማል።

- ኸ -

835. **ኸብቴ** (ዐማ) **ከብት** (ግእ)
ከበተ ተከበተ ካለው ግስ ከብት (ኸብት) ይወጣል።
ወሀበ ሰጠ ከሚለው ግስ ደግሞ ሀብት ይወጣል። ስዚህ ሀብት የሚለውን ተመልከት።
ኸብትዬ - ኸብቱ - ኸበታሙ
ኸብትነት - ኸብትደግ - ኸብታገኘሁ
ኸብቶም - ኸፍታም - ኸብትይመር
ኸፍታኢ - ኸፍታይ(ትግ)

836. **ኹሉምታየ** (ሁሉምታየ)
ያባት ስም ተዋሕዶ ቢል ይገጥማል
ኹሉምይፈር - ኹሉምሰው
ኹሉበላይ - ኹሉታዬ - ኹልጊዜ
ኹሉዓለም - ኹሉአንተን - ኹሌ
ኹሉወርቅ - ኹሉዐዲስ
ኹሉአገርኸ - ኹሉይመር
ኹሉይግር - ኹሉንአየሁ

837. **ኹነኛው**
ኹኔታው፣ ሥራው፣ ተፈጥሮው፣ መልኩ ቁመናው እሱን የመሰለ ለማለት ...።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።
ኹነኝ - ኹንልኝ - ኹንያለው

838. **ኾነልኝ - ኾነኝ**
ወላጆች ያሰቡት ነገር ሲኾንላቸው የሚሰየም ስም ነው ።
ያባት ስም መኩሪያ ቢል ይገጥማል።

- ወ -

839. **ወህምያ** (ጉራ) ከብር ማለት ነው።

840. **ወሃቤጸጋ** (ግእ)
ጸጋን የሰጠ (የሚሰጥ) ማለት ነው ።
ያባት ስም ፍጹም ቢል ይገጥማል።

841. **ወለላ - ወለላው**
የተጣራው የማር ሰፈፍ ማለት ነው።
ያባት ስም ማሩ ቢል ይገጥማል።

842. **ወሌ** (ግእ. ዐረ)
ወለየ ገዛ ተመረጠ ማለት ነው።

ለቁም ነገር መረጠ ፣ ለየ ለሹመት።
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ የአቴጌ ጣይቱ ብጡል ታናሽ ወንድም ወሌ ብጡል የራስ ጉግሳ ወሌ አባት ናቸው።

843. **ወልደ-ነጐድጓድ**
የነጐድጓድ ልጆች ማለት ነው ።
የዮሐንስና የያዕቆብ አባት ነጐድጓድ ይባል ነበር (ማር. 3፥17)።

844. **ወልዴ** (ግእ)
ወልድየ ከሚለው ። ልጄ ማለት ነው።
ለክርስትና ስም ቅጽል ነው።
ወልዱ - ወልዳይ - ወልደየስ
ወልደ ኢየሱስ ክርስትና ስም።

845. **ወማ** (ጉራ) በረከት ማለት ነው።

846. **ወረሰ**
ትምህርት፣ ሀብት፣ ለልጅ፣ ለዘመድ፣ ለወዳጅ የሚተላለፍ ንብረት (ዘፍ. 15፥3)።
ያባት ስም በጎይሉ ቢል ይገጥማል።
ወራሹ - ወራሽ - ወራሼ

847. **ወረታው**
ውለታው ፤ የበጎ ሥራ ዋጋው ...።
ያባት ስም ያዛቸው ቢል ይገጥማል።
ወረቱ - ወረቴ - ወሮታው

848. **ወረደ** (ግእ)
ዝቅ አለ፤ ከላይ ወደታች መጣ ...።
ያባት ስም **መ**ልአኩ ቢል ይገጥማል።

849. **ወርቁ**
የከበረ ማዕድን የከበር እና የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ነው (ዘፍ. 2፥11 ፤ 13፥2 ፤ 24፥53 ፤ ማቴ. 25፥11 ማቴ 10፥9 ፤ መዝ. 119፥72)።
ያባት ስም ታከለ ቢል ይገጥማል።
ወርቃለም - ወርቁ - ወርቃለማሁ
ወርቀበዙ - ወርቅበዛ - ወርቅሰው
ወርቅሽት - ወርቅሽዋ - ወርቅኝ
ወርቅነህ - ወርቅነው - ወርቃየሁ
ወርቃገኘሁ - ወርቅዬ - ወርቅያንጥፋ
ወርቅአፈራሁ

850. **ወሰኑ**
አንዱ ደነገጥ ሲኾን ።
ኹለተኛው ድንበሩ ከለሉ ማለት ነው።
ያባት ስም አይደፈር ቢል ይገጥማል።
ወሰነው - ወሰኔ - ወሰኖ
ወሰናቸው - ወሰን - ወሰንሰገድ
ወሰንየለህ - ወሰንየለው - ወሰንዬ

851. **ወንዳፍራሽ**
ያባት ስም እንተኹን ቢል ይገጥማል።
ወንዳለም - ወንዳለ - ወንዳንተ
ወንድዬ - ወንዳወቅ - ወንዳንተነኽ
ወንዳየኹ - ወንዳየን - ወንዳይ
ወንዳገኘሁ - ወንዳጥር - ወንዳፈራሁ
ወንዳቸው

852. **ወንድሙ**
ያባትና የእናት ልጅ። ከዚህም ሌላ በሥጋና በመንፈስ ፤ በፍቅርና በመረዳዳት፣ በጓደኝነት ያለ ኹሉ ወንድም ይባላል።
በሥጋ፣ በአገር ፣ በነገድ፣ በቤተሰብ፣ በወዳጅነት፣ በሃይማኖት (ሮሜ. 1፥13)።
ያባት ስም አዘዘው ቢል ይገጥማል።
ወንድማገኘሁ - ወንድማኝ -
ወንድሜ - ወንድሚነኽ - ወንድም
ወንድምኹኔ - ወንድምተካ

ወንድምስሻ - ወንድምነኽ
ወንድማለም - ወንድምገዛኹ
ወንድምግዛው - ወንድምሸዋ
ወንድምኹን - ወንድምጌታ
ወንድምጋሻ - ወንድምሽት

853. **ወንድወሰን (ወንዶሰን)**
ወንድ ድንበር መጪረሻ ማለት ነው።
ያባት ስም ተሻገር ቢል ይገጥማል።
ወንድአፈረ - ወንድይፍራው
ወንድይራድ - ወንድሻው - ወንዳጥር
ወንድያለው- ወንድዬ - ወንድይፍራው

854. **ወዬማ** (ኦሮ)
ተሻለሀ ማለት ነው ።
ወዬሳ (ኦሮ) ደኅንነት ማለት ነው።

855. **ወያ** (ኦሮ)
በጣሊያን ጊዜ በአጋዴን በኩል ይዋጉ ከነበሩት ጀግኖች አንዱ ደጃዝማች በቀለ ወያ አብሴ፤ አባታቸው ወያ ይባሉ ነበር።

856. **ወይራው**
አንጨቱ ጥሩ የኾነ የተመረጠ ። ዘይቱ ለመድኃኒት ፣ ለቅብዐ ቅዱስ ፣ ለምግብ ይኾናል። በምሳሌነት ደግሞ የብልጽግና የሀብት ምልክት ነው
(ዘዳ. 24፥20 ፤ መዝ. 127፥3 ፤ ሮሜ. 11፥17)።
ያባት ስም መ**ን**ግሥተ ቢል ይገጥማል።

857. **ወዳጄ**
የምወደው ፣ ወዳጄ ልቤ ...።
ያባት ስም አያልቅበት ቢል ይገጥማል።
ወዳጁ - ወዳጄነኽ - ወዳጄነው
ወዳጅ - ወዳጅኹን - ወዳጆ
ወዳጅነው

858. **ወገኔ – ወገኑ - ወገን**
ዘመዴ ፣ አለኝታዬ ...።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።

859. **ወጋየሁ**
በዚህ ስም ከሚጠሩት አንዱ፤ በኢትዮጵያ ስማቸው ከሚጠራ የመድረክ ተዋንያን አንዱ ወጋየሁ ንጋቱ ነበር።
(1936 - 1982 ዓ.ም.)።

860. **ወግደረሰ**
ወግ ማለት ከእባት የተላለፈ ሥርዓት ፣ ደንብ፣ ከሕግ የተነሳ የሚደረግ ልማድ ነው (1ቆሮ.11፥2 ፤ ተሰ. 2፥15 ፤ 3፥6)።
ወግኝ - ወግበላ - ወግበዛ
ወጋዩ - ወግደረሰን - ወጌ - ወጉ
ወግአገር

861. **ውብነኽ**
አሞራው ውብነኽ በመባል የታወቁ በጣሊያን ጊዜ ዐርበኛ መሪ ከነበሩት አንዱ ራስ ውብነኽ ተሰማ ናቸው።
ውብሸት - ውባቸው - ውባለ
ውብዬ - ውባንተ - ውባለም
ውበቴ - ውብይሻው - ውቤ
ውቤነኽ

862. **ዋለልኝ - ዋለ**
ውለታ ማለብኝ፣ ረዳኝ፣ አብሮኝ ቆየ ...።
ያባት ስም መ**ል**አኩ ቢል ይገጥማል።

863. **ዋሕድ** (ግእ)
አንድ ማለት ነው።
ያባት ስም አካሉ ቢል ይገጥማል።

864. **ዋሪ** (ኦሮ) ረፋድ ማለት ነው።

ዋ

865. **ዋርካው**
ቅርንጫፉ የበዛ ፤ ፍሬው የሚበላ ግርማ
ያለው ትልቅ ዛፍ ነው ።
ያባት ስም ረበበ ቢል ይገጥማል።

866. **ዋሚ** (ኦሮ) - **ዋሜ**
ጥሪ ማለት ነው።
ኢትዮጵያውያን ሩጫ ተወዳዳሪዎች **ዋሚ**
ቢራቱ እና ጌጤ **ዋሚ** ይታወቁበታል።

867. **ዋስይኹን (ዋሲኹን)**
ኹለተኛ ጥፋትን ላለመድገም ተያዥ
የኹነኝ ...። **ዋስዓለም - ዋሴ**
ያባት ስም ቢኾነኝ ቢል ይገጥማል።
ዋሱ - ዋሴነህ - ዋስዬ

868. **ዋቃ** (ኦሮ) **ዋቃዮ - ዋቆ**
ሰማይ፣ እግዚአብሔር ማለት ነው።
ዋቅጅራ እግዚአብሔር አለ ማለት ነው።

869. **ዋካ** (ጉራ)
እኹን ማግኘት ማለት ነው።
ዋካ (ግእ) ብርሃን ማለት ነው።

870. **ዋጋው**
የሚገመተው ሒሳብ፣ በገንዘብ።
ምሳሌ፦ የሉብ ዋጋ፣ የድካም ዋጋ
ያባት ስም **ዱባለ** ቢል ይገጥማል።
ዋጋነህ - ዋጋዬ - ዋጋአየሁ

871. **ውሂብ** (ግእ)
ስጦታ ማለት ነው።
ውሂበ ሥላሴ ክርስትና ስም።

872. **ውለታው**
በመከራ ቀን በጎ ነገር አደረገ ...።
ያባት ስም ከበደ ቢል ይገጥማል።

873. **ውዴነኽ**
የምትፈቀር ነህ፤ በዋጋ ሊተመን የሚወዳ
ደርህ የለም ፤ በጣሙን ውድነህ ።
እነሆ የውዴ ቃል ! በተራሮች ላይ ሲዘ
ልል። (መኃ. መኃ. 2፥8)።
ያባት ስም ይበቃል ቢል ይገጥማል
ውድሰው - ውዱ - ውድነኽ
ውዱዓለም - ወዳድ

- ዐ -

874. **ዐሎላ** (ዐ.ብ)
ከመጀመሪያው አንዱ ማለት ነው።
በዚህ ስም ራስ **ዐሎላ** አባነጋ ተብለው
የሚታወቁት ፤ **ዐሎላ** አንግዳ ቁቢ የጦር
መሪና አገረ ገዥ ነበሩ ። በቀይ ባሕር
በኩል ኢትዮጵያን ለመውረር የመጣውን
ጠላት ቱርኮችን ፣ ጣሊያኖችን በሱዳን
በኩል ደርቡሾችን ተዋግተው። ቀይ ባሕ
ርን አስከብረው የኖሩ ኢትዮጵያዊ ነበሩ።

875. **ዐመልሸት - ዐመሉ**
ጠባዩ ጥሩ የኾነ ...።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

876. **ዐማኑኤል** (ዕብ)
ይህ ስም የባሕርይ ስም ነው ፤
ስመ ሥጋዌ ፤ አንዳንድ ሰዎች ለልጆቻ
ቸው ስም ሰይመው ሲጠሩበት ይሰማል።
ሊጠሩበት የሚገባ ግን አይደለም (ኢሳ. 7)
ዘዐማኑኤል (ዘማኔል) ቢባል የተሻለ ነው።

877. **ዐምበሉ**
ቀስበትነት ያለው የፈረስ ኮርቻ ጌጥ።
ኹለተኛው ዐምበል፤ ሻምበል መሪ አለቃ
አዝማች ማለት ነው። **ዐምበል**

878. **ዐምደወርቅ**
በወርቅ የተለበጠ ምሰሶ መደገፊያ፣ በቅኔ
ማሕሌት እና በቅድስት መካከል ያለ።
ቤትን ለመደገፍ ፤ ለጌጥ ይቆማል።
(1ነገ ሥ. 7፥11)። ለክርስትና ስም ቅጽል
ይኾናል። **ዐምድነኽ - ዐምዱ ፡**
ያባት ስም ታየ ቢል ይገጥማል።
ዐምድ - ዐምድኹን - ዐምዱ

879. **ዐሥራት**
ከማንኛውም ገቢ ከመቶ ዐሥረኛውን
ወይም ከዐሥር አንድ ፤ ለሃይማኖት መሪ
ዎች ወይም ለመንግሥት የሚሰጥ
(ዘፍ. 14፥20)።
ዐሥራቱ - ዐሥራቴ - ዐሥራተ
ዓሥራተ ማርያም ክርስትና ስም ተመልከት።

880. **ዐረግነኽ – ሐረጎት** (ትግ)
በግእዝ ሐረግ ማለት ነው ።

881. **ዐረፈዐይኔ - ዐረፈሸዋ**
ዓይኔ ከመንከራተት ረጋ ...። ገጽ 176:713
ያባት ስም ሙሉቀን ቢል ይገጥማል።

882. **ዐሳቤ**
አወጣ አወረድው የነበረ ...።
ሐሳቤ ቢል ግእዝ ነው። ተመልከት።
ያባት ስም አንተነህ ቢል ይገጥማል።
ዐሳብ - ዐሳቡ

883. **ዐስዘ** (ግእ)
የሥራ ዋጋ ማለት ነው ።
ዘተወከፈ ነቢየ ዘስመ ነቢይ ዐስዘ ነቢይ
ይነሥእ። ትርጕም፤ በነቢይ ስም ነቢይን
የተቀበለ የነቢይን ዋጋ ያገኛል (ማቴ. 10፥
41)። **ዐስዘነቢይ - ዐሰቡ**
ዐስዘሐዋርያት - ዐስዘጻድቅ

884. **ዐበረ**
ተባበረ ፣ ተጨመረ ...።
ያባት ስም **ወዳጀ** ቢል ይገጥማል።

885. **ዐቢይ** (ግእ)
ዐቢይ እግዚአብሔር ወዐቢይ ጎይሉ።
ትርጕም፤ እግዚአብሔር ታላቅ ነው ኃይ
ሉም ታላቅ ነው (መዝ. 146፥5)።

886. **ዐባይ - ዐባየ - ዐባይነኽ**
ታላቅ ገናና ፤ ብርቱ ማለት ነው።
ከኢትዮጵያ ተነሥቶ ግብጽን አጠጥቶ
ታላቁ ባሕር (ሜዲትራንያን) የሚገባ
ወንዝ ። ሌላው ስሙ ጊዮን ነው (ዘፍ. 2
፥13 ፤ ኢሳ. 19፥7 ፤ 23፥3)።

887. **ዐብድ-አል-መሢሕ**
የመሲህ ባሪያ፤ ገብረ ክርስቶስ ማለት ነው።

888. **ዐብድ-ሩኅ**
የሩኅ ባርያ፤ ሚሳኤል ከመሰሉቱ ደቂቅ አንዱ።

889. **ዐወቀ – ዐወቀው**
ዕውቀት ኹሉ ከእግዚአብሔር ነው።
ዕውቀት ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችም
አንዱ ነው (መዝ. 93፥10 ፤ ዳን. 1፥7
1ቆሮ. 12፥8)።
ያባት ስም በቃሉ ቢል ይገጥማል።

890. **ዐዘነልኝ** (ሐዘነልኝ)
ሀዘን ከሚለው ግስ፤ አቤት አቤት አለ ፤
ራራልኝ ማለት ነው።
ያባት ስም የቺዋለ ቢል ይገጥማል።

ወ

891. **ዐየለ**
በረታ፣ በዛ፣ ማለት ነው።
ኃይለኛ ፤ የማይቻል ኾነ ...።

ያባት ስም ሚዛኑ ቢል ይገጥማል።
ዐየላቸው - ዐያሌው - ዐያልነህ
ዐየለወርቅ - ዐየለው

892. **ዐወቀ**
ተማረ፣ አጠና፣ ለመደ፣ ተረዳ፣ ለየ፣ ልብ አደረገ ማለት ነው።

893. **ዐይኑኩሉ** (ግእ) **(የኹሉዐይን)**
ዐይነ ኩሉ ነፍስ ይሴፎ ኪያከ።
ትርጒም ፤ የኹሉ ዐይን አንተን ተስፋ ያደርጋል (መዝ. 144(145)፥15)።
ያባት ስም **አንተነህ** ቢል ይገጥማል።

894. **ዐይናለም**
ብርሃንን ማየትን እንዲሁም የሰውን ጠባይንና ስሜት ይገልጣል (ዘዳ.7፥16፤ ኢሳ. 5፥15 ፤ ሕዝ. 14፥16)።
ዐይናበባ - ዐይናቸው - ዐይኔ
ዐይንዋጋ - ዐይናማው

895. **ዐደመ**
ሰውን ሰበሰበ ፤ በድብቅ በሰውር ዶለተ መከረ ነገር ቁጠረ ማለት ነው። **አደመ** ቢል አማረ ማለት ነው። አዳምን ተመል ከት።

896. **ዐደራ** (ሐደራ)
ጠብቀው፣ ኃላፊነትን፣ ታማኝ ኾነህ ተገኝ ያባት ስም **ታከለ** ቢል ይገጥማል።
ዐደራዬ - ዐደራው

897. **ዐዲሱ** (ሐዲሱ (ግእ))
ታይቶ ያልታወቀ ፣ ከዚህ በፊት ያልተሰማ፣ ያልታየ ፣ ያልተዳሰሰ፣ ያልተቀመሰ።
ያባት ስም **መስፍን** ቢል ይገጥማል።
ዐደሱ - ዐደሰ - ዐዲሴ (አሮ)

898. **ዐጅበው - ዐጅቡ - ዐጅቤ**
አድምቀው፣ ምሳሌ፦ ዐጀባ ኾኗል ደጅህ በየት ልይህ፤ እንዳለች ዘፋኝ።

899. **ዐጸደ ወይን – ዐጸደ**
የተከበበ የአትክልት ቦታ ዓሮ ።
ዐጸደ ወይን አፍለስከ አምግብጽ። ትር ጕም፤ ከግብጽ የወይን ግንድ አመጣኽ (መዝ. 79(80)፥8)።

900. **ዓለማየሁ - ዓለሜ - ዓለም**
ዐዲስ ሕይወት አየሁ ...።
ዓለምን እግዚአብሔር አስገኘው ።
ጠቅላላ ፍጥረት የዓለምን ሕዝብ ማለት ይኾናል (ዮሐ.1፥10 ፤ 16፥21)።
በዚህ ስም የዐፄ ቴዎድሮስ ልጅ ዓለማየሁ ቴዎድሮስ በእንግሊዞች ተማርኮ የተወሰደው በዚህ ስም ይጠራል።
ዓለሙ - ዓለሙብርሃን - ዓለማት
ዓለማያ - ዓለማይ - ዓለምሰፋ
ዓለምሸዋ - ዓለምቀረ - ዓለምቀና
ዓለምተሰፋ- ዓለምቢሻው- ዓለምባንተ
ዓለምብርሃን- ዓለምበጁ - ዓለምተድላ
ዓለምታየ - ዓለምነሽ - ዓለምነው
ዓለምነጋ - ዓለምዳሩ - ዓለምዘውድ
ዓለምሠናይ - ዓለምሽት
ዓለም ሰገድ (ዐፄ ፋሲል)

901. **ዕርቀሰላም**
ጠብ ባለበት መካከል ሰላም ሲኾን ዕርቅ ይባላል። ከፈጣሪ ጋር መታረቅ ፤ የሚያስታርቁም ብዙዎን ተብለዋል። (ማቴ. 5፥9 ፤ ሬል. 4፥2)።
ያባት ስም ወረደ ቢል ይገጥማል።
ዕርቅዓለም - ዕርቅኢየሱስ - ዕርቁ
ዕርቅኹን - ዕርቅይኹን

902. **ዕርገቱ - ዕርገተ**
ከታች ወደላይ መውጣት ማለት ነው።
ዕርገተ-ቃል ቢል ከርስትና ስም ይኾናል።
(የሐ. ሥራ. 1፥6 ፤ ሉቃ. 24፥50፤ ዕብ. 9፥11)።

903. **ዕንቍ**
የከበረ ከባሕር ውስጥ የሚገኝ ሰዳፍ የም ትወልደው ድንጋይ (ማቴ. 13፥45 ፤ ራእ. 21፥21)።
ያባት ስም ብርሃን ቢል ይገጥማል
ዕንቍኢየሁ - ዕንቋይ (ትግ)
ዕንቍኢየሁ - ዕንቁባሕርይ (ግእ)
ዕንቁ ሥላሴ ከርስትና ስም።

904. **ዕንባቆም** (ዕብ.)
ትንቢት ተናጋሪ ጠቢብ የልብን የሚያውቅ ማለት ነው (ዕን. 1፥1)።

905. **ዕዝራ** (ዕብ.)
ረዳ (ረድኤት) ማለት ነው ።
500 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት በም ርኮ በባቢሎን የእስራኤላውያን ሊቀ ካህ ናት የነበረ እና ጸሓፊ የነበረ ነው (ዕዝ. 7፥1-7 ፤ 11)።

906. **ዕድሉ**
ሀብት መጣ ፤ ሀብታም ኾነ ...።
ያባት ስም አማረ ቢል ይገጥማል ።
ዕድላም - ዕድሌወርቅ - ዕድል

907. **ዕድሜ - ዕድሜዓለም**
ዘመን ፣ ጊዜ ...።
ያባት ስም **ዘለቀ** ቢል ይገጥማል።

908. **ዕፁብ** (ግእ) **- ዕፁብድንቅ**
ድንቅ፣ የሚደንቅ ከቡድ ነገር ማለት ነው ።

- ዘ -

909. **ዘለለው**
ተራመደው ፣ አለፈው ...።
ያባት ስም **ሙላቱ** ቢል ይገጥማል።

910. **ዘለላው**
ፍሬዎች ያሉበት የሚያምር ሐረግ።
የወይን ፍሬ ዘወይን ሐረግ ላይ ተነባብሮ ተንዠርግጎ የሚታይ (ዘጉ. 13፥23)።
ያባት ስም **አማረ** ቢል ይገጥማል።

911. **ዘለቀ**
ተሻገረ ፣ አለፈ ...።
ያባት ስም **ትእዛዙ** ቢል ይገጥማል።

912. **ዘለዓለም (ዘለዓለም** (ግእ))
ዅልጊዜ ፍጻሜና ወሰን የሌለው ማለት ነው (መዝ. 89፥2)። **ለወንድም ለሴትም** ጸታ ይኾናል ። ያባት ስም ፣ ለይኩን፣ ለገሠ፣ ባየሀ፣ ሰንቄ፣ ሰመኘ፣ እውነት፣ ምገሰ፣ መሐሪ፣ ከብረት፣ ተመስገን ቢል ከኹሉም የሚገጥም ስም ነው።

913. **ዘመልአከ** (ግእ)
የመልአከ ነህ ማለት ነው።
ያባት ስም ከብሩ ቢል ይገጥማል።
ከርስትና ስምን ተመልከት።

914. **ዘመረ - ዘመረወርቅ**
አመሰገነ ፣ አንጐራጐረ ...።
ያባት ስም **ያሬድ** ቢል ይገጥማል።

915. **ዘመነ**
ዘመነ (ግእ) (ዘመነ) ዘመናዊ ኾነ ፤ ዘመን ቆጠረ ማለት ይኾናል።
ያባት ስም ዮሐንስ ቢል ይገጥማል።
ዘመነሰላም - ዘመኑ - ዘመኔ - ዘመን

ወ

916. **ዘመድ**
የቅርብ ዘመድን ወይም ጠቅላላ ወገንን ሊያመለክት ይችላል (ሉቃ. 14፥12)።
ያባት ስም በዛብህ ቢሊ ይገጥማል።
ዘመደወርቅ - ዘመዳገኘሁ - ዘመድ ዘመድኹን - ዘመድኩን (ግእ)
ዘመድአገኝ - ዘመዴ - ዘመዱ ዘመዳለም

917. **ዘማቹ – ዘማቹ**
ለጦር፣ ለትምህርት፣ ለሥራ ተጉዋዥ ...።
ያባት ስም ወራዊት ቢሊ ይገጥማል።

918. **ዘረመጭት** (ጉራ)
ምርጥ ዘር ማለት ነው።

919. **ዘሩባቤል** (ዕብ)
የባቢሎን ዘር ማለት ነው (1ኛ ዜና. 3፥16፤ 16–19) ።

920. **ዘርዐ ያዕቆብ**
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ ንጉሥ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ናቸው ። ኢትዮጵያን ሠላሳ አራት ዓመት አስተዳድረዋል።
መጽሐፍ አዋቂና ፣ ለሃይማኖት ቀናኢ ነበሩ (1426- 1460) ።

921. **ዘር-ይኹን (ዘሪኹን) - ዘርኹን**
እስከ ብዙ ትውልድ የሚወለድ ልጅ ዘር ይባላል (ዘፍ. 3፥15 ፤ 38፥8፤ ማር. 4፥1)።
ያባት ስም በላቸው ቢሊ ይገጥማል።

922. **ዘርዓይ ድረስ**
በጣሊያን አስረኛ ኾኖ በሮም የጣሊያን ቋንቋ አስተርጉሚ የነበረ ፤ የራስ ዐሉላን ጎራዴ ይዞ በይሁዳ አንበሳ ሐውልት ላይ ቆመው ስለኢትዮጵያ ነጻነት የተናገረ ጀግና ናቸው። በስሙም የመጀመሪያ የኢትዮጵያ የጦር መርከብ ተሰይማ ነበር።
ዘርዐሠናይ - ዘርዐማርያም - ዘረብዙ ዘርዐብሩክ - ዘርዐዳዊት - ዘርአበዛ ዘርዐብርሃን - ዘርዓይ - ዘሩ ዘርዐጽዮን

923. **ዘርጋ – ዘርጋልኝ - ዘርጋው**
አጅኽን፣ ልብስኽን፣ ጸጋኽን ...።
ያባት ስም ምሕረት ቢሊ ይገጥማል።

924. **ዘርፉ - ዘርፍነህ**
አባት እና እናትን መላይነትን፣ ያሳያል።
ያባት ስም ተገኘ ቢሊ ይገጥማል ።

925. **ዘበርጋ** (ጉራ) አሰፋ ማለት ነው።

926. **ዘበነ (ዘመኑ)**
ዘበናይ (ዘመናይ) - ዘበኑ (ዘመኑ)
ኹለተኛው ትርጉም
ዘበነ (ግእ) ጀርባ ኾነ ። (ዘባን)
ምዕረ በዘባንኪ ወምዕረ በገቦኪ፤ ማርያም ብዙኃ ቤሐዚለ ሕማን ደከምኪ።
ትርጉም ። አንዴ በጀርባሽ አንዴ በወገብሽ ፤ (ሰቆቃ. ድን ገጽ 51.)

927. **ዘበአማን** (ግእ)
እውነተኛ ...።
ያባት ስም መንግሥቱ ቢሊ ይገጥማል።

928. **ዘብርሃን** (ግእ)
የብርሃን ...።
ያባት ስም መላኩ ቢሊ ይገጥማል።
ከርስትና ስምን ተመልከት (ዮሐ. 8፥12)።

929. **ዘብዴዎስ** (ዕብ)
ስጦታ ፤ ስጦታዬ ማለት ነው።
የያዕቆብና የዮሐንስ አባት (ማር.1፥19 ፤ ማቴ. 27፥56)።

930. **ዘነበ – ዘነቡ**
ዝናብ የበረከት ምሳሌ ነው።
ያባት ስም ፍሬው ቢሊ ይገጥማል።

931. **ዘንባባው - ዘንባባዬ**
ብዙ ሕዝብ ጌታ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌ ምእንደሚመጣ በሰሙ ጊዜ፥ የዘንባባ ዛፍ ዝንጣፊ ይዘው ሊቀበሉት ወጡ (ዮሐ. 12 ፥13) የሰላም ምልክት ነው።
አበበ ፣ አፈራ ፣ ጸደቀ ...።
ያባት ስም በቀለ ቢሊ ይገጥማል።

932. **ዘንጊዘር** (ጉራ) መከታ ማለት ነው።

933. **ዘኘኒ** (ጉራ) መለሰ ማለት ነው።

934. **ዘአልቦ** (ግእ)
ምንም የሌለ ማለት ነው።
ያባት ስም ወሰን ቢሊ ይገጥማል።

935. **ዘካርያስ** (ዕብ.)
እግዚአብሔርን የሚያስበው፤ (ዝኩር እግዚአብሔር) ማለት ነው ። በቅዱስ መጽሐፍ ከ20 በላይ የሚኾኑ ሰዎች ተጠርተውበታል (ሉቃ.11፥51)።

936. **ዘኬዎስ** (ግሪ)
ንጹሕ እግዚአብሔር ያነጻው ።
የቀረጥ ተቀባዮች አለቃ የነበረ ባለጠጋ ቁመቱ ዐጭር የነበረ ሰው ፤ ጌታ ኢየሱስም በቤቱ ተስተናገደ (ሉቃ. 19፥1)።

937. **ዘወትር**
የኹልጊዜ ጸሎቴ፣ ናፍቆቴ ...።
ያባት ስም ወዳጄነኽ ቢሊ ይገጥማል።

938. **ዘውዳገኘኹ**
ንጉሥ እና ንግሥት የሚቀዳጁት ከወርቅ ዐልማዝ እና ከዕንቊ ከከበረ ድንጋይ የሚሠራ የክብር አክሊል ነው (2ኛ ዜና. 23፥11 ፤ ሕዝ. .21፥26 ፤ አስ. 2፥17 ፤ ራእ. 19፥12)። **ዘውዳይ - ዘውዳቸው - ዘውድ - ዘውዱ ዘውድነህ - ዘውዴ - ዘውድዓለም**

939. **ዘውገ** (ግእ) **ዘውገ ማዕነቅ**
ኹለት ጥንድ ጣምራ ወገን አደረገ ።
(ሉቃ. 2፥24 ፤ ምሳ. 17፥10)
ዘውግ - ዘውግነህ

940. **ዘድንግል**
የድንግል ማለት ነው።
ያባት ስም ዱባስ ቢሊ ይገጥማል።

941. **ዘገነ – ዘገነወርቅ - ዘገነው**
በእጁ መዳፍ አፈሰ፣ ተረፈሰ ...።
ያባት ስም ወርቁ ቢሊ ይገጥማል።

942. **ዘገየ - ዘገዩ - ዘግያለው**
ወደኋላ ቆየ ...።
ያባት ስም ሞሴ ቢሊ ይገጥማል።

943. **ዘፈረ** (ግእ) - **ዘፈረወርቅ**
ዘርፍ፣ የልብስ ጫፍ፣ ዳርቻ፣ ቅጽል (ዘጎ.15፥38 ዘዳ. 22፥12፤ ማቴ. 23፥5)
ያባት ስም ብርሃን ቢሊ ይገጥማል።
ከርስትና ስምን ተመልከት (ዮሐ. 8፥12፤ 1)።
ዘፈረ ብርሃን - ዘፈረ ማርያም

944. **ዙርባቸው - ዙርቤ**
ፊትኽን መልሰባቸው ...።
ያባት ስም በጊዜው ቢለ ይገጥማል።

945. **ዛፉ - ዛፌ**
ዋርካው፣ ታላቁ ፤ ቁመታሙ ...።
ያባት ስም በቀለ ቢለ ይገጥማል።

946. **ዜና**
ወሬ ፣ ዐዲስ ነገር፣ የምሥራች ...።
ያባት ስም መዋዕል ቢለ ይገጥማል።
ዜናው - ዜናዊ - ዜናነህ
ዜና ሥላሴ ከርሰትና ስም።

947. **ዝምታ**
አለመናገር ...። ማዳመጥ ...።
ያባት ስም ተሻለ ቢለ ይገጥማል።
ዝምበላቸው - ዝምታወርቅ

948. **ዝቅአርጋቸው (ዝቃርጋቸው)**
ወረድ አርጋቸው ...።
ያባት ስም በፍርዱ ቢለ ይገጥማል።
ዝቅአርጌ (ዝቃርጌ)

949. **ዝናዬ - ዝና**
የኔ ዝና፣ ለሜ ገናና ኾነ፣ ገነነ ...።
ያባት ስም ባልካቸው ቢለ ይገጥማል።
ዝናኽብዙ - ዝናኽ

950. **ዝናቡ - ዝናቤ - ዝናብነኽ**
በረከቱ፣ ጥጋቡ መጣ ...።
ያባት ስም ወረደ ቢለ ይገጥማል።

951. **ዝግጁ**
ያባት ስም በጊዜው ቢለ ይገጥማል።

- ዠ -

952. **ዠቅ-አለ - (ዠቃለ)**
እንደ ፈሰሰ በሰቶ መጣ ። በቁሙ ተንዠረቀቀ፣ ወረደ ...።
ያባት ስም ጸጋው ቢለ ይገጥማል።

953. **ዠማ (ጀማ)**
ጀ እና ዠ ተወራራሾች ናቸው።
በሰሜን ሸዋ መንዝና ተጉለትን የሚለያይ አንዲኹ በወሎ አዋሳኝ የሚያልፍ ታላቅ ወንዝ። **ጀማው - ጀማነኽ**

954. **ዣቡሬ** (ጉራ) ዐለፈ ማለት ነው።

- የ -

955. **የሉልወርቅ**
ከባሕር የሚገኝ የከበረ ዕንቁ (ዘፍ. 2፥12)።
ሉል ንጉሥ ሲነግሥ በእጁ የሚጨብጠው።
ያባት ስም ታደለ ቢለ ይገጥማል።

956. **የሐረግ (ያረግ)**
ቢወርድ ቢዋረድ የመጣ የዘር ሐረግ ...።
ያባት ስም በቀለ ቢለ ይገጥማል።

957. **የሐሳብ (ያሳብ) – ያሳብወርቅ**
የምኞቴ ፍጻሜ ተሟላ ...።
ያባት ስም ሞላ፣ ተገኘ ቢለ ይገጥማል።

958. **የሚያምረው – የሚያምር**
የሚናፈቀው፣ የሚወደደው ...።
ያባት ስም ተስፋ ቢለ ይገጥማል

959. **የማታ**
በስተመጨረሻ የተገኘ ...።

ያባት ስም ይመር ፣ መኮሪያ ፣ ተድላ ቢለ ይገጥማል።
የማታው - የማታፀሐይ - የማታነህ

960. **የማርሸት (የማር-አሸት)**
የማር ወለላ፤ በጥቅምት ወር የሚቆረጥ።
ያባት ስም ታደለ ቢለ ይገጥማል።
የማር - የማርውሃ

961. **የማነ (ግእ) የማን - የማነብርሃን**
ቀኝ ማለት ነው ።
የማናይ - በጊታ ቀኝ የተሰቀለው ፈያታዊ ዘየማን በመንግሥትኽ በመጣኽ ጊዜ ዐስበኝ ብሎ ጌታን የተማጸነ (ሉቃ. 23፥40)።

962. **የምሩ - የምር**
አምላክ ይኽን አጅ የሰጠን የአውነቱ ይኾን፡ ማለት ይኾናል።
ያባት ስም ነጋ ቢለ ይገጥማል ።

963. **የምሥራች**
በግእዝ ብሥራት ማለት ነው።
ዐዲስ ዜና፣ ዐዲስ ወሬ ...።
ያባት ስም ተሰማ ፣ ዕጓለጽዮን ፣ ቢለ ይገጥማል።

964. **የምሻው**
ያለምኩት፣ የምፈልገው ተገኘ።
ያባት ስም ወሰኔ ቢለ ይገጥማል።

965. **የምወደው**
ዓይኔን የጣልኩበት ደስ የሚያሰኘኝ ...።
ያባት ስም ተገኘ፣ ታረቀኝ ቢለ ይገጥማል

966. **የራስወርቅ**
ከዘውድ፣ ከአክሊል ቀጥሎ የራስ ወርቅ አለ ። ክብሬ ነህ ለማለት ነው።
ያባት ስም አበራ ቢለ ይገጥማል።

967. **የሱነህ**
በጥያቄ፣ አሱን ትመስላለህ ...።
ያባት ስም ተወዳጅ ቢለ ይገጥማል።

968. **የሺ – የሺጌታ - የሺጥላ**
የብዙዎች፣ ረዳት መከታ ነህ ...።
ያባት ስም መኮሪያ ቢለ ይገጥማል።

969. **የሻሸወርቅ**
ነጭ በፍታ፣ ሥሥ ራስ ማሠሪያ ፣ ነጭ ሻሽ፤ መሸፈኛ ማለት ነው (ዘጸ. 34፥4)።
ያባት ስም ክብሩ ቢለ ይገጥማል።

970. **የቃልኪዳን - የቃልነኽ**
በእግዚአብሔር ስም የተማማልንበት ቃል የተገባባንበት ፤ ምስክር፣ ማጽኛ ...።
ያባት ስም ክብሩ ቢለ ይገጥማል።

971. **የቄየሰው - የቄየ**
በሕይወት ያለ፣ የሰነበተ ደስታ አየ ...።
ያባት ስም አበበ ቢለ ይገጥማል።

972. **የኔኹን**
የግሌ ፣ የብቻዬ ኹን ...።
ያባት ስም ዳኛው ቢለ ይገጥማል።
የኔሰው - የኔነኽ - የኔዓለም
የኔመብት - የኔመንግሥት - የኔማር
የኔነው - የኔአባት - የኔአክል
የኔዐዛኝ - የኔንአየሁ - የኔውብ
የኔገዳም - የኔፈንታ

973. **የባሕርሸት (የባሕር-አሸት)**
ያባት ስም አይጠገብ ቢለ ይገጥማል።

974. **የነገው**
የዛሬው አበባ የነገ ፍሬው ...።
ያባት ስም ተሰፋዬ ቢለ ይገጥማል።

975. **የናትፈንታ/ው/**
በእናት ምትክ የተገኘህ ማለረሻ ...።
ያባት ስም እንተነህ ቢል ይገጥማል።

976. **የኋላወርቅ**
በመጨረሻ የተገኘኽ ...።
ያባት ስም ዋጋዬ ቢል ይገጥማል።
የኋላሸት - የኋላው - የኋላዬ

977. **የኛውጌጥ**
የኹላችን ውበት ጌጣችን ...።
ያባት ስም መርጊያ ቢል ይገጥማል።
የኛዓለም - የኛው - የኛነኽ

978. **የኹሉወርቅ**
በጸባይህ፣ በውበትህ የምትወደድ ...።
ያባት ስም እንተነህ ቢል ይገጥማል፤
የኹሉጌታ - የኹሉምሸት

979. **የወንድ-ወሰን (የምንዶሰን)**
የወንዶች መጨረሻ፣ ጀግና፣ ተወዳጅ...።
ያባት ስም አበራ ቢል ይገጥማል።

980. **የውብነኽ**
የምታምር ቆንጆ ነህ ...።
ያባት ስም ተመስገን ቢል ይገጥማል።
የውቤ - የውብርስት - የውብዛፍ

981. **የዘወትር – የዚህዓለም**
የኹልጊዜ፣ የሠርክ፣ የዕለት፣ የቀን፣
ደስታ ሀብት ፣ ጸሎት፤ ምግብ፤ ልብስ።
ያባት ስም ሀብቱ ቢል ይገጥማል።

982. **የግሌ - የግል - የግሉ**
የኔ የብቻዬ ነህ ...።
ያባት ስም መኳሻ ቢል ይገጥማል።

983. **ያለም (የዓለም (ግእ))**
የሰው ኹሉ፣ የሕዝቦች ኹሉ ...።
ብርሃን፣ ተስፋ፣ ገንዘብ፣ ጌጥ፣ ከለላ፣
መመኪያ ...።
ያባት ስም ጥላኹን ቢል ይገጥማል።
ያለምሸት - ያለም ብርሃን
ያለምጌጥ - ያለምሰው - ያለም ተስፋ
ያለምወሰን - ያለምጥላ - ያለምፍቅር

984. **ያለው**
የተናገረው ፣ ያዘዘው ፣ የፈቀደው ፣ የወ
ደደው ማለት ነው ።
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።
ያለው = የሚኖረው ማለት ነው።

985. **ያማረ - ያምራል**
መልኩ፣ ውበቱ፣ ግርማው፣ ደግነቱ፣ ቸር
ነቱ፣ ስራው ...።
ያባት ስም ቃልኪዳን ቢል ይገጥማል።

986. **ያረጋል**
ብጥብጥን ያረጋጋል፤ ይፈጽማል ...።
ያባት ስም በፈቃዱ ቢል ይገጥማል።

987. **ያሬድ** (ዕብ.)
ወረደ ማለት ነው ።
በዘመነ አበው የመላልኤል ልጅ ያሬድ
ይባል ነበር። ያሬድም ሄኖክን ወልዷል
(ዘፍ. 5፥15) በዚህ ስም ታዋቂው ኢትዮጵ
ያዊው የቤተ ክርስቲያን የዜማ ደራሲ
ቅዱስ ያሬድ ተጠርቶበታል።

988. **ያሳብነኽ – ያሳቤ - ያሳብ**
ዘወትር በሕልም፣ በምኞት የነበርክ ...።
ያባት ስም ተመስገን ቢል ይገጥማል።

989. **ያብራዓለም**
እንደ ብርሃን፣ ፀሓይ፣ ኮከብ፣ ጨረታ።
ያባት ስም ፋና ቢል ይገጥማል ።

990. **ያብባል**
ዐዲሱ ችግኝ ፣ ዘር፣ ተክል ...።
ያባት ስም ዘወትር ቢል ይገጥማል።

991. **ያንተነው**
የራስህ ፣ የሚመስልህ ...።
ያባት ስም ግዛቸው ቢል ይገጥማል።
ያንተይኹን - ያንተአምላክ

992. **ያንጥፍወርቅ**
ይጎዝጉዝ ...።
ያባት ስም በፈቃዱ ቢል ይገጥማል
ያንጥፍ – ያንጥፉ

993. **ያዕቆብ** (ዕብ.)
ተረከዝን ይይዛል (አኃዜ ሰኮና) ማለት
ነው። ጠባዩን ይገልጻል፤ የይሥሐቅ ልጅ
ነው ፤ ወንድሙ ኢሳው ነው።
በሐዲስ ኪዳንም ሐዋርያው ያዕቆብ እና
ሌሎችም በዚህ ስም ተጠርተውበታል
(ዘፍ. 25፥19–26)

994. **ያዛቸው - ያዘው**
ጀግንነትን፣ ብርቱ መኾንን ያመለክታል።
ያባት ስም ነብሮ ቢል ይገጥማል ።

995. **ያየህይራድ**
የጀግንነትን፣ ግርማ ምገስ የተላበሰ መኾኑን
ያመለክታል ። **ያየህ - ያይኔብርሃን**
ያየሰው - ያይንዋጋ - ያይናዲስ

996. **ያደቴ** (ኦሮ) **ያደታ - ያደሳ**
አሰታወስኩኝ፤ አሰታወሰ (በትክዜ) ማለት
ነው።

997. **ያደግድጉ**
ሸር ጉድ ይበሉ፣ ይታጠቁ፣ ያሸርጡ ...።
ለክብርህ፣ ለውበትህ ...።
ያባት ስም በሐርወርቅ ቢል ይገጥማል።

998. **ያገርሰው – ያገርፋሬ**
ወገኔ፣ ተወዳጅ ...።
ያባት ስም አየሁ ቢል ይገጥማል።

999. **ያፈት** (ዕብ)
ከኖኅ ልጆች ከካም ከቤም አንዱ አባቱ
የመረቀው ነው (ዘፍ.5፥32 ፤ 6፥10)።

1000. **ይኼወርቅ**
ውበትን ፣ ቁንጅናን ያመለክታል ።
ያባት ስም ዱባለ ቢል ይገጥማል።

1001. **ይኼነው**
እሱ ነው። እንደዚህ ነው ...።
ያባት ስም ኅብረት ቢል ይገጥማል።

1002. **ይህዓለም**
አስደናቂ፣ የሚያምር፣ የሚያታግል ...።
ያባት ስም አሸናፊ ቢል ይገጥማል።

1003. **ይለካል**
ቁንጅናው፣ ቁመናው፣ ክብደቱ ...።
ዋጋው፣ በሚዛን፣ በስንዝር፣ በሜትር ...።
ያባት ስም ውለታው ቢል ይገጥማል።

1004. **ይለፈኝ**
መአቱ፣ ቁጣው፣ መከራው ...።
ያባት ስም በጊዜው ቢል ይገጥማል።

1005. **ይልሃል - ይላላ**
ይነግርሃል፣ ጥበብ፣ ሥርዓት፣ ሃይማኖት ...።
ያባት ስም ዘወንጌል ቢል ይገጥማል።

1006. **ይላቅ - ይልቃል**
ይብለጥ፣ ከፍ ከፍ ይበል ...።
የአባት ስም ፍቅሬ ቢል ይገጥማል።

1007. **ይልማ**
ይለምልም፣ ዘሩ አዝመራው ይብዛ ...።
በዚህ ስም ለኢትዮጵያውያን ዘፋኞች የዘፈን ግጥም በመግጠም ድርሰት ይደርሱ የነበሩት የኪነጥበብ ሰው ገጣሚ **ይልማ** ገብረ አብ ይታወቁበታል። -
ይልማሸዋ - ይልማወርቅ

1008. **ይመር - ይመሩ**
ቆንጆ ይኹን፣ በሥራው፣ በዕውቀቱ፣ በችሎታው፣ በጠባዩ ...።
ያባት ስም በጸጋው ቢል ይገጥማል።

1009. **ይመስገን**
ለገሰኝ፣ አበረከተልኝ ጌታ፣ ፈጣሪ ...።
ያባት ስም ሰጠኝ ቢል ይገጥማል።

1010. **ይመኑ - ይመን**
በሃይማኖት፤ ሃቁን ይቀበሉ ...።
ያባት ስም በእውነቱ ቢል ይገጥማል።

1011. **ይማለደኝ - ይማልድ**
ያስታርቀኝ፣ ይርዳኝ፣ ይለምንልኝ ...።
ያባት ስም መልአኩ ቢል ይገጥማል።

1012. **ይማር - ይምረኝ**
ይቅር ይበለኝ፣ ምሕረት ይድርግልኝ ...።
ያባት ስም በፈታዱ ቢል ይገጥማል።

1013. **ይምጡበዝና**
ወሬውን ሰምተው፣ ታላትነቱን ተረድተው
ያባት ስም ዓለምቱና ቢል ይገጥማል።

1014. **ይርጋ**
ይረጋጋ ፣ መነዋወጡ፣ ሰላም ማጣቱ ...።
ያባት ስም ዓለሙ ቢል ይገጥማል።
ይርጋወሰን - ይርጉ - ይረጋል
ይርጋልኝ - ይርጋው - ይርጋለም
ይርጋሸዋ

1015. **ይርበብ**
ይዘርጋ፤ ጸጋው፣ ስጦታው ...።
ያባት ስም ከንፉ ቢል ይገጥማል።

1016. **ይርዳው**
ይደግፈው ...።
ያባት ስም ሚልዮን ቢል ይገጥማል።
ይርዳቸው - ይርዳ

1017. **ይሰማ**
ይረዳው ፣ ይነገረው ፤ ወደ ዐዲስ ዓለም መምጣትኽን ...።
ያባት ስም ዳኛቸው ቢል ይገጥማል።
ይሰማው - ይሰማሸዋ

1018. **ይሥሐቅ (ዕብ.)**
መደሰት ወይም ይሥቃል ማለት ነው በአር ጅና ዘመን ልጅ እንዲት ይወለዳል ብላ ሥቃ ነበርና በዚሁ ተጠራ
(ዘፍ. 17፣17 ፤ 18፣9)።

1019. **ይሰገድ - ይሰገዱ**
ያጎንብስ፣ ይንበርበሩ፣ ማለት ነው።
ያባት ስም ለአምላክ ቢል ይገጥማል።

1020. **ይሰፋልኝ - ይሰፋሸዋ**
በዓለም ይዳረስ ...። ከጠባብ ወደ ሰፊ ...።
ያባት ስም ዝናዬ ቢል ይገጥማል።

1021. **ይሳለሙ - ይሳለሙህ**
ይስገዱ፣ ያደግድጉ፣ ለኩብርህ ...።
ያባት ስም በላቸው ቢል ይገጥማል።

1022. **ይቁም - ይቁምላቸው**
በሕይወት ይቆይ፣ ቀጥ ይበል ...።
ያባት ስም ትንቢቱ ቢል ይገጥማል።

1023. **ይቅርታ - ይቅርታው**
ይቅር ለአግዚአብሔር ፤ ከኹሉ ይበልጣል ...።
ያባት ስም በልአንተ ቢል ይገጥማል።

1024. **ይቅደም**
መጀመሪያ ይኹን ...።
ያባት ስም በዕውቀቱ ቢል ይገጥማል።

1025. **ይበል - ይበልጣል**
ይናገር፣ ይወደዳል ፣ ይድገመው ...።
ያባት ስም በሱፈቃድ ቢል ይገጥማል።

1026. **ይበቃል**
በቃ ስጦታው ...።
ያባት ስም በጎበው ቢል ይገጥማል።

1027. **ይበይን**
በዳኝነት ይመልከት ፤ ይታይ ...።
ያባት ስም በፍርዱ ቢል ይገጥማል።

1028. **ይባስ**
ይበልጥ ...። የተሻለ ...።
ያባት ስም አሠጋኸኝ ቢል ይገጥማል።

1029. **ይባቤ** (ግእ)
የበዘ ካለው ግስ የወጣ ነው። አልል አለ ፣ ዘፈነ ። አልልታ ማለት ነው።

1030. **ይቤ** (ግእ) አለ ማለት ነው
ያባት ስም በቃሉ ቢል ይገጥማል።

1031. **ይብለጥ**
በችሎታው፣ በዕውቀቱ፣ በሥራው...።
ያባት ስም ምሲጋና ቢል ይገጥማል።

1032. **ይብዛወርቅ**
ይጨመር ...።
ያባት ስም ምኞቱ ቢል ይገጥማል።

1033. **ይብቃ**
ተጨማሪ አይኑር ...።
ያባት ስም ሀብቴ ቢል ይገጥማል።

1034. **ይነገር**
ለሰው ይወራ፣ ዜናው ይሰማ ...።
ያባት ስም ታምራት ቢል ይገጥማል
ይነግሩታል - ይናገር - ይናገሩ

1035. **ይታረቅ**
ሰላም ይኹን፣ ሥራ ይሠራ ...።
ያባት ስም አገሬ ቢል ይገጥማል።

1036. **ይታየው**
ግልጽ ኾኖ፣ በጥራት፣ በርቀት ...።
ያባት ስም ፍኖተጽዮን ቢል ይገጥማል።
ይታያል - ይታይ - ይታዩ
ይታይህ - ይታጠቁ - ይታፈሩ

ወ

1037. **ይታገሡ**
መከራን፣ ሰቃይን፣ ይቻሉ፣ ዝም ይበሉ፣ ተሰፋ ያድርጉ ...።
እነሆ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላ ቸዋለንን፤ ኢዮብ እንደ ታገሠ ሰምታችኋል (ያዕ. 5፥11)።

1038. **ይትመሐር** (ግእ)
ምሕረት ያግኝ ማለት ነው።
ያባት ስም በዕድሉ ቢል ይገጥማል።

1039. **ይትረፍ**
ከሞላው፣ ከተጨመረው፤ ከአደጋው ...።
ያባት ስም ምስክር ቢል ይገጥማል።

1040. **ይትባረክ** (ግእ)
ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዊነ። ትርጉም፤ ያባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ማለት ነው (ጸሎ. ዳን. 3፥26)።
የዐፄ ላሊበላ ልጅ የመጨረሻውን የዛጔ መንግሥት ይዞ የነበረው ይትባረክ ተብሎ ይጠራ ነበር።

1041. **ይትፈሣሕ** (ግእ)
ይደሰት ማለት ነው ።
ያባት ስም በጎይሉ ቢል ይገጥማል።

1042. **ይጌይስ** (ግእ)
ይጌይስ ተአምኖ በእግዚአብሔር
እግዚአብሔርን መታመን ፣ ማመስገን መልካም ነው (መዝ. 91(92)፥1)።
ያባት ስም ተአምኖ ቢል ይገጥማል።

1043. **ይነሡ – የነሡልኝ**
ይቁሙ፣ ከእንቅልፍ፣ ከቸልኝነት ...።
ያባት ስም ወገኔ ቢል ይገጥማል።

1044. **ይነጋል**
ፀሓይ ይወጣል፣ እንደ ጨለመ አይቀርም ብርሃን ይታያል ፣ ፀሓይ ይሞቃል ...።
ያባት ስም በላቸው ቢል ይገጥማል።

1045. **ይኑርሰው – ይኑር**
በሕይወት ሰው ኹሉ ይኑር፤ ምረታ ነው። በሰላም፣ በጤና፣ በፍቅር፣ በመተሳሰብ።
ያባት ስም ባላገር፣ ከተማ፣ በዓለም፣ ቢል ይገጥማል።

1046. **ይንገሥ**
ክብር ያግኝ ፣ ይምራ፣ ዘውድ ይድፋ፣ ወገንን ይጥቀም፣ አገርን ያቅና ...።
ያባት ስም እውነቱ ቢል ይገጥማል።

1047. **ይክበር**
በሥራው፣ በችሎታው ...።
ያባት ስም ዳኖቹው ቢል ይገጥማል።

1048. **ይኩኖአምላክ** (ግእ) ይኩኖ ዐፄ ይኩኖ አምላክ ወላጆቻቸው ያወጡ ላቸው ስም ተሰፋ ኢየሱስ ነበር ።
ሐምሌ 12 ቀን 1262 ዓ. ም. በአቡነ ተክ ለሃይማኖት ትብዐ መንግሥት ተቀብተው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ኾነው መንግ ሥትን ከዛጔ ያመጡ ናቸው ። ዕመ መን ግሥቱ ይኩኖ አምላክ ነው። ይኹን የአ ምላክ ማለት ነው።

1049. **ይኹን**
ይኩን ግእዝ - ሀብት፣ ረዳት ...።
ያባት ስም እንዳላማው ቢል ይገጥማል።
ይኹንሰው - ይኹነው - ይኹኔ
ይኹንየበላይ - ይኹንጸጋ - ይኹናል

1050. **ይድነቃቸው**
በዚህ ስም የሚታወቁ **የነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ልጅ ይድነቃቸው ተሰማ ናቸው ።**
ዕድሜያቸውን በሙሉ ለኢትዮጵያ እግር ኳስ ዕድገት ሲሠሩ የኖሩ ነበሩ።
ይደንቃል - ይድነቀው - ይደነቁ
ይደነቅ

1051. **ይደግ**
ከፍ ከፍ ይበል፣ በቁመት፣ በዕድሜ፣ በጤንነት፣ በሀብት፣ በሥራ ...።
ያባት ስም ለታሪክ ቢል ይገጥማል።

1052. **ይድከሙ**
ያለ ልፋት ፤ ያለ ድካም ዋጋ አይገኝም።
ያባት ስም ሊቃውንት ቢል ይገጥማል።

1053. **ይግረማቸው**
ይደነቁ ሌላ ተጨመረ ...።
ያባት ስም **ቢልልኝ** ቢል ይገጥማል።
ይገረሙ - ይገረም - ይግረመው
ይግረም - ይገርማል

1054. **ይገሥግሡ**
በማለዳ ፣ በሸዋት ተነስተው ቶሎ በቶሎ ይኺዱ፤ ይቅደሙ ...።
ያባት ስም ለዕለት ቢል ይገጥማል።

1055. **ይገባኻል – ይገባዋል**
ለበጎ ሥራህ ፣ ለመልካምነትህ
ወርቅ፣ ስጦታ፣ ይገባሃል ...።
ያባት ስም ክብሩ ቢል ይገጥማል።

1056. **ይግዛው**
አገሩን ፣ ሕዝቡን ...። ለማለት ...።
ያባት ስም ጥበቡ ቢል ይገጥማል።
ይግዛቸው - ይገዙልኝ - ይገዙ

1057. **ይገደብ**
ይከለል፣ ለእኛ ጥቅም ይዋል ...።
ያባት ስም ዓባይ ቢል ይገጥማል።

1058. **ይግለጡ**
ምስጢሩ ይታወቅ፣ ይታዩ፣
ያባት ስም በጊዜው ቢል ይገጥማል።

1059. **ይጐዝጕዙ**
ይደላደሉ ፣ ይመቻቹ ...።
ያባት ስም በላቸው ቢል ይገጥማል።

1060. **ይጥና – ይጥናጋቸው**
ይጠንክር፣ ባለበት ይቆይ ...።
ያባት ስም በጸሎት ቢል ይገጥማል

1061. **ይፍረድ**
ይዳኝ ፣ ፍርድ ይስጥ ...።
ያባት ስም ታሪኩ ቢል ይገጥማል።
ይፋረዱ - ይፍረደው - ይፋረድ

1062. **ይፍሩ – ይፍራቸዋ**
ይሰጉ ፣ ይደንግጡ ...።
ያባት ስም ምስክር ቢል ይገጥማል።

1063. **ይኩራባቸው**
ተቆነንባቸው፣ ይጓደድባቸው ...።
ያባት ስም በሥልጣኑ ቢል ይገጥማል።

1064. **ዮሐንስ** (ዕ.ብ)
የአምላክ ስጦታ፣ ደስታና ምሕረት፤ ለጋስ ማለት ነው ። በዚህ ስም ብዙዎች ተጠር ተውበታል ፤ መጥምቁ ዮሐንስ ፤ ወንጌላ ዊው ዮሐንስ ሌሎችም (የሐ. 1፥1) በኢት ዮጵያውያን ነገሥታቱ ጭምር ተጠርተው በታል ።

1065. **ዮርዳኖስ** (ዕብ.)
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበት ወንዝ ዮርዳኖስ ይባላል (ማቴ. 3)።
ትርጓሜው የዳን ወንዝ ማለት ነው።
ዳን ከ12ቱ የእስራኤል ልጆች አንዱ ነው

1066. **ዮሴፍ** (ዕብ.)
ይጨምር ማለት ነው ።
በብሉይ ኪዳን የያዕቆብና የራሔል ልጅ መጠሪያ ነው ። ዮሴፍ በባርነት ለግብጽ ፈርኦን ተሸጦ ነበር ። በዚያም እግዚአ ብሔር ጐብኝቶታል። በዚህ ስም በዐዲስ ኪዳን የተጠሩ ብዙዎች ናቸው (ዘፍ.30፥22) ።

1067. **ዮሴዴቅ**
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ ደጃዝማች ዮሴዴቅ ከጎጃም ባላባቶች አንዱ ነበሩ።

1068. **ዮናስ** (ዕብ.)
ርግብ ማለት ነው። ዮናስ በዐሣ አንበሪ ሆድ ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት ቈይቷል። በኋላም ወደ ነነዌ ከተማ ኼዶ ንስሓ እን ዲገቡ ሰብኳል ፤ ነነዌም ከተማ በዮናስ ስብከት ከመጣው ቊጣ ተርፋለች (ትን. ዮና. 1፥1) ።

1069. **ዮናታን** (ዕብ.)
እግዚአብሔር ሰጥቷል ማለት ነው።
(1ኛ ሳሙ.14፥49 ፤ 1ኛ ዜና 8፥33)።

1070. **ዮፍታሔ** (ዕብ)
ከእስራኤል መሳፍንት አንዱ ነው።
(ዕብ. 11፥32 ፤ ዘዳ. 12፥29)።
በኢትዮጵያ ቀኝ ጌታ ዩፍታሔ ንጉሤ የተባሉ የተውኔትና የቅኔ ምሁር ነበሩ።

- ደ -

1071. **ደለለኝ - ደለለው - ደለሉ**
አሞኘኝ፣ አታለለኝ ፣ ሸነገለኝ ፣ የማያደ ርገውን አደርገዋለሁ አለኝ (ኤር 4፥30)።
ያባት ስም ባላሰብ ቢለ ይገጥማል።

1072. **ደመረ**
ሰበሰበ፣ አከማቸ፣ አንድ ላይ አደረገ ማለት ነው።
ያባት ስም ማዕርጉ ቢለ ይገጥማል።
ደመረወርቅ - ደመራው - ደምረው

1073. **ደመራሽ** (ዶር)
አገኘሁ ማለት ነው ።

1074. **ደመቀ**
ገነነ፣ ጐላ፣ አማረ፣ (ዘጸ. 26፥36)።
ያባት ስም ማኅተቤ ቢለ ይገጥማል።
ደመቃ - ደመቆ - ደመቀልኝ

1075. **ደመቅሳ** (ኦሮ)
አነቃ ፣ አነቃቂ ማለት ነው።

1076. **ደመወዝ (ደሞዝ)**
በልዩ ልዩ አይነት አንደ ሥራው የሚከ ፈል ዋጋ (ዘፍ. 29፥15 ፤ ዘሌ. 19፥13 ፤ ሉቃ. 10፥7፤ ሮሜ. 4፥4፤ ኤር. 22፥13)።
ያባት ስም ስጠኝ ቢለ ይገጥማል።
ደሞዜ - ደመወዙ

1077. **ደሜ** (ኦሮ) - **ደማ**
ማሬ (ማር) ማለት ነው ።
ያባት ስም በዳዳ ቢለ ይገጥማል።
ደማ ሲለ ጣር፣ ጣሬ

1078. **ደማም**
መልክ መልካም ፣ ደሙ ውበቱ አባቱን የሚመስል ።
ያባት ስም ተገኘ ቢለ ይገጥማል።
ደማሙ - ደሙ - ደመልሽ

1079. **ደምሰው**
በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በፍርድ በዋቂነታቸው ታዋቂ ዳኛ የነበሩ የአፈ ንጉሥ ነሲቡ መሰቀሌ ልጅ ራስ ደምሰው ነሲቡ ይባሉ ነበር። **ደምሌው - ደምሴ**
ደምሱ - ደምሳቸው - ደምስ
ደምስስ - ደምስሳቸው - ደምሳ

1080. **ደምቦባ** (ኦሮ)
ትዕግሥተኛ ማለት ነው።
ሸንበቆ ማለት ይኾናል ።

1081. **ደረሰ - ድረሴ**
ደረሰ፣ ድርሰት ደረሰ፣ ተቀኘ፣
ኼደ፣ መጣ፣ ተመለሰ፣ ከተፍ አለ።
ያባት ስም ወንድሙ ቢለ ይገጥማል።
ደረሰላቸው - ደርሶልኝ - ደረሰልኝ
ደረሰው - ደረሰኝ - ደረሱ - ደረሳ
ደርሶኽ - ደረሳ - ደረሰኽ - ደረሶ

1082. **ደርበው**
ደረበ ጨመረ ፤ ጨምረው ፣ ኹለተኛ አድርግ ፣ ደራርበው ...።
ያባት ስም ደስታ ቢለ ይገጥማል።
ደረቡ - ደርብ - ደረባ
ደርቤ - ደርባቸው - ዲረባ (ኦሮ)

1083. **ደረጀ - ደረጄ - ደረጃው**
ተመቻቸ፣ ተደላደለ፣ በሀብት ላይ ሀብት ጨመረ፤ ወገን አዘዘ፣ ሥር ሰደደ፣
ያባት ስም በሀብቱ ቢለ ይገጥማል።

1084. **ደራሽ**
ድንገት የኾነ ድንገት የመጣ ማለት ነው።
ደራ - ደራው
ያባት ስም ገበያው ቢለ ይገጥማል።

1085. **ዴራሳ** (ኦሮ)
ረኽም ማለት ነው።
የወለጋ ተወላጅ የነበሩ በጣሊያን ጊዜ ውጭ አገር ተምረው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሠሩ የነበሩ **ይልማ ዴራሳ** አባታቸው ዴራሳ በመባል ይታወቃሉ ።

1086. **ደርዛ** (ዶር)
ብዙነኽ ማለት ነው።

1087. **ደርግ** (ግእ)
አንድነት ማለት ነው። ዳርጌን ተመልከት

1088. **ደሴ**
የወሎ ከተማ ...።
ያባት ስም ተሻገር ቢለ ይገጥማል።

1089. **ደስታ**
ድሎት፣ ተድላ፣ ፍሥሓ፣ ምቾት፣ ሀዘን ትካዜ የሌለበት ። በጌታ ኾል ጊዜ እን ድንደሰት ተነግሯል።
መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ውስጥ የሚፈጥረ ው ስሜት ደስታ ነው (መዝ. 103፥31 ፤ ዮሐ. 5፥11 ፤ ገላ. 5፥22 ፤ ፊልጵ. 4፥4፤ 1ተሰ. 5፥16)።
በዚህ ስም በመጠራት ከሚታወቁት አንዱ ዐርበኛ ራስ ደስታ ዳምጠው ናቸው።
ደስታዓለም - ደሱ - ደሳለኝ
ደስታኹን - ደሳለ - ደስታው
ደስታዬ - ደሳለው - ደስዬ
ደሳለን - ደስይሳለ

1090. **ደቅስዮስ**
ቅድስት ድንግል ማርያምን በጣም የሚ ወድ ሰው ነበር። ተአምራቶቿን አሰብስቦ ያጻፈ የጥልጥልያ ሊቀ ጳጳስ ነው።

1091. **ደበሌ** (ኦሮ)
ጨመረ፣ ደገመ ማለት ነው። በገዳ ሕግ ዕድሜያቸው ከ17- 24 ዓመት የኾኑት ወን ድና ሴቶች **ደበሌ** ተብለው ይጠራሉ።
ደበላ (ኦሮ) ደገመ ወይም ድጋሚ።
ደበላ (ዐማ) ስራስ ጥምጥም የሚኾን ሻሽ።

1092. **ደበበ** (ግእ)
ጥላ ዘረጋ፣ ከለለ ወጠረ ማለት ነው።
ያባት ስም ፍቅሩ ቢል ይገጥማል።

1093. **ደባልቀው - ደባልቄ**
አዋሕደው፣ ቀላቅለው ...።
ያባት ስም ደባለኝ ቢል ይገጥማል።

1094. **ደብሩ**
ከፍታ ቦታ ፤ ደብረ ሊባኖስ። ትርጉም፤ የሊባኖስ ተራራ። ደብረ ጽዮን ዘአፍቀረ። ትርጉም ፤ የወደደውን የጽዮንን ተራራ (መዝ. 77(78)፥68)።
ደብራቸው - ደብረወርቅ - ደብራይ

1095. **ደቻሳ** (ኦሮ)
መለሰ ማለት ነው ።
በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የግቢ ወታ ደር ታማኝ የነበሩ ቀኛዝማች ደቻሳ ይባሉ ነበር።

1096. **ደኅናሰው**
ጥሩ፣ መልካም፣ በጸባዩ፣ በሥራው ...።
ያባት ስም ገበየሁ ቢል ይገጥማል።
ደኅና - ደኅናዬ - ደኅኔ - ደኅንነት

1097. **ደነቀው**
አስገረመው ...።
ያባት ስም ቢተው ቢል ይገጥማል።
ደነታቸው - ደነቀ - ድንቄነህ
ዲንታ (ኦሮ) - ደንታም

1098. **ደነገጡ**
ድንገት የኾነ ነገር፤ ያልታሰበ ነገር ...።
ያባት ስም አልታሰብ ቢል ይገጥማል።

1099. **ደንድር** (ጉራ)
ወፍራም ማለት ነው።

1100. **ደይጸ** (ዶር) ከበደ ማለት ነው

1101. **ደጀን**
ተከላካይ፣ ከለላ፣ ከፊት የሚኾን ...።
ያባት ስም አገኘኹ ቢል ይገጥማል።
ደጀኔ - ደጀናቸው - ደጀኑ

1102. **ደጅይጥና**
በደጅ ይቀመጥ፣ ይቆይ ...።
ሹመት፣ ሽልማት ፈለገ በደጅ ታየ።
ያባት ስም ሲያምረኝ ቢል ይገጥማል።

1103. **ደገመኝ – ደገሙ**
ደግሞ ሰጠኝ፣
ያባት ስም በረከት ቢል ይገጥማል።

1104. **ደገፉ** (ኦሮ)
መደገፍ ማለት ነው። **ደገፋ - ደግፈ**
ደጋፊ - ደግፍ - ደግፋቸው

1105. **ደጉ**
ጥሩው፣ ርኅራሔ ያለው ...።
ያባት ስም ታዬ ቢል ይገጥማል።

ደጉሰው - ደጉዓለም - ደግዋለ
ደጉና - ደጋቸው - ደጋጉ - ደጌ
ደግነህ - ደግነቱ - ደግነት - ደግነው

1106. **ደፋር**
ጀግንነትን ያመለክታል ...።
ያባት ስም በጋሻው ቢል ይገጥማል።
ደፈረ - ደፋሩ - ደፈረው - ደፈረ

1107. **ደፋ** (ዶር) ሳዘው ማለት ነው።

1108. **ዱባለ**
ሳይታሰብ መጣ፣ ወረደ ማለት ነው።
ዱባ - ዱቤ ከብደትን ያመለክታል።

1109. **ዲሜጥሮስ** (ግሪ)
ተከታይ ማለት ነው፤ ወይም ደግሞ እናት መሬት ማለት ይኾናል። የመጀመሪያውን የኢትዮጵያውያንን የዘመን አቈጣጠር የቀ መረ አባት ነው።

1110. **ዲታ**
ሀብታም ማለት ነው።
ዲታም - ዲንሳ - ዲንሳሞ - ዲኖ

1111. **ዲንግዴ** (ጉራ.ኦሮ) ሀብት
የምኒልክ ጦር አዘጋዝ የነበሩ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ አባታቸው **ዲንግዴ** ይባሉ ነበር ።

1112. **ዳመነ - ዳመና - ዳመኔ**
ዝናብ ሊዘንብ ምልክት አሳየ ...።
ያባት ስም በረከት ቢል ይገጥማል።

1113. **ደመረ - ዳመራው**
ደመረ ካለው ግስ የወጣ ነው። ጨመረ፣ ቀላቀለ፤ አንድ አደረገ ማለት ነው።
ያባት ስም መስቀሌ ቢል ይገጥማል።

1114. **ዳምጠው – ዳምጤ**
ቀጥ አድርገው፣ አስተካከለው፤ ጥጥን ከፍሬ ለይ፤ ደፍጥጠው ለማለት ...።
በዚህ የሚጠሩት ታዋቂ ዐርበኛ ራስ ደስታ ዳምጠው አባታቸው ፊታውራሪ ዳምጠው ከተማ በ1888 ዓ.ም. አደዋ ላይ የተዋደቁ ናቸው። - **ዳምጣቸው**

1115. **ዳርምየለው**
መጨረሻ፣ ፍጻሜው አይታወቅም ...።
ያባት ስም ገብያው ቢል ይገጥማል ።
ዳርሰማ - ዳርቻ

1116. **ዳርዮስ**
በዚህ ስም የሚጠሩ ሦስት ሰዎች በቅ ዱስ መጽሐፍ ተጠቅሰዋል ። ከነዚህም ውስጥ አንዱ በበጉንቱ ይታወቃል ። ዳር ዮስ የሂስታስጲስ ልጅ የፋርስ ንጉሥ ጎያ ል የነበረና በክብር የእንደኛነትን ማዕረግ ያገኘ ሰው ነው (ዕዝ. 4-6 ፤ ሐጌ. 1፥1)።

1117. **ዳርጌ** (ግእ. ኦሮ)
በዚህ ስም የተጠሩ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ልጅ የንጉሥ ጎይለ መለኮት ወንድም የዐፄ ምኒልክ አጎትና የልዑል ራስ ካሣ ጎይሉ አያት ራስ ዳርጌ ሣህለ ሥላሴ ናቸው ። ደርጉ - ደርጋ - ደርጌ

1118. **ዳባ** (ኦሮ)
በዚህ ስም የሚታወቁት የወለጋው ተወ ላጅ ዐርበኛ ፊታውራሪ ዳባ ብሩ ጮርቃ ናቸው (1889 - 1935 ዓ.ም.)።

1119. **ዳን** (ዕብ.)
ዳኛ ማለት ነው (ዘፍ.30፥6) ይህ ሰው ከራሔል አገልጋይ የተወለደ ነው ። (ዘፍ. 30፥6)

ዐ

1120. **ዳንኤል** (ዕብ)
ዳን ማለት ዳኛ ቢኾን **ኤል** እግዚአብሔር ማለት ነው። እግዚአብሔር ፈራጅ ዳኛ ነው ማለት ነው። (ዳን. 1፥1) በዚህ ስም ብዙ ኢትዮጵያውያን ይጠሩበታል።

1121. **ዳኛቸው**
ፍረድላቸው፣ ገላግላቸው ማለት ነው። ያባት ስም ተፈራ ቢል ይገጥማል ። ደጃዝማች ዳኘው ተሰማ በጣሊያን ጊዜ በማይጨው ታዋቂ ከነበሩት ዐርበኞች አንዱ ነበሩ።
ዳኜ - ዳኘው - ዳኘ - ዳኝነት - ዳኙ

1122. **ዳዊት** (ዕብ) ዳውድ (ዐረ)
ልበ አምላክ፤ ቅንና ተወዳጅ ማለት ነው። ከእስራኤል ነገሥታት ዅሉ ተወዳጅና ታላቅ የኾነ ነበር ። ዳዊት እና ዮናታን በጣም ፍቅር ነበሩ ። ብዙ ኢትዮጵያው ያን ነገሥታት ጭምር ተጠርተውበታል።

1123. **ዳዲ** (ኦሮ) ጠጅ ማለት ነው።

1124. **ዳግም**
ዅለተኛ፣ ታናሽ፣ ተከታይ፣ ምትክ ማለት ነው። **ዳግማዊ - ዳግምብርሃን**
ያባት ስም ወንድማገኝ ቢል ይገጥማል።

1125. **ዳጪ** (ኦሮ)
የራስ ጎበና ዳጪ አባት በዚህ ስም ይታ ወቁ ነበር። **ዳጩ - ዳጮ**

1126. **ድል-ነአድ** (ግእ)
በ1ሺ ዓ. ም. የነበረ የኢትዮጵያ ንጉሥ ስሙ ድልን የሚንድ የሚያፈርስ ለማለት ድልነአድ በመባል ይታወቃል።

1127. **ድልነሳኹ - ድልነሳው**
አሸንፍኩ፣ ማረኩ፣
በጦርነት፤ በፍቅር፤ በችሎታ ...።
ያባት ስም ብዙሰው ቢል ይገጥማል።
ድልለረጋቸው - ድላረገ - ድላረጋቸው - ድልገባ

1128. **ድምበሬ** (ድንበሬ)
የኔ ክልል ፣ የአጥሬ፣ የቦታዬ ክልል።
ያባት ስም አድማሱ ቢል ይገጥማል።
ድንበሩ (ድምበሩ) - ድንበርነህ

1129. **ድርሻዬ**
የእኔ ድርሻ፣ ክፍሌ፣ አድሌ ለማለት...።
ያባት ስም ወየለ ቢል ይገጥማል።
ድርሻቸው - ድርሻ

1130. **ድባቤ**
ከሐርና ከወርቅ የተሠራ የታቦት ጥላ የወ ርቅ ዘርፍ ያለው። ድባቡ- ዲባባ (ኦሮ)

1131. **ድብኔ** (ጉራ)
ጨመረ ማለት ነው።

1132. **ድንቃየኹ (ድንቅአየኹ)**
የሚያስገርም ያማረ ፣ የተዋበ የደስ ደስ ያለው አየሁ ለማለት ነው።
ያባት ስም በፈቃዱ ቢል ይገጥማል።
ድንቅነህ - ድንቁ - ድንቅሰላሙ
ድነቁሳ - ድንቂ - ድንቁዬ - ድንቃ
ድንቃየ - ድንቃዩ - ድንቅሰው
ድንቂሳ - ድንቅሥራው - ዲንቃ

1133. **ድንገቱ**
ሳይታሰብ ዱብ አለ። ታየ፣ ወረደ ...።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።
ድንገቴ - ድንገታለም

1134. **ድጋፌ – ድጋፉ** (ዐማ ኦሮ)
ደጋፊዬ፣ ደግፍ ለማለት ነው ...።
ያባት ስም አርጋው ቢል ይገጥማል።

- ጀ -

1135. **ጀቤሳ** (ኦሮ)
አጠንክር ፣ አበረታ ማለት ነው።

1136. **ጀንበሬ - ጀንበሩ ጀንበር**
የፀሐይ ስም ትርጓሜዋ፤ ትልቅ ብርሃን ለማለት ነው። የምሽት ፀሐይ ፣ አየጣፈ ጠች የምትጠልቅ ።

1137. **ጀግናው - ጀግና**
ጎበዝ ፣ የማይበገር ፣ ለማንኛውም ነገር የማይሸነፍ ማለት ነው።
ያባት ስም አንተነህ ቢል ይገጥማል።

1138. **ጂፋር** (ኦሮ) **ጂፋራ - ጃፈሮ**
የጂማ ባላባት የነበሩ የሚጠሩበት።

1139. **ጃለታ** (ኦሮ) **ጃለል - ጃለቶ**
ወዳጅ የሚወድ ተወዳጅ ማለት ነው።

1140. **ጃራ** (ኦሮ)
አንድን ታሪክ አሳልፎ የሚነሣ ታሪክ ጂራ ማለት አለ ማለት ነው።

1141. **ጆርሶ** (ኦሮ) - **ጃርሳ**
ሽማግሌ አስታራቂ ማለት ነው።

1142. **ጃንጥራር**
የንጉሥ ጋሻ ፤ ያምባሰል ባላባት ስም።

1143. **ጆቴ** (ኦሮ)
በዚህ ስም በዐፄ ምኒልክ ዘመን ምዕራብ ወለጋን ይገዙ የነበሩ ደጃዝማች ጆቴ ቱሉ ነበሩ። ልጃቸው ወይዘሮ አስካለማርያም ጆቴ ልጅ ኢያሱን አግብተው ነበር።

- ገ -

1144. **ገለታ** (ኦሮ)
ወሮታ፣ ውለታ ወይም ምስጋና ማለት ነው ። በዚህ ስም የሚታወቁት ገለታ ቆሪች ናቸው። በጣሊያን ጊዜ ተዋቂ ዐርበ ኖ ነበሩ። **ገለቴ - ገለታው - ገለቶ**

1145. **ገላን** (ኦሮ)
የሞላ ጎርፍ፣ ወንዝ ብዛትን ያሳያል።
ስንቅ ነህ ማለት ነው።
ገላን - ገላና - ገላኒ - ገለልቻ

1146. **ገላው**
አካሉ ፣ ሰውነቱ ...።
ያባት ስም መዓዛ ቢል ይገጥማል ።
ገላኹን - ገላነው - ገላወርቅ
ገላዬነሽ - ገላ - ገላዬ

1147. **ገላውዴዎስ** (ግሪ)
በኢትዮጵያ የዐፄ ልብነ ድንግልና የቴጌ ሱበለ ወንጌል ልጅ ገላውዴዎስ ይባሉ ነበር ። ስመ መንግሥታቸው አድናፍ ሰገድ ነው።

1148. **ገላጋይ**
በ'መኽል ገብቶ የሚያስታርቅ ...።
(ማቴ. 5፥9)
ያባት ስም ማለደ ቢል ይገጥማል።
ገላግላቸው - ገላግል - ገላግሌ

1149. **ገመና**
የውስጥ ሚስጥር ... የግል ጉዳይ ...።
ያባት ስም አንተነህ ቢል ይገጥማል።

1150. **ገመቹ** (ኦሮ)
ደስታ ማለት ነው።
ገመቺ - ገመችሰ - ገመቺሳ

1151. **ገመዳ** (ኦሮ)
ደስተኛ ማለት ነው። **ገመዲ - ገመዱ**

1152. **ገሞራው** (ግእ)
ገመረ ቻለ ያዘ ከሚለው ፤ ብርቱ ፣ ኃይለኛ ፣ ጎበዝ ፣ አደጋና መከራን ቻይ ማለት ነው።
ገሞራው ካሳ የግሊያን ጦርነት ጊዜ በጀግንነት የታወቁ ዐርበኛ ነበሩ።
ገሞራ (ግእ) ቃሉ ሲጠብቅ ደግሞ የበሰለ ማለት ነው ፍሬው ገሞራ።

1153. **ገረመው**
ገረመ ካለው ግስ የወጣ አሰፈራ፣ ተገረመ ደነቀው ማለት ነው።
ገረመኝ - ገረመን - ገርሙት
ገረሙ - ገራሙ - ገርማሜ

1154. **ገሥገሥ**
በማለዳ በቶሎ ድረስ ፤ ተጣድፈህ ኺድ ማለት ነው።

1155. **ገረዚ** (ኦሮ)
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ ዐርበኛ ጀጃዝማች ገረሡ ዱኪ ናቸው።
(1897 - 1958 ዓ.ም.) ።

1156. **ገሪማ** (ግእ)
ድንቁ፣ የሚደነቁ፣ ተአምር ያደረጉ ...።
ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ ይሥሐቅ የሚባሉት ገሪማ ይባላሉ። የግብር ስም ነው።
የሚታሰቡት ሰኔ 17 ቀን ነው
ግሩምነህ - ገረማየ - ገራኝ - ግሩም

1157. **ገሩ - ገርየ - ገርባባው**
ደጉ፣ ሩኅሩኁ፣ ቸሩ ...።
ያባት ስም አንዳርጋቸው ቢል ይገጥማል።

1158. **ገሰሰ – ገሰሰው - ገሰሰ**
ዳሰሰ፣ ነካ፣ ዳበሰ፣ ማለት ነው።
ሌላው ትርጉም ፤ ገለበጠ ፍርድን ሻረ ይኾናል።
ያባት ስም በጎይሉ ቢል ይገጥማል።

1159. **ገበየኹ**
በዐደዋ ዘመቻ ከዐፄ ምኒልክ ታዋቂ የጦር አዛዥ የነበሩ ፊታውራሪ ገበየሁ እዛ ጎራው ነበሩ ።
የዲዋ ሥላሴን ጠላት እረከሰው፤
ገበየሁ በሞቴ ግባና ቀድሰው።
ተብሎ ስለጀግንነታቸው ተገጥሞላቸዋል።
ገበየኽ - ገበዩ - ገበያ - ገበያነኽ
ገበያው

1160. **ገብሬ** (ገብረ)
ልጄ ፣ አገልጋዬ ...። ማለት ነው
የክርስትና ስም ቅጽል ገብረ **ማርያም** ቢል ገብሬ ተብሎ በማኅጠር ይጠራበታል ።
ገብርዬ
በዚህ ስም የዐፄ ቴዎድሮስ የጦር አለቃ ፊታውራሪ ገብርዬ በክርስትና ስማቸው ገብረ ሕይወት ከእንግሊዙ የጦር ጀነራል ናፒየር ወታደሮች ጋራ ሲዋጉ ዐርብ የስቅለት ዕለት ማለፋቸው ይነገራል።
ገብሩ - ገብራይ (ትግ)
ገብረ ማርያም ክርስትና ስም።

1161. **ገነሜ**
ማለደ ማለት ነው።
በጋሞጎፋ ካምባ የቋራ ማርያምን ቤተክርስቲያን በ1912 ዓ.ም.የተከሉት ደጃዝማች ገነሜ የሚባሉ ናቸው። **ገነመ - ገነሞ**

1162. **ገነነ - ገናናው - ገነነው**
ዐየለ፣ በረታ፣ በጣም ከበረ፣ ታላቅ ኾነ ታዋቂ ኾነ ማለት ነው።... ።
ያባት ስም ጎይሌ ቢል ይገጥማል።

1163. **ገኑት** (ጉራ) ጻድቅ ማለት ነው።

1164. **ገና - ገናሽት**
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት የሚከበርበት ዓመታዊ በአል ።
ያባት ስም ልደቴ ቢል ይገጥማል።

1165. **ገንዘቤ - ገንዘብ - ገንዘቡ**
ሀብቴ፣ ዋጋዬ፣ ብሬ ...።
ያባት ስም ተካ፣ ቢል ይገጥማል።

1166. **ገንሸብተ** (ጉራ)
አስታራቂ፣ (ታረቀኝ ማለት ነው።

1167. **ገዛኸኝ**
ዋጋ አወጣህብኝ ...። ተቆጣጠርከኝ ...።
በሲድኒ (አውስትራሊያ) በተደረገ የኦሊምፒክ ውድድር በማራቶን አሸቅድድም አንደኛ በመኾን ያገሩን ስም ያስጠራ ገዛህኝ አበራ በዚህ ስሙ ይታወቃል ። የማራቶን ሽልማቱን ለአንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን ቤተ መዘክር ሰጥቶ ቱሪስት እየጐበኘው ነው። **ገዛኝ - ገዜ - ገዛኢ**
ገዙ - ገዛ - ገዛኸን - ገዛነው

1168. **ገደቡ — ገደበ - ገደብ**
አቆመ ፣ የቀን መጨረሻው ጊዜን ያመለክታል ...።
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።

1169. **ገድሉ - ገድሌ**
ሰማዕታት ስለ ክርስቶስ እጅ እግራቸውን ለሰንሰለት ዐይናቸውን ለፍላት ሰጥተው የፈጸሙት መንፈሳዊ ተጋድሎ። ጸድቃን በጸሎት መጋደላቸው ፤ መልካም ሥራ መሥራታቸው፤ ጾሙ፣ ጸሎቱ፣ ስግደቱ ኹሉ ገድል ይባላል ።
በክርስትና ስም ገድለ ጊዮርጊስ ይባላል።

1170. **ገዳ** (ኦሮ) የኦሮሞ ሕግ ነው።

1171. **ገዳመ**
የመነኰሳት ፣ የመነኰሳውያት መኖሪያ።
ያባት ስም ሊባኖስ ቢል ይገጥማል።
ገዳሙ - ገዳሜ - ገዳምነህ

1172. **ጉልቱ**
ርስት ፣ ቦታ ...።
ያባት ስም **ይበቃል** ቢል ይገጥማል።
ጉልተሞ - ጉልተ - ጉልቴ - ጉልታ

1173. **ጉርሙ** (ኦሮ)
ቅርንጫፍ ማለት ነው።
የአደአ ባላባት ማኛ አምራች ገበሬ የነበሩት ጉርሙ ጎበና ገዳ በዚህ ስም ተጠርተው ውበታል።

1174. **ጉዳ** (ኦሮ)
ጉዳ ታላት ወይም ትልቅ ማለት ነው።

1175. **ጉዲሳ** (ኦሮ) - **ጉደታ**
አደገ ማለት ነው።

የወዬ ጎይለ ሥላሴ ቅድመ አያት፤ የደጃ ዝማች ወልደ ሚካኤል አባት ጉዲሳ በመ ባል ይታወቃሉ ። ጉዲና

1176. **ጉግሳ** (አማ. ኦሮ)
በዚህ ስም የሚታወቁት የቴጌ ጣይቱ ብጡል ታናሽ ወንድም ልጅ በአናታቸው ደግሞ የንጉሥ ሚካኤል አጎት ከኾኑት የተወለዱ የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ባለቤት የነበሩ ራስ ጉግሳ ወሌ ናቸው።

1177. **ጉጂ** (ዶር) ጨመረ ማለት ነው

1178. **ጉልማ** (ኦሮ)
ለዘመድ፣ ለወዳጅ፣ ተከፍሎ የሚሰጠው ማሳ፣ ድርሻ ማለት ነው።

1179. **ጉልላት - ጉልላቴ**
አናት ፣ ከቤት ጣሪያ ላይ የሚደረግ።
ያባት ስም በላይነህ ቢል ይገጥማል።

1180. **ጉራቻ** (ኦሮ)
ጥቁር ማለት ነው።
የመልክ አይነት መግለጫ (ራእ. 6፥5)።

1181. **ጉበኛ**
ሰላይ ተመልካች። የበር ጠባቂ ዘበኛ ጉበ ኛ ሊባል ይችላል (2ሳሙ. 13፥34፤ ኢሳ. 21፥11 ፤ ሕዝ. 33፥2) ደራሲ አቤ ጉበኛ አባታቸው በዚህ ስም ይጠሩ ነበር።

1182. **ጊዜ ወርቅ**
ዘመን እንደ ዋዛ በቀልድ ማለፍ የለበትም በመሥራት፣ በጥናት፣ በመማር ...።
ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ጊዜ ይታሰባል (ዘፍ. 1፥1)።

1183. **ጋረደው - ጋረድ - ጋረጠው**
ገለው ካለው ግበ፤ ሸፈነ ፣ ደበቀ፣ ጋረደ ይወጣል።
ያባት ስም ፍቅሩ ቢል ይገጥማል።

1184. **ጋሻው - ጋሻዬ**
በአጅ የሚያዝ የጦር መከላከያ፤ የእምነ ትና የእግዚአብሔር ረድኤት ምሳሌ ነው።
(ኢሳ. 21፥5፤ መዝ. 34፥2፤ ኤፌ. 6፥16)።
ጋሻውጠና - ጋሻቸው - ጋሻኹን
ጋሻውበዛ - ጋሻነህ - ጋሻየንኽ

1185. **ጋድ** (ዕብ.)
ጥሩ ዕድል ያለው ማለት ነው፤ የያዕቆብ ከአገልጋዩ የወለደው ሰባተኛ ልጅ (ዘፍ. 30፥10..)።

1186. **ጋዲሳ** (ኦሮ)ጥላዬ ማለት ነው።

1187. **ጌራ** (ግእ)
የራስ ወርቅ ፣ የብረት ቆብ ፣ በአልማዝ የተንቆጠቆጠ ማለት ነው።

1188. **ጌታቸው**
አለታቸው ፣ ሀብታቸው ...።
ያባት ስም አማረ ቢል ይገጥማል።
ጌታመሳይ - ጌቱ - ጌታ
ጌታኹን - ጌታሰጠኝ - ጌታበለው
ጌታብሉት - ጌታነኽ - ጌታነው
ጌታወርቅ - ጌታው - ጌትነት

1189. **ጌዴዎን** (ዕብ.)
እግዚአብሔር በጎያልነቱ የጸናኘ ቀስተኛ ማለት ነው ። ከእስራኤል መሳፍንት አንዱ ነው (መጻ. መሳ. 6፥1– 8፥35)።

1190. **ጌጤ - ጌጡ**
ሽልማቴ፣ የሚያሰማምረኝ ፣ የሚያቆነጃ ጀኝ ... ማለት ነው።
ያባት ስም ታከለ ቢል ይገጥማል።
ጌጤኹን - ጌጤነኽ - ጌጤነው

1191. **ግሩም - ግሩምነህ**
የምትደነቅ ነህ ፤
ያባት ስም ጌታ ቢል ይገጥማል።

1192. **ግርማቸው - ግርማኹን**
የመፈራት የመወደድ የመልክ ውበት ደምግባት የሚያስደስት፣ የሚያስፈራልክ አንደ አንበሳ ምገስ ያለው።
(ግርማ ርእየቱ ለኤልያብ 1ኛ ሳሙ. 16፥6 ፤ 1ኛ ዜና. መዋ 14፥17)።
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ ከኢትዮጵ ያው ደራሲ፣ ታሪክ ጸሓፊ ደጃዝማች ግር ማቸው ተክለ ሐዋርያ ናቸው።
ግርማሚ - ግርማሞ - ግርማሞገስ
ግርማው - ግርማይ - ግርማ

1193. **ግምጃ**
ከልዩ ልዩ ሐርና ወርቅ የሚሠራ ልብስ፤ የወርቀ ዘቦ መጋረጃ ። ማስቀመጫ ቤቱ ግምጃ ቤት ይባላል።
ወይም የተቀለመ በፍታ (ምሳ. 31፥22)።

1194. **ግንባሩ**
ፍስፉቱ፣ ከዓይኑ በላይ ያለ ።
ያባት ስም ታዬ ቢል ይገጥማል።

1195. **ግዛው - ግዛቸው - ግዛቱ**
አስተዳድረው፣ ዋጋ አውጣበት ...።
በዚህ ስም የሚታወቁ ንቡረ እድ ግዛው አበራ የልዕልት ሣራ አባት ናቸው ። ዐርበኛ እንዱሁም የእክሱም ጽዮን ንቡረ እድ ነበሩ ።

1196. **ግዮን** (ዕብ)
ከዔዴን የሚወጣ ኢትዮጵያን ምድር የሚ ከብ ወንዝ (ዓባይ) (ዘፍ.2፥13)

1197. **ጎላ**
ደምቆ ታየ ...።
ያባት ስም ታሪኩ ቢል ይገጥማል።

1198. **ጎሐጽባሕ** (ግእ)
ንጋት ላይ ለማይና ምድር የተጋጠመበት ብርሃን ወገግታ ። በዚህ ሰዐት ላይ የተወ ለደ ጎሐጽባሕ ሊባል ይችላል።
በጽባሕ ስምዐኒ ታልየ፤ በጽባሕ አቀውም ቅድሜከ። ትርጉም ፤ በማለዳ ድምጼን ሰማኝ። በማለዳ በፊትህ እቆማለሁ (መዝ. 5፥2)። **ጎሕ - ጎሐ**

1199. **ጎመጂ - ጎመጀ**
ጉዋኑ ፣ ናፈቁ ...።
ያባት ስም በዝና ቢል ይገጥማል።

1200. **ጎርጎርዮስ** (ግሪ)
ጎርጎርዮስ የመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲ ያን አባቶች (380) ጎርጎርዮስ ዘንሲሱና ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዝ ናቸው ። በዚህ ስም ታዋቂው የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀጳ ጳስ አቡነ ጎርጎርዮስ በጽድስና ስም ተጠ ርተውበታል።

1201. **ጎበና** (ኦሮ)
በዚህ ስም የሚታወቁት በዐፄ ምኒልክ ዘመን መንግሥት ከነበሩት ታላላቅ ሹማ ምንትና የጦር አዘጋዞች አንዱ **የልጅ ሚካኤል** እምሩ አያት ራስ ጎበና ዳጪ የሚባሉ ናቸው ። በሰላሌ ሀገረ ስብከት በሱሉልታ ፋሲ ደብረ መድኀኒት መድኀኔ ዓለምን ተክለዋል።

1202. **ጎባ** (ዶር) ጎበዜ ማለት ነው።

1203. **ጎይቶም** (ትግ)
ጌታቸው ማለት ነው። **ጎይታ - ጎየታ**

1204. **ጎዳናው - ጎዳና**
መንገዱ፣ ቀጥ ያለው ረዥሙ መንገድ።
ያባት ስም ታደሰ ቢል ይገጥማል።

1205. **ጐረፈ - ጐርፍነህ - ጐርፋ**
በዝቶ መጣ ፣ ተሰብስቦ ደረሰ ...።
ያባት ስም ገበያው ቢል ይገጥማል።

1206. **ጐሥዓ** (ግእ)
አገሣ፣ ተናገረ ጐሥዓ ልብየ ቃለ ሰናየ።
ትርጉም ፤ ልቤ መልካም ነገርን አወጣ
(መዝ. 44(45)፥1)ቅዳ. ማር.)።

1207. **ጐሳ**
ነገድ ...።
ያባት ስም ተዋሐደ ቢል ይገጥማል።
ጐሳኹን - ጐሳዬ - ጐሳወርፈቅ
ጐሳዬነህ

1208. **ጐሸሜ**
ነካ አደረገ ፤ በክንድ ፣ በነገር ...።
ያባት ስም ክንዴ ቢል ይገጥማል።
ጐሸመ - ጐሸመ

1209. **ጐሹ - ጐሸየ**
የበሬ ዝርያ ፣ በሬ የሚመስል ተዋጊ እን
ስላ ፤ በጹር የሚኖር ተወዳጅ፣ ኃይለኛ
የኾነ ነው።
በዚህ ስም አራት ወይና ጐሹ የቤተ ክርስ
ቲያን ሊቅ ይጠሩበታል ።

1210. **ጐበዜ**
የኔ ጐበዝ ማለት ነው፤ ጠንካራ ኾነ ...።
ወጼ ተክለ ጊዮርጊስ ዳግማዊ (1860 -1864
ዓ.ም) ከወዜ ቴዎድሮስ ቀጥሎ ከወዜ
ዮሐንስ በፊት የነገሡ ናቸው ። ከንግሥና
ቸው በፊት ዋግ ሥዩም ጎበዜ ተብለው
ይጠሩ ነበር።
ጐበዘ - ጐበዛየኹ - ገበዝአ
ጐበዘይ - ጐበዝ - ጐበዝ

1211. **ጓንጐል** (አሮ)
ጌጤነህ እንደ ማለት ነው።
በዚህ ስም የሚታወቁት የዋግ ሹም የነበ
ሩት ጓንጐል ብሩ ናቸው። በወደዋ ጦርነት
በወዜ ምኒልክ ትእዛዝ ከጣሊያን ጋር ጦር
ነት ላይ ተሳትፈዋል ። ዋግ ሹም የሚባለ
ው ሥልጣን ከዛጌ መንግሥት ሲወርድ
ሲዋረድ የመጣ ሥልጣን ነው።

- ጠ -

1212. **ጠበቀው**
አጋጅ አረኛ ኾነው፤ አዳነው፤ ቆየው።
ፈጣሪ፣ ንጉሥ፣ አባት፣ አረኛ ...።
(ኤር. 23፥1 ፤ ሕዝ. 34፥2 ፤ ዳን. 4፥17)።
ያባት ስም ያገርሰው ቢል ይገጥማል።
ጠብቃቸው - ጠብቄ

1213. **ጠና**
ጠነከረ፣ በረታ ፤ ወይም ቆየ፣ ደጅ ጠና።
ያባት ስም ምንይክሰው ቢል ይገጥማል።
ጠናጋሻው - ጠናወርቅ

1214. **ጠንክር**
በርታ፣ ጐብዝ፣ ብርታት አግኝ (ኢዮ.6፥12)
ያባት ስም ጎብረት ቢል ይገጥማል።

1215. **ጠየቁ - ጠይቅ**
ተረዱ ፣ ዕወቁ ...።
ያባት ስም ዝና ቢል ይገጥማል።

1216. **ጢሞቴዎስ** (ግሪ)
እግዚአብሔርን አክባሪ፤ እንዲሁም ደግ
ሞ ዘአልቦቱ ጥሪት (ሀብት ያላካበተ)
ማለት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በልስጥራን
ያገኘው ወጣት ነው።
(የሐ. ሥራ 16፥1–3) ብዙ ሰው በዚህ ሲ
ጠራበት አይታይም። ሊቃነ ጳጳሳትማን ይ
ጠሩበታል።

1217. **ጢኖ** (አሮ)
ትንሽ ወይም ጥቂት ማለት ነው።
በዚህ ስም በወዜ ሱሰንዮስ ዘመን የአሮ
ሞን ነገድ፣ የወዜ ሱሰንዮስን ታሪክ የጻፉ
አዛዥ ጢኖ ይታወቁበታል።

1218. **ጣፋ** (አሮ.)
በዚህ ስም የሚታወቀው የረዥም የሩጫ
ውድድር ተወዳዳሪው **ጣፋ ባይሳ** ነው ።
በዚህም ኢትዮጵያ አገሩን በዓለም አሳው
ቋል።

1219. **ጣሰው - ጣሳቸው - ጣሴ**
ገፋ ፣ ከፈለው፣ ሰንጥቆ ገባ ማለት ነው።
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ የማይጨ
ው ዐርበኛ ደጃዝማች ጣሰው ዋለቡ
ናቸው (1894 - 1947 ዓ.ም.)።

1220. **ጣዕሙ** (ግእ)
መጣፈጡ...። ምግቡ ሽቶው ...።
ጠዐሙ ወታእምሩ ከመኀር እግዚአብ
ሔር። ትርጉም፤ እግዚአብሔር ቸር እን
ደ ኾነ ቅመሱ አዩም (መዝ. 33(34)፥7)።
ያባት ስም በዛብህ ቢል ይገጥማል።
ጣዕምያለው - ጣዕሞ - ጣዕመ

1221. **ጣፈጠ**
ጣምን ሰጠ ማለት ነው።
ጣም ተገኘ፣ ሰኳር፣ ጨው፣ ቅመም፤
የሚሸት ሽቶ፣ ዕጣን (ሉቃ. 8፥14)።
ያባት ስም ሸንኩሩ ቢል ይገጥማል።

1222. **ጤንነት**
ደኅንነት ማለት ነው።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።
ጤናነህ - ጤናው - ጤናኹን

1223. **ጥላዬ**
የኔ ጥላ ማለት ነው።
የሰው፣ የዛፍ የፀሓይ ከለላ ።
ጥላኹን - በዚህ ስም ከሚታወቁት
አንዱ ድምፃዊው ጥላኹን ገሰሰ ነው።
ጥላዬነህ - ጥላ - ጥላነህ

1224. **ጥምቀቱ**
የጥምቀት አይነት ልዩ ልዩ ነው። በውሃ
እና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ፤ በስቃይ
መጠመቅ፣ መንጻት፣ መለወጥ (ማር. 1፥4)
ያባት ስም ዮርዳኖስ ቢል ይገጥማል።
ጥምቀቴ - ጥምቀተ

1225. **ጥሩነህ**
መልክ መልካም ነህ፣ ደግ ሰው ነህ ...።
ያባት ስም ምግባሩ ቢል ይገጥማል።
ጥሩሰው - ጥሩማዕድ - ጥሩምንጭ
ጥሩቀለም - ጥሩብርሃን - ጥሩ
ጥሩዓለሜ - ጥሩአየሁ - ጥሩአየ
ጥሩዐይኔ - ጥሩወርቁ - ጥሩዘር
ጥሩገበያ - ጥሩፀሓይ

1226. **ጥሪት**
ሀብት፣ ቀሪ ገንዘብ የሚቀመጥ ...።
ያባት ስም አለነ ቢል ይገጥማል።

1202. **ጎባ** (ዶር) ጎበዜ ማለት ነው።

1203. **ጎይቶም** (ትግ)
ጌታቸው ማለት ነው። **ጎይታ - ጎየታ**

1204. **ጎዳናው - ጎዳና**
መንገዱ፣ ቀጥ ያለው ረዥሙ መንገድ።
ያባት ስም ታደሰ ቢል ይገጥማል።

1205. **ጐረፈ - ጐርፍነህ - ጐርፋ**
በዝቶ መጣ ፣ ተሰብስቦ ደረሰ ...።
ያባት ስም ገበያው ቢል ይገጥማል።

1206. **ጐሥጓ** (ግእ)
አገሣ፣ ተናገረ ጐሥጓ ልብየ ቃለ ሰናየ።
ትርጉም ፤ ልቤ መልካም ነገርን አወጣ
(መዝ. 44(45)፥1)ቅዳ. ማር.)።

1207. **ጐሳ**
ነገድ ...።
ያባት ስም ተዋሐደ ቢል ይገጥማል።
ጐሳዬን - ጐሳዬ - ጐሳወርፈቅ
ጐሳዬነህ

1208. **ጐሸሜ**
ነካ አደረገ ፤ በከንድ ፣ በነገር ...።
ያባት ስም **ክንዴ** ቢል ይገጥማል።
ጐሸመ - ጐሸመ

1209. **ጐሹ - ጐሸየ**
የበሬ ዝርያ ፣ በሬ የሚመስል ተዋጊ እን
ስሳ ፤ በዱር የሚኖር ተወዳጅ፣ ኃይለኛ
የኾነ ነው።
በዚህ ስም አራት ዐይና ጐሹ የቤተ ክርስ
ቲያን ሊቅ ይጠሩበታል ።

1210. **ጐበዜ**
የኔ ጐበዝ ማለት ነው፤ ጠንካራ ኾነ ...።
ዐጼ ተክለ ጊዮርጊስ ዳግማዊ (1860 -1864
ዓ.ም) ከዐፄ ቴዎድሮስ ቀጥሎ ከዐፄ
ዮሐንስ በፊት የነገሡ ናቸው ። ከንግሥና
ቸው በፊት ቀሣ ሥዩም ጎበዜ ተብለው
ይጠሩ ነበር።
ጐበዝ - ጐበዛየኹ - ገበዝአ
ጐበዘይ - ጐበዝ - ጐበዝ

1211. **ጓንጕል** (አሮ)
ጌጤነህ አንደ ማለት ነው።
በዚህ ስም የሚታወቁት የቀሣ ሹም የነበ
ሩት ጓንጕል ብሩ ናቸው። በዐደዋ ጦርነት
በዐፄ ምኒልክ ትእዛዝ ከጣሊያን ጋር ጦር
ነት ላይ ተባትፈዋል ። ቀሣ ሹም የሚባለ
ው ሥልጣን ከዛጌ መንግሥት ሲወርድ
ሲዋረድ የመጣ ሥልጣን ነው።

- ጠ -

1212. **ጠበቀው**
አጋጅ አረኖ ኾነው፤ አዳነው፤ ቆየው።
ፈጣሪ፣ ንጉሥ፣ አባት፣ አረኖ ...።
(ኤር. 23፥1 ፤ ሕዝ. 34፥2 ፤ ዳን. 4፥17)።
ያባት ስም ያገርሰው ቢል ይገጥማል።
ጠብቃቸው - ጠብቁ

1213. **ጠና**
ጠነከረ፣ በረታ ፤ ወይም ቆየ፣ ደጅ ጠና።
ያባት ስም ምንይካሰው ቢል ይገጥማል።
ጠናጋሻው - ጠናወርቅ

1214. **ጠንከር**
በርታ፣ ጐብዝ፣ ብርታት አግኝ (ኢዮ.6፥12)
ያባት ስም ኀብረት ቢል ይገጥማል።

1215. **ጠየቁ - ጠይቅ**
ተረዱ ፣ ዕወቁ ...።
ያባት ስም ዝና ቢል ይገጥማል።

1216. **ጢሞቴዎስ** (ግሪ)
እግዚአብሔርን አክባሪ፤ አንዲሁም ደግ
ሞ ዘአልቦቱ ጥሪት (ሀብት ያላካበተ)
ማለት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በልስጥራን
ያገኘው ወጣት ነው።
(የሐ. ሥራ 16፥1-3) ብዙ ሰው በዚህ ሲ
ጠራበት አይታይም። ሊቃነ ጳጳሳትግን ይ
ጠሩበታል።

1217. **ጢኖ** (አሮ)
ትንሽ ወይም ጥቂት ማለት ነው።
በዚህ ስም በዐፄ ሱስንዮስ ዘመን የአሮ
ሞን ነገድ፣ የዐፄ ሱስንዮስን ታሪክ የጻፉ
አዛዥ ጢኖ ይታወቁበታል።

1218. **ጣፋ** (አሮ.)
በዚህ ስም የሚታወቀው የረዥም የሩጫ
ውድድር ተወዳዳሪው **ጣፋ ባይሳ** ነው ።
በዚህም ኢትዮጵያ አገሩን በዓለም አሳው
ቋል።

1219. **ጣሰው - ጣሳቸው - ጣሴ**
ገፋ ፣ ከፈለው፣ በንጥቆ ገፃ ማለት ነው።
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ የማይጨ
ው ዐርበኛ ደጃዝማች **ጣሰው ዋለሉ**
ናቸው (1894 - 1947 ዓ.ም.)።

1220. **ጣዕሙ** (ግእ)
መጣፈጡ...። ምግቡ ሽቶው ...።
ጠዐሙ ወታእምሩ ከመኄር እግዚአብ
ሔር። ትርጉም፤ እግዚአብሔር ቸር እን
ደ ኾነ ቅመሱ እዩም (መዝ. 33(34)፥7)።
ያባት ስም በዛብህ ቢል ይገጥማል።
ጣዕምያለው - ጣዕሞ - ጣዕመ

1221. **ጣፈጠ**
ጣምን ሰጠ ማለት ነው።
ጣም ተገኘ፣ ሰኳር፣ ጨው፣ ቅመም፤
የሚሸት ሽቶ፣ ዕጣን (ሉቃ. 8፥14)።
ያባት ስም ሸንኩሩ ቢል ይገጥማል።

1222. **ጤንነት**
ደኅንነት ማለት ነው።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።
ጤናነህ - ጤናው - ጤናኹን

1223. **ጥላዬ**
የኔ ጥላ ማለት ነው።
የሰው፣ የዛፍ የፀሐይ ከለላ ።
ጥላኹን - በዚህ ስም ከሚታወቁት
አንዱ ድምፃዊው ጥላኹን ገሰሰ ነው።
ጥላዬነህ - ጥላ - ጥላነህ

1224. **ጥምቀቱ**
የጥምቀት አይነት ልዩ ልዩ ነው። በውሃ
አና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ፤ በስቃይ
መጠመቅ፣ መንጻት፣ መለወጥ (ማር. 1፥4)
ያባት ስም ዮርዳኖስ ቢል ይገጥማል።
ጥምቀቴ - ጥምቀተ

1225. **ጥሩነህ**
መልከ መልካም ነህ፣ ደግ ሰው ነህ ...።
ያባት ስም ምግባሩ ቢል ይገጥማል።
ጥሩሰው - ጥሩማዕድ - ጥሩምንጭ
ጥሩቀለም - ጥሩብርሃን - ጥሩ
ጥሩዓለሜ - ጥሩአየሁ - ጥሩለየ
ጥሩዐይኔ - ጥሩወርቁ - ጥሩዘር
ጥሩገበያ - ጥሩፀሐይ

1226. **ጥሪት**
ሀብት፣ ቀሪ ገንዘብ የሚቀመጥ ...።
ያባት ስም አለነ ቢል ይገጥማል።

ጠ

1227. **ጥቅሜ - ጥቅማቸው**
አገልጋዬ፣ የሚረዳኝ ...።
ጥቅማቸው ፤ አገልጋያቸው ...።
ያባት ስም ብዙኃኝ ቢል ይገጥማል።

1228. **ጥበበ**
ጠቢብ ፤ ብልሀ፣ ዐዋቂ፣ ፈላስፋ፣ አስተዋይ ማለት ነው (ኢር. 9፥23 ፤ ምሳ. 1፥7)።
ያባት ስም ሲራክ ቢል ይገጥማል።
ጥበቡ - ጥበብ - ጥበብኝ
ጥበበ ሥላሴ ክርስትና ስምን ተመልከት።

1229. **ጥንቅሼ - ጥንቅዬ- ጥንቅሽ**
የኔ ማር፣ የኔ ጣፋጭ ማለት ነው።
ማር ማር የሚል ጣፋጭ የዘንጋዳ ፤ የማ ሽላ አገዳ። ሽንኮራ ማለት ነው።
ያባት ስም ጣዕመ ቢል ይገጥማል።

1230. **ጥዑመልሳን**
ደስ የሚያሰኝ ድምጽ፤ ጥዑም ዜማ ።
ያባት ስም ያሬድ ቢል ይገጥማል።
ጥዑማይ - ጥዑሜ - ጥዑም

1231. **ጥጋቡ**
በመብል በመጠጥ የሆድ ሙላት ...።
ሀብት ፣ ኃያልነትን ፣ አልሰማ ባይነትን ያመለክታል ። አንዲሁ ዘመነ ጥጋብን ያመለክታል (መክ. 5፥12)።
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።
ጥጋቤ - ጥጋብ - ጥጋቦ

1232. **ጡቢያ - ጡቢያው**
ማለፊያ፣ መልከ መልካም ማለት ነው።
አናንተ የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት ሆይ እኔ ጥቁር ነኝ፤ ነገር ግን ውብ ነኝ።
(ማኃ. 1፥5)።

ከአሰራኤል ወገን የተወለደ የገባኤል **አጅ** የጦቢት **አጅ** ጦቢያ ይባል ነበር ጻድቅ እና ቸር የነበረ ሰው ነው (ጦቢ.1፥1 ፤ 14 ፥4 ፤ ንሀ. 2፥10)።
ጦቢት =ደግ፣ ጻድቅ የሚያምር ማለት ነው።

1233. **ጦና** (ዶር)
አሸናፊ ማለት ነው።
በዚህ ስም የሚታወቁት ጦና ጋጋ ናቸው።
ከዎ ጦና 21ኛው የወላይታ ንጉሥ ነበሩ።

1234. **ጥግነህ - ጥጉ**
ቦታን ያመለክታል ...። ታቹን፣ በሥር፣ ወደ ሰው መጠጋት፣ ጥግ ማድረግ ።
ያባት ስም ይቁም ቢል ይገጥማል።

ጨ

1235. **ጨመረ - ጨምር - ጨምሩ**
አከለ፣ ደባለቀ፣ ቀላቀለ ...።
ያባት ስም በረከት ቢል ይገጥማል
ጨምረው - ጨመደ - ጨመዲ
ጨመዳ - ጨመድሳ - ጨሙ

1236. **ጨቦዴ**
ጨባጭ ማለት ነው።
ጎይለኛ ጠንካራ ጉልበተኛ ማለት ነው።

1237. **ጨነቀው - ጨነቀ**
ከችግር የተነሳ የሚሰየም ስም ነው።
ጠበበው ቸገረው፣ አወከው (ኢሳ.63፥9)።
ያባት ስም በፍርዱ ቢል ይገጣማል።

1238. **ጫለ** (ኦሮ.) – **ጫልቺሳ**
በለጠ ማለት ነው። **ጫሌ - ጫሊሳ**

1239. **ጫንያለው – ጫኔ - ጫንዬ**
ያባት ስም ጎበዜ ቢል ይገጥማል።

- ጸ -

1240. **ጴጥሮስ** (ግሪ)
መሠረት ወይም አለት ማለት ነው። ከዐ ሥራ ዅስቱ ሐዋርያት አንዱ በመጀመ ሪያ ስምዖን ተብሎ ይጠራ የነበረው ነው። ጌታም የቅጽል ስም ጴጥሮስ ነኝ ብሎ ጠራው (ማር. 3፥16 ፤ ዮሐ.1፥43) ።

1241. **ጳውሎስ** (ግሪ)
ታናሽ ዐጭር እና ምርጥ ማለት ነው የዕብ ራይስጥ ስሙ ሳውል ነበር፤ በሮማዊ ስሙ ጳውሎስ ተብሎ ተጠራ (የሐ. ሠራ 13፥9)

- ጸ -

1242. **ጸበሉ** (ጠበሉ)
ያባት ስም መድኃኒት ቢል ይገጥማል።
ጠበለማርያም - ጠበሌ

1243. **ጸደቀ** (ጠደቀ)- **ጸድቅ**
አንዱ ጸድቅነትን፤ ዅለተኛው ትርጉም በቀለ ማለት ነው። **ጸዲቄ - ጸድቃን**
የክርስትና ስም ወልደ ጸድቅ የኾናለ።
ያባት ስም **አ**ትክልቴ ቢል ይገጥማል።

1244. **ጸዳሉ - ጸዳል - ጸዳለ**
ብርሃን ወይም የብርሃን ፍንጣቂ ጮራ ወጸዳሉኒ ከመ ብርሃን ውእቱ። ትርጉም፤ ጸዳሉም እንደ ብርሃን ነው።
(ዕን. 3፥4 ፤ ኢሳ. 59፥9 ፤ አሞ. 5፥20)።

1245. **ጸገየ** (ግእ) - **ጽጌ**
አበበ ፣ አፈራ ማለት ነው።
በለስ ወአውዕአ ሠርጸ፤ አውያን ጸግዩ ፤ ወወሀቡ መዐዛ። ትርጉም፤ በለሱ ጐመራ ወይኖችም አበቡ መዓዛቸውንም ሰጡ (ማኃ. 2፥6(13))።

1246. **ጸጋዬ** (ግእ) ጸጋ
ጸግው ሰጠ ለገሰ መጸወተ ካለው የግእዝ ግስ የወጣ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ (ጸጋ) ይባላል። ለዅሉም የሚሰጥ የመን ፈስ ቅዱስ ስጦታ አለ። ወይም ጸጋ መን ፈስ ቅዱስ (የሐ. ሥራ 2፥8)።
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ ደራሲ ጸጋ ዬገብረመድኅን ናቸው። አባታቸው ርዕ ቃሌሳ እናታቸው ወይዘሮ ፈለቀች ዳኜ ይባሉ ነበር ። ጸጋቸው - ጸጋነኽ
ጸጋዅሉ - ጸጋዅን - ጸጋሕይወት
ጸጋዓለም - ጸጋለበሰ - ጸጋውብዙ
ጸጋመስቀል- ጸጋመላይ- ጸጋማርያም
ጸጋሰጠኝ - ጸጋሥላሴ - ጸጋብርሃን
ጸጋአምላክ - ጸጋኪሮስ - ጸጋው

1247. **ጸጥታ**
እርጋታ፣ ዝምታ፣ ሰላም ...።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

1248. **ጽዱነኽ** (ጥዱነህ)
የጸዳ ፣ ንጹሕ ማለት ነው።
ያባት ስም የሉልወርቅ ቢል ይገጥማል።

1249. **ጽጌ**
ሽታው ደስ የሚል አበባ ።
ወከመ ጽጌ ገዳም ከማሁ ይፈሪ ። ትር ጉም፤ እንደ ዱር አበባ እንዲሁ ያብባል
(መዝ. 92፥15፤ መኃ.2፥12 ፤ ኢሳ. 35፥1)።

- ፀ -

1250. **ፀሐይ - ፀሐዩ - ፀሐዬ**
ቀንና ሌሊት ጊዜያትና አቅጣጫዎች የሚ ታወቁትና የሚለዩት በፀሐይ ነው
(ዘፍ. 1፥14–16)።

1251. **ፀምሩ - ፀምረ** (ግእ)
ፀምር፤ ለምድ የበግ ጸጉር፤ የሐር ባዘቶ።
መስክ ማለትም ይኾናል (መሳ. 6፥36)።

ፀ

ያባት ስም ጌዴዎን ቢል ይገጥማል።
ፀምረ ድንግል ከርስትና ስምን ተመልከት።

- ፈ -

1252. **ፈለቀ**
መነጨ፣ ወጣ፣ በራ፣ አንጸባረቀ...።
ያባት ስም ሲሳይ ቢል ይገጥማል።

1253. **ፈለገ** (ግሥ)
የወንዝ የምንጭ ውሃ ማለት ነው።
ፈለገ ጢሮስ ፤ ፈለገ ዮርዳኖስ ይላል።
ፈለገ እግዚአብሔር ምሉእ ማያተ። ትር ጉም፤ የእግዚአብሔር ወንዝ ውሃን የተ ሞላ ነው (መዝ. 64(65)፥4)።
ያባት ስም ዮርዳኖስ ቢል ይገጥማል
ፈለገሰላም - ፈለግ- ፈለገጥበብ (ስም)
ፈለገብርሃን- ፈለገሕይወት ከርስትና ስም

1254. **ፈረደ – ፈረደኝ - ፈረጀ**
ዳኝነት አየ፣ በየነ ...።
ያባት ስም **በፈቃዱ** ቢል ይገጥማል።
ፈረጃ - ፈረጃው - ፈረጅ - ፈረጆ

1255. **ፈቀደ - ፍቃደ**
አሰበ፣ ከጀለ፣ ወደደ፣ አየ፣ ተመለከተ፣ አስተዋለ፣ ጎበኘ ማለት ነው።
ያባት ስም **በለጠ** ቢል ይገጥማል።
ፈቀደልኝ - ፈቃዱ - ፈቃደ
ፈቃዴነኽ - ፈቃዴ - ፍቃደ ሥላሴ
ፈቃደ አምላክ ከርስትና ስም።

1256. **ፈይሳ** (ኦሮ . ጉራ)
ፈወሰ ፣ አዳነ ማለት ነው።
ፈየራ (ጉራ)- ፈያ - ፈየዱ

1257. **ፈጠነ - ፈጠኑ - ፈጣን**
በመኼድ ፣ በመናገር ፣ በማንኛውም ጉዳይ ቸኩለ። **ቀለጠፈ፣ ከዝግታ ከቀስታ** ተለየ። ታላቁን ተከትሎ ቶሎ ተወለደ።
ያባት ስም ንጋቱ ቢል ይገጥማል።

1258. **ፈልጰስ**
ፈረሶችን የሚወድ ጋላቢ ማለት ነው ወንድ ሞችን የሚወድ ሊኾን ይችላል ከዐሥራ ኹለቱ ሐዋርያት አንዱ ነው (ማቴ. 10፥3 ፤ የሐ. ሥራ 6፥3) ። በቅዱስ መጽሐፍ ወደ አምሰት ሰዎች ተጠርተውበታል።

1259. **ፈደሉ - ፈደል**
የአሱ ፈደል ማለት ነው።
ያባት ስም ጀመረ ቢል ይገጥማል።

1260. **ፈጣ** (ኦሮ)
ጨረሰ ማለት ነው። **ፈጤ**

1261. **ፋሲል** (ግሪ)
ፋሲል ማለት የንጉሥ ልጅ ማለት ነው። በዚህ ስም ዐፄ ፋሲል ስመ መንግሥታ ቸው ሥልጣን ሰገድ የተባሉት ተጠርተው በታል። 36 ዓመት ኢትዮጵያን አስተዳድ ረዋል። በግራኝ አሕመድ የፈረሰውን የአ ክሱም ቤተክርስቲያን ሕንፃን አሰርተዋል።

1262. **ፋሲለደስ**
በሰንክሳር ከታወቁት አንዱ ሰማዕት ነው። የዐፄ ኢያሱ (አድያም ሰገድ) ልጅ። የዐፄ ባካፋ (መሲሕ ሰገድ) ወንድም ፋሲለደስ ይባላል።

1263. **ፋሲካ - ፋሲካው - ፋሲኬ**
ከትንሣኤ በዓል አስክ ዳግም ትንሣኤ ያለው ጊዜ በዕብራይስጥ ፓሲካ ይባላል። የደስታ ጊዜ፤ ደስታ ነው ለማለት ፋሲካ ነው ይባላል። ፋሲካ ማለት ወሰፈ ማለት ነው (ዘጸ. 12፥1)።

1264. **ፋንታዬ**
የኔ ድርሻ ፣ ስኔ የሚሰጠኝ ...።
ድርሻ፣ ዕድል፣ ተራ፣ ምትክ፣ ስውጥ ማለት ነው (ዘጸ. 35፥5፤ ኢሳ. 57፥6)።
ፈንታኹን(ፋንታሁን) - ፋንታው
ፋንታዬ - ፈንታይ - ፋንቴ

1265. **ፋኖሴ - ፋኖስ - ፋኑስ**
ብርሃኔ፣ ጭለማን የሚገልጥልኝ ...።
ከብርጭቆ እና ከመስታወት የተሰራ ፓኖስ ወይም ወፍራም ጧዋፍ (ኢሳ. 62፥1 ፤ ዮሐ. 18፥3)።

1266. **ፋኑኤል** (ዕብ)
ከነገደ አሴር የኾነችው ነቢይት ሐና አባ ቷ ፋኑኤል ይባላል (ሉቃ. 2፥10)።
ከሊቃነ መላእክት አንዱ ፋኑኤል በመ ባል ይታወቃል (ሄኖ. 10፥15)።

1267. **ፍሬ - ፍሬሰላም**
አበባ ካበበ በኋላ የሚገኝ ...።
ፍሬሰው - ፍሬዘር - ፍሬሠናይ
ፍሬኹን - ፍሬወርቅ - ፍሬው
የከርስትና ስሞች ተመልከት።
ፍሬ ኢየሱስ - ፍሬ ድንግል
ፍሬ ስብሐት - ፍሬ ማርያም
ፍሬ ሰንበት - ፍሬ እግዚእ

1268. **ፍሬምናጦስ** (ግሪ)
በቅዱስ አትናቴዎስ የተሾሙ የመጀመሪ ያው የኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ ናቸው ። ከጵ ጵስና በፊት በግሪክ ስማቸው ፍሬምናጦስ በመባል ይታወቁ ነበር። **ከሣቴ ብርሃን - ሰላማ** የሚለውን ተመልከት።

1269. **ፍላጎቴ - ፍላጎት**
የኔ ፍላጎት ማለት ነው።
ያባት ስም አለነ ቢል ይገጥማል።

1270. **ፍርዳወቅ (ፍርድዐወቅ)**
ዳኝነት፣ መዳኘት ዐወቀ ማለት ነው።
ያባት ስም በየነ ቢል ይገጥማል።

1271. **ፍሥሓ** (ግእ)
ደስታ ፣ ሰላም ማለት ነው።
ያባት ስም ለይኩን ቢል ይገጥማል።
ፍሥሓዬ - ፍሥሓይ- ፍሥሓ ጽዮን

1272. **ፍቅሬ - ፍቅረ ማርያም**
የማፈቅረው፣ የምወደው ...።
ያባት ስም ዐየለ ቢል ይገጥማል።
ፍቅረዓለም - ፍቅሩ - ፍቅር
ፍቅረሕይወት - ፍቅራይ - ፍቅረ
ፍቅረሰላም - ፍቅርዐዲስ - ፍቅርዬ

1273. **ፍትሐነገሥት** (ግእ)
የቤተ ክርስቲያን እና የመንግሥት መተዳ ደሪያ ሕግ ነው።
ያባት ስም ሕጉ ቢል ይገጥማል።
ፍትሕዓለም - ፍትሕ አምላክ
ፍቱንወርቅ - ፍትሕ - ፍትሕና

1274. **ፍኖተጽዮን** (ግእ) - **ፍኖተ**
የጽዮን መንገድ ማለት ነው።
ፍኖተሰላም

1275. **ፍጹም – ፍጹምወርቅ**
ምሉእ የኾነ ጉድለት የሌለበት
(ዘዳ. 25፥15፤ ዕብ. 5፥14፤ ያዕ. 1፥24)።
ያባት ስም ክብረት ቢል ይገጥማል።
ፍጹምብርሃን - ፍጹማዊ

(፪) የሴቶች የመጠሪያ ስሞች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ስሞች ወላጆች ለሴት ልጆች የሚሰይሙት የመጠሪያ ስም ነው ።

በዚህ ውስጥም ለመጀመሪያ ጊዜ የምታገባ ሴት ልዩም ክብር አላትና ብወንድ ቤተሰብ የምራት ስም የሚኾኑ ስሞች አሉበት ። ይህ የምራት ስም ወይም የዳቦ ስም የወንድ አናት (አማት) ለልጇ ሚስት የኾነችውን ሙሽሪት (ምራት) የምትጠራበት ነው። ይህም ስም ዕጣ ተጥሎ ዳቦ ተቆርሶ ይሰየማል። ይህንም ስም የወንድ ወገን ቤተሰቡ ኹሉ ይጠራዋል ። ምራት ወደ ልጃቸው ስለሚያደሉ ልጅቷን እንዲህ እየያሉ ይጠሯታል (ዮሐ.3፥29 ፤ ኤር.2፥32 ፤ ራእ. 21፥2)።

ለምሳሌ፦
መንበርሽ ወርቅ
ርካብሽ ወርቅ
መጨጊያሽ ወርቅ

የምራት ስም በአብዛኛው የሰየመው እንደ ክርስትና ስም ቅጽልን በመጨመር ነው ። ወርቅ የከበረና ውድ የኾነ ማዕድን ስለኾነ ብዙ ጊዜ ይህን የከበረ መዕድን ቅጽል በማድረግ ይሰየማል ።
ያለ ቅጽል ደግሞ በነጠላው አበባዬ፣ ጽጌ፣ ሔዋኔ ሌላም ምራት የወደደች ውን ትሰይማለች ማለት ነው ። ኹሉም እንደ ባህሉ ይሰይማል። ምራት የም ትሰይመው የዳቦ ስም የሚኾንም ከዚህ የመጠሪያ ስም ውስጥ ይገኛል ማለት ነው። ይህን አካቶ ኢትዮጵያውያን ሲጠሩበት የኖሩትን የሴት ልጅ የመጠሪያ ስም ተመርጦ ቀርቧል ።

- ሀ -

1. **ሀብታሚ**
ሀብት የሚለው ወሀበ ከሚለው ግስ ሰጠ የሚል ትርጉም ይወጣል። ልጅ ሲወለድ ሀብት በመገኘቱ የተሰየመ ስም፤ ወይም ልጅ መገኘቱ ብቻ ሀብት ነው ለማለት ፤ ሀብት ሰጠኝ ይባላል።
ሀብታም - ሀብትይ - ሀብቴዋ
ሀብቴነሽ - ሀብታለም - ሀብትሽ
ሀበትአገኘሁ - ሀብትሽይመር
ሀብትሽደግ - ሀብትሽወርቅ

2. **ሀገሪቱ** (ግእ) **አገሪቱ**
አገርን መታሰቢያ ለማድረግ፤
ያባት ስም ይልማ ቢል ይገጥማል።
ሀገርነሽ - ሀገር- ሀገሬ - ሀገርአቀኑ
ኹሉ ገጽ 173 ቁ. 684 ይመልከቱ::

3. **ሃይማኖት** (ግእ) - **ሃይማኖቴ**
ሀይመነ ከሚለው አመነ ታመነ ይወጣል። አምነት ማለቷ ነው። የነገረ መለኮት ትም ህርት፤ ሥርዐትን ያጠቃልላል (2ኛጢ. 4፥7፤ ይሁ.3፥20፤ ዕብ.11)።
ያባት ስም ተዋሕዶ ቢል ይገጥማል

4. **ሄርሜላ**
የመቤታችን ቅድመ አያቶቿ ቴክታና በጥ ሪቃ ይባሉ ነበር ። ከዘር ሰድስተኛ የኾነ ችው የቅድስት ሃና እናት የቅድስት ድን ግል ማርያም አያት ሄርሜላ ነች (ትር.ቅ ዳ.ማር.)።

5. **ሃና** (ዕብ.)
ጸጋ ወይም እግዚአብሔር መርጦኛል ማለት ነው። የአመቤታችን የቅድስት ድን ግል ማርያም እናት።
የነቢዩ ሳሙኤል እናት በዚህ ስም ይታ ወቃሉ (1ኛ ሳሙ. 1፥1–2፤21)። ሃና ነቢ ይት (ሉቃ.2፥37) ሌሎችም ተጠርተውበ ታል።

6. **ህልውና** (ግእ)
መኖር ማለት ነው።
ያባት ስም ለይኩን ቢል ይገጥማል።

7. **ሆሳዕና** (ግሪ)
አኹን አድን ማለት ነው ። ወይም መድ ኀኒት ማለት ይኾናል (ማቴ. 21፥9)።
ያባት ስም ወልደ ዳዊት ቢል ይገጥማል።

8. **ሆድዬ**
የኔ ሆድ ማለት ነው።
ከፍቅር የተነሣ ወላጅ የሚሰይም ስም።

- ለ -

9. **ለምለም**
ሐመልማል ቡታያ ሣር፣ ቅጠል፣ ተክል፣ ዛፍ (ዘፍ. 1፥11 ፤2፥5) ልብን ደስ የሚያ ሰኝ መስክ ።
ያባት ስም ዘለለም ቢል ይገጥማል።
ለምለሚቱ - ለምነሽ - ለምወርቅ

10. **ለባሲተ** (ግእ) **ለበሰች**
ያባት ስም ምነሰ ቢል ይገጥማል።
የምነሰን ልብስ የለበሽ የተላበሽ ።
(መልካ. ማር)

ሴ

11. **ለባዊት** (ግእ)
ልብ ያደረገች፤ ያስተዋለች፤ የማስታወስ ችሎታ ያላት ማለት ነው።

12. **ለቤዛ - (ለቤዛዓለም)**
ምሳሌ፥ በይሥሐቅ ምትክ የተሠዋ በግ።
(ዘፍ. 22፥13 ፤ ማቴ. 26፥28)
ያባት ስም መድኅኔት ቢል ይገጥማል።

13. **ለታሪክ**
ይህ ኹሉ ያልፍና ለታሪክ እናውጋው።
ያባት ስም ተመቸ ቢል ይገጥማል።

14. **ለኹሉም - ለኹሉ**
ለብዙዎች መኾን ።
ያባት ስም ታደለ ቢል ይገጥማል።

15. **ለወግነሽ**
አለኝ ብዬ ለመናገር ፤ ለማውጋት
ያባት ስም ጌጤ ቢል ይገጥማል።
ለወግ - ለወግሰጠኝ - ለወጌ

16. **ለወጠችኝ**
ከወጣትነት ዘመን ልጅ ሲወለድ መለወጥ፤
ያባት ስም በፍቅሩ ቢል ይገጥማል።

17. **ለውዘገነት**
የገነት ፍሬነሽ ለማለት ነው።
(ለውገ ጣፋጭ ፍሬ ፤ ቀይና ነጭ አበባ ያለው ። የኮክ ዛፍን የሚመስል ተክል።
(ዘፍ. 43፥11 ፤ መክ. 12፥5፤ ኤር 1፥11)
ያባት ስም ታክለ ቢል ይገጥማል።

18. **ለዓለም**
አንትሙ ለዓለም ብርሃኑ። ትርጕም ፤ የዓለም ብርሃን ናችሁ (ማቴ. 5፥14)።
ያባት ስም ብርሃኑ ቢል ይገጥማል።

19. **ለዕለት**
ማምሻም ዕድሜ ነው እንደሚባለው።
ያባት ስም አገኘኹ ቢል ይገጥማል።

20. **ለገሠች**
ሰጠች ፤ ቸርነት አደረገች
ያባት ስም ዕንቊብርሃን ቢል ይገጥማል።
ለገሢኝ - ለጋሥ - ለጋሥነሽ

21. **ለጋነሽ**
ለምለም ያልጎመራ (ያልበሰለ)።
ያባት ስም አሸቴ ቢል ይገጥማል።
ለጋወርቅ - ለጋዓለም

22. **ሉሊት** (ሉል)
የከበረ ድንጋይ ዕንቊ ማለት ነው።
(ዘፍ. 2፥12)
ያባት ስም ድንቅነህ ቢል ይገጥማል።
ሉልወርቅ - ሉልሸት - ሉልዬ
ሉልዓየኹ (ሉላየኹ) - ሉሉ

23. **ሊሊ** (ግሪ)
ከግሪክ የተወሰደ ቃል ነው። ከምድር የተ ጣዘቀች ትንሽ አበባ፤ እቴጌ ጣይቱ ፀዲስ አበባ አገኘኹ ያሏት አይነት፤ ሜዳ ላይ የምትበቅል ደሰ የምታሰኝ (ማቴ. 6፥28)።
ሊሊት - ሊሊያና

24. **ላንቺይደሩ**
ይገዙልሽ ፣ ይታዘዙልሽ
ያባት ስም በእምነት ቢል ይገጥማል።

25. **ላመስግን – ላመስግናት**
በተሰጠኝ ሰጦታ ፣ በረከት ላመሰግን።
ያባት ስም ይበቃል ቢል ይገጥማል።

26. **ላቀች**
ከኹሉም በለጠች ፣ ተሻለች ...።
ያባት ስም በሐርወርቅ ቢል ይገጥማል።
ላቁ - ላቁብሽ

27. **ላንቻደላኹ – ላንቺበል**
ኹሉን በመተው፤ አንድ ወገን ኾንኩ ...።
ያባት ስም በፍርዱ ቢል ይገጥማል።

28. **ላዋይሽ – ላዋይ**
ላጫውትሽ፤ የሚነገር ምስጢር አለኝ...።
ያባት ስም መስከረም ቢል ይገጥማል።

29. **ላዩሽ - ላየሽ**
የሚመለከትሽ ኹሉ፤ ውበትሽን፣ ሞያሽን ሀብትሽን... ።
ያባት ስም አማረ ቢል ይገጥማል።

30. **ልመንሽ**
ማመን ፣ መታመንን ያመለክታል።
ያባት ስም በሐርወርቅ ቢል ይገጥማል።

31. **ልቡብርሃን**
አእምሮዋ ብሩህ የኾነ። ንቁ የነቃች።
ያባት ስም ያጠኝ ቢል ይገጥማል።

32. **ልባሟ**
አስታዋሽ ፣ የተነገረውን ፣ የተሠራውን የማትረሳ። **ልባዊት – ልቤነሽ**
ያባት ስም ጥበቡ ቢል ይገጥማል።

33. **ልብሰወርቅ**
የወርቅ ልብስን የተላበሰች።
ያባት ስም ዐዲሱ ቢል ይገጥማል።
ልብሰታል - ልብስተ - ልብሰፀሓይ
ልብስነሽ - ልብሴ
ልብሰ ማርያም ክርስትና ስም።

34. **ልንገርሽ**
ምስጢር ወይም ያየኹትን ?
ያባት ስም ቡዙአየሁ ቢል ይገጥማል።

35. **ልክየለሽ**
የሚወዳደርሽ ፣ የሚተካከልሽ የለም።
ያባት ስም አጥናፍዓለም ቢል ይገጥማል።
ልክምየለሽ - ልኬ - ልክዬ
ልኬወርቅ - ልኬቱ - ልኬነሽ
ልክአለሽ - ልክነሽ

36. **ልዕልተወይን**
ባሕረ ሐሳብን ወይም የዘመናትን አቆጣጠር ያዘጋጀ ዲሜጥሮ ከአጎቱ ልጅ ጋር 48 ዓመት በንጽሕና በአንድ አልጋ ላይ ኖረዋል። የንጽሕና የድንግልና ምሳሌ ነች።
ልዕሊሳ - ልዕልተ - ልዕልተወርቅ
ልዕልቷ - ልዕልቲ - ልዕልና - ላዕላይ

37. **ልያ** (ዕብ)
የላባ ታላቅ ልጅ የራሔል እኅት ለያዕቆብ የተዳረች ነች ። የመጀመሪያዋ የያዕቆብ ሚስት ነች (ዘፍ. 29፥16 - 30)።

38. **ልይሽ - ልየት**
ናፍቆትን ፣ መጓጓትን ያመለክታል።
ያባት ስም ወዳጄ ቢል ይገጥማል።

39. **ልዩወርቅ**
ከማንም የማትተካከል ተወዳዳሪ የሌላት።
(ዘፍ. 2፥12)
ያባት ስም በትዛዙ ቢል ይገጥማል።
ልዩሥራ - ልዩነሽ - ልዩ - ልዩፋንታ
ልዩጌጥ - ልዩዜና - ልዩዝና

40. **ልድያ** (ግሪ)
ልድያ በተባለች አገር ያለች ሴት ልጅ ማለት ነው። ልድያ የሚባለው ቦታ የሚገኘው በፊልጲስዩስ በእስያ ክፍል ነው። በመጀመሪያ በቅዱስ ጳውሎስ ስብከት ክርስትናን ተቀብላ የተጠመቀች ሀብታም የትያጥሮን ተወላጅ ነች (ሐዋ.ሥራ 16፥14 -15፥40)።

41. **ልጃለም (ልጅዓለም) – ለጃምሮ**
ደስታን የምትሰጥ ።
ያባት ስም ለጠኝ ቢል ይገጥማል።

42. **ሎሚ – ሎሚናት - ሎሚቱ**
መዓዛው ጥፍጥ ፤ የሚመጠጥ ኮምጠጥ የሚል ተወዳጅ ፍሬ ነው።
ያባት ስም ፍሬሰላም ቢል ይገጥማል።

43. **ሎዛ (ዕብ.)**
የለውዝ ቦታ (የረድኤት ቦታ) ማለት ነው። ስመ ሀገር ፤ በኢፍሬም ድርሻ ውስጥ ያለች (ዘፍ. 28፥10)፤ ያዕቆብ በመንገድ ሲጓዝ እደረባት ፤ በዚህች ቦታ ሕልም እለመ። ሲነጋም ቦታዋን ቤተል ብሎ ሰየማት ።

- ሐ -

44. **ሐመር** (ግእ) - **ሐመረ**
መርከብ ፤ ሐመረ ኖኅ ትርጉም የኖኅ መርከብ ማለት ነው ። (ዘፍ 6፥14)
የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ። ሐመረ ሥላሴ ሐመረ ድንግል ተብሎ ክርስትና ስም ይሰ የማል ።

45. **ሐመልማል** (ግእ)
ለምለም ቡቃያ ሣር፤ ቅጠል፤ ተክል፤ ዛፍ ወሐመልማለ ለቅኔ አጓለ አመሕያው ። ትርጉም ለምለሙን ለሰው ልጆች ጥቅም (ዘፍ.1፥11፤ 2፥5 ፤ መዝ.103 (104) ፥13) በዚህ ስም ብዙ ኢትዮጵያውያን የጠሩበ ታል። **ሐመልማለ ወርቅ**
ክርስትና ስም ሐመልማለ ድንግል ይባላል።

46. **ሐረገወይን** (ግእ)
ይህ ስም ቅድስት ድንግል ማርያምን ያመለክታል። አሷ በሐረግ ስትመሰል ወይን የጌታ ምሳሌ ነው ።
ሐረግነሽ - ሐረጊቱ - ሐረጊት
ሐረጌ - ሐረግ - ሐረግሽወርቅ
ሐረጓ - ሐረገወይኒ (ትግ)

47. **ሐሜት** (ግእ)
ታላቅ ደስታ፤ ደስ መሰኘት ማለት ነው። በትፍሥሕት ወበሐሴት ። ትርጉም፤ በደስ ታና በሐሴት (ሉቃ. 10፥21 ፤ ዮሐ. 8፥56)።

48. **ሐሳብነሽ**
ከመወለድ በፊት በሐሳብ የነበረች።
ያባት ስም **መልክሙ** ቢል ይገጥማል።
ሐሳቤ - ሐሳበወርቅ - ሐሳቢ

49. **ሐብለወርቅ**
በአንገት ላይ የሚደረግ ። ወዳጅነትን ያመለክታል። (ያንገት ወርቅ)
ያባት ስም ማተቤ ቢል ይገጥማል።

50. **ሐኪምነሽ - (ዐኪምነሽ)**
የምትፈውስ ፤ ያዳነች ማለት ነው።
(ኤር. 8፥28)
ያባት ስም መድኀኒት ቢል ይገጥማል።

51. **ኀዋ** (ዐረ. ኦሮ) ንፋስ ማለት ነው።
ኀዋ (ግእ) ጠፈር ማለት ነው።

52. **ሐዊ** (ኦሮ) ምሾት ማለት ነው።

53. **ሐውልቴ**
መታሰቢያ ፤ ምስክር ማለት ነው።
(ዘፍ. 28፥18 ፤ 31፥45-54 ፤ ኢያ. 4፥1-9 ፤ 24፥27)።
ያባት ስም መታሰቢያ ቢል ይገጥማል።
ሐውልት - ሐውልቲ (ትግ)

54. **ሐይቀብርሃን** (ግእ)
ብርሃን የኾነ ሐይቅ ማለት ነው።

55. **ሐይነሽ** (ጉራ)
አዋቂ (ብልህ) ነሽ ማለት ነው።

56. **ሐዲስ** (ግእ) **ሐዲሴ**
ዐዲስ ማለት ነው። (ኢር. 31፥31)
ሐዳሲ- ሐድሽ (ትግ)
የሽቱ ቅጠል ስም ። ቤቶች ከቅቤ ጋር የሚቀቡት፣ የዳቦ ማጣፈጫ በዐማርኛ ዐደስ የሚባለው ማለት ነው።

57. **ሔለን**
የንጉሥ የቆስጠንጢኖስ እናት ንግሥት አሌኔ በምዕራባውያን ሔለን በመባል ትታ ወቃለች (255-330 ዓ.ም)። ገጽ 196 ቁ. 625

58. **ሔዋን** (ዕብ.) - **ሔዋኔ**
የሕያዋን ኹሉ እናት ማለት ነው ፤ (ዘፍ. 3፥15 ፤ 1ኛጢሞ. 2፥14) ። በዚህ ስም ብዙዎች ይጠራሉ።

59. **ሕልመ**
በሕልም የታየች ሊኾን ይችላል።
(ዘፍ. 20፥3 ፤ 28፥12 ፤ 37፥5-11 ፤ 40፥5 ፤ ዳን. 2፥25 ፤ ማቴ. 1፥20 ፤)
ያባት ስም **ዮሴፍ** ቢል ይገጥማል።
ሕልምነሽ - ሕልሙነሽ- ሕልሜ

60. **ሕንደኬ** (ግሪ) (ጌርሳሞት)
በ35 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ንግሥት ስሟ ሕንደኬ ወይም ጌርሳሞት ይባል ነበር ። ጃን ደረባው ወደ ኢየሩሳሌም ተልኮ በአግዚአ ብሔር መንፈስ ቅዱስ ትዛዝ ፊልጶስ አጠ መቀው። የክርስትናንም ሃይማኖት ለቤተ መንግሥቱ አስተዋወቀ (የሐ.ሥ 8፥27)።

61. **ሕዝባለም**
ያባት ስም ተዋሕዶ ቢል ይገጥማል።
ሕዝባየኹ - ሕዝባዊት - ሕዝባንቺ

62. **ሕይወት**
ተሐድሶ፤ መዳን፤ ጤና ያመለክታል ፤ ሕይወት ኹሉ ከእግዚአብሔር የሚገኝ ነው። የነፍስ ሕይወት ፤ የሥጋ ሕይወት አለ (ዘፍ.2፥7 ፤ ዘፍ. 6፥17 ፤ ሮሜ.8፥6)።
ሕይወተ - ሕይወትነሽ - ሕይወቴ

63. **ሕገሥላሴ - ሕግነሽ**
ለማድረግ የሚያገዝ ፤ ከማድረግ የሚከለክል ውሳኔና ሥርዓት (ዘጸ. 20፥1)።
ያባት ስም በእምነት ቢል ይገጥማል።
ሕጋችን - ሕገእግዚአብሔር

- መ -

64. **መለሰች**
አዳነች፤ አተረፈች ማለት ይኾናል።
እንዳይኼድ ወደቀድሞው ቦታው እንዲ መለስ አደረገች። **መለሱ - መልሺው**

65. **መሉ - መለኪያ**
በዛን፤ ደርዘን ሞላን፤ ሙሉ ኾንን፤ አበቃን ማለት ይኾናል።

66. **መላ**
ዘዴ ፣ ብልሃት ማለት ይኾናል።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

67. **መልከአ ማርያም** (ግእ)
የማርያም መልኳ።
ቅድስት ድንግል ማርያምን ከብሯን ልዕል ናዋን የሚገልጽ ። **መልኪቱ**

68. **መልካሟ - መልካም**
ጥሩዋ ፣ ማለፊያዋ ማለት ነው።
ደግነትን ፣ ጥሩ ባሕርይን ያመለክታል።
(ዘፍ. 3፥8 ፤ ፸ዳ. 4፥22)።
ያባት ስም ቀናው ቢል ይገጥማል ።
መልካምሰው - መልካሚ
መልካምነሽ - መልካምዘር

69. **መልክርስት**
ውበትን ፣ ቁንጅናን ለማድነቅ ።
መልኬ በቃኝ እንደማለት ያለ ነው።

70. **መሓሪ** (ግእ)
መሐሪ ርሑቀ መዓት ወብዙኀ ሣህል።
ትርጉም ፤ ይቅር ባይ ከቀሩጣ የራቅኽ ይቅርታኽ የበዛ (፸ሎ. ምና. 2ዜና. መዋ. 33፥5)። **መሓሪት - መሓሪነሽ**

71. **ምሕረት**
ምሕረትክ ወጽድቅክ ዘልፈ ይርክባኒ።
ትርጉም፤ ቸርነትህና እውነትህ ዘወትር ይጠብቁኝ (መዝ. 39፥11)።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል

72. **መሠረት**
ከሥር የሚጀምር ወይም የሕንጻ ግድግዳ መሠረት (1ቆሮ. 3፥10–15)።
በዚህ ስም በሩጫ ውድድር አገሯን ኢት ዮጵያን ለዓለም ያሳወቀችው መሠረት ደፋር ነች። አንዱን የመርቅ ሜዳልያ በቅ ድስት ሥላሴ ካቴድራል ቤተ መዘክር በመስጠቷ ቱሪስት አየጉበኘው ነው።
መሠረተ - መሠረቷ

73. **መሥራት**
በድካምህ ወጥተህ ወርደህ ብላ (ዘፍ.3፥17)
ብልጽግና የሚመጣውም በሥራ ነው።
ያባት ስም መኩሪያ ቢል ይገጥማል።

74. **መረጡሽ – መረጠች**
በቁ ኾኖ በመገኘት ነው።
ያባት ስም ምስክር ቢል ይገጥማል።

75. **መሪኮከብ - መሪመቤት**
ቀድማ የምትወጣ፣ ንጋት ላይ የምት ታይ ። የንጋት ኮከብ ።
ያባት ስም ታየ ቢል ይገጥማል።

76. **መርሻ**
ያለፈውን፣ የተደረገውን ፣ ላለማስታወስ የምታስረሳ ማለት ነው።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።
ማስረስ - መርሻዬነሽ - መርሻዓለም

77. **መረተ**
አህሉ ከአብቅ ከገለባ ተለየ። ፍሬ ብቻ ኾነ ፤ ጠራ፣ ጥሩነትን አገኘ ...።

78. **መርከቤ**
ካንዱ ወደ አንዱ መሸጋገሪያ (ኢሳ.18፥2)።
ያባት ስም አሻጋሪ ቢል ይገጥማል።
መርከብ - መርከቧ

79. **መርኬዛ** (ግሪ)
የቅዱስ ገብረ ክርስቶስ እናት የንጉሥ ቴዎዶስዮስ ባለቤት ንግሥት መርኬዛ ትባ ላለች (ስክ. ጥቅ.14 ፥ገጽ 196) **የንጉሥ ነአኩቶ ለአብ እናት መርኬዛ ትባላለች።**

80. **መርዓት** (ግእ)
ሙሽሪት ማለት ነው።
ነአ አርኢክሃ ለመርዓት ለብእሲት በግሉ።
ትርጉም ፤ ና ሙሽራዪቱን በጉ የተዋ ሐዳትን ላሳይህ ። ሙሽራዪት የቤተክር ስቲያን ምሳሌ ነች (ራእ. 21፥9 ፤ 22፥17፤ ኤር. 2፥32)።
የክርስትና ስም **መርዓተ መድኅን** ይባላል።

81. **መርጊያዬ - መርጊያነሽ**
ማቆሚያ፣ ማረፊያ፣ አረጋጊኝ ...።
መረጋጋትን ፣ መጽናትን ያመለክታል።
ያባት ስም ይጥና ቢል ይገጥማል።

82. **መሰለች - መሳይነሽ - መሳይት**
አባትን ወይም እናትን መስላ ተገኘች።
መልክ መልካም ኾነች።
መሳየወርቅ - መሰሉ - መሳይቱ

83. **መሰንበት**
በመቆየት፣ በመታገሥ፣ ዐዲስ ነገር ታየ።
ያባት ስም ደጉ ቢል ይገጥማል።

84. **መስቀሌ**
ጌጥ፤ እምነትን፣ መከራን ያመለክታል።
ያባት ስም መታሰቢያ ቢል ይገጥማል።

85. **መስተዋት**
መልክን የሚያሳይ (ዘጸ. 38፥8 ፤ ቆሮ. 13 ፥12 ፤ ያዕ.1፥23)።
በዚህ ከሚታወቁት አንዷ የወረሁ-ይመኑ ገዝ የነበሩ **ወይዘሮ መስታዋት** ናቸው።
በዐፄ ቴዎድሮስ፣ በዐፄ ተክለጊዮርጊስ፣ በዐፄ ዮሐንስና በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግ ሥት ገናና ጀግና፣ ጦረኛ ኾነው ኖረዋል።
መስታወት - መስታወቴ

86. **መስከረም**
ከረምት አልፎ ዐዲስ ዘመን፤ ዐዲስ ወር ላይ የተገኘች ።
ያባት ስም ቢራቁ ቢል ይገጥማል።

87. **መሶበወርቅ**
በወርቅ ቅጠል የተለበጠ ፤ ከክር የተሰፋ የተጠለፈ ፤ በቤተ መንግሥት እና በቤተ ክርስቲያን የሚገኝ። በአለላ የተሸለመለ መች ፤ ኅብስት ያሚቀርብባት የክብር ዕቃ (ዕብ. 9፥4)።
እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በመሶበወርቅ ትመሰላለች (ውዳ. ማር.)።
ያባት ስም ክብሩ ቢል ይገጥማል።

88. **መሸሻዬ - መሸሻ**
መሰወሪያዬ፣ መደበቂያዬ ...።
ያባት ስም ንብረቴ ቢል ይገጥማል።

89. **መቅደላዊት** (ዕብ)
የቦታ ስም ሲኾን፤ መቅደሎ ከፍ ብላ በገ ሊላ ባሕር አጠገብ የምትገኝ ከተማ ነች፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ይከተሉት ከነበ ሩት የገሊላ ሴቶች ከሠላሳ ስድስቱ ቅዱ ሳን አንስት አንዲቷ የመቅደሎ ሰው ማር ያም ነች። የጌታን ትንሣኤ ያየች ምስክር ከኾኑት አንዲቷ ነች (ሉቃ. 8፥2)።

90. **መቅደሰወርቅ - መቅደሰ**
ሰዎች ከአምላካቸው ጋር የሚገናኙበት የተቀደሰ ቦታ (ዘጸ. 25፥8፤ መዝ. 113፥2 ፤ አሞ. 7፥9)።

91. **መቅድም**
የመጀመሪያ ማለት ነው።
ያባት ስም ታምሩ ቢል ይገጥማል።

92. **መቄያ**
ዋናው አስከሚደርስ ድረስ መጠበቂያ።
ያባት ስም ሥፍራዬ ቢል ይገጥማል።
መቄያሽ - መቄያነሽ

93. **መባ**
ለአምላክ የሚቀርብ ስጦታ (ዘሌዋ. 1፥3፤ ዘኍል 7፥12 - 17 ማቴ. 5፥24)።
ያባት ስም ሰጠኝ ቢል ይገጥማል።

94. **መብራሂት** (ትግ)
ያባት ስም ፋኖሴ ቢል ይገጥማል።

95. **መተኪያ - መተኪያነሽ**
በጠፋው፣ በጎደለው፣ በተሰወረው ...።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

96. **መታሰቢያ**
ሐውልት፣ ምልክት ምስክር ማለት ነው። (ዘፍ. 28፥18 ፤ 31፥45-54 ፤ ኢያ. 4፥1-9 ፤ 24፥27)።
ያባት ስም ቢተው ቢል ይገጥማል።

97. **መታደል**
ድንገት በመገኘታ ፤
ያባት ስም በእምነት ቢል ይገጥማል።

98. **መነን**
ባለሙያ፣ መልክ መልካም፣ ትክክል፣ ፍጽምት፣ ሕጸጽ የሌለባት ማለት ነው።
በሙያቸው የሴት ራሰ በመባል የሚታወቁት የጃንጥራር አስፋውና የወይዘሮ ስኂን ሚካኤል ልጅ የበዔ ጎይለ ሥላሴ ባለቤት እቴጌ መነን ተብለው ይጠሩበታል።

99. **መና** (ዕብ.)
እስራኤላውያን 40 ዓመት በበረሓ ሲጓዙ ከሰማይ የወረደላቸው ምግብ ነው (ዘጸ. 16፥35)።
ያባት ስም ወረደ ቢል ይገጥማል።

100. **መንበረ** (ግእ)
ቡሩክ አንተ በዲበ መንበረ መንግሥትከ፤ ትርጉም ፤ በጌትነትኽ ዙፋን ላይ አንተ የተመሰገንኽ ነህ ፤ የሠለስቱ ደቂቅ ጸሎት (ዳን.3፥55)።
ያባት ስም ዳዊት ፤ ክብሩ ቢል ይገጥማል።
መንበረወርቅ - መንበሩነሽ
መንበርሽወርቅ - የምራት ስም።

101. **መንግሥቴ - መንግሥት**
ግዛትን ያመለክታል ።
ያባት ስም ዘላለም ቢል ይገጥማል።

102. **መአድም** (ግእ)
የምታምር ማለት ነው (ስን. ጎዳ 27)።
ያባት ስም ብርሃኑ ቢል ይገጥማል።

103. **መከለያ - መኻለያ**
መጋረጃ መኾንን፤ ማዳንን ያመለክታል።
ያባት ስም ድንበሩ ቢል ይገጥማል።

104. **መኸዳ**
ትራስ ድጋፍ በውስጡ የሚደለደል ጠጉሩ የሚደላ ጥጥ፤ በላዩ በግምጃ፣ በሐር የተሰፋ የሐረግና የለበባ ጥልፍ ያለበት፤ በክፉይ ልብስ የተጠቀለለ እንደ ትራስ ያለ መደገፊያ (ሕዝ. 13፥18 ፤ አስ. 1፥6)።

105. **መኩሪያነሽ**
አንቺን በማግኘታችን ተኩራራን ...።
ያባት ስም ዓለማየሁ ቢል ይገጥማል።
መኩሪያ - መኩሪት

106. **መካሻዬ**
መታረቂያዬ፣ ተጎድቼ...። ተካስኩ ማለት ነው።

107. **መከሊት** (ግሪ)
የጥንት የከብደት መለኪያ፤ እንደዚሁም በጥንት ዘመን ገንዘብ ነበር (2ኛ ነገሥ. 18 ፥14 ፤ ማቴ. 25፥15)።

108. **መውደድ**
ወዳጅነትን ያመለክታል ።
ያባት ስም በልካቸው ቢል ይገጥማል።

109. **መዐዛ፡ መዐዛነት - መዐዛሽ**
ግሩም ሽታ (ዘፍ.8፥21 ፤ ኢሬ.5፥2)።
ያባት ስም ጽጌ ቢል ይገጥማል ።
መዐዛወርቅ - መዐዛነሽ - መዐዙ
ክርስትና ስምን ተመልከች።
መዐዛ ሕይወት - መዐዛ ቅዱሳን

110. **መዝለቂያ**
አልፎ መኼጃ ፣ መንገድ ተራራ፣ ብቅ ማያ መታያ ማለት ነው።
መዝለቂያሽወርቅ
የልዑል ራስ አምሩ ጎይለ ሥላሴ እናት ወይዘሮ መዝለቂያሽወርቅ ተብለው ይጠሩ ነበር ።

111. **መዝገቤ - መዝገብነሽ**
ማስታወሻዬ ማለት ነው።
ብዙ ማስታወሻ የያዘች።
ያባት ስም ታየ ቢል ይገጥማል።

112. **መደምደሚያ**
ማስተካከያ ፣ መጨረሻ፣ ማጠቃለያ ፤ መፈጸሚያ ... ። (ማኃ. 5፥2)
የመውለድና የውበት ፍጻሜ ማለት ነው።
ያባት ስም ይኹነው ቢል ይገጥማል።

113. **መድኀኒት (መዳኒት) መድኀኒት**
በሥጋም በነፍስም ከማናቸውም ጕዳት የምታድን ማለት ነው (ኢሳ. 38፥21፤ ኤር ፤ 8፥22 ፤ ሕዝ. 47፥12)። **መድኀኒቴ**

114. **መገርቱ** (ኦሮ)
በቀለች ፤ ለመለመች ማለት ነው።

115. **መጨረያሽወርቅ - መጨረያሽ**
መጨረያ ትራስ ማለት ነው።

116. **መጽሐት - መጽሐተ**
ሥዕሌ ነሽ፣ ንባቤ ነሽ ...።
ያባት ስም እንየው ቢል ይገጥማል።

117. **ሙሉ** ቁጥሩ የሞላ ።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።
ሙሉፀሓይ - ሙሉነሽ - ሙሉዬ
ሙሉወርቅ - ሙላቷ - ሙሉሀብታም
ሙሉሀብት - ሙሉመቤት
ሙሉመብራት - ሙሉሙጠት
ሙሉመንገዝ - ሙሉሚዛን - ሙሉሸዋ

ሙሉቀን - ሙሉብርሃን - ሙሉበር ሙሏለም - ሙሉሰው - ሙሉዋጋው ሙሉዘውድ - ሙሉገበያ - ሙሉጸጋ ሙሉጋት - ሙሉፈለግ

118. **ሙሽሪት**
ብርቅ የኾነች አምራ ደምቃ የምትታይ። ሙሽራ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ነች (ራእ. 21፥9 ፤ 22፥17 ፤ ኤር. 2፥32)። ያባት ስም አበባው ቢል ይገጥማል።

119. **ሙኔራ** (ዕብ. ዐረ)
መቅረዝ (ሻማ መብራት ማብሪያ)

120. **ሙና** (ዐረ. ዐማ)
ይመኙሻል ማለት ነው ። **ሞንሟናዬ** ሴት ልጅ ሞንሟና ቆንዞ፣ የተሞናሞኑች ማለት ነው። **ሙናዬ - ሙኒት**

121. **ሚሚ**
በዚህ ብዙ ኢትዮጵያውያን ይጠራሉ። **ማሚቱ - ማሚ - ማሚት - ማሚቴ**

122. **ሚዛን**
ክብደትን ፣ ፍርድን፣ ዳኝነትን ...። የክብደት መለኪያ ፤ መለፈሪያ (ዘሌ. 19፥36 ፤ ሕዝ. 45፥10)። ያባት ስም በፍርዱ ቢል ይገጥማል።

123. **ማስፈያ**
ጥሩ፣ በጎ የኾነች ማለት ነው ...። ያባት ስም ከፈለኝ ቢል ይገጥማል።

124. **ማስዳ**
ጠዋት ሌሊት ከ11 ሰዓት አስከ 12 ሰዓት ያለው ጊዜ ፤ ወፎች ሲንጫጩ ፣ ኅሉ ሲቀድ ማለት ነው። (ማቴ. 28)

125. **ማሕሌት** (ግእ) - **ማኅሌታይ**
ሐሰየ አለዘበ፤ ዘፈነ ከሚለው ግስ የወጣ ነው። በከበሮ፣ በጽናጽል፣ የሚደረግ መን ፈሳዊ የዜማ የጸሎት ምስጋና ። ሐሰየት ማሕሌተ፤ እኅተ ሙሴ በከበሮ።ትርጉም፤ የሙሴ እኅት በከበሮ መዝሙር ዘመረች፣ ዘፈነች (መዝ. 91፥3 ፤ 1ኛ ነገ. 4፥32)። በተጨማሪ ከመቅደስ፣ ከቅድስት፣ ቀጥሎ ያለው ክፍል ቅኔ ማሕሌት ይባላል (መክ. 7፥5፤ 12፥4፤ ራእ. 14፥3፤ መዝ.137፥)። ማሕሌት ሊቆም ደወል ሲደወል የተወለ ደች ልጅ ማሕሌት ብርሃኑ ተብላለች።

(ሐ ፤ ኀ ደበታ ተክለወልድ ፤ ከሣቴ ብርሃን መዝገበ ቃላት የተለያየ አስተያየት አላቸው)

126. **ማሕፀንተ** (ግእ)
ሐፀነ ካለው ግስ ፦ አሳደገ፣ ተንከባከበ ይወጣል ። አደራ ማለት ነው።

127. **ማማነሽ – ማማዬ**
አገመራውን ወፎች እንዳይበሉ የሚከላከ ሉበት ከፍተኛ ቦታ ላይ የተሠራ ሰገነት ወይም ግማ ። ደስ የምታሰኝ ቦታ።

128. **ማሚቴ - ማሚት**
ሴት ልጅ በትወለድ የሚሰጥ የቁልምጫ ስም ትርጓሜውም ደስ የምታሰኝ ልጅ ማለት ነው።

129. **ማረልኝ – ማረን - ማራት**
ራርቶ ይቅር አለልኝ (ማር. 10፥47)። ያባት ስም በጸጋው ቢል ይገጥማል።

130. **ማረግነሽ** (ማዕረግነሽ) - **ማዕረጓ**
ከፍ ከፍ ያደረግሽኝ፤ ሥልጣን አገኘኹ። ያባት ስም ክብሩ ቢል ይገጥማል።

131. **ማራኪ**
ደስ የምታሰኝ፣ የምታዝናናዝር፣ የምታጓጒ ። ኹለተኛ ድል የምታደርጊ ፣ የምታሸንፊ ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

132. **ማር** (መዓር) - **ማርሸት**
የማትጠገቢ ጣፋጭ ነሽ ...። መዓዛሽ ...። ከተጠበሰ ዓሣ አንድ ቁራጭ፥ ከማር ወለ ላም ሰጡት ተቀብሎም በፊታቸው በላ። (ሉቃ. 24፥42) **ማርትኹን - ማርዬ**
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል። **ማርወለላ - ማሪቱ - ማሪት - ማሪዋ ማርነሽ - ማርሴት - ማሬ - ማርነት ማርናት - ማርዓለም**

133. **ማርታ** (ሮማ.)
ማርታ ማለት ሴት ወይዘሮ ማለት ነው። የአልአዛር እና የማርያም እኅት ነች (ሉቃ.10፥38፤ ዮሐ.11፥20)

134. **ማርያ** (ዕብ)
በዕብራይስጥ ሟሪሃም የሙሴ እኅት ማር ያ ትባል ነበር ።
በእስክንድርያ ከታላላቆች ወገን የኾነች የከበረች ሰማዕት ማርያ በመባል የምት ታወቅ ነበረች (ስንክ. ጥር 24 ገጽ 676)። **ማርያም ቢል ግን ቅድስት ድንግል ማር ያም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ነች።** ይህም የባሕርይ ስም ስለኾነ ቅጽል በመጨመር ካልኾነ ሊወረስና ሊጠሩበት አይገባም። **የማርያም ወርቅ - ዘማርያም** ሊባል ግን ያቻላል።

135. **ማርያማዊት**
የማሪያም ወገን የኾነች ማለት ነው። የዐፄ ፋሲል ሴት ልጅ ማርያማዊት በመባል ትጠራ ነበር ። የማርያም ነች ለማለት ነው። ኢትዮጵያዊት እንደሚለው

136. **ማርያምሥና** (ግእ)
ሠነየ አማረ፤ ተዋበ፣ ካለው ይወጣል። መልካምነት፣ ደግነት በጎነት ፤ መልኪ እ ንደ ማርያም፤ የማርያም የመልክ ውበት። **የዐፄ ሠርጸ ድንግል ባለቤት አቴጌ ማርያ ም-ሥና** ይባሉ ነበር።

137. **ማሰረሻ**
ያሰፈውን እንዳላስታውስ፤ እንድረሳ። ያባት ስም ሰጠኝ ቢል ይገጥማል።

138. **ማስተዋል**
በጥልቀት አርቆ ማሰብ ።
ያባት ስም ገንዘቤ ቢል ይገጥማል።

139. **ማስታወሻ**
ላለመርሳት ፤ መታሰቢያ ።
ያባት ስም አንተኹን ቢል ይገጥማል።

140. **ማተቤ - ማዕተብ** (ግእ)
ዐተበ ከሚለው ግስ አማተበ አመሳቀለ የሚለው ይወጣል።
ወከመ ማዕተብ በመዝሙራውትክ ።
ትርጉም ፤ እንደ ማኅተብ ምልክትህ በክንድኽ አኑረኝ (መሓ.. 5፥2(6))።
ሐር ከጥቁር ክር የተሠራ ድሪ ለጌጥ የሚታሰር ነው። እንዲሁም የክርስትና ምልክት፤ የአምነት ጥንካሬን ያሳያል።
ያባት ስም አይደፈር ቢል ይገጥማል።
ማተቤነሽ - መተቧ - ማተብነሽ

141. **ማኅተመ**
ምልክት አደረገ ማለት ነው።
የውል የማኅኖውም ነገር መተማመኛ ፤
ስም የተቀረጸበት ሊኾን ይችላል።
ፈርኦን ለዮሴፍም በእንገቱ የወርቅ ዝር
ግፍ (ማኅተብ) አደረገለት (ዘፍ. 41፥42 ፤
ኤር. 32፥10–14)። **ማኅተብ - (ማኅተቤ)**
ማኅተመ ስላሴ ክርስትና ስም።

142. **ማኅቶት (ግእ) ማኅቶት**
ብርሃን ማለት ነው ።
ያባት ስም ኅለም ቢል ይገጥማል።

143. **ማኅደረ (ግእ)**
ማደሪያ ማለት ነው ። ማኅደረ ለመንፈስ
ቅዱስ ። ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ።
ማኅደረ ማርያም ክርስትና ስም።

144. **ማኅፈድ (ግእ)**
ግንብ፣ መክለያ፣ አንባ ማለት ነው።
እነ ቅጽር፤ ወእጥባትየ ከመ **ማኅፈድ**።
እኔ ቅጥር ነኝ ጡቶቼም እንደ ግንብ
ናቸው (መሐ. ዘሰሎ. 5፥6(10))።
ያባት ስም ነበልባሉ ቢል ይገጥማል።

145. **ማናኸሎሽ (ማንአህሎሽ)**
በሙያ፣ በሥራ፣ በውበት ማለት ነው።
ማንም አይደርስብሽም ለማለት ነው።
ያባት ስም በዕውቀት ቢል ይገጥማል።
ማናልሞሽ - ማናለብሽ - ማናየሽ
ማንተጋፍቶሽ - ማንተዳፍርሽ
ማንያኸልፃል - ማንይሉሻል
ማንያዝሻል - ማንይንካት
ማንደፍሯት - ማንጠግቦሽ

146. **ማንሴት**
የሚተካከልሽ ፣ የሚደርስብሽ ...።

147. **ማእዜ (ግእ)**
ምንጊዜ፤ በምን ሰዓት ማለት ነው።
ማእዜ አበጽሕ ወአራኢ ገጸ ለአምላ
ኪየ። ትርጉም፤ **መቼ** እደርሳለኹ ? የአ
ምላክንስ ፊት መቼ አያለኹ?
(መዝ. 41፥2)።

148. **ማኅዳ**
የኢትዮጵያ ንግሥት ወይም የሳባ ንግሥት
ነች ። ዘሯ ከኩሽ ልጅ የወረደ ነው ይባ
ላል። አዜብን - ሳባን ይመልከቱ።

149. **ማዕረጓ - ማዕረጌ**
ከብሯ፤ ከብሬ። ከፍ ከፍ ያደረገችኝ።
ያባት ስም አንተነህ ቢል ይገጥማል።

150. **ማዕዶት (ግእ)**
ማዶ ፣ መሻገሪያ፤ ከሞት ወደ ሕይወት
መሻገርያ ማለት ነው ። የትንሣኤ ሰኞ
ቀን ማዕዶት ይባላል።

151. **ማዘንጊያ – ማዘንጊያሽ**
ማስረሻ ማለት ነው።
በዚህ ስም የሚታወቁት የእስቃ ገብረሃና
ባለቤት ወሮ ማዘንጊያ የሚባሉት ናቸው፤
ያባት ስም ፀየስ ቢል ይገጥማል።

152. **ሜላተ (ግእ) – ሜላተወርቅ**
ነጭ የሐር ግምጃ ማለት ነው።
መንበሩ ዘሜላት። ትርጉም፤ ዙፋኑ የቀይ
የነጭ ሐር (መሐ. ዘሰሎ. 3፥5)። **ሜላት**
ሜላተ ሥላሴ፤ ሜላተ ድንግል (ክር)

153. **ሜርን (ግሪ)**
ቅባ ቅዱስ ከበለሳ እና ከዕጣን ከልዩ ልዩ
እንጨቶች የተቀመመ ሽቱ። ተነጥሮ የሚ
ወጣ ዘይት ማለት ነው። የመንፈስ ቅዱስ
ምሳሌ ነው። በክርስትና ጊዜ ጸጸስ ፣

ንጉሥ፣ ቄስ ሲሾም የመቀባ ማለት ነው
(ዘጸ. 30፥22 ፤ 1ኛ ዮሐ. 2፥20)።

154. **ሜቲ (ኦሮ)**
አንባሪ፣ ጌጤነሽ፣ ወርቄነሽ ማለት ነው።

155. **ምልዕተ (ግእ) ምልዕተ ክብር**
ክብርን የተሞላች ማለት ነው ።
ያባት ስም ጸጋ ቢል ይገጥማል።

156. **ምሕረት (ግእ) ምሕረተ - ምሕረቴ**
ይቅር መባል ፤ ርኅራኄ ፣ ቸርነት
ቅጣት ለሚገባው ምሕረት ማድረግ
እንዲሁም ለደካሞች ለበሽተኞች ርዳታ
ማድረግ (መዝ. 50 ፤ 129፥7 ፤ ምሳ. 14፥
21)። የኪዳን ምሕረት በዐል ዕለት የም
ትወለድ ወይም የክርስትና ቅጽል ይኾናል።

በዚህ ስም ከተጠሩት አንዷ የመጀመሪ
ያዋ ኢትዮጵያዊት ነርስ ሲስተር ምሕረት
ጳውሎስ ይባሉ የነበሩ በጣሊያን ጊዜ በስ
ደት ዘመን በዒ ኃይለ ሥላሴን በአስተር
ጓሚነት ያገለገሉ ናቸው ።
ምሕረተ ኪዳን ክርስትና ስምን ተመልከች።

157. **ምሥራቅ – ምሥራቄ**
አምሥራቀ ፀሓይ እስከነ ዐረብ። ትርጉም
፤ **ከፀሓይ መውጫ** እስከ መግቢያ ድረስ
(መዝ. 112፥3)።
ያባት ስም በረኹን ቢል ይገጥማል።

158. **ምሥሬች**
የደስታ ወሬ፣ ነገር፣ ልጅ በተወለደና ድል
በተገኘ ጊዜ፤ ሌላም ይህንን የመሰለ የሚ
ያስደስት ጉዳይ በተገኘ ጊዜ ፤ የሚነገር
ቃል በግእዝ ብሥራት ይባላል።
አብሣሪ ዐዲስ ነገርን የሚናገር ማለት
ነው (ሉቃ. 1፥26 ፤ ግብ. ሐዋ. 12፥14)።

159. **ምርትነሽ**
በእጥፍ ትርፍ ማግኘት ።
ያባት ስም **በሸይበሉ** ቢል ይገጥማል።

160. **ምርቃት**
በረከት ፣ ጸጋ (ዘዳ. 20፥5)።
ባለው ላይ ተጨማሪ ስጦታ።
ያባት ስም አገኘኹ ቢል ይገጥማል።

161. **ምርጥነሽ - ምርጫዬ**
የተመረጠች ፤ የተለየች ፣ የተወደደች
ምልምል (ሮሜ. 8፥33)።
ያባት ስም **ወርቁ** ቢል ይገጥማል።

162. **ምሳሌ**
አንድን ነገር ግልጥ ለማድረግ ሲፈለግ
የሚቀርብ ማስረጃ ማብራሪያ እና መግለጫ
ማቅረብ ማለት ነው። ሰሎሞን ብዙ ምሳ
ሌዎች ተናግሯል (1ኛ ነገሥ. 4፥32)።

163. **ምሳዬ**
ሆድ ባዶ ኾኖ በአኩለ ቀን የሚገኝ ...።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።

164. **ምስለአበባ (ግእ) - ምስሌ**
የአበባ ምስል ፣ አበባ የመሰለች ፤
ያባት ስም ተውሀቦ ቢል ይገጥማል።

165. **ምስክርነሽ – ምስክር**
ስሕተት የሌለበት ማስረጃ ነሽ ፤ እንዲ
ሁም ቃል ኪዳን ማለት ነው (ዘፍ. 31፥44
፤ ዘዳ. 31፥19–20) ።
ያባት ስም ዘላለም ቢል ይገጥማል።

166. **ምስጢረ (ግእ)**
ረቂቅ ስውርና ድብቅ ሽሽግ ማለት ነው።

መግለጽ ያልተቻለ ሐሳብና ምክር ። ምስጢረ ነገሥ ማለት ነው።
ምስጢረ ሥላሴ ክርስትና ስም።

167. **ምስጋና**
እግዚአብሔርን ሌሎችንም ፍጡራን ከፍ የሚያደርግና የሚያከብር ቃል። ሃሌ ሉያ ማለት ምስጋና ነው (መዝ. 111 – 117)።

168. **ምትኬ**
ቦታዬን ተክታ የምትይዝ ...።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።
ምትክነሽ - ምትኬነሽ - ምትኪ

169. **ምቹዓለም**
የሚመች ፣ የተሳካ ፣ የተቃና ።
ያባት ስም ቢኾነኝ ቢል ይገጥማል።

170. **ምንትዋብ**
በዚህ ስም ይጠሩ ከነበሩት ኢትዮጵያዊ የዐፄ ባካፋ ባለቤትና የዐፄ ኢያሱ ዳግማዊ (ቋረኛው ኢያሱ) እናት እቴጌ ምንትዋብ መንበሩ ነበሩ ። እቴጌ ምንትዋብ ከሠሯቸው ቤተክርስቲያን የነን ደር ቍስቋም አንዱ ነው።

171. **ምንይሉሽ**
ያባት ስም ወርቅዘዋ ቢል ይገጥማል።
ምን የሚለው ቅጽል ተጨምሮለት
ምናለች - ምናለሽዋ - ምናሉ ምንይሉ

172. **ምንታምር**
እንዴት ታምር ...።
ያባት ስም ወጌ ቢል ይገጥማል።
ምንትችል - ምንተስኗት - ምንውዬ ምንውዬልሽ

173. **ምኞቴነሽ – ምኞት - ምኞቴ**
ከፍ ባለ ስሜት አንድን ነገር መሻት ፤ ሴት ልጅ ለማግኘት ሲመኙ የነበሩ ቤተሰቦች ምኞታቸው ሲፈጸም የሚሰይሙት ሊኾን ይችላል ። (1ኛ ጴጥ. 2፥2 ፤ ማቴ 13፥17)።

174. **ምክር – ምክሬ**
መከረ ከሚለው ግስ አወጣ አወረደ አስተዋለ መለት ይኾናል ። ምክር ወሠናይት ለኩሉ ዘይገብራ ። ትርጕም፤ (ምክር) ለሚያደርጉት ኹሉ ደኅና ማስተዋል አላቸው (መዝ. 110፥10)።
ያባት ስም በትዛዙ ቢል ይገጥማል።

175. **ምዕራፌ - ምዕራፍ**
ማረፊያዬ ማለት ነው።
ማረፊያ ቦታ ማለት ነው (ሉቃ. 24፥13)።

176. **ሞጣሕተ ብርሃን - ሞጣሕተ**
የብርሃን ልብስ ማለት ነው ...።
ሞጣሕት ማለት ታቦት ተሸካሚ የሚያጠልቀው ልብስ ነው ። የወርቅ መርገፍ ያለበት፤ ዘርፍ ያለበት ቀይ ከፋይ ጎኑ ከሰን ዝር የማይበልጥ መስቀለኛ ነው። (ቅ.ገብ)

- ሠ -

177. **ሠላስ** (ትግ)
ሦስት ዐሥር ማለት ነው። ሦስተኛ።
የዐፄ ዮሐንስ አራተኛ የእናታቸው ስም ሥላስ ድምፁ ይባል ነበር።

178. **መረገላ – መረገላዬ**
በኹለት ፈረስ የሚሳብ ንግሥት እና ነገሥታት፤ በከብር የሚጓዙበት ። ኤልያስ በአሳት መረገላ ዐረገ ይህም የእግዚአብሔርን ክብር የሚያመለክት ነው።

(2ኛ ነገሥ. 2፥11) ቤትን የሚሸከም ወራጅ መረገላ ይባላል (1ኛ ነገሥ. 7፥2)።
ያባት ስም ክብሩ ቢል ይገጥማል።
መረገላኤልያስ - መረገላፀሐይ

179. **መራሽ**
ፈጠረሽ ወይም እንደ ገና አበጃጀሽ ማለት ነው። **መራዓስም - መራወርቅ መራሽድንቅ - መራሽብዙ - መራት መራሕይወት - መራሽ - መራንሽ**

180. **መርካለም - (መርከዓለም)**
ኹል ጊዜ ዐዲስ ፤ ኹል ጊዜ ደስታ ማለት ነው። ማታ ለቀን ቀን ለማታ የማትጠገብ ። **መርከሸት**
መርካበባ - መርካዲስ - መርኬ

181. **መናይት** (ግእ) መናይ - **መናያት**
መልካም ፣ ውብ ፣ ደግ ፣ በጎ ፣ ቅን ደስ የሚያሰኝ የመልክ የጠባይ ተሰጥዎ ። መናይ ዜና መልካም ዜና ማለት ነው።
መናይተ ምክረ ወጥበበ ምህረኒ፤ ትርጕም መልካምን ምክርና ዕውቀትን አስተምረኝ (መዝ. 118፥65)።

182. **መዊተ** (ዕብ. ግእ) **ሸዊት**(ትግ)
የደረሰ እሸት (ጎሞር) ዛላ ዕንቡጥ ታሸተ ተፈልፍሎ የሚበላ የእህልና የተክል ዘር (ዘፍ.41፥5)።
ወአርዳኢሁሰ ርኅቡ ወአኀዙ ይምሐዉ ሰዊተ ወይብልዑ። ትርጕም፤ ደቀመዛሙርቱ ተርበው ነበረና እሸት እያሹ ይበሉ ነበር (ማቴ. 12፥1)።

183. **ሣህሏ** (ግእ) (ሣህለ ማርያም)
ቸርነቷ ፣ ይቅርታዋ ማለት ነው።
ሣህሌ- ሣህለ - ሣህላ - ሣህለወርቅ

184. **ሣራ**
ልዕልት ማለት ሲኾን ሦራ ደግሞ ልዕልቴ ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን የአብርሃም ባለቤት ነች፤ ባሏን አክባሪ ስለነበረች የጋብቻ የፍቅር ምልክት ኾና ስትጠራ ትኖራለች (ዘፍ.11፥29)።
በዚህ ሰም ከሚጠሩ ኢትዮጵያን አንዷ የዐፄ ኀይለ ሥላሴ ልጅ ልዕልት ሣራ ገዛው ናቸው።

185. **ሣሮን** (ዕብ)
ደስ የሚል የባሕር የወንዝ ዳር ሜዳ።
ረባዳ ቦታ ከኢዮጴ እስከ ቀርሜሎስ ያለ ቦታ (ኢሳ. 33፥9፤ 1ኛ ዜና. 5፥15)።

186. **ሥሌናት** (**ሥዕሌናት**)
መልኬ፣ የምትመስለኝ፣ ውበቴ ናት ...።
ያባት ስም ውበቴ ቢል ይገጥማል።
ሥዕሌ - ሥዕልሽ - ሥዕሉንሽ

187. **ሥምረት** (ግእ) ሥምረተ ኪዳን
የተወደደች ማለት ነው ።
ያባት ስም ሰጠኝ ቢል ይገጥማል።

188. **ሥራዬ - ሥራነሽ**
እግዚአብሔር ሰውን ለሥራ ፈጠረ።
እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ (ይሠራ ዘንድ) በኤደን ገነት አኖረው። (ዘፍ. 2፥15)
ያባት ስም ደሳለኝ ቢል ይገጥማል።

189. **ሥነምግባሯ** (ግእ) - **ሥነ**
ሠነየ ከሚለው አማረ፣ ተዋበ ይወጣል።
ያባት ስም አማረ ቢል ይገጥማል
መልካምነት ደግነት በጎነት ማለት ነው (መዝ. 44፥49 ፤ ሲራ. 9፥8፤ 11፥4)።
ሥነሕይወት - ሥነፀሐይ
ሥነ ማርያም

190. **ሥንቁ** (ግእ)
ሠነቀ ከሚለው ግስ የወጣ ነው ይህም ማለት ፣ ያዘ ማለት ነው። ምግቤ ...። በጥዘ አብር የሚጓዝ የመንገደኛ ምግብ። ለሚ ስንቅ ነው የአመቤተ እንዳለ ዘማሪ
ያባት ስም እሸቴ ቢል ይገጥማል።
ሥንቅነሽ - ሥንቃቸው - ሥንቅሽ

191. **ሦራ** (ሶራ)
የታቦት ልብስ መጎናጸፊያ መለት ነው።
ሦራ ሦራ ልበሺ የታቦት ዘፈን ።

192. **ሥፍራዬ -ሥፍራሽ - ሥፍራነሽ**
ቦታዬ፣ መቀመጫዬ፣ አገሬ ....።
መኖሪያን ያመለክታል።
ያባት ስም ደስአለኝ ቢል ይገጥማል።

- ረ -

193. **ረድኤት** (ግእ.)
የእግዚአብሔር ርዳታ ተጨምሮበት የተዘ ረከተች ማለት ነው (መጽ. ነገ. 17፥12)።
ረዳኢት - ረዳኤ

194. **ረቂቅ**
ምስጢር ፤ በዓይን ፣ በዳሰሳ ሊደረስበት የማይቻል።
ያባት ስም ወርቅነሽ ቢል ይገጥማል።

195. **ረበበ** (ግእ) – **ረበቡ**
ዘረጋ ማለት ነው።
ያባት ስም ጸጋዬ ቢል ይገጥማል።

196. **ረታች** – **ረታሽ**
ረትዓ ከሚለው ግስ ቀና ረታ ማለት ነው
ያባት ስም በፍርዱ ቢል ይገጥማል።

197. **ረክብኪ** (ግእ)
አገኘሽ፣ ማለት ነው።
ረከበ ካለው ግስ፡ አገኘ ተገናኘ ይወጣል
ያባት ስም ጸጋ ቢል ይገጥማል።

198. **ረጋች**
ረግዓ ከሚለው ግስ የወጣ ነው ። ረጋች ቆመች ፤ ርጋታን ያመለክታል ።
ያባት ስም ፍቅሬ ቢል ይገጥማል።
ረጋሸዋ - ረጊሌት (ትግ) - ረገቡ

199. **ሩቅነሽ**
ርቀትን ያመለክታል።
ያባት ስም ዘረብዙ ቢል ይገጥማል።

200. **ሩት** (ዕብ)
ቦኤዝን ያገባች ፤ የቅዱስ ዳዊት ቅደመ አያት ስትኾን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረግ ውስጥ ተቆጠረች (መጽ.ሩት 1፥1 ፤ ማቴ. 1)።

201. **ራሔል** (ዕብ)
አንስተ አባግዕ ማለት ነው ወይም የሴት በግ) የተመረጠችው የያዕቆብ ሚስት ነች ፤ ቆንጆ ምገስና ግርማ ያላት፤ ያዕቆብም አሷን ለማግኘት በጎችን በመጠበቅ ብዙ ለፍቷል (ዘፍ.29፥16) ስሟም ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው።

202. **ራኬብ** (ዕብ)
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረግ የተቆጠሩ ከአራቱ ሴቶች አንዷ ራኬብ ነች ። ራኬብ የቦኤዝ አናት ነች (ማቴ. 1፥5)።

203. **ርስቴ - ርስቴነሽ**
ቦታን ፣ ይዞታን እንዲሁም የትውልድ ቦታን ያመለክታል።
ያባት ስም ደሴ፣ አገሬ ቢል ይገጥማል።

204. **ርብቃ** (ዕብ.)
የአብርሃም ወንድም የናኮር ልጅ የለባ አኳት ፤ የተመረጠች የይሥሐቅ ሚስት ነች ፤ በመጀመሪያ መኻን ነበረች፤ ባሏ ከጸለየላት በኋላ መንቶች ልጆችን ወለደች (ዘፍ. 22፥ 23)።

205. **ርካቧ**
ያባት ስም ወርቁ ቢል ይገጥማል።
በፈረስና በበቅሎ ኮርቻ ግራና ቀኝ የሚ ንጠለጠል ለመወጣጫ ፣ ሚዛን ለመጠበ ቂያ የሚያገለግል ።
ርካብሽ - ርካብ - ርካብነሽ
ርካብሽወርቅ - የምሬት ስም።

206. **ርግበ** (**ርግብ**) (ግእ)
ያባት ስም ሠናይ ቢል ይገጥማል።
ኖኅ የጥፋት ውሃን መጕደል ያረጋገጠባት የውበት፤ የሐዘን፤ የሰላም፣ የየዋኅነት ምሳሌ ናት። መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል ተገልጿል (ዘፍ.8፥8 ፤ መኅ.1፥15 ፤ ኢሳ.59፥11 ፤ ማቴ 3፥6)።
ርግቤ - ርግብነሽ - ርግበሰላም

207. **ርኅነሽ - ርኅዬ - ርኅ**
የኔ ርኅ ሚለት ነው። ተወዳጅነሽ ለማለት የረጋ ወተት፣ ወፍራም፣ ዝብጥብጥ ያለች ቆንጉር ያማረች ። የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል (ዘፍ. 18፥8)።
ያባት ስም በረከት ቢል ይገጥማል።

208. **ሮማን**
አበባውና የፍሬው ቅርፊት ቀይ፤ በውስጡ ፍሬው ብዙ የኾነ። ከመ ቅርፍተ ሮማን መለትሕኪ። ትርጕም፤ ጉንጭና ጉንጭሽ እንደ ተከፈለ ሮማን ናቸው (ዘጸ. 28፥33 ፤ ሐጌ. 2፥19 ፤ መኅ. 6፥11)።
ያባት ስም ፍሬው ቢል ይገጥማል።

209. **ሮማንወርቅ**
በዚህ ስም የዐፄ ኀይለ ሥላሴ ልጅ ልዕልት ሮማንወርቅ ተጠርተውበታል ። ከባላቸው ከደጃዝማች በየነ መርዕድ ጋር በ1928 ዓ.ም. ጦርነት ከጣሊያን ጋር ገጥመው ባላቸው ሲሞቱ አሳቸው ከሦስት ልጆቻቸው ጋር ተማርከው ነበር።

210. **ሮዛ**
ጽጌረዳ አበባ ማለት ነው።
ይህ የጽጌ-ረዳ አበባ በአመቤታችን ምሳሌ ነት ይመሰላል ። ከአበቦች ኹሉ የሚበልጥ መዐዛ ያላት አበባ ነች ። ሮዛ የሚለው ስም ሮዳ ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ነው።

211. **ሮዳ** (ግሪ)
ሮዳ ወይም ሮዛ (ጽጌ ረዳ) አበባ ማለት ነው (የሐ. ሥራ 10፥11–13)።

- ሰ -

212. **ሰላም**
በስምምነትና በአንድነት አብሮ በመኖ እና የኅሊና ዕረፍትን ማግኘት ሰላም ይሰጣል ማለት ነው (ዘፍ. 43፥27፤ ዘጸ. 4፥18 ፤ መጽ.መሳ 19፥20)። የክርስትና ስም ሰላመ ድንግል ሊኾን ይችላል ።
ሰላማዊት - ሰላምይኹን

213. **ሰልፏ**
በመከተል ፤ በተራ የመጣች።
ያባት ስም አግረ ቢል ይገጥማል።

214. **ሰሎሜ** (ሮማ.)
ሰላማዊት ማለት ነው።
የዘብዴዎስ ሚስት፤ የእመቤታችን ድንግል ማርያም ዘመድ ነች። ከአረጋዊ ዮሴፍና ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጋራ ጌታን ታቅፋ አብራ ተሰደደች ። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር በት ንሣኤው ዕለት ተገኝታ ነበር (ማር. 15፥40 ፤ 16፥1 ፤ ማቴ. 27፥56)።

215. **ሰመመን**
እንቅልፍ ያልኾነ ሽለብታ ፣ በመተኛትና በመንቃት መካከል ያለ። የምትወደድ እና ጣዕም ያላት ።
ያባት ስም ያዛቸው ቢል ይገጥማል።
ሰመመንሽ - ሰመመኔ

216. **ሰማዕታ - ሰማዕተ** (ግእ)
ምስክር ኾነ ማለት ነው ። መሥዋዕትነ ትን፣ ምስክርነትን መስጠት (የሐዋ. ሥራ. 22፥20) ።
ያባት ስም አስጢፋኖስ ቢል ይገጥማል።

217. **ሰማያዊት**
ቀለምን ፤ እንዲሁ የሰማይ መኾንን ፤ ከምድር በላይ ያለ። የእግዚአብሔር ቦታ ፤ ኩኑ ፍጹማነ ከመ አቡክሙ ሰማያዊ ፍጹም ውእቱ ። ትርጉም ፤ ሰማያዊ አባ ታችሁ ፍጹም እንደኾነ ፍጹማን ኹኑ ። (ማቴ. 5፥48 ፤ ዘዳግ . 26፥15)
የምእመናን ቦታ (1ኛ ጴጥ 1፥4)
ያባት ስም ክብሩ ቢል ይገጥማል።
ሰማይነሽ - ሰማዬነሽ - ሰማይቱ
ሰማይነሽ - ሰማያት

218. **ሰሙ**
አዳመጡ፣ ተነገራቸው ...።
ያባት ስም በዝና ቢል ይገጥማል
ሰሙንጉሥ - ሰሙወርቅ - ሰማሸኝ
ሰማኝእዜር - ሰማኢት - ሰማንሽ
ሰማችኝማርያም - ሰማዒነሽ
ሰማኝኢየሱስ - ሰማልኝ

219. **ሰራዊት**
ብዙ የሰማይ ሰራዊተ መላእክትን ያመለክ ታል ። በቅዳሴ ሰራዊተ መላእክቲሁ ለመድኃኔ ዓለም እንደማለት ነው። ብዙ የጦር ሰዎች ወይም ማለት ነው።

220. **ሰርዲኖስ** (ግእ)
ሰርዲኖስ ምስለ ተርሴስ
(መኃ. ዘሰሎ.3፥5) የሸቱ ዓይነት ነው።

221. **ሰርጌ**
ሰርግ = ጌጥ፤ ሽልማት ማለት ነው።
ያባት ስም አግረ ቢል ይገጥማል።
ሰርጋዊ - ሰርጓ - ሰርጓለም
ሰርጉትን ተመልከች።

222. **ሰበሰብሻቸው – ሰበሰብሽ**
ምክንያት ኾነሽ አገናኘሻቸው።
ያባት ስም በሐርወርቅ ቢል ይገጥማል።

223. **ሰብለወንጌል**
የወንጌል ሰብል ማለት ቢኾን ይህም ኢት ዮጵያ መኾኗን የሚያመለክት ነው።
በዚህ ስም የነገሥታት ኹሉ እናት እየ ተባሉ የሚጠሩት የጉጃም አመቤት ተብ ለው የሚታወቁት ፤ **የወጌ ልብነ ድንግል** ባለቤት **የወጌ ገላውዴዎስ፣ የወጌ ሚናስ** እናት **የወጌ መርዐ ድንግል** አያት ያቤቶ ያዕቆብ የሌሎቹም አያት ቅድመ አያት

አቴጌ ሰብለወንጌል ናቸው።
ሰብለ - ሰብለወርቅ - ሰብለገነት
ሰብለ ማርያም ክርስትና ስም

224. **ሰንደቅ**
ክብር ያለው ዓላማ የባንዲራ መስቀያው።
ያባት ስም ዓላማው ቢል ይገጥማል።
ሰንደቁ - ሰንደቅነሽ

225. **ሰካወርቅ**
ወርቅ አጠለቀ ፤ አገኘ ።
ያባት ስም በልኹ ቢል ይገጥማል።

226. **ሰውነት**
አካልን ያመለክታል። ሥጋና ነፍስ ተዋሕ ደው የሚታዩበት (ማቴ. 5፥29 ፤ 6፥22)።
ያባት ስም መብራቱ ቢል ይገጥማል።
ሰውዓለም (ሰዋለም) - ሰውሐረግ

227. **ሰዋሰው** (ግእ) **ሰዋሰወ ምሕረት**
መወጣጫ መሰላል፤ መወጣጫ መውረጃ ማለት ነው። ያዕቆብ በሕልሙ ያያት መወጣጫን ወይም መሰላል የሚለውን ያመለክታል (ዘፍ. 28፥12)።
ያባት ስም ያዕቆብ ቢል ይገጥማል።

228. **ሰገነት – ሰገኒት** (ጉራ)
በቤት ጣራ ላይ የሚሠራ መናፈሻ ቦታ ወይም ማደሪያ ክፍል (2ኛ.ሳሙ. 11፥2 ፤ ዳን. 4፥29 ፤ 1ኛ ነገሥ. 17፥19)።
ያባት ስም ደርበው ቢል ይገጥማል።

229. **ሰጠችኝ – ሰጠሸኝወርቅ**
ስጦታን፣ ገጸ በረከትን፤ ያመለክታል።
ያባት ስም በረከት ቢል ይገጥማል።

230. **ሰፈረወርቅ - ሰፈረ**
የተሰፈረች፣ የተመዘነች ወርቅ ነች ...።
ወርቅን ሰፍሮ ሰጠኝ ...። መሰፈሪያ የሚ ኾን፤ ቁና .. መስኪያ
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

231. **ሰፈፍ – ሰፈፈች - ሳፈች**
የማር ምጣጭ ፤
ያባት ስም ማሩ ቢል ይገጥማል።

232. **ሰፋኒት** (ግእ) **ሰፈነች**
ሰፈነ ማለት ሞላ፣ ገዛ፣ በገዛቱ የሞላ።
ያባት ስም **መንግሥቱ** ቢል ይገጥማል።

233. **ሲሳይ**
ሲሳየን ዘለለ ዕለትን ሲል ። የዕለት ምግ ብን አንጀራን ያመለክታል። ከአርሻ ከእን ሰሳት ይገኛል ።
በድሆች አርሻ ላይ ብዙ ሲሳይ አለ።
ከፍርድ መጉደል የተነሳ ግን ይጠፋል።
(ምሳ. 13፥23 ፤ 14፥4 ፤ 27፥27)።
ያባት ስም ለይኩን ቢል ይገጥማል።
ሲሳዬ - ሲሳይነሽ - ሲሳዬነሽ

234. **ሲፓራ** (ዕብ)
የሙሴ ሚስት የምድያም ካህን የዮቶር (የራጉኤል) ልጅ። ጌርሶን እና አልአዛር የሚባሉ ልጆችን ለሙሴ ወለደች ።
(ዘጸአ. 2፥16–22 ፤ 18፥1–5)።

235. **ሳለችማርያም**
ቅድስት ድንግል ማርያምን በመማጸን።
ያባት ስም ረታ ቢል ይገጥማል።
ሳላትአግዜር - ሳለአምላክ

236. **ሳላስብ - ሳላስብሽ**
ድንገተኛ መኾንን ያመለክታል።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

237. **ሳላይሽ - ሳላያት**
በርቀት መኖርን ያመለክታል ...። **ሳልሽ**

238. **ሳምራዊት**
የሳምራዊት ሴት ማለት ነው። ኢትዮጵያዊት እንደሚለው ። ስለዚህች ሴት በዮሐንስ ወንጌል ተገልጿል (ዮሐ. 4፣7)።

239. **ሳሮን**
በእስራኤል በታላቁ ባሕር አጠገብ ከኢዮጴ እስከ ቀርሜሎስ ያለው ፍሬያማ ቦታ (1ዜና.27፣29 ፤ ኢሳ.35፣2 የሐ.ራ 9፣35)።

240. **ሳሳኹልሽ**
መጓጓትን ፣ መሰስትን ያመለክታል።
ያባት ስም ወዳጄ ቢል ይገጥማል።

241. **ሳበች**
ከዚያም ከዚህም ወለደች አገናኘች።
ያባት ስም በለው ቢል ይገጥማል።
ሳበችሽዋ - ሳበችይፋት

242. **ሳባ - ሳባነሽ - ሳባወርቅ**
በመጽሐፈ ነገሥት ሳባ፤ በክብረ ነገሥት ሰሚ ግከዳ ፤ በወንጌል ስመ መንግሥቷ (ያገሯ ስም) እዜብ በመባል የምትታወቀው የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ንግሥት የቀዳማዊ ምኒልክ እናት ነች።
እናንተ የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት ሆይ እኔ ጥቁር ነኝ ፤ ነገር ግን ውብ ነኝ። እንደ ቄዳር ድንኳኖች እንደ ሰሎሞንም መጋረጃዎች (መኃ. መኃ. 1፣5)።

243. **ስለናት**
የወላጅ እናት ምትክነሽ ለማለት የሚሰየም ስም ነው። **ስለዓይኗ - ስለወገን**
ያባት ስም አላምረው ቢል ይገጥማል።

244. **ስመኝ**
በምዕራብ ሸዋ በቡራዩ የተመሠረተው ገዳም ጴዴንያ ስመኝ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይባላል። መሥራቹ ስማቸው ወይዘሮ ስመኝ በኋላ እግዚአ በክርስትና ስማቸው ወለተ ጊዮርጊስ ይባላሉ።
ያባት ስም ዐዲስ ቢል ይገጥማል።
ስንመኝ - ስመኛት - ስመኝሽ - ሲመኙሽ

245. **ስሚሸዋ - ስሚአቸው**
ስሙልኝ ፤ ተረዱልኝ ለማለት ።
ያባት ስም በላቸው ቢል ይገጥማል።

246. **ስሜነሽ**
ምትክ መኾንን ያመለክታል።
ያባት ስም ክፍሌ ቢል ይገጥማል።
ስመጥሩ - ስሜነሽ - ስሜወርቅ

247. **ስርጉተ (ግእ) ስርጉት**
የተጌጠች ማለት ነው።
ስርጉተ ሥላሴ ክርስትና ስምን ተመልከች።

248. **ስብሐት**
ስብሐ አመሰገነ ከሚለው የመጣ ነው።
ያባት ስም ምስጋናው ቢል ይገጥማል።
ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማይት (ሉቃ. 2፣14)።
ስብሐተ ሥላሴ ክርስትና ስም ይኾናል።
ስብሐቲ (ትግ) - ስብሐትለአብ

249. **ስታረገው - ስታረግ**
ድርጊትን ይገልጻል።
ያባት ስም አየነው ቢል ይገጥማል።

250. **ስናፍቅሽ**
ስፈልግሽ ፣ አገኘሁሽ ...።

በጉጉት የምትጠበቅ መኾንን ይገልጻል።
ያባት ስም አገኘሁ ቢል ይገጥማል።

251. **ስንሻት**
ስንፈልጋት፣ ስንመኝሽ፤ ስሻሽ፣ ስፈልግሽ ለማለት ነው።
ያባት ስም በጸሎት ቢል ይገጥማል።

252. **ስንታየሁ**
በጎ የኾነን እና መጥፎንም ማየትን ያመለክታል። **ስንቱ - ስንታዬ - ስንታየ**
ያባት ስም ቸርነት ቢል ይገጥማል።

253. **ስንዱ**
የተሰናዳች፣ የተዘጋጀች ፣ ዝግጁ ማለት ነው። መዘገጃጀትን ያመለክታል።
ያባት ስም ለይኩን ቢል ይገጥማል።
ስንዲ - ስንዳዬ (ትግ) - ስንዳይ

254. **ስኂን (ግእ) ስኂን ምዑዝ**
ልብን ልባንጃ ፤ ነጭ ዕጣን ሽታው የሚጣፍጥ ማለት ነው።
አሐውር ለልየ ጎበ ደብረ ከርቤ ወውስተ አውግረ ስኂን ምዑዝ። ትርጉም፤
ወደ ከርቤው ተራራ ወደ ዕጣኑም ኮረብታ እኼዳለኹ.(መኃ. ዘሰ.3፣12)።

በዚህ ስም ብዙዎች ይጠሩበታል ።
የልጅ ሊያሱ ታላት አጎት፤ የአቴጌ መነን እናት ስኂን ሚካኤል ይባላሉ። (ስሀን)
ያባት ስም መዓዛ ቢል ይገጥማል።
ስኂን ማርያም ክርስትና ስምን ተመልከች።

255. **ስጦታ**
ልግስናን ያመለክታል።
ያባት ስም ግሩም ቢል ይገጥማል።
ስጦታሽ - ስጦታዋ - ስጦታነሽ

256. **ስፈልግሽ**
ጠፍቶ ፣ ታጥቶ የነበረን ያመለክታል።
ያባት ስም ፋኖሌ ቢል ይገጥማል።

257. **ስኳሬ – ስኳሬነሽ**
ጥፍጥ መኾንን፣ መወደድን ያመለክታል።
ያባት ስም ጣፈጠ ቢል ይገጥማል።

258. **ስብሐት (ግእ)**
የተመሰገነች ማለት ነው። ለወንድ **ስብሐት** ይኾናል ።

259. **ሶልያና (ግሪ) ጨረቃ** ማለት ነው።
ድንግል ማርያም ጊዜ ዕረፍታ **ለሶል ያና** ተብላ በያሬድ ድጓ ተጠርታለች።

260. **ሶስና (ዕብ.)**
ሳሳኹልሽ ማለት ነው ።
ሶስና እጅግ መልከ መልካም ነበረች ፤ ፈጣሪዋን እግዚአብሔርን ትፈራ ነበር። ባሏም ኢዮአቄም ይባል ነበር በሐሰት ተከሳ ንጹሕ መኾኗን ዳንኤል ፈረደላት (መጽ. ሶሰ. 1፣1)።

261. **ሶፍያ (ግሪ)**
ጥበብ ማለት ነው ። የቤት አመቤት ማለት ይኾናል።
በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በቁስጥንጥንያ በኢስታንቡል የተሠራ ቤተክ ርስቲያን ሀግያ ሶፍያ ተብሎ ይጠራል ፤ ምስጢራዊ ጥበብ ማለት ነው ።
ከቅድስት ሥላሴ አንዱ አካል ወልድ ጥበብ ተብሎ ይጠራል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዚህ ስም የሚታወቁ ብዙ ሴቶች አሉ (ተአ.ማር.)።

- ሸ -

262. **ሸለለች**
አማረች፣ ተዋበች፣ ፎከረች፣ አቅራራች ማለት ነው።

263. **ሸቱ – ሸታወርቅ**
ከልዩ ልዩ ተክሎች የሚቀመም ጣፋጭ መዓዛ ያለው ሽታ።
ሸታኹኝ - ሸታለም - ሺቲ
ሺታየ - ሸታዬ - ሸታይ - ሸቶ
ሺታ - ሸታኹኝ - ሸታነሽ - ሸታዋ

264. **ሸዋረጋ (ሸዋ)**
በዚህ ስም ይጠሩ የነበሩት የዐጼ ምኒልክ የመጀመሪያ ልጅ የንጉሥ ሚካኤል ባለ ቤትና የልጅ ኢያሱ እናት ናቸው። ይህ ስም ዐጼ ምኒልክ የመንግሥታቸውና የሕዝቡ መረጋጋትን የሚገልጽ ነው።
ሸዋለማ - ሸዋለም - ሸዋለሉ
ሸዋሉA - ሸዋላይ - ሸዋሐረግ
ሸዋሙበራት - ሸዋመና - ሸዋማማሸ
ሸዋማረ - ሸዋማናለ - ሸዋምኒል
ሸዋረታ - ሸዋረዳሽ - ሸዋደግ
ሸዋረዳት - ሸዋረገድ - ሸዋረጋሽ
ሸዋረጋ - ሸዋረግ - ሸዋርካብሽ
ሸዋበዛ - ሸዋብራ - ሸዋብርሃን
ሸዋብዛ - ሸዋነጋ- ሸዋነሽ- ሸዋናፈቁ
ሸዋንላንቺ - ሸዋንግዢው - ሸዋዳኝ
ሸዋአመነ - ሸዋዓለም - ሸዋነሰሽ
ሸዋወርቅ - ሸዋዘመድ - ሸዋዘራሽ
ሸዋዘርፍ - ሸዋዘርፍሽ - ሸዋዘውዴ
ሸዋዬነሽ - ሸዋጸጋ - ሸዋየ - ሸዋዬ
ሸዋይልፋ - ሸዋይርጋ - ሸዋይስማ
ሸዋደም - ሸዋጌጥ - ሸዋጫማሽ
ሸዋፈራ - ሸዋፈራሽ

በጥንት ዘመን የወሎ ባላባት ሴት ልጁን ለግሼው ባላባት ወንድ ልጅ አጋብቷት ስትኖር ከብዙ ዘመን በኋላ ልጆቿን ይዛ አባቷን ለማየት ወሎ ኼደች ፤ አባቷም በልጆቿ ብዛት ተደንቆ አነዚህ ኹሉ ምና ችስ ናቸው ቢላት እኩሉ ልጆቼ፣ እኩሉ የልጅ ልጆቼ ናቸው አለችው። ልጄ ሺዋ ልጄ ሺዋ ቀድሞም ስድርሽ ሺ ኹን ሺ ያድርግሽ ብዬ መርቄሽ ነበር አኹንም እንደ ምርቃቴ ሺ ሰለኹንሽ ከአንግዲህ ወዲህ ስምሽ ሺዋ ይኹን ብዬሻለሁ አላት (ኪዳ. ክፍ. ገጽ 861)።

ምናልባት ለአብርሃም አንደ ተደረገው ምርቃት ይኾን? ዘርኽን እንደ ሰማይ ከዋ ክብትና በባሕር አንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ (ዘፍ. 22፥17)።
ስመ ሀገር፤ ስመ ብእሲት ነው፤ ምሰጢሩ ብዙ ነው አሸዋ ከሚለው ይስማማል።

ይህ የማይመስል ተረት ነው የሚሉም አሉ ። ምክንያቱም ወሎ ዐዲስ ስም ነው ። ሸዋ ግን እጅግ ይቀድማል "ሴዋ" "ሠዋ" ካለው ግስ የወጣ ነው ብዙዎች የሚያምኑት ማስረጃው የጥንት የግእዝ መጻሐፍት ሠዋ ይላል ። መሥዋዕትነት ማለት ነው። በዕብራይስጥ "ኾለህ" ነው። የሚሉ አሉ።

265. **ሸጊቱ (ኦሮ)**
ቆንጆ ፣ ዐዲስ የምታስደስት ማለት ነው ። **ሸጋነሽ**
ሸጋወርቅ - ሸቱ - ሸጌ - ሸጋ

266. **ሸፈናት – ሸፈነችወርቅ**
መደበቅን ወይም ክብርን ያመለክታል።
ያባት ስም ስንሻው ቢል ይገጥማል።

267. **ሹመት**
ለክብር ለትልቅ መመረጥ ማለት ነው።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።
ሹሜ - ሹምየ - ሹመቴነሽ

268. **ሺረጋ**
በሺ ቁጥር ታላቅነትን መግለጽ ።
ሺማጫሽ - ሺሰማ - ሺትኹን
ሺምልጃሽ - ሺኩሪ - ሺወርቄ
ሺመብራት - ሺሸልማት

269. **ሺብሬ (ጉራ.) ሺብሪት - ሺብር**
የኔ ገንዘብ፣ ከገንዘብ የበለጠች።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።
ሸብሬ ካኾነ አሸባሪ ማለት ነው።

270. **ሻሺ (ኦሮ) ሻሺቲ - ሻኪ**
ነጭ በፍታ፣ ሥሥ ራስ ማሠሪያ ፣ ነጭ ሻሽ፤ መሸፈኛ ማለት ነው (ዘጸ. 34፥4)።

271. **ሸልማት - ሸልማቴ**
የልፋትን የክብር ዋጋ ማግኘት።
ያባት ስም አገኘሁ ቢል ይገጥማል።

272. **ሸምብር** (ጉራ) ጀግና ማለት ነው።

273. **ሸሸጌ**
ሸሸገ ከሚለው የወጣ ነው ። የብቻዬ ማለት ነው። **ሸሸግ**

- ቀ -

274. **ቀለሚ**
የወርቅ ቀለም ማለት ይኾናል (ኤር. 36፥18 ፤ 2ኛ ቆሮ. 3፥3 ፤ ዮሐ. 13)።
ቀለመወርቅ - ቀለሞዋ - ቀለሚ (ኦሮ)
ቀለሜነሽ - ቀለሜ - ቀለም

275. **ቀለበት**
የቃል ኪዳን ምልክት ነው ። በግራ እጅ አራተኛ የቀለበት ጣት ላይ ይጠልቃል።
የጌጥ ቀለበት ወርቅ (ዘፍ. 24፥22)።

276. **ቀለብ - ቀለቤ**
የላቤ ዋጋ። በየጊዜው የማገኘው ...።
ያባት ስም ታደለ ቢል ይገጥማል።

277. **ቀረብሽ - ቀረዓለም**
ኦሮ ፣ አኗኗር ተለወጠ ለማለት።
ያባት ስም ገዳሙ ቢል ይገጥማል።

278. **ቀነኒ** (ኦሮ) ማዕረጓ ማለት ነው።

279. **ቀኑ - ቀኒቱ** (ኦሮ)
ድሎተኛ የተቃናላት ማለት ነው።
ቀን (ዐማ) ከሚለው የተገኘ ነው።

280. **ቀኑብሽ**
ተመኙ ፣ ተመቀኙ ።
ያባት ስም ደግሰው ቢል ይገጥማል

281. **ቀኜነሽ**
ረዳቴ ነሽ ፣ ተገኔ ነሽ ...።
በቀኝ ያለ የሚያገለግል እጅ።
ያባት ስም ኃይሉ ቢል ይገጥማል።

282. **ቀዳሚጥበብ**
ጥበብ ይቅደም ፣
ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሀ እግዚአብሔር፤
ትርጉም፤ የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው (መዝ. 110(111)፥10)

283. **ቀጸላ – ቀጸላወርቅ**
የራስና የፊት መሸፈኛ ዘውድ፣ አክሊል ቆብ የራስ ቁር ማለት ነው ። የሐር የፈትል ሽልማት (1ኛ ነገሥ 21፥38 ፤ 41)።
ያባት ስም መንግሥቱ ቢል ይገጥማል።
ቀጸላ ጊዮርጊስ ፣ ቀጸላ ማርያም ከር

284. **ቁምነገር**
ዋዛ ፈዛዛ ያይደለ ፤ ቁም-ነገር።
ያባት ስም ወረሰ ቢል ይገጥማል።

285. **ቁጥሬ** (ኦሮ)
በዚህ ስም የምትታወቀው በሩጫ በዓለም አቋራጭ ውድድር በመሳተፍና አገሯን ያሳወቀች ቁጥሬ ዱለቻ ነች።

286. **ቃልኪዳን - ቃሌነሽ**
ኹለት ሰዎች ወይም ከኹለት በላይ የኾኑ ሰዎች ሲስማሙ ነገሩን ለማጽናት በእግዚአብሔር ፊት ቃል ይገባሉ (1ኛ ሳሙ. 18፥3)።
ያባት ስም **ዘለቀ** ቢል ይገጥማል።

287. **ቅመም**
ማጣፈጫ ማለት ነው።
ያባት ስም ማናዬ ቢል ይገጥማል።
ቅመሚት - ቅመምነሽ

288. **ቅርሴ**
ታሪክን የያዘ ቀሪ ሀብት።
ያባት ስም ዘላለም ቢል ይገጥማል።

289. **ቅብዓት - ቅባቷ**
ከልዩ ልዩ እጸዋት የተቀመመ ዘይት።
ያባት ስም መድኃኔት ቢል ይገጥማል።

290. **ቅድስት** (ግእ)
የተለየች ክፍል ፣ ከማሕሌት መቆሚያ ቀጥሎ ከመቅደስ መግቢያ በፊት መኾል ላይ ያለ ክፍል (ዘጸ. 26፥33 –35)።
ቅድስቲ - ቅድስቱ

291. **ቅጅነሽ**
የተቀዳች ፣ የተወሰደች ማለት ነው።
ያባት ስም ደሜ ቢል ይገጥማል።

292. **ቆንጂት (ቆንዢት) - ቁንጭና**
ውበትን ይገልጣል፣ የደስ ደስ ያላት።
ማእከለ ደናግል ዘባጥያተ ከበር።
ትርጕም፤ ከበሮን በሚመቱት በቆንጃጅት መካከል ፤ እግዚአብሔርን በጉባኤ አመሰግኑት (ዘፍ. 24፥43 ፤ መዝ. 67፥25)።
በማይጨው ጦርነት ለነጻነት ፣ ለሀገር ክብር ጣሊያንን ድል ያደረጉ ዐርበኛው ራስ አበበ አረጋይ ባለቤታቸው ወይዘሮ ቆንጅት በመባል ይታወቁ ነበር።

293. **ቄዲልኝ**
ኦሪልኝ ፣ ሰንብቺልኝ ማለት ነው።
ያባት ስም ዘመነለላም ቢል ይገጥማል።

- በ -

294. **በሀብቷ – በሀብትሽ**
ያባት ስም ሚሊዮን ቢል ይገጥማል።

295. **በለጥሻቸው**
በውበት፣ በዕውቀት በለጠች ፣ ላቀች ፣ ረዘመች ፣ በዛች ፣ ገነነች፣ ከበረች ...።
ማለት ነው። ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የዐፄ ምኒልክ አያትከወለዷቸው ልጆች አንዷ በለጥሻቸው በመባል ይታወቁ ነበር።
በለጠቻቸው - በለጤ - በለጡ
በለጠሽ - በለጠች

296. **በለሴ - በለሳን**
በበለሳ አገር ይሠራ የነበረ ወፍራም የተፈተለ ከርዳዳ ሽማ፣ የሚሞቅ። የበለስ ትር ጕም፡ ዕድል ቀናው ፤ ሀብት አገኘ ማለት ነው። አደን የሚያድኑ ሰዎች ወደ በለሳ በርሃ አየወረዱ በአደን ሀብት ሲገኘ ማቸው ከበለስ በረሃ አገኘኹ ቀናኝ ለማ ለት በለሴ ይላሉ (ወሎ)።

297. **በለሰ - በለሶ**
ቅጠሉ ሰፋፊ ነጭ ደም ያለው ፤ ፍሬው የሚበላ ዛፍ (ዘፍ. 3፥7 ፤ ሚኪ. 4፥4)
ጥሩ ሽቱ ያለው ቁጥቋጦ (ዘፍ.37፥25)።

298. **በላይነሽ - በላይቱ**
በመጀመሪያ ፣ ከአናት የኾነች።
ያባት ስም ይፍሩ ቢል ይገጥማል።

299. **በልዩ – በልዬ**
በተለየ ኹኔታ ።
ያባት ስም ጥበቡ ቢል ይገጥማል።

300. **በልጌነሽ**
በለገ ከሚለው ግስ የወጣ ነው።
አቆጠቆጠ፣ ለመለመ ለማለት ነው።
ከአራቱ ወቅቶች አንዱ ከረምት፣ ጸደይ፣ ሀጋይ ፣ በልግ (መጸው) ። በደጋ ቦታ ኹለተኛ የምርት ዘመን ነው።
ያባት ስም እሸቱ ቢል ይገጥማል።
በልግ - በልግነሽ - በለጓ

301. **በሐርወርቅ**
ሐር፤ ከትል የሚገኝ ድር በጣም የከበረ፤ ለጌጥና ለክብር ልብስ ያገለግላል (ሕዝ. 16፥10፥13 ፤ ራእ. 18፥12)።
ያባት ስም ጌጡ ቢል ይገጥማል።
በሐሩ - በሐርነሽ

302. **በሕይወት**
ሕይወት እያለ ...።
ያባት ስም አንለይ ቢል ይገጥማል።

303. **በረከት**
እግዚአብሔር ይባርካል ፤ ሰዎችም ይባርካሉ። ማንኛውም ነገር እንዲባረክ፤
ጠቃሚና መልካም ነገር ተገኘ ማለት ነው።
(ዘፍ. 1፥22 ፤ 2፥3 ፤ ኤፌ. 1፥3 ፤ ዘጎ 6፥22 ፤ 2ኛ ቆሮ.13፥14)።

304. **በሩ** (ኦሮ) ቦራ
ምልክት ማለት ነው ። ቦራ ከሚለው የመጣ ነው። **አባቦራ**

305. **በርነሽ – በሪቱ - በርያምቹ**
መግቢያ ፣ ደጃፍ ።
ያባት ስም ድርሻዬ ቢል ይገጥማል።

306. **በሰልፏ – በሰልፍዋይ**
በተራዋ ፤
ያባት ስም ይከበር ቢል ይገጥማል።

307. **በሥራ**
ወጥቶ ወርዶ ሥራ በመሥራት ።
ያባት ስም ተወረሰ ቢል ይገጥማል።

308. **በሸዋምየለሽ – በሸዋምየለች**
በማወዳደር የሚገለጽ። (ስመ ሀገር)
ያባት ስም ወርቃለም ቢል ይገጥማል።

309. **በሺወርቅ**
ዋጋን በማወዳደር።
ያባት ስም ይግዛው ቢል ይገጥማል።

310. **በሻዱ** (ኦሮ) አማረች ማለት ነው።

311. **በቀለች – በቀሉ**
ብቅ አለች ። አትክልት ፣ ችግኝ ምሳሌ ነው። ተገኘች ፣ ወጣች።

312. **በቃሽቢል**
በፈጸምልኝ ፤ ምኞትን ይገልጸል።
ያባት ስም መላኩ ቢል ይገጥማል።

313. **በቃልዋ**
ቃሏ በተናገረው፤ በተናገረችው መሠረት።
ያባት ስም ታመነ ቢል ይገጥማል።

314. **በቅባቷ**
በግርማዋ ፣ በጸጋዋ ።
ያባት ስም ውብነኽ ቢል ይገጥማል።

315. **በተሰፋነሽ – በተሰፋ**
በጉጉት የተጠበቅሽ ።
ያባት ስም ፋንታዬ ቢል ይገጥማል።

316. **በተውልኝ - በተወሽ -**
ያባት ስም ጸጋ ቢል ይገጥማል።

317. **ቢታደግልኝ** (ግእ)
በተለመነኝ ፣ ብታድግልኝ
ያባት ስም በጸሎት ቢል ይገጥማል።

318. **በትረወርቅ - በትረሃይማኖት**
ከወርቅ የተሠራ ዘንግ ፣ መቋሚያ።
ያባት ስም ክብሩ ቢል ይገጥማል።

319. **በትዛዟ**
በፍቃደ ፤ በኃይልዋ
ያባት ስም ደመቀ ቢል ይገጥማል።

320. **በትግሏ**
በራስዋ ኃይል ፤ በጥረቷ።
ያባት ስም አሸናፊ ቢል ይገጥማል።

321. **በቸኒ** (ጉራ)
መጣችልኝ ማለት ነው ።

322. **በጎይሏ – በጎይልሽ**
በችሎታዋ ፣ በጉልበቷ ...።
ያባት ስም ይዳኙ ቢል ይገጥማል።

323. **በነበርሽ – በነበረች**
ቀደም ብሎ ባየሽ ፤ በተረዳሽ
ያባት ስም ዳኖቸው ቢል ይገጥማል።

324. **በአምላክሽ - በአምላኪ**
ፈቃድ፣ ትእዛዝ ...።
ያባት ስም ፈቃዱ ቢል ይገጥማል።

325. **በአምነት (በምነት)**
በማመን ኾኖልኛል ፤ ተደርጎልኛል።
ያባት ስም አርጋቸው ቢል ይገጥማል።

326. **በአደብርሃን**
አድ ማለት አጅ ማለት ነው። በብርሃን አጅ። **በአደወርቅ - በአደማርያም**

327. **በዐለማርያም – በዐሉነሽ**
በአምርት ዕለት በዓልነ ። ትርጉም፤ በክ ፍተኛ በዐላችን ቀን። (መዝ. 80(81)፥3)።
ያባት ስም ክብሩ ቢል ይገጥማል።

328. **በዓለም (ባለም)**
በሕይወት የመኖሪያ ቦ፤ ጉደለት የሌለበት በሀብት ፤ በድምቀት።
ያባት ስም ሽታዬ ቢል ይገጥማል።

329. **በዕውቀት (በውቀት)**
በጥበብ፣ በብልሀት (1ቆሮ. 8፥1)።
ያባት ስም ወርቃገኘኹ ቢል ይገጥማል።

330. **በዛብሽ**
የንጉሥ ጎይለ መለኮት አናት የዐፄ ምኒ ልክ አያት አቴጌ በዛብሽ ደጀን በመባል ይጠሩ ነበር ። በዛጌጥ - በዙብሽ በዛወርቅ - በዛረድኤት - በዙ በዛወርቁ - በዛዬነሽ - በዛጉልትሽ

331. **በዝና - በዝናሽ - በዝናዋ**
በገናናነትሽ ...።
ያባት ስም ሰሙ ቢል ይገጥማል።

332. **በየነች**
ፍርድ ሰጠች፣ ፈረደች፣ ዐወቀች፣ ለየች፣ ወሰነች ማለት ነው ።
ያባት ስም በፍርዱ ቢል ይገጥማል።

333. **በድሏ**
በተሰጣት፤ ከእግዚአብሔር በታዘዘው።
ያባት ስም ታረቀን ቢል ይገጥማል።

334. **በጸሎቴ**
ከብዙ ጸሎትና ልመና በኋላ ተገኘች ማለት ነው። **በጸሎትሽ - በጸሎቷ**

335. **በጸጋሽ - ብጸጋዋ**
በተሰጠሽ ዕድል ፣ ሰጦታ ፣ ክብር።
ያባት ስም ታደለ ቢል ይገጥማል።

336. **በፈቃዲ**
እሷ ባለችው መሠረት።
ያባት ስም ነገሠ ቢል ይገጥማል።

337. **ቡርትካን (ብርቱካን)**
በኩረ ሎሚ ይባላል።
ፖርቹጋን ከሚለው ቡርቱካን ተፈጠረ ።
ጣፋጭ የኾነ ፍሬ ማለት ነው ።
የመልክ ደምግባትን፤ ውበትን ያመለክታል ያባት ስም ፋንታዬ ቢል ይገጥማል።
ብርቱካን - ብርቱካኔ

338. **ቡርክት**
የተባረከች፤ የተመሰገነች፤ ክብርት ማለት ነው (ሲራ. 45፥1 ፤ ሉቃ.1፥42 ፤ ዘጸ. 29፥21) ። **ቡርክቲ (ትግ) - ቡሩኬነሽ ቡርክተ - ቡርክቴ - ቡርክት ቡርክነሽ - ቡርክት - ብርክታዊት**

339. **ቢሩታዊት - ቤሩታዊት**
ቅዱስ ጊዮርጊስ ከዘንዶው ያዳናት ወጣት ሴት ልጅ (ገድ. ጊዮ) የቤሩት ተወላጅ።

340. **ቢተውሽ – ቢተዋት**
ቢለቅሽ ፣ ባይዝሽ ።
ያባት ስም በጎሰው ቢል ይገጥማል።

341. **ቢነጋፀሓይ**
ውበትን፣ ደምግባትን ይገልጸል ።
ንጋት ላይ ፀሓይ ቢወጣ ተገኘች።
ያባት ስም ታዬ ቢል ይገጥማል።

342. **ቢፍቱ** (ኦሮ) ፀሓይ ማለት ነው።

343. **ባሕረጥበብ - ባሕርነሽ**
የባሕር፤ ከባሕር ማዶ የመጣች ጥበብ።
ያባት ስም ታከለ ቢል ይገጥማል።

344. **ባለሟል - (በዓለ - ሙዓል)**
ብልህ፣ ዐዋቂ፣ ባለብዙ ዕውቀት፤ ሙያዋ ያማረ ፤ የሴት ቁነጮ ማለት ነው።
ያባት ስም ጥበቡ ቢል ይገጥማል።

345. **ባላገር (በዓለ ሀገር) - ባለወርቅ**
ያገር ተወላጅ፤ አገርና አርሰት ያላት።
(ዘሌ. 17፥15) ተወዳጅ ...።

ሴ

አንግዲህስ ወዲያ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮች እና የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናችሁ (ኤፌ. 2፥19)። ምእመናን በእግዚአብሔር መንግሥት እንደ ባለርስት ናችሁ። ያባት ስም ታደለ ቢል ይገጥማል።

346. **ባምላኪ (በአምላኪ)**
በፈጣሪዋ ...።
ያባት ስም ችርነት ቢል ይገጥማል።

347. **ባራኪ**
የመጀመሪያዋ፤ የምትባርክ ማለት ነው።
ያባት ስም መልከጼዴቅ ቢል ይገጥማል።

348. **ባንቺአምላክ**
በፈጣሪሽ ፈቃድ ...።
ያባት ስም ታፈሰ ቢል ይገጥማል።
ባንቺይዋሉ - ባንቺ - ባንቻየሁ
ባንቺይርጉ - ባንቺጊዜ - ባንቺይዳኝ
ባንቺአየሁ - ባንቻለም - ባንቺይርጋ
ባንቺይመስን - ባንቺይደር

349. **ባንቺይለኩ**
ሌሎች ቤቶች ባንቺ ይመጡኦ ማለት ነው።
ባንቺዬ - ከፊለ ስም የኔ አንቺ ማለት ነው።

350. **ባንቁዕ (ጉራ)** የኔነሽ ማለት ነው።

351. **ባዩሽ – ባዩሽዓለሜ - ባዩሺ**
ምነው እነዚያ ዘመዶችሽ ባዩሽ፤ ቁንዥና ሽን ባዩ ማለት ወይም ደግሞ መሳይ መኾንሽን ባዩ ማለት ይኾናል።
ባየች - ባየንሽ - ባየናት

352. **ባይኔ (በዓይኔ)**
ያባት ስም እንግዳየኹ ቢል ይገጥማል።

353. **ባደገች (በአደገች)**
ያባት ስም ችሮታው ቢል ይገጥማል።

354. **ባፈና**
በማፈን ፤ በከበባ ማለት ነው።
በዚህ ስም የዐፄ ምኒልክ ኹለተኛ ባለቤት ወይዘሮ ባፈና ይታወቃሉ ። ዐፄ ምኒልክ የመጀመሪያ ባለቤታቸው ፤ የዐፄ ቴዎድሮስ ልጅ ወይዘሮ አልጣሽ ነበሩ ፤ ሦስተኛዋ ጣይቱ ናቸው።

355. **ቤርባቤህ (ዕብ.)**
ሰባተኛ ልጅ ወይም ታላቅ ደስታ ኾነ ማለት ነው ። መልክ መልካም የነበረች ነች። ባሏ ኦርዮ በተንኮል እንዲሞት ተደረገ ። ንጉሥ ዳዊት አግብቷት ሰሎሞንን ወለደች። የንጉሥ ሰሎሞን እናት ነች። (ማቴ. 1፥6) ።

356. **ቤተልሔም**
የእንጀራ ቤት ። ጌታ የተወለደበት ቦታ የቀድሞ ስሟ ኤፍራታ ትባል ነበር (ዘፍ. 35፥19 ፤ ማቴ.2፥1)።

357. **ቤቴል (ዕብ) (ቤቴ - ኤል)**
የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው ። ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን የነበረ ከተማ (ዘፍ. 12፥8)።

358. **ቤዛ**
ስለ ፋንታ (መድኃኒት ዋጋ) ጥላ ከለላ አዳኝ ማለት ነው ። የጠፋን ነገር ለመመለስ የሚከፈል ዋጋ፣ ካሣ፣ ለውጥ ማለት ነው (ማር. 10፥45፤ ኤፌ. 1፥7፤ ጢሞ.2፥5 ፤ ዕብ. 9፥12)። **ቤዛዊት - ቤዛለም**
ቤዛነሽ - ቤዛወርቅ - ቤዛኩሉ

359. **ብሌን**
የሚሳሳላት፣ በጥንቃቄ የምትጠበቅ ...።
ከዐይን ውስጥ ጥቁሩ ክፍል ። በምሳሌነት እግዚአብሔር ለሚጠብቃቸው ኹሉ ይነገራል (ዘዳ. 32፥10፤ መዝ. 16፥8 ፤ ምሳ. 7፥2 ፤ ዘካ. 2፥8)።

360. **ብልጫነሽ – ብልጫዬ**
ከሁሉ የተሻልሽ ...።
ያባት ስም ኪነጥበብ ቢል ይገጥማል።

361. **ብሥራት (ግእ)**
የምሥራች ዐዲስ ወሬ ማለት ነው።
በሠረ ፤ አብሠረ ካለው ግስ የወጣ። (ሉቃ. 1፥31)። **ብሥራተ - ብሥራቴ**
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።

362. **ብሬነሽ**
በኹለት ይተረጐማል። አንዱ ገንዘብን። አንዱ ማዕድንን ከወርቅ ቀጥሎ ለከበረ ዕቃ መሥሪያ ይጠቅማል (ዘፍ. 23፥15 ፤ ኤር. 32፥9)።
ያባት ስም ደሞዜ ቢል ይገጥማል።
ብርጣሉ - ብርሽት - ብሬ - ብሬቱ
ብርይከቡ - ብርዛፌ - ብርነሽ

363. **ብርሃነሕይወት – ብርሃን**
እግዚአብሔር ብርሃን ነው (1ኛ ዮሐ. 1፥5 ፤ 1ኛ ጢሞ. 6፥16) እግዚአብሔር በመጀመሪያው ቀን ብርሃን ይኹን (ስይኩን ብርሃን) ብሎ ብርሃንን ፈጠረ፤ (ዘፍ. 1፥3–18) ይህ ስም ለሴት ለወንድ ይኾናል ።
ብርሃነፀሐይ - ብርሃንሽ - ብርሃኒ
ብርሃነዓለም - ብርሃናት - ብርሃናዊት

364. **ብርሃኔ**
በዚህ ስም ታዋቂ የኾነችው በሩጫ ውድድር የዓለምን ክብር ወሰን በመያዝ አገሯን ያስከበረች **ብርሃኔ አደፍ** ነች። ፓሪስ ላይ ያገኘችውን የወርቅ ሜዳልያ ሽልማት እንዲሁም በዱባይ የተገኘውን ሜዳልያ ለእንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመስጠት በመዘከር ተቀምጦ ጐብኝ ይነበንዋል።

365. **ብርቃየኹ (ብርቅለየኹ)**
የመጀመሪያ ልጅ ... ።
ያባት ስም ከተማ ቢል ይገጥማል።
ብርቁ - ብርቅሽ - ብርቅነሽ
ብርቁነሽ - ብርቃየሁ - ብርለገኘሁ
ብርቂ - ብርቅነች - ብርቅዓለም
ብርቂ - ብርቂቱ (ኦሮ)

366. **ብርዝዬ**
የኔ ጣፋጭ ብርዝ ...።
ብርዝ ከማር ጋር የተቀላቀለ ማለት ነው።
ብርዚ - ብርዜ - ብርዝነሽ

367. **ብርጉዴ ብርጉዲነሽ - ብርጉድ**
እንደ ዕጣን ያለ ሽታው ቤትን የሚያውድ። ከሩቅ የሚሸት ስር። ሴቶች የሚሞቁት እንደ ወገርት ግሩም ሽታ ያለው ማለት ነው (ዘጸ. 30፥24 ፤ ሕዝ. 27፥19)።

368. **ብስኩት – ብስኩቴ**
ጣፋጭ ምግብ ማለት ነው ።
ያባት ስም ተረፈልኝ ቢል ይገጥማል።

369. **ብትወጣ**
የራስ ዐሉላ እንግዳ ቁቢ (አባ ነጋ)፣ የመጀመሪያ ባለቤት ወይዘሮ ብትወጣ ይባሉ ነበር።

370. **ብዙነሽ - ብዙዬ**
ያባት ስም ሀብቴ፣ ግንደፍር፣ ሞላ ትርፌ፣ እሸቴ ቢል ይገጥማል።

ብዙወርቅ - ብዙአየን - ቡዙ
ብዚኹ - ብዙወርቅ - ብዙ
ብዙሰው - ብዙነሽ - ብዙዓለም
ብዙዐይኔ (ብዙ ዐይኔ) **- ብዙዐይኔ**

371. **ብፅዕት - ብፅዐቴ - ብፅዐት**
የተባረከች ደስተኛ ማለት ነው (የሐ. ሥራ. 20፥35 ፤ ሉቃ.1፥48 ፤ ማቴ.5፥3)።
ያባት ስም ስሞታው ቢል ይገጥማል።

372. **ቦሰና** (ኦሮ) ጫካ ማለት ነው።

373. **ቦንቱ** (ኦሮ)
የሴት አንበሳ ኩራተኛ ማለት ነው።

374. **ቦጋለች**
በጎይል በራች፣ ታየች፤ ዓይናማ መኾኗን ያሳይል።
ያባት ስም ፀሐይ ቢል ይገጥማል።

- ተ -

375. **ተመሰገነች - ተመሰገን**
ምስጋናን ማግኘትን ያመለክታል ።
ያባት ስም አገኘሁ ቢል ይገጥማል።

376. **ተመቸሽ**
መደላደልን፣ መረጋጋትን ያመለክታል
ያባት ስም ሰንቄ ቢል ይገጥማል።
ተመቸ - ተመቹ - ተመቸሻቸው

377. **ተመኘ**
አሰቡ፣ ከጀሉ፣ ፈለጉ (1ዜና. 11፥17)።
ምኞት፣ መጓጓትን ያመለክታል።
ያባት ስም ሙሉቸዋ ቢል ይገጥማል።
ተመኙ - ተመኙሽ - ተመኘሽ

378. **ተሙኒ** (ጉራ) **ተመኔ**
ተመኑ ሰንት ነው። ዋጋው ሰንት ነው።
ያባት ስም ዋጋው ቢል ይገጥማል።

379. **ተማረች - ትምህርተ**
ልጆችን ማስተማር ይገባል (ዘጸ. 12፥25)።
ያባት ስም ጥበብ ቢል ይገጥማል።

380. **ተምኔት** (ግእ)
ሐሳብ፣ ምኞት ማለት ነው።
ረከብኩ ስእለትየ ረከብኩ ተምኔትየ ።
ትርጉም፤ ልመናየን ፣ ምኞቴን አገኘሁ ማለት ነው። **ተምኒት**
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።

381. **ተረጨች**
እንደ ጠበል መዳረስ፤ ለኹሉ ተዳረሰች።
ያባት ስም ንጥርወርቅ ቢል ይገጥማል።

382. **ተረዳች**
መረዳት መገንዘብ ይኾናል። መታገዝ ታገዘች ይኾናል።
ያባት ስም ሃይማኖት ቢል ይገጥማል።

383. **ተረፈችልኝ - ተረፈች**
ከመከራ ወጣች ፣ ቀረች ።
ያባት ስም ለዓለም ቢል ይገጥማል።

384. **ተሰማሽ - ተሰሙ**
ሰሜትን ያመለክታል ። በጆሮ መስማትን ያመለክታል።
ያባት ስም ነጻነት ቢል ይገጥማል።

385. **ተስፋ - ተስፋዓለም**
ናፍቆት (መጓጓት)፣ ምኞት፣ አለኝታ እና መተማመን የሚገኝበት። ተስፋ በዚህ ዓለም አይወሰንም (ሮሜ.15፥13 ዕብ.11፥1)።
ተስፋይ - ተስፋዬነሽ - ተስፋነሽ

386. **ተሻለች - ተሻይ**
በማወዳደር ከሌላው በለጠች።
ያባት ስም በምነት ቢል ይገጥማል።

387. **ተሻወርቅ - የተፈለገች ወርቅ።**

388. **ተሾመች**
ማዕርግ አገኘች ፤ ከፍ ከፍ አለች።
ያባት ስም ላውጋለት ቢል ይገጥማል።

389. **ተቀባሽ**
ቅባት ፣ ግርማ ሞገስ ፣
ያባት ስም ጸጋ ቢል ይገጥማል።

390. **ተቋመ - ተቋም**
የብርሃን መቋሚያ መቅረዝ (ዘጸ. 40፥4)።
ያባት ስም ወርቅነኽ ቢል ይገጥማል።
ተቋመ ወርቅ - ተቋመ ማሕቶት (ግእ)

391. **ተናኘች - (ተናኜ) ተናኘወርቅ**
ተሰጠች ፣ ታደለች፣ ተሰራጨች፣ ተነዛች ተበተነች፣ ተዘራች፣ ተዘረከተች ማለት ነው። በዚህ ስም የራስ መኰንን እናት የዐፄ ኃይለ ሥላሴ አያት ልዕልት ተናኘወርቅ ይባሉ ነበር። እንዲሁም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የመጀመሪያ ልጅ ልዕልት ተናኘወርቅ ይባሉ ነበር።

392. **ተንከተም** (ግእ)
መወጣጫ (መሰላል) ማለት ነው።

393. **ተአምር** (ታምር)
አስደናቂ ድርጊት ። የማይኾነው ሲኾን። ድንቅ ነገር ከእግዚአብሔርና ከቅዱሳኑ የሰዎችን ችግር የሚያቃልል ማለት ነው። (የሐዋ. 9፥36 - 41 ፤ 20፥9 - 12)።
ተአምርነሽ - ተአምራቴ - ተአምራትነች
ተአምረ ማርያም ከርሰትና ሰም።

394. **ተከለች**
አታክልትን ሊኾን ይችላል።
ያባት ስም መሠረት ቢል ይገጥማል።

395. **ተካበች**
ተደራረበች ፤ ካብ ካብ ተደረገች ፤ ከፍ ከፍ አለች። **ተካበወርቅ - ተካቡ**
ያባት ስም እሸቴ ቢል ይገጥማል።

396. **ተክሊል**
ሌላ ሰው የማይደርስበት የተከለለ ። በመ ከለሉ ተጠበቀ ማለት ነው።
ያባት ስም ከብሩ፣ ጸጋው ቢል ይገጥማል

397. **ተኩላሽ**
ደመቅሽ፣ ተቀባሽ፣ ጠራሽ፣ ተወለወልሽ፣ ተዋብሽ...። ኩል የተኳለች ማለት ነው። ዓይንን ለማሳመር የሚቀቡት ቅባት። ሽፋሽፍት በኩል መኳኳል (2ነገሥ. 9፥30፤ ኤር. 4፥30 ፤ ራእ. 3፥18)።
ያባት ስም ውበቴ ቢልይገጥማል።

398. **ተወዳጅ – ተወዳድ**
በሾክ መካከል አንዳለ የሱፍ አበባ እን ዲሁ ወዳጄ (ተወዳጅ) በቆንጆዎች መካ ከል ናት (መኃ. መኃ. 2፥2)።
ያባት ስም አገሬ ቢል ይገጥማል።

399. **ተዋበች – ተዋቡ**
አማረች፣ ቆንጆች ማለት ነው ።
(1ሳሙ. 17፥42) አንቺ በሴቶች ዘንድ የተ ዋበሽ ሆይ (መኃ. መኃ. 1፥8)።

400. **ተዘራሽወርቅ**
ተባዛች ፣ ተዳረሰች ።
ተዘራወርቅ - ተዘሩ - ተዘራ

ሴ

401. **ተድባበ** (ግእ) - **ተድባብ**
ጫፍ ፣ ድጋፍ ጥላ ማለት ነው።

402. **ተገንሽ - ተገንነሽ**
ከለላ ፣ መከላከያ ፣ አለኝታ ...።
ያባት ስም ይርዳው ቢል ይገጥማል።
ተገኒ - ተገንወርቅ

403. **ተገኘች - ተገኘችወርቅ**
የታሰበችው፤ የተፈለገችው ።
ያባት ስም ሲሳይ ቢል ይገጥማል።

404. **ተጌጠች**
በከበረ ዕንቊ ፤ በወርቅ ።
ያባት ስም በእምነት ቢል ይገጥማል።

405. **ቱሪ** (ኦሮ)
ዘገየች ቈየች ማለት ነው።

406. **ታሪኳ - ታሪክአየሁ (ታሪካየሁ)**
ያለፈ የሚወሳ ነገር ያላት ።
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።
ታሪኬ - ታሪክ - ታሪካዊ

407. **ታለጌታ – ታለጌታሽ**
የምመካበት ፣ የምጽናናበት ።
ያባት ስም ተመስገን ቢል ይገጥማል።

408. **ታመነች - ታማኝ**
ቃሏን የምትፈጽም፤ ጠባይዋ ጨዋ የኾነ፤ ክርስቲያን (ሉቃ. 12፥41 ፤ 16፥10 ፤ 2ቆሮ. 1፥18 ፤ 2ኛ ጢሞ. 2፥11)።
ያባት ስም በቃሉ ቢል ይገጥማል።

409. **ታምራለች - ታምሪያለሽ**
ውበት፣ ቁንጅና፣ ታይታ የማትጠገብ።
ያባት ስም ከተማ ቢል ይገጥማል።

410. **ታረቀች – ታረቀችኝ - ታረቁ**
ጠብ ባለባቸው መካከል ሰላም ወረደ ።
የሚያስታርቁም ብፁዓን ተብለዋል (ማቴ. 5፥9 ፤ ፊል. 4፥2)።
ያባት ስም በፈቃዱ ቢል ይገጥማል።

411. **ታከለች**
ተጨመረች ፤ ተደረበች ...።
ያባት ስም አዱኛ ቢል ይገጥማል።
ታከሉ - ታከል - ታኪያ - ታኪላ

412. **ታየች – ታዩ**
ዐዲስ ብቅ አለች፤ በአይን መታየት ...።
ያባት ስም ፀሐዩ ቢል ይገጥማል።

413. **ታደሰች - ታዱሴ - ታደሱ**
በዕድሜና በጊዜ እንደ ገና መታደስ ...።
ያባት ስም የኹሉወርቅ ቢል ይገጥማል።

414. **ታደገችኝ**
ተቤዣችኝ፣ አዳነችኝ፣ አስጣለችኝ፣ አስለቀቀችኝ ማለት ነው።
ያባት ስም የእኔሰው ቢል ይገጥማል።

415. **ታደለች**
በተራ ተሰጠች፣ ተቸረች (አሰ. 1፥7)።
ኹለተኛው በጎ ነገር ተደረገላት ታደለች።
ያባት ስም አገሬ ቢል ይገጥማል።
ታደሉ - ታደልሽ

416. **ታገሠች**
ቻለች ተሰፋ በማድረግ ጸናች፤ ዝምአለች (ሮሜ. 2፥4 ፤ 15፥5 ፤ 1ኛ ጴጥ. 3፥20 ፤ ገላ. 5፥22)።
ያባት ስም በሱፈቃድ ቢል ይገጥማል።

417. **ታጎቴ** (ዶር) ባለቤቴ ማለት ነው።

418. **ታጠረች - ታጠረችበወርቅ**
ተከበበች ፣ ተጠበቀች ...።
ያባት ስም በጸጋው ቢል ይገጥማል።

419. **ታፈሠች - ታፈሠወርቅ- ታፈሡ**
ተሰብስባ ተወሰደች ።
ያባት ስም ሚሊዮን ቢል ይገጥማል።

420. **ታየድራ**
አለአሰከንድሮስና አትናቴዎስ ያስተማሯት ስማዕት ቅድስት ታየድራ ትባል ነበር (ስንክ. ሚያ. 11 ገጽ. 173)።

421. **ቴክላ** (ግሪ)
የመለኮት ክብር ማለት ነው (ተአ.)።
በሰማዕታት ዘመን ንጉሡ ዲዮቅልጥያኖስ
የቅዱስ አባ ኤሲ አኅት ቴክላ
አባታቸው **ኤልያስ** እናታቸው **ማርያ** ይባሉ ነበር ። እነርሱም ለጣዖት ባለመስ ገዳቸው በሰማዕትነት ተሰየሩ
(ስን. ታሕሣ 8 ገጽ. 432 ቁ. 37)።

422. **ቴዎብስታ**
በግሪክ ቋንቋ አቅሌስያ ማለት ነው። በግ አገዝ ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው። የቅዱስ ጊዮርጊስ እናት ስም ነው (ገድ. ጊዮ.)።

423. **ቴዎድራ** (ግሪ)
የአግዚአብሔር ስጦታ ማለት ነው ።
በቤተክርስቲያን ታሪክ በስንክሳር በብዙ ቦታ ተጠቅሷል። የወሬ ልብነ ድንግል ቤተ አጅ ቴዎድራ ትባል ነበር ።

424. **ቴዎዶስያ** (ግሪ)
በዘመነ ሰማዕታት ስማዕትነትን የተቀበለች ቅድስት ቤት (ስን. ሐም.6 ገጽ 522)።
የገብረ ክርስቶስ እናት ።

425. **ትሕትና - ትሕትናሽ**
እግዚአብሔር ትሕትናን ይወዳል። ራስን ዝቅ ማድረግ፤ ሌላው ሰው እንዲጠቀም መፈለግ (2ኛ ዜና. 7፥14 ፤ ያዕ. 4፥6) ። ሙሴ እጅግ ትሑት ሰው ነበር (ዘኍል. 12፥3)።

426. **ትመስገን**
ምስጋናን መስጠትን ያመለክታል ።
ያባት ስም ገንዘቤ ቢል ይገጥማል።

427. **ትመስል** (ግእ)
ትመስላለች ማለት ነው።

428. **ትምህርት**
ዐዲስ ነገርን ማወቅ ማሰረዳት፣ መንገር (ዘዳ. 12፥25)።
ያባት ስም ጥበቡ ቢል ይገጥማል።
ትምህርታቸው - ትምህርተ

429. **ትሩፋት** (ግእ)
ተረፈ ቀረ ተትረፈረፈ ። በጎ ሥራን መሥራት ፤ ስድስቱ ቃላተ ወንጌል (ሕገ ወንጌል) የፍጹምነት ሕግ ነው።
(ማቴ. 5፥21 ፤ 6፥1 ፤ ማቴ. 25፥42)።
ያባት ስም ምግባሩ ቢል ይገጥማል።

430. **ትርሐስ** (ግእ)
ትራስ ፤ መጪጊያ ማለት ነው።
በትግሪኛ ጥሩ ዕድል የመጀመሪያ ልጅ ማለት ይኾናል።
ርሕስ ከሚለው ግስ ከወጣ ከኾነ ራስ ፣ ረጠበ የሚል ትርጕም አለው።

431. **ትርሚት** (ግእ)
ጌዋ ሽልማት የክብር ልብስ ማለት ነው።
አባት ለልጁ የሚሰጠው ሀብት
(ሮሜ 8፥15፤ 9፥4፤ ኤፌ.1፥5፤ ገላ. 4፥5)
ትርሚተ ወልድ ክርስትና ስም።

432. **ትርንጎ**
ጣዕም እና መዐዛ ያለው ደሰ የሚል፤
በደጋማ ቦታ ላይ የሚበቅል ፍሬ ነው።
ያባት ስም ፍሬሠናይ ቢል ይገጥማል።

433. **ትርዳማርያም**
ማርያም ትደግፈኝ ፣ ትቅረበኝ ...።
ያባት ስም ጤናነህ ቢል ይገጥማል።

434. **ትርጋዓለም** (ትርጋለም)
መረጋጋትን ያመለክታል ...።
ያባት ስም በፍቅሩ ቢል ይገጥማል።

435. **ትርፌ - ትርፏ**
ያተረፍኩት ዋጋዬ ...።
አምስት የተቀበለው ሌላ አምስት አተረፈ
ኹለት የተቀበለው ሌላ ኹለት አተረፈ፤
(ማቴ. 25፥15)። **ትርፍዓለም** -
ያባት ስም በለጠ ቢል ይገጥማል።
ትርፍነሽ - ትርፈሳ - ትርፉ

436. **ትሰሜ**
የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ የራስ
ዳርጌ ልጅ ትሰሜ ትባል ነበር።

437. **ትሻል**
ምርጫን፣ ማወዳደርን ያመለክታል።
ያባት ስም በነበረ ቢል ይገጥማል።

438. **ትሻገር - ተሻገሪ**
ወንዝን ፣ መከራን ማለፍ።
ያባት ስም አድግስ ቢል ይገጥማል።

439. **ትቀድስነ ማርያም**
አባ ቶማስ የሚባሉ የገዳም አበምኔት
(አስተዳዳሪ) **እናታቸው ትቀድስነ ማርያም**
ይባሉ ነበር (1290 ዓ. ም.)።

440. **ትቅደም**
ወደፊት ትኺድ፣ ትራመድ፣ መጀመሪያ
ትኹን። ያባት ስም አገሬ ቢል ይገጥማል።

441. **ትበርህ** (ትግ)
ትብራ ፤ ትበራ ዘንድ ።
ያባት ስም ጸጋው ቢል ይገጥማል።

442. **ትበይን**
ፍርድ ትሰጥ፣ ትተች፣ ትለይ፣ ትወሰን...።
ያባት ስም ኅሊና ቢል ይገጥማል።

443. **ትቤ ጽዮን** (ግእ)
የደብ በግዕን ገዳም የመሠረቱ እባ ሕፃን
ሞዐ እናታቸው ትቤ ጽዮን ይባሉ ነበር።
ትርጕሙ ጽዮን አንዳለች ማለት ነው።

444. **ትብቃለ - ትብቃ**
ከዚህች ሌላ ተጨማሪ አያሻኝም አለ።
ያባት ስም ትዛዙ ቢል ይገጥማል።

445. **ትብዛለም** (ትብዛዓለም)
ደስታ ትብዛ፤ ዓለም ታየ ስማለት ...።
ያባት ስም ፍሥሓ ቢል ይገጥማል።

446. **ትብለጥ** (ትብለጽ)
ማወዳደርን ያመለክታል።
ያባት ስም ነጻነት ቢል ይገጥማል።
ትበልጪ- ትበልጪያለሽ

447. **ትንብብ** (ግእ) **ትነብብ**
ትናገር ማለት ማለት ነው ።

448. **ትኦር**
ትቆይ፣ ትሰንብት ...።
ያባት ስም ዘላለም ቢል ይገጥማል።

449. **ትንሣኤ**
ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣበት ዕለተ
አሑድ (ከሞት መነሣት) ማለት ነው።
ያባት ስም ታዬ ቢል ይገጥማል።
ትንሣኤ ክርስቶስ ክርስትና ስም ተመልከች።

450. **ትንቢተ - ትንቢት**
በነቢይ የተባለው ኹሉ ይፈጸም ዘንድ
ይህ ኹሉ ኾነ ። የሚመጣውን የሚገልጽ
(ማቴ. 1፥21፤ ዕብ. 1፥1፤ 1ጴጥ. 1፥10)።
ያባት ስም ሚልኪያስ ቢል ይገጥማል።

451. **ትንቢለል**
አንዳቫት ትኹን ፣ ትዝናና ...።
ያባት ስም ከተማ ቢል ይገጥማል ።

452. **ትንታጓ**
ሽንፈት የማይታይባት ። እንደ ልቧ በሠ
ፊው ትኦር፣ ትዝናና ማለት ነው።
ያባት ስም በለጠ ቢል ይገጥማል።

453. **ትንግርቷ - ትንግርቱነሽ**
የተነገረልሽ ፣ የተተነበየልሽ ነሽ ማለት
ነው። ወደፊት የሚጠበቅ ...።
ያባት ስም አልታዬ ቢል ይገጥማል።

454. **ትከበር**
ከፍተኛነትን ፤ በጎጽሕናዋ ክብር ታግኝ
(ሮሜ. 13፥7)።
ያባት ስም ቀምነገር ቢል ይገጥማል።

455. **ትኩን** (ግእ) ትኹን ማለት ነው።

456. **ትካቦ** (ትግ)
እንደ ምጽዋት የተሰጠች ልጅ ማለት ነው

457. **ትካብ**
ከዐበ ከሚለው ግስ ካበ፣ ደረደረ ፣ አነባ
በረ ማለት ነው። **ትካቤ**
ያባት ስም በሐርወርቅ ቢል ይገጥማል።

458. **ትክለነሽ**
አንድ ቦታ የተወሰንሽ፤ የጠበቀች ።
ያባት ስም መታሰቢያ ቢል ይገጥማል።
ትክሌ - ትክልወርቅ

459. **ትክክሏ**
ያልተዛባች ፤ ያልተጓደለች፤ መሳይ።
ያባት ስም ደሞዜ ቢል ይገጥማል
ትክክልነሽ - ትክክል

460. **ትኹንዘር – ትኹንሽ**
ትበርክት ፣ ተሰፋ ትኹን።
ያባት ስም መርጊያ ቢል ይገጥማል።
ትኹኔ - ትኹን

461. **ትውሰታ**
ያለፈን ማሰታወሻነትን ያመለክታል።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

462. **ትዕግሥት** (ግእ) (ትግሥት)
በመከራ መጽናት ፤ ተሰፋ ማድረግ። ትዕ
ግሥት የመንፈስ ፍሬ ነው ፤ እግዚአብ
ሔር ለሰዎች ብዙ ትዕግሥት አሳይቷል
(ሮሜ. 2፥4 ፤ 15፥5 ፤ 1ኛ ጴጥ. 3፥20 ፤
ገላ. 5፥22)። **ትዕግሥቲ** (ትግ)
ትዕግሥቴ - ትዕግሥትዓለም

463. **ትዕግር**
የዘንባባ ቅጠል ማለት ነው።
ዅለት ሰዎች በዚህ ተጠርተዋል ። የን ጉሡ የዳዊት ልጅ ተጠርታበታለች (ዘፍ. 38፥6- ፤ 2ኛ ሳሙ. 13፥1-)። ከ12ቱ የያዕ ቆብ ልጆች አንዱ የሁዳ ከትዕግር ዛራን እና ፋሬስን ወልዷል ። በዚህ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ ወስጥ ከተቆጠሩት አንዷ ሴት ነች።

464. **ትዛዟ**
አድርጊ ፣ አታድርጊ የሚል ።
ትዛዛት ለአዳም ፣ ለኖኅ ፣ ለአብርሃም ለሙሴ ፣ እንዲሁም ለሐዋርያት ተሰጥተ ዋል (ዘፍ. 2፥16፤ ዘጸ.3፥15፤ ማቴ. 28፥19)።
ትዘዘው - ትዛዝ - ትዛዛቸው

465. **ትዝታ**
ትውስታ ፤ ያለፈን ነገር ማስታወስ።
ያባት ስም አስቻለው ቢል ይገጥማል።
ትዝታነሽ - ትዝታወርቅ - ትዝታቸው

466. **ትደነቂያለሽ**
መወደስን፣ መገረምን አስገራሚ መኾንን ያመለክታል ።
ያባት ስም አልባሴ ቢል ይገጥማል።
ትደነቁ - ትደነቅ - ትደንቅ

467. **ትደግ - ትደግልኝ**
በዕድሜ፣ በሥጋ ግዝፈት፣ በቁመት፣ በዕውቀት፣ በጥበብ።
ያባት ስም ተስፋዬ ቢል ይገጥማል።

468. **ትግዛ**
ትቆጣጠር፣ ሀብቷ ታድርግ ...።
ያባት ስም አንዳርጋቸው ቢል ይገጥማል
ትትግዛት - ትግዛው - ግዛቸው

469. **ትዓደድ**
ዞር ዞር ፣ ጎደድ ጎደድ ትበል ...።
እንደ ልቧ ትኹንበት።
ያባት ስም ነጻነት ቢል ይገጥማል።

470. **ትፍሥሕት** (ግእ)
ተድላ ደስታ፤ ዕረፍት ማለት ነው።
ያባት ስም ሞላ ቢል ይገጥማል።

- ቸ -

471. **ቸርነቷ – ቸርዬ**
ለጦታዋ፣ ካለ ማካፈልን ያመለክታል።
ያባት ስም አያልቅበት ቢል ይገጥማል።

472. **ቸኰለች**
ቶሎ አለች ፤ ፈጠነች ።
ያባት ስም ፍቅሬ ቢል ይገጥማል።

- ኀ -

473. **ኀረያ** (ግእ)
መረጣት ማለት ነው ።
አስመ ኀረያ እግዚአብሔር ለጽዮን።
ትርጉም፤ እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና። (መዝ. 131(132)፥13
እግዚእ ኀረያ ክርስትና ስም።

474. **ኂሩት** (ግእ)ኂሩተ - ኄር
ቸርነት፣ ደግነት፣ በጎነት ማለት ነው።
(መዝ. 118፥68 ፤ ምሳ. 11፤ ሚሬ. 42፥14)
ወበኂሩትከ ምህረኒ ኵነኔከ። ትርጉም፤ በቸርነትህ ሥርዓትን አስተምረኝ።
ኂሩተ ሥላሴ ክርስትና ስም።

475. **ኄራን** (ግእ)
ኄረ ቸር፣ ሊጋስ ከሚለው የመጣ ነው።
አስመ ውእቱ ያሠርቅ ፀሓየ ላዕለ ኄራን ወእኩያን። ትርጉም ፤ አርሱ ለደጎችም ለክፉዎችም ፀሐይን ያወጣል (ሚቴ. 5፥45)።

476. **ኅለተ ወርቅ** (ግእ)
የወርቅ ዘንግ ልምጭ ማለት ነው።

477. **ኅሉፍ** (ትግ) **ኅልፍቲ**
ያለፈች ማለት ነው።

478. **ኅሊና** (ግእ) **ኅሊናዬ**
ከፉና ደግን የሚለይ መመዘኛ፤ ሐሳብ ምኞት ማለት ነው (ሲራ. 38፥26 ፤ ምሳ. 6፥18፤ ይሁ. 10 ፤ ሮሜ. 2፥14 ፤ 15)።
ያባት ስም ፈቃዱ ቢል ይገጥማል።

479. **ኅሪት** (ግእ) (ኅሩይ ለወንድ)
የተመረጠች (ለሹመት) ማለት ነው።
ወይእቲ እብን አንተ በጎበ ሰብእ ምንጎት ወበጎበ እግዚአብሔርሰ ኅሪት ወክብርት።
ትርጉም፤ ይህቺ ድንጋይ በሰው ዘንድ የተ ናቀች ናት በእግዚአብሔር ዘንድ ግን የከበ ረች የተመረጠች ናት (1ጴጥ. 2፥4)።
አምነ ቀሲስ ዲኅሪት። ትርጉም ፤ ከቄሱ ለተመረጠች (2ዮሐ. 1፥1)።

480. **ኅብረት - ኅብረወርቅ - ኅብር**
ዐበረ፣ ተባበረ፤ የተባበረ የተቀላቀለ።
ያባት ስም ታከለ ቢል ይገጥማል ።
ኅብረተወርቅ - ኅብሪቱ - ኅብሬ

481. **ኅብስት**
ከሰማይ የወረደ ኅብስት እኔ ነኝ።
(ዮሐ. 6፥59)።
ያባት ስም ወረደ ቢል ይገጥማል።
ኅብስተመና - ኅብስቴ

482. **ኅዳግ** (ግእ)
የመጽሐፍ ጠርዝ ግርጌ ማለት ነው።
ያባት ስም ለይኩን ቢል ይገጥማል።

483. **ኃያልነሽ** (ዐያልነሽ ተመልከት)
ያባት ስም ባስጊል ቢል ይገጥማል።

484. **ኀራኒ** (ግሪ)
የስጢ ትርጉም ሰላም ፍቅር ኾነ ማለት ነው ። በንጉሥ ሉክያኖስ ዘመን ሰማዕት የኾነች ቅድስት (ስን. ነሐ. 21 ገጽ 712)።

485. **ኖኅተ** (ግእ)
ደጅ ወይም በር ማለት ነው።
ርኢኩ ኖኅተ በምሥራቅ። ትርጉም ፤ በምሥራቅ በር አየሁ (ሕዝ. 44፥1)።
በክርስትና ስም ኖኅተ ብርሃን ቢል
ያባት ስም ምሥራቅ ፣ ሕዝቅኤል ቢል ይገጥማል።

486. **ኖየረች** (ጉራ)
ጥሩ ልጅ ማለት ነው።

- ነ -

487. **ነቃሕይወት - ነቅወንጌት**
የሕይወት ምንጭ ማለት ነው ።
ያባት ስም ፈለቀ ቢል ይገጥማል።

488. **ነቢይት**
ትንቢት የምትናገር (ሉቃ. 2፥36)።

489. **ነገደፀሓይ** (ግእ)
የፀሓይ፤ የወርቅ ወገን ማለት ነው።
ነገደወርቅ - ነገደ

490. **ንጹርት** (ግእ)
አየች ማለት ነው። **ነጸረአብ**
ያባት ስም ፍሬሰላም ቢል ይገጥማል።

491. **ነጸነት**
ነጻ መኾን ፣ ካገልጋይነት ፣ ከመጨቆን ነጻ መውጣት (ገላ. 5፥1)።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

492. **ኦሪልኝ**
ቁሚልኝ ፣ ቆይልኝ፣ ማለት ነው።

493. **ኦኦሽት**
የሙገሳ ስም ፤ ከዋና ስም ቀደም ብሎ የሚሰየም። **ኦንሽ - ኢኒ - ኒና - ናኦ**
ያባት ስም በቀለ ቢል ይገጥማል።
ኦኦ - ኦኦሼ - ኦኦሽ - ኦኦዬ

494. **ኒሻን (ሊሻን) – ኒሻነወርቅ**
በክብር፣ በሥራ ውጤት የሚሸለም።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

495. **ናርዶስ**
የናርዶስ ቅጠል ፤ ደስ የሚያሰኝ ሽቱ ናርዶስ ወሀበ መዐዛሁ ። የኔ ናርዶስ መዐዛውን ሰጠ (ማኅ. ዘሰሎ 1፥12 ፤ 3፥20 ፤ 4፥13) ። ናርዶስ ዘምስለ መጽርይ ቀጸመታት ወቀናንሞስ። ትርጉም ፤ ናርዶስና ከቀጋ ጋራ ሽቶ ሣርና ቀረፋ ማለት ነው።

496. **ናፍቆት**
ጽኑ ምኞት፤ የሚወዱትን በፍቅር ማሰብ። (2ኛ ቆሮ. 7፥7፥11፤ 1ኛ ተሰ. 2፥17፤ 3፥6)

497. **ንባበ – ነበበች - ነበቡ** (ግእ)
ነዘበ ከሚለው የወጣ፡ ተናገረች ፣ ተረጎመች ማለት ነው።

ከውርድ ንባብ በኋላ ተማሪ አየጮኸ በፍጥነት የሚናገረው የሚያነበው።
ያባት ስም ነቢያት ቢል ይገጥማል።

498. **ንብረቴ - ንብረት**
ሀብቴ፣ ገንዘቤ፣ ቅርሴ፣ ኀብት ...።
ቅርሰ ሊኾን ይችላል ።
ያባት ስም ታያቸው ቢል ይገጥማል።

499. **ንቢ - ንብወርቅ - ንብነሽ**
ተወዳጅ ማርን የምትሰጥ ነች ። በኃይለኝነት ትመሰላለች (መዝ. 117 (118)፥12)።
ንቦ ንቦ አትናደፊ ንቦ አትናደፊ እንዳለ ዘፋኝ ።

500. **ንዋይነሽ** (ንዋይነሽ) - **ንዋዬ**
ሀብት ሲመጣ የምትወለድ ልጅ ወይም ራሷ ሀበት ኾና በመምጣትዋ ንዋይነሽ ትባላለች።

501. **ንጋቷ - ንጋት - ንጋቴ**
ማለዳ ፣ ጠዋት ...።
ዝነኛዋ ባለቅኔ አቀንቃኝ ንጋቷ ከልካይ በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዷ ናቸው።

502. **ንግርቱነሽ**
ትንቢቱ ፣ ተሰፋው ፍጻሜ ያገኘሽ ...።
ያባት ስም ተሰፋዬ ቢል ይገጥማል።

503. **ንግሥት**
በቅዱስ መጽሐፍ የኢትዮጵያ ንግሥቶችን ያመለክታል፤ ማክዳ (1ኛ ነገ. 10፥1 ማቴ. 12፥ 42 ፤ ሉቃስ 11፥31) እንደሁም ሕንደኬን (ሐዋ. ሥራ 8፥27)።
ንግሥቴ- ንግሥቴ - ንግሥትሳባ -

504. **ንጥረወርቅ**
የነጠረች ንጹሕ ወርቅ እንዝን የሌለባት።

ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።
ንጹወርቅ - ነጠረወርቅ - ነጠረች

505. **ንጽሕተ - ንጽሕት**
የነጻች፣ የጸዳች ፤ ሰውነትን፣ ልብስን፣ ማጽዳት፤ ከረከሰ ነገር መንጻት። ንጹሕ መሥዋት ማቅረብ፤ ከኀጢአት መንጻት (ዘሌ.15፥8–11፤ መዝ.50፥7፤ ሕዝ. 36፥25)
ንጹሓን - ንጹሕ - ንጹሰው - ንጽሕና
ንጹፍሬ - ንጹሕብር (ንጹብር)

506. **ኖላዊት** (ግእ)
የበግ ፣ የሕዝብ ጠባቂ (ዮሐ.10)።
ያባት ስም ቹሩ ቢል ይገጥማል።

507. **ኖኃሚን (ዕብ.)**
ደስታዬ ማለት ነው ፤
የቤተልሔም ተወላጅ የነበረች በሞአብ የኖረች የሩትና የእርፋ አማት ነበረች (መጽ. ሩት 1፥20)።

- አ -

508. **አሁጂ** (ጉራ)
አግዚአብሔር ይመልከትሽ ማለት ነው።

509. **አለሙሽ**
በሕልም ፣ በራእይ።
ያባት ስም ፍቅሬ ቢል ይገጥማል።

510. **አለማኹ**
አለመለምኳት፣ አበጀኋት፣ አሳመርኳት፤ አንድታድግ ተንከባከብኩ ...።
ያባት ስም መቁያ ቢል ይገጥማል።
አለማች - አለማሽ - አለማት

511. **አለችኝ**
ወርቅ፣ በልግዝ፣ አንቁ ...።
ያባት ስም የማታወርቅ ቢል ይገጥማል።

512. **አለኝታ**
የወደፊት ተስፋን ያመለክታል።
ያባት ስም መከተ ቢል ይገጥማል።

513. **አለፈች - አለፉ**
ኼደች ...።
ያባት ስም ታሪኩ ቢል ይገጥማል።

514. **አሉሽ**
ውብ፣ ባለሟያ ...።
ያባት ስም ማሰረሻ ቢል ይገጥማል።

515. **አላዩ**
አልተመለከቱም ...።
ያባት ስም ዕንቁባሕርይ ቢል ይገጥማል።
አላዩሽ - አላይ - አላየንሽ

516. **አላውጋ**
አልናገር ዝም ልበል ...።
ያባት ስም ዝና ቢል ይገጥማል።

517. **አልማዝ**
ከማዕድናት ኹሉ ዋጋው የከበረ ጠንካራ ዕንቁ ድንጋይ (ዘጸ.28፥18፤ ሕዝ.3፥9፤ ዘካ .7፥12)። **አልማዙ - አልማዜ**
አልማዝወርቅ

518. **አልባሰወርቅ** (ግእ)
የወርቅ ልበስ ማለት ነው።
በአልባሰ ወርቅ ውጽፍት ወሕብርት። ትርጉም ፤ በወርቅ ልብስ ተጎናጽፋና ተሸፋፍና (መዝ. 44፥9)

519. **አልታየች**
ማንም ያያት የለም ...።
ያባት ስም ያለምሽት ቢል ይገጥማል።
አልታየወርቅ - አልታየ
አልታሸወርቅ - አልታዩ

520. **አልጣሽ**
በዚህ ስም **የዐፄ ቴዎድሮስ** ልጅ **የዐፄ ምኒልክ** የመጀመሪያ ባለቤት **አልጣሽ** ይባሉ ነበር።

521. **አመቴ - አመተ**
ልጄ አገልጋዬ ማለት ነው ።
በክርስትና አመተ ማርያም ቢል ይኾናል።

522. **አመነች**
መጠራጠርን አስወገደች ።
ያባት ስም በላቸው ቢል ይገጥማል።

523. **አመዘነች – አመዘነ**
ወደ አንደኛው ወገን አደላች።
ያባት ስም በትዛዙ ቢል ይገጥማል።

524. **አማለደች**
ተጣልተው የነበሩትን አስታረቀች ፤ አስማማች ማለት ነው ።
የጐደለውን ሞልታ ፤ ከአዳ፣ ከመከራ፣ ከጣጣ፣ አዳነችኝ።
ያባት ስም ታረቀኝ ቢል ይገጥማል።

525. **አማረች - አማርን - አማሩ**
ውብ መልክ መልካም ኾነች ።
ያባት ስም ውብሸት ቢል ይገጥማል።

526. **አማን** (ግእ)
እውነት ማለት ነው ።
አማን አማን አብለክ ! ከመ ዘነአምር ንኑ ግር። ትርጉም ፤ እውነት እውነት አልህ ለሁ የምናውቀውን እንድንናገር (ዮሐ. 3፤11)።
አማኒቱ - አማኔ - አማንነሽ

527. **አማከለች**
ከአባቷ እና ከእናቷ መልክን በትክክል ወሰደች። ወይም ኹለተኛ ልጅ መከከል የገባች ማለት ነው ።

528. **አምለሱ**
የራስ ዐሉላ አንግዳ ቁቢ ኹለተኛ ባለቤት **አምለሱ አርአያ** ይባሉ ነበር።

529. **አምሮቴ - አምሮት**
ጓጕቼ አንቺን አገኘኹ ማለት ነው።
ውልታዬ፣ ፈቃዴ፣ (ኤር. 12፤10)።
ያባት ስም ይብቃል ቢል ይገጥማል።

530. **አምሳል** (ግእ) **አምሳያ**
በምሳሌ፣ በታሪክ፣ በተረት፣ ውስጠ ወይራ ንግግር ። **አምሳለወርቅ**
አምሳለ ወርቅ ይገበሩ ለኪ ኩሰኩሰ ዘብ ሩር። ትርጕም፤ ባለ ብር ጉብጉብ የኾነ **የወርቅ ጠልሰም** እና ደርግልሻለን (መሐ. ዘሰ. 1፤11)። **አምሳለ - አምሳለች**
አምሳሉ - አምሳልነሽ - አምሳሏ

531. **አምባነሽ**
ከፍታ ቦታ በርቀት የሚታይ (ጊሸን አምባ)
ያባት ስም አሸቴ ቢል ይገጥማል።
አምባወርቅ - አምባሸት

532. **አሞኘኹሽ**
አታለልኩሽ ...።
ያባት ስም ፍቅሬ ቢል ይገጥማል።
አሞኜሼ - አሞኘኝ

533. **አሠጋሽኝ - አሠጊ - አሠጋሽ**
አሳሰብሽኝ ...።
ያባት ስም ባይከዳኝ ቢል ይገጥማል።

534. **አረገደች**
አሰጨፈረች ...። **አረገዱ - አረጉ**
ያባት ስም ተዋነይ ቢል ይገጥማል።

535. **አረጋሽ - አረግሽወርቅ**
መረጋጋት፣ የልብ መርጋትን ያመለክታል
ያባት ስም በሐርወርቅ ቢል ይገጥማል።

536. **አርሴማ** (ግሪ)
በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን ከደናግላን ገዳም አስወጥቶ ጋብቻ ቢሻት አንቢ በማለቷ፤ በአምነቷ ሰለጸናች በሰይፍ አንድትሰየፍ የተደረገች ። ሰማዕትና ቅድስት ነች (ስንክ. መስከ. 29)።

537. **አሰለፈች**
ከበሰተኋላዋ በተራ አስከተለች ፤ ሥርዓትን አስያዘች።
ያባት ስም ሚሊዮን ቢል ይገጥማል።
አሰለፉ - አሰለፍ - አሰለፌ

538. **አሰማሸ - አሰማች**
ድምጽን ፣ የምሥራችን ፣
ያባት ስም ብሥራት ቢል ይገጥማል።
አሰማሸው - አሰሜ - አሰም

539. **አሰገደች**
ታዘዙላት ፣ አክበሯት፣ እጅመንሻ አቀረቡላት ።
ያባት ስም በጎይሉ ቢል ይገጥማል።
አሰገዱ - አስገድሻቸው

540. **አሰፋሽ**
ቦታን ፣ ግዛትን ፣ ዝምድናን።
ያባት ስም ጎብረት ቢል ይገጥማል።
አሰፉ - አሰፍዬ

541. **አሳመነች**
አሰረዳች፣ አወን አሰኘች፤ ስሕተትን፤ እውነትን እንዲቀበሉ አደረገች ።
ያባት ስም መርዓዊ ቢል ይገጥማል።
አሳመነሽ - አሳመነችው - አሳምና

542. **አሳበች**
አገናኘች፣ አያያዘች፣ አመጣች ማለት ነው።

543. **አሳየች - አሳየሽው - አሳዩ**
በርቀት ያለውን ፤ አስተዋወቀች።
ያባት ስም ሲሳይ ቢል ይገጥማል።

544. **አስማረች**
ይቅር አሰባለች ፤ አማለደች።
ያባት ስም በጸሎቱ ቢል ይገጥማል።
አስማሩ - አስምሪ - አስመረት
አስማረወርቅ - አስምራት

545. **አስናት** (ግብ)
የኔ ሀብት ወይም በአባቷ ወገን የኾነች ማለት ነው ። በቅዱስ መጽሐፍ ዮሴፍ የፈርኦኑን ሕልም ከተረጐመ በኋላ የአጥፈራ ልጅ አስናት ተሰጠችው ። ከሷም ምናሴንና ኤፍሬምን ወለደ (ዘፍ.41)።

546. **አስረሳሽ**
ያለፈን ነገር አንዳይታወስ አደረግሽ።
ያባት ስም ያይኔንብርሃን ቢል ይገጥማል።
አስረሳሽኝ - አስረሳች - አስረስሽ

547. **አሰራደች**
ርዕደ ከሚለው ግስ የወጣ ነው ። ተንቀጠቀጠ ፈራ ። አሰራደች አንቀጠቀጠች አሰፈራች ። ግርማ ያላት ማለት ነው።
ያባት ስም ይርጋመሰን ቢል ይገጥማል።

548. **አስተካከለኝ – አስተካከለሽ**
አኩል አረገኝ ። **አስተካከለችኝ**
ያባት ስም የሺጥላ ቢል ይገጥማል።

549. **አስታረቀችኝ**
በጠብ መካከል ሰላም አወረደች። የሚያስታርቁም ብፁዐን ተብለዋል (ማቴ. 5፥9፤ ፊል. 4፥2)።

550. **አስታወሰችኝ – አስታወሳት**
የተዘነጋውን ፣ የተረሳውን።
ያባት ስም ወሮታው ቢል ይገጥማል።

551. **አስቴር**
በፋርስ ቋንቋ ክዋክብ ማለት ነው ። ቆንጆ ነበረች ወላጆቿ በልጅነቷ ዐርፈውባት የአጎቷ ልጅ አሳደጋት ። የመጀመሪያ ስሟ ሐደሳ ይባል ነበር (መጽ. አስ. 2፥7)።

552. **አስቻለች**
አስታገሠች ፤
ያባት ስም አንዳይከፋኝ ቢል ይገጥማል።
አስቻሉ - አስቻሌ- አስችላ

553. **አስናቀች – አስናቁ**
የበለጠ ኾነች። የሚተካከላት የለም።
ያባት ስም ለዓለም ቢል ይገጥማል።

554. **አስካል** (ግእ) **አስካለ - አስካሉ**
የወይን ፍሬ ዘለላ ማለት ነው። ደመ አስካል እንደ ማሽላ ራስ ያለው ።
(ዘፍ. 40፥10 ፤ ኢሳ. 5፥2) **አስካለ ወይን** የወይን ዘለላ ማለት ነው።
አስካለ ማርያም ከርስትና ስም።

555. **አስደሳች**
የምታምር ፤ የምትማርክ ።
ያባት ስም ፍሬገነት ቢል ይገጥማል።

556. **አስደነቀች – አስደነቅ**
በችሎታዋ ፣ ተአምር በማድረጓ።
ያባት ስም ዓለም ቢል ይገጥማል።

557. **አስጋረደች** አስጋረዱ -አስጋርጂው
ከመከራ፣ ከፈተና፤ አንዳይታይ አረገች።
ያባት ስም ሕይወት ቢል ይገጥማል።

558. **አሸነፈች**
ረታች ፤ ታግላ ፣ ተከራክራ ...።
ያባት ስም ኅብረት ቢል ይገጥማል።

559. **አሻገረች - አሻጋሪነሽ -አሻግሪው**
አሳለፈች ፤ መከራውን፣ ፈተናውን ...።
ያባት ስም ባሕሩ ቢል ይገጥማል።

560. **አቅሌስያ** (ግሪ) (አቅሌሳ)
የጸድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እናት አቅሌስያ ይባላሉ። ቤተ ክርስቲያን ስላሳደገቻቸው እናቴ አቅሌስያ ናት ፤ አባቴ ስምዖን (ጴጥሮስ) ነው አሉ። ገድላቸው።

561. **አበረደች**
የሚያታግለውን ፤ በኃይል የመጣውን አቀዘቀዘች።
ያባት ስም ተመስገን ቢል ይገጥማል።

562. **አበራሽ**
ጨለማን አራቅሽ፣ አሳየሽ ...።
ያባት ስም ክብሩ ቢል ይገጥማል።
አበሩ - አበራች - አበር - አበርዬ

563. **አበበች**
በዚህ ስም በኢትዮጵያ ውስጥ አጓለማውታን በማቋቋም የዕርዳታ ድርጅት የመሠረቱ ወይዘሮ አበበች ጎበና በመባል ይታወቃሉ። **አበብዬ - አበቤ - አበብ**
አበባነሽ - አበባሽ - አበቡ - አበባ
አበባወርቅ - አበባየኹ - አበባዬ
አበባዬነሽ - አበባይ - አበባይቱ

564. **አበዛሽ**
ብዙ አደረግሽ ...።
ያባት ስም ተድላ ቢል ይገጥማል።
አበዜ - አበዝ - አበዙ

565. **አበጀሽ - አበጁ**
ደግ አደረግሽ ፤ ጕስቁልናዬ ሠራሽ ...።
ያባት ስም ጉልላት ቢል ይገጥማል።

566. **አብሠራ** (ግእ)
እንደ አበሠራት፤ የምሥራች አላት፤
ያባት ስም መላኩ ቢል ይገጥማል።

567. **አቦነሽ - አቦወርቅ - አቦዬነሽ**
የአቡየ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ነሽ ፤
ወይም አባት ነሽ ...።
ያባት ስም ተክሰ ቢል ይገጥማል።

568. **አቦገረድ** (ጉራ)
በጣም ጎበዝ ማለት ነው።

569. **አቢጋኤል**
ትርጕሙ አባት ደስ አለው ማለት ነው። የንጉሥ ዳዊት ታናሽ እኅት ። እንዲሁም ሌላዋ ሚስቱ የነበረች ነች።
(1ኛሳሙ. 16፥10 ፤ 1ኛሳሙ. 25፥24)።

570. **አብረኸት** (ትግ.)
አበራች ማለት ነው።

571. **አተረፈች - አተረፉ**
ከዋናዋ ሌላ አገኘች ማለት ነው።
ያባት ስም በላቸው ቢል ይገጥማል።

572. **አታክልት**
ያባት ስም በቀለ ቢል ይገጥማል።
አታክልቴ - አታክልቲ (ትግ)
አታክልትይ

573. **አትናስያ** (ግሪ)
ከቁስጥንጥንያ ቤተ መንግሥት ልጅ የእግዚአብሔር አገልጋይ ቅድስት አትናስያ ትባል ነበር። የመታሰቢያ ቀኗ የሚከበርላት መስከረም 10 ነው (ስን. ገጽ51 ቁ.24 ፤ ጥር 26 ገጽ684 ቁ. 26)።

574. **አትጠገብ**
በዚህ ስም የሚታወቁት የዐፄ ቴዎድሮስ እናት እሜይቴ አትጠገብ ወንድወሰን ይባሉ ነበር።

575. **አትደፈር**
ማንም የማይነካት ፣ የማይጠጋት።
ያባት ስም ክብሩ ቢል ይገጥማል።

576. **አቻምየለሽ - አቻሚ**
የሚተካከልሽ የለም ማለት ነው።
ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከወይዘሮ ማረፊያ የወለዷቸው አቻምየለሽ ይባሉ ነበር ።

577. **አነስተስያ** (ግሪ)
ትንሣኤ ማለት ነው፤

ቤ

በትንሣኤ ጊዜ የሚወለዱ ይህ ስም ይሰየ
ምላቸው ነበር ። በመጀመሪያው በሰማዕ
ታት ዘመን በጣም ይታወቅ ነው።

578. **አንቀጸ** (ግእ)
መውጫ ማለት ነው።
ያባት ስም ብርሃን ቢል ይገጥማል።
አንቀጸሰላም - አንቀጸአድኅኖ
አንቀጸ ብርሃን

579. **አንቺነሽ**
ተስፋ፣ አለኝታ። በሆድ አንቺ ነበርሽ?
ያባት ስም ሰይፉ ቢል ይገጥማል።
አንቻለም - አንቺዬ - አንችናየሁ
አንቺአናኔ - አንቺኹኝ

580. **አንዳርጊያቸው**
አስማሚያቸው፣ አስታርቂያቸው ...።
ያባት ስም ይርጉ ቢል ይገጥማል።

581. **አንቺናሉ (አንቺነአሉ)**
አንቺን ፈለጉ ...።
ያባት ስም ደሳለኝ ቢል ይገጥማል።

582. **አንቺንሰጠኝ**
ልዩ ውብ ሰጠኝ ጌታ ...።
ያባት ስም ታሪክ ቢል ይገጥማል።

583. **አንጓችነሽ – አንጓች**
ወዳጄነሽ ለማለት ። አንጎቻ የምታነጉቺ ...።
ያባት ስም ጥጋቤ ቢል ይገጥማል።

584. **አካሌ**
የኔ አካል ማለት ነው።
ያባት ስም ብርሃን ቢል ይገጥማል።
አካልነሽ - አካል - አካለ
አካለ ሥላሴ ከርስትና ስምን ተመልከቱ።

585. **አክሊለ**
ዘውድ የራስ ጌጥ ሽልማት፤ የክብር ምል
ክትና ትልቅ ማዕረግ ያላቸው ሰዎች የሚ
ቀዳጁት። (2ጦሞ. 4፥8 ፤ ራእ. 2፥10 ፤
ማር. 15፥17 ፤ ሰቆ. 5፥16)።
ያባት ስም ጽጌ ቢል ይገጥማል።
አክሊለወርቅ - አክሊል - አክሊሏ
አክሊልሰጠኝ
አክሊለ ጊዮርጊስ ክርስትና ስም ተመልከች።

586. **አወጣሽ - አወጡ**
ከችግር ፣ ከመከራ ፤ አሻገርሽ ።
ያባት ስም **መልአኩ** ቢል ይገጥማል።

587. **አዋየኹሽ**
ያባት ስም ተሰፋ ቢል ይገጥማል።

588. **አዘነጋሽ – አዘነጋች**
ዘንግፀ ከሚለው ይመጣል፤ አሰረሳሽ ...።
ያባት ስም ተድላ ቢል ይገጥማል።

589. **አዛለች - አዛሉ**
አደከመች ፣
ያባት ስም ዘማቹ ቢል ይገጥማል።

590. **አዜብ**
የደቡብ ምዕራብ ያለ አቅጣጫ ፤ ንገ
ሥት ሳባ (ማከዳ) የነገሠችበት ያገር ስም
ስመ መንግሠቷ ነው።
(ማቴ. 12፥42 ፤ ዘፍ. 12፥9 ፤ 13፥1)።

591. **አዝመራዬ**
አርሻዬ፣ አጨዳዬ፣ ቁፋሮዬ ፣ የመከር
ፍሬዬ ...። ወንጌልም አዝመራ ነው።
ያባት ስም በዛብህ ቢል ይገጥማል።
አዝመራይቱ - አዝመራ - አዝመረት

592. **አዝማች - አዝማችነሽ**
ፊት መሪ ፣ ፊታውራሪ ነሽ።
ያባት ስም አሰባለው ቢል ይገጥማል።

593. **አዝፋረወርቅ** (ግእ)
የወርቅ መጉናጸፊያ ማለት ነው።
(መዝ. 44(45) ፥ 13)

594. **አየኹ**
ተመለከትኩ ፣ አረጋገጥኩ ...።
ያባት ስም ጸጋ ቢል ይገጥማል።
አየኹብርሃን - አየኹሽ - አየኹብዙ
አየኹዓለም - አየኹጸጋ - አየኹልሽ
አይቼሽ - አየልዩ - አየሽ - አየኋት

595. **አየናቸው - አየናት**
ተመለከትናቸው ...።
ያባት ስም ተዋሕዶ ቢል ይገጥማል።

596. **አያኽሉሽም**
አይተካከሉሽም በውበት በቁንጅና ...።
ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከወይዘሮ ማለፊያ
ከወለዷቸው ልጆች አንዷ ልዕልት አያ
ህሉሽም ይባሉ ነበር ።
አያኽሉሺ - አያከሉሽ - አይችሉሽም

597. **አያልነሽ**
ኃያልነሽ ቢል ግእዝ ነው። ጎይልን ያመ
ለክታል ።
ያባት ስም መድኅኔት ቢል ይገጥማል።

598. **አያንቱ** (አሮ)
በድኋ ፣ ዕድለኛ ማለት ነው።

599. **አይድዐ** (ግእ)
አስተማረች፣ አመለከተች፣ ተናገረች አሳ
ወቀች ማለት ነው።

ወለነ አየድዕ ግብርየ ለንጉሥ።
ትርጉም ፤ እኔ ሥራዬን ለንጉሥ እናገራ
ለሁ (መዝ. 44 ፤ ምሳ. 8፥6 ፤ አስቴ. 2፥2
0)። ዓይድአ ተመልከች።

600. **አደላሽ**
ወደ አንድ ወገን ኾንሽ።
ያባት ስም በጎይሉ ቢል ይገጥማል።

601. **አደመች** (ግእ)
አማረች ቆነጀች ማለት ነው።
ያባት ስም ፍቅሬ ቢል ይገጥማል።

602. **አደራዬ**
አደራ በሰማይ አደራ በምድር እንደሚባ
ለው ...። አለብኝ አደራ ...።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።

603. **አደነቁ – አደነቅሽ - አደነቀች**
ደምግባቷን ፣ ውበቷን አይተው ...።
ያባት ስም ደሳለኝ ቢል ይገጥማል።

604. **አደይ – አደይ አበባ**
በመስከረም የሚወጣ የመጸው አበባ
ቀለሙ ቢጫ የኾነ ደስ የምትል ማለት
ነው።

605. **አዱኛሽ** (አሮ. ግእ)
አደነ ከሚለው የወጣ ነው።
ሀብትሽ ማለት ነው።
ያባት ስም በዛ ቢል ይገጥማል።

606. **አዳምነሽ**
የሰው ዘር ለማለት የሚሰየም ነው።
ያባት ስም ዘሩ ቢል ይገጥማል።
አዳምወርቅ - አዳሟ

607. **አዳነችኝ**
ከህልፈት ፣ ከመጥፎ ነገር ሰወረች ...።
ያባት ስም በአምላኩ ቢል ይገጥማል።
አዳነች - አድኒ - አዳኜ - አድሳነ

608. **አድማሰወርቅ – አድማስ**
አጥናፈ ወርቅ ማለት ነው።
ሰማይና ምድር የተገናኘ የሚመስልበት ቦታ ወይም የምሥራቅ ጮራ በትሬነጥት የሚታየው ወጋገን ማለት ነው።

609. **አጂየት** (ጉራ)
አመቤት ማለት ነው።

610. **አገሬ - አገርነሽ**
የትውልድ ቦታ፤ አርስት ።
ያባት ስም አማረ ቢል ይገጥማል።
አገርዓለም - አገር - አገሬነሽ

611. **አገኘኹሽ – አገኘኹ**
ሴት ልጅ ወለድኩ ማለት ነው።
ያባት ስም ፍቅሬለም ቢል ይገጥማል።

612. **አጊኔ** (ዶር) ደመቀች ማለት ነው።

613. **አጋረደች**
ከመከራ ከችግር ከለለች ሰወረች ማለት ነው።

614. **አጎዜ** (ዶር) ገንፎ ማለት ነው።

615. **አጓጓሽ – አጓጓኝ**
የደስ ደስ ያለሽ ...።
ያባት ስም ውብእሸት ቢል ይገጥማል።

616. **አጥሊ – አጥሌ**
መከራን አሳልፊ፣ ጋርጂ ፤ ጥላሸን፣ ድባ ብሸን አጥሊባቸው ...።
ያባት ስም የራሰወርቅ ቢል ይገጥማል።

617. **አጥናፍ (አጽናፍ ግእ)**
ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ፍጻሜ የሌለው ማለት ነው፤ ለግዛትም ይኾናል።
አጥናፏ (አጽናፉዋ) - አጥናፈዓለም አጥናፈወርቅ

618. **አፀደ - አፀዱ** (ግእ)
የአትክልት የመዝናኛ ቦታ ዓሮ ፤
አጨደ ማለት ነው።

619. **ኢትዮጵያ**
ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ሐበ እግዚ አብሔር፤ ትርጉም፤ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ተዘረጋለች (መዝ. 67 (68)፥31)። በሴት አንቀጽ መጠራቷ ፍት ርን ያመለክታል።

620. **ኢየሩሳሌም**
ቅድስት አገር ...።
ያባት ስም ገዳሙ ቢል ይገጥማል።

621. **ኤልሳቤጥ (ዕብ) – ኤልሳ**
በቅዱስ መጽሐፍ በመጀመሪያ የካህኑ የአ ሮን ሚስት (ዘጸ. 6፥23) ፤ በአዲስ ኪዳን የካህኑ የዘካርያስ ሚስት እና የዮሐንስን መጥመቁ እናት ። ፀንሳ ሳለች ቅድስት ድንግል ማርያም በጎበኘቻት ጊዜ ፅንሱ በማሕፀኗ ዘለለ (ሉቃ. 1፥39)። በዚህ ስም ዝዙ ኢትዮጵያውያን ይጠሩበታል።

622. **ኤደና** (ዕብ)
ደስታ ማለት ነው። የአቡነ አረጋዊ እናት በዚህ ስም ይታወቃሉ ።

623. **ኤዶም** (ዕብ)
ቀይ ማለት ነው ።
ኤሳው የተሰየመበት ስም ነው ። እንዲሁ የአገር ስም ነው (ማር. 3፥8) በዚህ ስም ወንዶችም ሴቶችም ይጠሩበታል።

624. **ኤፍራታ** (ዕብ)
ፍሬያማ ቦታ ማለት ነው።
ራሔል የተቀበረችበት ቦታ። በኋላ ዘመን የዳዊት ከተማ የኾነችው ጌታ የተወለደ ባት ቦታ ቤተልሔም ነች። ናሁ ሰማዕናሁ በኤፍራታ ። ትርጉም፤ እነሆ በኤፍራታ ሰማነው (መዝ. 131(132)፥6)።

625. **ኤሌኒ** (ግሪ)
የምታበራዋ ብርሃን ማለት ነው ።
የንጉሥ ቆስጠንጢኖስ እናት ፤ ኢየሩሳ ሌም ኼዳ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል አስቆፍራ ያስወጣች ፤ አብያተ ክርስቲያንን ያሳነጸች ነች። በኢትዮጵያው ያን ዘንድ የተለመደ ስም ነው። **የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ** (ቆስጠንጢኖስ) ሦስተኛና የመጨረሻ ባለቤት **እሌኒ** ይባላሉ።
ገጽ 127 : 57 ይመልከቱ

626. **አልፍነሽ** (ግእ)
ብዙነሽ ለማለት ነው (ዐሥር ሺህ)።
በዚህ ስም በማራቶን ሩጫ ወርቅ በማስ ገኘት አገሯን ያስጠራች ኢትዮጵያዊት **አልፍነሽ** ዓለሙ ነች። **አልፍያምጡ አልፍዓለም - አልፈ - አልፍኝ አልፍአደግ - አልፍዋጋሽ - አልፏ**

627. **አመቤት**
ባለቤት፣ የተከበረች የደስ ደስ ያላት።
በቤተሰብ መካከል አስተዳዳሪ፣
ጎላፊና ተወዳጅ የኾነች ማለት ነው።
(2ኛ ዮሐ. 1፥2)። **አሙቼ - አማዬነሽ አመቡ - አሙሰላም - አመናት**

628. **አማዋይሽ**
የምነግርሽ አለኝ ማለት ነው ።
ያባት ስም ዘገየ ቢል ይገጥማል።

629. **አምሯ**
አሻራዋ፣ ምልክቷ፣ ቁንጮዋ፣ ጫፏ ፣
አሻራዋ፣ ዓይኗ ... ማለት ነው።

630. **አምቅድመዓለም** (ግእ)
ከዓለም በፊት።
ያባት ስም ታምሩ ቢል ይገጥማል።

631. **አምዩ**
እናት ነሽ ለማለት በእናትነት ቦታ የሚ ሰጥ ስም ነው።
አምየነሽ - አምዬ - አመይቱ- አማዩ

632. **አምነት – አምነቴ**
በአምላክ ወይም በሰው ፍጹም ተስፋ ማድረግ። ሰው በአምነት ሲኖር በእግዚአ ብሔር ቃል ይመራል። በተሰፋ ይኖራል (ሮሜ. 4፥16 – 22 ፤ ዕብ. 11)።
ያባት ስም ይልቃል ቢል ይገጥማል።

633. **አምወድሽ** (ምወድሽ)
መውደድን ያመለክታል።
ያባት ስም ፍሬስላም ቢል ይገጥማል።

634. **አሰይነሽ – አሰዬ**
ልጅ አገኘሁ ደስታ ነሽ፤ ይኹንልኝ።
ያባት ስም ፍቅሬ ቢል ይገጥማል።

635. **አስከላለም - አስካለም**
አስከ መጨረሻው ...።
ያባት ስም ፍጹም ቢል ይገጥማል።

ሴ

636. **አስከዳር - አስካጥናፍ**
አስከ መጨረሻው ...።
ያባት ስም ያንተይኹን ቢል ይገጥማል።

637. **እሸት — እሸታየሁ**
የበሰለና የጎመራ የእህል ፍሬ። ተቀጥፎ የሚበላ (ዘዳ. 23፥25 ፤ ማቴ. 12፥1)።
እሸቷነሽ - እሸቴነሽ - እሸትዬ

638. **አጎት አለማሁ** (ግእዝ ነው)
የቤተሰብ፣ ወይም ለመ ተዘምዶ ነው።
አታፈራሁ (በማርኛ ነው)
አታበባ - አታበዛው - አታቸው
አታዋ - አታየዘሩ - አታየሁ
አታገኘሁ - አታገኝ - አታፈር
አታጉ - አቱነሽ - አታለም

639. **አቴማርነሽ** (አቴማር)
ስመ ተዘምዶ ነው። **አቴናት - አቴ**
አቴማንች - አቴሜቴ - አቴቱ
አቴአንቺ - አቴቴ - አቴነሽ

640. **አትኹኝ -**
ስመ ተዘምዶ ነው።
አትሞላሽ - አትሞላኝ - አጎትትኹን
አትይብዛ - አታበባ - አተወርቅ
አጎትነሽ (ግእዝ)

641. **አቴጌ** (ቴጌ)
የንጉሥ ሚስት ፤ የንጉሥ እናት ማለት ነው ። (1ኛ ነገ. 2፥19 ፤ 15፥13 ፤ ኤር. 13፥18) ። ለምሳሌ የወጌ ጎይስ ሥላሴ ባለቤት አቴጌ መነን በ1923 ዓ.ም. የአቴጌ ነት ዘውድ ጭነው አቴጌ ተባሉ ።

642. **አጎተ - አጎትአፈራሁ** (ግእ)
በስጋና በመንፈስ ወይም በሥራ የወዳጅነ ትና የመረዳዳት አንድነት ያላት። በአባት እና በእናት በኩል ፤ በሚስትነት ፤ በክር ስቶስ ፤ በአገር አጎት ይባላል (ዘፍ. 20፥ 12 ፤ መሐ. 4፥9 ፤ ዘጎ. 25፥18 ፤ ኤር. 3፥7 ፤ ሮሜ. 16፥1) **አጎትነሽ** (ግእዝ)
አትነሽ (በማርኛ)
አጎተ ማርያም ከርስትና ስም።

643. **እናት - እኑ - እናንዬ**
ለእናት ወይም በናት ቦታ ለሚታይ የሚ ሰጥ የቁልምጫ ስም ። መጠሪያ ስም ይኾናል ። የወለደች አንከባከባና መግባ ያላደገች በሥጋ በመንፈስ ይእናትነትን ሥራ የፈጸመች ። ወላጅ ፤ የክርስትና እናት ፤ ምእመናንን የምትረዳ (ሮሜ. 16 ፥13)።
እኑነሽ - እኒዓየሁ - እኑዬ - እናና
እናታገኝ - እናኒት - እናት - እናኑ
እናትዬ - እናታፈራሁ - እናቴ
እናቴነሽ - እናትኹኝ - እናትነሽ
እናታለም - እናትቱንታ

644. **እኔማየሁ** (እኔምአየሁ)
ዘመን እና ጊዜ አልፎ።
ያባት ስም ብርሃን ቢል ይገጥማል።

645. **እንጉዳዬ - እንጉዳይ**
በውሃ ዳር ወይም በክረምት የሚበቅል የምትበቅል ደባብ የምትመስል የምትበላ ተክል ነች ። የማይበላም አለ።
እንጉዳዬ ነሽ የኔ እንጉዳይ እንዳለ ዘፋኝ።

646. **አከንየለሽ**
ምንም የሚወጣልሽ አቃቂር የለም።
ያባት ስም ወርቁ ቢል ይገጥማል።

647. **እንይሽ**
ብቅ በይ ካለሽበት ስማለት ነው።
ያባት ስም ተስፋዬ ቢል ይገጥማል።
እንያት - እንያቸው - እንዬ

648. **እንኮይ**
ጣፋጭ የጫካ ውስጥ ፍሬ ነች።
ያባት ስም ፍሬው ቢል ይገጥማል።
ወዳጄ በቆነጃጅት መካከል ናት፤ በዱር እንዳለ እንኮይ (መኃ. መኃ. 2፥3)።
እንኮይነሽ - እንኮዬ

649. **እንዳሻሽ**
እንደ ተመቸሽ ፣ እንደ ፈለግሽ።
ያባት ስም **በሸይበሉ** ቢል ይገጥማል።
እንዳለልሽ - እንዳለሽ - እንዳለች - እንዳለማው - እንዳለማሁ

650. **እንዳየሁ**
ሌላን ዐይኔ እንዳየ ።
ያባት ስም ደሳለኝ ቢል ይገጥማል።
አዳንቺየለም - እንዳንቺ - እንዳወርቅ

651. **እንጉዳይ**
በበረሀ የሚበቅል ፤ ተወዳጅ ነጭ ተክል።
ያባት ስም በቀለ ቢል ይገጥማል።

652. **እንግዳሽት — እንግዳጌጥ**
"ለአገሩ ባዳ ለሰው እንግዳ" ይባላል።
ከሌላ ወገን የመጣ (ዕብ. 11፥13–11)።
ያባት ስም ባዩ ቢል ይገጥማል ።
እንግድ - እግዳነሽ - እግዳዘር
እንግዳየሁ - እንግዳዬ - እንግዳይ

653. **እንጎቻ**
ታናሽ የምታስደስት ፣ የምታጓጓ።
ትንሽ እንጀራ። ማብቂያ ።

(ዘጸ. 29፥2 ፤ 1ነገሥ. 17፥13)
ያባት ስም ጥጋቤ ቢል ይገጥማል።

654. **እንጎታት** (ግእ)
እንኮይ ማለት ነው።
እንጎታት ወሀቡ መዐዛ። ትርጕም
እንኮይ መዐዛውን ሰጠ (መኃ. ዘሰ. 7)።

655. **እጅጋየሁ** (እጅግአየሁ)
በዚህ ስም የሚታወቁት የዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ እናት እመት እጅጋየሁ ናቸው።
ትልቅ ንጉሥ በመውለዳቸው
መኳንኖች በዙ በሮም በሶርያ፤
ወለድ እጅጋየሁ በኢትዮጵያ፤
ተብሎ የውደሳ ግጥም ተገጥሞላቸዋል።
እጅጓ - እጅግሰማሁ - እጅግነሽ

656. **እግዚአ ኃረያ**
ጌታ የመረጣት። ከርስትና ስምን ተመልከች።

657. **እጥፍወርቅ**
ከአንድ በላይ የኾነ ። የተደራረበ።
ያባት ስም ተወረሰ ቢል ይገጥማል።

658. **አራቤ** (ዶር) ዐዲስ ማለት ነው።

659. **አርፋ** (ዕብ.)
የምአብ ተወላጅ የኖኃሚን ምራት ነች (መጽ.ሩት 1፥4)።

- ከ -

660. **ከለላሽ**
ከለለቻት፣ ጋረደችሽ፣ መጋረጃሽ።
ያባት ስም ብዙነው ቢል ይገጥማል።
ከለሉሽ - ከለለች - ከለላዬ
ከልካይ - ከልይ

661. **ከበቡሽ - ከበበች - ከበበሽ**
ብዙዎች ፤ ዙሪያውን ከበቡ።
ያባት ስም ዓለሙ ቢለ ይገጥማል።
ከበበፀሐይ - ከበቡ - ከበቢት

662. **ከበደች**
ከበረች ማለት ነው በቁጥር በሚዛን
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዷ የራስ
ሥዩም መንገሻ ሴት ልጅ የደጃዝማች
አበራ ካሣ ባለቤት በማይጨው ጦር ሜዳ
ዐርበኛ የነበሩት ከበደች ሥዩም ይጠሩበ
ታለ (1904 - 1976 ዓ.ም.)። **ከበድኝቸው**

663. **ከብካብ** (ግእ)
ሰርግ ማለት ነው።
ከብካበ ኮነ በቃና ዘገሊላ ። ትርጉም ፤
በገሊላ ከፍል በቃና ሰርግ ኾነ (ዮሐ. 2፥1)
ያባት ስም መርዓዊ ቢለ ይገጥማል።

664. **ከተማነሽ - ከተማ - ከተማሽ**
የደመቀች የለስለሰነች ...።
ያባት ስም ይድነቃቸው ቢለ ይገጥማል።

665. **ከፍያለች – ከፍአለች**
ወደላይ የታየች ። በቁመት ፣ በሙያ ፣
በውበት፣ **ከፍነሽ - ከፍከፍ**
ያባት ስም ጮልላቴ ቢለ ይገጥማል።

666. **ኩሉብርሃን** (ግእ)
ኩሉብርሃን ማለት ነው ።
ያባት ስም ታየ ቢለ ይገጥማል።

667. **ኩሊቱ - ኩሊ** (ኦሮ)
ኩል የተሟለች ማለት ነው። ዓይንን ለማ
ሳመር የሚቀቡት ቅባት ።የጥንት ሰዎችም
ዘመናዊዎችም የዓይናቸውን ሽፋሽፍት
በኩል ይኩዋሉ ነበር (2ነገ. 9 ፥ 30፤
ኤር. 4 ፥ 30 ፤ ራእ. 3፥18)።

668. **ኩሪ – ኩሪባቸው**
ተንቀባረሪባቸው ...።
ያባት ስም **ሙሉዓለም** ቢለ ይገጥማል።

669. **ኪሮስ** (ግሪ)
በዚህ ስም አመቤታችን ቅድስት ድንግል
ማርያም በሥዕሏ ተገልጻ ያነጋገረችው
ጻድቀ-ሰማዕት መነኩሰ እባ ኪሮስ በመባል የሚ
ታወቁ ጸድቅ ናቸው (ስን. ሐም.8 ገጽ.535-
-541) ። ወለተ ኪሮስ ከሚለው የክርስትና
ስም ተወሰዶ ኪሮስ በማለት ይጠራሉ።

670. **ኪያ** (ኦሮ) የእኔ ማለት ነው።

671. **ኪያኪ** (ግእ) **ኪያኪሙናይተ**
አንቺ በጎ መልካም ማለት ነው።

672. **ኪዳኗ** (ግእ)
የተዋዋልችው ቃሏ ...።
ተካየደ ካለው የወጣ ነው። ተዋዋለ፣ ቃል
ኪዳን ተጋባ፣ ተማማለ ማለት ነው።
(ዘዳ. 29፥1 ፤ ኤር. 31፥31 ፤ 32፥33)።

673. **ካሰች**
ዋጋ ከፈለች ፤ ከፈለችኝ።
ያባት ስም ለመኝ ቢለ ይገጥማል።
ክሳነሽ - ካሰችኝ - ካለኝ - ካሱ
ካሕሚት - ካሕሚይ - ክሚይቱ
ክሚይነሽ (ትግ)

674. **ካንቺወዲያ**
ሌላ አያስፈልገኝም ፤ ፍጹምነትን ያመለ
ክታል።
ያባት ስም መዐርጉ ቢለ ይገጥማል።

675. **ኬና** (ኦሮ) ስጦታ ማለት ነው።

676. **ከAAተወርቅ – ከAነሽ**
ከለለ ከሚለው ግስ ፤ ጋረደ አከበረ ይመ
ጣል ። የተከበረች ወርቅ።
ያባት ስም መንግሥቴ ቢለ ይገጥማል።

677. **ክብር**
ከፍተኛነትን፣ ብርሃንነትን ፣ ሰው በንጽሕ
ናው ክብር ያገኛል (ሮሜ. 13፥7)።
ያባት ስም ማኅተቤ ቢለ ይገጥማል።
ክብራነሽ - ክብረወርቅ - ክብሯ
ክብረመንግሥት - ክብርነሽ - ክብራ
ክብረዓለም - ክብርዬ - ክብረማርያም
ክብረ ቅዱሳን ክርስትና ስም።

678. **ከበበ**
ዙሪያዋ የተከበበ ፤ የተሸመች።
ያባት ስም ጌራወርቅ ቢለ ይገጥማል።
ከበቢያቸው - ከበቢ - ከበበፀሐይ
ከበብነሽ - ክብነሽ - ክቢቱ
ከበበወርቅ - ክብዬ - ክቤ

679. **ከባስወርቅ**
ከበሰ ከሚለው ግስ ፤ ጠመጠመ ጠጉር
ጠቀለለ ማለት ነው።

680. **ክትነሽ**
የተከተተች ፤ በዐዲስነት ያለች።
ያባት ስም ደሳለኝ ቢለ ይገጥማል።

681. **ከፈይ**
አንደ ድርሻቸው አዳርሽ፤ አኩል አኩል
አካፍይ ፤ ሚዛን ኹኝ ...።
በዚህ ስም የሚታወቁት የቴጌ ጣይቱ
ታናሽ ወንድም የራስ ወሌ ብጡል ሴት
ልጅ ወይዘሮ ከፈይ ወሌ ይባላሉ። የበጌ
ዮሐንስ ልጅ የራስ መንገሻ ባለቤት።

682. **ኩራሽ - ኩራን - ኩሬ**
ኩራት ማለት መቆንን፣ መኮፈስ ነው።
ኩራት ልጅ በመገኘቱ።
ያባት ስም በቃሉ ቢለ ይገጥማል።

683. **ኮከቤ - ኮከብ - ኮከብነሽ**
ኮከቦች የአምላክን ክብርና ታላቅነት
ያስታውቃሉ (ዘፍ.1፥16 ፤ አሞ. 5፥8)።

- ኘ -

684. **ኙለመናሽ - ኩለመናሽ** (ግእ)
ፍጹም አካል አና ሙሉ አካል
(ሉቃ. 11፥34)።
ውበትን ለመግለጽ ይሰየማል።
ያባት ስም አሸናፊ ቢለ ይገጥማል።
ኙሉዬ - ኙሉምታየ - ኙሉምይፈር
ኙሉምሰው - ኙሉባንቺ - ኙሉታዬ
ኙሉንቻይ - ኙሉንዓየሁ -ኙሉዓለም
ኙሉዐዲስ - ኙሉአገሬ - ኙሉአገር
ኙሉአገርሽ - ኙሉወርቅ -ኙሉይማር
ኙሉግርጌሽ - ኙሉዋ - ኙልጊዜ
ኙሉሰፍራሽ

685. **ኻብታም** (አማ)
ከበተ፣ ተከበተ ካለው ካብታም (ግእ)
ኻብታሚ - ኻብትይ - ኻብቴዋ
ኻብቴነሽ - ኻብታለም - ኻብትሽ
ኻበትአገኘሁ - ኻብትሽይመር
ኻብትሽደግ - ኻብትሽወርቅ
ሀብት የሚለውን ተመልከች።

686. **ኽነችልኝ**
ኽነ ከሚለው ግስ ፤ ኾነ ይወጣል ። ያሰ
ብኩት ኾነ ።
ያባት ስም ዐልግዝ ቢለ ይገጥማል።

- ወ -

687. **ወለላ**
ከማር የሚፈስ የማር ውሃ ወይም ከዳ የሌለው ንፁሕ ማር ። ወለላ የመልካም ቃል የጥበብም ምሳሌ ነው።
(መዝ. 18፥9 ፤ ምሳ. 16፥24 ፤ 24፥13)።

688. **ወለቴ** (ግእ) **ወለተ - ወለቱ**
ወለትየ ከሚለው የወጣ ። ልጄ የኔ ልጅ ማለት ነው። ለክርስትና ስም ወለተ ጊዮር ጊስ ፤ የጊዮርጊስ ልጅ ይባላል ።

689. **ወሊንሳ**
ቀይ ከፋይ ወይም አርንጓዴ ባለወርቅ ዘርፍ በዙፋንና በመክዳ ላይ የሚጠጋ።

690. **ወረሰኛ**
ጠባይን ፣ መልክን ፣ ሥራን ።
ያባት ስም የናትፋንታ ቢል ይገጥማል።

691. **ወረደኛ**
ዱብ አለች። አቆለቆለች።
ያባት ስም ሊባኖስ ፣ ዬርዳኖስ ቢል ይገጥማል።

692. **ወርቀዘቦ**
ወርቅ ያለበት በወርቅ የተዘመዘመ የክብር ልብስ፣ ግምጃ፣ ካባ (ሕዝ. 16፥10፤ 27፥7)።

693. **ወርቁ**
የከበረና ውድ የኾነ ማዕድን የክብር እና የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ነው (ዘፍ. 2፥11 ፤ 13፥2 ፤ 24፥53 ፤ ማቴ. 25፥11 ማቴ 10፥9 ፤ መዝ. 119፥72)።
ያባት ስም በዛብህ ቢል ይገጥማል።

ወርቅነሽ - ወርቃለማሁ
ወርቅይጠሩ - ወርቂቱ - ወርቅይጣሉ
ወርቃየሁ - ወርቃፈራሁ - ወርቃፈስ
ወርቃለም - ወርቂያ - ወርቅዬ
ወርቅብዙ - ወርቃበዛሁ - ወርቅዋዛ
ወርቅሰው - ወርቅሽት - ወርቅሸዋ
ወርቅነሽ - ወርቅነች - ወርቃበባ
ወርቃንጥሩ - ወርቂ - ወርቅይላኩ

694. **ወርቅውሃ**
የወርቅ ውሃ በእሳት የቀለጠ ፤ እንደ ወርቅ የተወደደ የጣመ ውሃ።
ያባት ስም ፈለቀ ቢል ይገጥማል።

695. **ወሰንየለሽ**
እንቺን የመሰለ በየትም የለም ለመወደድ ድንበር የሚከለከል የለሽም ።
ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከወይዘሮ በዛብሽ ከወለዷቸው ሴት ልጆች አንዷ ወሰንየ ለሽ ይባሉ ነበር። ወሰኔ - ወሰን - ወሰናቸው

696. **ወይናበባ - ወይንሽት**
ከጥንት ጀምሮ የታወቀ ተክል ነው።
(ዘፍ. 14፥18 ፤ ሕዝ. 17፥6)።
ያባት ስም አበበ ቢል ይገጥማል።
ወይኗ - ወይኒቱ - ወይንየ - ወይኒ
ወይናረግ -(ወይንሐረግ) - ወይናለም
ወይነአብ - ወይንአፈራሁ
ወይነግርያም (መሐ. ዘሰ.7)።

697. **ወደርየለሽ – ወደሬ**
የሚተካከልሽ ፤ የሚመስልሽ የለም።
ያባት ስም ሕብስተመና ቢል ይገጥማል።

698. **ወዳጂነሽ - ወዳጂ**
የምትወጂኝ ነሽ ማለት ነው።

የወደዱትን ስሙን እየጠሩ መግል ...።
ወዳጂ ሆይ ተነሽ ፤ ውበቴ ሆይ ነዪ፤
(መኃ. መኃ. 2፥10)።
ያባት ስም መላኩ ቢል ይገጥማል።

699. **ወገን**
ያገር ልጅ፣ ዘመድ፣ ነገድ፣ ቤተሰብ።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።
ወገኔ - ወገንነሽ - ወገንበዛ

700. **ወግበዛ - ወግነሽ – ወጌ**
ለኹሉ የሚወሳ ፤ የሚነገር።
ያባት ስም ጌጡ ቢል ይገጥማል።

701. **ውልታ**
አምሮት፣ ትዝታ፣ ማማር ...።

702. **ውባንቺ**
በዚህ ስም የሚታወቁት የኩስኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ባለቤት ውባንቺ ቢሻው ናቸው ።
ውብቢሻው - ውቢቱ - ውብሐረግ
(ውብአረግ) - ውብርስት - ውበት
ውባለም - ውብጅግ - ውቢት
ውባለሸዋ - ውባለሰው - ውባለች
ውብአለን - ውብአላት - ውብአምላክ
ውባየሁ - ውባዩ - ውብዐዲስ
ውብባገኝ - ውብርስት - ውብሥራ
ውብነሽ - ውብናት - ውብይሻው
ውበቴ - ውብታየ - ውብዕድል

703. **ውዴቤ**
ለእግዚአብሔር ክብር እና ምስጋና ማቅረብ (ራእ. 4፥9)።

704. **ውዴ**
ወዳጂ ሆይ እነሆ ውብ ነሽ ።
(መኃ. መኃ. 1፥15)። **ውድዬ**

ያባት ስም ታከለ ቢል ይገጥማል ።
ውዴነሽ - ውዴዓለም - ውድነሽ

705. **ዊንታ** (ትግ) ደስታ ማለት ነው።

706. **ዋለሉ - ዋለለች**
ወዲያ ወዲህ ። ጠላቶች ዛበሩ
(ሉቃ. 12፥29) ።
ያባት ስም በቃሉ ቢል ይገጥማል።

707. **ዋርካነሽ**
ትልቅ ዛፍ ፤ ታላቅ ነሽ ፣ ብዙ ቅርንጫፎች ፤ ሰፋፊ ቅጠሎች ያለው የአድባር ዛፍ። ያባት ስም ከለላ ቢል ይገጥማል።

708. **ዋሴነሽ – ዋሰዓለም - ዋሴ**
ተሼዘሸኝ ፣ ካሳ ኾንሽኝ ...።
ያባት ስም ምስክር ቢል ይገጥማል።

709. **ዋጋዬ - ዋጋነሽ - ዋጋሽ**
የላብ የድካም ።
ያባት ስም በዛ ቢል ይገጥማል።

- ዐ -

710. **ዐልጋነሽ**
የክብር ማረፊያ ቦታ።
ያባት ስም ማዕርጉ ቢል ይገጥማል።
ዐልጋብርሃን - ዐልጋወርቅ

711. **ዐመለወርቅ(ቁ) - ዐመልሸት**
ደግ ሰው፣ አይቁረቁራ፣ አያስቀይሚ ጠባየዋ ያማረ ። የረጋች የተረጋጋች።
ያባት ስም ታየ ቢል ይገጥማል።
ዐመሏ - ዐመለ - ዐመለዘውድ

712. **ዐሥራት - ዐሥራቴ - ዐሥራተ**
ከማንኛውም ገቢ ከአሥር አንድ ፤

ለሃይማኖት መሪዎችና ለመንግሥት የሚ
ሰጥ (ዘፍ. 14፥20)።
ያባት ስም ሰጠኝ ቢል ይገጥማል።
ዐሥራተ ሥላሴ ክርስትና ስም።

713. **ዐረፈዐይኔ**
ከመጓጓት ፤ የዓይን ማረፊያ ።
ያባት ስም ተመስገን ቢል ይገጥማል።
ዐረፈሸዋ - ዐረፈች

714. **ዐሰበልኝ** (ሐሰበ (ግእ))
ተቆረቆረልኝ፣ ተጨነቀልኝ ...።
ያባት ስም ወዳጂ ቢል ይገጥማል።
ዐሰበች - ዐሰበችወርቅ

715. **ዐሳቤ** (ሐሳቤ (ግእ))
ተፈጸመ፣ ተቃና፣ ኾነልኝ ...።
ያባት ስም ፍጹም ቢል ይገጥማል።
ዐሳቢ - ዐሳብ - ዐሳብነሽ

716. **ዐበረች**
ተባበረች፣ ዐብራ ኾነች ...።
ያባት ስም በኅብረት ቢል ይገጥማል።

717. **ዐወቀች**
ተረዳች ...።
ያባት ስም መሸሻ ቢል ይገጥማል።

718. **ዐዘነች**
ያባት ስም ዘማርያም ቢል ይገጥማል።
ዐዛኜ - ዐዛኝቱ - ዐዘነች - ዐዘነችልኝ

719. **ዐየለች** (ኀየለች (ግእ))
በዚህ ስም የምትጠራው በሩጫ ውድ
ድር አገሯን ለዓለም ያሳወቀች ዐየ
ለች ወርቁ ነች። **ዐየሉ - ዐያልነሽ**

720. **ዐይናለም** (ዐይንዓለም)
ማስተዋልን፣ ብርሃንን ማየትን አንዲሁም
የሰውን ጠባይንና ስሜት ይገልጣል (ዘዳ.
7፥16 ፤ ኢሳ. 5፥15 ፤ ሕዝ. 14፥16)።
ያባት ስም ብርሃኔ ቢል ይገጥማል።
ዐይናበባ - ዐይናቸው - ዐይናዲስ
ዐይንሽት - ዐይኔነሽ - ዐይኔ
ዐይነፀሐይ - ዐይኒዬ - ዐይንዋጋ
ዐይናማ - ዐይኔ

721. **ዐደሰች** (ሐደሰች (ግእ))
ዐዲስ አደረገች ...።
ያባት ስም ሕይወት ቢል ይገጥማል።
ዐዲሴ - ዐዲስ - ዐዲሷ - ዐደሱ
ዐደሰወርቅ

722. **ዐዲስዘመን** (ሐዲስ (ግእ))
ዐውደ ዓመት ፤ ክረምት አለፈ።
ዐዜ ኃይለ ሥላሴ የጣሊያን ጦርነት አንዳ
በቃ ከድል በኋላ ጋዜጣዋን ዐዲስ ዘመን
አሏት ። **ዐዲስ ምራፍ**
ያባት ስም ዮሐንስ ቢል ይገጥማል
ዐዲስ - ዐዲሳለም - ዐዲስ ሕይወት

723. **ዐጀቡሽ – ዐጀብነሽ**
ያባት ስም ሙሉዓለም ቢል ይገጥማል።

724. **ዐዜነሽ** (አጤነሽ (ግእ))
ያባት ስም መንግሥቴ ቢል ይገጥማል።

725. **ዐጸደ ወይን** (ግእ) (አጠደ ወይን)
ስፍራ ቦታ፣ የቤተ ክርስቲያን ዛፍ፣
አደግር ። የወይን አታክልት ።
ዐጸደ ወይን አፍለስክ አምግብጽ።
ትርጕም፤ ከግብጽ የወይን ግንድ አመጣኽ
(መዝ. 79(80)፥8)። አጠደ ዐማርኛ ነው።
ዐጸደ - ዐጸዱ = አፀደ ተመልከት።

726. **ዓለም - ዓለምዘውድ**
ዓለም ያለነበረበት ጊዜ ነበር በኋላ ግን
እግዚአብሔር አስገኘው ። ጠቅላላ ፍጥረ
ትን የዓለምን ሕዝብ ማለት ይኾናል ።
(ዮሐ.1፥10 ፤ 16፥21)
ዓለመወርቅ - ዓለመብርሃን
ዓለምሸዋ - ዓለሚ - ዓለሜ - ዓለም
ዓለምሰፋ - ዓለምሸት - ዓለሚቱ
ዓለምቀናሽ - ዓለምሻ - ዓለምቀረ
ዓለምባንቺ - ዓለምብርሃኔ
ዓለምብርሃን - ዓለምተሰፋ
ዓለምታሪክ - ዓለምታየ - ዓለምላንቺ
ዓለምሰላም - ዓለምትኩን - ዓለምነሽ
ዓለምይርጋ - ዓለምናት - ዓለምዬ
ዓለምይሰፋ - ዓለምገላ - ዓለምገነት
ዓለምፀሐይ - ዓለምጸጋ - ዓለምፍሬ

727. **ዓላማዬ**
ለዘመቻ ለሌላም የሚይዙት ምልክት
ወይም የሚያቆሙት ምልክት (ዘኍ. 2፥2
መሐ. 6፥4 ፤ የሐዋ. 28፥11)።

728. **ዓባይ**
ትልቅ ማለት ነው። በዚህ የሚጠራው
ትልቁ ወንዝ ጊዮን ነው (ዘፍ. 2፥13)።
ዓባይሽ - ዓባይነሽ - ዓባይነች

729. **ዓያና** (ኦሮ.)
በዓል፣ ሰንበት እንዲሁም ቀናኝ፣
ቆንጆ ማለት ነው። **ዓያንቱ - ዓዬቱ**

730. **ዓይዳ** (ዐረ) **ዓይድዐ**
ምኞት ማለት ነው።

731. **ዔደን** (ዕብ) **ዔዶም** (ግእ)
ምቹ ሥፍራ፣ ገነተ ተድላ የግእዝ መጽ
ሐፍ ዔዶም ይላል። የሰላም የደስታ ቦታ
እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ፈጥሮ ያስ
ቀመጠበት ቦታ ከበሕተት በፊት የነበሩበት
ምድረ ገነት (ዘፍ. 2፥10፤ 3፥24፤ ዘፍ.1፥8)

732. **ዕርቀሰላም** (ርቀሰላም)
ጠብ ባለባቸው ኹለት ሰዎች መካከል
ሰላም ሲኾን ዕርቅ ይባላል። ከፈጣሪ ጋር
መታረቅ ፤ የሚያስታርቁም ብፁዓን ተብለ
ዋል። (ማቴ. 5፥9 ፤ ፊል. 4፥2)።
ያባት ስም ወረደ ቢል ይገጥማል።
ዕርቀኢየሱስ - ዕርቅነሽ - ዕርቁ
ዕርቃለም

733. **ዕሴተ** (ግእ)
ዋጋ ማለት ነው።
ዕሴተ ፍሬሀ ለክርሥ ። ትርጕም ፤
የሆድም ፍሬ የሱ ዋጋ ነው (መዝ.126፥3)።

734. **ዕንቁ**
ኦል ፤ አልማዝ የከበረ ድንጋይ ፤ ከባ
ሕር ውስጥ የሚገኝ ሰዳፍ የምትወልደው
(ማቴ. 13፥45 ፤ ራእ. 21፥21)።
ዕንቁባሕርይ - ዕንቁአየሹ
ዕንቁአየሽ - ዕንቁዬ - ዕንቁአለች
ዕንቁዬነሽ - ዕንቁብርሃን
ዕንቁ ሥላሴ ክርስትና ስም ተመልከች።

735. **ዕድሜዓለም**
ዕድሜ ለሰጠው ማየት ደግ ነው።
ያባት ስም ስገሙ ቢል ይገጥማል።

736. **ዕፀገነት – ዕፀሕይወት**
በገነት ያለች ፍሬ ፤ የሕይወት ፍሬ።
ያባት ስም መድኃኒት ቢል ይገጥማል።

737. **ዕፁብነኝ – ዕፁብ**
ያባት ስም ፍጹም ቢል ይገጥማል።

- ዘ -

738. **ዘለቃሽ**
መጪረሻሽ ፤ ፍጻሜሽ።
ያባት ስም ይመር ቢል ይገጥማል።
ዘለቃወርቅ - ዘለቀች - ዘለቁ - ዘለታ

739. **ዘላለም**
ፍጻሜና ወሰን የሌለው ፤ ጊዜ የማይወሰ
ነው ፤ ያልተወሰነ (መዝ. 89፥2 ፤ 2ጴጥ.
3፥8 ፤ ዳን. 12፥2 ፤ 1ሳሙ. 1፥22)።
ያባት ስም መንግሥቱ ቢል ይገጥማል።

740. **ዘመረት - ዘመረወርቅ**
ያባት ስም ያሬድ ቢል ይገጥማል።

741. **ዘመነሰላም - ዘመን**
የሰላም ዘመን። - **ዘመነወርቅ**
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል

742. **ዘመናይ (ዘበናይ)**
ጊዜን ተከትሎ የሰለጠነ ማለት ነው።
ዘመናዊ - ዘመኒት - ዘመነች

743. **ዘመደወርቅ**
ያባት ስም ታደሰ ቢል ይገጥማል።
ዘመዲቱ - ዘመድ - ዘመዳ
ዘመዳለም - ዘመዳንቺ - ዘመዷ
ዘመዳየኹ - ዘመዳገኝ - ዘመዴ

744. **ዘመአድም** (ግእ)
አደመ አማረ ከሚለው የወጣ ነው።
ዘመአድም ያማረች ማለት ነው።
ያባት ስም ብርሃኑ ቢል ይገጥማል።

745. **ዘማርያም**
የማርያም ነሽ ማለት ነው።

746. **ዘረብዙ - ዘርትኹን**
የሰፋ የተሰፋፋ ፤ በአገር የሞላ።
ያባት ስም ታከለ ቢል ይገጥማል።
ዘሪቱ - ዘረወርቅ - ዘርዓ ጽዮን

747. **ዘርጊልኝ - ዘርጊ**
አጅሽን ፣ ተሰፋ ስጭኝ ...።
ያባት ስም ሙሉዋጋ ቢል ይገጥማል።

748. **ዘርፈሽዋል**
ውበቱን፣ ሀብቱን ወስደሽዋል ማለት ነው።
በዚህ ስም ይታወቁ የነበሩት የንጉሥ
ሚሀለ ሥላሴ የልጅ ልጅ ወይዘር ዘርፈ
ሽዋል ሲይፉ ናቸው ። ከዐፄ ምኒልክ
አስከ ንግሥት ዘውዲቱ በቤተ መንግሥት
አማካሪ ነበሩ ። **ዘርፈቱ - ዘርፍነሽ**
ዘርፈ - ዘርፍሽ - ዘርፈወርቅ

749. **ዘበነች – ዘበኑ - ዘበናይ**
ዘመነች ከሚለው ጋር ይዛመዳል።

750. **ዘበአማን** (ግእ)
እውነተኛ የኾነች ።
ያባት ስም ፍጹም ቢል ይገጥማል።

751. **ዘቢብ - ዘቢብነሽ**
የደረቀ የወይን ጣፋጭ ፍሬ ማለት ነው
(1ኛ ሳሙ. 25፥18) ።
ያባት ስም ፍሬሥናይ ቢል ይገጥማል።

752. **ዘብርሃን** (ግእ) **የብርሃን**
የብርሃን ...።
ያባት ስም ከኸዱ ቢል ይገጥማል።

753. **ዘብይደሩ (ዘቢደሩ) ዘቢደር**
ያባት ስም ተገኔ ቢል ይገጥማል።

754. **ዘነበወርቅ**
በዚህ ስም የሚታወቁ የዐፄ ኀይለ ሥላሴ
አራተኛ ልጅ ናቸው ። በስማቸው ሆስፒ
ታል ተሰይሞ ነበር ።
በዚህ ስም የንጉሥ ሚሀለ ሥላሴ እናት
ይጠሩበት ነበር።
ዘነብሽ - ዘኑ - ዘነበች - ዘነቡ

755. **ዘወርቅ (ግእ) የወርቅ**
የወርቅ ማለት ነው ...።
ያባት ስም ጌጡ ቢል ይገጥማል።

756. **ዘወትር**
ዅል ጊዜ ...።
ያባት ስም ዐዲስ ቢል ይገጥማል።

757. **ዘውዲቱ**
በዚህ ስም የሚታወቁት የዐፄ ምኒልክ
ልጅ፤ የራስ ጉግሳ ባለቤት፤ የልጅ ኢያሱ
ሚካኤል እክስት ፤ የዐፄ ኀይለ ሥላሴ
የቅርብ ዘመድ ንግሥተ ነገሥታት ዘው
ዲቱ ምኒልክ ናቸው። 13 ዓመት ኢትዮጵ
ያን አስተዳድረዋል ። **ዘውዲት**
ዘውዳለም - ዘውዴ - ዘውድነሽ
ዘውዳይ - ዘውዳገኘሁ - ዘውዲ

758. **ዘየደች**
ብልህ ኾነች ...።
ያባት ስም በፍርዱ ቢል ይገጥማል።

759. **ዘይቱ - ዘይቱን**
ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚጠቀም፤
ከወይራ ፍሬ የሚጨመቅ፤ ለምግብ የሚያ
ገለግል። (1ሳሙ 10፥1 ፤ 1ነገሥ፤ 17፥2
፤ ሉቃ. 10፥34 ፤ ያዕ. 5፥14)።
ያባት ስም ንጹሕ ቢል ይገጥማል።

760. **ዘገነች - ዘገነወርቅ - ዘገኑ**
አፈሰች ...።
ያባት ስም ወርቁ ቢል ይገጥማል።

761. **ዘገየሽ - ዘገየች - ዘገዩ**
በቶሎ አልመጣሽም ...።
ያባት ስም በረቃዱ ቢል ይገጥማል።

762. **ዙሪያሽ - ዙሪያሽወርቅ**
የከበበሽ በሙሉ።
ያባት ስም ሕብስተመና ቢል ይገጥማል።

763. **ዙፋን**
ከብር ያለው የንጉሥ ወንበር ። ወይም
የከብር ሰው መቀመጫ (ዘፍ. 41፥40) ።
ዙፋንሽ - ዙፋኔ - ዙፋንሽወርቅ

764. **ዛብሽ - ዛብሽወርቅ**
ምትይገርው፤ የምትጨብጭው
(የመጥረቢያ እጀታ) ማለት ነው
ያባት ስም ታዬ ቢል ይገጥማል።

765. **ዜና - ዜናዊ - ዜናዊት**
ዐዲስ ነገር፤ የምሥራች ወሬ።
ያባት ስም ትንሣኤ ቢል ይገጥማል።

766. **ዝማም**
ስናግ የጥጃን አፍ መያዣ ዝም የሚያሰኝ
ነው። ዝምታ እርምም ፤ ልጓም ማለት
ነው (ኢዮ. 40፥20 ፤ ኢሳ. 37፥29) ።
ዘማሚ - ዝማምነሽ
ዝማምወርቅ - ተመልሶ የተነጠረ ወርቅ።
የወርቅ ዝማም በሴቶች አናና አፍንጫ በጆሮ
መካከል የሚንጠለጠል ቀለበት (ዘጸ. 37፥17)።

767. **ዝግሬ**
መዝሙር ማለት ነው ። ከትዱሰ ቁርባን በኋላ የሚዘመረው ከ5ቱ ጽዋትወ ዜማ አንዱ የቅዳሴ ወንድም የሚባለው መዝሙር ምስጋና (ዘጸ. 25፥2.)።
ያባት ስም ዳዊት ቢል ይገጥማል።

768. **ዝምታ - ዝምታወርቅ - ዝምነሽ**
ዝም ማለት (ኢዮ. 4፥16 ፤ መክ. 3፥7)።
ያባት ስም ታደለ ቢል ይገጥማል።

769. **ዝናሽ**
ገናናነት ፤ ታላቅነት ።
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።
ዝናወርቅ - ዝናአየሁ - ዝናዬ
ዝናሸብዙ - ዝናሸወረቅ - ዝናነሽ

770. **ዝናቢ**
ዝናብ የእግዚአብሔር በረከት ነው።
(ዘዳ. 28፥ 9 -12 -15)። **ዝናብወርቅ**
ያባት ስም ወረደ ቢል ይገጥማል።
ዝናብነሽ - ዝናቤ - ዝናብ

771. **ዞማዬ - ዞማ - ዞማነሽ**
ጠንረ ልበልበ ፤ የተንዠረገገ።
ያባት ስም ውበቱ ቢል ይገጥማል።

- ሸ -

772. **ሸማነሽ - ጀማነሽ**
በሰሜን ሽዋ እና በወሎ መካከል የሚገኝ ታላቅ ወንዝ።
ያባት ስም ሙላቱ ቢል ይገጥማል።

- የ -

773. **የሀገር (ግእ) የትውልድ ቦታ።**
ያባት ስም ክብሩ ቢል ይገጥማል።

774. **የሉልወርቅ**
የከበረ ድንጋይ ዕንቁ ማለት ነው።
(ዘፍ. 2፥12)
ያባት ስም ታረሰ ቢል ይገጥማል።

775. **የልፍኝ**
ልዩ የክብር ቦታ ፤ አዳራሽ ።
ያባት ስም ተሾመ ቢል ይገጥማል።
የልፍኝስም - የልፍኞጋ - የልፍኞጋሽ

776. **የሐሳብ (የዐሳቤ (ዐግ))**
የምኞቴ ፤
ያባት ስም ሞላ ቢል ይገጥማል።

777. **የማርያም ወርቅ**
የቅድስት ድንግል ማርያም ወርቅ።
ያባት ስም ክብሩ ቢል ይገጥማል።

778. **የማርውሃ**
የሚጣፍጥ ብርዝ ...።
ያባት ስም ፈለቀ ቢል ይገጥማል።

779. **የማታ - የማታፀሐይ**
በኋላ የተገኘች ... ።
ያባት ስም ሀብት ቢል ይገጥማል።
የማታወርቅ - የማታሸት - የማታነሽ

780. **የማነሽ ? (የማንነሽ)**
ጥያቄን ሥልስን ። የማነሽ ቆንጆ።
ያባት ስም አዱኛ ቢል ይገጥማል።

781. **የምሥራች**
አብሣሪ፣ ዐዲስ ነገርን የሚናገር ፤ ተና ጋሪ ማለት ነው (ሉቃ. 1፥26)።
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።

782. **የምሻሽ**
የምፈልገሽ ፤ የምናፍቅሽ።
ያባት ስም ከተማ ቢል ይገጥማል።

783. **የምወድሽ**
ታላቅ እኅት የምትጠራበት ...።
ያባት ስም መታሰቢያ ቢል ይገጥማል።

784. **የሩቅነሽ**
ማንም አይደርስብሽም በሙያሽ ...።
ያባት ስም ምሥራቅ ቢል ይገጥማል።

785. **የራስወርቅ**
አክሊል፣ ዘውድ፣ የምታምር ...።
ያባት ስም አክሊሉ ቢል ይገጥማል።

786. **የሽዋፀሐይ**
የምታምር ቆንጆ የሚወዳደራት የሌለ።
ያባት ስም ደረሰ ድረሴ ቢል ይገጥማል።

787. **የሺ**
አመቤት፣ ዳኛ ...።
ያባት ስም በላይ ቢል ይገጥማል።
የሺወርቅ - የሺዓለም - የሺሐረግ (የሻረግ) - የሺነሽ - የሺጥላ

788. **የሺመቤት**
የራስ መኩንን ባለቤት የዐፄ ኀይለ ሥላሴ እናት ወይዘሮ የሺመቤት ይባሉ ነበር። በምሥራቅ ሐረርጌ የጥምቀተ ባሕር ሚካኤልን ያሰተክሉ ናቸው።

789. **የሻሸ ወርቅ**
በዚህ የሚታወቁት የዐፄ ኃይለ ሥላሴ ታላቅ ወንድም የደጃዝማች ይልማ መኩንን ባለቤት የወይዘሮ አሰለፈች ወንዱ አድ ልዕልት የሻሸ ወርቅ ይልማ ።
እንደዚሁ የዐርበኛው የበላይ ዘለቀ ሴት አድ ዐርበኛ የሻሸወርቅ ዘለቀ ናቸው።

790. **የቃልነሽ - የቃልኪዳን**
ምልክት፣ መታሰቢያ...።
ያባት ስም መዝገቡ ቢል ይገጥማል።

791. **የባሕርነሽ - የባሕርወርቅ**
የባሀር ውስጥ ወርቅ...።
ያባት ስም ሉልዬ ቢል ይገጥማል።

792. **የባሌወርቅ**
ባሌ አገር ነው ...። ሌላው ባልዋ ነው።
ያባት ስም ንዴሕ ቢል ይገጥማል።

793. **የብርጓል**
ከወርቅ ቀጥሎ ከሌሎች ማዕድናት በልጦ በኹለተኛነት የተመረጠ ማዕድን ብር ነው (ዘፍ. 44፥2 ፤ ዘጸ. 12፥35)።
ያባት ስም ላቀው ቢል ይገጥማል።
የብሬ - የብርውሃ

794. **የብቻወርቅ - የብቻዬ**
የግሌ ፤ የብቻዬ የኾነሽ ...።
ያባት ስም ሀብቴ ቢል ይገጥማል።

795. **የብዙወርቅ**
ብዙዎች ለማግኘት የሚጓጉት ...።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

796. **የትምወርቅ**
በየቦታው ወርቅ።
እንዳንቺ ያለ የትም ወርቅ የለም ...።
ያባት ስም ተረጨ ቢል ይገጥማል።

797. **የትነበርሽ**
ከጊዜ በኋላ ተገኘሽ ።
ከብዙ ወንዶች በኋላ።
ያባት ስም **ማዕረጉ** ቢል ይገጥማል።

798. **የትናየት**
ማንም አይደርሰብሽም ...። በሙያ፣ በውበት፣ በቁንጅና ...። ርቀትን ያመለክታል።
ያባት ስም **አጥናፉ** ቢል ይገጥማል።

799. **የናትነሽ**
የእናት ምትክ ነሽ ...።
ያባት ስም **ማሰረሻ** ቢል ይገጥማል።
የናትፈንታ - የናትፈንታነሽ

800. **የኔነሽ**
የኔ የብቻዬ ነሽ ፤ እኔን መሰለሻል ...።
ያባት ስም **ፋንታዬ** ቢል ይገጥማል።

801. **የኔዓለም - የኔፈንታ**
የኔ ደስታ፣ በሕይወቴ ደስታ አየሁ ...።
ያባት ስም **ገላው** ቢል ይገጥማል።
የኔሙቱት - የኔማር - የኔመንግሥት
የኔአካል - የኔናት - የኔአዛኝ
የኔአበባ - የኔውብ - የኔገዳም

802. **የንጉሥነሽ - የንጉሥ**
ታላቅነትን፣ ክብርን መመኘት ...።
ያባት ስም **ዘውዱ** ቢል ይገጥማል።

803. **የንጋት - የንጋትኪብ**
ጠዋት ላይ ብቅ ያለች፤ የማትጠገብ ...።
ያባት ስም **ፀሐይ** ቢል ይገጥማል።

804. **የኖዓለም (የኖለም) – የኖነሽ**
የእኖ ደስታ፣ ሀብት፣ ክብር ...።
ያባት ስም **ጌጤ** ቢል ይገጥማል።

805. **የኢትዮጵያ ወርቅ**
ብዙ ጊዜ በአገር እና በሠፈር በቅጽልነት ወርቅ እየተጨመረበት የሚጠራ ስም አለ ለዳቦ ስም ሊኾን ይችላል።
የመንዝወርቅ - የይፋትወርቅ
የየጁወርቅ - የጎጃምወርቅ
የሐረርወርቅ - ያድአወርቅ
የሰላሌወርቅ - የቀ·ስቋምወርቅ
የሾላወርቅ - የየጁወርቅ - የዲላወርቅ
የጅማወርቅ - የጁቲወርቅ
የጉናወርቅ - የጎላወርቅ
የጎንደርወርቅ - የጎጃምወርቅ
ሌላም.. ብዙ ሊባል ይቻላል።

806. **የኢትዮጵያ ጌጥ**
የሸዋጌጥ - የጎንደርጌጥ - የሐረርጌጥ
ሌላም መጠሪያ አንደሚኾን ይታወቃል።

807. **የክቴ - የክትነሽ**
የኔ የክት ነሽ፤ በተከበረ ቀን የምትታዪ
ያባት ስም **ኒሻን** ቢል ይገጥማል።

808. **የኹሉ**
በውበትሽ የኹሉ በላይ ...።
ያባት ስም **በላይ**፣ **ክብሩ** ቢል ይገጥማል

809. **የወርቅውሃ**
ውበትን ያመለክታል ።
ያባት ስም **ዘነበ** ቢል ይገጥማል።

810. **የወይንሐረግ (አረግ)**
ያባት ስም **አበበ** ቢል ይገጥማል።
የወይንሸት- የወይንውሃ- የወይንዐዲስ

811. **የወዲያሴት**
ያባት ስም **ተገኝ** ቢል ይገጥማል።

812. **የውብነሽ**
ውብ ቆንጆ ነሽ ...።
ያባት ስም **ወጋየኹ** ቢል ይገጥማል።
የውብዛፍ - የውቤ - የውበርስት

813. **የውብዳር**
የቆንጆዎች መጨረሻ ነሽ ...።
የእቴጌ ጣይቱ እናት ወይዘሮ የውብዳር ይባሉ ነበር።

814. **የኋላሸት**
በስተ መጨረሻ የተገኘሽ ...።
ያባት ስም **አማረ** ቢል ይገጥማል።
የኋላወርቅ - የኋላ - የኋላዬ

815. **የዘወትር**
ደስታ፣ ሀብት፣ ...።
ያባት ስም **ፍሬው** ቢል ይገጥማል።

816. **የዝናዬ - የዝናሽ - የዝናሽወርቅ**
የኔ ዝና ነሽ ...።
ያባት ስም **ኒሻን** ቢል ይገጥማል።

817. **የግሌነሽ**
የኔብቻ ነሽ ...።
ያባት ስም **በለው** ቢል ይገጥማል።

818. **የገነትፍሬ – የገነትሽታ**
ጠፋ·ም፣ ሕይወት ሰጪ ...።
ያባት ስም **አበበ** ቢል ይገጥማል።

819. **የጣትወርቅ**
ብርቅ የሆንሽ የማትለይ የቃል ኪዳን ምልክት ...።
ያባት ስም **ኪዳኔ** ቢል ይገጥማል።

820. **ያሆቼት** (ጉራ)
አረጋሽ ማለት ነው።

821. **ያለምሸት (የዓለምሸት)**
ያባት ስም **ታፈሰ** ቢል ይገጥማል።

822. **ያለምፀሐይ**
ያለም ብርሃን፣ መብራት ...።
ያባት ስም **ታዬ** ቢል ይገጥማል።
ያለምሰው - ያለምነሽ- ያለምዘውድ
ያለምወርቅ - ያለምጌጥ - ያለም
ያለምፍቅር - ያለምብርሃን

823. **ያልታሸወርቅ**
ገና ዐዲስ ...።
ያባት ስም **ገሙ** ቢል ይገጥማል።

824. **ያልታየሽ - ያልታየች - ያልታዩ**
የተደበቅሽ ...።
ያባት ስም **ፍሰሐ** ቢል ይገጥማል።

825. **ያምሮት (የአምሮት)**
የፈቃድ፣ አንዳይቀረብኝ ...።
ያባት ስም **ሰጦታው** ቢል ይገጥማል።
ያምሮቴ - ያምሮትነሽ

826. **ያምባሸት (የአምባሸት)**
የምትወደጅ የማዶው፣ የለምለሙ ቦታ...።
ያባት ስም **ታከለ** ቢል ይገጥማል።

827. **ያሳብነሽ - ያሳብ - ያሳቤ**
በሐሳብ የነበርሽ ...።
ያባት ስም **ሰጠኝ** ቢል ይገጥማል።

828. **ያቦነሽ**
የጸድቁ ነሽ ...።
ያባት ስም **ያንጥሩ** ቢል ይገጥማል።

829. **ያቦወርቅ (የአቦወርቅ)**
የገብረ መንፈስ ቅዱስ ልጅ ...።
ያባት ስም ተክበ ቢሉ ይገጥማል።

830. **ያንቺአምላክ**
ፈጣሪሽ ጎበኘን ...።
ያባት ስም ታምሩ ቢሉ ይገጥማል።

831. **ያንገትሐብል**
የምትወደድ ማለት ነው...።
ያባት ስም አበራ ቢሉ ይገጥማል።
ያንገትጌጥ - ያንገትድሪ- ያንገትወርቅ

832. **ያዩሽ - ያየሽ**
ያዩሽ ኹሉ ያደንቁሻል ...።
ያባት ስም በዙ ቢሉ ይገጥማል።

833. **ያይኔብርሃን**
ተስፋዬ መሪዬ ነሽ ...።
ያባት ስም አበራ ቢሉ ይገጥማል።
ያይንዐዲስ - ያይንዋጋ - ያይንዋጋሽ

834. **ያይንአበባ**
ውበትን ይገልጻል፤ ይኔ አበባ ነሽ።
ያባት ስም በዛብህ ቢሉ ይገጥማል።
ያይንሽት - ያይኔአበባ

835. **ያደግድጉ - ያደግድጉልሽ**
ይታጠቁ፣ ሽር ጉድ ይበሉ ...።
አደገደገ፣ ተላበሰ፣ ታጠቀ፣ አሸረጠ፣ አገ
ለመደ፣ ሽርጉድ አለ፣
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዷ ጠቅላይ
ሚኒስትር የነበሩት ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ
ሀብተወልድ እናት ወይዘሮ ያደግድጉ ፍል
ፍሉ ይባሉ ነበር ።

836. **ያድንቁሽ**
ያባት ስም ፕዝዜ ቢሉ ይገጥማል።
ያዳንቁሽ - ያደንቁ

837. **ያድቡሽ - ያጅብነሽ - ያድቡሻል**
አፍን አፍን ያድርጉሽ ፤ መወደድን ያመ
ለክታል።
ያባት ስም ዘላለም ቢሉ ይገጥማል።

838. **ያጥቢያነሽ – ያጥቢያ**
የቅርብ የምታበሪ ፣ የምታምሪ ...።
ያባት ስም ኮኸቡ ቢሉ ይገጥማል።

839. **ይሉሻል**
ውብ ነሽ፣ ቆንጆ ነሽ ...።
ያባት ስም አረጋዊ ቢሉ ይገጥማል።

840. **ይልፋሽዋ**
አንቺን ለማገኘት ይንከራተቱ ...።
ያባት ስም ቢነጋ ቢሉ ይገጥማል።

841. **ይመችሻል**
ይደላሻል፣ አይከፋሽም ...።
ያባት ስም አገሬ ቢሉ ይገጥማል።

842. **ይመኑ - ይመኑሽ - ይመንሽ**
በሃይማኖት ፤ አውነቱን ይወቁ ...።
ያባት ስም በዝና ቢሉ ይገጥማል።

843. **ይመናኙ**
ወንዶች ባንቺ ላይ ይዋጉ ...።
መመናኛ - ጉልማሶች የሚዋጉባት የምታ
ምር ሴት፤
ያባት ስም ውቤ ቢሉ ይገጥማል።

844. **ይመኙሻል - ይመኙሽ - ይመኝሽ**
በውበትሽ፣ በሙያሽ፣ ይሙሻል ...።
ያባት ስም ዳኛው ቢሉ ይገጥማል።

845. **ይመኩብሽ - ይመካብሽ**
ተስፋ አለኝታ ያርጉሽ ...።
ያባት ስም ዓለም ቢሉ ይገጥማል።

846. **ይማልዱሽ - ይማልዱ**
አጅመንሻ ይዘው ይለምኑሽ ...።
ያባት ስም የዕልፍዋጋ ቢሉ ይገጥማል።

847. **ይምጡበዝናሽ - ይምጡበዝና**
በታላቅነትሽ፣ በውበትሽ ...።
ያባት ስም ተመስገን ቢሉ ይገጥማል።

848. **ይርበቡ (ግእ)**
አጃቸውን ይዘረጉልሽ ...።
ያባት ስም በለው ቢሉ ይገጥማል።

849. **ይርገዱ - ይርገዱልሽ**
ሰዎች ይፍሩ፣ ይንቀጥቀጡ ማለት ነው።
ያባት ስም በጋሻው ቢሉ ይገጥማል።

850. **ይርጋዓለም - ይርጋሸዋ - ይርጉ**
ጸጥ ይበል፣ ይረፍ ...።
ያባት ስም ቢልልኝ ቢሉ ይገጥማል።

851. **ይሳለሙሽ - ይሳለሙ**
ይስገዱልሽ፣ ለክብርሽ፣ ለገናሽ ...።
ያባት ስም ዘላለም ቢሉ ይገጥማል።

852. **ይስማ - ይስማሽዋ**
ወደ ዐዲስ ዓለም መምጣትሽን ...።
ያባት ስም ደነገጡ ቢሉ ይገጥማል።

853. **ይናዱ**
ጠላቶች ይሸሹ ማለት ነው።

854. **ይኹንልሽ - ይኹንጸጋ**
ሀብት፣ ጸጋ ፣ በረከት ...።
ያባት ስም በምደወርቅ ቢሉ ይገጥማል።

855. **ይዘሽዋል (ይዘሺዋል)**
ውበቱን፣ ሙያውን፣ ኹሉንም ...።
ያባት ስም ይመኑ ቢሉ ይገጥማል።

856. **ይጋረዱ - ይጋርዱሽ**
መጋረጃውን ፣ መከለያውን ይሸፍኑ ...።
ያባት ስም የሻሸወርቅ ቢሉ ይገጥማል።

857. **ይደነቁ**
በውበትሽ ፣ በቁንጅናሽ ...።
ያባት ስም ዘመድ ቢሉ ይገጥማል።

858. **ይገባሻል**
ለበጐ ሥራሽ ፣ ለውበትሽ ...።
ያባት ስም ወርቁ ማዕረጉ ቢሉ ይገጥማል
ይገባልወርቅ - ይገቡሻል

859. **ይፍቱሥራ**
አንቺን እያዩ፣ ውበትሽን እያደነቁ ...።
ያባት ስም ውብነሽ ቢሉ ይገጥማል።

860. **ይፏክሩሽ**
አንቺን እያዩ ወድድር ይያዙ ...።
ያባት ስም ዘመድ ቢሉ ይገጥማል።

861. **ዮርዳኖስ** (ግሪ. ግእ)
ዮር ማለት ወራጅ ውሃ ፤ ዳን ደየን
ፈረደ ማለት ዳኜ ማለት ነው።
ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበት ዝኙ
ለት ቃል ተወስዶ ዮርዳኖስ ይባላል ።

በዚህ ስም ሴቶችም ወንዶችም ይጠሩበ ታል (ማቴ. 3)።

862. **ዮክብድ** (ዕብ.)
እግዚአብሔር ክብር ነው ማለት ነው። የሙሴና የአርን እናት (ዘጸ. 2፥1፤ 6፥20 ፤ ዕብ. 11፥23)።

863. **ዮዲት** (ዕብ.)
የሜራሪ ልጅ ነች ። ናቡከደነጸር አሰራሌ ልን ሊወጋ ቢል እንዴት እንደተካለከለች የሚገልጽ ታሪክ በመጽሐፈ ዮዲት ውስጥ ተጽፏል (መጽ. ዮዲ 8፥1)።

- ደ -

864. **ደመቀች - ደመቅሽ**
አበራች፣ ፈካች፣ አማረች ...።
ያባት ስም ምትኩ ቢል ይገጥማል።
ደመቁ - ደመቅሽኝ - ደምቀሻል

865. **ደመረወርቅ - ደመራሽ**
ወርቅ ጨመረ ማለት ነው።
ያባት ስም ታደለ ቢል ይገጥማል።

866. **ደሚቱ** (ኦሮ) - **ደሚ** -
ማሬ ፣ ማር ማለት ነው ።
ደሚ - ደማሚ - ደመወርቅ (ዐ.ማ)
በቀጥታ ዐማርኛ ትርጉም።

867. **ደሞዜ** (ደመወዜ)
የላቤ ዋጋ፣ ገንዘቤ (ዘሌ. 22፥10)።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።
ደመወዝ - ደሞዜነሽ - ደሞዝ

868. **ደራርቱ** (ኦሮ) - **ደረራ**
ዘረዘረ (ለአህል) አበበች ፣ ደረሰች ከአ ዝመራ ጋር የተያያዘ ።

በዚህ ስም የምትታወቀው በ10 ሺ ሜትር የኦሎምፒክ ውድድር ኢትዮጵያን ወክላ በሰፔን ፣ ባርሴሎና ከተማ ፣ በአውስትራ ልያ ሲድኒ ተወዳድራ የወርቅ ሜዳልይ ተሸላሚ የኾነች ኩለኔል ደራርቱ ቱሉ ናት።

869. **ደራሼ**
ድንገቴ ማለት ነው ...።
ያባት ስም ታዬ ቢል ይገጥማል።

870. **ደስታ - ደሱዬ**
ፍሥሓ ፣ ድርብ አጥፍ የኾነ።
ያባት ስም ታዬ ቢል ይገጥማል።
ደስታኹን - ደስታዓለም - ደሳለች

871. **ደብሬ - ደብሪቱ**
ታላቅ ነሽ፣ የክብር ሰው ነሽ ...።
ከፍታ ቦታ ፤ ደብረ ሊባኖስ። ትርጉም፤ የሊባኖስ ተራራ ። ደብረ ጽዮን ዘአፍ ቀረ ። ትርጉም ፤ የወደደውን የጽዮንን ተራራ (መዝ. 77(78)፥68)።
ያባት ስም ከፍያለው ቢል ይገጥማል።
ደብረወርቅ - ደብርነሽ - ደብርሽ
ደብርዓለም - ደብሯ
ደብርሽወርቅ - የምሬት ስም።

872. **ደጅይጥኑ - ደጂነሽ - ደጂቱ**
በደጅ ይቆዩ፣ ይቀመጡ፣ ጊዜ ይሰጥ ...።
ያባት ስም በላቸው ቢል ይገጥማል።

873. **ደግነሽ – ደጊ - ደጊቱ**
ጥሩነሽ፣ ቸርነሽ፣ ርኅሩኅ ነሽ ...።
ያባት ስም ስሎታው ቢል ይገጥማል።

874. **ደግዓለም**
ጥሩ የኾነ ጊዜ፣ ዘመን፤ ዓለም ...።
ያባት ስም ተሻገ ቢል ይገጥማል።

875. **ዱባለች**
ሳትታሰብ መጣች፣ ወረደች ...።
ያባት ስም ፋንታዬ ቢል ይገጥማል።

876. **ዲቦራ** (ዕብ.)
ንብ ማለት ነው ።
የእስራኤል ነቢይትና ዳኛ ነበረች ፤ በጦር ነት ጊዜ የጦር አዝማች ፤ በሰላም ጊዜ በፈራጅነት እስራኤልንና እግዚአብሔርን ያገለግሉ ከነበሩት አንዲቷ ነች (መሳ.4)።

877. **ዲና** (ዕብ.)
ፈረደ ማለት ነው።
ልያ የወለደችለት የያዕቆብ ሴት ልጅ (ዘፍ. 30፥21 ፤ 46፥15)።

878. **ዳመነች – ዳመኑ**
ጥሩ ዝናብ ልታመጪ ነው።።
ከረምትን ያመለከታል ...።
ያባት ስም በጊዜው ቢል ይገጥማል።

879. **ዳርምየለሽ**
ለቁንጅናሽ ወሰንም፣ ድንበርም የለሽ።
ያባት ስም ዓለሜ ቢል ይገጥማል።
ዳርእስከዳር - ደሩነሽ - ዳሪነሽ

880. **ዳባሽ**
ኹሉን የምትፈልጊ ...።
ያባት ስም ሰውነት ቢል ይገጥማል።

881. **ዳኘልኝ**
ፍረጂልኝ ማለት ነው።
ያባት ስም ሞላልኝ ቢል ይገጥማል።
ዳኛነሽ - ዳኝነት - ዳኝአቸው።

882. **ዳቶ** (አፋር)
ዐሜ ዮሐንስ ባለቤት ናቸው። የአፋር ልጅ ከርስትና አሰጠምቀው ጥበበ ሥላሴ በማዕ ኘት አግብተው አርአያ ሥላሴን ወለዱ። ለኢየሩሳሌም ገዳም ደብረ ዝኑ ኪዳን ምሕረትን ለማሠራት ብዙ ገንዘብ ረድተ ዋል።

883. **ዳግማዊት**
ኹለተኛ ማለት ነው።
ያባት ስም ምስክር ቢል ይገጥማል።
ዳግምብርሃን - ዳግም - ዳግማዊ

884. **ድልቧንቺ**
ባንቺ የተነባ ድል ተደረገ፣ ተገኘ ...።
ያባት ስም ይበቃል ቢል ይገጥማል።
ድላረገኝ - ድል-ወንበሯ

885. **ድርብ**
እጥፍ የኾነች (ሩት. 3፥4)።
ያባት ስም ሀብቴ ቢል ይገጥማል።
ድርቧ - ድርቤነሽ - ድርብወርቅ

886. **ድምብላል**
ማጣፈጫ ቅመም ...።
ድንብልብል ያለች የምታምር ...።
ያባት ስም ቅመሙ ቢል ይገጥማል

887. **ድርሻዬነሽ – ድርሻነሽ**
ፋንታዬ ነሽ ...።
ያባት ስም እንዳይከፋኝ ቢል ይገጥማል።

888. **ድባቤ - ድባብነሽ - ድባብሽ**
ከሐር እና ከወርቅ የተሠራ የታቦት ጥላ የወርቅ ዘርፍ ያለው።
ያባት ስም ይመር ቢል ይገጥማል።

889. **ድብቅነሽ – ድብቅ**
ምስጢር፣ ረቂቅ ....።
ያባት ስም ይርጋዓለም ቢል ይገጥማል።

ሴ

890. **ድንበሬ (ኦሮ) ድንበር**
የደሰ ደሰ ያላት ቆንጆ ማለት ነው።

891. **ድንቅነሽ**
የምታስገርሚ ነሽ ...።
በአፋር በቁፋሮ የተገኘችውን የሴት አጽም ድንቅነሽ ወይም ሉሲ ብለው ሰይመዋታል። **ድንቅዬ**
ያባት ስም **ያገርፍሬ** ቢለ ይገጥማል።
ደነቅሻቸው - ድንቂቱ - ድንቂ
ድንቃስም - ድንቃየኹ - ድንቄ

892. **ድንበሯ - ድንበርነሽ**
ቀጥታ ቢተረጉም ወሰኗ፣ ክልሏ ...።
ያባት ስም **አጥናፉ** ቢለ ይገጥማል።
ድንበርየልሽ - ድንበሪቱ - ድንበሬ -

893. **ድንብል (ድምብል)**
አንገት ላይ የሚደረግ ጌጥ ...።
ያባት ስም **ጌጡ** ቢለ ይገጥማል።

- ጀ -

894. **ጀማነሽ (ዝማነሽ)**
ታላቅነሽ፣ በቂ ነሽ፣ የደስ ደ.ሪ. ያለሽ ነሽ በውሎ እና በሽዋ፤ በተጉለት እና ቤመንዝ የሚያዋስን ታላቅ ወንዝ ነው።
ያባት ስም **ይበቃል** ቢለ ይገጥማል።
ጀማወርቅ - ጀማዬ - ጀማየነሽ

895. **ጀምበር - ጀምበሬ**
የፀሓይ ሰም፤ ትልቅ ብርሃን ማለት ነው። (ዘፍ. 1፥16) የማታ ጀንበሬ ይባላል።
ያባት ስም **ዘገየ** ቢለ ይገጥማል።
ጀምበሬነሽ - ጀምበርነሽ - ጀምበሪቱ

896. ጀመሬ (ኦሮ) ጀምሪያለሁ ማለት ነው።

897. ጂፋሬ (ኦሮ) ጀፍጀፌ ማለት ነው።

898. ጃለለ (ኦሮ) የምወድሽ፣ የማፈቅርሽ።

- ገ -

899. **ገሊላ**
ከእስራኤል ክፍለ ሀገሮች አንዲቷ ነች። ወደዚህች ክፍለ ሀገር መልእኩ ቅዱስ ገብርኤል አመቢታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አንደ ምትፀንስ ሊያበሥራት በናዝሬት ከተማ ተገኘ (ዮሐ. 7፥15)።

900. **ገላነሽ**
በዚህ ሰም ይታወቁ የነበሩት የደብረ ጽላ ሎ የቅኔ ሊቅ አማሆይ **ገላነሽ** ሐዲስ ናቸው። በቅጽል ስማቸው ዳግማዊ ሆሜር ተብለዋል ። **ገላይቱ**
ገገላዬነሽ - ላዬ - ገላወርቅ - ገላሽ

901. **ገላኔ (ኦሮ)**
የሞላ ወንዝ፤ ስንቅ ነሽ ማለት ነው።

902. **ገላጋይ - ገላጋዬነሽ**
አስታራቂ፣ አስታራቂዬ፤ ሰላምን አመጣሽ ማለት ነው ።
ያባት ስም **ቢኾነኝ** ቢለ ይገጥማል።

903. **ገርሳሞት**
ወይም ንግሥት ሕንደኬ ከልደተ ክርስቶስ ቢኋላ የኢትዮጵያ ንግሥት ነበረች። በዘ መኗም ጃንደረባዋ (በጅሮንዷ) ወደ ኢየሩ ሳሌም ተልኮ ፤ ጥምቀተ ክርስትናን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል።
(የሐ. ሥራ. 8፥26 -40)

904. **ገሰሰች**
ፍርድን ሻረች ...።
ያባት ስም **ቹሙ** ቢለ ይገጥማል።

905. **ገበያነሽ - ገበያ - ገበያዬ**
ኹሉ ነገር የሞላበት፤ ዋጋ አወጣሁበሽ።
ያባት ስም **ይግዛው** ቢለ ይገጥማል።

906. **ገብሬሏ**
የገብርኤል ነሽ ስማለት ነው። ዘገብርኤል የክርስትና ስም ...።

907. **ገነት - ገነተወርቅ**
በያይነቱ ተክል ያለበት ምቹ ስፍራ።
የደስታ ቦታ ። እግዚአብሔር አዳምን በዔደን አትክልት ወተተከለበት ገነት አኖረው (ዘፍ. 2፥8 ፤ 3፥7)።

908. **ገነኘች**
ዝነኛ ኾነች፣ ባገር ታወቀች ...።
ያባት ስም **አገሬ** ቢለ ይገጥማል።

909. **ገናዬ - ገናነሽ - ገናሽት**
የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል።
ያባት ስም **ልደቱ** ቢለ ይገጥማል።

910. **ገንዘቤ - ገንዘብነሽ**
የላቢ ዋጋ፣ ደሞዜ ነሽ ።
ያባት ስም **ተናኘ** ቢለ ይገጥማል።

911. **ገዛሽኝ - ገዛችን - ገዛሽወርቅ**
በኃይልሽ፣ በውበትሽ፣ በሥራሽ ፤ በቁጥርሽ አደረግሽኝ ...።
ያባት ስም **በጊዜው** ቢለ ይገጥማል።

912. **ገዳምነሽ - ገዳም - ገዳሚ**
የመመነኛ ቦታ ፣ የብቃት ቦታ ...።

913. **ጉልላትነሽ**
ለዘመድ ለወዳጅ የምትታዩ ...።
ያባት ስም **ታዬ** ቢለ ይገጥማል።
ጉልላቴ - ጉልላት

914. **ጉልትነሽ**
ደመወዝ ፣ ርስት ፣ የላብ ዋጋ ነሽ።
(ዘዳ. 13፥14)።
ያባት ስም **ደሞዜ** ቢለ ይገጥማል።

915. **ጉዳዬ - ጉዳየነሽ - ጉዳይ**
ተፈላጊዬ ነሽ።
ያባት ስም **ቀናው** ቢለ ይገጥማል።

916. **ጉደቱ** (ኦሮ) የምታድግ ማለት ነው።

917. **ጉዲቱ** (ኦሮ) አዳጊ ማለት ነው።

918. **ጊቤነሽ** (ጉራ) አሰፋሽ ማለት ነው።

919. **ጊዜወርቅ - ጊዜዋ**
ዘመን፣ ዓመት፣ ወር፣ ሰዓት፣ አፍታ፣ የደግ ጊዜ፣ የሰላም ጊዜ፣ የጤና ዘመን፣ የጦርነት ፣ የረሀብ፣ የአልቂት ዘመን ኹሉ። ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ጊዜ ይታሰባል (ዘፍ. 1፥1) ።
ጊዜሽወርቅ - ጊዜነሽ - ጊዜዓለም

920. **ጊፍቲ** (ኦሮ)
አመቢት ማለት ነው። ጎላፊና ተወዳጅ የኾነች ማለት ነው (2ኛ ዮሐ. 1፥2)።

921. **ጋረደች**
አዳነች፣ ሸፈነች ...።
ያባት ስም **ፀሓይ** ቢለ ይገጥማል።

922. **ጋቢነሽ – ጋቢ**
ተወዳጅ፣ ሙቀት የምትሰጭ ...።
ያባት ስም ስንሻው ቢል ይገጥማል።

923. **ጋዲሴ** (ኦሮ) ጥላዬ ማለት ነው።

924. **ጌራወርቅ - ጌራ**
በከበረ ዕንቁ ያሸበረቀ ዘውድ የራስ ወርቅ ማለት ነው ። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በራሷ ላይ የሚታየው ዘውድ (ኢሳ. 59፥17 ፤ ሕዝ. 26፥16)።

925. **ጌጤ**
የኔ ጌጥ ነሽ ለማለት ...።
በዚህ ስም የምትታወቀው ብዙ ሚዳልያ ያገኘች ሩዋጭ ጌጤ ዋሜ አንዷ ነች።
ጌጤበዛ - ጌጤነሽ - ጌጤናት - ጌጥዬ

926. **ግርግለሽ - ግርግነሽ**
ድንቅ የኾነ ደስ የሚያሰኝ የሚያስፈራ።
ያባት ስም ሺፈራው ቢል ይገጥማል።
ግርግሽ - ግርግዬነሽ - ግርግዊት

927. **ግምጃ - ግምጃወርቅ**
ከጥጥ ከሐር ተፈትሎ የተሠራ በቀለም የተዋበ ልብስ (ዘጸ. 26፥1)።
የንዋየ ቅድሳት ማስቀመጫ ፤ ወይም የመንግሥት ንብረት ማስቀመጫ የተከበረ ቦታ ግምጃ ቤት ይባላል ፤ ሹሙም የግምጃ ቤት ሹም ይባላል ።

928. **ግሩምነሽ - ግሩምወርቅ**
የምትወደጅ፣ የምታምረ፣ የምታስደንቂ
ያባት ስም ጥበቡ ቢል ይገጥማል።

929. **ጎመጂ - ጎመጂሽ**
ወደዱሽ፣ ሊያዩሽ ናፈቁ ለማለት...።
ያባት ስም በዝና ቢል ይገጥማል።

930. **ጎበዛየን - ጎበዛየሁ**
ፈጣን፣ ባለሙያ፣ ታታሪ ...።
ያባት ስም ነጋሢ ቢል ይገጥማል።

931. **ጉርፍነሽ – ጉርፌ**
ድንገተኛ ደራሽ ነሽ።
የዘርን ብዛትና ኃይል ያሳያል።
ያባት ስም ፈለገሕይወት ቢል ይገጥማል።

- ጠ -

932. **ጠለላ (ጸለላ)**
መጠለያ፣ መሸሸጊያ፣ እስኪያልፍ ድረስ መቆያ ፣ ከመከራ የምትሰውር ...።

933. **ጠበሌ - ጠበለግርያም (ጸበል)**
መድኃኒቴ ነሽ ለማለት ።
ያባት ስም ፈለቀ ቢል ይገጥማል።

934. **ጠጂቱ** (ኦሮ)
ማር ያለብሽ ማለት ነው።
ያባት ስም ዳዲ ቢል ይገጥማል።
ጠጂ - ጠጄ - ጠጂነሽ (ዐማ)

935. **ጣፋጭ – ጣፈጡ**
የምትወደጅ ፣ የምትፈቀሪ ነሽ ...።
የመራራ ተቃራኒ ።
ያባት ስም ሸንኮራ ቢል ይገጥማል።

936. **ጣይቱ** (ፀሓይቱ (ግእ.))
በዚህ ስም የሚታወቁ ብርሃን ዘኢትዮጵያ የሚባሉት **የዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ባለቤትና** በዲ የጣሊያን ጦርነት ጊዜ ጦር አዛዥ ከነበሩት አንዲቷ እቴጌ ጣይቱ ብጡል ነበሩ ።

937. **ጣሊታ** (ሮማ)
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጣሊታ ቁሚ ብሎ ከሙታን ያስነሣት የ12 ዓመት ልጅ (ማር.5፥41)።

938. **ጤናለም**
ከኹሉ በላይ ጤና ዓለም ነው።
ብዙ ጊዜ ከበሽታ መራቅንና መዳንን ያመለክታል (ማቴ.9፥12፤ መዝ. 37፥3)።
ጤናነሽ - ጤንነት - ጤናዬ

939. **ጤናዳም**
ጥሩ ሽታ የሚሰጥ ተክል ። በልዩ ልዩ መድኃኒት ላይ የሚጨመር (ሉቃ. 11፥42)

940. **ጥላዬ - ጥላዬነሽ**
የኔ ጥላ ነሽ ...። **ጥላሽወርቅ - ጥላነሽ**
ያባት ስም ደመቀ ቢል ይገጥማል።

941. **ጥልፍነሽ - ጥልፈወርቅ - ጥልፌ**
ውበት ያለው የሚያምር ጥልፍ።
ያባት ስም ጥበቡ ቢል ይገጥማል።

942. **ጥምቀቷ**
የጥምቀት አይነት ልዩ ልዩ ነው። በውሃ እና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ፤ በሰቃይ መጠመቅ፣ መንጻት፣ መለወጥ (ማር. 1፥4)
ያባት ስም ታደሰ ቢል ይገጥማል።

943. **ጥሩነሽ**
በዚህ ስም በረኸም ርቀት የሩጫ ውድድ አገሯን ኢትዮጵያን ያሳወቀች ዘጠኝ የወርቅ ሜዳልያ የተሸለመች ታዋቂ ሯጭ
ጥሩነሽ ዲባባ ነች።
ጥሩመቤት - ጥሩመንግሥት
ጥሩማር - ጥሩማዕድ - ጥሩምርት
ጥሩምጭ - ጥሩሞያ - ጥሩሥራ
ጥሩሠራ - ጥሩሰብል - ጥሩሰው
ጥሩሸዋ - ጥሩመቤት - ጥሩምርት
ጥሩቀለም - ጥሩብሃን - ጥሩዓለሜ
ጥሩለየ - ጥሩለየሁ - ጥሩዐይን
ጥሩዐይኔ - ጥሩአዳም

944. **ጥሩወርቅ**
በውስጡ ቅልቅል የሌለበት ንጹሕ ወርቅ ማለት ነው።
የከተማይቱ አደባባይ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረች (ራእ. 21፥18-21)።
በዚህ ስም ይጠሩ ከነበሩት አንዷ የዐፄ ቴዎድሮስ ኹለተኛ ባለቤት ጥሩወርቅ ውቤ ነበሩ።
ሌላዋ ውብ መልከ መልክም ኢትዮጵያ ዊቷ ጥሩ ወርቅ በረደድ ነች።
ጥሩገበያ - ጥሩፀሓይ - ጥሩወይን
ጥሩውሃ - ጥሩዘውድ - ጥሩዘር
ጥሩድንቅ - ጥሩዬ ሲቱላመጥ

945. **ጥሬብር**
ያልተነካች፣ የልተጎላላች ...።
ያባት ስም ዋጋው ቢል ይገጥማል።

946. **ጥበበ**
ማስተዋልና ዘዴ ማንኛውም ነገር ለማግኘት የመመርመር ችሎታ ያላቸው ጥበበኞች ይባላሉ ። የጥበብ ሰዎች የተባሉት የተወለደውን ጌታ ኢየሱስን ለማየት ከምሥራቅ ወደ ቤተልሔም ተጉዘው ነበር (ማቴ. 2፥1 ፤ ዘጸ. 31፥2 ፤ ሕዝ. 27፥8)።
ጥበብ - ጥበብነሽ - ጥበቧ - ጥበቤ

947. **ጥንቅሼ - ጥንቅሽ**
የማትጠገቢ ጣፋጭ ሽንኩራቴ ነሽ ...።
የዘንጋዳ፣ የማሽላ አገዳ የምትጣፍጥ።
ያባት ስም ጣፈጠ ቢል ይገጥማል።

948. **ጥንፍየለሽ**
ለቀጐንሾናሽ ፣ ለሙያሽ ወለን የለሽ ...።
ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከወይዘሮ **ግለፊያ** ከወለዲቸው ሴት ልጆች አንዲ ጥንፍየ ለሽ በመባል ይታወቁ ነበር።

949. **ጥጋብነሽ**
ቁንሾናን፣ ውበትን ያመለከታል።
ታይታ የማትጠገብ፤ ሠርክ ዐዲስ።
ያባት ስም **ወዳጄ** ቢል ይገጥማል።
ጥጋብ - ጥጋቢ - ጥጋቤ

950. **ጦቢያ** (ዕብ) ጦቢት
ወንድም ሴትም ይጠራበታል።
በንጉሥ ስልምናሶር ዘመን ወደ አሶር በም ርኮ ከተወሰዱ በኋላ እግዚአብሔር በመል አኩ ሩፋኤል አማካኝነት ረድቷቸው ከች ግር የወጡ (መጽ. ጦቢ. 1፤2 ፤ 12፤15)።

- ፈ -

951. **ፈረቃ**
ውበት ያላት የምታምር።
ፈረቃ በሌሊት የምታበራ (ዘፍ. 1፤16)።
ያባት ስም **ጥሩአየሁ** ቢል ይገጥማል።

952. **ፈሙት** (ጉራ)
የሴት ቁንጮ ማለት ነው።

953. **ፈዋነሽ**
ቁጥብ፣ ድምጿ የማይሰማ ...።
ያባት ስም **ደሳለኝ** ቢል ይገጥማል።

954. **ፈፈመርቅ**
ያባት ስም **ሀብቱ** ቢል ይገጥማል።

955. **ፈሊ - ፈልቱ** (አሮ.)
የበላይ፣ በለጠች ፣ በለው ፣ ብለጭ ማለት ነው።

- ጸ -

956. **ጸሎተ** (ግእ)
መለመን ፣ መሳል ነው።
የንባብ ጸሎት፣ የዜማ ጸሎት ...።
ሰው ከእግዚአብሔር የሚገናኘው በጸሎት ነው፤ ጸሎት መጽናኛ ነው፤ ጸሎት ብዙ ኃይል አለው (1ሳሙ. 12፤23 ፤ 1ኛ ጴጥ. 3፤12 ፤ ያዕ. 5፤17)።
የተወለደች ልጅ በጸሎት ከኾነ በጸሌቱ አገኘኹሽ ለማለት ... ።
ያባት ስም **ኢሳይያስ** ቢል ይገጥማል።

957. **ጸደቀች** (ግእ) - **ጸደቀችወርቅ**
ጸድቀ ከለው ግስ የወጣ ነው።
ኾቀኖ ኾነች፣ ታመነች ማለት ነው።
ያባት ስም **ፍቅረኃስም** ቢል ይገጥማል።

958. **ጸደይ**
ከክረምት ቀጥሎ ከመስከረም 25 ጀምሮ የሚለወጠው ወቅት ጸደይ ይባላል። ልም ላሜ የሚታይበት የወራጅ ውሃ የሚጠራበ ት፤ አበቦች የሚያብቡበት (ዘካ. 10፤11)
ያባት ስም **አበባው** ቢል ይገጥማል።

959. **ጸዳለ - ጸዳለች - ጸዳሉ**
የብርሃን ወጋጋን ጮራ ነፀብራቅ፤ የፍርድ ና የጽድቅ ምሳሌ ነው። **ወጸዳሉኒ** ከመ ብርሃን ውእቱ። ትርጉም ፤ **ጸዳሉም** አንደ ብርሃን ነው (ዕን. 3፤4፤ ሊሳ 59፤9 ፤ አሞ.5፤20)።
ጸዳለ ማርያም ከርስትና ስም።

960. **ጸዳሽ - ጽዱነሽ** (ጥዱነሽ)
ገጹሕ ሐነሽ፣ ምንም ያልተቀለቀለብሽ።
ያባት ስም **አበባው** ቢል ይገጥማል።

961. **ጸጋ** (ጠጋ)
ምሕረት፣ በጎነት ያለ ብድራትና ያለ ዋጋ የሚደረግ ስጦታ ዕድል (ቲቶ 2፤11 ፤ ሉቃ. 1፤30)።
ጸጋነሽ - ጸጋአየሁ - ጸጋነሽ - ጸጋሽ
ጸጋዓለም - ጸጋለበለ - ጸጋሰጠኝ
ጸጋኪሮስ - ጸጋወይን - ጸጋይ
ከርስትና ስም ተመልከቱ።
ጸጋ ሕይወት - ጸጋ ማርያም
ጸጋ ሥላሴ - ጸጋ ብርሃን - ጸጋ አምላክ

962. **ጸጥታ**
ሰላም፣ ዝምታ፣ አረፍት ...።
ያባት ስም **ጥሩነህ** ቢል ይገጥማል።

963. **ጸድቃን – ጻዲቁ - ጸድቃኔ**
በሕግ የጸናች፤ በሕግ የምትኖር ፤ አካኼዳቸውን ከአግዚአብሔር ጋር ያደ ረጉ (ማቴ 25፥ 46 ፤ ሮሜ. 5፤19)።

964. **ጼናታም** (ግእ)
ጤና አዳም ማለት ነው። ጥሩ ሽታ የሚ ሰጥ ተክል ። በልዩ ልዩ መድኃኒት ላይ የሚጨመር (ሉቃ. 11፤42)

965. **ጽላተ - ጽላት**
ማደሪያ፤ የአምላክ ማደሪያ።
በላዩ ስመ አምላክና ዐሠርቱ ቃላት ባጭር ቃል የሚጣፉበት ። መሥዋዕት የሚሠዋበት፤ (2ቆሮ. 3፤3፤ ዘጸ. 31፤18)።
በዚህ ስም ሲጠሩበት የሰማል።
ያባት ስም **ሙሴ** ቢል ይገጥማል።
ጽላተ ኪዳን ከርስትና ስም

966. **ጽዮን** (ዕብ.)
መጠጊያዬ ...። እናቴ ማርያም ...።
ኢየሩሳሌም ከተሠራችባቸው ተራራዎች አንዱ ሲኾን ትርጉሙ መጠጊያ ማለት ነው። ድንግል ማርያም አማናዊት ጽዮን ትባላለች ታቦተ ጽዮንም በዚህ ስም ትጠራለች (መዝ. 125፤1)።

967. **ጽጌ**
ሽታው ደስ የሚል አበባ።
ወከመ ጽጌ ገዳም ከማሁ ይፈሪ ። ትር ጉም፤ እንደ ዱር አበባ እንዲሁ ያብባል (መዝ. 92፤15፤ መኃ.2፤12 ፤ ኢሳ. 35፤1)።
ጽጌ አስተርእየ በውስተ ምድርኑ።
ትርጉም አበቦች በምድር ላይ ተገለጡ።
እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም **በጽጌ** (አበባ) ትመሰላለች።
ጽጌ ሃይማኖት - ጽጌረዳ - ሽታው ልብ የሚማርክ እንጨቱ እሾክ ያለው ቀይ፣ ነጭ፣ ሮዝ ... አበባ ነው።
ጽጌ ወይን (የወይን አበባ)
ጽጌ ድንግል ከርስትና ስም።

- ፀ -

968. **ፀሓይ** (ጠሓይ)
ቀንና ሌሊት ጊዜያትና አቅጣጫዎች የሚ ታወቁትና የሚለዩት በፀሐይ ነው (ዘፍ. 1፤14)።
ፀሓይቱ - ፀሐዬ - ፀሓይነሽ

969. **ፀአዳ** (ግእ)
ነጭ ፣ የጸዳች ማለት ነው።
አትየ ፀአዳ ወቀይሕ። ትርጉም፤ ፍቅሬ ነጭና ቀይ ነው (መኃ. 4፤3)።

970. **ፄዴንያ - ፀደንያ**
ቅድስት ድንግል ማርያም በሥሏ አድራ ተአምራት ያደረገችበት ግርታ ትኖርበት

የነበረ ቦታ ነው ። መስከረም 10 ቀን ይከ በራል (ታሊ. ማር.)።

- ፈ -

971. **ፈለቀች – ፈለቁ**
መነጨች፣ ወጣች፣ አንጸባረቀች፣ በራች
ያባት ስም ጥበቡ ቢል ይገጥማል።

972. **ፈለገብርሃን**
የብርሃን ምንጭ፣ የብርሃን ወንዝ ማለት
ነው። **ፈለገጥበብ -**
ፈለገ ሕይወት ክርስትና ስም ተመልከች።

973. **ፈለጉሽ**
ይሹሻል፣ ይፈልጉሻል ...።
ያባት ስም አንድነት ቢል ይገጥማል።

974. **ፈረደች**
ዳኝነት ሰጠች ...።
ያባት ስም ግሩም ቢል ይገጥማል።

975. **ፈሰሰወርቅ - ፍሳሴ - ፈሰሰች**
ያባት ስም በለው ቢል ይገጥማል።

976. **ፈቃዱ**
በስዋ ፍላጎት ...።
ያባት ስም አንተነህ ቢል ይገጥማል።
ፈቃደአምላክ - ፈቀደች - ፈቃድ

977. **ፈትለወርቅ – ፈትለ - ፈትሏ**
ፈተለ ገመደ ካለው ግስ የወጣ ነው።
ያባት ስም ብሥራት ቢል ይገጥማል።

978. **ፈጠነች – ፈጠኑ - ፈጣን**
በመሄድ፣ በመናገር፣ ቸኩለች፣ ቀለጠፈች
ታላቋን ተከትላ ተወለደች።
ያባት ስም ንጋቴ ቢል ይገጥማል።

979. **ፋሲካ** (ግሪ)
ፍሥሓ፣ ተሻገረ ይኾናል። ፓሳህ ዐለፈ
ማለት ነው (ዘጸ. 12፥1)። ከትንሣኤ
ጀምሮ እስከ ዳግም ትንሣኤ ፋሢካ ይባ
ላል። የደስታ ሳምንት ነው።

980. **ፋና – ፋናዬ**
ፋ ብላ የምትታይ ጭለማን የምታርቅ።
ወይም ደግሞ እንደ ፋና የበራች ቆንጆ።
መብራቴ፣ ብርሃንን የምትሰጥ ማለት ነው።
ስለጽዮን ዝም አልልም፤ ስለኢየሩሳሌም
ጸጥ አልልም ፤ ጽድቋ እንደ ጸዳል ማዳ
ንዋም እንደ ሚበራ ፋና እስኪወጣ ድረስ
(ኢሳ. 62፥1 ፤ ዮሐ. 18፥3)

981. **ፋኖሴ**
መብራቴ፣ ብርሃኔ ፣ እንደ ፋኖስ የምታ
በራ፣ ብርሃንን ገላጯ፣ ውብ ቆንጆ ...።
በውስጡ ዘይት የሚጨመርበት አሳቱ በፈ
ትሉ ሰር ዘይቱን እየመጠጠ ብርሃንን የ
ሚሰጥ መብራት ነው።

982. **ፋንታዬ - ፋንቴ - ፋንታይቱ**
የኔ ድርሻዬ፣ ዕድሌ ...።
ያባት ስም ይበቃል ቢል ይገጥማል።
ፋንታሽ - ፋንታነሽ - ፋንቱ

983. **ፋጡማ** (ዐረ. ጉራ.)
በዚህ ስም የምትታወቀው ባለም የማራቶን
ሩጫ ውድድር በአሸናፊነት እንደ አበበ
ቢቂላ የመጀመሪያዋ ሴት ኢትዮጵያዊት
ፋጡማ ሮባ ነች ። ያገሯ ባንዲራ በአት
ላንታ ኦሎምፒክ ከፍ እንዲል አስደርጋ
ለች ።

984. **ፋጡት** (ጉራ) ምርጫ ማለት ነው።

985. **ፌቤን**
በክንክራአስ ባለች ቤተ ክርስቲያን ዐሥ
ራት በኩራቷን እያወጣች አገልጋይ የነበ
ረች የቅዱስ ጳውሎስ የስብከተ ወንጌል
ረዳት ከነበሩት አንዷ ቤት ነች። እሷም
ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መልእክት ይዛ
የኼደች ናት (ሮሜ 16፥1)።

986. **ፍሬሕይወት - ፍሬ - ፍሬያት**
የሕይወት ፍሬ ማለት ነው።
መልካም በጎነት ውስጥ ያለች (ዘፍ. 3፥7)።
ፍሬሰላም - ፍሬኽኝ - ፍሬገኑት
ፍሬሥናይት - ፍሬነሽ - ፍሬወርቅ -
ፍሬወይን - ፍሬወይኒ - ፍሬዘር -
ፍሬዘውድ -
ክርስትና ስም ተመልከች።
ፍሬ ማርያም - ፍሬ ድንግል
ፍሬ ኢየሱስ - ፍሬ እግዚእ

987. **ፍርኦሴ**
ፍርኦስኦስ ያለች ፤ የተምነሸነሸች ፤ ደስ
የምትል ማለት ነው።
ፍርኦስ - ፍርኦሽ - ፍርኖ - ፍርኖስ

988. **ፍርዳወቀች**
ዳኝነትን ፣ መገላገልን ቻለች ...።
ያባት ስም ዳኖቸው ቢል ይገጥማል።

989. **ፍሥሓ** (ግእ)
ፍሥሓዬ ፣ ደስታዬ ማለት ነው።
ፍሥሓነሽ - ፍሥሓጽዮን
ፍሥሓ ጽዮን ክርስትና ስም ተመልከች።

990. **ፍቅሬ - ፍቅር**
የኔ ፍቅር ማለት ነው።

ፍቅር የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው። የክ
ርስትና ሃይማኖት መሠረት ነው ። ሰው
ከሰው ጋራ ሰው ከእግዚአብሔር ጋራ እን
ዲተባበር ፍቅር ያስፈልጋል (1ዮሐ. 4፥8
፤ ማቴ. 22፥37- 39፤ ሮሜ. 8፥31-39)።
ያባት ስም እንደገና ቢል ይገጥማል።
ፍቅረዐዲስ - ፍቅረዓለም - ፍቅርዬ
ፍቅረሕይወት - ፍቅርተ - ፍቅሬ
ፍቅረሰላም - ፍቅረፀሐይ - ፍቅሬይ

991. **ፍትሕ** (ግእ) **- ፍተዓለም**
ፈትሐ ከሚለው ግስ የመጣ ነው።
ዳኝነትን አየች፤ ፈረደች ...።
ያባት ስም ዳኖቸው ቢል ይገጥማል።

992. **ፍቱንወርቅ**
የነጠረ ፣ የተፈተነ ወርቅ ፤ ፍቱን መድኃ
ኒት እንደ ማለት ።
ያባት ስም ይልሃል ቢል ይገጥማል።

993. **ፍትፍቴ**
ምግቤ ማለት ቢኾን፣ ውበትን፣ ቁንጅናን
ያመለክታል።
ያባት ስም ጣፈጠ ቢል ይገጥማል።

994. **ፍኖት** (ግእ)
መንገድ ማለት ነው። **ፍኖተሰላም** ቢል
የሰላም መንገድ ። **ፍኖተጽዮን**

995. **ፍጹም**
የበቃ ነውር የሌለባት ፤ ሙሉ የኾነ ጉድ
ለት የሌለባት (ዘዳ 25፥15 ፤ 16፤ ዕጣ.5፥
14፤ ያዕ.1፥4)። **ፍጹመብርሃን -**
ፍጹማዊት - ፍጹምነሽ - ፍጹምወርቅ

ምዕራፍ ፪

የክርስትና ስሞች (ስመ ጥምቀት)

የክርስትና ስም መነሻው ቅዱስ መጽሐፍ ነው። የብዙኃን አባት የተባለው አብርሃም ይታወቅ የነበረ አብራም ተብሎ ነበር። በኋላ ግን ስምህ አብራም ሳይኾን አብርሃም ይባላል ተብሎ በእግዚአብሔር ተሰየመለት። ይህም ማለት የብዙኃን አባት (የሕዝቦች አባት) የሚል ስም ነው ። ቃል ኪዳኑንም በግዝረት አደረገለት፤ ተባረከም (ዘፍ.17፥5 ፤ ሉቃ.1፥59)። በዐዲስ ኪዳን ግን ቃል ኪዳኑ በጥምቀት አደረገ (ሮሜ. 6፥1-11)።

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የክርስትና ስም መሰየም የሚገባው በታቦጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትዛዝ መሠረት መኾን አለበት የሚሉ አሉ።

> አንግዲህ ኺዱና አሕዛብን ዅሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኳችኹን ዅሉ እንዲጠብቁ አድርጉ (ማቴ 28፥19)።

አንዳንድ ሊቃውንት ደግሞ ጥምቀተ ጸሎቱ የሚከናወነው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ስለኾነ በመላእክት በቅዱሳን በጻድቃን ስም መሰየም ጉዳት የለውም ይላሉ ። ምክንያቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን በተመለከተ በመዋዕለ ትምህርቱ ትዛዝ ሰጥቷል ።

> **እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤** ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ያገኛል። ጻድቅን በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል (ማቴ. 10፥40)።

እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል በማለት በተናገረው ቃል ኪዳን የገባላቸው መላእክት ፣ ጻድቃን ፣ ሰማዕታት ፣ ... በስማቸው ጽላት ተቀርጾላቸው ፤ ቤተክርስቲያን ታንጸላቸው እ አምላክ ቅዱስ አገሌ ይባላሉ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እስከ ዛሬ ድረስ ሲሰየም የኖረው በዚህ አይነት መንገድ ነው። ይህም በጥናት ቀርቧል።

በዐፄ ልብነ ድንግል ዘመን (1500 – 1533 ዓ. ም) ግራኝ መሐመድ ኢትዮጵያን የእስላም አገር ለማድረግ ክርስቲያንን በጨፈጨፈበት፤ አብያተ ክርስቲያናትን በሚያቃጥልበት ዘመን የነበሩት ክርስቲያኖች በስመ ጥምቀታ

ቸውና በቅዱሳን ስሞች ይጠሩ ነበር። ዋናው የጦርነቱም መነሻ አንዱ ምክንያት ይህ የክርስትና ስም መጠሪያ ስለነበረ ነው ። ለምሳሌ የዐፄ ልብነ ድንግል ልጆች ሰበነ ጊዮርጊስ፣ ወለተ ቅዱሳን፣ አመተ ጊዮርጊስ፣ ያዕቆብ፣ ታያ ድራ፣ ወለተ ማርያም ፣ ገላውዴዎስ፣ ሚናስ ፣ ፊቂጦር በመባል ሰስመ ጥምቀታቸውና በቅዱሳን ስሞች ይጠሩ ነበር። የራሳቸው የንጉሠ ስም ልብነ ድንግል (ዕጣነ ድንግል) ተብለው ይጠሩ ነበር። ይህም የሚያሳየው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን እምነት በአማንያኑ ዘንድ በጣም ጠንካራና ጠበቅ ያለ በት ዘመን እንደ ነበረ ነው ። የግራኝ ወታደሮችም ማኅተብ ክርስትናቸውን በመበጠስ፤ ስመ ጥምቀታቸውን እንዲለውጡ ሲያስገድዱ አልለውጥም ያሉ ትን ብዙ ክርስቲያኖች የተጨፈጨፉበት ዘመን ነበር ። ጦርነቱ ከ15 ዓመት በኋላ ሲያበቃ እጨጌ ዕንባቆም ባዘጋጁት መጽሐፈ ቄደር ጸሎት እየተደረገ የንሥሓ ጥምቀት እንዲጠመቁ፤ ጠበል እየተረጨ ስመ ጥምቀታቸውን ወደ ቀድሞው እንዲመለስ ተደረገ።

በጎንደር ዘመነ መንግሥት ዐፄ ሱሲንዮስ ልጁ ዐፄ ፋሲለደስ ኢትዮጵያን በሚያስተዳድሩበት ዘመን ከካቶሊክ እምነት ጋር አለመግባባት ነበረ። ያብዛኛው ሕዝብ መጠሪያ የጥምቀተ ወይም የክርስትና ስማቸው እንደ ነበረና በኦርቶዶክስ ተዋሕዶና በካቶሊክ ፍጡክር የነበረበት ጊዜ እንደነበረ ታሪክ ይመሰክራል።

የዐፄ ፋሲል ስም የግሪክ ቋንቋ ሲኾን የንጉሥ ልጅ ማለት ነው። በተለያየ ጊዜ ያገቧቸው ሚስቶቻቸው አመተ ድንግል እና አኅተ ክርስቶስ ይባሉ ነበር። ልጆቻቸው ወንጌላዊት ፣ መለኮታዊት፣ ገሊላዊት እና ዮሐንስ ይባሉ ነበር። መንግሥቱን የወረሱት ዮሐንስ ሲኾኑ ጸሎተኛ ፣ ይቅርባይ ስለ ነበሩ ጻዲቁ ዮሐንስ ይባላሉ።

አኹን ባለንበት ዘመን በተመሳሳይ የፕሮቴስታንት አማንያን ይልቁንም የጴንጠቆስጤ አማንያን በኢትዮጵያ በመስፋፋታቸው ምክንያት በክርስትና በኢትዮጵያውያን ስሞች መጠራት ቀርቶ ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጠቀሱ ስሞች ላይ ብቻ ትግል በማድረግ ዅሉም በፍርሐት እና በሽቅድም ድም ወደዚያው ያተኰረ ይመስላል።

(ሀ) የሚያከራክሩ የክርስትና ስሞች

ከላይ እንደተገለጸው ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን የሚያከራክሯቸው ነጥቦች አሉ ፤ የመልአክትን ወይም የቅዱሳንን ስም ወሰዶ ያለቅጽል መጥራት ባለ ቤትነትን እንደመቀማት ወይም አንደ መውሰድ ይኾናል በማለት ሊቃውንተ

ቤተክርስቲያን ይናገራሉ። በአንዳንድ ሊቃውንት ዘንድ ያለ ቅጽል የተሰየሙ የክርስትና ስሞች አሉ ።

ስመ ክርስትና ሲሰየም በፈጣሪ፣ በስመ ቅዱሳን፣ በስመ መላእክት፤ በስመ ሰማዕታት ስም ቅጽል ተጨምሮበት ነው ። ያለቅጽል በቁሙ ስምን ብቻ መጥራት የኦርቶዶክሳውያን ባህል አይደለም። በቀጥታ ሚካኤል ፣ (ማይክል)፣ ገብርኤል፣ ጊዮርጊስ (ጆርጅ)፣ ማርያም (ሜሪ) ሌሎችም በነጠላ መጥራት የምዕራባውያን (የፕሮቴስታንት) ባህል ነው። ሚካኤል ተብለው የሚጠሩ ብዙዎች አሉ። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ **ንጉሥ ሚካኤል አሊ** አንዱ ናቸው። **የክርስትና አባታቸውም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ዮሐንስ** ነበሩ ይህንን ተከትሎ ሊኾን ይችላል ብዙ ሰዎች ሚካኤል የሚለውን በመጠሪያ ስምነትም ሲጠሩበት ይሰማል ። ገብርኤል ተብሎ ሲጠራ ግን ብዙ አይሰማም። በነጠላው ያለቅጽል ሚካኤል ፣ ገብርኤል ተብለው የሚሰየሙት ጻጻሳት ብቻ ናቸው ።

መሐልየ መሐልይ ዘሰሎሞን ወይም ከመዝሙር ጕሉ የሚበልጠው የሰሎሞን መዝሙር (መሐ. ዘሰ. 1፥1) በምሳሌነት የተሞላ ነው። በምሳሌነት የተነገረው ስለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ነው። **ዐፀደ ወይን ፣ አምሳለ ወርቅ ፣ አስካለ ወይን** (የወይን ፍሬ) በማለት ያነሳል ። እመቤታችን **ቅድስት ድንግል ማርያም በጽጌ፣ አበባ** ትመሰላለች። ምእመናንም ጽጌ፣ ጽዮን፣ አስካለ ፣ ዐፀደ ወይን ተብለው ይጠራሉ። ብዙዎች ምእመናን ሲጠሩበትም ኖረዋል።

ቅድስት ድንግል ማርያም የሚለው ስሟ ግን የባሕርይ ስሟ ነው። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ወላዲተ አምላክ ነች። ይህም የባሕርይ ስም ስለኾነ ቅጽል በመጨመር ካልኾነ ሊወረስና ሊጠሩበት አይገባም።

የክርስትናን ስም ሲጠሩበት ትርጉም የሚሰጥና አንደበትን ወይም አፍን ያዝ የማያደርግ በቅዱሳን መጻሕፍት መሠረት ምስጢር ሊገለጽ የሚችል ቅጽል ተጨምሮበት መሰየም አለበት።

ለምሳሌ መንበረ ፀሓይ ተብሎ ስም አይጠራም። ስመ መካን (**የቦታ ስም**) የአንጦሎ ማርያም የደብር መጠሪያ ስም ስለኾነ ለክርስትና የመጠሪያ ስም አይኾንም ። ሌላም መንበረ ጸባዖት ተብሎ አይሰየምም ። እንዲሁም ደግሞ **ስመ ሀገር** የክርስትና ስም ሊኾን አይገባም። **ወለተ እስራኤል፣ ወለተ ኢትዮጵያ** ፣ **ወለተ ቊስቋም** ተብሎ አይሰየምም።

መንበረ ማርያም ተብሎ ሊሰየም ግን ይችላል ። ሲጠሩት ስሜት የሚሰጥ፤ ምስጢርና ትርጉም ያለው ሊኾን ይገባል።

የመጠሪያ ስም ወላጆች መጠሪያ ስም ከሰየሙ በኋላ ከአርባና ከሰማኒያ ቀን ወይም በማንኛውም ጊዜ ለሚጠመቅ ከእግዚአብሔር ልጅነትን ለማረጋገጥ የተለየ የስም ስያሜ ይደረጋል። ካህኑና የክርስትና አባት ወይም እናት እንዲሁም ወላጆች ከተቻለ ተነጋግረው መርጠው ልጃቸው በስለት የተገኘ(ች) ከኾነ ስመ ክርስትና (የመጽሐፍ ስም) በመረጡት ቅዱስ ስም ይህ ይኹንልን ማለት ይችላሉ። የክርስትና ስም ከተሰየመ በኋላ ስምከ ይኩን... አገሌ ... አያለ የሚያውጀው ካህኑ ነው ።

የሕይወት መጽሐፍ ወይም የመጽሐፍ ስም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ የተመዘገበ ነው (ዘጸ.32፥32 ፤ ዳን.12፥1 ፤ ሉቃ.10፥20 ፤ ፊል.4፥3፤ ራእ.3፥5 ፤ 20 ፥12 ፤ 21፥27)።

የክርስትና አባትና እናት መኾን ከዝምድና ሐረግ ገብቶ ይቆጠራል። ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እና ለቲቶ የመንፈስ ቅዱስ አባታቸው እኔው ደግሞ ፍጹም ልጆቹ ነበሩ (2ኛ. ጢሞ. 2፥1) ።

ወላጆችም ይህንን ኀላፊነት የሚረከብ ሰው ልጁ ሳይወለድ በፅንስ ሳለ ይመርጣሉ ። ወይም በተዘዋዋሪው ዝምድናውን ወዳጅነቱን የፈለገ ቤተሰብ አስቀድሞ ክርስትናውን ለማንሳት እና ቤተ ዘመድ ለመኾን ዝምድናውን እንፈልገዋለን በማለት ቤተሰቡን መለመንና ፍቃዳቸውን መጠየቅም የተለመደ ነው። ወይም ባልና ሚስት ተመካክረው ምርጫ ያደርጋሉ ።

ወላጆች (ባልና ሚስት) ከወለዱ በኋላ ወንድ ወይም ሴት መኾኑን ካረጋገጡ ለመረጡት ሰው ክርስትናውን ይሰጣሉ ።

ክርስትናው የተሰጣቸው ሰዎችም ዝምድናውና ኀላፊነቱ የጋራ መኾኑን በመረዳት አክብረው በደስታ በመቀበል ሕፃኑ ሲጠመቅ ጣት በመያዝ **ከልጄ አለየውም፤ እንደ ልጄ አድርጌ አጠብቀዋለኹ ፤ ሃይማኖቴን አስተምረዋለኹ በማለት ቃል ኪዳን በእግዚአብሔር ፊት ይገባሉ።**
ሕፃኑ ከተጠመቀ በኋላ በገዙለት ዐዲስ እና ንጹሕ ፎጣ ጠቅለው ከካህኑ ተቀብለው ያቅፋሉ። ዝምድናውም ከሥጋዊ ዝምድና የበለጠ የሚኾን እንጂ አይተናነስም። በክርስትና ቤተሰብ የተሳሰረ በጋብቻም፣ በሌላ ነገር እንደ ሥጋዊ ዝምድና ዘር ይቆጠርለታል። በዚህ ዝምድና የተሳሰሩ ጕሉ ከሥጋዊ ዝምድና የበለጠ ስለኾነ መጥፎ ነገር አይተሳሰቡም።

የክርስትና አባትና እናት (አበልጅ) ከዝምድናው ባሻገር ዋና ዓላማው

ለሃይማኖቱ ጎላፊ በመኾን ሕፃኑ በሃይማኖት በእምነት እንዲያድግ ስማስ ተማር ጎላፊነትን ስመውሰድም ነው ። በዓመታዊ በዓላት ጊዜ ለልጇ ብሎ ዐዲስ ልብስ መግዛት ፤ ልዩ ልዩ ስጦታ መስጠት፤ ማፍቀር የአበ ልጅ ተግባር ነው። ልጆችም የክርስትና አባት ወይም እናት የሚያመጡላቸውን ፤ የሚያደርጉላቸውን በናፍቆትና በጉጉት ይጠብቃሉ። ይህ ሥርዐት ከቀድሞ ጀምሮ የክርስትና ወላጆች ሲያስተምሯቸው ስለ መልካም አስተዳደጋቸው ሲጠነቀቁላቸው፤ ባጠቃላይ ስለኑሯቸው ኹሉ ሲያስቡላቸው ይኖሩ ነበር።

የክርስትና አባትና እናት ክርስትና ያነሱትን ልጃቸውን በኦዛዜ ጊዜም እንኳን ከልጆቻቸው አይለዩዋቸውም ። ምክንያቱም በእግዚአብሔር አገል ጋዩ ካህን ቄስ ፊት ቃል ኪዳን ሲገባ ሕፃኑን ሲረከብ ፤ ከበኩር ልጅህ እን ዳትለይ ፣አስተምር፣ ዳር፣ ኳል ስለተባለ እሱም ቃል ኪዳን ስለገባ ይህንን ይፈጽማል ማለት ነው። ሕፃኑም ካደገ በኋላ የክርስትና አባቱን ልክ እንደ አባቱ አድርጎ ያከብራል፤ ትዛዙንም ይሰማል ። ይህ ከቀድሞ ጀምሮ ሲኖር ሲተካ አዚህ ደርሷል ማለት ነው።

በሌላ መልኩ ወላጆች በስለት የተወለደ ከኾነ ወይም ደግሞ ራሳ ቸው ሕፃኑን በሃይማኖት ለማሳደግ ጎላፊ ኾነው ለታቦት ይሰጥልኝ በታቦቱ ስም ይነሳልኝ ይላሉ። ይህም ማለት ቤተ ክርስቲያን እና ወላጆች ጎላፊነቱን ይወስዳሉ ማለት ነው ። ነገር ግን ከዚህ ይልቅ ወላጆች የክርስትና አባትና እናትን ቢመርጡ ዝምድናም ማጠንከር እንዲሁም ልጆችን በማሳደግ መረዳ ዳትም ቢኖር ጠቀሜታ ይኖረዋል ።

የክርስትና ስም ቅድሱ ከስሙ ተነጥሎም መጠሪያ ይኾናል ። ለም ሳሌ ገብረ እግዚአብሔር የተባለው ሰው በአጭሩ ገብሬ ፤ ሀብተ ማርያም የተባለው ደግሞ ሀብቴ ተብሎ ሊጠራ ይችላል ማለት ነው ።

አሥራ ኹለቱንም ወራት ከመስከረም ወር አንስቶ የወር በዐላት እና የዓመት በዐላት አሉ። በዚህ ጊዜ የተወለደ ወይም የሚጠመቅ ልጅ ዕለቱን በተመለ ከተ በማያያዝ ስም ይሰየምለታል ማለት ነው ። ስለዚህም በታሪክ ኢትዮጵያ ውያን ሲጠሩበት የኖሩት ስሞች ተሰብስበው ቀርበዋል ።

(ሐ) የወንዶች የክርስትና ስሞች

- ዕ -

ልደታ ማርያም ፣ ኢልያስ ፣ ዮሐንስ ፣ ራጉኤል

በመስከረም ፩ ዓውደ ዓመት

ራጉኤል፤ ሐዋርያው በርቶሌማዎስ፤ ኢል ያስ። ግንቦት ፩ ቅድስት ድንግል ማርያም ልደት ።

- ፩ -

ልደተ ዮሐንስ መጥምቅ፤ ታዴዎስ

መስከረም ፪ መጥምቁ ዮሐንስ አንገቱ የተሰየፈበት፤ በታኅሣሥ ፪ በስንክሳር እን ደተገለጸው ሠለስቱ ደቂቅ ከአሳት የዳኑ በት፤ እንዲሁም ሐዋርያ ታዴዎስ ይከ በራል።

መጥምቁ መለኮት
መጥምቁ ዮሐንስ

- ፫ -

በዐታ ለማርያም ፣ ፋኑኤል መልአከ ፣ ዜና ማርቆስ

አበው ቤተከ ምስለ መባዕየ ።
ወእሁብ ብፅዐትየ ዘነበብኩ በአፋየ ።
ትርጉም፤ ከመባ ጋር ወደ ቤትህ እገባለኹ። በመከራዬ ጊዜ በእፈ የተናገርኩትን ። ከንፈሮ ቼም ያሉትን ስእለቴን (መዝ. 95፤13)።
ታኅሣሥ ፫ በዐታ ለማርያም ፤ ፋኑኤል አብሮ ይከበራል ።

ብፅዐተ ማርያም
ስብሐተ ፋኑኤል

- ፬ -

ዮሐንስ ወንጌላዊ (ወልደ ነጐድጓድ)

ወተመይጦ ጴጥሮስ ርእየ ለዝኩ ረድእ ዘያፈ ቅር እግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይተልዎ፤ ውእቱ ረድእ ፤ ትርጉም ፤ ጴጥሮስም መለስ ብሎ ያን ጌታ ኢየሱስ ይወደው የነበረውን ደቀ መ ዝሙር ሲከተለው አየ (ዮሐ. 21፤20፤ 13፤23)።

ጥር ፬ ሐዋርያው **ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓ ድ** ፤ ታኅሣሥ ፬ ሐዋርያው **እንድርያስ** ይከበራል ።

ብርሃነ ዮሐንስ – መዝገበ ዮሐንስ
ተስፋ ዮሐንስ – ተክለ ዮሐንስ
አርአያ ዮሐንስ

ከፍለ ዮሐንስ
ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ሳልሣዊ 1921 -1993 ዓ.ም. የነበሩት ከጵጵስና በፊት በስመ ጥምቀታቸው **ከፍለ ዮሐንስ** በመባል ይታወቁ ነበር። የወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ነበሩ።

ወልደ ዮሐንስ
መልአከ ብርሃናት ወልደ ዮሐንስ በቦሩ ሜዳ ከሦስት ልደት ባዮች ጋር ይከራከ ሩት ከነበሩት አንዱ በስመ ጥምቀታቸው ወልደ ዮሐንስ በመባል ይታወቃሉ ።

ወምደ ዮሐንስ

ወርክ ዮሐንስ
አጨጌ ወርክ ዮሐንስ ዘሰጋ (1814 - 1815 ዓ.ም.) በስም ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

ወ.ከ

ዐስበ ዮሐንስ
ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ቀዳማዊ (1933 -1991 ዓ.ም.) የነበሩት ከጵጵስና በፊት **ዐስበ ዮሐንስ** በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይታወቁ ነበር ። የምዕራብ ሀረርጌ አንዲኹም የወለጋ ሀገረ ስብከትሊቀ ሊቀ ጳጳስ ነበሩ።

ዘዮሐንስ – ገብረ ዮሐንስ

ሐዋርያት

ወይቤሎሙ አግዚእ ኢየሱስ ንዑ ትልዉኒ ፤ ወአሬስየክሙ ትኩኑ መሠግራነ ሰብእ።
ትርጉም ፤ ጌታ ኢየሱስ ኑ ተከተሉኝ ፤ ሰውንም የምታጠምዱ አንድትኹኑ አደርጋችኋለሁ አላቸው (ማቴ.4፤19 ፤ ማር.1፤16 ፤ ሉቃ.5፤1)።

በኩረ ሐዋርያት

ተክለ ሐዋርያት
አቡነ **ተክለ** ሐዋርያት በ14ኛው መቶክ ፍለ ዘመን የነበሩ አበምኔት በስመ ጥምቀ ታቸው ይጠሩ ነበር።

ተስፋ ሐዋርያት
አቡነ **ተስፋ** ሐዋርያት በ14ኛው መቶክ ፍለ ዘመን የነበሩ አበምኔት በስመ ጥምቀ ታቸው ይጠሩ ነበር።

ክፍለ ሐዋርያት

ወልደ ሐዋርያት
አጨጌ **ወልደ** ሐዋርያት በስመ ጥም ቀታቸው ይጠሩ ነበር (1695 -? ዓ.ም)

ዐርከ ሐዋርያት – ዜና ሐዋርያት

- ሯ -

ጴጥሮስ ወጳውሎስ ገብረ መንፈስ ቅዱስ

መጋቢተጾ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ (አቦ) ያረፉበት ዕለት ነው።
ሐምሌ ፮ ጴጥሮስ ወጳውሎስ፤ ሰማዕት የኾኑበት፤

ሠርፀ ጴጥሮስ
በቀዳማዊ ዳዊት (1374 ዓ.ም.) ዘመን በደብረ ወርቅ ቅድስት ማርያም የገዳሙን ሥርዓት ያጸኑትና የቆረቆሩ አባ **ሠርጸ ጴጥሮስ** በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

ገብረ መንፈስ ቅዱስ

ገብረ አብ ፣ ገብረ ወልድ ፣ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እንደሚባለው ኹሉ በስመ ጥምቀት **ገብረ መንፈስ ቅዱስ** መጠሪያ ኾናቸው።

ገብረ መንፈስ ቅዱስ
የመንፈስ ቅዱስ አገልጋይ ማለት ነው።
በዚህም የተጠሩት አቡነ **ገብረ መንፈስ ቅዱስ** በኢትዮጵያ ምድር በዙ ዘመን ቢጸልዩ ኖረው መጋቢት 5 ቀን 1374 ዓ.ም. ዐረፉ።

ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ (1868 -1925 ዓ.ም.) የነበሩት ከጵጵስና በፊት በስመ ጥምቀታቸው **ገብረ መንፈስ ቅዱስ** በመባል ይታወቁ ነበር ። ማኅደረ ሰብሐት ልደታን ያሠሩ ናቸው።

መዓዛ ሕይወት - ማኅደረ ሕይወት
በረከተ ሕይወት - ብርሃነ ሕይወት

ገብረ ሕይወት – ወልደ ሕይወት
ዘመንፈስ ቅዱስ – ዘመንፈስ
የማነ ሕይወት – ፈለገ ሕይወት

- ኌ -

ኢየሱስና ቊስቋም ማርያም

ወአመ ተፈጸመ ሰሙን ዕለት ወወሊድዮ ለሕፃን ዘመ ይግዝርዎ ፤ ወሰመይዎ ስሞ ኢየሱስ በከመ ሰመዮ መልአክ እምቅድመ ትፀንሶ ትርጉም ፤ ስምንት ቀን በተፈጸመ ጊዜም ሕፃኑን ሊገዝሩት ወሰዱት ሳትፀንሰው መልአኩ አንዳወጣለትም ስሙን ኢየሱስ አሉት (ሉቃ .2፤21 ፤ ም.1፤31 ፤ ማቴ. 1፤28)።
ጥር ፮ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ በስምንተኛው ቀን ግዝረት። ጎዳር ፮ ቅድስት ድንግል ማርያም በግብፅ ተሰዳ ደብረ ቊስቋም የገባችበት ዕለት ነው።

ሀብተ ኢየሱስ (ሀብተየስ)
መርሐ ኢየሱስ

ሠምረ ኢየሱስ
በ16 ኛው ምእት መጀመሪያ በገሙ ጎፋ ብርብር ማርያም የነበሩ ካህን ሰምረ ኢየሱስ በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይታወቃሉ።

በረከተ ኢየሱስ – ብርሃነ ኢየሱስ

ተስፋ ኢየሱስ
በስማቸው እና በስመ መንግሥታቸው ይኩኖ አምላክ (በ1263 –1277 ዓ.ም) ተብለው የሚታወቁት ኢትዮጵያዊ ንጉሥ የክርስትና ስማቸው **ተስፋ ኢየሱስ** ይባል ነበር ።

ተክለ ኢየሱስ (ተክለየስ)
ነገደ ኢየሱስ – ጎይለ ኢየሱስ

ንዋየ ኢየሱስ
አቡነ **ንዋየ** ኢየሱስ በ15ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ አበምኔት በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

አምኃ ኢየሱስ (አምኃየስ)
ዐሥራተ ኢየሱስ

ዐምደ ኢየሱስ
በዚህ ስም 1425 ዓ. ም. የኢትዮጵያ ንጉሥ የነበሩት **ዐፄ ዐምደ ኢየሱስ** ተጠርተውበታል ።

ወልደ ኢየሱስ (ወልደየስ)
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ ክፍል ጎሳፊ የነበሩት አለቃ አያሌው ታምሩ በጥምቀተ ክርስትና ስማቸው **ወልደ ኢየሱስ** ይባሉ ነበር።

ክፍለ ኢየሱስ
የራስ ሚካኤልና የወይዘሮ ስኂን **ልጅልጅ** ኢያሱ በስመ ጥምቀታቸው **ክፍለ ኢየሱስ** በመባል ይታወቁ ነበር።
ዘኢየሱስ

ገብረ ኢየሱስ
አጨጌ **ገብረ** ኢየሱስ ዘናበጋ በስም ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።
ፍቅረ ኢየሱስ – ፍሬ ኢየሱስ

- ኗ -

በዓለ ሥላሴና ጽንሰታ ለማርያም

በቀትርም ጊዜ አብርሃም በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ ያድባር ዛፍ ተገለጠለት (ዘፍ. 18፤1) ።

ወ.ክ

ሐምሌ ፯ አምላክ ለአብርሃም እግዚአ ብሔር አምላክ በአንድነት በሦስትነት የተ ገለጸበት ዕለት ነው ።
ነሐሴ ፯ ቅድስት ድንግል ማርያም የተፀ ነሰችበት ዕለት ነው።

ህብተ ሥላሴ – መብዐ ሥላሴ
መዐዛ ሥላሴ

መዝገበ ሥላሴ
ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልአይ (1932-1982 ዓ.ም.) ክቷቷሰና በፊት በስመ ጥም ቀታቸው መዝገበ ሥላሴ በመባል ይታወቁ ነበር ።

ማኅተመ ሥላሴ – ምክረ ሥላሴ

ሣህለ ሥላሴ
የንጉሥ ጎይለ መለኮት አባት ንጉሠ ሸዋ ሣህለ ሥላሴ ይባሉ ነበር።

ሰርጎ ሥላሴ – በረከተ ሥላሴ
ብርሃነ ሥላሴ – ተስፋ ሥላሴ
ተክሥተ ሥላሴ

ተክለ ሥላሴ
በዚህ ስም የካቶሊኮችን እና የዐፄ ሱስን ዮስን ታሪክ የጸፉ ተክለ ሥላሴ ጢሮ ተ ጠርተውበታል (ያረፉበት ዘመን 1630 ዓ. ም. ነው)።

ጎይለ ሥላሴ
በዚህ ስም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት የመጠሪያ ስማቸው ተፈሪ ፤ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ተጠርተውበታል። የተወለዱ በትም ሐምሌ16 ቀን 1884 ዓ.ም. ነበር።

ጎሩየ ሥላሴ — አምኃ ሥላሴ

አርአያ ሥላሴ
የዐፄ ዮሐንስ አናት የወይዘሮ ሥላሰ ወን ድም ራስ አርአያ ሥላሴ በዚህ ስም ይ ጠሩና ይታወቁ ነበር።
የአፄ ዮሐንስም ልጅ ራስ አርዓያ ሥላሴ ዮሐንስ ተብለው ይጠሩ ነበር

አለምሮ ሥላሴ – አካለ ሥላሴ
ወልደ ሥላሴ – ውሂበ ሥላሴ

ዐምደ ሥላሴ
በዐፄ ሱስንዮስ ዘመን 1590 ዓ.ም. ማኅበረ ሥላሴ ገዳምን የመሠረቱ ሰው በስመ ጥምቀታቸው አባ ዐምደ ሥላሴ ተብለው ይጠሩ ነበር።

ዐሥራቱ ሥላሴ – ዕንቁ ሥላሴ
ቤና ሥላሴ – ዘሥላሴ

ገብረ ሥላሴ
አጨጌ ገብረ ሥላሴ ዘጎርፎ በስም ጥም ቀታቸው ይጠሩ ነበር።

ጥበበ ሥላሴ — ፈቃደ ሥላሴ
ፍቅረ ሥላሴ — ፍሬ በብሐት

<u>ልደተ ሐናና ዕረፍተ ኢያቄም</u>
መሠረታቲሃ ውስተ አድባር ቅዱሳን።
ትርጉም ፤ መሠረቶቹ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው (መዝ. 86፥1)።

በትረ ሐና – ወልደ ሐና
ጽጌ ሐና

ገብረ ሐና
የዐፄ ኃይለ ሥላሴ የቀድሞ ባለሥልጣናት ከነበሩት አንዱ አባ ገብረ ሐና በዓለም መጠሪያ ስማቸው ጂግ ይባሉ ነበር።

ስምና ወርቅ ንግግር ዘመናገር ጠቢብ የነበ ሩት አስቻ ገብረ ሐና ገብረ ማርያም በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር

- ፐ -

ልደተ ስምዖንና አባ ኪሮስ
ወሀሎ አሐዱ ብእሲ በኢየሩሳሌም ዘስሙ ስምዖን ፤ ወውእቱ ጻድቅ ወየዋህ፤ ወይሴፎ ይርአይ ፍስሓሆሙ ለእስራኤል ፤ መንፈስ ቅዱስ ላእሌሁ ።
ትርጉም ፤ በኢየሩሳሌም ስሙ ስምዖን የሚ ባል አንድ ሰው ነበር ፤ እሱም ጻድቅ ደግ ሰው ነበር ። የእስራኤልን ደስታቸውን ሊያይ ተስፋ ያደርግ ነበር ። መንፈስ ቅዱስም ያደረ በት ነበር (ሉቃ. 2፥22)።

የካቲት ፳ ጌታ ከተወለደ ፵ ቀናት ሲኞ ነው ወደ ቤተ መቅደስ ሲወሰድ ይጠባበቀ ው የነበረው አረጋዊ ስምዖን
ሰኔ ፳ በግብፅ ስደት ላይ ሳሉ ከዐስት ድንጋይ ጠበል ያፈለቀበት ዕለት ነው
መጋቢት ፳ ሐዋርያው ማትያስ ። ጎዳር ፳ አፍኒንና (ሊቃነ መላእክት) ዐርባዕቱ እንስሳ የሚከበሩበት ነው።

- ..ፗ -

የቅዱሳንና የሰማዕታት፣ ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ የክብር ቀን ነው።

- ፐ -

በዐለ መስቀል ብርሃን
(መስቀለ ኢየሱስ)

እነ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም ፤ ዘተለወኒ ኢየሐ ውር ውስተ ጽልመት ፤ አላ ይረክብ ብርሃነ ሕይወት

እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝም ጕሉ የሕይወት ብርሃን ይኾንለታል (ዮሐ. 8፥12)።

መስከረም ፲ በዐፄ ዳዊት ግማደ መስቀል ወደ ኢትዮጵያ የገባበት ቀን ፤ ዔዴንያ በምትባለ ሀገር በማርታ ቤት ቅዱስ ሉቃስ የሣላት ሥዕለ ቅድስት ድንግል ማርያም ተአምራት የታየበት
ቀን ነው። የካቲት ፲ ሐዋርያው ያዕቆብ ወልደ ኤልፍዮስ ። ሐምሌ ፲ ሐዋርያው ናትናኤል ይከበራል።

ሐዋዘ ብርሃን – ምጣኔተ ብርሃን

ሠረቀ ብርሃን
የደብረ ሐይቅ እስጢፋኖስ ዓቃቤ ሰዓት **ሠረቀ ብርሃን** (1365 -1404 ዓ.ም.)በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

ተክሥተ ብርሃን
አቡነ ተክሥተ ብርሃን በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ አበምኔት በስመ ጥም ቀታቸው ይጠሩ ነበር ።

ተክለ ብርሃን

ተወልደ ብርሃን
ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ካልአይ ክቷቷሰና በፊት በስመ ጥምቀታቸው ተወልደ ብር ሃን በመባል ይታወቁ ነበር።

ነገደ ብርሃን – አንቀጸ ብርሃን
ዐምደ ብርሃን

አክሊለ ብርሃን
በዚህ ስም የሚታወቁ መርሐ ልቡና የተባ ለውን መጽሐፍ የጸፉ አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ ናቸው።

ወልደ ብርሃን

ወ.ክ

ዘፈረ ብርሃን
ወደ ግብጽ ኼደው ጵጵስና ከተሾሙት አ ምስቱ ጳጳሳት አንዱ የነበሩት አቡነ ያዕ ቆብ ዘፈረ ብርሃን በመባል በስመ ጥምቀ ታቸው ይጠሩ ነበር።

የግነ ብርሃን
የትግሬ አጨጌ የነበሩት የግነ ብርሃንበመ ባል በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

- ፲፩ -

ጥምቀተ ክርስቶስ፣ ቅድስት ሐና፣ ቅዱስ ያሬድ
አሜሃ መጽአ እግዚእ ኢየሱስ እምገሊላ ውስ ተ ዮርዳኖስ ፤ ከመ ይጠመቅ እም ዮሐንስ። ትርጉም ፤ በዚያን ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ከዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ (ማቴ.3፥ 3፤ ማር.1፥9፤ ሉቃ.3፥21 ፤ ዮሐ.1፥31)።

ጥር ፲፩ ቀን መጥምቀ መለኮት የተባለው የዘካርያስና የኤልሳቤጥ ልጅ ጌታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስን ያጠመቀበት ዕለት ነው።

መጥምቀ መለኮት — ብርሃነ መለኮት

ተጠምቀ መድኅን
በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ገዳም አበምኔት ኾነው የተሾሙ በስመ ጥምቀታቸው አባ ተጠምቀ መድኅን ተብ ለው ይጠሩ ነበር (1474 - ?ዓ.ም.)።

ኀይለ መለኮት
የመለኮት ኀይል ማለት ነው።
የዐፄ ምኒልክ አባት ፤ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ልጅ ፤ የሸዋው ንጉሥ ኃይለ መለ ኮት በመባል ተጠርተውበታል፤

(ሕዳር 1 ቀን 1848 ዓ.ም. የረፍታቸው መታሰቢያ ቀን ነው።)

ወረደ ቃል — ወረደ ወልድ

- ፲፪ -

ቅዱስ ሚካኤል
የእግዚአብሔር ሰራዊት አለቃ ኾኖ አኹን መ ጥቻለሁ አለ። ኢያሱም ወደ ምድር በግንባሩ ተደፍቶ ሰገደ ።
(ኢያ.5፥14 ፤ ዳን.10፥13፤ ይሁ. 9፤ ራእ.12፥7)

ጎዳር ፲፪ ቅዱስ ሚካኤል አስራኤላውያ ንን የረዳ። ስኢያሱ የተገለጸበት እየመራ ወደ ቃል ኪዳኗ አገር ያስገባበት ቀን ነው ። ቅዱስ ሚካኤል በየወሩም ተአ ምር ሰርቷል።
ጥር ፲፪ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገ ሊላ ቃና ውሃውን ወደ ወይን የለወጠበት የመጀመሪያ ተአምራቱን ያደረገበት ነው። ጥቅምት ፲፪ ሐዋርያው ማቴዎስ ነው

ሀብተ ሚካኤል — መዝገበ ሚካኤል
ሠምረ ሚካኤል — ሠርጸ ሚካኤል
ሣህለ ሚካኤል — ሥሁል ሚካኤል
ሰርጎ ሚካኤል — ስበሐተ ሚካኤል
በጸሎተ ሚካኤል

ተሰፋ ሚካኤል
ለቤተክርስቲያን ጠቀሜታ የሰጡትን ቅዱሳ ት መጽሐፍትን በማተሚያ ቤታቸው ሲያ ትሙ የኖሩት ቀኞኛማች ተሰፋ ገብረ ሥላሴ ስመ ጥምቀታቸው ተሰፋ ሚካ ኤል ይባል ነበር።

ተክለ ሚካኤል — ነገደ ሚካኤል

ጎይለ ሚካኤል
ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ቀዳማዊ የጣሊያ ንን ወረራ በመቃወም እንኳን ሕዝቡ ምድሪቱ እንዳትገዛላችሁ ብለው ያወገዙ ናቸው ። ጎዳር 21 ቀን 1928 ዓ. ም በሰ ማዕትነት ዐረፉ ። ስመ ጥምቀታቸው ኃይለ ሚካኤል በመባል ይታወቃል ።

ዐምደ ሚካኤል — ዐሥራተ ሚካኤል

ክንፈ ሚካኤል
ንግሥት ምንትዋብ (ከምልምል ኢያሱ) የተወለደ የልጅ ልጅ ክንፈ ሚካኤል በመ ባል በስመ ጥምቀቱ ይታወቅ ነበር።

ወልደ ሚካኤል
ዐፄ ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው በአክሱም ጽዮን በአቡነ አትናቴ ዎስ ቅብዓ መንግሥት ተቀብተው የነገሡ ንጉሥ ናቸው። ስመ ጥምቀታቸው ወልደ ሚካኤል ነበር።
በኢየሩሳሌም ታላቁን የገዳም ቦታ ደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረትን ለማሳነጽ የጀመሩ ናቸው።

ዘሚካኤል
ጥቅምት ፲፪ ኢትዮጵያ ከገቡት ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ አቡነ አረጋዊ ዘሚካኤል ይባሉ ነበር ።

ፀምረ ሚካኤል
ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ካልአይ 1885 -1959 ዓ.ም. የነበሩት ከጵጵስና በፊት በስመ ጥምቀታቸው ገብረ ሚካኤል በመባል ይታ ወቁ ነበር። የጋሞ ጎፋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ነበሩ።

- ፲፫ -

እግዚአብሔር አብ
(በዓለ እግዚአብሔር ፤ ባለ እግዚሐር)

መጽአ ደመና ብሩህ ወጸለሎሙ ወናሁ መጽአ ቃል እምውስተ ደመና ዘይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ዘቦቱ ሠመርኩ ወሎቱ ስምዕዎ።
ትርጉም ፤ ደመናም መጥቶ ጋረዳቸው ፤ የም ወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት የሚል ድምጽ መጣ (ማቴ. 17፥1 ፤ ማር. 9፥7 ፤ ሉቃ. 9፥28)።
ነሐሴ ፲፫ በደብረ ታቦር (በታቦር ተራራ) ላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ብርሃነ መለኮቱን የገለጸበት ዕለት ነው።

መሠረተ አብ — መንግሥተ አብ
መዝራኢተ አብ

ሠምረ አብ
አቡነ ሠምረ አብ በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ አበምኔት በስመ ጥምቀታ ቸው ይጠሩ ነበር።

ሥምረተ አብ — ስብሐተ ለአብ
በረከተ አብ — ተክለ አብ
ነአኩቶ ለአብ — ነጸረ አብ

ገብረ አብ
ብፁዕ አቡነ ሬልጰስ ቀዳማዊ (1888 - 1974 ዓ.ም.) የኢየሩሳሌም ሊቀጳጳስ ነበሩ ከጵጵስና በፊት በስመ ጥምቀታቸው ገብረ አብ በመባል ይታወቁ ነበር።

ገብረ እግዚአብሔር
በሊቀጵጵስና ስማቸው ብፁዕ አቡነ መርቆ ሬዎስ ካልአይ (1888 - 1968 ዓ.ም.) በቀ ድሞ ስማቸው በስመ ጥምቀታቸው አባ ገብረ እግዚአብሔር ተብለው ይጠሩ ነበር

ገብረ ዋሕድ – የማነ አብ

ጸጋ ዘአብ
የጻድቁ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት አባት ጸጋ ዘአብ በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር ።

- ፲፬ -

አረጋዊና ገብረ ክርስቶስ

ወዘተወለደ ጻድቅ በስመ ጸድቅ ዐበይ ጸድቅ ይነሥእ። ትርጉም I እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላልI ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነ ቢይን ዋጋ ያገኛል። ጸድቅን በጸድቅ ስም የሚ ቀበል የጸድቁን ዋጋ ይወስዳል (ማቴ. 10፥40 I 18፥5 I ሉቃ. 10፥16 I ዮሐ. 13)።

ጥቅምት ፲፬ ኢትዮጵያ ከገቡት ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ አቡነ አረጋዊ (ዘሚካኤል) የሚከብሩበት ዕለት ። እንዲሁም ደግሞ የንጉሥ ቈጶዶስዮስ ልጅ ጻድቁ ገብረ ክር ስቶስ የሚከበሩበት ዕለት ነው።

መዝገበ አረጋዊ (አረጋይ)
ሠርጸ አረጋዊ – ተክለ አረጋዊ

ወልደ አረጋዊ (አረጋይ)
በዚህ ስም የአውሮፓው ሊቀ ጳጳስ የነበ ሩት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ከመባላቸው በፊት ተጠርተውበታል። አባ አረጋዊ ተብ ለው በመጀመሪያ በእንግሊዝ አገር በለን ደን ከተማ ደብረ ጽዮንን ያቋቋሙ አባት ናቸው።
መስከረም 1 ቀን 1932 ዓ. ም. ከተሾሙት ሊቃነ ጳጳሳት አንዱ ብፁዕ አቡነ ቄር ሎስ በስመ ጥምቀታቸው መምህር ወልደ አረጋይ ተብለው ይጠሩ ነበር።

ዘአረጋዊ
ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ አቡነ አረጋዊዘሚ ካኤል ተብለው በስመ ጥምቀታቸው ይታ ወቃሉ ።
ገብረ አረጋዊ

- ፲፭ -

አስጢፋኖስና ቂርቆስ ወኢየሉጣ

ወአሕለፍከነ ማዕከለ አሳት ወማይ።
ወአውፃእከነ ውስተ ዕረፍት።
ትርጉም I በእሳትና በውሃ መካከል አለፍን። ወደ ዕረፍት አመጣኸን (መዝ. 65፥12)።

አክሊለ ሰማዕት – ወልደ ቂርቆስ
አክሊለ አስጢፋኖስ - ፍቅረ ሰማዕት

ወልደ ሰማዕት
በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ገዳም በአበምኔት ኾነው የተሾሙ መም ህር ወልደ ሰማዕት በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር ። ከወዴ ዮሐንስ በተላከው ወርቅ ደብረ ጌንት ኪዳነ ምሕረትን በኢየ ሩሳሌም አሰርተዋል።

- ፲፮ -

ኪዳነ ምሕረት

አስመ ትቤ ለዓለም አሐንጽ ምሕረተ።
በስማይ ጸንዐ ጽድቀክ ። ኪዳነ ተካየድኩ ምስለ ጎሩያንየ።
ትርጉም I ምሕረትህ ለዘላለም ይመሠረታል ብለሃልና። እውነትህም በሰማይ ይጸናል። ከመረጥኩት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ (መዝ. 88፥2)።
ኑሐሴ ፲፮ የቅድስት ድንግል ማርያም ፡ሥጋ ትንሣኤና ዕርገት። የካቲት ፲፮ ቅድ ስት ማርያም ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰሟን ለጠራI መታሰቢያዋን ያዘከረ I ቃል ኪዳኑን የሰጠበት ኣሷም የአማላጅ ነት ሥልጣን የተቀበለችበት ዕለት ነው።

መዝገበ ኪዳን – ምሕረተ ኪዳን
ሠምረ ኪዳን – ተሰፋ ኪዳን
ተክለ ኪዳን

ኪዳነ ማርያም
ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ሣልሳይ (1938 - 19 91 ዓ.ም.) በደቡብ አሞ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ነበሩ። ከድጽሰና በፊት በስመ ጥምቀታቸው ኪዳነ ማርያም በመባል ይታ ወቁ ነበር።

ኪዳነ ቃል

ኪዳነ ወልድ
የመጽሐፈ ሰዋስው ወግስ መዝገበ ቃላት ደራሲ አለቃ ኪዳነ ወልድ ከፍሌ ቤተ ተክለሃይማኖት (1837 ዓ.ም. ተወለዱ) በስመ ጥምቀታቸው ኪዳነ ወልድ በመባል ይታወቁ ነበር።

ገብረ ኪዳን
መስከረም 1 ቀን 1932 ዓ. ም. ከተሾሙት አንዱ የኾኑት ብፁዕ አቡነ ገብርኤል የጎ ንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ መምህር ገብረ ኪዳን በመባል ይታወቁ ነበር።

ወልደ ኪዳን – ፍቅረ ኪዳን

- ፲፯ -

በዓለ መስቀልና ቅ. አስጢፋኖስ

መስከረም ፲፯ ጠፍቶ የነበረውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ንግሥት እሌኒ አስፈልጋ ያስገኘችበት ቀን ጥቅምት ፲፯ ሰማዕቱ ቅዱስ አስጢፋኖስI ሚያዚያ ፲፯ ሐዋርያው ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ ይከበራል።

መስቀል ዕበይ — በትረ መስቀል

ብርሃነ መስቀል
በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ገዳም አበምኔት ኾነው የተሾሙበስመ ጥ ምቀታቸው አባ ብርሃነ መስቀል ተብለው ይጠሩ ነበር (1574 - ? ዓ.ም)።

ተሰፋ መስቀል
በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ገዳም አበምኔት (1915-1919 ዓ.ም) ኾነው የተሾሙ በዓለም ስማቸው ይርዳው የሚ ባሉ በስመ ጥምቀታቸው አባ ተሰፋ መስ ቀል ተብለው ይጠሩ ነበር።

ጎይስ መስቀል
ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ካልኣይ (1919- 19 96 ዓ.ም.)የኢየሩሳሌም ሊቀጳጳስ ነበሩ። ከድጽሰና በፊት በስመ ጥምቀታቸው ሊቀ ሊቃውንት ጎይስ መስቀል በመባል ይታ ወቁ ነበር።

ወልደ መስቀል
የብላቴ ጌታ ማኅተመ ሥላሴ አባት ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ታረዙ በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር ።

በምደ መስቀል

ገብረ መስቀል
ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ካልኣይ የነበሩት ከድ ጽሰና በፊት በስመ ጥምቀታቸው ገብረ መስቀል በመባል ይታወቁ ነበርየትግራይ ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ ነበሩ። (1887 - 1983 ዓ.ም.)

የዐፄ ካሌብ ኹለተኛ ልጅ ዐፄ ገብረ መስ ቀል በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር::

ወ.ክ

በዚህ ዘመን ቅዱስ ያሬድ የተነሳበት ድን የተደረሰበት ጊዜ ነበር I ኢትዮጵያን ከ527 እስከ 572 ዓ.ም. በንግሥና መርተዋል ።

- ፲፫ -

ፊልጶስ ሐዋርያና

ዝርወተ ዐፅሙ ለቅዱስ ጊዮርጊስ

ወእጽዋንከ ሰብእ ዲበ አርእስቲሃ።
አኅለፍከነ ማእከለ እሳት ወማይ ። ወአውጻዕከነ ውስተ ዕረፍት።
ትርጉም I በራሳችን ላይ ሰውን አስረገጥኸን። በእሳትና በውሃ መካከል አለፍን ። ወደ ዕረፍትም አወጣኸን። (መዝ. 65፥12)
ጎዳር ሐዋርያው ፊልጶስ ይከበራል ።
ሐምሌ ያዕቆብ የጌታ ወንድም ፣

ዐፅመ ጊዮርጊስ

- ፲፱ -

ቅዱስ ገብርኤል

አነ ውእቱ ገብርኤል ዘአቀውም ቅድመ እግዚአብሔር I
ትርጉም I እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ (ሉቃ. 1፥19)።

ሀብተ ገብርኤል – መዝገበ ገብርኤል
ሞጣሕተ ገብርኤል – ሥነ ገብርኤል
ስብሐተ ገብርኤል - ብርሃነ ገብርኤል
ብሥራተ ገብርኤል
ተአምረ ገብርኤል
ጎይለ ገብርኤል – አምኃ ገብርኤል

ክንፈ ገብርኤል

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ አባል ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አለታዬ በስመ ሞም ቀታቸው ይጠራሉ።

ወልደ ገብርኤል – ውሂበ ገብርኤል
ዐምደ ገብርኤል - ዐሥራተ ገብርኤል
ዜና ገብርኤል – ዘገብርኤል
ዘመልአክ

- ፳ -

ሕንጸታ

ደብረ ጽዮን ዘእፍቀረ I ሐነጸ መቅደሶ በእር ያም። ወሣረራ ውስተ ምድር ዘለዓለም።
ትርጉም I የወደደውን የጽዮንን ተራራ ። መቅደሱን እንድ እርያም ሠራ። ለዘላለም በም ድር ውስጥ መሠረታት (መዝ. 77፥69)።

በኔ ፳ ቀን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያት በማርያም ስም የተቀደሰውን ቤተ ክርስቲያን የሠሩበት ዕለት ነው። ሕንጸታ በኔ ፳፩ ቀን የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያን የተቀደሰበት ዕለት የሚከበርበት ነው።

- ፳፩ -

ቅድስት ድንግል ማርያም

ናሁ አምይእዜሰ ያበተበጽዑኒ ኩሉ ትውልድ ትርጉም I እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ኹሉ ያመሰግኑኛል (ሉቃ. 1፥48 I 11፥27) ።

ጥር ፳፩ አስተርእዮ I ቅድስት ድንግል ማርያም ያረፈችበት ዕለት ነው።
መስከረምና ጎዳር ዕረፍቷን ለማሰታወስ ይከበራል ። በጎዳር ወር የታቦተ ጽዮን በዐል ። ታጎሣሥ፣ የካቲት፣ መጋቢት ፣ ሚያዚያ፣ ግንቦት፤ ሐምሌ ዕረፍቷን ለማ ስታወስ ይከበራል ። ከግንቦት ፳፩ ቀን እስከ ፳፩ ግብፅ ሀገር በደብረ ምጥማቅ ብርሃን ወርዶ ለስነበር በዓል ይደረግላታል ሐምሌ ፳፩ ቀን ዑራኤል (ሊቃነ መላእክት) ይከበራል።

ሀብተ ማርያም

በጽድስና ስማቸው አቡነ መልከ ጼዴቅ ቀዳማዊ ከጽድስና በፊት ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

ላእከ ማርያም

ሣህለ ማርያም

አፄ ምኒልክ ነሐሴ 12 ቀን 1836 ዓ. ም. ሰሜን ሸዋ አንጎለላ ተወለዱ I በአርባ ቀናቸው አንጎለላ ኪዳነ ምሕረት ሣህለ ማርያም በሚል ስመ ጥምቀተ ክርስትና ተሰጣቸው ።

ሥነ ማርያም – ሰበነ ማርያም
ቀጸላ ማርያም – በትረ ማርያም

በእደ ማርያም

የዐፄ ዘርአ ያዕቆብ የመጀመሪያ ልጃቸው (1416 –1471 ዓ.ም.) በስመ ጥምቀታቸው በእደ ማርያም ተብለውይጠሩ ነበር። የነገሡበት ዕለት ጽጉሜ4 ቀን 1460 ዓ.ም. ነበር።

ቤተ ማርያም – ተሰፋ ማርያም
ተአምረ ማርያም

ተክለ ማርያም

ብፁዕ አቡነ አቡነ ያዕቆብ ካልአይ (1917 – 1996 ዓ.ም.) ወደ ኤርትራ በመ ኼድ ፓትርያርክ ኾነው ነበር። ከጽድስና በፊት በስመ ጥምቀታቸው ተክለ ማርያም በመባል ይታወቁ ነበር።

ጎይለ ማርያም

ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቀዳማዊ ከጽድስና በፊት በስመ ጥምቀታቸው ጎይለ ማርያም በመባል ይታወቁ ነበር። የጣሊያንን ወረራ ስላወገዙ ከዐርበኞች ጋር በግራዚያኒ ትዕዛዝ በመገደላቸው ሰማዕት ኾነው አልፈዋል ። ሐውልትም ቆምላቸዋል።

ጎሩየ ማርያም

ንዋየ ማርያም

ስመ መንግሥቱ ወድም ረዓድ (1364 – 1374 ዓ.ም.) የነበረው የኢትዮጵያ ንጉሥ ዐፄ ንዋየ ማርያም በስመ ጥምቀታቸው ተጠርተዋል ።

አምኃ ማርያም – አክሊለ ማርያም
ኪዳነ ማርያም – ክፍለ ማርያም

ወልደ ማርያም

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ I ከጽድስና በፊት በመጠሪያ ስማቸው መልአከቱ ሲባሉ I በስመ ጥምቀታቸው ወልደ ማርያም በመባል ይታወቁ ነበር ።

ውሂበ ማርያም

ዐምደ ማርያም

የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የልጅ ልጅ የበእደ ማርያም ወንድ ልጅ ዐምደ ማርያም በመ ባል በስመ ጥምቀቱ ይጠራ ነበር።

ዐሥራት ማርያም – ዘማርያም
ዘፈረ ማርያም – ዜና ማርያም

ገብረ ማርያም

ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ቀዳማይ (1911 - 1991 ዓ.ም.) የአሰሳ፣ የመተከል የደንቢዶሎ ከዚያም የኢየሩሳሌምና የድሬ ዳዋ ሊቀ ጳጳስ ነበሩ ። ከጽድስና በፊት በስመ ጥምቀታቸው ገብረ ማርያም በመ ባል ይታወቁ ነበር።

ገብረ ማርያም
አጨጌ ገብረ ማርያም ዘጎንጅ በስም ጥም ቀታቸው ይጠሩ ነበር።

ፍቅረ ማርያም – ፍሬ ማርያም

ድንግል

ወናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ወይስ መይ ስሙ ዐማኑኤል ።
ትርጉም I እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች ስሙም ዐማኑኤል ይባላል (ኢሳ. 7፤14 I ማቴ.1፤23 I ሉቃ. 1፤31)።

ልብነ ድንግል
ትርጒሙ የድንግል መዐዛ ያለው የዕጣን አይነት ማለት ሲኾን (1500 –1533 ዓ.ም.) በነገሢ በዓመቱ ፷ኛው ሺ ገባ ተባለ ። ከግራኝ መሐመድ ጋር ተዋጉ።

መከብበ ድንግል

መዝሙረ ድንግል
አቡነ መዝሙረ ድንግል በ15ኛው ክፍለዘ መን የነበሩ አበምኔት በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

ሠመረ ድንግል

ሥርዳ ድንግል
በዚህ ስም የኢትዮጵያ ንጉሥ የነበሩት በስመ መንግሥታቸው መስከ ሰገድ (1555- 1589 ዓ.ም. ነገሡ) የሚባሉት በስመ ጥምቀታቸው ሥርዳ ድንግል ተብለው ይጠሩ ነበር።

ሰበነ ድንግል
ደብረ አሰቦ በኋላ ዘመን ደብረ ሊባኖስ ተብሎ ገዳም ሲገደም አበምኔት ከነበሩት አንዱ አባ ሰበነ ድንግል በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

ሣህለ ድንግል
በዚህ ስመ ሣህለ ድንግል በመባል የሚጠሩ ብዙ ነገሥታት በኢትዮጵያ ነግሠዋል ከነዚያም ውስጥ አንዱ 1825 –1832 ዓ.ም የነገሡት በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ የነበር።

በትረ ድንግል ..... በኩረ ድንግል
ብርሃነ ድንግል ... ተስፋ ድንግል
ተክለ ድንግል ..... አርከ ድንግል
አምኃ ድንግል .... ዐጽቀ ድንግል
ዜና ድንግል ..... ዘድንግል

ጽጌ ድንግል
ጥቅምት 27 ቀን በቅድስናቸው ታስበው የሚውሉት I በዐል የሚደረግላቸው አባ ጽጌ ድንግል በስመ ጥምቀታቸው ይታወቃሉ። እኝህ ሰው የማኅሌተ ጽጌ ደራሲ የነበሩ ናቸው።

ፀምረ ድንግል — ፍቅረ ድንግል
ፍሬ ድንግል

ጽዮን

አስመ ጎረያ እግዚአብሔር ለጽዮን።
ወአብደራ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ። ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም።
ትርጉም I እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና ማደሪያው ትኾነው ዘንድ ወዷታልና፤ እንዲህ ብሎ ይህች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት (መዝ.131፤(132) ፥13)።

ሀብተ ጽዮን – መብዐ ጽዮን
መዝገበ ጽዮን

በትረ ጽዮን
የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የልጅ ልጅ የበእደ ማርያም ወንድ ልጅ በትረ ጽዮንበመባል በስመ ጥምቀቱ ይጠራ ነበር።

ተስፋ ጽዮን

ተክለ ጽዮን
አቡነ ተክለ ጽዮን በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ አበምኔት በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

በኩረ ጽዮን – አምኃ ጽዮን
አብርሃ ጽዮን

ዐምደ ጽዮን
ስመ መንግሥቱ ገብረ መስቀል የነበርየኢትዮጵያ ንጉሥ በስመ ጥምቀቱ ዐምደ ጽዮን ተጠርቶበታል (1370- 1336 ዓ.ም)።

ዕጓለ ጽዮን
የጽዮን ልጅ ማለት ነው ። በዚህ ስም 1793 - 1810 ዓ.ም. የነገሡት የኢትዮጵያ ንጉሥ ተጠርተውበታል።

ዘርዐ ጽዮን — ዜና ጽዮን
ገብረ ጽዮን

ግርማ ጽዮን
ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ቀዳማይ (1878 - 1953 ዓ.ም.)። የኢርትራ ሊቀጳጳስ የነበሩና፤ ማኅበረ ሐዋርያትን ያቋቋሙ ናቸው ከጵጵስና በፊት በስመጥምቀታቸው ግርማ ጽዮን በመባል ይታወቁ ነበር።

ፍሥሓ ጽዮን
የጸድቁ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ስመጥም ቀታቸው ፍሥሓ ጽዮን ነው ።

- ሸ፱ -

ደቅስዮስ፣ ብሥራተ ገብርኤል፣ ቅዱስ ዑራኤል
መልአኩም ወደ እሷ መጥቶ ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ I እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው I ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ አላት (ሉቃ. 1፤28 Iዮሐ. 1፤16)።

ጥቅምት ፳፱ ቅዱስ ሉቃስ ይከበራል ታኅሣሥ ፳፱ የፐፕፐልያ ጸጸስ አባ ደቅስዮስ በዐሲን ያወጀበት I ታምራቷን የሰበሰበበት ዕለት የሚከበርበት ቀን ነው።

ስብሐተ ዑራኤል – ወልደ ዑራኤል
ብሥራተ ገብርኤል – ዘገብርኤል

- ሸ፲ -

ቅዱስ ጊዮርጊስ
የፈሰሰውን የባሮችኽን ደም በቀል። የዕረኞቹ ጩኸት ወደ ፊትኽ ይግባ (መዝ 78 (79)፤10)።
ትርጉም I ሚያዚያ ፳፫ ቅዱስ ጊዮርጊስ በሰማዕትነት ያረፈበትI ሰማዕት የኾነበት ዕለት ነው።

ሀብተ ጊዮርጊስ
በዚህ ስም የኢትዮጵያ የጦር መሪ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነጼ ተጠርተውበታል ። ያረፉበትም ታኅሣሥ 3 ቀን 1919 ዓ. ም. ነው።

ሠመረ ጊዮርጊስ

ሰበነ ጊዮርጊስ
ከዐፄ ልብነ ድንግል ልጆች አንዱ ሰበነ ጊዮርጊስ በመባል በስመ ጥምቀቱ ይጠራ ነበር ።

ወ.ክ

ቀጸላ ጊዮርጊስ

በትረ ጊዮርጊስ
የዐፄ መርዘ ድንግል ባለቤት እቴጌ ግርያም ሥና ያሳደገቻቸው አንዱ አባ በትረ ጊዮርጊስ ኹለተኛው አባ በትረ ማርያም በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር

ተስፋ ጊዮርጊስ
አጨጌ ተስፋ ጊዮርጊስ ዘወዶ (1774 ዓ.ም) በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር ።

ተአምረ ጊዮርጊስ

ተክለ ጊዮርጊስ
ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ቀዳማዊ (1889 - 1971 ዓ.ም.) ከጵጵስና በፊት በስመ ጥምቀታቸው ተክለ ጊዮርጊስ በመባል ይታወቁ ነበር ።

ኀይለ ጊዮርጊስ — አስበ ጊዮርጊስ አክሊለ ጊዮርጊስ

አፅመ ጊዮርጊስ
የሊያሱ አድያም ሰገድ ልጅ ዐፄ ባካፋ ስመ ጥምቀታቸው አፅመ ጊዮርጊስ ነበር።

ክፍለ ጊዮርጊስ
እምኀበ መምህር ዐቢይ ክፍለ ጊዮርጊስ ወአምኀበ ረድኡ ንዑስ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ወልደ አባ ተክሌ ። ያለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ረዳት የነበሩ መምህር ክፍለ ጊዮርጊስ ተብለው ይጠሩ ነበር።

ዐምደ ጊዮርጊስ

ዕቍበ ጊዮርጊስ
በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቅ የነበሩት ምግሰ ዕቁበ ጊዮርጊስ የሚባሉት የአባታቸው ስም ዕቍበ ጊያርጊስ ተብሎ በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

ወልደ ጊዮርጊስ
የዐፄ ምኒልክ የአክስት ልጅ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ልጅ የኾኑት ልዕልት አያህ ሉሽም ልጃቸው ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ እቦዬ በመባል በስመ ጥምቀት ይጠሩ ነበር ።

ውሂበ ጊዮርጊስ
ዘጊዮርጊስ — ዜና ጊዮርጊስ

ገብረ ጊዮርጊስ
ጥር 6 ቀን 1943 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ኾነው የተሾሙት፤ በኋላም ፓትርያርክ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የቀድሞ ስማቸው በስመ ጥምቀታቸው እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ይባሉ ነበር።

ገድለ ጊዮርጊስ — ፍቅረ ጊዮርጊስ ፍሥሓ ጊዮርጊስ

- ፐ ዐ -

አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ ፩ወ፬ቱ ካህናተ ሰማይ፣ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ስደተ ግብፅ

ዘኪያክሙ ተወክረ ኪያየ ተወክፈ፤ ወዘኪያየ ተወክር ለዘፈነወኒ ። ዘተወክረ ነቢየ በስመ ነቢይ ይነሥእ ፤ ወዘተወክፈ ጻድቀ በስመ ጻድቅ ዕስበ ጻድቅ ይነሥእ።
ትርጒም፤
እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ያገኛል።

ጻድቅን በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል (ማቴ. 10፡40 ፤ 18፡5 ፤ ሉቃ. 10፡16 ፤ ዮሐ. 13፡20)።

በጎዳር ፭፬ ቀን 24ቱ ካህናተ ሰማይ የሚከበሩበት ዕለት ነው።
ታኅሣሥ ፭፬ ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የተወለዱበት ፤ ነሐሴ ያረፉበት ዕለት ነው ።
በግንቦት ፭፬ ቅድስት ድንግል ማርያም ሄሮድስ ልጇን እንዳይገሉባት ከሰሎሜና ከዮሴፍ ጋራ ወደ ግብፅ የተሰደደችበት፤ የገባችበት ዕለት ነው ።

ወልደ ተክለ ሃይማኖት
ተክለ ሃይማኖት
ንዋየ ተክለ ሃይማኖት

ጽድቃን
ዝክረ ጻድቅ ስዓለም ይሄሉ ፤
የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል።
ከከሱ ነገር አይፈራም።
በእግዚአብሔር ስመታመን ልዑ የጸና ነው (መዝ. 111(112)፥6)።

ስብሐተ ጻድቃን

ተክለ ጻድቅ
የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪ የነበሩት አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የተወለዱበትም ዘመን መስከረም 1 ቀን 1906 ዓ.ም. ሲኾን በስመጥምቀታቸው ተጠርተውበታል

ወልደ ጻድቅ
የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አባታቸው ደብተራ ወልደ ጻድቅ በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር

ዐስበ ጻድቅ — ገብረ ጻድቅ ፍቅረ ጻድቅ

ቅዱሳን
ፈቃድህ ኹሉ በምድር ባሉት ቅዱሳንና ከሙሪን ላይ ነው (መዝ. 15፡3) ።

መዐዛ ቅዱሳን ...	መዝገበ ቅዱሳን
ሥነ ቅዱሳን	ታሪ ቅዱሳን
ስብሐተ ቅዱሳ	በዙረ ቅዱሳን
ብርሃነ ቅዱሳን	አጽቀ ቅዱሳን
ዐስበ ቅዱሳን	ዜና ቅዱሳን
ገድለ ቅዱሳን	ፍቅረ ቅዱሳን

- ፕ ፫ -

መርቆሬዎስ ሰማዕት
ግንቦት ፭፫ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሕፃንነቱ ዘንጎችን ተክሎ ዛፎች ያደረገው ዕለት ነው ።

- ፕ ፭ -

ቶማስ ሐዋርያ፣ ቅዱስ ዮሴፍ
ግንቦት ፭፭ ሐዋርያው ቶማስ የዕረፍቱ መታሰቢያ ቀን ነው ።

- ፕ ፯ -

መድኃኒዓለም
እግዚአብሔርሰ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም ፤
ትርጒም ፤ እግዚአብሔር ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው፤
በምድርም መካከል መድኀኒትን አደረገ።
አንተ ባሕርን በኀይልህ አጸናኻት (መዝ.73(74)፥12)።
መጋቢት ፭፯ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤

መድኀኒዓለም የተሰቀለበት (ጥንተ ስቅለት) ነው ። ፐር ፩፭ ሱርያል (ሊቃነ መላእክት) ይከበራል።

ሠርጸ መድኅን – ተወልደ መድኅን
ገብረ መድኅን

ክርስቶስ

ከመ ኢይንግሩ ለመኑሂ ከመ ውእቱ ክርስቶስ ትርጉሙ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደኾነ ለማንም ለማን እንዳይናገሩ አዘዛቸው (ማቴ.16፥21)።

ማኅደረ ክርስቶስ - ልሳነ ክርስቶስ
ሕላዌ ክርስቶስ – ሕንጸ ክርስቶስ

መልክዓ ክርስቶስ
አቡነ መልክአ ክርስቶስ በ15ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ አበምኔት በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

መርሐ ክርስቶስ
ብፁዕ አቡነ መርሐ ክርስቶስ የመቀሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እንዱኹም የሊቃውንት ጉባኤ ዋና ሰብሳቢም ነበሩ። የጵጵስና ስማቸው ስመ ጥምቀታቸው የነበረ ሲኾን የመጠሪያ ስማቸው ያሬድ ግርማይ ነበር ።

መርዓዊ ክርስቶስ – መብዓ ክርስቶስ

መዝሙረ ክርስቶስ
አቡነ መዝሙረ ክርስቶስ በ15ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ አበምኔት በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

መዝራእተ ክርስቶስ
አቡነ መዝራእተ ክርስቶስ በ15ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ አበምኔት በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

ማኅተመ ክርስቶስ

ሠምረ ክርስቶስ
አቡነ ሠምረ ክርስቶስ በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ አበምኔት በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

ሠርጸ ክርስቶስ – ሥዕለ ክርስቶስ

ሰፋኔ ክርስቶስ
አጨጌ ሰፋኔ ክርስቶስ በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር (1683 ዓ.ም- ጎዳር)።

ተንሥአ ክርስቶስ – ተላዌ ክርስቶስ
ተሰፋ ክርስቶስ – ተወልደ ክርስቶስ
ቃለ ክርስቶስ – ብርሃነ ክርስቶስ

ንዋየ ክርስቶስ
ዐፄ ንዋየ ክርስቶስ ስመ መንግሥታቸው ሰይፈ አርዕድ ይባላል፤ በዚህ የክርስትና ስም ይጠሩና ይታወቁ ነበር።

ኃይለ ክርስቶስ
በአንኮበር የመሰጫ ማርያምን ገዳም የመሰረቱ አባ ኃይለ ክርስቶስ በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይታወቃሉ።

ጎረዮ ክርስቶስ – አባለ ክርስቶስ
አካለ ክርስቶስ – አምኃ ክርስቶስ
አስትንፋሰ ክርስቶስ - አኅው ክርስቶስ
አደ ክርስቶስ – ወልድ ክርስቶስ

ዘክርስቶስ
የደንከላ አጨጌ ዘክርስቶስ (1660 ዓ.ም) ይመባል በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር

የማነ ክርስቶስ

ገብረ ክርስቶስ
ዐፄ ላሊበላ ስመ መንግሥታቸው በጥምቀት ስማቸው ገብረ ክርስቶስ በማለት ተጠርተውበታል ።

አንዲሁም ደግሞ የንጉሥ ቴዎዶስዮስ ልጅ ጻድቁ ገብረ ክርስቶስ የሚጠራው በስመ ጥምቀቱ ነው። በዐረብኛ ቢተረጎም አብደል መሢሕ ይኾናል።

ግርማ ክርስቶስ

ጸጋ ክርስቶስ
አጨጌ ጸጋ ክርስቶስ ዘቤተልሔም በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።
ፍቅረ ክርስቶስ – ፍሥሓ ክርስቶስ

አልፋ

አነ ውእቱ አልፋ ወኦ።
አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ (ራእ.1፥8 ፤22፥13)።

ተክለ አልፋ

- ፳፫ -

ዐማኑኤል

ወናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ወይሰመይ ስሙ ዐማኑኤል ።
ትርጉም ፤ እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ልጅም ትወልዳለች ስሙም ዐማኑኤል ይባላል
(ኢሳ. 7፥14 ፤ ማቴ. 1፥23 ፤ ሉቃ.1፥31)።

ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ገና ይባላል (ልደት)
በዘመነ ዮሐንስ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን መዋሉ ቀርቶ በዚህ ቀን ይውላል ።

ብርሃነ ዐማኑኤል – ወልደ ዐማኑኤል
ዘዐማኑኤል – ገብረ ዐማኑኤል

ሰንበት

መጽአ ላእሌየ መንፈሰ በዕለተ ሰንበት አሐዱ ወሰማእኩ ቃለ ዐቢየ (ራእ.1፥10)
ገብረ ሰንበት

ወልደ ሰንበት
የታወቁት ያቋቋም መምህር የነበሩት **አሊቃ ወልደ ሰንበት** በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር ።

አምላክ

እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ።
(ዘጸ. 20፥1)
መዝገበ አምላክ – ብርሃነ አምላክ
ወልደ አምላክ – ዘአምላክ
ገብረ አምላክ – ፈቃደ አምላክ

- ፳፱ -

በዕለ ወልድ (ትስብእት)
ወይም በዕለ እግዚእ

ወወለደት ወልደ ዘበኵራ ወአሰረቶ መንኰብያ ቲሁ ፤ ወጠብለለቶ በአፅርቅት ፤ ወአስከበቶ ውስተ ኅጸ ፤ አስሙ አልዖሙ መካን ውስተ ማኅደሮሙ።
ትርጉም ፤ የበኵር ልጇንም ወለደችው አውራ ጣቱንም አሰረችው ፤ በጨርቅም ጠቀለለችው፤ በበረትም አስተኛቸው ፤ በማደሪያቸው ቦታ አልነበራቸውምና (ሉቃ. 2፥7)።

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በዓል ። በሰግር ዓመት በዘመነ ዮሐንስ ታኅሣሰ ፳፰ ይኾናል። መጋቢት ፳፱ ደግሞ ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታን የፀነሰችበት ዕለት ነው ።

ሁበተ ወልድ — ማኅተመ ወልድ
ቃለ ወልድ — ገብረ ወልድ
ተክለ ወልድ

አካለ ወልድ
በዚህ ስም ኢትዮጵያዊው የነገረ መለኮት ሊቅ መምህር አካለ ወልድ በመባል ቢታወቁ ። ያረፉበት ዘመን ኅዳር 9 ቀን 1912 ዓ.ም. ነው።

ተወልደ መድኅን
አጪጌ ተወልደ መድኅን ዘአዘዙ በስም ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

ተወልደ ብርሃን
ጥቅምት18 ቀን 1983 ዓ.ም. የመላው የኢትዮጵያ ገዳማት ኤጲስ ቆጶስ ተብለው የተሾሙት ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ በቀድሞ ስማቸው ይታወቁ የነበሩት አባ ተወልደ ብርሃን በሚል ስመ ጥምቀታቸው ነበር።

ግሳተመ እግዚእ – ቃለ እግዚእ
በረከተ እግዚእ – ወረደ እግዚእ
ዐቢየ እግዚእ – ዕቍብ እግዚእ
ዘርዐ እግዚእ – ዘመድኅን
ያፍቅረነ እግዚእ – ገብረ እግዚእ
ጥበበ ወልድ

ፈቀደ እግዚእ
በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ገዳም አበምኔት (1895 - 1898 ዓ.ም) በስመ ጥምቀታቸው አባ ፈቀደ እግዚእ ተብለው ይጠሩ ነበር። የተሾሙትም በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነበረ።

ፍቁረ ወልድ

- ሸ -

ሐዋርያው ቅ. ማርቆስ
ወእስክ አጽናፈ ዓለም በጽሐ ነቢሶሙ።
ትርጉም I ቃላቸው አሰክ ዓለም ዳርቻ ወጣ (መዝ. 18፤3)

ወልድ ማርቆስ

ዜና ማርቆስ
በዐፄ ይኩኖ አምላክ ዘመን ይኖሩ የነበሩት የሞረት መምህር በስመ ጥምቀታቸው አቡነ ዜና ማርቆስ በመባል ይታወቃሉ።

ትንሣኤ
ወእሙሥእ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ ንሥትዎ ለዝንቱ ቤተ መቅደስ ወበሠሉስ ዕለት አነሥኦ ።
ትርጉም I ጌታ ኢየሱስም ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሦስተኛውም ቀን አነሣዋለኹ ብሎ መለሰላቸው I ቤት ስለ ተባለው ሥጋው ነገራቸው (ዮሐ. 2፤19 I 20፤1 I ማቴ 26፤ 61)።

ብርሃነ ትንሣኤ – ትንሣኤ ክርስቶስ
ትንሣኤ ኢየሱስ

ወልደ ትንሣኤ
ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ቀዳማይ (1911- 1989 ዓ.ም.) ከጵጵስና በፊት በስመ ጥምቀታቸው ወልደ ትንሣኤ በመባል ይታወቁ ነበር። ሀብተ ፈውስ ተሰጥቷቸው በወሊሶ ብዙ ህመምተኞችን እያጠመቁ ፈውሰዋል።

ዘፈረ ብርሃን — ገብረ ትንሣኤ

በዕርገት
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሥራውን ጨርሶ ወደ ሰማይ ዐረገ (የሐ. ሥራ1፤6 I ሉቃ. 24፤50)።

ዕርገተ ቃል – ዕርገተ እግዚእ
ዕርገተ ኢየሱስ – ዕርገተ መድኅን

ቃል
ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ወውእቱ ቃል ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ፤ ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል
ትርጉም I ያ ቃል ቀዳማዊ ነው I ያ ቃል በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ነበረ I ያ ቃል እግዚአብሔር ነው (ዮሐ.1፤1 I 17፤5 I ዘፍ.1፤1 I 1ኛዮሐ. 1)።

አዐሰ ቃል - መዝገበ ቃል
ወረደ ቃል - ብርሃነ ቃል
ኀይለ አዐል - ነቢየ አዐል (ዮሐንስ)

ጸጉሜ ፫
ሩፋኤል
ከከበሩ ከመላእክት አንዱ ሩፋኤል ነው (መጽ. ሄኖ. 6፤3)።

ስብሐተ ሩፋኤል – ኀይለ ሩፋኤል
ወልደ ሩፋኤል

ከዚህ በላይ ያሉት የክርስትና ስም አንዱሁም የመጠሪያ ስም ኾነው ያገለግላሉ ። ከበድ ያሉትን እና ትርጉም የሚያስፈልጋቸውን የግእዝ ቅጽል ትርጉም ችም በመጠሪያ ስም ተተርጕሟል ።

ማሳሰቢያ፦

በግእዝ ወለተ ማርያም የሚለው ቅጽል በትግርኛ ባህል በአንዳንድ ቦታ ለተ ማርያም ይላሉ። በዚህ ጽሑፍ ግን በግእዙ በመሠረታዊው ቋንቋ ተጽፏል ። እንዲህ አይነቱ ለሕተት በቋንቋ የተለመደ ነው። ለምሳሌ፦ በግእዝ ገብረ እግዚአብሔር የሚለውን በዐማርኛም ገበረእግዚያር፤ ገብረ መድኅን ከማለት ገብረመድን ማለት የተለመደ ነው ። ስለዚህ ኹሉም በግእዙ መንገድ ተሰተካከለው ቀርበዋል ። በዚህ ውስጥ ያልተካተቱ የክርስትና ስሞች አሉ ይህ ግፕ፞ስመነሻነት ቀርቧል።

(መ) የሴቶች የክርስትና ስሞች

- ፩ -

ልደታ ማርያም ፣ ኤልያስ ፣ ዮሐንስ ፣ ራጉኤል

በመስከረም ፩ ዓውደ ዓመት (ዕንቁጣጣሽ) ፣ ራጉኤል ፲ ሐዋርያው በርቶሎሜዎስ ። በታኅሣሥ ፩ቀን ኤልያስ ። ግንቦት ፩ ቅ. ድንግል ማርያም ልደት።

ወለተ ኤልያስ – ወለተ ራጉኤል
ወለተ ዮሐንስ

- ፪ -

ልደተ ዮሐንስ መጥምቅ ታዴዎስ ሐዋርያ

አማን አማን እብለክ ከመ ዘንአምር ንነግር፤ ትርጉም ፲ እውነት እውነት አልሀለሁ የምናውቀውን እንድንናገር ባየነውም እንድንመሰክር፤ ምስክርነታችንን ግን አትቀበሉትም (ዮሐ.3፥11 ፲ 8፥17)።
መስከረም ፪ መጥምቁ ዮሐንስ አንገቱ የተሰየፈበት፤ በታሕሣሥ ፪ በሰንከሳር አንደተገለጸው ሠለስቱ ደቂቅ ከአባት የዳኑበት ፲ ሐዋርያ ታዴዎስ ይከበራል።

እኅተ ታዴዎስ – ወለተ ታዴዎስ
ወለተ ዮሐንስ

- ፫ -

በዐታ ለማርያም ፣ ፋኑኤል መልአክ ፣ ዜና ማርቆስ

እበው ቤተክ ምስለ መባዕየ ።
ወእሁብ ብፅዐትየ ዘነበብኩ በአፋየ ። ዘእ ቤ በከናፍርየ እመ ምንዳቤየ።
ትርጉም ፲ ከመባ ጋር ወደ ቤትህ እገባለሁ። በመከራዬ ጊዜ በአፌ የተናገርኩትን ። ከን ፈርጀም ያሉትን ስእለቴን (መዝ. 95፥13)

ታኅሣሥ ፫ ቅድስት ድንግል ማርያም በሦስት ዓመታ ቤተ መቅደስ የገባችበት ዕለት (በዐታ ለማርያም) ። ፋኑኤል መልአክም ይከበራል ።

ብፅዓተ ማርያም – ወለተ ፋኑኤል

- ፬ -

ዮሐንስ ወንጌላዊ(ወልደ ነጎድጓድ)

ወተመይጦ ጴጥሮስ ርእዮ ለዝኩ ረድእ ዘያፈቅር እግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይተልዮ፤ ወውእቱ ረድእ ፤
ትርጉም ፲ ጴጥሮስም መለስ ብሎ ያን ጌታ ኢየሱስ ይወደው የነበረውን ደቀ መዝሙር ሲከተለው አየ (ዮሐ. 21፥20 ፲ 13፥23)።

ታሕሣሥ ፬ ሐዋርያው እንድርያስ ይክበራል። ጥር ፬ ሐዋርያው ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ይከበራል ።

መዓዛ ዮሐንስ – መንበረ ዮሐንስ
መርዓተ ዮሐንስ - ሥርጉተ ዮሐንስ
አስካለ ዮሐንስ – እኅተ ዮሐንስ
ዐፀደ ዮሐንስ – ዕፀ ዮሐንስ
ወለተ ዮሐንስ – ፍቅርተ ዮሐንስ

ሐዋርያት

ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ንዑ ትልዉኒ፤ ወእሬስየከሙ ትኩኑ መሠግራነ በብእ።
ትርጉም ፲ ጌታ ኢየሱስ ኑ ተከተሉኝ ፲ ሰውንም የምታጠምዱ እንድትኾኑ አደርጋች ኋለሁ አላቸው (ማቴ. 4፥19 ፲ ማር. 1፥16 ፲ ሉቃ. 5፥1)።

መንበረ ሐዋርያት
አስካለ ሐዋርያት- አኅተ ሐዋርያት
ወለተ ሐዋርያት – ዐፀደ ሐዋርያት
ዜና ሐዋርያት – ፍቅርተ ሐዋርያት

- ፭ -

ጴጥሮስ ወጳውሎስ፣ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ።

መጋቢትኽ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ (አቦ) ያረፉበት ዕለት ነው። ሐምሌ ፭ ጴጥሮስ ወጳውሎስ፤ በዚህ ቀን የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ መታሰቢያ በዐል ይከበራል።

እኅተ ጴጥሮስ

ወለተ ጴጥሮስ
በ1609 ዓ. ም. በዐፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት ንጉሤን በመኮትለካቸው የተቃወሙ ። በሃይማኖት ብጥብጥ የተነሳ ዘጌ ገዳም የገቡ (እመምኔት) ወለተ ጴጥሮስ በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይታወቁ ነበር።

ወለተ ጳውሎስ – ፍቅርተ ጴጥሮስ
ፍቅርተ ጳውሎስ

ገብረ መንፈስ ቅዱስ

መዓዛ ሕይወት
ማኅደረ ሕይወት – ብርሃነ ሕይወት
ወለተ ሕይወት
በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ገዳም ከ1838 ዓ.ም. ጀምሮ የመኖሪያ ጎጆዎቹን በመሥራት ከቀኑት ቤቶች አንዷ እማሆይ ወለተ ሕይወት በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይታወቁ ነበር

መዓዛ ሕይወት - ምሥራቀ ሕይወት
ሥርጉተ ሕይወት – እኅተ ሕይወት
ዕፀ ሕይወት – ፍቅርተ ሕይወት

- ፮ -

ኢየሱስና ቅዱስ ማርያም

ወእመ ተፈጸመ ሰሙን ዕለት ።
ትርጉም ፲ ሰምንት ቀን በተፈጸመ ጊዜም ሕፃኑን ሊገዝሩት ወሰዱት ሳትፀንሰው መልአኩ እንዳወጣለትም ስሙን ኢየሱስ አሉት (ሉቃ .2፥21 ፲ ም.1፥31 ፲ ማቴ. 1፥28)።

ጥር ፮ ቀን ጌታ ኢየሱስ በተወለደ በስምንተኛው ቀን ግዝረት ። ጎዳር ፮ ቅድስት ድንግል ማርያም በግብፅ ተሰድዳ ደብረ ቁስቋም የገባችበት ዕለት ነው።

ሐመረ ኢየሱስ - መርዐተ ኢየሱስ
በረከተ ኢየሱስ – ብርሃነ ኢየሱስ
ጥኅተ ኢየሱስ – አመተ ኢየሱስ
ዓሥራተ ኢየሱስ – ዘኢየሱስ
ወለተ ኢየሱስ – ፍሬ ኢየሱስ
ነገደ ኢየሱስ – ፍቅርተ ኢየሱስ

- ፯ -

በዓለ ሥላሴና ጽንሰታ ለማርያም

በቀትርም ጊዜ አብርሃም በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ ያድባር ዛፍ ተገለጠለት (ዘፍ. 18፥1)።

ሐምሌ ፯ አምላክ ለአብርሃም አግዚአ ብሔር በሦስትነት (በሥላሴ) የተገለጸበት ዕለት ነው። ነሐሴ ፯ ቅድ ስት ድንግል ማርያም የተፀነሰችበት ዕለት ነው።

ጎይመተ ሥላሴ

ጊሩተ ሥላሴ
በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን የኢትዮጵ ያ ገዳም ከ1838 ዓ.ም. ጀምሮ የመኖሪ ያ ጎጆዎቹን በመሥራት ከቀኑት ሴቶች አንዲ እማሆይ ጊሩተሥላሴ በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይታወቁ ነበር።

መዐዛ ሥላሴ – መርዓተ ሥላሴ
ምዕራፈ ሥላሴ – ማኅደረ ሥላሴ
ሜላተ ሥላሴ – ምሕረተ ሥላሴ
ምስጢረ ሥላሴ – ሣህለ ሥላሴ
ስርጉተ ሥላሴ – ሠዊተ ሥላሴ
በረከተ ሥላሴ – ብርሃነ ሥላሴ

ትርሚተ ሥላሴ
ቀደምት ከኾኑት የሰበታ ቤተ ደናግል መነኰሳይት እማሆይ ትርሚት እባለ በስመ ጥምቀታቸው ትርሚተ ሥላሴ በመባል ይጠራሉ። በእንግሊዝ አገር የርእሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም አገልጋይ ናቸው።

ዜና ሥላሴ
ኖኅተ ሥላሴ – አስካለ ሥላሴ
ዓሥራተ ሥላሴ – ዕንቆ ሥላሴ
ወለተ ሥላሴ – ዘሥላሴ

ጥበበ ሥላሴ
የዐፄ ዮሐንስ አፈተኛ ባለቤት ጥበበ ሥላሴ ተብለው በስመ ጥምቀታቸው ይ ጠሩ ነበር ።

ጸጋ ሥላሴ – ፍቅርተ ሥላሴ

ልደተ ሐናና ዕረፍተ ኢያቄም
መሠረታቲሃ ውስተ አድባር ቅዱሳን። ትርጉም፤ መሠረቶቹ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው (መዝ.86፥1)።

ወለተ ሐና – ጽጌ ሐና
ፍቅርተ ሐና

- ፕ -

ልደተ ስምዖንና አባ ኪሮስ
ወሀሎ አሐዱ ብእሲ በኢየሩሳሌም ዘስሙ ስምዖን ፤ ወውእቱ ጻድቅ ወየዋህ፤ ወይሴሮ ይርእይ ፍሰሓሆሙ ለአበራኤል ፤ መንፈሰ ቅዱስ ላእሌሁ ።
ትርጉም ፤ በኢየሩሳሌም ስሙ ስምዖን የሚ ባል አንድ ሰው ነበር፤ እርሱም ጻድቅ ደግ ሰው ነበር። የእስራኤልን ደስታቸውን ሊያይ ተስፋ ያደርግ ነበር። መንፈስ ቅዱስም ያደ ረበት ነበር (ሉቃ. 2፥22)።

የካቲት ፳ ጌታ ከተወለደ ፵ ቀናትሲኾ ነው በቤተ መቅደስ ይጠባበቀው የነበ ረው አረጋዊ ስምዖን የታቀፈበት፤ ሰኔ ፳ በግብፅ ስደት ላይ ሳሉ ከዐለት ድንጋይ ጠበል ያፈለቀበት፤ መጋቢት ፳ ሐዋርያው ማትያስ፤ ኅዳ ር ፳ አፍኒን (ሊቀ መላእክት) እና ዐር ባእቱ እንሰባ የሚከበሩበት ቀን ነው።

- ፖ -

የቅዱሳንና የሰማዕታት ፤ ሐዋር ያው ቅዱስ ቶማስ
የፈለሰውን የባርቶኬን ደም በቀል ። የሰረ ዮቹ ጨኸት ወደ ሬትኽ ይግባ (መዝ 78 (79)፥ 10) ።

- ፐ -

በወለ መስቀል ብርሃን (መስቀለ ኢየሱስ)
እነ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም ።
ትርጉም፤ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ፤ የሚከ ተለኝም ዅሉ የሕይወት ብርሃን ይኾንለታል (ዮሐ. 8፥12)።

መስከረም ፤ በዐፄ ዳዊት ግማደ መስቀ ል ወደ ኢትዮጵያ የገባበት ። ዔዴንያ በምትባለ ሀገር በማርታ ቤት ቅዱስ ሉቃስ የሳላት ሥዕለ ቅድስት ድንግል ማርያም ተአምራት የታየበት ቀን ነው። የካቲት ፤ ሐዋርያው ያዕቆብ ወልደ ኤልፍዮስ፤ ሐምሌ ፤ ሐዋርያው ናትና ኤል ይከበራል።

ወለተ ብርሃን – ማኅደረ ብርሃን
ሞጣኅተ ብርሃን – ኖኅተ ብርሃን
ተቋመ ብርሃን – አንቀጸ ብርሃን

- ፐ -

ጥምቀተ ክርስቶስ፣ ቅድስት ሐና፣ ቅዱስ ያሬድ
ባሕርኒ ርእየት ወጕየት ። ወዮርዳኖስኒ ገብአ ድኅቴሁ ። አድባር አንፈርፀጹ ከመ ሐራጊት። ትርጉም ፤ ባሕር አየች ሸሸች ም። ዮርዳኖስም ወደ ኋላው ተመለሰ። ተራ ሮች እንደ ኮርማዎች ዘለሉ ።
(መዝ. 13(14)፥3)።

ጥር ፤ ቀን መጥምቀ መለኮት የተባ ለው የዘካርያስና የኤልሳቤጥ ልጅ ጌታ ኢየሱስን ያጠመቀበት ዕለት።

ብርሃነ መለኮት - ትርሚተ መለኮት
ፍቅርተ መለኮት – ፍሬ መለኮት
አስካለ መለኮት

- ፐ -

ቅዱስ ሚካኤል
የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ኾኖ እኹን መጥቻለሁ አለ። ኢያሱም ወደ ምድር በግ ንባሩ ተደፍቶ ሰገደ (መጽ. ኢያ.5፥14፤ ዳን. 10፥13፤ 12፥1 ፤ ይሁ. 9 ፤ ራእ. 12፥7)።

ሕዳር ፤ ቅዱስ ሚካኤል አስራኤላው ያንን የረዳበት። ለኢያሱ የተገለጸበት ዕለት ነው (መጽ. ኢያ. 5)።
አስራኤላውያንን እየመራ ወደ ቃል ኪዳኗ አገር ያስገባበት ቀን ነው። ቅዱ ስ ሚካኤል በየውሩም ታምር ሰርቷል። ጥር ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃና ዘገሊላ ውሃውን ወደ ወይን የለ ወጠበት የመጀመሪያ ተአምራቱን ያደረ ገበት፤ ጥቅምት ፤ ሐዋርያው ማቴዎስ

ጊሩተ ሚካኤል - ስርጉተ ሚካኤል
ትርሚተ ሚካኤል
አመተ ሚካኤል – አኅተ ሚካኤል

ወለተ ሚካኤል
የዐፄ ምኒልክ ባለቤት አቴጌ ጣይቱ (ብርሃነ ዓለም) ስመ ጥምቀታቸው ወለተ ሚካኤል ነው ።

ዐሥራተ ሚካኤል – ዘሚካኤል
ፍሬ ሚካኤል – ፍቅርተ ሚካኤል

- ፐ -

እግዚአብሔር አብ
(በዓለ እግዚአብሔር ፤ ባለ እግዚሐር)
መጽአ ደመና ብሩህ ወጸለሎሙ ።
ትርጉም ፤ ደመናም መጥቶ ጋረዳቸው፤ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት

ሴ.ሐ

የሚል ድምጽ መጣ (ማቴ. 17፥1 ፤ ማር. 9፥7 ፤ ሉቃ. 9፥28)።

ነሐሴ ፲፫ በደብረ ታቦር ላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ብርሃነ መለኮቱን፤ የገለጸበት ዕለት ነው።

መሠረተ አብ – ማኅደረ አብ
ሥምረተ አብ – ሰላመ አብ
ጎሩተ አብ – ወለተ አብ
ፍቅርተ አብ – ጸጋ ዘአብ
ወለተ እግዚአብሔር

- ፲፬ -

አቡነ አረጋዊና ገብረ ክርስቶስ

ዘኪያክሙ ተወክረ ኪያየ ተወክፈ ፤ ወዘኪያየ ተወክፎ ለዘፈነወኒ ። ዘተወክፈ ነቢየ በስመ ነቢይ ይነሥእ ፤ ወዘተወክፈ ጻድቀ በስመ ጻድቅ በዕበ ጻድቅ ይነሥእ።
ትርጉም ፤ እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበል ሓል፤ ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ያገኛል። ጻድቅን በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል (ማቴ. 10፥40 ፤ 18፥5 ፤ ሉቃ. 10፥16 ፤ ዮሐ. 13፥20)።
ጥቅምት ፲፬ ኢትዮጵያ ከገቡት ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ አቡነ አረጋዊ (ዘሚካኤል) የሚከብሩበት ዕለት። እንዲሁም ደግሞ የንጉሥ ቴዎዶስዮስ ልጅ ጻድቁ ገብረ ክርስቶስ የሚከበሩበት ዕለት ነው።

ወለተ አረጋዊ
እኅተ አረጋዊ – ፍቅርተ አረጋዊ

- ፲፭ -

ቅ. አስጢፋኖስና ቅ. ቂርቆስ ወኢየሉጣ

ወአሕለፍክነ ማዕከለ አሳት ወማይ። ወአውፃእከነ ውስተ ዕረፍት።
ትርጉም፤ በእሳትና በውሃ መካከል አለፍን። ወደ ዕረፍት አመጣኸን (መዝ. 65፥12)።

አክሊለ ሰማዕት
አክሊለ አስጢፋኖስ
ወለተ ሰማዕት – ወለተ ቂርቆስ
ፍቅርተ ሰማዕት – መንበረ ሰማዕት

- ፲፮ -

ኪዳነ ምሕረት

አስመ ትቤ ለዓለም አሐንጽ ምሕረተ። በሰማይ ጸንዐ ጽድቀከ ። ኪዳነ ተካየድኩ ምስለ ኅሩያንየ።
ትርጉም፤ ምሕረትህ ለዘላለም ይመሠረታል ብለሃልና። እውነትህም በሰማይ ይጸናል። ከመረጥኩት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ። (መዝ. 88፥2)።
ነሐሴ የቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋ ትንሣኤና ዕርገት። የክቲት ቅድስት ማርያም ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ስሟን ለጠራ፤ መታሰቢያዋን ያዘከረ ቃል ኪዳኑን የሰጠበት፤ ኢሷም የእግላጅነት ሥልጣን የተቀበለችበት ዕለት ነው።

ሐመረ ድንግል – መርዐተ ድንግል
ምሕረተ አብ – ምሕረተ ኪዳን
ምሕረተ ድንግል – ሥምረተ ኪዳን
ትርሢተ ኪዳን – ትርሢተ ወልድ
ኪዳነ ቃል

ወለተ ኪዳን
በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ገዳም ከ1838 ዓ.ም. ጀምሮ የመኖሪያ ጎጆዎቹን በመሥራት ካቀኑት ቤቶች አንዷ እግዘአብ ወለተ ኪዳን በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይታወቃሉ።

ጽላተ ኪዳን – ፍቅርተ ኪዳን

- ፲፯ -

በዓለ መስቀልና ቅ. አስጢፋኖስ

ወወሀብኩሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ ፤ ከመ ያምለጡ እምገጸ ቀስት ። ወይድኅኑ ፍቁራኒከ።
ትርጉም ፤ ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ ። ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠኻቸው። ወዳጆች ኽም እንዲድኑ (መዝ. 59(60)፥4)።

መስከረም ፲፯ ጠፍቶ የነበረውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ፤ መስቀል ንግሥት አሌኒ አስፈልጋ ያስገኘች በት ቀን።
ጥቅምት ፲፯ ሰማዕቱ ቅዱስ አስጢፋኖስ።
ሚያዚያ ፲፯ ሐዋርያው ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ ይከበራል።

መስቀል ክብራ
የዐፄ ላሊበላ ባለቤት መስቀል ክብራ በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር ።

ማኅደረ መስቀል – ብርሃነ መስቀል
ጎሩተ መስቀል – ወለተ መስቀል
ኖኅተ መስቀል

- ፲፰ -

ፊልጶስ ሐዋርያና ዝርወተ ዐፅሙ ለጊዮርጊስ

እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ያገኛል ጻድቅን በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል። (ማቴ.10፥40 ፤ 18፥5፤ ሉቃ. 10፥16 ፤ ዮሐ. 13፥20)።

ኅዳር ፲፰ ሐዋርያው ፊልጶስ።
ሐምሌ ፲፰ ያዕቆብ (የኢየሩሳሌም ሊቀጳጳስ የጌታ ወንድም)።
ወለተ ሐዋርያት- ፍቅርተ ሐዋርያት

- ፲፱ -

ቅዱስ ገብርኤል

እነ ውእቱ ገብርኤል ዘአቀሙ ቅድመ እግዚአብሔር ፤
ትርጉም ፤ እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ (ሉቃ. 1፥19)።

ታኅሣሥ ፲፱ ቀን መጋቢት ፳፱ ቀን ቅዱስ ገብርኤል ቅድስት ድንግል ማርያምን ያበሠረበትና መለከቱ ደቂቅን ከአሳት ያወጣበት ዕለት ።

ጎሩተ ገብርኤል
ስርጉተ ገብርኤል
ሥጊነ ገብርኤል
ብርሃነ ገብርኤል
ተአምረ ገብርኤል
ትርሢተ ገብርኤል
እኅተ ገብርኤል

ወለተ ገብርኤል
በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ገዳም ከ1838 ዓ.ም. ጀምሮ የመኖሪያ ጎጆዎቹን በመሥራት ካቀኑት ቤቶች አንዷ እግዘአብ ወለተ ገብርኤል በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይታወቁ ነበር።

ዐሥራተ ገብርኤል

ዐፀደ ገብርኤል
የሰበታ ቤተደናግል መሥራች ከኾኑት መነኩሳይት እግዘአብ ዐፀደ በስመ

ጥምቀታቸው ዕፀደ ገብርኤል በመባል ይጠራሉ ። በሚኖሩበት በእንግሊዝ አገር የርእሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያምን መሥራች ከኾኑት አንዷ ናቸው።

ዕሴተ ገብርኤል – ዕፀ ገብርኤል
ዘገብርኤል – ዜና ገብርኤል
ጸወነ ገብርኤል - ፍቅርተ ገብርኤል

መልአክ

የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሠፍራል፤
ትርጉም፤ ያድናቸውማል እግዚአብሔር ቸር እንደ ኾነትመሱ አዩም (መዝ. 33(34)፥7)።
አኅተ መልአክ – ፍቅርተ መልአክ

- ፳ -

ሕንጸታ

በኔ ፳ ቀን ጌታ ኢየሱስ ከርስቶስ እና ሐዋርያት በማርያም ሰም የተቀደሰውን ቤተ ክርስቲያን የሠሩበት ዕለት ነው። (ሕንጸታ) ሰኔ ፳፩ ቀን ፤ የመጀመሪያ ው ቤተ ክርስቲያን የተቀደሰበት ዕለት የሚከበርበት ነው።

- ፳፩ -

በዓለ ቅ. ድ. ማርያም

ጥር ፳፩ አስተርእዮ ቅ. ድንግል ማርያ ም ያረፈችበት። መስከረምና ኅዳር ዕረ ፍቷን ለማስታወስ ይከበራል ። በኅዳር ወር የታቦተ ጽዮን በዐል ይከበራል ። ታኅሣሥ፣ የካቲት፣ መጋቢት፣ ሚያዚያ ግንቦት፤ ሐምሌ ዕረፍቷን ለማስታወስ ይከበራል። ከግንቦት ፳፩ ቀን እስከ ፳ ፭ ግብፅ ሀገር በደብረ ምጥማቅ ብርሃን ወርዶ ስለነበር ታላቅ በዓል ይደረግላታል ። ሐምሌ ፳፩ ቀን ዑራ ኤል (ሊቀ መላእክት) ይከበራል።

መቅደሰ ማርያም
መንበረ ማርያም
መዐዛ ማርያም – ማርያም ሠምራ
ማኅደረ ማርያም – ምልዕተ ጸጋ

ሣህለ ማርያም
በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን የኢትዮ ጵያ ገዳም ከ1838 ዓ.ም. ጀምሮ የመኖ ሪያ ጎጆዎቹን በመሥራት ከቀኑት ሴቶ ች አንዷ እማሆይ ሣህለ ማርያም በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይታወቃሉ

ሥርጉተ ማርያም - ሥኒነ ማርያም
ሰበነ ማርያም – ቀጸላ ማርያም
ትርሢተ ማርያም
ትቀድሰን ማርያም
ትዕራብ ማርያም

አመተ ማርያም
በአድአ ወረዳ ጎዴቲ ገብርኤል ከመሠ ረቱትና የሙጋድ እንጨት፣ መገበሪያ በማቅረብ ካቀኑት አንዷ በዓለም ስማ ቸው ወይዘሮ ግምጃ በሩ ፤ አመተ ማር ያም በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።
ሌላዋ፡ የዋልድባ ገዳምን የመሠረቱት አባ ሳሙኤል እናታቸው አመተ ማር ያም ይባሉ ነበር ።

አዛዕነ ማርያም

አስካለ ማርያም
የማርያም ፍሬ ማለት ነው። በዚህ ስም የዐፄ ምኒልክ ልጅ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የተጠሩበት ነው ከ20 በላይ ቤተ ክርስቲያን አሠርተ ዋል። ለሴቶች ማዋለጃ የንግሥተ ነገ ሥታት ዘውዲቱ ሆስፒታል ያቋቋሙ ናቸው።
የምዕራብ ወለጋ ገዝ የነበሩት ደጃዝማ ች ጆቴ ቱሉ ልጅ ፤ የልጅ ኢያሱ ባለ ቤት አስካለ ማርያም በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

አኅተ ማርያም
የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ልጅ ተናኘወርቅ ሴት ልጅ አኅተ ማርያም በመባል
በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩነበር ። ወን ድማቸው የዐፄ ኃይለ ሥላሴ አባት ራስ መኮንን ናቸው።

ወለተ ማርያም
የዐፄ ልብነ ድንግል እናት ንግሥት
ወለተ ማርያም በመባል በስመ ጥምቀታ ቸው ይጠሩ ነበር (ስን. ግን.3 ገጽ 236)።

ዐሥራተ ማርያም – ዐፀደ ማርያም

ዕሴተ ማርያም
በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን ገዳም ከ1838 ዓ.ም. ጀምሮ የመኖሪያ ጎጆዎ ቹን በመሥራት ከቀኑት ሴቶች አንዷ እማሆይ ዕሴተ ማርያም በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይታወቃሉ።

ዜና ማርያም
ዝክረ ማርያም
የዓቢ ክብራ ለማርያም
ጽጌ ማርያም
ጸዳለ ማርያም
ፍቅርተ ማርያም

ድንግል

ሐመልማለ ድንግል
ሐመረ ድንግል – መብዐ ድንግል
መዓዛ ድንግል - መዝሙረ ድንግል
ማኅደረ ድንግል – ኖኅተ ድንግል
ሜላተ ድንግል (ነጭ የሐር ግምጃ)
ሰላመ ድንግል – ሰበነ ድንግል
ሰብለ ድንግል – ሰዋስወ ድንግል
ስኒነ ድንግል – ብርሃነ ድንግል

አመተ ድንግል
የዐፄ ናየድ ሴት ልጅ የዐጼ ልብነ ድን ግል አኅት አመተ ድንግል በመባል
በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

አዛዕነ ድንግል – አኅተ ድንግል
ዕሴተ ድንግል – ዕጣነ ድንግል
ዐጽቀ ድንግል – ዕፀ ድንግል
ዘድንግል

ጽዮን

ሐመረ ጽዮን – ማኅደረ ጽዮን
ሜላተ ጽዮን – ሥኒነ ጽዮን
ተሰፋ ጽዮን – ትፍስሕተ ጽዮን

አመተ ጽዮን
በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን የኢትዮጵ ያ ገዳም ከ1838 ዓ.ም. ጀምሮ የመኖሪ ያ ጎጆዎቹን በመሥራት ከቀኑት ሴቶች አንዷ እማሆይ አመተጽዮን በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይታወቃሉ።

አብርሃ ጽዮን – አኅተ ጽዮን
ወለተ ጽዮን – ዘርዐ ጽዮን
ፍሰሐ ጽዮን – ፍቅርተ ጽዮን

ሴቶች

ዑራኤል

ይትዐየን መልአክ እግዚአብሔር አውደሙ። ትርጉም ፤ የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት በዎች ዙሪያ ይሠፍራል ፤ የእድናቸው ግል ። እግዚአብሔር ቸር እንደ ኾነ ቅመሱ አዩም (መዝ. 33(34)፤7)።

ወለተ ዑራኤል

- ፳፪ -

ደቅስዮስ፣ ብሥራተ ገብርኤል ቅ. ዑራኤል

ወቦአ መልአክ ኀቤሃ ወይቤላ ተፈሥሒ ፍሰሕት እ ምልአተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ ቡርክት አንቲ እምአንስት ።

ትርጉም ፤ መልአኩም ወደ እሷ መጥቶ ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ፤ እግዚአብሔር ካንቺጋር ነው ፤ ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ አላት (ሉቃ. 1፤28 ፤ ዮሐ. 1፤16)።

ጥቅምት ፳፪ ቅዱስ ሉቃስ ይከበራል። ታኅሣሥ ፳፪ የጥልጥልያ ጳጳስ አባ ደቅስዮስ በዐልዋን ያወጀበት ተአምራቱን የለበሰበት ዕለት የሚከበርበት ቀን ነው።

ብሥራተ ገብርኤል – ዘገብርኤል

- ፳፫ -

በዓለ ቅ. ጊዮርጊስ

የፈሰሰውን የባሮችኽን ደም በቀል ። የስረ ኞቹ ጩኸት ወደ ፊትኽ ይግባ (መዝ. 78 (79) ፤ 10)።

ሚያዚያ ቅ. ጊዮርጊስ ሰማዕት የኾነበት ዕለት ነው ።

መቅደሰ ጊዮርጊስ
ማኅደረ ጊዮርጊስ
ሜላተ ጊዮርጊስ - ስርጉተ ጊዮርጊስ

ሰበነ ጊዮርጊስ
የዐፄ ልብነ ድንግል አምስተኛ ሴት ልጅ ሰበነ ጊዮርጊስ በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር ።

ሥጊነ ጊዮርጊስ – ቀጸላ ጊዮርጊስ

አመተ ጊዮርጊስ
የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የልጅ ልጅ የበእደ ማርያም ሴት ልጅ አመተ ጊዮርጊስ በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር ።

አሣዕነ ጊዮርጊስ – አኅተ ጊዮርጊስ
ዐሥራተ ጊዮርጊስ
ዕሴተ ጊዮርጊስ
ወለተ ጊዮርጊስ - ፍቅርተ ጊዮርጊስ
ዘጊዮርጊስ – ዜና ጊዮርጊስ

- ፳፬ -

አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፣ ፳፬ወ፪ቱ ካህናተ ሰማይ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ፣ ስደተ ግብፅ

ወዘተወክረ ጸድቀ በስመ ጸድቅ ዕሰበ ጸድቅ ይነሥእ።

ትርጉም ፤ እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ያገኛል ጻድቅን በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል (ማቴ. 10፤40 ፤ 18፤5 ፤ ሉቃ.10፤16 ፤ ዮሐ. 13፤20) ።

በኅዳር ፳፬ ቀን ፳፬ቱ ካህናተ ሰማይ የሚከበሩበት፤ ታኅሣ ፳፬ ጻድቁ ተክለ ሃይማኖት የተወለዱበት፤ ነሐሴ ፳፬ ያረፉበት ፤ በግንቦት ፳፬ ቅድስት ድንግል ማርያም ሄሮድስ ልጇን እንዳይገ

ልባት ፤ ከሰሎሜና ከዮሴፍ ጋር ወደ ግብፅ የተሰደደችበት ዕለት ነው ።

ወለተ ተክለ ሃይማኖት
የዐፄ ባካፋ ሴት ልጅ ወለተ ተክለሃይማኖት በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር ።
በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ገዳም ከ1838 ዓ.ም. ጀምሮ የመኖሪያ ጎጆዎቹን በመሥራት ካቀኑት ሴቶች አንዷ እማሆይ ወለተተክለ ሃይማኖት በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይታወቁ ነበር።

መዐዛ ተክለ ሃይማኖት
ሥጊነ ተክለ ሃይማኖት
አኅተ ተክለ ሃይማኖት
ፍቅርተ ተክለ ሃይማኖት
ትርሢተ ተክለ ሃይማኖት

ጽድቃን

የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል።
ከክፉ ነገር አይፈራም ። በእግዚአብሔር ለመታመን ልቡ የጸና ነው (መዝ. 111 (112) ፤6)።

ስርጉተ ጻድቅ ..– ሲሩተ ጻድቅ
አስካለ ጻድቅ – እኅተ ጻድቅ
ወለተ ጻድቃን – ዕሴተ ጻድቅ
ፍቅርተ ጻድቅ – ጸሎተ ቅዱሳን

ቅዱሳን

አስመ ኢትፈቅዳ ለሠናይትየ። ለቅዱሳን አለ ውስተ ምድር።
ተሰብሐ ኩሉ ሥምረትከ በሳእሌሆሙ።
ትርጉም ፤ ፈቃድህ ኹሉ በምድር ባሉት ቅዱሳንና ከኵራን ላይ ነው (መዝ. 15፤3) ።
መዐዛ ቅዱሳን – መቅደሰ ቅዱሳን
ማኅደረ ቅዱሳን – ሣህለ ቅዱሳን

አስካለ ቅዱሳን – እኅተ ቅዱሳን

ወለተ ቅዱሳን
የቅዱሳን አገልጋይ ማለት ነው። በዚህ ስም የንጉሥ ልብነ ድንግል ስድስተኛ ሴት ልጅ ወለተ ቅዱሳን ተብለው ተጠርተዋል። ያረፉበት ዘመን (1550 ዓ.ም. በግራኝ ጦርነት ጊዜ ነው።)

ዘቅዱሳን – ዜና ቅዱሳን

- ፳፭ -

በዓለ ቅ. መርቆሬዎስ ሰማዕት

የፈሰሰውን የባሮችኽን ደም በቀል ። የስረ ኞቹ ጩኸት ወደ ፊትኽ ይግባ (መዝ. 78 (79) ፤10)።

ግንቦት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሕጻ ንነቱ ዘንጎችን ተክሎ ዛፎች ያደረገበት አለት ነው ።

ወለተ መርቆሬዎስ

- ፳፮ -

ቅ. ቶማስ ሐዋርያ ፣ ቅ. ዮሴፍ

የፈሰሰውን የባሮችኽን ደም በቀል ። የስረ ኞቹ ጩኸት ወደ ፊትኽ ይግባ (መዝ 78 (79) ፤10)።

ግንቦት ሐዋርያው ቶማስ የዕረፍቱ መታሰቢያ ቀን ነው ።

- ፳፯ -

መድኃኒዓለም

እግዚአብሔርስ ንጉሥ ውእቱ አምላከ ዓለም፤ ወገብረ መድኀኒተ በማእከለ ምድር
ትርጉም ፤ እግዚአብሔር ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው ። በምድርም መካከል

መድኀኒትን አደረገ ። እንተ ባሕርን በኀይል አክ አጸናኻት (መዝ.73(74)፥12)።

መጋቢት ፳፭ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒዓለም የተሰቀለበ ፤ (ጥንተ ስቅለት) ነው። ጥር ፳፭ ሱርያል (ሊቃነ መላእክት) ይከበራል።

ወለተ መድኅን – መርዐተ መድኅን
ስርጉተ መድኅን – አስካለ መድኅን
አኅተ መድኅን – ፍቅርተ መድኅን

ክርስቶስ

ኢየሱስ ክርስቶስ እንደኾነ ለማንም ለማን እንዳይናገሩ አዘዛቸው (ማቴ. 16፥21)።

መርዐተ ክርስቶስ - መዓዛ ክርስቶስ
መቅደስ ክርስቶስ- ማኅደረ ክርስቶስ
ምዕራፈ ክርስቶስ - ወለተ ክርስቶስ
ስርጉተ ክርስቶስ

አኅተ ክርስቶስ
በ1609 ዓ. ም. በዐፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት ንጉሡን በመኮትኰካቸው የተ ቃወሙ ። በስመ ጥምቀታቸው ይታወ ቃሉ።

ብርሃነ ክርስቶስ – አመተ ክርስቶስ
አስካለ ክርስቶስ

ክርስቶስ ሠምራ
ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ በዚህ ስም ትታወቃለች (ስንመለ. 24)።

ዘክርስቶስ – ጸጋ ክርስቶስ
ፍቅርተ ክርስቶስ

- ፳፭ -

በግኦኤል

ወናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ወይ ሰመይ ስሙ በግኦኤል
ትርጉም ፤ እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ልጅም ትወልዳለች ስሙም በግኦኤል ይባላል (ኢሳ. 7፥14 ፤ ማቴ. 1፥23 ፤ ሉቃ. 1፥31)።

ታኅሣሥ ፳፭ ቀን ገና (ልደት) በዘመነ ዮሐንስ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን መዋሉ ቀርቶ ፤ በዚህ ቀን ይውላል።

ስርጉተ አግኦኤል
ትርሢተ አግኦኤል
አኅተ አግኦኤል
ወለተ አግኦኤል
ፍቅርተ አግኦኤል

ሰንበት

መጽአ ላእሌየ መንፈሰ በዕለተ ሰንበት እሑድ ወሰግእኩ ቃለ ዐቢየ (ራእ.1፥10)።

ወለተ ሰንበት - ሰንበት ኀይላ
ኂሩተ ሰንበት

አምላክ

እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ። (ዘጸ. 20፥1)

ማኅደረ አምላክ – ብርሃነ አምላክ
ኂሩተ አምላክ – ዕሴተ አምላክ
ውዳሴ አምላክ – ዘአምላክ
ዜና አምላክ – ፍቅርተ አምላክ

- ፳፱ -

በዐለ ወልድ (ትስብእት) ወይም በዐለ እግዚእ

ወወለደት ወልደ ዘበኵራ ወአስረቶ መንኰብ ያቲሁ፤ ወጠብለለቶ በአዕርቅትኒ ወአስከበቶ ውስተ ኅጸ ፤
ትርጉም ፤ የበኵር ልጇንም ወለደችው አውራ ጣቱንም አሰረችው ፤ በጨርቅም ጠቀለለችው ፤ በበረትም አስተኛቸው (ሉቃ. 2፥7)።
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደትን በሰባር ዓመት በዘመነ ዮሐንስ ታኅሣሥ ፳፭ ይኾናል ። መጋቢት ፳፱ ደግሞ ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታን የፀነሰ ችበት ዕለት ነው ።

ማኅደረ ወልድ – ትርሢተ ወልድ
ኂሩተ ወልድ – አስካለ ወልድ
አኅተ ወልድ – ወለተ ወልድ
ፍቅርተ ወልድ

እግዚእ ኀረያ
የጸድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት እናት እግዚእ ኀረያ በመባል በስመ ጥምቀታ ቸው ይጠሩ ነበር።

እግዚእ ክብራ

አመተ መሢሕ
የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የልጅ ልጅ የበእደ ማርያም ቤተ ልጅ አመተ መሢሕ በመ ባል በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

- ፴ -

ቅ. ማርቆስ ሐዋርያው

ወአስከ አጽናፈ ዓለም በጽሐ ነቢቦሙ።
ትርጉም ፤ ቃላቸው አስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ (መዝ. 18፥3)።

አስካለ ማርቆስ – አኅተ ማርቆስ
ወለተ ማርቆስ – ፍቅርተ ማርቆስ

በትንሣኤ

ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመ ዘንቃህ አምኀ ዋም። ትርጉም ፤ እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ (መዝ. 76፥65)።

ወለተ ትንሣኤ – ብርሃነ ትንሣኤ
ትንሣኤ ብርሃን– ትንሣኤ ኢየሱስ
ትንሣኤ ክርስቶስ – የማነ ብርሃን
እንቀጸ ብርሃን

ቃል

ዐርገ እግዚአብሔር በይባቤ ።
ትርጉም፤ እግዚአብሔር በመለከት ድምጽ ዐረገ (መዝ. 46፥5)።

ማኅደረ ቃል – ብርሃነ ቃል
አመተ ልዑል – አኅተ ቃል
ዕርገተ ኢየሱስ

ጸጉሜ ፫ ሩፋኤል

ከከበሩ ከመላእክት አንዱ ሩፋኤል ነው። (መጽ. ሄኖ. 6፥3)።

አኅተ ሩፋኤል – አስካለ ሩፋኤል

ወለተ ሩፋኤል
ደጃዝማች ኀይሉ አሸቴ (1674- 1699 ዓ.ም.) የዐፄ ኢያሱ አድ ያም ስገድ የልጃቸው ልጅ የኾኑት እናታቸው በስመ ጥምቀታቸው ወለተ ሩፋኤል ተብለው ይጠሩ ነበር።

በዚህ ውስጥ ያልተጠቃለሉ የክርስትና ስሞች ሊኖሩ ይችላሉ ። በጥናት ተስማ ሚ ናቸው የተባሉት እንዲሁም ብዙ ጊዜ የሚሰሙትን ለማቅረብ ተሞክሯል።

ሰ.ክ

ምዕራፍ ፫

የማዕርግ ስሞች (ስመ ተቀብዖ)

የማዕረግ ስሞች እነዚህም፦ ያክብሮት ፣ የሙያ፣ የሥልጣን፣ የክህነት የቤተ መንግሥት፣ የወታደር ስሞች ፤ ከመጠሪያ ስሞች ኋላ እየገቡ ዋናውን ስም ያደምቁታል ፤ አንዳንዴም ብቻቸውን መጠሪያ በመኾን ያገለግላሉ ።

(ሀ) ጳጳሳት ቅብዐ ክህነት ሲቀቡ የሚሰየሙት ስሞች

ጳጳስ ቃሉ በግሪክ ቋንቋ ሲኾን ትርጉም ጠባቂ (አረኛ)፣ ተቆጣጣሪ የሃይማኖት መሪ ማለት ነው። መነኰሳት ከሚኖሩበት ገዳም ወይም ደብር በምግባራቸው ፣ በጸሎታቸው፣ በዕውቀታቸው ለዚህ ማዕረግ ተመርጠው ሲበቁ ፤ ዐዲስ የሐዋር ያነት የብፅዕና ስም ይሰጣቸዋል ።

በጠባቂነት የነበሩትን አባቶች ሐዋርያትን ከዚያም ተላቂ ሐዋርያት ኾነው ያለፉትን አባቶች ፤ የቅዱሳንን ፤ ያለፉ አባቶች ስም ይወርሳሉ ። ውር ርሱም ቀዳማዊ ፤ ዳግማዊ ፤ ሣልሳዊ እየተባለ ይቀጥላል እንጂ አይቋረጥም ማለት ነው ።

ቅዱስ ጴጥሮስ ሊቀ ሐወርያት ተብሎ ከመጠራቱ በፊት ስምዖን ነበር ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የጠባቂነት ማዕረግ ሰጥቶት ጴጥሮስ ብዬሀ ለሁ ብሎታል። ከዚያም አንተ ብፁዕ ነኽ አለው ። ጳጳሳት ሲመረጡ የቀድሞ ው የመጠሪያ ስማቸውን ይቀየራል ። በምትኩም የሐዋርያት ስም ወይም የሐ ዋርያት ተከታይ የነበሩ አባቶች ስም የቅዱሳን ስም ይሰጣቸዋል ማለት ነው።

ይህም የብፅዕና ሥልጣን የተለየ ንፁሕ ፤ መንፈሳዊ የታመነ ፤ ሠራ ውና ልቡናው የቀና ፤ ቸር ፣ ብእሴ እግዚአብሔር የኾነ የበጎች ጠባቂ ይኾ ናል (ዮሐ. 1፡42 ፤ ማር. 16፡18)። ብፁዕ የመባል ትርጉሙም፤ ክቡር፣ ምስጉን፣ ምሩቅ፣ በክቡር እና በቅዱስ መካከል ያለ ማለት ነው።

እንደዚሁም ከጠባቂዎች ሊቃነ ጳጳሳት መካከል የጴጥሮስን ቦታ የሚይዝ የአባ ቶች አባት ማለትም በትረ-ያርክ ይመረጣል (በግሪክ ፓትሪአርኻ) ይህም ማለት ሊቀ ጳጳስ የሲኖዶሱ መሪ ቀዳሚ የሚኾን ከንቱ ውዳሴ የሌለበት ደግ አባት ፣ ጎዳጌ በቀል የሌለበት (ይቅር የሚል) ማለት ነው ። በዚህ መሠረት የሊቃነ ጳጳሳት ጉባኤ ሲኖዶስ ዐዲስ ጳጳሳት ስም እየሰየመ ይመርጣል (ሰንክሳር መጋ 13፣ ታኅሣ. 1)።

ለምሳሌ፦
ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ. ም. ሲመተ ጵጵስና የተፈጸመላቸው አምስቱ የኢትዮ ጵያ ጳጳሳት።

■ **አቡነ ባስልዮስ**
የመጀመሪያው የኢትየጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ናቸው። ሊቀ ጳጳስ ከመኾናቸው በፊት የመጀመሪያ የመጠሪያ ስማቸው ። እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ነበር ።

■ **አቡነ ሚካኤል**
የመጀመሪያ ስማቸው መምህር ገሪማ ወልደ ኪዳን በመባል ይታወቁ ነበር።

■ **አቡነ ቴዎፍሎስ**
መጠሪያ ስማቸው ሊቀ ሥልጣናት **መልእክቱ ወልደ ማርያም** በመባል ይታወቁ ነበር።

■ **አቡነ ያዕቆብ**
መምህር ዘፈረ ብርሃን ገብረ ጻድቅ ይባሉ ነበር ።

■ **አቡነ ጢሞቴዎስ**
የመጠሪያ ስማቸው ጌታኹን **ወልደ** ሐዋርያት (መምህር) ይባሉ ነበር ።

■ **አጨጌ የሚለው ስም ታሪክ።**
ከጸድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን ማንኛውንም አስተዳ ደር የሚመራ በደብረ ሊባኖስ በአቡነ ተክለሃይማኖት መንበር የሚቀመጥ ነው። አቡነ ተክለ ሃይማኖት በወላሞ ሞተሌሚ የሚባለውን ንጉሥ አስተምረው ከአረ መኔነት ወደ ክርስትና መለሱት። ከዚህ በኋላ እጨጌ አሏቸው። በወላሞ ቋንቋ ጨጋ ማለት በጣም የከበረ ሰው ማለት ነው። ከዚያ ተያይዞ የመጣ ሥርዓት የደብረ ሊባኖስ ገዳም እጨጌ እየተባለ በአስተዳደሩ ዅሉ ተጠሪ ፣ ተጠያቂ ኾኖ ኖረ ።

(ለ) ሥልጣነ ክህነት እና ያስተዳደር የማዕርግ ስሞች

(፩) የደብር አለቆች የማዕርግ ስም

ቀደም ባሉ ዘመናት ለታላላቅ ደብር የሚሾሙት አለቆች በነገሥታቱ ትዛዝ ሜምር በማዕርግ ይሾሙ ነበር።

- ንቡረ እድ የአከሱም እና የዐዲስ ዓለም አለቃ።
- ጸባቴ የደብረ ሊባኖስ የገዳሙ አስተዳዳሪ ያገሩ ተጠሪ ምስለኔ ነው።
- ሊቀ ሊቃውንት የበአታ ገዳም አለቃ ። የአለቆች አለቃ ።
- ሊቀ ሥልጣናት መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ አለቃ።
- ሊቀ ካህናት የካህናት አለቃ ፤ ሹም።
- መልአከ ብርሃን የደብረ ብርሃን ቅ. ሥላሴ አለቃ ።
- መልአከ ሰላም የአሰጢፋኖስ አለቃ ።
- መልአከ ገነት የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ አለቃ።
- መልአከ ፀሓይ አንጦሎ መንበረ ፀሓይ ቅድስት ማርያም አለቃ።
- አለቃ መሪ ፣ አስተዳዳሪ ማለት ነው።
- መምህር አስተማሪ አለቃ ማለት ነው።

ደብሩ ኹሉ የራሱ መጠሪያ ስላለው ለመግቢያ ያህል ለምሳሌነት ይህ የተገለጠው በቂ ነው ።

(፪) በደብር የክህነት አገልግሎት የማዕርግ ስሞች

- መምሬ

ሕግ ጠብቆ የሚኖር፤ የምእመናን መሪ፣ አስታዋሽ፣ አስተማሪ፣ ዘካሪ፣ የንስሐ አባት፣ ቀድሶ የሚያቆርብ፣ አምሮ ጠምጥሞ ጎላ ብሎ የሚታይ፤ ግርማ ሞገስ የተሞላ። የጸዋትወ ዜማ መምህር ሌሎችም ዕውቀቶች ሊኖሩት ይችላል።

- ቀሲስ (ግእ) ቄስ (ዐማ)

ተዘክረኒ ኦ አቡየ ቀሲስ ፤ (ቅዳ) ቀሰ አገለገለ ከሚለው ግስ የመጣ ነው ። ከመምሬ ጋር ተመሳሳይ ነው።

- ቄስ ገበዝ (ጎበዝ)

ብርቱ የቤተ ክርስቲያን ጠባቂ ፤ የሰሞነኞች አለቃ ፤ ምስጢር ዕቃ ጠባቂ ፤ የመንበር ቁልፍ በእጁ የኾነ ። ባለ አደራ ታማኝ ።

- ሊቀ ዲያቆናት

ከሰባቱ ዲያቆናት አንዱ አስጢፋኖስ ሊቀ ዲያቆን የዲያቆናት አለቃ ኾኖ ተሾሞ ነበር። በዚያ መሠረት የዲያቆናት አለቃ ታማኝ ፣ ንፁሕ፣ ግብረገብ ፣ ትጉህ ለሃይማኖቱ ቀናኢ የኾነ (የሐ. ሥራ. 6፤5)።

- ዲያቆን

ለተልእኮ የሚፋጠን የቁስ ረዳት የምእመናን አገልጋይ።

(፫) የአብነት ትምህርት ቤት መምህራን የማዕርግ ስሞች።

- መጋቤ ምስጢር የቅኔ መምህር።
- መጋቤ መዝሙር የዝማሬ መዋሥዕት ያቋቋም መምህር።
- መጋቤ ብሉይ የብሉይ ኪዳን መምህር።
- መጋቤ መምህራን የሊቃውንት መጻሕፍት መምህር።
- መጋቤ ምክር የመጽሐፍተ መነኰሳት መምህር።
- መጋቤ ስብሐት የምዕራፍ እና የጸመ ድጓ መምህር።
- መጋቤ ላእካን የፊደል ንባብ መምህር።

(፬) የሊቅነት ፣ የመዘምርነት የማዕርግ ስሞች።

- ሊቄ (የኔ ሊቅ)

ይህ ማዕርግ በጥንት ዘመን በነገሥታቱ ይሰጥ እንደነበር ይነገራል። የዐራቱን ጉባኤያት የሐዲስ እና የብሉይ፣ ፍትሐ ነገሥት፣ መጽሐፈ መነኰሳት መዝሙረ ዳዊት ሊቅ።

- ሊቀ ማዕምራን አጠቃላይ ዕውቀት ያለው።
- ሊቀ ጉባኤ የብሉይ የሐዲስ መምህራን አለቃ ።
- ሊቀ ጠበብት የጠቢባን በላይ ፣
- ሊቀ መዘምር የመዘምራኑ አለቃ ወይም ሊቀጠበብት።

አጠቃላይ ዕውቀት ያለው ፤ የደጓ ያቋቋም ፣ የቅኔ፣ የቅዳሴ፣ የትርጓሜ መምህር የኾነ። በነዚህ በአንዱ የሰለጠነ።

- ርዕሰ ደብር

የደብሩ ራስ በግራ በኩል የሚቆም ፤ የደብሩ የጸዋትወ ዜማ ሊቅ መምህር።

- መሪ ጌታ

ያቋቋም የጽዋትወ ዜማ ይትበሀልን ጠብቆ የማሕሌትን ሥርዓት የሚያስከብር።

■ ቀኝ ጌታ

በቀኝ በኩል የሚቆም የጸዋትወ ዜማ ሊቅ። በቀኝ ያለውን የዜማ ስልት የማሕሌቱን ሥርዓት የሚጠብቅ።

■ ግራ ጌታ

በግራ በኩል የሚቆም የጸዋትወ ዜማ ሊቅ። በግራ ያለውን የዜማ ስልት የማሕሌቱን ሥርዓት የሚጠብቅ።

■ ደብተራ በቤተመንግሥት በድንኳን የሚያገለግሉ ነገሥታት ስለ ቤተክርስቲያን የሚያከራክሯቸው ሊቃውንት ናቸው። ትርጉሙም ድንኳን ማለት ነው (ካህናተ ደብተራ)

■ አጋፋሪ ሥርዓት አስጠባቂ ፤ የካህናት አስተባባሪ።

■ መጫኔ ከአጋፋሪ ቀጥሎ ተጠያቂ አስተባባሪ።

■ ዐቃቢት ጠባቂት፤ ተመልካች- የቁርባኑን መገበሪያ የምታዘጋጅ። (1ጢሞ. 5፥9)

(ኗ) የመነኰሳት ገዳማውያን የማዕርግ ስሞች።

■ ቆሞስ ምንኩስና ሰጭ፣ ታቦት ባራኪ።

■ አበ ምኔት አባት ፤ መነኰሴ (አስተዳዳሪ) ባለገዳም።

■ አመምኔት የመነኰሳይያት አለቃ ፤ እናት (አስተዳዳሪ)።

■ አጎው ወንድሞች በገዳም የሚኖሩ የመነኰሳት ማኅበር።

■ አኃት አኃቶች መነኰሳይያት ማኅበር።

■ ሊቀ ምርፋቅ ስለ ገዳሙ ጉዳይ የሚሰበሰብ አለቃ

■ ሊቀ ረድ በገዳም መነኰሳት የሚረዱ መነኰሳት ሹም።

■ ሊቀ መጣኒ መጋቢ ፣ የመጋቢዎች አለቃ።

(ሐ) ነገሥታት ቅብዐ መንግሥት ሲቀቡ የሚሰየሙት ስሞች

ነቢይና ካህን የነበረው ሳሙኤልን ሕዝቡን ይመራ ዘንድ **የንግሥና ቅብዐት እንዲቀባ** እግዚአብሔር አዘዘው። **በዚህ ትዛዝ ሳዖልን** ቅብዐ መንግሥት ቀብቶ ንጉሥ አደረገው (1ኛ ሳሙ. 10፥1) ።

ከዚያም **በሳዖል** ምትክ እንደ ገና ዳዊትን ቀባው (2ኛሳሙ. 1-24)። ከዚህ በወረደው ንግሥና መሠረት የኢትዮጵያ ነገሥታት አስከ **ዐፄ ገብረ መስቀል** ዘመነ መንግሥት ድረስ (515 ዓ.ም) ሥርዓተ ንግሣቸው ሳባ እና የንጉሥ ሰሎሞን ልጅ ቀዳማዊ ምኒሊክ ከኢየሩሳሌም ባመጡት በዚህ የንግሥና ሥርዓት መሠረት ይካኼድ ነበር።

ዐፄ ገብረ መስቀል በአክሱም ሲነግሡ የአሪቱን ሥርዓት ለውጠው በክርስትና ሥርዓት እንዲኾን አደረጉ። ሕዝቡም ፣ ወጣቶች (ሕፃናት) የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው ፤ ካህናቱ (ቀሳውስቱ) መስቀልና ጽና ይዘው፤ ከዳዊት "ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር" ትርጉም በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው። (መዝ. 117(118)፥3) በማለት እየዘመሩ ስለ ንግሥና ስለ ክህነት የሚናገረውን ቃል ከአሪትም ከነቢያትም ከሐዲስም አይመረጡ በልዩ ልዩ መንገድ በድግምት በዜማ እያዜሙ ይጸልዩ ነበር ።

የነጉሡ ዙፋን ከቅኔ ማሕሌት ይዘረጋል ፥ ዙሪያውን አበባ ይነሰነሳል። በዙፋኑ ላይ አበባ ምንጣፍ ተነጥፎ በዚያ ላይ ይቀመጣል። የወርቅ የብር ሳህን ባንዱ ወተት ፥ ባንዱ ጠጅ፥ ባንደኛው ወይን አምጥተው የንጉሡን ራስ ይቀቡታል ። የዮርዳኖስንም ጠበል ይረጩታል። የራሱን ጠጉር ቆርጠው ቀሳውስትና ዲያቆናት ከጥና ጋራ ወሰደው ሦስት ጊዜ ታቦቱን ይዞሩና መልሰው አምጥተው የነገሥታት መማጸኛ ደንጊያ በሚባለው ላይ ያስቀምጡና በላዩ ክጽናው ውስጥ ያለውን የሳት ፍህም አፍስሰው ንጉሡን እግዚአብሔር አይለይህ ። እግዝአትን ማርያም ትርዳህ ፤ ሺ ዓመት ያንግሥህ፤ ብለው አማጽነው ይመርቁታል። ከዚያ እምቢልታ ነጋሪት መመታት ይቀልጣል። ንጉሡ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ስለ መንግሥቱ ወደ እግዚአብሔር ይማጽናል ይጸልያል።

ዛሬም በአክሱም በዐፄ ፋሲል ባሳነጹት ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት የሚታዩ ዐሥራ ኹለት የደንጊያ ወንበሮች ስድስቱን በቀኙ ስድስቱን በግራው አድርጎ በመካከል ይቆማል ። ጳጳስ ፣ ቀሳውስት ፣ ካህናት ፣ ዲያቆናት አፊቱ እየመጡ ሺ ዓመት ያንግሥህ ይሉታል።

ታላላቆች፣ ሹማምንት፣ ሰራዊት በየወገናቸው ይቀበሉታል ። ደናግል ሴቶች የቀይ ሐር መጋረጃ በቀኝና በግራ ይዘው መንገዱን ይዘጉበታል ። ከልጃገረዶቹ አንዷቱ "መኑ ውእቱ ዝንቱ" ትርጉም "አንተ ማነህ!" (መዝ. 23፥10) ብላ ትጠይቀዋለች ። እሱም "ንጉሥ ነኝ" ይላታል ፤ አይደለህም ትልና አንደ ገና አንተ ማነህ ! ብላ ስትጠይቀው "ንጉሥ ነኝ" ይላታል ፤ ጥያቄውና መልሱ ኹለት ጊዜ ከተደጋገመ በኋላ በሦስተኛው አንተ ማነህ ! ስትለው ሰይፉን መዘ የሐሩን መጋረጃ ይቆርጠውና "የጽዮን ንጉሥ እኔ ነኝ" ይላታል። በዚህ ጊዜ የጽዮን ንጉሥ እውነት በእውነት (አማን በአማን) ስትለው ሕዝቡም አርሷን ተከትለው "የጽዮን ንጉሥ አማን በአማን መንግሥተ — ዘለዓለም።.... ይሉታል ። ይህ ሥርዓት **ዐፄ ገብረ መስቀል** በዘመናቸው የደነገጉት ነው ይባላል ።

ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ አሻሽለው ያወጡትና በዐፄ ኢያሱ (ስመ መንግሥታቸው እድያም ሰገድ) ዘመነ መንግሥት ታደሰ የሚባለው ቅብዓ ቅዱሰን ሌላም ወግና ሥርዓት ይጨምራል ዐሥራ ሰባት ቅመም የተቀመመ በሎሚ ውሃ የተለወሰ ቅብዐ

ማ

ቅዱስ (አፍዋተ መንግሥት) እንዲሁም ከወደ ምሥራቅ ከሚፈስ ውሃ አምጥተ ው ሰባት ዕጣን ጨምሮ ሰባት መነኩሳት መዝሙረ ዳዊት (መዝ 23) ከነቢያት እንዲሁም መሕልየ ሰሎሞንን ውዳሴ ማርያም ፤ አንቀጸ ብርሃን ፤ መልከአ ተክለ ሃይማኖት እየደገሙ ሰባት ሱባኤ ገብተው ይጸልያሉ ።

ሲነግሥም "ንዑስ አነ እም አጎውየ" ትርጉም "ከወንድሞቼ ይልቅ ትንሽ ነበርኩ" ከሚለው ጀምሮ "ወቀብዐኒ ቅብዐ ቅዱስ" ትርጉም "ቅብዐ መንግሥትን ቀብቶ አነገሠኝ" እስከሚለው (መዝ.150 ፥1-4) በግእዙ ይደገማል ።

ከሀናቱም ተቀብለው "ተክአወ ሞገሰ አምከናፍረከ" ትርጉም "ሞገስ ከከን ፈሮችህ ፈሰሰ" ይሉና "ቅንት ሰይፈከ ጎያል ውስተ ሐቋከ" ትርጉም "ሰይፍኽን በወገብህ ታጠቅ" (መዝ. 44(45)፥3) እያሉ ባለወርቅ ሰገባ ሰይፍ ያስታጥቁታል።

ከዚያም "አርትዕ ተሠራሕ ወንገሥ" ትርጉም "አቅና ተከናወን ንገሥም" (ቁ. 3) ይሉና ወደ ቤተ መቅደስ ይገባሉ ። ከዚያም ጳጳሱ ቅብዓ መንግሥት የተቀመመውን ሜሮን በራሱ ላይ ያፈሱበታትል ። ስመ መንግሥት የሚኾን ስም እየተመረጠው ይቀርባል ። ዐዲሱ ስመ መንግሥቱ ይኩን ስምከ አገሌ ..... ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሥዩመ እግዚአብሔር ይሉታል።

የወርቅ ዘንግ ያስጨብጡታል ፤ የወርቅ ዘውድ ይደፉለታል ፥ በወርቅ ዙፋን ላይ ይቀመጣል ። ከሀናቱ መንበርከ አግዚኦ ለዓለም ፤ ከርቤ ወቀንአት የሚለው ላይ ሲደርሱ (ቁ.6) ያቆማሉ ። ከዚያም ዲያቆኑ ወዐልዐልኩ ኅሩይየ አምሕዝብየ ይልና ምስባክ ይሰብካል።

ንቡረ እዱ (አለቃው) ከሱቃስ ወንጌል ብእሲ ክቡር ትርጉም "አንድ የከበረ ሰው መንግሥት ይዞ ሊመለስ ወደ ሩቅ አገር ኼደ" (ሉቃ. 19፥12) የሚለውን ያነባል ፤ ጳጳሱ "በእንተዝ ቀብዐከ አግዚአብሔር አምላክከ" ትርጉም "አ ግዚአብሔር አምላክህ የደስታ ዘይት ቀባህ" (መዝ.44(45)፥7) አያለ ይቀባዋል።

ይህም ዓይነቱ ሥርዓት ሴት ልጅ ስትዳር የዳቦ ስም እንደሚሰየምላት ኹሉ የንጉሡም በዚሁ ዓይነት ከብዙዎቹ ስሞች ተመርጦ ዕጣ ይወጣና ስመ መንግሥቱ ተሰጥቶት ይነግሣል ማለት ነው።
በዚህ ዓይነት ሲሰየም ኖሯል። በምሳሌነትም ከዚህ በታች ቀርበዋል።

መጠሪያ ስም	ስመ መንግሥት
▪ ዐፄ ይኩኖ አምላክ	ተሰፋ ኢየሱስ (1263-1277 ዓ.ም)
▪ ዐፄ አምደ ጽዮን	ገብረ መስቀል (1307-1336 ዓ.ም)
▪ ዐፄ ንዋየ ማርያም	ውድም እስፈሪ (1364- 1374 ዓ.ም)
▪ ዐፄ ዳዊት	ቆስጠንጢኖስ (1374 -1406 ዓ.ም)
▪ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ	ቆስጠንጢኖስ (1426-1460 ዓ.ም)

▪ ዐፄ በእደ ማርያም	ዳዊት (1461 -1471 ዓ.ም)
▪ ዐፄ እስክንድር	ቆስጠንጢኖስ (1471 - 1487 ዓ.ም)
▪ ዐፄ ናዖድ	መርስኤ ሐዘን (1488 - 1500 ዓ.ም)
▪ ዐፄ ልብነ ድንግል	ወናግ ሰገድ (1500 - 1533 ዓ.ም.)
▪ ዐፄ ገላውዴዎስ	ኢጥናፍ ሰገድ (1533- 1551 ዓ.ም.)
▪ ዐፄ ሚናስ	አድማስ ሰገድ (1551-1555 ዓ.ም.)
▪ ዐፄ ሠርጸ ድንግል	መለክ ሰገድ (1555-1589 ዓ.ም.)
▪ ዐፄ ፋሲል	ዓለም ሰገድ (1624 - 1660 ዓ.ም)
▪ ዐፄ ዮሐንስ	አእላፍ ሰገድ (1660 - 1674 ዓ.ም.)
▪ ዐፄ ኢያሱ	እድያም ሰገድ (1674 -1698 ዓ.ም.)
▪ ዐፄ ተክለ ሃይማኖት	አብራክ ሰገድ (1698 -1700 ዓ.ም.)
▪ ዐፄ ቴዎፍሎስ	አጽራር ሰገድ (1700 -1704 ዓ.ም.)
▪ ዐፄ ዮስጦስ	ፀሐይ ሰገድ (1704 - 1708 ዓ.ም.)
▪ ዐፄ በካፋ	መሚሕ ሰገድ (እስክንድር)(1713 - 23 ዓ.ም.)
▪ ዐፄ ዳዊት	አድባር ሰገድ
▪ ዐፄ ኢያሱ	ብርሃን ሰገድ (1723 -1747 ዓ.ም.)
▪ ዐፄ ኢዮአያስ	እድያም ሰገድ (1747 -1761 ዓ.ም.)
▪ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ	ፍቅር ሰገድ (1772 - 1777 ዓ. ም.)
▪ ዛህለ ሥላሴ	ንጉሥ ዛህለ ሥላሴ (1832 -1840 ዓ.ም)
▪ በዣህ ውረድ	ንጉሥ ኃይለ መለኮት (1840-1848 ዓ.ም)
▪ ደጃዝማች ካሣ	ዐፄ ቴዎድሮስ (1848 -1860 ዓ.ም.)
▪ ወሜም ጎበዜ	ዐጼ ተክለ ጊዮርጊስ (1860 -1864 ዓ.ም)
▪ በዝብዝ ካሣ	ዐፄ ዮሐንስ (1864 -1888 ዓ.ም.)
▪ ምኒልክ	ዐፄ ምኒልክ (1881 -1906 ዓ.ም)
▪ ልጅ ኢያሱ	ክፍለ ያዕቆብ (1906 -1909 ዓ.ም.)
▪ አስካለ ማርያም	ንግሥት ዘውዲቱ (1909-1922 ዓ.ም.)
▪ ደጃች ተፈሪ	ዐፄ ኃይለ ሥላሴ (1922-1967 ዓ.ም.)

(፩) አባ – የሚለው የማዕርግ እና የመጠሪያ ስም

አባ ከመጠሪያ ስም ጋር ተጨምሮ የሚነገር የክብር ተቀጽላ ነው ። በሃይማኖት መነኩሴ የኾነ በአባትነት የሚታይ አባ አገሌ ወይም ባሮሩ አባ በመባል ይጠራል ።

- **አባ ጊዮርጊስ** የጸሎት መጻሕፍትን የደረሱ (1417 ዓ. ም.)
- **አባ ባሕርይ** መዝሙረ ክርስቶስንና የኦሮሞን ታሪክ የጻፉ።(1528 ዓ.ም.)

በኹለተኛ ደረጃ ደግሞ አባ የሚለው ቅጽል በባህል ረገድ የመጀመሪያ ልጅ በኩር (አንጋፋ) ሲወለድ አባት የኾነው አባ አገሌ ወይም የአገሌ አባት እየተ ባለ ይጠራበታል። በተለይም በኦሮምኛ ባህል በመጀመሪያ ልጅ መጠራት የተለ መደ ነው ። ሴት ልጅም ብትኾን ወንድ ልጅ የመጀመሪያ ከኾነ በልጁ ስም ይጠራል። ለምሳሌ ሙሴ ከኾነች አባ ሙሴ ። ይጠራል ማለት ነው ። አንዲ ሁም ደግሞ አባ ወራ ፤ የቤት ጌታ ፤ ባለቤት አሳዳሪ ማለት ነው ።
የጅግ ባለአባቶች አባ በሚለው ቅጽል ስም ይጠራሉ

- **አባ ጅፋር** - የጅፋር አባት

አባ ጅፋር በዐፄ ምኒልክ ዘመን የጅግ ባላባት ነበሩ ። የአባ ጆቢር ልጅ አባ ቢያ በአዲስ አበባ ዩኒበርሲቲ የሕግ ምሩቅ የኾኑ የኦርቶዶክስ ክርስትና አማኝ ነዋሪነታቸው በአሜሪካ ነው ።

- **አባ ቢያ** – ያገር አባት ፤ ዋና የአገር ተጠሪ አስተዳዳሪ ማለት ነው።
- **አባ ገዲ**
- **አባ ዱላ**
- **አባ ገዳ**

ምስተኛው አባ ግን የኢትዮጵያውያን ነገሥታት፤ አርበኞች ፤ በፈረስ ጉግሥ ጫወታ ፈረሳቸው የሚጠራበት ስም አባ በማለት ቅጽል ተሰጥቷቸው ይጠሩበ ታል። ይህ የንጉሥ ጨዋታ ብዙ ጊዜ ይታይ የነበረው ክልደት ጊዜ ጀምሮ ባለው ጊዜ ውስጥ ነበር ። ለዚህ ለጥምቀት በዓል እና ለአስተርዮ እንደ ገና ጨዋታ ግጥሚያ ይኖር ነበር ። ጨዋታው ከግብ አስከ ግብ በመጋለብ ለጠላት ሳይገኝ መቅደም ። ከኋላው እየሮጠ በሽመል ሲሰበቅበት በጋሻው መከላከል ነበር ።
የኢትዮጵያ ሕዝብ የፈረስ ግልቢያ ወይም የጉግሥ ልምድ ስለነበረው ለጦርነት ጊዜ ይረዳው ነበር። በፈረስ ግልቢያ ችሎታውና ጎይሉ ተማምኖ ጣሊያንን ድል ማድረግ ችሏል። ለምሳሌ ፦

- **አባ ዲና** ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ
- **አባ ዳምጠው** ንጉሥ ጎይለ መለኮት
- **አባ ታጠቅ** ዐፄ ቴዎድሮስ
- **አባ በዝብዝ** ዐፄ ዮሐንስ
- **አባ ዳኘው** ዐፄ ምኒልክ ነበሩ

- **አባ ጠቅል** ዐፄ ኀይለ ሥላሴ ነበሩ

ዐርበኞች

- **አባ ጉራቻ** ደጃዝማች ወልደሚካኤል ጉዲሳ
- **አባ ይትረፍ** ራስ አባተ
- **አባ ነጋ** ራስ ዐሉላ ምርጫው
- **አባ መቻል** ሪታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ
- **አባ ነፍሶ** ደጃች ባልቻ ፤ ለነፍሳቸው ይመጸውቱ ነበር።

(፪) ነገሥታት ማዕርግ ሲሰጡ የሚሰይሙት ስሞች።

ይህ የሹመት ስም ከጥንት ጀምሮ የነበረ ነው። በቅርብ ዓመታት ወዲህ የፊውዳሎች ስም ነው እየተባለ ይኰነናል ። ነገር ግን በቅዱስ መጽሐፍ እንደ ተገለጸው የንግሥት ህንደኬ በጅሮንድ እንደነበረ ይታወቃል (የሐ. ሥራ.8፥26)።

- **ዐፄ**

የማይወቀስ የማይከሰስ የሕዝብ አባት (ንጉሠ ነገሥት) ሥልጣኑን የሚያገኘው የዳዊት ወንበር የተባለው ላይ ተቀምጦ ከተጠመቀ በኋላ ነው።

- **መርዕድ** (ግእ) (መርድ)

ደባትሪሁ ዘነድ ወሠረገላሁ **መርዕድ**።
ትርጉም ፤ የሚያነቀጠቅጥ ጽምጹ የሚያስፈራ (ዕዝ. ሱቱ 1፥19)።
የከበራታ ስም ከንጉሥ በታች ከራሶች በላይ አልጋ ወራሽ የሚጠራበ ነው።

- **ልዑል**

ተለዓለ ከፍ ብፍ ያለ ማለት ሊኾን። ከፍተኛ ማዕረግ ነው።

- **ልዕልት** ከፍ ከፍ ያለች የንጉሣውያን ቤተሰብ ቤት ልጅ።
- **ራስ** የዘላይ ጦር አለቃ (ጀነራል) ማለት ነው።
- **ቢቶደድ** ጠቅላይ ሚኒስትር። (በልዩ ኹኔታ የተወደደ)
- **አፈ ንጉሥ** የፍርድ ሚኒስትር።
- **ጸሐፌ ትእዛዝ** የጽሕፈት ሚኒስቴር።
- **አዛዥ** የግቢ ሚኒስትር ።
- **በጅሮንድ** የገንዘብ ሚኒስትር።

(በጆሮ ወእድ – በጆሮና በእጅ?) ምስጢርን በጆሮ ነጋሪና የማምጃ ቤትን ቁልፍ አዛዥ ነው ። ለሴት ንግሥት በጆሮ ወንድ የሚኾነው ጃንደረባ ነው።

- **ነጋድራስ** የንግድ ሚኒስትር (ነጋ ድረስ?)።
- **ከንቲባ** የከተማ መዘጋጃ ቤት ሹም (ከንት ይባዕ?)።

- **ብላቴን ጌታ** — በሚኒስትርነት ለሠሩ የመጨረሻው ማረግ።
- **ሊቀ መኳስ** — ንጉሥ ሲነግሥና ግብር በግራና በቀኝ የሚቆም።
- **ብላታ** — ለሥራ ክፍል ኀላፊዎች የሚሰጥ ሹመት።
- **ልጅ** — የመኳንንት ልጆች መጠሪያ ስም።
- **መስፍን** — የነገሥታት ዘር የሌለው በጋብቻ የተዋሐደ አገረ ገዢ።
- **ራስ** — የመጨረሻ የዐርበኞች ማዕረግ (ዝነራል)።
- **ደጃዝማች** — ኃላ ላለ ተከላካይ ደጀን ጦር መሪ (ኩለኔል)።
- **ፊት አውራሪ** — ቀድሞ የሚጓዝ።
- **ቀኝ አዝማች** — በቀኝ ለሚዘምተው ለሚጓዘው ጦር አለቃ።
- **ግራ ዝማች** — በግራ በኩል ለሚዘምተው ጦር አለቃ።
- **መኰንን** — የሺ አለቃ፣ መቶ አለቃ ወይም ሃምሳ አለቃ።
- **ባላምባራስ** — (በዐለ ርእስ ወምባ) ኩለት ሻንበል አዛዥ ።

(ይ) ማንኛውም ሰው የሚጠራበት የክብር ስም።

- **ክቡር**

የክብር ስም ቅጽል። ፈረንጆቹ ሠር ይሉታል (ሚራ. 44፥1 ፤ ሕዝ. 26፥17)።

- **አቶ**

የማንኛውም ሰው የክብር መጠሪያ ስም ነው፤ አቶ ማለት አንተ ካለው ቅጽል የወጣ ነው። (አ–አባት ፥ ቶ–ቤት)።

- **እመቤት**

የቤት የክብር መጠሪያ ስም - የቤተሰብ አናት። የቤት ንግሥት ፤ ተጠሪ። (2ኛ ቆሮ. 11፥3)።

- **ወይዘሪት** — ያላገባች ሴት የክብር መጠሪያ ስም።
- **ወይዘሮ** — ያገባች ሴት የክብር መጠሪያ ስም።

በዚህ የሹመትና የማዕረግ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓትን ደረጃውን ለመተር ጉም ተሞክሯል። በአጠቃላይ ስለ ኢትዮጵያውያን የመጠሪያ ስም፣ የክርስትና ስም፣ የማዕረግ ስሞችን ሌሎችንም ተጠቃሎ ቀርቧል ። በጎደለው በመሙላት፤ የተገደፈውን በማስተካከል እንዲጠቀሙበት አሳስባለሁ ።

አስጀምሮ ላስፈጸመን ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው።
አሜን !!!

ሀ	ሁ	ሂ	ሃ	ሄ	ህ	ሆ
ለ	ሉ	ሊ	ላ	ሌ	ል	ሎ
ሐ	ሑ	ሒ	ሓ	ሔ	ሕ	ሖ
መ	ሙ	ሚ	ማ	ሜ	ም	ሞ
ሠ	ሡ	ሢ	ሣ	ሤ	ሥ	ሦ
ረ	ሩ	ሪ	ራ	ሬ	ር	ሮ
ሰ	ሱ	ሲ	ሳ	ሴ	ስ	ሶ
ሸ	ሹ	ሺ	ሻ	ሼ	ሽ	ሾ
ቀ	ቁ	ቂ	ቃ	ቄ	ቅ	ቆ
በ	ቡ	ቢ	ባ	ቤ	ብ	ቦ
ተ	ቱ	ቲ	ታ	ቴ	ት	ቶ
ቸ	ቹ	ቺ	ቻ	ቼ	ች	ቾ
ኀ	ኁ	ኂ	ኃ	ኄ	ኅ	ኆ
ነ	ኑ	ኒ	ና	ኔ	ን	ኖ
ኘ	ኙ	ኚ	ኛ	ኜ	ኝ	ኞ
አ	ኡ	ኢ	ኣ	ኤ	እ	ኦ
ከ	ኩ	ኪ	ካ	ኬ	ክ	ኮ
ኸ	ኹ	ኺ	ኻ	ኼ	ኽ	ኾ
ወ	ዉ	ዊ	ዋ	ዌ	ው	ዎ
ዐ	ዑ	ዒ	ዓ	ዔ	ዕ	ዖ
ዘ	ዙ	ዚ	ዛ	ዜ	ዝ	ዞ
ዠ	ዡ	ዢ	ዣ	ዤ	ዥ	ዦ
የ	ዩ	ዪ	ያ	ዬ	ይ	ዮ

ደ	ዱ	ዲ	ዳ	ዴ	ድ	ዶ
ጀ	ጁ	ጂ	ጃ	ጄ	ጅ	ጆ
ገ	ጉ	ጊ	ጋ	ጌ	ግ	ጎ
ጠ	ጡ	ጢ	ጣ	ጤ	ጥ	ጦ
ጨ	ጩ	ጪ	ጫ	ጬ	ጭ	ጮ
ጸ	ጹ	ጺ	ጻ	ጼ	ጽ	ጾ
ፀ	ፁ	ፂ	ፃ	ፄ	ፅ	ፆ
ፈ	ፉ	ፊ	ፋ	ፌ	ፍ	ፎ
ፐ	ፑ	ፒ	ፓ	ፔ	ፕ	ፖ

ቨ	ቩ	ቪ	ቫ	ቬ	ቭ	ቮ
ደ	ዱ	ዲ	ዳ	ዴ	ድ	ዶ

ኘ	ኙ	ኚ	ኛ	ኜ	ኝ	ኞ
ቐ	ቑ	ቒ	ቓ	ቔ	ቕ	ቖ

፩	፪	፫	፬	፭	፮	፯	፰	፱	፲
1	2	3	4	5	6	7	8	9	10

፳	፴	፵	፶	፷	፸	፹	፺	፻	፼
20	30	40	50	60	70	80	90	100	

ሏ ሟ ሯ ሷ ሿ ቧ ቷ ቿ ኗ ኟ ዟ ዷ ጧ ጯ ጿ ፏ ፗ ፟ ፧

አ	ቡ	ጊ	ዳ	ሄ	ው	ዞ
በ	ጉ	ዲ	ሃ	ቄ	ዝ	ዠ
ገ	ዱ	ሂ	ዋ	ዜ	ዥ	ዅ
ደ	ሁ	ዊ	ዛ	ዤ	ሕ	ጠ
ሀ	ዉ	ዚ	ዣ	ሔ	ጥ	ጨ
ወ	ዙ	ዢ	ሓ	ዜ	ጨ	ዮ
ዘ	ዠ	ሒ	ጣ	ጩ	ይ	ዅ
ዠ	ሑ	ጢ	ጫ	ዬ	ክ	ዅ
ሐ	ጡ	ጩ	ያ	ኬ	ኽ	ሎ
ጠ	ጩ	ዬ	ካ	ኼ	ል	ሞ
ጨ	ዩ	ኪ	ኻ	ሌ	ም	ኖ
የ	ኩ	ኺ	ላ	ሜ	ን	ኾ
ከ	ኹ	ሊ	ማ	ኔ	ኝ	ዖ
ኽ	ሉ	ሚ	ና	ኜ	ስ	ዯ
ለ	ሙ	ኒ	ኛ	ሴ	ሽ	ዖ
መ	ኦ	ኚ	ሳ	ቬ	ዕ	ፎ
ነ	ኯ	ሊ	ሻ	ዔ	ፍ	ጸ
ኝ	ሱ	ሺ	ዓ	ፌ	ጽ	ቆ
ሰ	ሹ	ዒ	ፋ	ጼ	ቅ	ሮ
ሽ	ዑ	ፊ	ጻ	ቈ	ር	ሥ
ዐ	ፋ	ጺ	ቃ	ሬ	ሥ	ቶ
ፈ	ጱ	ቈ	ራ	ሢ	ት	ች

ጸ	ቋ	ሪ	ሣ	ቴ	ች	ኖ
ቀ	ሩ	ሢ	ታ	ቼ	ኅ	ጸ
ረ	ሡ	ቲ	ቻ	ኄ	ጵ	ዖ
ሠ	ቱ	ቺ	ኃ	ጼ	ፀ	ፖ
ተ	ቹ	ኂ	ጳ	ዔ	ፐ	ጆ
ቸ	ኍ	ጲ	ፃ	ፔ	ጅ	አ
ኀ	ጱ	ፂ	ፓ	ጄ	እ	ቦ
ጳ	ፁ	ፒ	ጃ	ኤ	ብ	ኅ
ፀ	ፑ	ፒ	ጃ	ኤ	ብ	ኅ
ፀ	ፑ	ጂ	አ	ቤ	ግ	ዶ
ፐ	ጁ	ኢ	ባ	ጌ	ድ	ሆ
ጀ	ኡ	ቢ	ጋ	ዴ	ሀ	ዎ

ኰ	ኵ	ኲ	ኳ	ኴ
ጕ	ጙ	ጟ	ኟ	ጌ
ቈ	ቊ	ቋ	ቌ	ቄ
ጐ	ጔ	጖	ኋ	ኌ

ቿ	ቯ	ቷ	ቇ	ቈ

ዋቢ መጽሐፍት

- ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት) (አቡነ መልከ ጼዴቅ) ማኅበራዊ ኑሮ በኢትዮጵያ ። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት። ዐዲስ አበባ ።
- ለይኩን ብርሃኑ [ዶክተር] የግእዝ መማሪያ ዋሽንግተን ዲሲ ጥር 1998 ዓ. ም.።
- ሐዲስ ኪዳን በሊቃውንት ጉባኤ የተዘጋጀ ዐዲስ አበባ 1975 ዓ. ም.።
- መዝሙረ ዳዊት ትንሣኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት።
- መጽሐፈ ሰንክሳር በግእዝና ዐማርኛ ዅሉቱንም ያመቱን። ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት ዐዲስ አበባ 1993 ዓ. ም. ።
- መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ዐዲስ አበባ 1972 ዓ.ም. ።
- መጽሐፍ ቅዱስ I የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት 1980 ዓ.ም. ።
- መርሻ አለኸልኝ {ዲያቆን} ዜና ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን ማኅበረ ቅዱሳን ዐዲስ አበባ 1997 ዓ. ም. ።
- ማቴዎስ {አባ ማቴዎስ ሊቀጳጳስ}ደብረ ሥልጣን በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ታሪክ ማስታወሻ 1988 ዓ.ም. ።
- ተሰማ ሀብተ ሚካኤል I ከሳቴ ብርሃን ተሰማ ዐማርኛ መዝገበ ቃላት ዐዲስ አበባ 1951 ዓ. ም.
- ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል ዐዲስ አበባ ታሕሣሥ 1 ቀን 1966 ዓ. ም. ።
- ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ዐፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት 1983 ዓ. ም.።
- አማኩለ ገበየው ቅድስት አገር በኢየሩሳሌም ታሪካዊ ቦታዎች ኢየሩሳሌም 1992 ዓ.ም።
- ኤልያስ አያልነኽ ዐዲስ ዓለማየሁ በሐያስያን እይታ 1997 ዓ.ም።
- ከፍያለው መራሒ {ቀሲስ} ሴቶች በኢትዮጵያ ዐዲስ አበባ ሰኔ 21 ቀን 1988 ዓ.ም።
- ኪዳነወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ መዝገበ ቃላት ሐዲስ ዐዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1948 ዓ.ም.።
- ዳንኤል ክብረት {ዲያቆን} የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች 1999 ዓ. ም. ዐዲስ አበባ ማኅበረ ቅዱሳን።
- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ ዐዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ድርጅት መስከረም 1990 ዓ.ም. ።
- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የስልክ ቍጥር ማውጫ ዐዲስ አበባ 1999 ዓ. ም. ።
- ደስታ ተክለ ወልድ [አለቃ] ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት ዐዲስ አበባ 1962 ዓ. ም.
- ጌታቸው ጎይሌ [ፕሮፌሰር] ባሕረ ሐሳብ የዘመን ቈጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስ ታወሻ ጋር ኮሌጂቢል ሚኔሶታ 1993 ዓ. ም. ።
- ፋንታኹን እንግዳ ታሪካዊ መዝገቡሰብ ከጥንት አስከ ዛሬ ዐዲስ አበባ 2000 ዓ. ም.።
- መለከት መጽሔት ዴቅስዮስ ሽብሩ {ዲያቆን } (አዘጋጅ) አምስተኛ ዓመት ኀሐሴ 1989 ዓ. ም።



መልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት

በአጠቃላይ ይዘቱ በጣም ጥሩ ነው። ሐሳቡም ከዚህ በፊት ያልተዳሰሰና በዚህ ርዕስ መጽሐፍ ያልተዘጋጀ ስለኾነ ዝግጅቱ የተዋጣለት ነው።

ኾኖም መጽሐፉ ብዙ ወራትና ዓመታትን መስዋዕትነት ያስከፈለ መኾኑ የታወቀ ቢኾንም ለመጭውም ኾነ ለአለው ትውልድ ፈር ቀዳጅ መመራመሪያ መንገዱን እንደሚከፍት ጥርጥር የለውም። ዕውቀት በዶማ እንደሚቆፈር ጓሮ በበሬ እንደሚታረስ ማሳ ሳይኾን ከአንዱ ጭንቅላት ወደ ሌላው ጭንቅላት የሚተላለፍ የብርሃን ፋና ነው። ስለዚህ አንዱ ከሌላው አይቶና ሰምቶ የሚገበየው ሀብት ስለኾነ በጸሐፊው መልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት የተዘጋጀው መጽሐፍ ጠቃሚነቱ የጎላ ከመኾኑም ለሀገርም ኾነ ለወገንም ለትምህርት ቤት ማስተማሪያ ስለሚጠቅም ጸሐፊው የመጀመሪያ መጽሐፋቸው የመጨረሻ እንደማይኾን ባለሙሉ ተስፋ በመኾን ሌላም አዘጋጅተው እንዲያቀርቡልን ብርታቱንና ጽናቱን እንዲሰጣቸው ያምላክ ፈቃድ ይኹን።

አባ ማቴዎስ
የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊና
የዋግ ሕምራ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

ብዙ ወላጆች ለልጆቻቸው ስም ለማውጣት ሲጨነቁ ማየት የተለመደ ኹኔታ ቢኾንም ከዘመዶቻቸው የራቁ ወጣት ወላጆች ደግሞ ጭንቀታቸው የበዛ ነው። ለዚህም አንዱ ምክንያት በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ስለ ስም አወጣጥና ትርጉም የሚገልጽ ጽሑፍ እምብዛም ባለመኖሩ ነው።
ይህ በመልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት የተዘጋጀው መጽሐፍ በዚህ ረገድ በአገራችን ፈር ቀዳጅና ወቅታዊ ሲኾን፤ በየትኛውም የዓለም ክፍል ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን የሚያስፈልጋቸው ነው ብዬ አምናለሁ። መጽሐፉ ከያዛቸው የስሞች ዝርዝር በተጨማሪ የስያሜዎቹ አከፋፈልና ትርጉም እጅግ ጠቃሚ ኾኖ አግኝቼዋለሁ። በመኾኑም በዘርፉ ምርምር ለሚያደርጉ ሰዎችም ጥሩ መረጃ ሰጪ የሚኾን መጽሐፍ ነው።

ሰሙ ምትኩ (ዶ/ር)
አ.አ ዩኒቨርስቲ ረዳት ፕሮፌሰር

<u>ቀድሞ የወጣ</u>
- ኑሮና ክርስትና በአሜሪካ

<u>ወደፊት የሚወጡ</u>
- ፍኖተ አርቶዶክስ ዘተዋሕዶ
- ኑሮና ክርስትና በብሪታንያ

ኤች ዋይ ማተሚያ ቤት
+ 251-11-553 90 95

ዋጋ 25 ብር
£ 10 $ 15